ጋቢና ዋራንት

የቀይ ሽብር እስር ከሶደሬ እስከ ከርቸሌ

ተክልዬ በቀለ

ጋቢና ዋራንት

የቀይ ሽብር እስር ከሶደሬ እስከ ከርቸሌ

ተክልዬ በቀለ

2006 ዓ.ም. አዲስ አበባ

ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት፣ መገልበጥ ወይም ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው።

Tekelye Bekele © 2014
E-mail: tekelyeb@gmail.com

ይህ መጽሐፍ ለኢትዮጵያ ፍኖተ ዴሞክራሲ ፋና ወጊ በመሆን ሲታገሉ በደርግ የቀይ ሽብር ዘመን ለተሰቃዩ፣ ለታሰሩና ለተገደሉ ሁሉ መታሰቢያ ይሁን። በተለይም የቀይ ሽብር ዋና ኢላማ በመሆን ውድ ሕይወታቸውን የከፈሉት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ስማቸው ዘላለም ህያው ሆኖ ሲዘከር ይኑር።

የኢሕአፓ ጀግኖች ሰማዕታት ብዙ ስለሆኑ የሁሉንም ስማቸውን መዘርዘር ባይቻልም በቀይ ሽብር ከተገደለ በኋላ በርከት ያሉ ተማሪዎችና ገበያተኞች ተገደው አስከሬኑን እየረገጡ እንዲያልፉ የተደረገው ወልደአብ ደንቡ፣ እየፈከረችና ደርግን እያንቋሸሸች የተገደለቸው ልበሙሉዋ ጀግና አንቀፅ ተገኜ፣ ቆስላ ተይዛ ለኢሕአፓ ስል ደረቴን ለግድያ እሰጣለሁ እያለች የተሰዋችው ወጣት ትዕግሥት ዮሐንስ፣ በስር ማቀው በ1978 ዓ.ም. የተገደሉት አነጌታቸው ኩምሳ፣ የትጥቅ ትግል ሲያካሂዱ የደረሱበት ያልታወቀው እነፀጋዬ ገብረመድህን፣ ሞትን ሁለት ጊዜ የተጋፈጠው መምህር በላይነህ ገብረማርያም፣ ኦሞ ወንዝ ውስጥ ከነህይወታቸው ተጥለው በውሃ የተወሰዱትና የአዞ እራት የሆኑት እነኢንጅነር ፀጋዬና ሌሎች ዕልፍ አዕላፍ ኢሕአፓዎች የሚታወሱ ናቸው።

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ [illegible] ዲሞክራሲ ፋና ወጊ ሆነውን [illegible] በደርግ የቀይ ሽብር ዘመን ለተሰዉት፣ ለታሰሩና ለተገደሉ ሁሉ መታሰቢያ ይሁን፡፡ በተለይም የቀይ ሽብር [illegible] [illegible] በመሆን [illegible] ሕይወታቸውን የከፈሉት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች [illegible] ዘለዓለም ህያው ሆኖ ሊዘከር ይገባል። [illegible]

[illegible]

[illegible] በ1978 ዓ.ም. [illegible]

[illegible] ናቸው።

ማውጫ

ገጽ

አርእስት -- 8
አህጽሮተ ቃላት -- 9
ምስጋና --- 10
መግቢያ ---
ምዕራፍ አንድ
የኢትዮጵያ ቀደምት አሻራ
1. የኢትዮጵያ ገፅታ ከአሥራ ስደስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ---------- 15
2. ኢትዮጵያ ምንጊዜም ያው ናት? ------------------------------------ 22
ምዕራፍ ሁለት
የደርግ መንግሥትና የሕዝብ እልቂት
1. የደርግ መንግሥት አመሰራረትና የተካሄደው የፖለቲካ ትግል --- 24
2. የደርግ መንግሥትና ቀይ ሽብር -------------------------------------- 29
3. የኢሕአፓ መዳከምና የብሔርተኞች ማየል ------------------------ 36
ምዕራፍ ሦስት
የቀይ ሽብር አስከፊ ትዝታ --- 42
1. የማይረሳ ቀን -- 43
2. የከፍተኛና የደርግ ጽ/ቤት ምርምራ ------------------------------
ምዕራፍ አራት
እስር በሶደሬና በሌሎች እስር ቤቶች ------------------------------- 50
1. ሶደሬ ምንድን ነው? --- 52
1.1 የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች በሶደሬ ---------------------------- 61
1.2 የተለያዩ እስረኞች በሶደሬ ------------------------------------- 63
1.3 ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ደጋፊ እስረኞች በሶደሬ --- 64
1.4 የሶደሬ እስር ሁኔታ መሻሻል -------------------------------------- 66
1.5 የመጨረሻዎቹ የሶደሬ የእስር ሁኔታ -------------------------- 69
2. እስር በሌሎች እስር ቤቶች -- 70
2.1 የእስር ቤቶች መስፋፋት --------------------------------------- 71
2.2 የቀይ ሽብር ሰቆቃ -- 73
2.3 የሰቆቃው አብይ ተዋንያን -------------------------------------
ምዕራፍ አምስት
እስር በከርቸሌ -- 77
1. ከርቸሌ ምን ይመስላል? -- 78
2. የፖለቲካ እስረኞች መሰባሰብና የከርቸሌን ሕይወት መጀመር ----- 85
3. የእስረኞች ጥየቃ በከርቸሌ --- 88
4. የእስረኞች ትምህርት በከርቸሌ --------------------------------- 94
5. የእስረኞች መዝናኛ በከርቸሌ ----------------------------------- 97
6. የእስረኞች የጤና ችግር በከርቸሌ ------------------------------ 103
7. የእስረኞች መደጎሚያ ንግድ በከርቸሌ ------------------------- 105
8. በአበባ ያሸበረቀው የከርቸሌ የግድያ ቦታ ---------------------
ምዕራፍ ስድስት
ጋቢና ዋራንት -- 106
1. አንዳንድ የጋቢና ዋራንት ሰለባዎች ሲፈረዱ ------------------- 111
2. የኢሕአፓ ክፍልፋይ አንጃ ድርጊት -----------------------------

3. የአሕአፓ አባላት የርስ በርስ ሁኔታ--119
4. የጋቢና ዋራንት ጥሪ --121
5. የግድያ ጥሪ በሌሎች አስር ቤቶች --131
6. የአንድ አቅጣጫ መንገድ --132
7. የጋቢና ዋራንት ጥሪ በመጨረሻው የአስራት ዘመን ----------------133
8. የኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የከርቸሌ
ጉብኝትና ጋቢና ዋራንት---135
9. የጀኔራሎቹ ወር ተራ --136
10. የከርቸሌ የወንጀልና የፖለቲካ እስረኞች ግኑኝነት--------------------138
ማሳረጊያ
<u>ድህረ ቀይ ሽብር የኢትዮጵያ ፖለቲካ</u>
1. የኢሕአዴግ መንግሥት የፖለቲካ አቅጣጫ ---------------------------144
1.1 አሮጌውን ማደስ ---145
1.2 የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ -----------------146
1.3 የአስተዳደር ችግር ---151
1.4 የ1987 ዓ.ም. ምርጫ ችግር -----------------------------------156
1.5 የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና የአካባቢው የፖለቲካ ቅኝት--159
2. ያልተቋጨው የዴሞክራሲ ትግል -------------------------------------163
ድህረ ጽሑፍ --169
የግርጌ ማስታወሻ ---172
ዋቢ መረጃዎች ---179

አህጽሮተ ቃላት

ህወሐት/ወያኔ	-- የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ
ማሌሬድ	-- የማርክሳዊ ሌኒናዊ ሬቮለሽነሪ ድርጅት
መአሕድ	-- የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት
መኢሶን	-- የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ
ማዕከላዊ	-- የከባድ የፖለቲካ ወንጀል ምርመራ እስር ቤት
ሰደድ	-- የአብዮታዊ ሰደድ
አዘአኮ	-- የአብዮታዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ (የቀይ ሽብር ኮሚቴ)
ኢሕአሠ	-- የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት
ኢሕአዴግ	-- የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
ኢሕአወሊ	-- የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣት ሊግ
ኢሕአፓ	-- የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ
ኢሕዴቃ	-- የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ቃልኪዳን (ኢ.ፒ.ዲ.ኤ.)
ኢማሌድህ	- የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ህብረት
ኢሠፓ	-- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ
ኢሠፓኮ	-- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን
ኢሰመጉ	-- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ
ኢዴህ	-- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት
ኢዴኃቅ	-- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት
ኢጭአት	-- የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል
ኤህግሀ/ሻዕቢያ	-- የኤርትራ ሕዝባዊ ሀርነት ግንባር
ኤአግ/ጀበሐ	-- የኤርትራ አርነት ግንባር
ኤአግ-ህአ /አልዋህድ	-- የኤርትራ አርነት ግንባር-ሕዝባዊ ሀርነት ኃይላት
ኤድስ (AIDS)	-- Acquired Immune Deficiency Syndrome
ኦነግ	-- የኦሮሞ ነፃነት ግንባር
ከፍተኛ	-- በከተማ ክልል አንድ ወረዳ ነው::
ወዝ ሊግ	-- የወዝ አደሮች ሊግ
ወያኔ/ኢሕአዴግ	-- ህወሓት (ወያኔ) የሚመራው ግንባር
ደርግ	-- በአማርኛ ቋንቋ ኮሚቴ ማለት ሲሆን ከወታደራዊው ክፍል የተወጣጣው ቡድን መንግሥት ሲመሰርት መጠሪያው አድርጎ ተጠቅሞበታል::

ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ታሪክ በአብዛኛው በፀሐፊው የግል ማስታወሻ ላይ የተመረኮዘ ቢሆንም የብዙ ጓደኞቹ ድጋፍና ርብርቦሽ ታክሎበታል። ዝርዝሩ መጽሐፉ ውስጥ ሲገባ እንደሚያመለክተው በወቅቱ የጽሑፍ መረጃ ለመያዝ አስቸጋሪ ነበር። አሁንም ጊዜው ካለፈ በኋላ ያለፉ መረጃዎችን ማግኘት ያዳግታል። ስለዚህ በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን አንዳንድ ጉዳዮችና የሸብሩ ሰለባ የሆኑትን ግለሰቦች ስም ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ሕይወት ያሳለፉትን ማነጋገር ያስፈልግ ነበር።

ይህንን ጉዳይ በማጣራት በኩል ብዙዎች የተሳተፉ ቢሆንም የማንኛቸውንም ስም ከመግለጽ ተቆጥቤአለሁ። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉኝ። አንደኛው እርዳታ ያደረጉልኝ ግለሰቦች በሙብዛታቸው የተነሳ የማንን ስም ጠቅሸ የማንን እተዋለሁ የሚል ሲሆን ሁለተኛውና ዋነኛው ደግሞ የሁሉንም ስም በሚስጥር መያዝ የግድ አስፈላጊ ስለሆነ ነው። በደፈናው ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ከጀመርኩበት ቀን ጀምሮ ታትሞ ለአንባቢ እስኪቀርብ ድረስ ለተባበሩኝ የችግር ጊዜ ጓደኞቼ በሙሉ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ትግሉ የጋራ ስለነበረ መጽሐፉም የጋራ ሥራ ነው ማለት ይቻላል። ነገር ግን ምንም እንኳን መጽሐፉ የብዙ ሰዎች ጥምር ውጤት ቢሆንም በውስጡ ለሚገኙ ግድፈቶችና ስህተቶች ተጠያቂው ፀሐፊው ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ።

የመጽሐፉ አቀራረብና ቋንቋ ጥራት ለአንባቢ ተስማሚ ሆኖ እንዲገኝ ለረዳኝ ለመለስካቸው አምኃ፣ ይህን ታሪክ ለመፃፍ ለአበረታቱኝና በህትመት ለአገዙኝ ለክብሩ ክፍሌ፣ ወርቁ አበራ፣ ሮማን ሙሉጌታ፣ ንጉሤ መኩሪያ፣ ብስራት መኮንንና ፍሥሐ አካሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

መግቢያ

የደርግ የቀይ ሽብር እርምጃ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት ለስርና ለግድያ ዳርጓል። እስከ አሁን ድረስ ከዚህ አስከፊ ድርጊት ጋር በተያያዘ አንዳንድ የታሪክ መረጃዎች ቀርበዋል፣ ወደፊትም የተለያዩ ሰዎች የሚያውቁትን እንደሚያቀርቡ አይጠረጠርም። የዚህ መጽሐፍም ዋና አላማ በዚያን ጊዜ የተካሄደውን የሽብር ሰቆቃ በከፊል ለመዘገብ ነው። በደርግ ዘመን በተካሄደው እልህ አስጨራሽ የፖለቲካ ትግል የተሳተፉ ግለሰቦችና ቡድኖች የነበረውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በራሳቸው አቅጣጫ ይመለከቱታል። ስለዚህ የነበረው የፖለቲካ ሂደት አንድ ቢሆንም አተረጓጎሙ እንደ አመለካከቱ ይለያያል። በዚህ የተነሳ ይህ ጽሑፍ አንዱን ወገን ሲያስኮርፍ ሌላውን ሊያስደስት ይችላል፣ ትግሉም እንደዚሁ ስለነበረ ሁሉን ማስደሰት አይቻልም፣ ሁሉን የሚያረካ ታሪክም ለመጻፍ አይቻልም። የቀይ ሽብርን ታሪክ የስርአቱ አራማጆች የነበሩት በበጎ ጎን ሲመለከቱት ሌሎች በመጥፎ ድርጊቱ ያስታውሱታል።

መጽሐፉ በስድስት ተከታታይ ምዕራፎችና በማሳረጊያ የተከፋፈለ ሲሆን በምዕራፍ አንድ ውስጥ የኢትዮጵያ ያለፈ ገጽታ ከአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ባጭሩ ተገልጿል። በምዕራፍ ሁለት የደርግ መንግሥት አመሰራረትና የቀይ ሽብር አመጣጥ ተገልጿል። ምዕራፍ ሦስት ፀሐፊው በግሉ በቀይ ሽብር የደረሰበትን የሚያሳይበትና ከውስጡ ምን እንደሚሰማው የሚገልጽበትን ሐተታ ይዟል። የመጽሐፉ አቀራረብ በቀይ ሽብር ሰለባ የነበሩት ግለሰቦች በጋራ የሚጋሩትንና በግልም የተፈፀመባቸውን በጉልህ ለማሳየት የተደረገ ሙከራ ነው። አንድ ሰው የደረሰበትን ክፉ ወይም በጎ ነገር ከሱ ከራሱ በተሻለ መንገድ መግለጽ የሚችል የለም። ይህም ሲባል የተጋነነ አቀራረብ እንዳይገኝበት መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምዕራፍ አራት፣ አምስትና ስድስት የቀይ ሽብር ሰለባዎች በስቃዩ ጊዜ በጋራ ያጋጠሟቸውን ሕይወት በፀሐፊው ዕይታ ይዘረዝራሉ። በዚህ የተነሳ የአጻጻፍ ስልቱም ከምዕራፍ ሦስት በብዙ መልኩ ይለያል።

በአዲስ አበባ ከተማ ከነበሩት የከፍተኛ እስር ቤቶች መካከል ሶደሬ በሚል መጠሪያ ይታወቅ የነበረው የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት ዝርዝር ሁኔታ ቀርቧል። ይህም ሊሆን የቻለው በጊዜው የነበሩት እስር ቤቶች ምን እንደሚመስሉና የእስረኞቹም ሁኔታ ምን እንደነበረ የአንዱን በስፋት ለማሳየት የተደረገ ሙከራ ነው። ይህ እስር ቤት የተመረጠበት ዋናው ምክንያት ባጋጣሚ ሳይሆን ፀሐፊው የታሰረበት ቦታ በመሆኑና በእስር ላይ በቆየበትም ጊዜ ሁኔታውን ስለሚያውቅ ነው። ምርጫው የእስር ቤቱን የኋላ ታሪክ በማወቅ የተደረገ እንጅ ሌላ ምንም ምክንያት እንደሌለው መታወቅ አለበት። ከዚህ ውጪ ፀሐፊው ከሌሎች በእስር ላይ ከነበሩ ጓደኞቹ ጋር በጋራ ያሳለፈውን ሕይወት ከመተረክ በስተቀር የእያንዳንዱን የደርግ ጊዜ እስር ቤት ታሪክ ለማቅረብ ሰፊ ጥናትና ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ አቅሙም የለውም።

ከርቸሌ ከአገሪቷ በሞላ እስረኛ የሚጎርፍበትና የሚታሰርበት እስር ቤት ስለነበረ ፀሐፊው ከተለያዩ አካባቢዎች ከመጡ እስረኞች ጋር ለመገናኘት እድል ፈጥሮለታል። ከሶደሬና ከርቸሌ በተጨማሪ የማዕከላዊና የደርግ ጽ/ቤት እስር

ቤቶች ለምርመራ የተወሰደባቸውና ለአጭር ጊዜ ቆይታ ያደረገባቸው እስር ቤቶች ነበሩ:: የደርግ የቀይ ሽብር ድርጊት በ1969 ዓ.ም. ከተጀመረ ጀምሮ እስከ መጨረሻው አስኪወድቅ ድረስ ዘልቋል:: ዋናው ሽብር የተካሄደው በ1970 ዓ.ም. ቢሆንም በሌሎችም ዓመታት ብዙዎች ተገድለዋል:: ከ1971 ዓ.ም. እስከ 1979 ዓ.ም. በቀይ ሽብር የተገደሉትን ሰዎች በከፊል የሚያመለክት አሃዛዊ መረጃ በምዕራፍ ስድስት ተካቷል::

ከማንኛውም ታሪክ ጋር በድርጊቱ ዙሪያ የነበሩ የሰዎች ስሞች አብረው ይጠቀሳሉ:: የሰዎችን ስም ያልያዘ ሌጣ ጽሑፍ ተአማኒነት አይኖረውም:: በዚህ መልክ ከታሪኩ ጋር የተጎዳኙትን ስሞች ለመጥቀስ ችግሮች ያጋጥማሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ የዚህን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ተዋንያን በተለይም በሕይወት ያሉትን ሰዎች ስሞች ለመጥቀስ ፈቃደኝነታቸውን ማግኘት ያስፈልጋል:: አንዳንዶቹ ፈቃደኛ ሲሆኑ ሌሎች ስማቸውን መጥቀስ ቀርቶ በታሪኩም ዙሪያ መኖራቸው እንዲገለጽ አይስማሙም:: ሌለው ደግሞ በእስር ላይ ያሉ ግለሰቦችን ወንጀል ፍርድ ቤት በማጣራት ላይ እያለ ስማቸውን መጥቀሱም ተቀባይነት ባይኖረውም የጥቂቶቹ ተነስቷል:: ከዚሁ ከእስረኞች ጉዳይ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ታሪክ ለመረጃነት ቢያገለግልም ለፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል የሚቀርብ አይደለም:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የፀሐፊውን ሃሳብ የሚጋሩ የዚያን ጊዜ ሰቆቃ ሰለባ የነበሩ ብዙ ግለሰቦች በዚህ ይስማማሉ::

ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ዓይነት ችግሮች ያጋጠሟቸው የአንዳንድ አገር ፀሐፊዎች የባለታሪኮቹን ስም ፊደል በአህጽሮት በማስቀመጥ ለመጻፍ ተገደዋል:: በእኛም አገር በአንዳንድ ፀሐፊዎች ከዚህ በፊት ተሞክሯል:: የዚህ መሰል አቀራረብ ግልጽነት የሚኖረው ታሪኩን በቅርብ ለሚያውቁት ሰዎች እንጅ ለሌሎች አይሆንም:: ታሪክ ደግሞ የሚጻፈው መረጃዎችን ሳይቀር ለሚያገናዝቡትና ለማወቅ ለሚፈልጉት አንባቢዎች በሙሉ አንጅ ለጥቂቶች ብቻ አይደለም:: ለማንም በመረጃነት እንዲያገለግልና ለወደፊትም ትውልድ ለአርያነት እንዲያመች ተደርጎ መቅረብ አለበት:: ምንም እንኳን ይህ ጉዳይ ቢታወቅም በአሁን ጊዜ ሌላ አማራጭ ስለሌለ የአንዳንዶቹን ስሞች በአህጽሮት በማስቀመጥ ፍቃደኛ ሆነው የተገኙትን ሙሉ ስማቸው እንዲሰፍር ተደርጓል:: ሙሉ ስማቸውን ለማግኘት ያልተቻለውን ግለሰቦች የመጀመሪያ መጠሪያቸው ብቻ ተጠቅሷል:: በሕይወት የሌሉትን ግለሰቦች ሙሉ ስም አብዛኛው የመጽሐፉ ክፍል ይዞ ቢቀርብም በዚህም ረገድ በብዙ መልኩ ቁጥብ ለመሆን ተሞክሯል:: ከዚህ ሌላ በእስር ላይ በነበሩበት ጊዜ ለእስረኛው ደህንነትና የአስተሳሰብ እድገት በማስተማርና በሌላም ለእስር ቤቱ በሚጠቅም ማህበራዊ ግልጋሎት ያበረከቱትን እስረኞች ሙሉ ስም መጽሐፉ ይዞ ቀርቧል::

በጊዜው የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም እንደ ኢሕአፓ ያሉት በህቡዕ በመደራጀታቸውና በመንቀሳቀሳቸው አባሎቻቸው የሚተሳሰሩበት ሚስጥራዊ መዋቅር ነበራቸው:: ግኑኙነታቸውም በተፈቀደላቸው መዋቅር የተዋረድ ሰንሰለት ብቻ ነበር:: ይህም ለራሳቸውና ለድርጅታቸው ደህንነት ሲባል ነበር:: ነገር ግን በእስር ጊዜ መጋለጥ ሲመጣ አንዱ አንዱን በመጠቆምና በመሳሳብ እየታደኑ ለስርና ለግድያ ስለተዳረጉ የነበረው መዋቅር ሊፈራርስ ቻለ:: በዚህ መጽሀፍ ውስጥ በቀይ ሽብር ጊዜ በተለያዩ ግለሰቦች ላይ ያጋጠመውን እስር፣ ግርፋት፣ ግድያና ሰቆቃ ቢዘገብም በድርጅት መዋቅራዊ

ግኑኝነት ማን ማንን በመገደድ እንደጠቀመ ደራሲው መግለፅ አይፈልግም፣ የመጽሐፉ አላማም አይደለም። ምናልባት አንዳንድ ቦታ በታሪኩ ሂደት አስገዳጅነት ብቻ ሲጠቀስ ይችላል። ይህም ሲሆን የቻለው ሌላ አማራጭ ስለጠፋ የግድ መገለፅ ስላለበት ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ በደርግ ዘመን ከነበረው ብዙም የተሻለ አይደለም። ደርግም ወደቀ ወይም ኤርትራም ተገነጠለች የአገራችን ውስብስብ ችግሮች ብዙም አልተቀየሩም። በአገራችን የዴሞክራሲ አሰራር ባህል ስላላደገ የፖለቲካ ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ በሕዝብ ውሳኔ ሊፈቱ አልቻሉም። ልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚከተሉትን መንገድ ሊያሳኩ የሚችሉት በህዝብ ድጋፍ መሆኑን ቢቀበሉትም በተግባር ስራ ላይ አልዋለም። አሁንም እንደ በፊቱ የአገራችንን የፖለቲካ ችግር መፍቻ የሕዝብ ድጋፍ ሳይሆን የኃይል ሚዛን እንደዋንኛ መሣሪያ ተደርጎ ይቆጠራል። በኃይል አይሉ ሥልጣን መያዝ ማለት የሕዝብን ፍራቻ እንጅ ድጋፍን አያመጣም። ሰላምና እኩልነት ካልተፈጠረ ደግሞ ሰላማዊ ውድድር መፍጠር፣ የሚፈልጉትን የፖለቲካ መንገድ በሕዝብ መንፈስ ለማስረጽና ደጋፊ ለማበጀት አይቻልም።

የተለያዩ ቡድኖች በየተራ መሣሪያ ሲያነሱ፣ ሰላም ሲያደፈርሱ፣ አንዱ ሌላውን ሲያሸንፍ፣ ሌላው ደግሞ አዲስ መጪውን ሲጥል እንዲሁ ሲፋተጉ መኖር አያዋጣም። በዚህ መልክ የሚደረግ ፉክክር ሰላምም ዴሞክራሲም አያመጣም። በኢትዮጵያ ከበፊት ጀምሮ መሣሪያ ጨብጠው የነበሩት ድርጅቶች የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት/ወያኔ)፣ ወዘተ. (ጥቂቶቹን ብቻ ለመጥቀስ ያክል) መሰረታቸው ጠመንጃ መሆኑ ቀርቶ ሕዝብ እንዲሆን አጥብቀን እንመኛለን። ይህን ለማሟላት በሁሉም ወገን የተዘጋው መንገድ መከፈት አለበት። ሁኔታው ለራስ ምቾት ለሌላው የሚመር አሬት መሆን የለበትም። እስከ አሁን ሁሉም የፖለቲካ ስህተት ሰርተዋል። ከእንግዲህ ወዲያ ከሁሉም የሚጠበቀው የሰሩትን ስህተት እንዲያርሙ ነው።

የአንድን አገር የፖለቲካ ችግር መፍትሔ ለመስጠት ወደፊትም ወደኋላም መመልከት ያስፈልጋል። ወደኋላ ሳይገላመጡና ወደፊትም ሳይቃኙ የደረሱበት ላይ ብቻ ትኩረት መስጠት መፍትሔውን ዘላቂ አያደርገውም። አስተማማኝ የፖለቲካ መፍትሔ ከቂም በቀል የጸዳ አሰራር መከተልን ይጠይቃል። በደርግ ዘመነ መንግሥት ወንጀል የፈጸሙ ባለሥልጣኖችና የቀይ ሽብር አራማጆች በተራቸው በእስር ላይ ሆነው ፍርዳቸውን እየተጠባበቁ ናቸው። እነሱም በፊናቸው ከነሱ በፊት የነበረውን ሲቃወሙና የፖለቲካ ተቃዋሚዎቻቸውን ሲያሳድዱ ነበር። ከዚያም በፊት የነበረው እንደዚያው ነው። "አንዱ በአንዱ ሲስቅ (ወይም ሲፈርድ) ጀምበር ጥልቅ" እንዲሉ። ቢሆንም የደርግ ዘመን ባለሥልጣኖች ወንጀል ከማንኛውም ከዚህ በፊት የተፈጸመው የከፋ መሆኑ ይሰማኛል። እነሱ ሌሎችን በቀይ ሽብር እንዳሰቃዩና እንደገደሉ ተመጣጣኝ ቅጣት ማግኘት አለባቸው የሚለው ከፍትሕ አንጻር ትክክል ቢሆንም ለወደፊቱ ይህን መሰል ወንጀል እንዳይፈጽም "እኔን ያየህ ተቀጣ" በሚል ሌላውን ሊያስተምር መቻሉ ያጠራጥራል። በሕግ የተቀጣውም ቢሆን ቂም መቋጠሩን አይተውም። ምክንያቱም ከዚህ በፊት የሠራው ድርጊት ለሱ ትክክል መስሎ ስለሚታየው።

በህብረተሰባችን ደግሞ በፖለቲካ ችግሮች የተነሳ ቂም መቋጠሩ አንድ ደረጃ ላይ እንዲቀር ማድረግ ይገባል። ስለዚህ ከቅጣት ይልቅ ትክክል

አይደለህም ብሎ ማስተማሩ የበለጠ ሳይጠቅም አይቀርም:: ታዲያ ይህን መሰል ድርጊት የፈጸሙ ወንጀለኞችን እንዴት እንለውጣቸው? በማሰር፣ በመግደል፣ በማስተማር፣ እንደ ደቡብ አፍሪካ እርቀ ሰላም በማውረድ፣ ወዘተ.:: ሕዝብ ፍርዱን ይስጥ ከማለት በስተቀር በግሌ የማስቀምጠው መልስ የለኝም:: እዚህ ላይ ግን ከውስጤ የሚሰማኝን አንድ ነገር ማስቀመጥ እፈልጋለሁ:: በምንም መልኩ ቢሆን በፖለቲካ ቂም በቀል አላምንም:: ቂም ቋጥሮ በደልን ለመርሳት ከመሞከር ይልቅ ይቅርታ ማድረግን የተሻለ አማራጭ አድርጌ እቆጥረዋለሁ:: በአገሪቷ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት በፖለቲካ ቡድኖችም ሆነ በደርግ ወንጀለኞች ላይ ሁሉም የበደለውን ረስቶ ብሔራዊ እርቅ ማውረድ እንደሚያስፈልግ ለማሳሰብ እወዳለሁ::

በማሳረጊያው እንደቀረበው ለኢትዮ-ኤርትራ የባድማ ጦርነት ወቅታዊ መፍትሔ ሳይገኝለት ቀርቶ የብዙዎችን ሕይወት ቀጥፏል:: የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በመድፈር ጦርነቱን የጀመረው የኤርትራው መንግሥት በወረራ ከያዛቸው ቦታዎች በሙሉ ለቆ እንዲወጣና ሰላማዊ መፍትሔ እንዲፈለግለት ባለመስማማቱ የጦርነቱ መንገድ አማራጭ የማይገኝለት ሆኗል:: ጦርነት የአምባገነን መሪዎች የእልህ መወጫ ተደርጎ ቢቆጠርም የፖለቲካ ችግር መፍቻ ሊሆን አይችልም:: ጦርነት የብዙዎችን ሕይወት ይቀጥፋል፣ ኑሮአቸውንም ያቃውሳል:: በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትም ካጋጠሙት ውስብስብ ችግሮች መካከል ከሁለቱም አገሮች የተባረሩት ሕዝቦች ጉዳይ የብዙዎችን ትኩረት ሊስብ ችሏል:: በዚህ ጦርነት የተነሳ ሁለቱም አገሮች ለደህንነታቸው ያሰጉናል የሚሉትን አንዱ የሌላውን አገር ተወላጆች እንዳባረሩ ይታወቃል:: ይህም ለአገራቸውና ለህዝባቸው ደህንነት በማሰብ እስካደረጉት ድረስ ሁለቱንም አያስጠይቃቸውም በሚል ብዙዎች ይስማሙበታል:: ቢሆንም በሁለቱም በኩል የተባረሩት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስለሆነ አፈጻጸሙን አጠያያቂ አድርጎታል::

ሌላው ደግሞ ሁኔታውን አጠያያቂ የሚያደርገው የነኝህን የሁለቱን አገሮች ህዝቦች እድልና አጋጣሚ ወደኋላ መለስ ብሎ ሲመረመር የሚነሱት ጥያቄዎች ናቸው:: በፊት አብሮ መኖር፣ መጋባትና መዋለድ፣ ወይም በጦርነት ተዋግቶ መለያየት፣ በየትም ቦታ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክስተቶች ናቸው:: በመሰረቱ ኢትዮጵያዊ ከኤርትራዊ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ጋር አብሮ መኖር ይችላል:: ከሌሎችም መጋባት ይችላል:: በየአቅጣጫው በጉርብትና አብሮ ከሚኖራቸው ጋር የደምና የቋንቋ መተሳሰርም ሊኖረው ይችላል:: ከማንም ጋር አለመግባባት ካለ ጦርነትም ሊያጋጥም ይችላል:: በዓለም ላይ አንድ ላይ የነበሩ አገሮች ተከፋፍለዋል፣ ተለያይተው የነበሩም ተስማምተው አንድ ሆነዋል::

ከዚህ በተለየ መልኩ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል በፊት የነበረውን ታሪካዊ ሁኔታ ስንመለከት አንድ ነገር በስሜታችን ያጭራል:: ኤርትራ ገና በጣሊያን ቅኝ ግዛት በነበረችበት ጊዜ ጀምሮ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የኤርትራን ተወላጆች በኢትዮጵያ መጥተው እንዲኖሩና በአገሪቷ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት እንዲሳተፉ፣ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ውጭ አገርም ድረስ ሳይቀር ሄደው እንዲማሩ ሲፈቀድ ነበር:: ያ ሁሉ ከውለታ ባይቆጠርም እነ ኢሳያስ አፈወርቂ በፈጠሩት ችግር ኤርትራም ከኢትዮጵያ ተገንጥላ በኢትዮጵያ ተጠልለው እንደ ኢትዮጵያዊ ተቆጥረው ሲኖሩ የነበሩት ኤርትራያኖች መባረራቸውን ታሪክ እንዴት ይመለከተዋል? በአንዱ ትውልድ ተፈቅዶላቸው የገቡት ኤርትራያኖች በሌላው ትውልድ እንዲባረሩ ያደረጋቸው

ምንድን ነው? ኢትዮጵያኖችም እንዲሁ ከጦርነቱ በፊት ጀምሮ በየጊዜው ከኤርትራ ተባረዋል:: እንግዲህ ስህተቱ የት ላይ እንደተፈጸመ ሁሉም ራሱን ይመርምር:: ሌላው ደግሞ ጦርነቱን እንዲህ መራራና የብዙ ሰዎችን ሕይወት እንዲቀጥፍ ያደረገው ምንድን ነው? ከየአቅጣጫው እንደሚደመጠው ከሆነ ከሰባ እስከ መቶ ሺህ የሚገመት ሠራዊት ከሁለቱም በኩል መሞታቸው ይታወቃል:: ከሰላሳ ዓመት በላይ በተደረገው የርስ በርስ መቆራቆስም ይህን ያክል ሕዝብ አላለቀ:: የኮለኔል መንግሥቱ የቀይ ኮከብ ዘመቻ እንኳን ይህን ያክል መአት አላስከተለም:: ታዲያ መለያያትም ወይም አብሮ መኖርም ሰላም ካላመጣ ሌላ ምን አይነት መፍትሔ ሊገኝ ይችላል?

በአገራችን አጻጻፍ መሠረት የአንዳንድ ሰዎችን ታሪክ በአንቱታ የሌላውን ደግሞ በአንተ ሲጠቀሱ አናያለን:: ይህንን ዝብርቅርቅነት ለማስቀረት አንዳንድ ፀሐፊዎች አንዱን ብቻ በመከተል ለመጻፍ ተገደዋል:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የሁሉም ሰዎች ስሞች አንተ በሚል የቀረቡ ሲሆን ለአጻጻፍ እንዲያመችና አንድ ወጥ እንዲሆን የተመረጠ መንገድ እንጅ የአድሜ ባለፀጎችን አክብሮት ለመንፈግ የታቀደ አለመሆኑን እንዲታወቅ ያስፈልጋል:: በመጽሐፉ ውስጥ የአንዳንድ ድርጅቶች አህጽሮት ስም ሕዝብ በለመዳቸውና በሚያውቃቸው መሰረት እንዲጠቀሱ ተደርጓል:: ከህወሓት፣ ኢህግሀና ኢአግ ይልቅ ወያኔ፣ ሻዕቢያና ጀበሐ የሚባሉት አጠራሮች በጣም ተለምደዋል:: ይህም በመሆኑ አንዳንድ እነሱን የሚመለከት ታሪክ ሲያጋጥም ሕዝብ የተሻለ በሚያውቃቸው አጠራር እንዲጠቀሱ ተደርጓል:: ይህም ጉዳይ የማንንም ድርጅት ስም ለማጉደፍ ታስቦ ያለመሆኑን አንባቢያን እንዲረዱት ያስፈልጋል::

በመጨረሻ ይህ መጽሐፍ በአብዛኛው የደርግን ያገዛዝ ዘመን የሚዳስስ ቢሆንም ኦሮጌውን ከአዲሱ ጋር ለማገናኘት በማሰብ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ያጋጠመውን ድርጊት እስከ 1992 ዓ.ም. ያቀርባል:: ይህም ያለፈውን ከአዲሱ ጋር ለማገናኘት የተደረገ ሙከራ እንጅ በቅርብ ጊዜ ሥልጣን ላይ የወጣን መንግሥት ያላለቀ የታሪክ ሂደት ለመተረክ አይደለም:: በደርግ እስርና ግድያ የተሸማቀቀው ለውጥ ፈላጊ ትውልድና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደርግ ውድቀት በኋላ ምን እንደገጠመው ለማመልከት ነው:: ስለዚህ የአንድ አገር የፖለቲካ ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ ኢሕአዴግ ከ1992 ዓ.ም. በኋላ ያመጣውን ለውጥ በማገናዘብ አንባቢ በጥንቃቄ እንዲመረምረው እጠይቃለሁ::

ተክልዬ በቀለ፣ 1992 ዓ.ም.

ምዕራፍ አንድ

የኢትዮጵያ ቀደምት አሻራ

1. የኢትዮጵያ ገፅታ ከአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ

በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የኦቶማን ቱርክ የእስላም ኃያል መንግሥትና ታላቁ የአውሮፓ የፖርቱጋል የክርስቲያን መንግሥት አካባቢያችንን ለመቀራመት፣ የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠርና አንዱ በሌላው ላይ ለማየል የሚሻሙበት ጊዜ ነበር:: የኦቶማን ቱርክ መንግሥት ወደ ምስራቅ ግዛቱን እያስፋፋ አረቢያን አስገብሮ በከፊል ሜዲp ፅንያንንና ቀይ ባህርን ተሻግሮ ወደ ሕንድ ያለውን የንግድ መስመር ሲቆጣጠር በአንጻሩ በመርከበኞች ኃይሉ የሚመካው ፖርቱጋል ሕንድን ይዞ የቱርክን መስፋፋት ለመግታትና የአካባቢውን የንግድ መስመር በራሱ ቁጥጥር ስር ለማድረግ ይጥር ነበር:: የሁለቱ ግጭት በአካባቢው ሕዝብ የንግድ ልውውጥና የኤኮኖሚ ሕይወት ላይ ተጽኖ አስከተለ:: በጉርብትና አንዳንድ ጊዜም የኃይል ሚዛን ወደ አንዱ ሲያጋድል አንዱ ሌላውን ሲወሩና ሲያስገብሩ የንግድ መስመሩንም ሲቆጣጠሩ የቆዩት ተጎራባች የአፋር፣ የሱማሌ፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ፣ የሐዲያ፣ የአማራ፣ የአገው፣ የትግራይ፣ የወላይታ፣ የሺናሻ፣ የአኟዋክ፣ የኩናማ፣ ወዘተ. ሕዝቦች በኢትዮጵያና በምስራቅ አፍሪካ ይኖሩ ነበር:: በየደረጃው የማዕከላዊ መንግሥት ቅርፅ እየያዘ ከመጣው ከኢትዮጵያ የዘውድ መንግሥት ሌላ ልዩ ልዩ የአካባቢ ትናንሽ መንግሥታትም ነበሩ:: እነዚህ የአካባቢ መንግሥታት በጊዜው ለማስገበር ኃይል ለነበረው የማዕከላዊ መንግሥት እየገበሩ አንዳንድ ጊዜ እያመጹም የራሳቸውን የአካባቢ የውስጥ አስተዳደር ይቆጣጠሩ እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል:: በኤኮኖሚም የተሳሰሩ ነበሩ:: ከጥንት ጀምሮ በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙት ልዩ ልዩ ወደቦች እንደ ስዋኪን፣ ዳሕላቅ፣ ምፅዋ፣ አርቂቆ፣ ዘይላ፣ በርበራ፣ ሞቃዲሾና ሌሎችም ከኢትዮጵያ የንግድ መስመሮች ጋር ግኑኝነት ነበራቸው::(1) እነኝህን የንግድ መስመሮች ለመቆጣጠር አንዳንድ ገዜ ጦርነት ይካሄዳል::

በዚህ ግኑኝነትና አብሮ መኖር የተነሳ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የኤኮኖሚ ሕይወት፣ የአኗኗር መወራረስ በጋብቻም መደባለቅና አንዱ ከሌላው ጋር መቀላቀልና ብሎም መለወጥ አጋጥሟል:: ስለዘህ ጉዳይ ታደሰ ታምራት ሲጽፍ፣

> "በነዚህ ግንኙነቶች የሚለወጠው ደግሞ የአናሳ ብሔረሰቦች ወይም በጊዜው የኃይል ሚዛን ደካማ የሆኑት ወገኖች ብቻ አይደሉም:: የባሕል ቅቤ ማቅለጫ ድስት (Melting pot) ውስጥ የገባው ሁሉ ሌላ ባሕርይ ይዞ ነው የሚወጣው"::(2)

የአካባቢው ትላልቅ ሃይማኖቶች ቀደምት የሆነው ክርስትናና በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የገባው እስልምና በአማኞቻቸው አማካኝነት አንዳንድ ጊዜ ጠብ

ሲያበቅሉም ሌላ ጊዜ ሲስማሙም አብረው ለብዙ ዘመን ኖረዋል፣ ወደፊትም ጎን ለጎን አብረው ይኖራሉ። ኋላ መጡ የእስልምና እምነት ያለችግርና ጦርነት ተቀባይነት ያገኘው በኢትዮጵያ ብቻ ነበር ቢባል ከእውነቱ የራቀ አይደለም። የመጀመሪያው ስደት (ሐጂራ) ተብሎ በእስልምና አማኞች የሚጠቀሰው የነብዩ መሐመድ ተከታዮች ከመካ ሲያሳድዷቸው ቀይ ባህርን አቋርጠው መጥተው በሰላም መኖር የቻሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር።(3) የእስልምና ሃይማኖት በኢትዮጵያ አገባቡ በሰላም ይሁን እንጅ የክርስቲያኑን መንግሥት የሚፎካከሩ ጠንካራ የእስላም መሳፍንቶች በይፋት፣ በፈጠጋር፣ በሐዲያ፣ በሐረር፣ በደዋሮና በባሌ በተለያዩ ጊዜያት ተመሥርተዋል። ጎን ለጎንም አንዱ ለአንዱ እየገበረ ኖረዋል።

በአሥራ ስድስተኛው ክፍል ዘመን የተፈጠረው የኤኮኖሚ ውጥረት፣ የንግድ ልውውጥ መተጓጎል፣ የጊዜው ኃያል መንግሥታት ለአላማቸው ግብ መምታት ሃይማኖትን መሣሪያ በማድረግ ለሚያደሉለት ድጋፍ በመስጠት በምስራቅ አፍሪካ ለብዙ ጊዜ ደም ያፋሰስ የሃይማኖት ጦርነት ተቀሰቀሰ። ከሐረር የተነሱት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት የሐረሪ፣ የሱማሌ፣ የአፋርና የአርጎባ ሕዝቦች በመሪያቸው በአህመድ ግራኝ አመካኝነት የሰሜኑን ክፍል በመውረር በሽንብራ ኩሬ (የአሁኑ ሞጆ) በ1521 ዓ.ም. ከባድ ጦርነት አደረጉ። በጊዜው ከኦቶማን ቱርክ መድፍ ብበዛት አግኝቶ የነበረው የእስላም ጦር በክርስቲያኑ ጦር ላይ አየለ፣ አሸነፈም።(4) (5) መደበኛ መቀመጫው በሸዋ የነበረው የክርስቲያኑ ንጉሥ ልብነድንግልም የእስላምን ወረራ መቋቋም ስላቃተው ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ሕይወቱን ለማዳን ወደ ሰሜን ግዛቱ አፈገፈገ።

የአህመድ ግራኝ ጦርም ከሽንብራ ኩሬ ድል በኋላ አካባቢውን ዘርፎ ቢበታተንም እንደገና ተሰባስቦ ባሌን፣ ደዋሮን ፈጠጋርን፣ ሐዲያንና ሸዋን ካስገበረ በኋላ ልብነድንግልን ለማንበርከክ እስከ አንጎት (ወሎ)፣ ላስታ፣ ትግራይ፣ ጎንደርና ጎጃም ድረስ ዘመተ። ልብነድንግልም ጦሩን እያሰባሰበ በተለያዩ ቦታዎች ቢገጥምም ድል ከመሆንና እንዳይያዝ ከማምለጥ በስተቀር መቋቋም አልቻለም። በወቅቱም ብዙ ሕዝብ በጦርነቱ ተማገደ፣ ብዙ ንብረት ጠፋ፣ ብዙ ቤተክርስቲያኖች ተቃጠሉ፣ ተመዘበሩ። ልብነድንግልም የመጣበትን የእስላም ወረራ መቋቋም እንደማይችል በመረዳቱ የግራኝ የኃይል ምንጭ ከቱርክ የሚያገኘው ነፍጥና መድፍ መሆኑን በመገንዘብ በጊዜው ከነበረው የክርስቲያን ኃያል መንግሥት ከፖርቱጋል ጋር ተወዳጅቶ መሣሪያ ማግኘትና ባላንጣውን መቋቋም እንዳለበት ወሰነ፣ መልክተኛም ላከ። በአህመድ ግራኝ አሸናፊነት ጦርነቱ ለአሥራ አምስት ዓመት ሲካሄድ ልብነድንግል በሃይማኖቱ ፀንቶ እጁን ሳይሰጥ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ሲያመቸውም ኃይሉን እያሰባሰበ ሲመክት ቆይቶ ሞተ። እሱ ከሞተ በኋላ በቦታው የተተካው ልጁ ገላውዲዎስ ከፖርቱጋል የተላከው እርዳታ በምፅዋ በኩል ስለደረሰለት ኃይሉን አጠናክሮ ግራኝን ሊያሸንፍና ተከታዩንም ሊበታትን ቻለ።

ይህ አሥራ አምስት ዓመት የፈጀው የርስ በርስ ጦርነት በሕዝቡ ሕይወት ላይ ከፈጠረው ችግር ሌላ በኢትዮጵያ መንግሥት የኃይል ሚዛንና የመንግሥት መቀመጫ ላይ ትልቅ ለውጥ አስከተለ። መደበኛ መቀመጫው በሸዋ የነበረው መንግሥት ወደ ጎንደር እንዲቀየር አስገደደው። ይህንንም ለማድረግ የተገደደው አቅሙ በመድከሙ ፈንጠር ብሎ ኃይል ለማጠራቀምና ጉልበት ለማግኘት በጊዜው መቆራቆስ ከነበረበት አካባቢ መራቅ ስለነበረበት ነው። ነገር ግን ይህ ስልት አልሰመረም። በጦርነቱ የተፈጠረው መዳከምና

የኃይል መዛባት ልዩ ልዩ ክፍተት አስከተለ:: በመጀመሪያ ደረጃ በአካባቢው ግጭትና ግኑኝነት እስከ አሁን ድረስ የጎሳ ድርሻ ያልነበረው በኋላ መጡና ወደፊትም በኢትዮጵያ ታሪክ ታላቅ ሚና የሚጫወተውን ታላቁን የኦሮሞ ሕዝብ ፍልሰት አስከተለ:: በተጨማሪም የምፅዋና የአካባቢው የባሕር በር በ1550 ዓ.ም. በቱርኮች ሲያዝ ማስለቀቅ ስላልተቻለ የውጪ ግኑኝነት በከፊል ተቋረጠ::

የኦሮሞ ሕዝብ ቀደምት መኖሪያው ከባሌ በታች በገናሌ ወንዝ ዙሪያ ቦረና አካባቢ መሆኑን ብዙ የታሪክ ፀሐፊዎች እንደ አባ ባሕርይ(6)፣ አለቃ አጥሜ(7)፣ ይልማ ደሬሳ(8)፣ ሌዊስና(9) ሐንቲንግፎርድ(10) መዝግበውታል:: በየዘመኑ በሚነሱ የኢኮኖሚ ችግሮችና የጎሳ ግጭቶች የተነሳ አንዱ ሌላውን መውረሩ፣ ከቦታው መግፋቱና ማስለቀቁ፣ ይህም ድርጊት የአካባቢን ታሪክና የሕዝብ አሰፋፈር መቀየሩን ታሪክ ይመሰክራል:: የኦሮሞ ሕዝብ በአካባቢው ከሚገኙት የሶማሌ፣ የባንቱና ኢትዮጵያም ውስጥ ካሉት ሌሎች ብሔረሰቦች በግጭትም በጉርብትናም አብሮ ለብዙ ዘመን ኖሯል:: የኦሮሞ ሕዝብ የጥንት መኖሪያው በሆነው ከባሌ በታች በቦረናና በከፊልም ሲዳሞ (ወላቡ)፣ በጫሞና በአባያ ሐይቆች አካባቢ በቆየበት ጊዜ ሰላም አግኝቶ እንዲባዛና ኃይሉ እንዲጠናከር ረዳው:: ከዚያም ሰፊ ስፍራ በመፈለግ አሥራ አምስት ዓመት በሃይማኖት ጦርነት ኃይሉ ተዳክሞ ወደነበረው ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ አጋጣሚውን በመጠቀም በቀላሉ መፍሰስ መጀመሩን ከፍ ብሎ የተጠቀሱት የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ:: የአሥራ አምስት ዓመቱ ጦርነት የክርስቲያኑንም ሆነ የእስላሙን መንግሥታት በጣሙን ስላዳከማቸው የኦሮሞ ፍልሰት የክርስቲያኑንም ሆነ የአህመድ ግራኝ መንግሥት ይቆጣጠረው የነበረውን የኢትዮጵያ ክፍል አጥለቀለቀው:: በዚህ የተነሳ በእስላሙም በክርስቲያኑም ስር የነበሩ ግዛቶች በዚህ ጊዜ በኦሮሞ ስር ወደቁ::

ሌሎች የታሪክ ዘጋቢዎች ደግሞ አንዳንድ የኦሮሞ ስሞችን በመረጃነት በማቅረብ ኦሮሞዎች ከዚህ ጊዜ ቀደም ብለው በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፍተው ይኖሩ እንደነበር ይጠቅሳሉ::(11) አለቃ ታዬ መረጃ ባያቀርቡም ኦሮሞዎች ከ930 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ (አብሲኒያ) እንደኖሩ ጽፈዋል:: (12) ቢሆንም ሁሉም ወገኖች በዚህ ክፍለ ዘመን የተካሄደውን መስፋፋትና ጦርነት ይቀበላሉ::

የኦሮሞ መስፋፋት ጦርነት የተጀመረው በባሌ (በቀድሞው የሲዳማ ሕዝብ መኖሪያ) ሲሆን መቀመጫው ጎንደር የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ደረጃ በደረጃ የሚያስገብረው ግዛቱ በኦሮሞ የገዳ ሉባዎች (የጎሳ መሪዎች) ሲያዝ መመከት እንዳልቻለ አባ ባሕርይ (13)፣ አለቃ አጥሜና (14) ሐንቲንግፎርድ (15) ዘግበውታል:: የተለያዩ ሉባዎች ካካሄዱት ወረራ መካከል የአንደኛውን የአባ ባሕርይ የታሪክ ማስታወሻ በሚቀጥለው ዓይነት ይገልጸዋል::

> «አራተኛው ሉባ ቢፎሎ ተባለ:: እርሱም ደዋሮን በሙሉ ያጠፋው ነው:: ፈጠጋርን መውጋት ጀመረ:: ሰዎችንም መማረክ ጀመረ:: ባሮች አደረጋቸው:: ገባር ብሎ ጠራቸው:: ኮሶ መጠጣትም ጀመረ:: ስማቸውን ያነሳነው የፊተኞቹ ሉባ ግን ሰውን ወንድንም ሴትንም ይገድሉ ነበር:: ከበግና ከፍየል ከላሞችም በቀር ሌላውን አያተርፉም ነበር::» (16)

ደረጃ በደረጃ በተለያዩ ሰባዎች የተካሄደው ወረራ ብዙ ቦታ ሊያዳርስ ቻለ። በዚህም የተነሳ ሐዲያ፣ ፈጠጋር፣ ባሌ፣ ደዋሮና (የአሁኑ አርሲ) ከፊል ሸዋ በቀላሉ በኦሮሞዎች ተያዙ። ከፊል ሸዋን ያስገበረው ሠራዊት ወደ ምዕራብ ተሻግሮ ገንዝን (አምቦን)፣ ቢዛሞን (ወለጋ)፣ አባይንም ተሻግሮ አንዳንድ ግዛቶችን በጎጃም ያዘ። በእናርያ (ሊሙ)፣ በከፋና በኦሞቲክ ሕዝብ ላይም ክንዱን ጫነበት። በዚያ ዘመን የኦሮሞ ሕዝብ ፍልሰት መሬታቸውን የተነጠቁት የወላይታ፣ የሲዳማና የጉራጌ ሕዝቦች በትንሽ ቦታ ላይ ተጣበው እንዲሰፍሩ አስገደዳቸው። በየአቅጣጫው የተሰማራው የኦሮሞ ሠራዊት ሐረርን አስገብሮ ወደ ሰሜን ገሰገሰ። በአንጎት (የአሁኑ ወሎ)፣ በአማራና በትግራይም ፈሰሰበት። ወራሪው ያገኘውን እያስገበረ፣ ባህሉንና ቋንቋውን እያወረሰ ራሱም ከሌሎች ጋር እየተደባለቀ አዲሱንና ባህሉ ሌላ አቅጣጫ እየያዘ መጣ። ስለሆነም ከዚህ ሰፊ የኦሮሞ ሕዝብ እንቅስቃሴ በኋላ የኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት፣ የህዝቦች አሰፋፈር፣ ስርጭትና የቦታም ስሞች ብዙ ተለወጡ። ብዙ የታወቁ የዱሮ ታላላቅ የአካባቢ ስሞች እንደ ፈጠጋር፣ ደዋሮ፣ ዳሞት፣ አንጎት፣ አማራ ሣይንት፣ ቢዛሞ፣ እናርያና ሌሎችም ቀርተው ወይም አንሰው አሁን በምናውቃቸው በወሎ፣ አርሲ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቦረና ሣይንት፣ ራያ አዘቦ፣ ሜጫ፣ ሊሙና ሌሎችም ተተኩ። እነኝህ ስሞች አካባቢውን ያስገበረው የኦሮሞ የጎሳ ስሞች ናቸው። (17) በዚህ ወረራ የተነሳ የአማራው ተወላጆች እምብርትና መሠረት የነበሩት አንጎትና አማራ ሣይንት የሁለቱን የአማራና የኦሮሞ ብሔሮች የተዋሃዱበትን ወሎንና ቦረና ሣይንትን አፈሩ።

ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላ የፈለሰ በባህሉም ተደባልቆና ተዛምዶ መገኘቱ በኛ አገር ታሪክ ብቻ አልተከሰተም። በከብት አርቢነት ይተዳደሩ የነበሩት ኦሮሞዎች ከሌላው ጋር ከተደባለቁ በኋላ በግብርና መተዳደር ጀመሩ። ከገዳም ስርአት ወጥተው የራሳቸውን የንጉሥ አገዛዝ በወሎ፣ በጅማ፣ በሊሙና በሌሎችም አካባቢዎች መሰረቱ። ወሎ በእስላም ወረራ ጊዜ ብዙ ጥፋት የደረሰባት፣ ብዙ ቤተክርስቲያኖች የተመዘበሩባትና የተቃጠሉባት፣ ክርስቲያን የነበረው አማራ ሕዝብ እስላም የሆነባት አገር ናት። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በወሎ ገጠር ሃይማኖት ሲጠየቅ እስላም ነህ አማራ? በሚል እንጅ እስላም ነህ ክርስቲያን? የሚለው አባባል አልተለመደም። በእስላም ወረራ የተጎዳችው ወሎ ቁስሏ ሳይሽር የኦሮሞ ፍልሰት ቢያባብሰውም ወራሪዋን አስተናግዳ፣ እስልምና እምነቷን ለኋላ መጡ አካፍላ፣ ከአስገባሪዋ ስሙን ወርሳ በሂደት የአማራና የኦሮሞ ብሔሮችን ጋብቻ ያንፀባረቀችና ቦረና ሣይንትን (የጥንቱ አውራጃ ስም አጠራር) ያበረከተች ነች። እውነትም ወሎ አዲስ የተደባለቃትን አዋህዳና ቀይራ እዚህ ደርሳለች። እንደ ወሎ ሁሉ በሸዋም በአንዳንድ ቦታዎች በአማራና በኦሮሞ፣ በጉራጌና በኦሮሞ፣ በኦሮሞና በኦሞቲክ ሕዝቦች፣ እንዲሁም በሌሎች ጎሳዎች መካከል ተመሣሣይ ውህደት አጋጥሟል። በዚህ ሂደት ብዙ የሲዳማ ሕዝቦች ከኦሮሞ ጋር ተደባልቀውና ተውጠው የቀሩ እንዳሉ ይታወቃል። (18) በሐረርም ብዙ ኦሮሞዎች የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሆነዋል። ምናልባት የኦሮሞን የጥንት አኗኗርና የገዳ ስርአት ሳይደባለቅ እንዳለ ጠብቀው ለብዙ ዘመን ያቆዩት በደቡብ ጫፍ የሚኖሩት የቦረና ኦሮሞዎች ብቻ ሳይሆኑ አይቀሩም።

ከዚህ የታሪክ ወቀት በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ከማዕከሉ ከሸዋ ርቆ ጎንደር የቆየበት፣ የጎንደር መናገሻ ከተማ የተቀረቀረበትና የነፋሲል ግንብም የታነጹበት ጊዜ ነበር። በጊዜው በካህናቱ መካከል በሃይማኖት ጉዳይ በተለይም

በቆየው የኦርቶዶክስ ሃይማኖትና ከፖርቱጋል የድጋፍ ጦር ጋር በመጣው የካቶሊክ ሃይማኖት በሚነሱ ጭቅጭቆችና የቤተ መንግሥት ሸረባዎች ነገሥታቱ ተወጥረው አሳልፈዋል:: ከእነዚህ የጎንደር ነገሥታት መካከል ዘድንግልና ሱስንዮስ ቀደም ብሎ ከቆየው ልምድ ውጪ የካቶሊክ ሃይማኖትን በመቀበላቸው ትልቅ ደም መፋሰስ ሊያስከትል ችሏል::(19) ሰርፀ ድንግል ምፅዋን ለማስመለስ ባህረ ነጋሽ ይስሐቅ ከቱርክ ጋር አብሮ ባመፀ ጊዜ ያመፀውን ቀጥቶ የቱርክ ፓሻንም ዲባርዋ ላይ ቢያሸንፍም ወደቡን ሳይቆጣጠር አርቅ አድርጎ ተመልሷል::(20)

ጎንደር በተከታታይ በሥልጣን ላይ የወጡት ነገሥታት ስለተዳከሙ እንደ በፊቱ በየአካባቢው ለመዝመትና ኃይላቸውን ለመጫን አቅም አነሳቸው:: በዚህ የተነሳ በስራቸው የነበሩት የየአካባቢው መሣፍንቶች በሸዋ፣ በትግራይ፣ በጎጃም፣ በላስታ፣ በወሎ፣ በሐረር፣ በአውሳና በሌሎችም ቦታዎች ጉልበት እያገኙና እያንሰራሩ መጡ:: ኃይላቸውም ከነገሥታቱ ስለበለጠ የመሣፍንት ዘመን ተከሰተ:: በዚህ ዘመን ጎራ እየለዩና አካባቢን መሠረት እያደረጉ የተጀመረው መቆራቆስ፣ የባህር በር የነበረውን ምፅዋን በጊዜው ከወራሪዎች አለመከለከል እስከ አሁን ድረስ ያለቀቁን የታሪክ ጠባሳዎች ናቸው:: በዘመነ መሣፍንት የተቀያየሩት ጉልበተኛ መሣፍንት የፈለጉትን አሻንጉሊት ንጉሠ ነገሥት በጎንደር በማንገስ ሥልጣኑን ጠቅልለው ለራሳቸው ያዙ:: የሚቆጣጠሩትን ግዛትም ለማስፋፋት በመሣፍንቱ መካከል የተለያዩ ጦርነቶች ተካሄዱ:: የመሣፍንት ዘመንን የቀየሰው የትግራይ መሥፍን ራስ ሚካኤል ስሑል ሲሆን የሱም ተከታዮች ከወሎ ጎንደር ሄደው ለነገሥታቱ ካደሩ በኋላ ኃይል የተሰማቸው የወሎ መሣፍንት እነ ታላቁ ራስ አሊና ሌሎችም የየጁ ወረሴሖች ነበሩ:: (21)

ከመሣፍንት ዘመን በኋላ ጠንካራ ነገሥታት ተነስተው የመሣፍንቱን አርኩቻ ለማስቀረትና ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመግዛት ሞክረዋል:: ሆኖም በተከታታይ ሥልጣን የያዙት ነገሥታት ጠንካራ መንግሥት ለማቋቋም ቢጣጣሩም የአካባቢ ስሜት ያልጠፋ መሆኑን የሚያሳየው፣ ቴዎድሮስ በጎንደር፣ ተክለጊዮርጊስ በወሎ፣ ዮሐንስ በትግራይና ምኒልክ በሸዋ መፈራረቃቸው ነበር:: ይህ በአጭሩ በየዘመኑ የተቀያየሩትን የገዢ መደቦች ለመጥቀስ ያክል ሲሆን በጊዜያቸው አንዱ የመሣፍንቱን ኃይል ለማዳከም፣ ሌላው የውጭ ወራሪን ለመከላከል፣ ሌላው እስላም ክርስቲያኑን ተጭኗል በሚልና ሌላው ደግሞ በኦሮሞ ግዛቲና ሥልጣኔ ተደፍሮ አይቀርም በሚል ልዩ ልዩ ጦርነቶች አካሂደዋል:: በተለያዩ ምክንያቶች ካካሄዷቸው ከእነኝህ ጦርነቶች ባሻገር የአውሮፓ ሥልጣኔ በአገራችን ዘልቆ እንዲገባና አሻራ እንዲጥል፣ አገር አቀፍ ሠራዊት እንዲመሠረት፣ የመገናኛ አውታሮች እንዲዘረጉና ማዕከላዊ መንግሥት እንዲመሠረት ያደረጉት ጥረቶች የሚጠቀሱ ናቸው:: (22)

ይህ ገለፃ በአብዛኛው የየዘመኑን የገዢ መደቦች ታሪክና የጭቁኖችን ትግል ለማሳየት ሲሞክር ጭቆና ያለ ጨቋኝ፣ ወረራ ያለ ወራሪ፣ አዛዥ ያለ ጭፍራ፣ አስተዳደር ያለ ሕዝብ፣ የህዝብ አሰፋፈርና ስርጭት ያለ አገር በአጠቃላይ አንዱ ከሌላው ግኑኝነትና ግጭት ውጭ ለብቻው እንደማይኖር ለማስገንዘብ ነው:: የጭቁኖች ትግል በአመዛኙ ከአምባገነን መሪዎችና ከገዢ መደቦች ጋር መሆኑ ይታወቃል:: በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ ታሪክ በአብዛኛው የጦርነት ታሪክ ነው::

በየዘመኑ የተካሄዱት ጦርነቶች ያስከተሉት ውጤት ይለያያል ። ላይ የተጠቀሰው የመጀመሪያው መቆራቀስ እስልምናን በኢትዮጵያ ሲያስፋፋ ለኦሮሞ ፍልሰት መንገድ ጠረገ። ተከታዩ የኦሮሞ ፍልሰት የሕዝብን አሰረጫጨት ሲለውጥ ለተከታዩ የታሪክ ሂደትና ለአሁኑ ዘመን በብሔር ልዩነት ስበብ ለሚደረገው መናቆር የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። ይህንን የማይቀበል የአንድ ዘመን ጦርነት በተከታዩ የሕዝብ ሕይወትና ግንኙነት ላይ ምንም ተጽኖ አያደርግም ብሎ የሚሟገት ብቻ ነው። የምኒልክን ወረራ ከእነኝህ የተለየ ባያደርገውም ወራሪው የሸዋ ጦር በአቋሙ ያደገ ነገር ግን መደበኛ ደሞዝ ያልነበረው በመሆኑ ለመተዳደሪያው ጉልተኛ እያበጀ ነፍጡን እንግቦ የአካባቢውን ተወላጅ መሬቱን እየነጠቀ ያስገበረ ነበር። በዚህም ድርጊቱ የጋራ የነበረውን የደቡብ የመሬት ስሪት እንዲለወጥ፣ የመደቦች አመጣጥ እንዲጠናከርና የደቡብ አራሽ ገበሬም መሬት አልባ ገባር እንዲሆን አድርጓል። (23) የገገር መደቦች በአቆጠቆጡበት አካባቢዎችም ከእነሱ ጋር በማበር እንዲጠናከሩና ባላባቶች እንዲሆኑ አግዟል።

ምኒልክ ሊሙን ባስገበረበት ጊዜ በጎሳ መሪው በአባ ቆሮው ኃላፊነት የወል የነበረውን መሬት በመሸንሸን ከዚህ በፊት ያልነበረ ሥሪትና የመደብ ሆኔታ እንደሚከተለው ተፈጠረ።

1. ከመሬቱ 1/4 እጅ ለአካባቢው የጎሣ መሪ ለአባ ቆሮው የግል ንብረት እንዲሆን ተፈቀደለት።

2. ከተረፈው 1/4 ለጦሩ አበጋዝና ለበላይ አስተዳዳሪው እንደ ደመወዝ እንዲገለገልበት በሻለቃ መትከያ-መንቀያ ስም ተሰጠ።

3. የተረፈው 1/2 እጅ በመንግሥት ይዞታ ተመዝግቦ የመንግሥት መትከያ በመባል እንደ አስፈላጊነቱ ለመንግሥት፣ ለወታደሩ፣ ለሌሎች ሹሞችና ለቤተክርስቲያን በማደሪያ መልክ ለሰሞን መሬት፣ ለነፍጠኛ ማደሪያ፣ ግንደ በል፣ ምልምል፣ ወረገኑ፣ ባልደራስ፣ ጫን ገብ፣ ማድ ቤት፣ ሁዳድ ወዘተ ተሰጠ። በነኝህ በሦስቱም መሬቶች ላይ ይተዳደሩ የነበሩት ጭሰኛ በመሆን ከምርት ውጤታቸው አስራት ለመንግሥት (ባለመሬቱ ነበር የሚቀበለው)፣ ሲሶ ወይም እርቦ መሬቱን ለያዘው ይከፍሉ ጀመር።(24) በተጨማሪም እንደ አስፈላጊነቱ ለባለመሬቱ ነፃ አገልግሎትና ልዩ ልዩ ስጦታዎች ያበረክቱ ነበር። ጭሰኞች በጉልበት የሚያበረክቱት ነፃ አገልግሎት ሳይሰላ ከምርታቸው ሦስት እጅ ብቻ ለራሳቸው በመጠቀም ሁለት እጁን ለሌሎች ያስረክቡ ነበር። ይህም ከሞላ ጎደል ምኒልክ በዘመተባቸው ቦታዎች በሐረር፣ በአርሲ፣ በባሌ፣ በሲዳሞ፣ በከፋ፣ በኢሉባቦር፣ በወለጋና በሌሎችም ቦታዎች አጋጥሟል። በጦርነቱ ጊዜ ምኒልክ የዱሮ ግዛቴን ማቅናቴና ማስመለሴ ነው እያለ ወረራውን ሲያስፋፋ የአካባቢው ተወላጆች ደግሞ በምኒልክ ተወረርን፣ ተረገጥን፣ መሬታችንንም ተቀማን ይሉ ነበር።

የምኒልክ ሥልጣን መሰረትና መነሻ በነበረበት ሰሜን ሸዋም መሬት የሌላቸው ከባለመሬት እየተጋዙ በማረስ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ዓይነት የምርት ክፍፍል ማለትም ሦስት እጅ ለአራሽና ሁለት እጅ ለባለመሬት መከፋፈል የተለመደ ነበር።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል፣ በሰሜን ከነበረው የመሣፍንት ዘመን እርኩቻና አንዱ ሌላውን መውጋትና ማስገበር እስከ ምኒልክ ወረራ ድረስ ተገልሎ ቆይቷል። ከንግድና ከአንዳንድ የኤኮኖሚ ግኑኝነት በስተቀር ብዙዎቹ

ከሰሜኑ ጋር የነበራቸው ግኑኝነት ተቋርጦ ነበር:: (25) አንዳንዶቹም
የራሳቸው መንግሥት ነበራቸው::

የጥቁር ሕዝብ መኩሪያ የሆነው ምኒልክ በደቡብ ኢትዮጵያ በኃይለኛ
ነቱና በወራሪነቱ ሲወነጀል በሰሜን ደግሞ ኤርትራን በጣሊያን በማስቀማቱና
ከአድዋ ድልም በኋላ ባለማስመለሱ አንዳንድ ነቀፋ ይሰነዘርበታል:: በሰሜን
ያጋጠመው ችግር ከአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመንና ከአውሮፓውያን
አፍሪካን በቅኝ ግዛት መቀራመት ጀምሮ ተያይዞ የመጣ ችግር ስለሆነ
ከኢትዮጵያ ነገሥታት መካከል ምኒልክን ብቻ አያስወቅሰውም:: ምክንያቱም
የኤርትራ በወራሪዎች የቅኝ ግዛት መሆን ደረጃ በደረጃ የመጣ ጉዳይ እንጅ
በምኒልክ ጊዜ የተጀመረ አይደለም:: በቅድሚያ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ
ዘመን በቱርክ የባሕር በር በመንጠቅ የተጀመረው መዘዝ በኋላ በግብፅ ተተካ::
ግብፅ ምፅዋን እያስተዳደረ እያለ ጣሊያን በ1873 ዓ.ም. በአሰብ ተቆናጠጠ::
ከዚያም በ1887 ዓ.ም. በእንግሊዝና በግብፅ አይዞህ ባይነት ጣሊያን ምፅዋን
ደርቦ ለመያዝ በቃ:: ምፅዋን ከያዘ በኋላ ወደ ውስጥ ለመስፋፋት ያደረገው
ሙከራ ለጊዜው ቢገታም ዮሐንስ ከድርቡሾች ጋር ሲዋጋ በሞተበት ጊዜ
የጣሊያን ወራሪ ጦር እስከ ደጋው የባሕረ ነጋሽ ግዛት ድረስ ዘልቆ በመግባት
ወሮ ያዘ:: (26) (27) ከዚያም ኤርትራ የጣሊያን ቅኝ ግዛት ሆና ለስድሳ ዓመት
ቆየች:: በዘመኑ የምዕራብ አውሮፓ ኃያላን መንግሥታት አፍሪካን በቅኝ ግዛት
የሚቀራመቱበት ጊዜ ስለነበረ ከምኒልክ ጋር የተዋዋሉት አንዳንድ
ስምምነቶችም ቢሆኑ በተጽኖ የተደረጉ እንጅ በእኩልነት ላይ የተመሰረቱ ነበሩ
ለማለት አያስደፍርም::

ከአድዋ ድል በኋላ ምኒልክ የጦርነቱ መንስኤ የሆነውን የውጫሌን
ውል ቢያፈርስም ገፍቶ ሄዶ ኤርትራን ነፃ ለማድረግ በአካባቢው የገባው
ድርቅና የእንስሳት በደስታ በሽታ ማለቅ በስንቅና ትጥቅ ላይ የፈጠርው ችግር
ሃሳቡን አጨናግፎታል:: (28) ምንም እንኳን ጣሊያን በአድዋ ጦርነት ቢሸነፍም
ከአርባ ዓመት በኋላ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ኢትዮጵያን ወሮ ለአምስት ዓመት
ለመቆጣጠር ሞክሯል:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ
በእንግሊዝ ዕርዳታ ከጣሊያን ወረራ ነፃ ስትወጣ ኤርትራም ከጣሊያን ቅኝ
አገዛዝ ተላቀቀች:: ከዚህ በኋላ ኤርትራ በመጀመሪያ በእንግሊዝ የሞግዚት
አስተዳደር ለአሥር ዓመት፣ ከዚያም ለአጭር ጊዜ ከኢትዮጵያ ጋር
በፌዴሬሽን በመተሳሰር ከቆየች በኋላ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት
ከኢትዮጵያ ጋር ልትደባለቅ ቻለች::

ኤርትራን ለማስመለስና የባህር በር ለማግኘት በኢትዮጵያም
በኤርትራም በኩል ብዙ ትግል ተካሂዷል:: የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ኤርትራ
ከጥንት ጀምሮ በቋንቋ፣ በባህል፣ በኤኮኖሚና በሌሎች ግኑኝነቶች ከኢትዮጵያ
ጋር ተሳስራ የኖረች ስለሆነች ከእናት አገሯ መደባለቅ አለባት በማለት
ተሟግቷል:: በኤርትራውያኖችም በኩል በእንግሊዞች ግፊት ጥቂት ተቃውሞ
ቢኖርም ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሃድ በሚስጥር ባቋቋሙት «ማህበር
ፍቅረ ሀገር» ድርጅትና በኋላም በይፋ በሚታወቅበት «የኢትዮጵያ አንድነት
ማህበር» አማካኝነት ትልቅ ተጋድሎ ተደርጓል:: (29) የተባበሩት መንግሥታት
ከአባል አገራት የተወጣጡ የራሱን አጣሪ ኮሚሽን መልክተኞች በመላክ
የኤርትራንና የኢትዮጵያን ፍላጎት ለመረዳት ችሏል:: በእነኝህ አጣሪ ኮሚሽን
ዘገባ መሰረት የተባበሩት መንግሥታት ታህሳስ ሁለት ቀን 1950 እ.አ.አ. በ46
ደጋፊ፣ 10 ተቃዋሚና አራት ድምፀ ተአቅቦ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር

በፌዴሬሺን እንድትተዳደር ወሰነ:: (30) (31) ብዙም ሳይቆይ ኤርትራ ከእናት አገሯ ለመደባለቅ መረጠች በሚል ፌዴሬሺኑ ፈርሶ ከኢትዮጵያ ጋር ተደባለቀች:: ፌዴሬሺኑን ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ በሁለቱም በኩል ምቹ የፖለቲካ ሁኔታ አልነበረም:: ብዙዎች ለዚህ ፌዴራል ግኑኝነት መፍረስ፣ የኤርትራ ፓርላማ መበተን፣ የራስ አስተዳደር መቋረጥና የኤርትራ መብት መረገጥ የኤርትራን የገዢ መደቦችና የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ተጠያቂ ያደርጋሉ:: እውነትም ኤርትራን ለማስመለስና የባህር በርም ለማግኘት የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች ብዙ ቢዋጁም ያለ ኤርትራ ተወላጆች ተባባሪነት ስኬታማ ሊሆን፣ ፌዴሬሺኑም በአጭር ጊዜ ሊፈርስና ኤርትራም ከኢትዮጵያ ጋር ልትደባለቅ አትችልም ነበር:: (32)

ኤርትራ ከፊውዳላዊ የዘውድ አገዛዝ ስር ተጠቃላ ስትወድቅ ድርጊቱን በመቃወም የተለያዩ ገንጣይ ግንባሮች ለኤርትራ አርነት ለመታገል ተቋቋሙ:: እነሱም ሕዝብ በለመዳቸው አጠራር ጀበሐ/የኤርትራ አርነት ግንባር (ኤአግ)፣ ሻዕቢያ/የኤርትራ ሕዝባዊ ሀርነት ግንባር (ኤሕሀግ)፣ አልዋህድ/የኤርትራ አርነት ግንባር-ሕዝባዊ አርነት ኃይላት (ኤአግ-ሕአግ)፣ ወዘተ. ይባላሉ:: ሁሉም ቡድኖች በየግላቸው ለኤርትራ ነፃነት ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር በሽምቅ ውጊያ ሲታገሉ እርስ በርሳቸው በአላማ ሳይስማሙ ቀሩ:: እነኚህ ገንጣይ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ የተመሰረቱ ሲሆን የጎሳ፣ የሃይማኖትና የአካባቢ ልዩነት ነበሯቸው:: በዚህ የተነሳ በመካከላቸው ከፍተኛ የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ:: በኃይለ ሥላሴ ጊዜ አንዳንድ የኢትዮጵያ ተራማጅ ተማሪዎችና ምሁራኖች ኤርትራ በፊውዳል መንግሥት ስር መረገጥ የለባትም በማለት የነኚሁ ድርጅቶች አላማ ደጋፊ ሆነው ቆይተዋል:: «ከመሬት ለራሹ» መፈክራቸው ጎን ለጎን «ዴሞክራሲ ይከበር»፣ «የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ይከበር»፣ «በኤርትራም ጦርነቱ ይቁም» በማለት በየጊዜው አስገንዝበዋል::(33) ከተማሪዎች ትግልም አልፎ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሲመሰረቱ መጠነኛ ልዩነቶች ቢከተሉም የኤርትራን የብሔር ጥያቄና የራስን እድል በራስ መወሰን በመርህ ደረጃ ተቀብለዋል:: ሆኖም በሂደት እንደታየው አብዛኞቹ ቡድኖች፣ ከወያኔ በስተቀር፣ ተግባራዊ ይሆናል የሚል እምነት አልነበራቸውም:: በዚህ ጉዳይ ላይ የወያኔ ድርጅት ከሌሎቹ እንደሚለይና ለኤርትራም ነፃነት የሻዕቢያ አጋር ሆኖ እንደቆመ አይካድም:: በኤርትራም የተጫረውን እሳት በጊዜው የሚያጠፋው ጠፍቶ ሁሉንም ወገኖች አሁንም ድረስ ይለበልባቸዋል::

2. ኢትዮጵያ ምንጊዜም ያው ናት?

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራም ሆነ የግል ታሪካዊ አመጣጥ፣ አሰፋፈር፣ አኗኗር፣ ቋንቋና ባህል አላቸው:: በአገሪቷ ህዝቦች መካከል ያለው መተሳሰር፣ ማህበራዊ ሕይወትና የኤኮኖሚ ግኑኝነት የጠበቀ ቢሆንም የአገሪቱን የተፈጥሮ ሐብት ለጋራ እድገትና ልማት ለመጠቀም በመሪዎቿ ድክመት የተነሳ እስከ አሁን አልተሳካም:: አገሪቷም ከመቆርቆዝ በስተቀር ወደፊት አልተራመደችም::

በተለያየ ጊዜ በሥልጣን ላይ የወጡት የአገሪቷ መሪዎች ሕዝብን ለሥልጣናቸው መጠቀሚያ ከመከፋፈል፣ ያለፈውን አመራር ከመንቀፍና የቆየውን ታሪክ ከማጉደፍ በስተቀር የህዝብን ማህበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና

ፖለቲካዊ ሕይወት መቀየር አልቻሉም:: የጤና ጉድለት፣ ኋላቀር አስተሳሰብ፣ ኋላቀር አኗኗርና ኋላቀር የግብርና ዘዴዎች ሊሻሻሉ ያልቻሉ ስር የሰደዱ ችግሮች ናቸው:: ደርግ ለአገር ኤኮኖሚ መሰረት የሆነውን ግብርናን ለማሳደግ በፊውዳል ጊዜ ማነቆ የነበረውን የመሬት ስሪት በመንግሥት ባለቤትነት ቢተካውም ከፖለቲካ መጠቀሚያነት አልፎ አርሶ አደሩን የመሬት ባለቤት ስላላደረገው የርሻ ምርትን ለማሳደግና ድርቅ ባጋጠመ ቁጥር ከውጭ እርዳታ ከመለመን ሊያድን አልቻለም:: (34) (35) አምራች ኃይሉ ወጣትም ከወታደርነትና ከጦርነት ተላቆ ለአገር ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ አያውቅም:: መሪ ይቀያየራል፣ ነገር ግን የአገሪቱ ችግርና የሕዝቡ ሕይወት ዝንታለም አልተቀየሩም:: ኢትዮጵያ አንድ ነገር ብቻ ተደጋግሞ ይነገርላታል:: ለብዙ ዘመን ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች አገር መሆኗ ይገለፃል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በ1916 ዓ.ም. ስለ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር በጻፈው መጽሐፍ በዚያን ዘመን ስለ ኢትዮጵያ ያሰፈረው ሃሳብ አሁንም እውነትነት ያለው መሆኑን የሚከተለው ያመለክታል::

«እስቲ አሁን እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርነት አለን ሲባል ነውን፣ አርነት ያለው ሕዝብ ማለት እውነተኛ ትርጉሙ ለብቻው መንግሥት ያለው ሕዝብ ማለት ብቻ አይደለም፣ ራሱንም የቻለ ሕዝብ ማለት እንጂ::» (36)

በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት የተከማቹትንና ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ እየተንከባለሉ የመጡትን ችግሮች ለመፍታትና ከአምባገነን የፖለቲካ ስርዓት ለመገላገል ሰፊ ትግል ይጠይቃል:: የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየው ይህንኑ በገገር መደቦች ላይ የተካሄደውን ትግልና ጦርነት ቢሆንም ለአገሪቷ ጭቁን ሕዝቦች መፍትሔ አላገናጸፈም:: እንግዲህ ኢትዮጵያ እነኚህን ሁሉ ችግሮች ተሸክማ ወደፊት መራመድ እንደማትችል በመገመት ከዚህ አዙሪት ለመውጣት በተደረገ የአንድ ወቅት ትግል የደረሰው ጉዳት በከፊል ምን ይመስል እንደነበረ ለማስታወስ ይህ መጽሐፍ ተጻፈ::

ምዕራፍ ሁለት

የደርግ መንግሥትና የሕዝብ እልቂት

1. የደርግ መንግሥት አመሰራረትና የተካሄደው የፖለቲካ ትግል

ከምኒልክ ጊዜ ጀምሮ ሲጠናከር የመጣው የኢትዮጵያ ፊውዳል መንግሥት በኃለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ማዕከላዊነቱን እያጠናከረ በሀያኛው ክፍለ ዘመን ያለውን ቅርጽ ሊይዝ ቻለ:: ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች በማዕከላዊ መንግሥት ስር የሚተዳደሩ፣ ገዢዎቻቸውም በኃይለ ሥላሴ በቀጥታ የሚሾሙ ሆኑ:: የንጉሠ ነገሥቱንና የመሣፍንቱን ሥልጣን የሚያጠናክር ለሕዝቡ ብዙም መሰረታዊ መብት የማይሰጥ ሕገ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቷ በ1923 ዓ.ም. ተዘጋጀ:: የይስሙላ ፓርላማም ተፈቀደ:: በፓርላማው አሰራር መሰረት ንጉሠ ነገሥቱ የሕግ መወሰኛ አባላቱን ሲሰይም ሕዝቡ በሕግ ማመነጨቱ ተሳትፏል ለማሰኘት የሕግ መምሪያ ተወካዩችን በመጀመሪያ አውራጃ ገዢዎች በኋላ ሕዝቡ በቀጥታ እንዲመርጥ ተደረገ::

የኃይለ ሥላሴን አስተዳደር የሚያግዙና የአገሪቷን ኤኮኖሚ በእርሻ፣ በመገናኛ፣ በንግድ፣ በኢንዱስትሪና በሌላውም ዘርፎች የሚያበለጽጉ የተማረ ትወልድ ስለሚያስፈልግ በምኒልክ ጊዜ የተጀመረውን ትምህርት ለማስፋፋት ጥረት ተደረገ:: ውጪ አገር ድረስ የተላኩ ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ ኢትዮጵያውያን ከአውሮፓና ከአሜሪካ በእርዳታ ከመጡ ባለሙያዎች ጋር ተባብረው የኢትዮጵያን እድገት እንዲያፋጥኑ መሰረት ተጣለ:: ይህ ጥረት ከ1928-1933 ዓ.ም. በተካሄደው የጣሊያን ወረራ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ቢቋረጥም ከነፃነት በኋላ ሊቀጥል ችሏል:: ከኤርትራ መመለስም ጋር በተያያዘ የበፊቱ በ1923 ዓ.ም. የወጣው ሕገ መንግሥት ተሻሽሎ በ1948 ዓ.ም. በሌላ ቢተካም የኃይለ ሥላሴን ሥልጣን ከማጠናከር አልፎ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መብቶችን በሥራ ላይ ለማዋል አልተቻለም:: (1) ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ላይ እንደወጣ በዙሪያው ከነበሩት መሳፍንትና መኳንንት የተሻለ ዘመናዊ አስተሳሰብ የነበረው ቢሆንም ዕድሜው እየገፋ ሲሄድ ለለውጥ እንቅፋት እየሆነ መጣ:: በዚህም የተነሳ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በራሱ ቅራኔ የተወጠረ ሆነ፣ ከፍጹም የዘውድ አገዛዝ ለመውጣት እራሱ የተለመውን የአስተዳዳርና የልማት አቅጣጫ ለማራመድ ተሳነው::

መሬት በጥቂት የፊውዳል ባላባቶች በስፋት ስለተያዘ የእርሻ ምርት ሊያድግና የገባሩን ሕይወት ሊቀይር አልቻለም:: የመረረው መሬት አልባው ጭሰኛ የድካሙን ፍሬ በባለመሬቶች በመነጠቁ፣ የራሱን ሥራ እየተወ እነሱን በነጻ እንዲያገለግል በመደረጉ፣ ይህንን ማሟላት ካልቻለ ከሚያርሰው መሬት በቀላሉ በመነቀሉ፣ አነስተኛ ባለርስት ገበሬም ቢሆን በመሬት ግብር የተነሳ ለመክፈል ባለመቻሉ በአጠቃላይ የአብዛኛው ሕዝብ መተዳደሪያ የሆነው ግብርና ባለማዋጣቱ ሁኔታው ለአመጽ እየገፋፋ መጣ:: የውጭ እርዳታና ድጋፍ ለማግኘት ሲባል የአገሪቷ ኤኮኖሚ ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝና ለውጭ ምዝበራ ስለተጋለጠ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከዓለም አቀፍ ከበርቴዎች ጋር ሊወዳደሩና ሊያድጉ አልቻሉም:: የተማረውም ትውልድ እነኝህን የሕዝብ ሕይወት የሚያቆረቁዙ የፊውዶ-ቡርዣ የኤኮኖሚ ግኑኝነቶች መቀየር እንዳለባቸው ቢያምንም ሃሳቡን ለማንጸባረቅና ሁኔታውን ለማስቀየር የፖለቲካና

የዴሞክራሲ ነፃነት አልነበረውም:: በጋራም ለመታገል ድርጅት ለመመሥረት አይፈቀድለትም ነበር:: እነኝህን መሰል የአገሪቱ የኤኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ከብሔር ጭቆና ጋር የተቆራኙ ነበሩ:: በተለይም የፊውዳሉ ሥርአት በከፍተኛ ደረጃ በተንሰራፋበት በደቡብ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰብ ጭቆና የከፋ እንደነበር ይታወቃል:: በዚህ የተነሳ የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ነፃነታቸውን እየተጎናፀፉ ከኢትዮጵያ የተሻለ አስተዳደር ሲመሰርቱ የኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ሊቀጥል እንደማይችል ግልጽ እየሆነ መጣ::

እንግዲህ ከመሬት ጋር የተያያዙ የአርሶ አደር ችግሮች መብዛት፣ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች መረገጥ፣ የብሔር ጭቆና መኖርና የፊውዶ-ቡርዣው ኤኮኖሚ ለውጪ ምዝበራ መጋለጥ የፈጠረው ውጥረት የኢትዮጵያ ለውጥ ፈላጊ ተማሪዎችን «የመሬት ላራሹ» መፈክር፣ የጎጃምና የባሌ አርሶ አደሮችን አመጽ፣ የሜጫ ቱሉማ የኦሮሞ ብሔርተኞችን እንቅስቃሴ፣ የኦጋዴን ሱማሌዎችን የመገንጠል እንቅስቃሴና የኤርትራ ድርጅቶችን የመገንጠል ጦርነት ማፋፋም ሊያስከትል ቻለ:: (2) በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ የነበረው ጥላቻ እየጨመረ ሲመጣ ስርአቱን ለማስወገድ በተደጋጋሚ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራዎች ቢደረጉበትም (3) መሰረታዊ የነበሩትን ችግሮች በጊዜው ለመፍታት ምንም ጥረት አላደረገም:: እንዲያውም አንዱ ችግር ሌላውን እየወለደ የማህበራዊና የኤኮኖሚ ቀውሶች እየተወሳሰቡ መጡ:: የኑሮ ውድነት፣ የአራሹ ገበሬ ከመሬቱ እየተነቀለ ወደ ከተማ መፍለስ፣ የወሎ ሕዝብ በድርቅ ምክንያት ማለቅና በከፊልም መሰደድ ችግሩን ስላባባሰው የፊውዶ-ቡርዣው መንግሥት በ1966 ዓ.ም. በተፈጠረው ህዝባዊ አመፅ ሊወገድ ተገደደ::

በዚህ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ሕዝቡን የሚመራው ጠንካራ መሪ ድርጅት ባለመኖሩ ወታደሩ ሥልጣኑን ከሕዝብ በመንጠቅ ከራሱ በተወጣጡ ምርጥ መኮንኖችና ጥቂት የበታች ሹማምንት የሚመራ የወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ሊተካው ቻለ:: አንዱ አምባገነን ተነስቶ በምትኩ በሌላ አምባገነን የወታደር መንግሥት ተተካ:: በዚህ ግብታዊ እንቅስቃሴ አንዳንድ የተደራጁ አነስተኛ ወገኖችና ተራማጅ ምሁራን ህዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም በሰላማዊ ሰልፍና በሌሎች ህዝባዊ መድረኮች ግፊት ቢያደርጉም ሊሳካ አልቻለም::

የደርግ መንግሥት «የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነትን» (ሶሻሊዝምን) መስርቶ በኢትዮጵያ የቆየውን የፊውዳል የግል የመሬት ይዞታ የመንግሥት በማድረግና ለገበሬው እንዲጠቀምበት በመስጠት በከፊል ችግሩን ቢፈታም በሰብአዊ መብት፣ በዴሞክራሲ ጥያቄና በብሔር ጭቆና ላይ ተገቢውን መፍትሔ ለመስጠት ባለመቻሉ ከፍተኛ የፖለቲካ ተቃውሞ ገጠመው:: የፊውዳሊዝምን ኢኮኖሚያዊ ግኑኙነቶች ማፍረስ ማለት የኢትዮጵያን ችግሮች በሙሉ መፍታት አለመሆኑን ደርግ ሊገነዘብ አልቻለም:: የሚሰነዘርበት ተቃውሞም በጠንካራ ተቃዋሚ ድርጅቶችና ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የሚመራ ሆነበት:: ደርግ ደግሞ እንደማንም አምባገነን ጁንታ በኃይሉ የሚመካ ስለነበረ ያጋጠመውን ተቃውሞ ሁሉ ከማመቅ በስተቀር ቅራኔውን ለማስታረቅና ከተቃዋሚዎች ጋር ተቻችሎ ለመሥራት ባህርይው አልፈቀደለትም:: በዚህ የተነሳ ትግሉ ስለተፋፋመ በከተማ የብዙ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈ ሽብር፣ በገጠር መብትን ለማስከበር የማያቋርጥ የትጥቅ ትግልና በገንጣዮችም አገሪቷን ለመከፋፈል

የዳረገ ከባድ ጦርነት ተካሄደ:: ለመሆኑ እነኝህን ከደርግ ጋር የተደረጉ ትግሎች በዋነኛነት የመሩት ተዋንያን እነማን ነበሩ?

የኤርትራን ፌዴሬሽን መፍረስና ከኢትዮጵያ ጋር መደባለቅ በመቃወም የተለያዩ ለአርነት የሚታገሉ የገንጣይ ንቅናቄ ድርጅቶች ከ1950 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ በኤርትራ እንደተመሰረቱ ቀደም ብሎ ተገልጿል:: በተጨማሪም የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በሕዝብ አመፅ ሊገረሰስ አካባቢና ከወደቀም በኋላ ከ1960 ዓ.ም. መጀመሪያና አጋማሽ ጀምሮ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ተመስርተዋል:: እነሱም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት (ኢዴህ)፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ የኢትዮጵያ ወዝአደሮች ሊግ (ወዝ)፣ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ሬቮሊሽናዊ ድርጅት (ማሌሬድ)፣ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አባዮታዊ ትግል (ኢጭአት)፣ የአብዮታዊ ሰደድ (ሰደድ)፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ሕወሓት/ወያኔ)፣ ወዘተ. ናቸው:: ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ የደርግ ተቃዋሚ ሲሆኑ የደርግ ደጋፊዎችም የሆኑ ነበሩ:: ከደርግ ከወገኑት መካከል በሂደት አንዳንድ መሪዎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ከደርግ በመለየታቸው የስርና የግድያ ሰለባ ሲሆኑ ወዳጅ ሆነው የዘለቁት በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች ህብረት (ኢማሌድህ) ከዚያም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) የሚባለውን የደርግ ጋር ፓርቲ ሊመሰርቱ ችለዋል:: እነኝህ በደርግ ዙሪያ የነበሩ ልዩ ልዩ ድርጅቶች እንዴት ሊለያዩ እንደቻሉ ወደፊት በዝርዝር ይቀርባል::

ምንም እንኳን በወታደራዊ ጁንታ ከለላ የሚንቀሳቀሱ ቢሆኑም መኢሶን፣ ወዝ፣ ማሌሬድ፣ ኢጭአትና ሰደድ እንዲሁም የነሱ ቅንጅት የሆነው ኢሠፓም ጭምር የሕብረ በሔር ድርጅትነት ቅርጽ ነበራቸው:: በተቃራኒው ካምፕ የቆሙት ኢሕአፓና ኢዴህ እንዲሁ ህብረ ብሔር ድርጅቶች ሲሆኑ ደርግን ለማስወገድ በከተማም በገጠርም ተንቀሳቅሰዋል:: የኤርትራ ግንባሮችና ወያኔም ጭምር ለብሔሮችና ለአካባቢ አርነት የተዋጉ ነበሩ:: ኦነግ፣ አንዳንድ አባላቱ ከመኢሶንና ከኢጭአት የተወጣጡ፣ በአንድ ወቅት ከደርግ ጎን የተሰለፉ ቢሆንም፣ ስሙ እንደሚያመለክተው የኦሮሞን ሕዝብ መብት ለማጎናጸፍ የቆመ የብሔር ድርጅት ነው:: የደርግ ተቀዋሚ የነበሩት የህብረ ብሔርም ሆነ የብሔር ድርጅቶች ዋነኛ ጠላት አድርገው የሚቆጥሩት ደርግን ቢሆንም እርስ በርሳቸው ስምም አልነበሩም:: በተለይ የብሔርና ገንጣይ ድርጅቶች የህብረ ብሔር ድርጅቶችን አገራዊ አቋም ለአላማቸው ግብ መምታት እንቅፋት አድርገው ስለሚቆጥሩ ይቃወሟቸዋል:: ከገንጣይ ድርጅቶችም መካከል ሻዕቢያ፣ ወያኔና ኦነግ ተደጋጋፊ ሲሆኑ ሌሎችን ይጻረሩ ነበር::

ኢሕአፓ በጊዜው በአገሪቷ የነበረው ዋንኛ ቅራኔ የመደብ ቅራኔ መሆኑን በመገንዘብ የመደብ ትግልን (ሰፊ ሕብረ ብሔራዊ ግንባር በአገር ደረጃ በመፍጠር ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ብሮክራቲክ ካፒታሊዝም ትግል) በዋናነት ያካሂድና በአገሪቷ ዴሞክራሲ ለማምጣት ይንቀሳቀስ ነበር:: ሆኖም እንደ አንዳንድ ጠባብ ብሔርተኛ ድርጅቶች የብሔር-ብሔረሰቦች መብትንም ለማጎናፀፍ ታግሏል:: እንደ ዋነኛ ቅራኔ በመቁጠር የትግሉ መፍትሔ ዳርቻው ነፃነት ማወጅና ከአገሪቷ ተገንጥሎ መለየት ነው የሚል አቋም አልነበረውም:: የኢሕአፓ የትግል ስልት ብዙዎችን የሚስብ ሆኖ በመገኘቱ ደጋፊው በረከተ:: በዚህ የተነሳ ኢሕአፓ የበለጠ እያገነነ፣ ብዙም ደጋፊ እያበጀ መጣ:: ኢሕአፓ

የሚታገለው ደርግን ብቻ ሳይሆን አገራዊ አቋሙን (ፕሮግራሙን)፣ ህብረ ብሔራዊነቱንና ደጋፊ ማግኘቱን የማይወዱለትን የብሔርና ገንጣይ ድርጅቶችንም ጭምር ሆነ:: በዚህም የማይደሰቱ በደርግ ዙሪያ የነበሩ ድርጅቶችም ሆኑ ለአርነት እንታገላለን የሚሉት ወገኖች ኢሕአፓንና አባላቱን ማሳደድና መፍጀት ጀመሩ:: ኢሕአፓም በከተማ ከደርግ፣ በገጠር ከወያኔና ከሻዕቢያ የሚሰነዘርበትን ጣምራ በትር መቋቋም የግድ ሆነበት:: ይህም ሆኖ ተረባርበው ቢያዳክሙትም የቀመለትን አላማ ሊያስቀይሩት አልቻሉም::

በደርግና በሕዝብ መካከል የነበረው ፍጥጫ እየበረታ ሲሄድ የድርጅቶችም የርስ በርስ ሽኩቻ እየከፋ መጣ:: በተለያዩ ድርጅቶች መካከል መቆራቆስ፣ መፋተግ፣ መዋጋትና አንዱ ከአንዱ ጋር መቧደን በመጨረሻ ስኬታማ ሊያደርግ የቻለው የሻዕቢያና የወያኔን ጥምረት ነበር:: በ1972 ዓ.ም. በአመሰራረቱና በድርጅታዊ አቅሙ ቀደምት የነበረውን ጀበሐን ሻዕቢያ ከአጋሩ ከወያኔ ጋር በመሆን በጦር ፈታው:: (4) ጀበሐና ሻዕቢያ ተጻራሪ አቋም ያላቸው ኤርትራን ለመገንጠል ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጀምሮ ሲታገሉ የቆዩ ነበሩ:: ሁለቱም ከአረብ አገሮች ኢትዮጵያን ለማዳከምና ኤርትራን ለመገንጠል ድጋፍ ነበራቸው:: (5) ምንም እንኳን በመሣሪያውም ሆነ በተዋጊው ብዛት ጀበሐ ያይል የነበረ ቢሆንም ሻዕቢያ ሊያሸንፍ ቻለ::

የወያኔና የሻዕቢያ ፍቅር የበረታውና ተደጋጋፊ ሊሆኑ የቻሉት ያለ ምክንያት አልነበረም:: ወያኔ የተመሰረተው በሻዕቢያ ድጋፍ ሲሆን ታጣቂዎቹም ሥልጠናና የመሳሪያ ቁሳቁስ የሚያገኙት ከሱው ነበር:: የደርግ መንግሥት በምስራቅ በዚያድ ባሬ ወረራ፣ በሰሜን በገንጣዮች ትግልና በመሀል አገር በተቃዋሚዎች በተዋከበበት ጊዜ ሻዕቢያ ጦርነቱን በማስፋፋት ከረንን፣ አብዛኛውን የኤርትራን ገጠርና በከፊልም ምፅዋን ለመያዝ ቻለ:: አስመራንም ለመያዝ ተቃረበ:: ካሁን አሁን አስመራን አስለቅቆ ኤርትራን ነፃ ያወጣል ሲባል ደርግ በሶማሌ ግንባር የነበረበትን ጦርነት በድል ተወጥቶ ለመልሶ ማጥቃት ፊቱን ወደ ኤርትራ አዞረ:: በመልሶ ማጥቃቱም የሻዕቢያን ኃይል በመመከት የተያዘበትን የአስመራን ዙሪያና ብዙዎቹን ከተማዎች ለማስመለስ ቻለ:: (6) በዚህ ጊዜ በ1971 ዓ.ም. ኢሳያስ አፈወርቂን የ«ቢ.ቢ.ሲ.» (BBC-British Broadcasting Corporation) ጋዜጠኛ «በመልሶ ማጥቃት ተሸንፋችኋል ለወደፊቱ ምን እቅድ አላችሁ» በማለት ለጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ «ጦርነቱን ወደፊት በአሸናፊነት ለመወጣት በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች ማስፋፋት፣ ኢትዮጵያን መከፋፈልና ማዳከም ያስፈልጋል ብሎ ነበር::» (7) እውነትም እንዳለው ከተባባሪው ከወያኔ ጋር ጦርነቱን በኢትዮጵያ በሞላ እንዲቀጣጠል ለማድረግ ቻለ:: ለዚህም የወያኔ ተለዋዋጭ አቋም ሻዕቢያን በብዙ ረዳው::

ወያኔ ጠባብ ብሔርተኛ፣ የተዛባ ታሪክን ለራሱ የፖለቲካ ግብ መምቻ የሚጠቀምና አቋሙን በየጊዜው የሚቀያይር በመሆኑ የኤርትራ ጥያቄ በኢትዮጵያ ወራሪ ነገሥታት ቅኝ ግዛት የመሆንና አሁንም የምታካሂደው ትግል እራሷን ነፃ ለማውጣት የሚደረግ ህጋዊ የአርነት እንቅስቃሴ ትግል ነው የሚለውን የሻዕቢያን አቋም ያለማቅማማት ስለተቀበለና ስለሚያራምድ ከሻዕቢያ ጋር እጅና ጓንት ሊሆን ቻለ:: (8) ሻዕቢያ ኤርትራን ለመገንጠል እንደተቋቋመ ሁሉ ወያኔም ትግል ሲጀምር ትግራይን ለመገንጠል ነበር:: ሆኖም ይህንን የወያኔን ምኞት የትግራይ ሕዝብ እንደማይቀበለው ስለተረዳ ሃሳቡን በመቀየር ደርግን ለመጣልና በኢትዮጵያ የብሔሮች እኩልነትን

ለማምጣት እንደሚታገል አስታወቀ:: በዚህ መሰል የወያኔ ተለዋዋጭ አቋም ተጠቃሚ የሆነው የሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ነው:: በጊዜው ኢሳያስ አፈወርቂ ወያኔ ትግራይን ብቻ ለመገንጠል መነሳቱ ፋይዳ እንደሌለውና ለሁለቱም እንደማይበጅ ሳይመክር አልቀረም:: ምክንያቱም ጦርነቱ በሁለቱ ክልሎች ብቻ ተወስኖ ቢቀር ኢትዮጵያን የማያዳክምና የሻዕቢያንም ምኞት የማያሟላ መሆኑን ኢሳያስ አፈወርቂ ተረድቷል:: ለዚህም ሳይሆን አይቀርም የሻዕቢያና የወያኔ/ኢሕአዴግ ፍቅር አብቅቶ ጠላትንት አብቅለው ለባድማ ጦርነት በተዳረጉበት ጊዜ ድሮውንም ቢሆን ኤርትራ ብትገነጠልም የሌሎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች አንድነት ተጠብቆ መኖር እንዳለበት ኢሳያስ አፈወርቂ ለወያኔም ሆነ ለኦነግ ሳስገነዝብ ኖሬአለሁ ያለው:: (9)

የወያኔና የሻዕቢያ ተደጋጋፊ አቋም ኃይላቸውን አጠናክሮ ክንዳቸውን አፈረጠመው:: አንዱ በሰው ኃይል ሌላው መሣሪያና ገንዘብ በማቀበል ተደጋጋፊ ሆኑ:: በዚህም የተነሳ ሌሎችን በቀላሉ ማዳከም ቻሉ:: ኢሕአፓ የኤርትራን የራስን ዕደል በራስ መወሰን እስከመገንጠልና ነፃ መሆን ቢደግፍም የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች የሚለውን የተሳሳተ የታሪክ ትንተና አልተቀበለውም:: በዚህ የተነሳ ኢሕአፓ በኤርትራ ጥያቄ ላይ በወሰደው አቋም ጥርስ ተነከሰበት:: በተለይም ተስፋዬ ደበሳያና ኢሳያስ አፈወርቂ በ1969 ዓ.ም. በኤርትራ ጥያቄ ላይ የተፈራረሙት ስምምነት ከኢሕአፓ አቋም ጋር ተባራሪ ሆኖ መገኘት፣ በኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴም ተቀባይነት ማጣትና መሰረዝ፣ የሁለቱን ድርጅቶች ሆድና ጀርባ መሆን አባባሰው::

ኤርትራ ነፃ ወጣችም ቀረችም የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አይደለችም፣ ኢትዮጵያ በታሪኳ በዚህ ዘመን ማንንም ቅኝ ግዛት አድርጋ አታውቅም የሚል ነበር የኢሕአፓ አቋም:: ኢሕአፓ የተዛባን የታሪክ አቅጣጫ ለራሱ የፖለቲካ ሥልጣን መወጣጫ የማይጠቀም ግትር በመሆኑ፣ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም፣ ኢትዮጵያም ኤርትራን ቅኝ ግዛት የማድረግ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ የላትም በማለቱ አጣብቂኝ ውስጥ ገባ:: (10) በከተሞች የደርግ የቀይ ሽብር ሰለባ የሆነው ኢሕአፓ በትግራይና በጎንደር በሚንቀሳቀስበት የገጠር አካባቢዎችም ከደርግ የበለጠ በወያኔና በሻዕቢያ ጥቃት ደረሰበት:: እንደ ኢሕአፓና ጀበሐ ሁሉ ኢዴህም የነዚሁ የጣምራ ድርጅቶች ህብረት ሰለባ ሆኗል:: ከኢሕአፓም ጋር ፍቅር አልነበረውም::

ሌላው ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለማዳከም የተጠቀመበት ዘዴ የኦነግን የትግል አቅጣጫ ከወያኔ ጋር እንዲዛመድ ማድረጉ ነበር:: ይህም ውሎ አድሮ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ቢፈርስም በጊዜው ለሻዕቢያ ጠቅሞታል:: ደርግ ከመውደቁ በፊት በአሰሳ ሕዝብ ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ የዚህ ህብረት ውጤት እንደሆነ ሲጠረጠር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የጠበቀ ወዳጅነት አላቸው:: ማንም ኢትዮጵያዊ የኦሮሞንም ሆነ የሌላውን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር ይፈልጋል:: ያለፈን ታሪክ ለመወቃቀሻ ሳይሆን አሁን ለደረስንበት እንደ መነሻ መንደርደሪያ በመቁጠር ለአገራችን ችግር መፍትሔ መፈለግ ያስፈልጋል:: ተጋኖ የሚነገርለት የምኒልክ ወረራና የደቡብ ሕዝብ መጨቆን እውነትነት ቢኖረውም አንድን ታሪካዊ ወቅት ገንጥሎ በማጉላት ሌላውን መዘንጋት ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም:: ለራስ እንደሚስማማ ብቻ የኢትዮጵያን ታሪክ በአንድ መቶ ዓመት ለመገደብ መሞከር የትም አያደርስም:: የኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ ሂደት በምኒልክ አልተጀመርም፣ በሻዕቢያ፣ ወያኔና ኦነግም አያበቃም::

እንግዲህ ሻዕቢያ የሚያናፍሰውን የኢትዮጵያን ባለፉት መቶ ዓመታት መፈጠር፣ በወረራም በዙሪያዋ ያሉትን ሕዝቦች ኤርትራንም ጭምር ቅኝ ግዛት ማድረግ ለሚቀበሉ ድርጅቶች መንገዳችው ቀና ሆነ፡፡ ይህንን አላማ ለሚያራምዱ ድርጅቶች መሣሪያና ገንዘብ በገፍ በማቀበል ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዲያገኙ ተደረገ፡፡ ከአረቦች የሚያገኘውን ገንዘብና ቁሳቁስ ኢሳያስ አፈወርቂ ለሌሎች ማዳረስ ቻለ፡፡ ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ ወያኔም ከሻዕቢያ የወረሰውን በሥራ ላይ በማዋል ደጋፊ ድርጅቶችን በማባዛት (Multiplier System) ወደር የማይገኝለት ሆኖ ተገኘ፡፡ ዓላማውን የሚደግፉ ብሔርተኛ ወጣቶችን በተለይም ከየድርጅቱ ያፈነገጡትን በማጠራቀም የራሱ ደጋፊ ማድረግን ተያያዘው፡፡ የጦር ምርኮኞችም ሳይቀሩ በየብሔር ብሔረሰባቸው አንዳንዶቹም በየማዕረጋቸው እየተሸነሸኑ ስም እየወጣላቸው የወያኔ ተባባሪ ድርጅቶች ሆኑ፡፡ በዚህ አካሄድ የወያኔ ደጋፊ የሆኑ የአማራ፣ የኦሮሞና የሌሎችም ድርጅቶች እንደ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (በኋላ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ)፣ የኦሮሞ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ፣ ወዘተ. ሊፈጠሩ ቻሉ፡፡ ከእናት ድርጅታቸው ከወያኔ ጋር የጋራ መጠሪያ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) የሚል ስም ተሰጣቸው፡፡

የዚህ ሁሉ ጥርቅም ለሻዕቢያ ኢትዮጵያን ለማዳከም ግብ መምቻ ረዳው፡፡ የደርግም ራሱን በራሱ ማዳከም፣ በመፈንቅለ መንግሥት ሊገለብጡት የሞከሩትን ወታደራዊ መሪዎች መፍጀትና ማሰር፣ በሶቬት ህብረት መፍረክረክ የተነሳ ከውጪ የሚያገኘው ድጋፍ መቋረጥ፣ በደርግ ላይ በነበረው ጥላቻ የተነሳ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ማጣት ተጨማምሮበት ሻዕቢያና ወያኔ በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ በሚያካሂዱት የጋራ ጦርነት በ1983 ዓ.ም. ለማሸነፍ በቁ፡፡ ደርግም ተንኮታኩቶ ቀንደኛ መሪው የነበረው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከአገር ወጥቶ ወደ ዚምባብዌ ሲፈረጥጥ ሌሎች ባለሥልጣኖች እየተነዱ እስር ቤት ታጎሩ፡፡ አዲስ አበባና አስመራ ሲያዝ አካባቢ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከሥልጣን ገለል እንዲልና ዚምባብዌ ጥገኛ ሆኖ እንዲኖር የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች፣ የዚምባብዌ መሪ ሮበርት ሙጋቤና ሌሎችም በጋራ ሳይመክሩበት አልቀረም፡፡

በዚህ መቀራቀስ የበፊት ባላንጣ የነበሩት ኢሕአፓና መኢሶን ከሌሎች ደጋፊዎቻቸው ጋር በመሆን የኢሕአዴግ ተቀናቃኝ የሆነውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅትን (ኢድኃቅ) ቢመሰርቱም የውጪ ድጋፍ ስላልነበራቸው ውጤታማ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ የድርጅቶች ህብረት በውጪ ድጋፍ ካልታገዘ በራሱ ለውጥ ማምጣት እንደማያስችል የኢሕአዴግና የኢድኃቅ ዕድገትና ግዝፈት ልዩነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡

2. የደርግ መንግሥትና ቀይ ሽብር

ደርግ በቀይ ሽብር ስም ይፋ ግድያና የኃይል እርምጃ ከመጀመሩ በፊት ብዙ ተቀዋሚዎችን በድብቅም ሆነ በይፋ ያስርና ይገድል ነበር፡፡ በአንዳንድ የሰላማዊ ሰልፎች፣ የወታደር ክፍሎችና አምፀው እጅ አልሰጥም ያሉ በአሩምታ ከተገደሉት ወይም ከተደመሰሱት በስተቀር የመጀመሪያው የደርግ የግድያ ሰለባዎች በ1967 ዓ.ም. በይፋ የተረሸኑት 59 የኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖችና አብረው ተደባልቀው የተገደሉት ተቀዋሚዎች ሳይሆኑ አይቀርም፡፡ ከዚያም

በመስከረም 1969 ዓ.ም. ከፍተኛው የሽብር አርምጃ ይፋ ከመውጣቱ በፊት በተለያዩ ጊዜያት ብዙ ሰዎች ተገድለዋል። የተገደሉትም ከልዩ ልዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች ማለትም አርሶ አደሮች፣ የላብ አደር መሪዎች፣ ተቀዋሚ ወታደሮች፣ መምህራኖች፣ ተማሪዎች፣ የድርጅት መሪዎች፣ ሰላማዊ ሰልፈኞች፣ በቁጥጥር ስር የዋሉ ተቀዋሚዎች፣ ዕቃ ደብቃችኋል የተባሉ ነጋዴዎች፣ ወዘተ. ይገኙበታል። የፖለቲካ ውጥረቱ እየጨመረ ሲሄድ የደርግ የሽብር አርምጃ ደረጃ በደራጀ እያደገ መጣ እንጅ በአንድ ጊዜ አመርታ አሳይቶ ቀይ ሽብር አልተባለም። ሽብሩና ፍጅቱ ደረጃ በደረጃ እያደገ እንደመጣ ሁሉ የድርጊቱ ስያሜም «ፀረ አብዮተኞችን የማውደም ዘመቻ» ከሚለው ወደ «ቀይ ሽብር ዘመቻ» ተለወጠ። ሁለቱም ደረጃቸው ይለያይ እንጅ በድርጊት ተመሳሳይነት ስላላቸው የቀይ ሽብር ፍጅት የተጀመረው በ1969 ዓ.ም. መሆኑ ነው። ቀይ ሽብር ዘመቻ በአመዛኙ በጊዜው በነበሩት የደርግ ተቀዋሚዎች ላይ ያተኮረ ቢመስልም በዋነኛነት ያነጣጠረው በኢሕአፓ ላይ ነበር። ለመሆኑ ደርግና ተባባሪዎቹ ለምን ኢሕአፓን በቀይ ሽብር ለማጥፋት ወሰኑ?

የኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሊወድቅ አካባቢ በጊዜው የነበረውን የፊውዶ-ቡርዣ ስልተ ምርት ግኑኝነት፣ የዴሞክራሲ አለመኖር፣ በነባ ለመደራጀት አለመቻልና የብሔር ብሔረሰቦች ጭቆና ታግሎ ለመለወጥ የኢትዮጵያ ለውጥ ፈላጊ ተማሪዎችና ምሁራኖች ቢስማሙበትም የትግሉን አቅጣጫ በመቀየስና በብሔር ጥያቄ ላይ ልዩነት ነበራቸው። በዚህ የተነሳ በሁለት አቅጣጫዎች ያመሩ አስተሳሰቦችና ቡድኖች ተከሰቱ። አንዱ ወገን የፖለቲካ ድርጅት መስርቶ የገጠር የትጥቅ ትግልን እያራመደ የዴሞክራሲያዊ አብዮት ለማካሄድ ሲዘጋጅ (11) ሌላው ደግሞ ድርጅት መስርቶ መታገልን ቢያምንበትም በሕዝቡ ውስጥ ገብቶ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ተጨባጭ ሁኔታው አይፈቅድም ማስተማርና ማደራጀት መቅደም አለበት በማለት አያምነታ አያለ የ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አመፅና የደርግ ሥልጣኑን ከሕዝብ በመንጠቅ በሥልጣን ላይ መቀመጥ ተከሰተ። (12) በተማሪ ድርጅቶችና የጥናት ቡድኖች ሲንፀባረቁ የነበሩት ልዩነቶች የፖለቲካ ድርጅቶች ሲቋቋሙ ግልፅ እየሆኑ መጡ። በተለይም በዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሺን፣ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ህብረት፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ህብረት፣ ወዘተ መካከል የተፈጠረው ስንጥቅ የማይጠገን ሆኖ ቀረ። ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ለትጥቅ ትግል መሰናዶ ሲያደርጉ የነበሩት በሙሉ በኢሕአፓ ስር በመጠቃለል በተቃዋሚነት ሲቆሙ ሌሎች በፊትም ሕዝቡን ለመደባለቅ የተጠራጠሩት ከደርግ ጋር ወገኑ።

ኢትዮጵያን ከፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ለማላቀቅና የአገሪቷን ኋላ ቀር የምርት ግኑኝነት ለማሳደግ አዲሱን ዴሞክራሲያዊ አብዮት ማካሄድ አስፈላጊ ነው በሚል በዚያን ጊዜ በአብዮታዊያን ይታመንበት ነበር። ይህ ሊተገበር የሚችለው የሁሉም አብዮታዊ መደቦች (ላብ አደር፣ አርሶ አደርና ተራማጅ ምሁራንና ንኡስ ከበርቴ) የጋራ «ዲክታተርሺፕ» በላብ አደሩ አመራር ሰጪነት ሲመሰርቱ ነው። የዴሞክራቲክ መብቶችም ለነኝህ ጭቁን መደቦች መረጋገጥ አለበት። የአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት የኢኮኖሚ ዋና ተግባር የካፒታል ክምችትን መቆጣጠርና መሬትን ለአርሶ አደሩ መጠቀሚያ ማድረግ ነው። በዚህ ድርጊት የምርት ግኑኝነትን ለመቀየር፣ ኢኮኖሚውን ለማሳደግና ድሃውና መካከለኛ ደረጃ ያለውን አርሶ አደር፣ ላብ አደሩንና ንዑስ ከበርቴውን ተጠቃሚ ለማድረግ ይቻላል። ይህንን

አብዮታዊመርህ የተለያዩ ወገኖች ቢቀበሉትም በደርግ አደናጋሪ አቋም የተነሳ
በአንዳንዶች በኩል የተሳሳተ ሂደት ተስተውሏል::
በሕዝብና በአብዮታውያን ግፊት ደርግ መሬትን የመንግሥት በማድረግ
ሰፊው ሕዝብ እንዲጠቀምበት በማወጁ ኢሕአፓም ሆነ ሌሎች በጊዜው
ደግፈዋል:: ሆኖም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም፣ አብዮቱን ለመምራትና አገር
ለማስተዳዳር ወታደራዊ ጁንታው ብቃት ስለሌለው ደርግ ከሥልጣን እንዲወገድ
ኢሕአፓ ተቃውሟል:: መኢሶንና ሌሎች በደርግ ዙሪያ የነበሩት ድርጅቶች ግን
ደርግን እንደ አብዮታዊ ንዑስ ከበርቴ በመቁጠርና አመራሩን በመቀበል የደርግ
ተባባሪ ሆነዋል፤ አንዳንዶቹም የደርግ ፖለሲ ቀያሽና አመንጪ ነበሩ:: በዚህ
የተነሳ የአብዮትና የፀረ አብዮት ወገኖች በመባባል ደርግ ከነደጋፊዎቹ በአንድ
ወገን ቆሙ፤ የሱ ተቃዋሚ የነበሩት በሌላ ወገን ተሰለፉ፣ ወደ ትግልም
አመሩ:: በሂደት ደርግ እነመኢሶን እንደሳሉት ሳይሆን የፋሽስታዊ ጁንታ
ባህርይው እየነጠረ ወጣ:: የራሱን አምባገነን የፖለቲካ ድርጅት በመመስረት
ተቀዋሚ የነበሩትን ብቻ ሳይሆን አጋር የሚላቸውን ድርጅቶች ጭምር በቀይ
ሽብር አጠፋ፣ ለስርና ለግድያ ዳረገ:::
ከፍ ብሎ እንደተገለፀው ደርግ የመሬት አዋጅ ቢያውጅም
የዴሞክራሲን ጥያቄ፣ በነፃ የመደራጀትን፤ የሕዝቡን የኤኮኖሚ ችግር
መፍታትን፤ የመሬት ይዞታው አዋጅ እንዳይቀለብስ ገበሬውን ማንቃትና
ማስታጠቅንና በብሔር ብሔረሰቦች ላይ ያለውን ችግር በተለይም በኤርትራ
የነበረውን ጦርነት መፍትሔ ለመስጠት ባለመቻሉ በሕዝብና በደርግ፣ በደርግና
በተቀዋሚ ድርጅቶች እንዲሁም በደርግና በነፃ አውጪ ድርጅቶች መካከል
የፖለቲካ ትግሉና መቆራቆሱ ተፋፋመ:: ኢሕአፓ በቅድሚያ ትኩረቱ በገጠር
የትጥቅ ትግል ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የትግል
አቅጣጫውን በሰላማዊ መንገድ በማድረግ «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት»
እንዲመሰረት ሕዝቡን ይቀሰቅስ ነበር:: በተለይም በነሐሴ 1967 ዓ.ም. መጨረሻ
ድርጅቱ ለሕዝብ ይፋ ከሆነ በኋላ ዋናው የትግል መሣሪያው ይኸው ነበር::
የኢሕአፓ አቋም በብዙዎች ይደገፍ ነበር:: ደርግ ግን ሥልጣኔን ማን ተጋፍቶ
በሚል ግራ ቀኙን ይጨፈጭፍ ጀመር:: ምናልባት በጊዜው ከወታደራዊ አገዛዝ
ለመላቀቅ ድርጅቶችን፤ ላብ አደሮችንና ተራማጅ ግለሰቦችን የሚያካትት ጊዜያዊ የስቪል
የሽግግር መንግሥት ከመመስረት ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረም::
ምንም እንኳን «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» እንዲመሰረት የኢሕፓም
ሆነ የመኢሶን ድርጅቶች ፍላጎት የነበረ ቢመስልም ሁኔታው እየተካረረ ሲመጣ
መኢሶን ከደርግ ጋር በመወገን አቋሙን ሊቀይር ችሏል:: የመኢሶን
የመቀስቀሻ መፈክርም «የነቃ የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ ትግል ያሸንፋል»
በሚል ተተካ:: ይህ መፈክር መኢሶኖች ውጭ አገር እያሉ ከነበራቸው አቋም
ብዙም ያልተለወጠ ነበር:: የኢሕአፓና የመኢሶን ድርጅቶች ልዩነቶች
የሚመነጨው ከአመሰራረታቸው ጀምሮና በተማሪዎች ትግልም ጊዜ ቢሆንም
ከዚህ ጊዜ በኋላ በጣም እየተራራቁ መጡ፣ በባላንጣነትም መተያየት ጀመሩ::
ኢሕአፓ በ1968 ዓ.ም መጨረሻ ሰላማዊ ትግሉ አበቃለት ካለ በኋላ
ከደርግ የሚሰነዘርበትን አመቃ ለመከላከል ጥቃቱ በበረታበት በከተሞች አካባቢ
ታጥቆ ተነሳ:: ደርግም የከተማው ትንቅንቅ በጣም ስላሰጋው በወሰደው የቀይ
ሽብር እርምጃ ከኢሕአፓና ከሌሎችም በኩል በመቶ ሺዎች የሚገመቱ የሽብሩ
ሰለባዎች መሆናቸውን ባቢሌ ቶላ «አንድ ትውልድ ለመምተር፣ ቀይ ሽብር
በኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፍ ዘግቦታል:: (13) ሌሎች ደግሞ ከዚህ ዝቅ ያለ

ግምትም የሰጡ አይጠፋም:: እንግዲህ በጊዜው በደርግ ጭፍጨፋ የሞተውን ልክ በእርግጠኝነት ማስቀመጥ ባይቻልም በአዲስ አበባ ሽብሩ በበረታበት ስፍራ ከ40,000-50,000 እንደተገደሉ ይገመታል:: ደርግ በሥልጣን ላይ በቆየበት ጊዜ ባካሄደው የቀይ ሽብርና በገጠር አርሶ አደሮች ላይ በፈጸመው ጭፍጨፋ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ እንዳለቀ አያጠራጥርም:: ከዚህም በላይ ከሶማሊያ መንግሥት፣ ከተቃዋሚዎችና ከገንጣዮች ጋር በተካሄዱት ጦርነቶች ብዙዎች አልቀዋል:: ኢትዮጵያ በታሪኳ እንደ ደርግ ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ እልቂት ተካሂዶባት አያውቅም::

የደርግ የቀይ ሽብር እርምጃ አይነቱ ብዙ ነበር:: ፀረ አብዮተኛ የሚላቸውን ለማደን ከተማ አቀፍ ቤት ለቤት አሰሳ አካሂዷል:: በየመንገዱና በከተሞች የመውጫ በሮች እየጠበቀ እያሰረ ገድሏል:: በአነጣጣሪ ተኳሾች በነፃ እርምጃ ከሩቅ ገድሏል:: በቀበሌዎች፣ በከፍተኞች፣ በማዕከላዊ፣ በደርግ ጽሕፈት ቤት፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በወታደራዊ ካምፖች፣ በከተማና በገጠር እስር ቤቶች በሞላ በጅምላ አስሯል:: እስረኞችን እየገረፈ ሰውነታችውን በመቆራረጥ፣ በማቃጠልና በሌላም የግፍ ምርመራ ዘዴዎች አሰቃይቷል:: ገድሎ ሬሳን «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚል ጽሑፍ ለጥፎ በየቦታው ጥሎ ለትርኢት አሳይቷል:: በጅምላ ገድሎ አፈር አልብሷል:: እስረኞችን ከነሕይወታቸው አዞ እንዲበላቸው ጅረት ውስጥ ወርውሯል:: የእስረኞችን ቤትና ንብረት ወርሷል:: ሴቶች በግድ ተደፍረዋል:: በሽብሩ ዘመድ የታሰሩባቸውንና የሞቱባቸውን ሰዎች ለፀረ አብዮተኞች እንዳታዝኑ በማለት አስፈራርቷል:: እነኝህ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው::

የሽብሩ ዋና አላማ የደርግ ተቀዋሚ የነበረውን ኢሕአፓን መንጥሮ ለማጥፋትና ሕብረተሰቡም እንዳይደግፈው ለማስፈራራት የተካሄደ ድርጊት ነበር:: የዚህ ድርጊት ጠባሳ ሕዝቡን ለብዙ ጊዜ መጥፎ ትዝታ ጥሎበታል፣ ድርጅቱንም ጎድቶታል:: ከደርግና ከተባባሪዎቹ ከተሰነዘረበት ጥቃት ሌላ ኢሕአፓ በራሱ በድርጅቱ ውስጥ በተፈጠረው መከፋፈል ብርሀነመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ የፈጠሩት አንጃ ከጠላት ጋር ማበር ክፉኛ ጎድቶታል:: አንጃዎች ኢሕአፓዎችን በነፃ እርምጃ ከሩቅ እየጠቆሙ በማስገደል፣ ከደርግ ጋር ወግነው እያሳደዱ ተከበው እንዲያዙ በማድረግ፣ ካስያዟቸውም በኋላ የደርግ መርማሪ በመሆን ቁም ስቅላቸውን በማሳየት አስፈጅተዋል::

የሽብሩ ተዋናይ የነበሩት ሰዎች ብዛት ነበራቸው:: በ1969 ዓ.ም. ከተጀመረ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 1970 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ሁሉም በየፊናቸው ገዳይ ነበሩ:: ከዚያ በኋላ ደርግን ሳያስፈቅዱ በየአካባቢው እንደፈለጉ መግደል ታገደ:: በዚህ የተነሳ የጅምላ ግድያው ጋብ ቢልም ከርቸሌ ከተሰበሰቡት እስረኞች፣ ማዕከላዊና የደርግ ጽሕፈት ቤትም ከነበሩት መካከል በጋቢና ዋራንት እየተጠሩ ደርግ ከሥልጣን እስከተወገደ ድረስ መገደላቸው አላቋረጠም ነበር:: ስለዚህ ቀይ ሽብር የተጀመረበትን ጊዜ እንጅ የቆመበትን ማረጋገጥ አይቻልም:: ቢሆንም በ1969 ዓ.ም. እና በ1970 ዓ.ም. በኢሕአፓ ላይ የተፈጸመውን አይነት ጭፍጨፋ በሌላ ጊዜ አልተካሄደም::

ከደርግ ቀይ ሽብር ድርጊት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ሁለት ጥያቄዎች አሉ:: የመጀመሪያው ጥያቄ ሽብሩን ማን ጀመረው? የሚለው ሲሆን ከዚህ ጋር በተጓዳኝ ለሽብሩ ተጠያቂ ማን ነው? የሚለውም አብሮ መታየት አለበት:: በመሰረቱ ሁለቱ ጥያቄዎች ተጠቃለው አንድ ሊሆኑ ላይሆኑም ይችላሉ::

ደርግ፣ የመኢሶን አባል የነበረው ፍቅሬ መርእድ መስከረም 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ አባላት ስለተገደለ በድርጊቱ በመናደድ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ተገደደ:: (14) የመጀመሪያውን ጥይት በዚህ ቀን ኢሕአፓ ከተኮሰ በኋላ ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምና ግብረ አበሮቹ ለበቀል በቁጥጥር ስር የነበሩ የኢሕአፓ አባላትን መግደል ጀመሩ፣ ቀይ ሽብርም በዚሁ ተጀመረ:: ከዚህ በኋላ ደርግ በሰጠው ፈቃድ ኢሕአፓን በየቦታው ማሰርና መግደሉ ቀጠለ፣ የሚል ሙግት በደርግ በኩል በቆሙ ወገኖች ይሰነዘራል:: በጊዜው የፍቅሬ መርእድ መገደል በመገናኛ ብዙሐን ተነግሯል:: ምንም እንኳን ስለ ፍቅሬ መርእድ አሟሟት በአፎይታ መጽሔት የቀረበውን (15) ወይም በክፍሉ ታደሰ መጽሐፍ (16) የሰፈረውን እርስ በርሱ የሚጣረስ ሃሳብ ለመቀበል ብንቸገርም በኢሕአፓ በተተኮሰ ጥይት መገደሉ አያጠራጥርም:: የመኢሶን አመራር እንዳርጋቸው አሰግድ ስለ መኢሶን ድርጅት በጻፈው ታሪክ ከፍቅሬ መርእድ መገደል ቀደም ብሎ መስከረም 16 ቀን 1969 ዓ.ም. ሁለት የድርጅቱ አባላት የሆኑ ተማሪዎች መገደላቸውን ማስፈሩም ሁኔታውን አይቀይረውም:: (17)

በመሰረቱ ኢሕአፓ የሕቡዕ ድርጅት ስለነበረና እንቅስቃሴውም በድብቅ ስለሆነ ቀድሞ የተናገረው ወይም የአገሪቷን የመገናኛ ብዙሐን የሚቆጣጠረው ወገን ብቻ የሚያስራጨው ይታመናል ካልተባለ በስተቀር ይህ አባባል እውነትነት የለውም:: እነ ኮለኔል መንግሥቱና ሌሎችም በቅድሚያ በኢሕአፓ ጥይት የተገደለብን ፍቅሬ መርእድ ነው ካሉ መከራከር አይቻልም:: በኢሕአፓ በኩል ግን ደርግ በሥልጣን ላይ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሰዎች ሲታሰሩና ሲገደሉ የኢሕአፓም አባላት አብረው እንደተገደሉ ክፍሉ ታደሰ «ያ ትውልድ» በሚል በጻፈው መጽሐፍ አስፍሮታል:: (18) በሱም መረጃ መሰረት የኢሕአፓ የጅማ ዞን ፀሐፊ የነበረው ክበበው ገብረፃድቅ፣ ሌሎች የኢሕአፓ አባላት፣ በርከት ያሉ የላብ አደር መሪዎችና ሌሎች ግለሰቦች የደርግን የራዛ ዘመቻ ዕቅድ በጅማ ከተማ በመቃወማቸው ግንቦት 1968 ዓ.ም. በደርግ አባሉ ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺና በመኢሶን አባል በነበረው የሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ኃላፊ ደመቀ ሐረገወይን አማካኝነት ተገድለዋል:: የራዛ ዘመቻ የኤርትራን ተቃዋሚዎች በተለይም ጀበሐን በአርሶ አደሮች ድጋፍ በጦር ለማንበርከክ የታቀደ ነበር:: ገና ከውጥኑ በህዝብ ያልተደገፈው ዘመቻ በማስገደድ በተሰባሰበ የገበሬ ጦር በጎንደርና በትግራይ በኩል ተሞክሮ ፋይዳ ቢስ ሆኖ ከሽፏል::

የጅማን መሰል እስርና ግድያ በድሬደዋም በ1968 ዓ.ም. በኢሕአፓ አባላት፣ በላብ አደር መሪዎችና በሌሎች ተቃዋሚዎች ላይ ተካሂዷል:: በ1968 ዓ.ም. የላብ አደሮች ቀን በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በተደረጉት ፀረ መንግሥት ሰልፎች ከፍተኛ ፍጥጫና መቆራቆስ ተካሂዷል:: በአንዳንድ ከተሞችም ሰልፈኞች የግድያ ሰለባ ሆነዋል:: እንግዲህ በ1968 ዓ.ም. በደርግና በኢሕአፓ መካከል ውጥረት የጨመረበትና የተካረረበት፣ የኢሕአፓ አባላትና አመራሮች ሳይቀሩ ለስርና ለግድያ የተዳረጉበትና ደርግም ኢሕአፓን ለመደምሰስ ያኮበኮበበት ጊዜ ነበር:: ባጭሩ መጪውን ፍጅትና የቀይ ሽብር ጠቋሚ ነበር::

ሌላው ከደርግ በኩል ከቆሙት ሰዎች የሚነሳው ሙግት የሚያመለክተው ደርግ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ሰዎችን ሲገድል የነበረው በፍርድ ሳይሆን ለበቀል መወጫ መሆኑን ነው:: ደርግ ለሕግ የማይገዛ ሰውን በመግደል ብቻ የሚያምን መሆኑን የሚያሳየው የኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች

የሠሩትን ወንጀል ለመመርመር የተቋቋመው መርማሪ ኮሚሽን ሥራውን ሳይጨርስ በፖለቲካ ውሳኔ 59 ባለሥልጣኖችን በዘፈቀደ መረሸኑ ነበር:: አንድ ስልጣን ላይ ያለ መንግሥት ሰዎችን ከጥፋታቸው እንዲታረሙ በፍርድ ይቀጣል ቢባልም ያለ ፍርድ በአደባባይ ይረሸናል ማለት አይደለም::

በተጨማሪ የጊዜው የፖለቲካ እንቅስቃሴ መታየት ያለበት በአጠቃላይ ሂደቱ አንድ ቀድሞ ማን ጥይት ተኮሰ ወይም ማ በተናጠል ማንን ገደለ በሚለው ሙገት አይደለም:: ደርግ የቀይ ሽብርን ዘመቻ የጀመርኩት በኢሕአፓ ተገፋፍቸ ነበር የሚል ከሆነ በሌሎች ላይ የፈጸመውን ግድያ በማን ተገፋፍቶ እንዳካሄደው የግድ አስተማማኝ ምክንያት ማቅረብ አለበት:: ሰውን ለመግደል የሚያስፈልገው ስበብ ከሆነ በደርግ ጊዜ በርበሬም የደበቀ ተገድሏል:: እንግዲህ ከዚህ አንጻር የደርግን የቀይ ሽብር ደርጊት ስንመዝነው የደጋፊዎቹ ውልግድግድ ያለ ጩኸት ሽብሩን ቀይና ነጭ አያሰኘውም፣ ከተጠያቂነትም አያድነውም:: ስለዚህ ቀይ ሽብርን የጀመረውም ሆነ ሐላፊነቱን መውሰድ የሚገባው ደርግና ወዳጆቹ እንጅ ሌላ መሆን የለበትም:: የቀይ ሽብር ድርጊት በዘር ማጥፋት ወንጀል ደርግን ያስጠይቀው አያስጠይቀው ከአገራችንና ከዓለም አቀፍ ደንቦች ጋር በማገናዘብ በጥልቀት መመርመርን ይጠይቃል::

የደርግ መንግሥት ኢሕአፓንና አንዳንድ ተቃዋሚዎችን ለመደምሰስ መስከረም 2 ቀን 1969 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉን ተከትሎ መስከረም 13 ቀን 1969 ዓ.ም. በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ላይ የተደረገው የመግደል ሙከራ መክሸፍ የደርግ መንግሥትን የሽብር እርምጃ እንዳጠናከረው ጥርጥር የለውም:: በጣሊያን ወረራ ጊዜ ጀኔራል ግራዚያኒን በቦንብ ለመግደል በነአብራሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶምና ሌሎችም ከተሞከረ በኋላ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. የተፈፀመው የበቀል እርምጃ ከቀይ ሽብር ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ግራዚያኒ ከ30,000 በላይ ኢትዮጵያኖችን እንደጨፈጨፈ ሁሉ በደርግ የቀይ ሽብርም ከ100,0000 በላይ ተመትረዋል፣ ተረሽነዋል፣ተሰቃይተዋል:: ከዚህ እንደምንረዳው የአንዳንድ አምባገነን መሪዎች ድርጊት ከቅኝ ገዢዎች የሚበልጥ እንጅ የማይተናነስ መሆኑን ነው::

ኢሕአፓ በቀይ ሽብር ወንጀለኛነት ባይከሰስም የራሱ ስህተት እንደፈጸመ መታወቅ አለበት:: ለዚህም ነው የቀይ ሽብርን ማን ጀመረውና ማን ተጠያቂ ሆነበት የሚሉት ሁለት ጥያቄዎች ተለያይተው መታየት አለባቸው የሚባለው:: ኢሕአፓም የራሱ ድርሻ አለው:: ኢሕአፓን የሚያስወቅሰው ከደርግ የተሰነዘረበትን ሽብር አቅም በፈቀደ መከላከሉ ሳይሆን ደርጊቱ ሕልውናውን እስኪፈታተነው ድረስ መራዘሙን አለማወቁና መመለሻውን አለማዘጋጀቱ ነበር:: በከተማው ትግል አባላቱ ውጥረት ሲበዛባቸው የሚያፈገፍጉበትና የሚሸሸጉበት፣ በትላልቅ ከተሞች አካባቢ በተለይም በመሃል አገር ከከተማ ወጣ ብለው በትጥቅ ትግል የሚመክቱበት ባለማዘጋጀቱ ኢሕአፓ የሽብሩን ሁኔታ መቀየር አልቻለም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም እንኳን ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ የትጥቅ ትግል በሸዋ ክፍለ ሃገር ለማካሄድ መሰናዶ ሲደረግ ቢቆይም (19) ተግባራዊ እንቅስቃሴው ዘግይቶ በ1969 ዓ.ም. መጨረሻና 1970 ዓ.ም. በመጀመሩ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል:: የኢትዮጵያ አርበኞች በጣሊያን ጊዜ በመሃል አገር በአዲስ አበባ ዙሪያ እየተሽከረከሩ ራሳቸውን ለማዳንና ጠላትን ለማስጨነቅ መቻላቸውን እዚህ ላይ ማስታዎስ ይገባል:: ሌላው ቀርቶ ብርሃነ መስቀል ረዳ በአንጃነት ከተለዩ በኋላ ኢሕአፓ

ባሰናዳው ቦታ በመርሃቤቴ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ያደረገው ሙከራ ለህይወቱ መጥፊያ ዳረገው እንጅ አልተጠቀመበትም።

በሲዳሞ ክፍለ ሃገርም እንደዚሁ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ የተደረገው ሙከራ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቶ የእንቅስቃሴው መሪዎችና ወታደራዊ ስልጠና በአሲምባና ጎንደር የወሰዱት የአካባቢው ተወላጆች ለአልቂትና ለቀይ ሽበር ተዳርገዋል። ኢሕአፓ በሰላማዊ ትግል ላይ በማተኮር የከተማውን ትግል ከገጠሩ ጋር ማገናኘት አልቻለም ነበር።

ከፍ ብሎ ከተዘረዘረው ሁኔታ በመነሳት ኢሕአፓ ራሱን ከመከላከል ባለፈ በ1969 ዓ.ም. የፖሊት ቢሮ ድርሳን (20) በሚል ባዘጋጀው ሰነድ እንዳቀነቀነው የከተማውን የትጥቅ ትግል እንደ ዋና የትግል ስልት አድርጎ መውሰድና ለህዝባዊ አመፅ ለመገፋፋት እንደ አቋራጭ መቁጠር የተሳሳተ ነበር። የሚሸሸግበትና የሚያፈግፍግበት ቦታ ሳይኖረው የደርግን ጦር በከተሞች ለመፋለም ማቀድ የሚያዋጣ አልነበረም። የኢሕአፓ የትጥቅ ትግል በከተማና በገጠር መስፋፈት አለበት የሚለው አባባልም በጊዜው ትክክል ቢመስልም ውሎ አድሮ እራሱን ለመከላከል በከተማ ሲካሄድ የነበረው ትግል ዳራው የትድረስ እንደሆነ ባለመታወቁ ድርጅቱን ጉዳት ላይ ጥሎታል። የከተማው የትጥቅ ትግል የገጠሩን ትግል ለመደጎምና መሣሪያና ሌሎች ቁሳቁሶች ለማቀበል ያስችላል የሚለው አባባልም ህልም ሆኖ ቀርቷል። የከተማው ራስን የመከላከል ትግል ጊዜያዊ ችግር መፍቻ እንጅ ዘላቂ የትግል ስልት መሆን አይችልም።

የከተማ የትጥቅ ትግል በሕዝብ መካከል እየተሽለከለኩ በአድሃሪያን ላይ ጥቃት ለማድረስ የሚያስችል ነው እየተባለ ይነገርለታል። ሆኖም በአካባቢ መሸሸጊያና መስፈንጠሪያ ቦታ ከሌለና ከገጠር የትጥቅ ትግል ውጊያ ጋር ካልተቀናጀ የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ መሆኑን ከኢሕአፓ ትምህርት ማግኘ ት ይቻላል። ኢሕአፓ በከተማ ራሱን ለመከላከል ባካሄደው የትጥቅ ትግል የሚተማመነው በወኔ በሥሩ በተደራጁ፣ ነገር ግን ተገቢውን ትጥቅ ባልታጠቁና በአግባብ ባልሰለጠኑ የጥቃት መከላከያ አባላት ነበር። እነኝህ አባላቱ ደግሞ ከባድ መሣሪያ ከታጠቁና ከሰለጠኑ አብዮት ጥበቃዎችና ከወታደሩ ክፍል ከተመለመሉ ወታደሮች ጋር የሚነፃፀሩ አልነበሩም።

ኢሕአፓን በሰሜን በኩል የጀመረው የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴም ያስወቅሰዋል። ይህን ትግል ለመጀመር የታሰበው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከመውደቁ በፊት ነበር። (21) ለዚህም የተዘጋጀው ጥንስስ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ውጪ አገር በፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅቶች እርዳታ ከሰለጠነ በኋላ በኤርትራ በኩል ወደ ትግራይ ለማስገባት ብዙ ውጣ ውረድ ገጥሞታል። (22) ጉዞውን የሚያዘገዩ የተለያዩ ችግሮችን ተቋቋሞ ትግራይ ቢደርስም በአሲምባ ለመቆናጠጥና በቀላሉ ግኑኝነት ለመፍጠር አልቻለም። ሠራዊቱ ከመደላደሉ በፊት የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በመገልበጡና የስርአት ለውጥ በማጋጠሙ ለታለመው የትጥቅ ትግል በአንድ በኩል እንቅፋት ሲገጥመው በሌላ በኩል ደግሞ ሳይደግስ አይጣላምና ከሰማይ የወረደ ህብስተመና አይነት ሰናይ ሆኖለታል።

በዚህ የስርአት ለውጥ የተነሳ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ስለተቀየረ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በአጭር ጊዜ ሲፈጠሩ ቻሉ። በነሱም መካከል የተጀመረው የከረረ ትግልና ሽኩቻ አንዱ ከሌላው ጋር የሚፈጥረው መጎዳኘ ትና መጠላለፍ ኢሕአፓ ለወጠነው መንገድ እንቅፋት ሆነበት። በዚህ ሂደት

የገንጣዮችና የብሔር ድርጅቶች ከአገር አቀፍ ድርጅቶች ጋር ያላቸው ልዩነት እየጎላ መጣ:: በሌላ በኩል የኢሕአፓ የትጥቅ ትግል በስሜን ጫፍ እንዲጀመር ሲታቀድ ከኤርትራ ተዋጊዎች ጋር ልምድ ለመለዋወጥና ለመደጋገፍ በሱዳንም በኩል መረማመጃ ለማግኘት ታስቦ የተደረገ ቢሆንም ፊውዳሊዝምን ለመታገል መሬት አልባው ገባር የነበረው በደቡብ እንደመሆኑ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባይገረሰስ ኖሮ አጉል ቦታ የተጀመረው ትግል ወደፊት መግፋት ይችላል ለማለት ያጠራጥራል:: ለዚህም ነው የስርአቱ መለወጥ በአንድ በኩል ሲጎዳ በሌላ በኩል ጠቅሟል የሚባለው:: ምናልባት የትጥቅ ትግሉን በስሜን ጫፍ በመጀመር ወደ ሌላ አካባቢ ለመሸጋገር ታስቦ ሊሆን ይችላል:: ለዚህም ቢሆን የአካባቢውን የተለያዩ ተዋጊዎች መሰረ አካሄድ በቅጥ መመርመር ያስፈልግ ነበር:: ይህም ባለመደረጉ ኤርትራን ለመገንጠል የቆሙት ድርጅቶች ለኢሕአፓ ድጋፍ በመስጠት እንደማይተባበሩ ጥንስስ ሠራዊት ካሰበበት ለመድረስ ብዙ ችግሮች ሲያጋጥመው ሳይገነዘብ አልቀረም::

ኢሕአፓ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት እንደወደቀ በሁለት መንታ መንገድ ላይ የቆመ እንደነበረ አይካድም:: በአንድ በኩል በሰላማዊ ትግል «ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት» እንዲመሰረት ሲቀሰቅስ በሌላ በኩል የገጠሩን የተራዘመ ህዝባዊ ጦርነት ያልም ነበር:: ደርግ ይህንን ቅስቀሳ ቢቀበል ኖሮ ኢሕአፓ ሁለቱን እንዴት ሊያጣጥም እንደሚችል ወይም የትጥቅ ትግሉ ምን አቅጣጫ ሊወስድ እንደሚችል ግልፅ አልነበረም:: ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በትግራይ አሲምባ የነበረው ጥንስስ ሠራዊት በርከት ላሉ ጊዜያት ከግኙኝነትና ከመረጃ ውጭ ስለነበረ የተዘነጋ የመሰለው:: (23)

እንግዲህ ኢሕአፓ ከቁጥጥሩ ውጪ ያጋጠመውንና ራሱም የሰራውን የግምት ስህተት ለማስተካከል ከባድ መሰዋእትነት ከፍሏል:: እነኝህን መሰል የውስጥና የውጪ ችግሮች መደራረብና በኋላም የከተማውን የትጥቅ ትግል ከገጠሩ ጋር ለማገናኘት አለመቻል የኢሕአፓን እንቅስቃሴ በጣሙን ገድቦታል:: በተጨማሪም ኢሕአፓ በድርጅቱ የተከሰተውን የመከፋፈል አደጋ በጊዜው መፍትሔ መስጠት ባለመቻሉ በቀይ ሽብር ጊዜ ጉዳቱን አበርክቶበታል:: ይኸው በ1969 ዓ.ም. የተጀመረው የመከፋፈል አደጋ መልኩን እየቀያየረ እስከ 1972 ዓ.ም. ዘልቋል፣ የድርጅቱ አባላትንም በከፊል ለመበታተን ዳርጓል::

ሌላው የኢሕአፓ ችግር በአገር ውስጥ ደጋፊ እንደማብዛቱ በውጭ አገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተባባሪና ደጋፊ አለማበጀቱ በጣሙን ጎድቶታል:: በዚህ የተነሳ ከራሱ አባላት በስተቀር ከሌሎች የሚያገኘው የኢኮኖሚና የቁሳቁስ ድጋፍ ውስን ስለሆነ የታለመውን የትጥቅ ትግል በቅጥ ሊያካሂድ አልቻለም:: የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ደግሞ የመሣሪያ ድጋፍ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው:: እነኝህ ሁሉ ሲጠቃለሉ በኢሕአፓ በኩል በጊዜው ገኖ የወጣው አልከኝነቱ እንጂ የፖለቲካ ብልሃቱ አልነበረም::

3. የኢሕአፓ መዳከምና የብሔርተኞች ማየል

በአንጃ አማካኝነት በከተሞች አካባቢ የተጀመረው የመከፋፈል አደጋ የኢሕአፓን ድርጅት በመፈታተን በአሲምባና በጎንደር የገጠር አካባቢዎች በሚንቀሳቀሰው የሠራዊቱ አባላትም ተዛምቶ መልኩን እየቀያየረ ተከስቷል:: (24) በየካቲት 1970 ዓ.ም. በተካሄደው የማጋለጥ ዘመቻ የአንጃውን መስመር በሠራዊቱ ውስጥ ሲያራምዱ የነበሩ ግለሰቦች ራሳቸውንና ሌሎችንም

አጋልጥዋል:: (25) በዚህ ጊዜ ከተጋለጡት መካከል ቁጥራቸው 14 የሚሆኑት 1) በድርጅት ውስጥ ድርጅት ለመመሥረት በመሞከር፣ 2) ያልተፈቀደ ስብሰባ በማካሄድ፣ 3) የኢሕአፓን አመራር ለመገልበጥ በማሴር፣ 4) ከጠላት ጋር በመደለትና ግንኙነት በመፍጠር ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው ወታደራዊ ፍርድ ቤት ቀርበው የሞት ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል:: (26) ከእነኝህ መካከል በተማሪዎች ትግል ውስጥ በግምባር ቀደምትነት የሚታወቀውና የኢሕአሠ ወታደራዊ አመራር ኮሚቴ አባል የነበረው ይርጋ ተሰማ፣ ምንም እንኳን የተመሰረተበትን ክስ ቢክድም፣ በቁጥጥር ስር ከመዋሉ በፊት በቀጥታ መገናኘት ከሚገባው ድርጅታዊ መዋቅር ውጪ ከአንዳንድ ግለሰቦች ጋር በተለያዩ ጊዜያት ሚስጥራዊ ስብሰባዎች አካሂዶ በመገኘቱ አብሮ ተገድሏል:: (27) የአንጃ ችግር በከተሞች አካባቢ ትልቅ ጉዳት እንዳስከተለና ለቀይ ሽብርም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይታወቃል:: ይህንን መሰል እርምጃ በማያዳግም ሁኔታ መወሰድ የነበረበት ከአንጭጩ በድርጅቱ ውስጥ በከተሞች ነበር እንጅ አሁን አልነበረም:: አሁን በኢሕአሠ ውስጥ ላጋጠመው ችግር በአንጃነት የተጠረጠሩትንና የተከሰሱትን ከሠራዊቱ በማስወገድ መቋቋም ይቻል ነበር:: ምክንያቱም ተዋጊው ሠራዊት እንደ ከተማው ትግል ሳይሆን የራሱ ትጥቅ፣ መንቀሳቀሻ ስፍራና (Base Area) የህዝብ ድጋፍ እንዳለው ስለሚቆጠር የተወሰደው እርምጃ አግባብ ነበር ለማለት ያስቸግራል::

በወቅቱ ወያኔ በሻዕቢያ ድጋፍ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት የሰነዘረበት ጊዜ ስለነበር በሰዎቹ ላይ የተመሰረተውን ክስና ጥርጣሬ ውስብስብ ሊያደርገው ችሏል:: እንዲያውም የሞት ቅጣቱ ከተወሰነ በኋላ በማዕከላዊ ኮሚቴ ፀድቆ ሊፈጸም የቻለው በዚሁ ውጥረት የተነሳ ሳይሆን አይቀርም:: ወያኔም ቢሆን ጦርነቱን በዚያን ጊዜ የከፈተው የኢሕአፓን የውስጥ ችግር ከተረዳና ሁኔታውን በደንብ ካገናዘበ በኋላ ነበር:: (28) ወያኔ ይህንን ጦርነት በሚያካሂድበት ጊዜ ከሻዕቢያ ብቻ ሳይሆን ከደርግም ድጋፍ ሳያገኝ እንዳልቀረ ይጠረጠራል:: በተጨማሪም ይህ ጦርነት የኢሕአፓ ሠራዊት በ1969-1970 ዓ.ም. በአሰራሩና አመራሩ የተከሰተውን ድክመት ለማሻሻል የእርማት እንቅስቃሴ ያካሄደበትና የኢሕአሠን አመራር የቀየረበትን ጊዜ ተከትሎ ስለነበረ ብዙም የተረጋጋበትና የሰከነበት ጊዜ አልነበረም:: በቀይ ሽብርና በመከፋፈል አደጋ የተጎዳው ኢሕአፓ በዚህ ጦርነት መመከት ስላቃተው ከአሲምባ ለማፈግፈግ ተገደደ:: ይህ ሽንፈት የሠራዊቱን አባላት ለበለጠ መጠራጠርና መከፋፈል የዳረገና የድርጅቱን አመራር ብቃት የተፈታተነ ነበር::

ከዚያም በ1971 ዓ.ም. በጎንደር የተካሄደው አራተኛው አጠቃላይ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ ሁኔታውን ከማስታረቅ ይልቅ ሠራዊቱን የበለጠ ከፋፈለው:: ስብሰባው ሲጠቃለል የተላለፉት ውሳኔዎችም ሆኑ የአመራሩ ስብጥር ተራውን አባላት ሳያረካው ቀረ:: (29) በዚህ ስብሰባ ከተላለፉት ውሳኔዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ይገኙበታል::

1. በ1969 ዓ.ም. የተዘጋጀው የፓሊት ቢሮ ድርሳን ከድርጅቱ መሰረታዊ የትግል አቅጣጫ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ውድቅ ተደረገ፣ ሰነዱን ያዘጋጁትና ያሰራጩትም ተወቀሱ::

2. በከተማ የተካሄደውን የትጥቅ ትግል ስብሰባው ቢደግፈውም ከገጠሩ የትጥቅ ትግል ጋር ባለመቀናጀቱ የአፈፃፀም ስህተቶች እንደነበሩበት ነቀፋ ተሰነዘረበት:: በተለይም የከተማውን የትጥቅ ትግል ከህዝባዊ አመጽ ጋር

ለማቀራኘት የተደረገው ሙከራ የተሳሳተ እንደነበረ ስብሰባው አጥብቆ ተቃወመ::

3. የኢሕአሠን እንቅስቃሴ በመመርመር ወደፊት ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች እንዲስፋፋ ስምምነት ተደረሰ::

4. ኤርትራ ነፃ እንድትወጣ ቀደም ብሎ በ1969 ዓ.ም. የተላለፈውን ውሳኔ በድጋሚ ስብሰባው ቢያረጋግጥም የሻዕቢያን ድርጅት ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጠላት በማለት ፈረጀ::

5. የኢሕአፓ አመራር ወያኔን ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አድርጎ በመቁጠር ስህተት እንደፈጸመና በቅርቡም በተደረገው ጦርነት የወያኔን አቅም ዝቅ አድርጎ በመገመት ሽንፈት እንዳስከተለ ሂስ ቀረበበት::

6. የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ከመረመረ በኋላ ኢሕአፓ ራሱን ለተሻለ ትግል እንዲያሰናዳ፣ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ፣ የድርጅቱን ፕሮግራም እንዲያሻሽልና አዲስ መተዳደሪያ ደንብ እንዲቀርጽ ወሰነ:: ይህንንም ለማሳካት አዲስ የፖሊት ቢሮ አባላት መረጠ፣ ቀድሞ ከነበሩትም መካከል የጎላ የአመራር ድክመት ያሳዩትን ከድርጅቱ አባረረ::

ከዚህ ስብሰባ በኋላ ለመጥራት የታቀደው አጠቃላይ የአባላት ጉባኤ መዘግየት፣ አንዳንድ የቆዩ አባላት ተስፋ እየቆረጡ ድርጅቱን መልቀቅ፣ አንዳንዶች ደግሞ በገጠሩ ሕይወት መሰላቸትና ከስነሥርአት ውጪ መሆን ሁኔታውን ከቁጥጥር ውጪ አደረጉት:: በዚህ የተነሳ በልዩ ልዩ የሠራዊቱ ክፍሎች ወታደራዊ አመፆች ተቀሰቀሱ:: አንዳንዶቹ ችግሮች በድርድር ሲፈቱ ቢችሉም አንዳንዶቹ መፍትሔ ሳይገኝላቸው ቀሩ:: በዚህ ሳንካ ብዛት ያላቸው የቆዩ የድርጅቱና የሠራዊቱ አባላት በ1972 ዓ.ም. አራሳቸውን እያገለሉ ወደተለያዩ አገሮች ተበታተኑ፣ የተወሰኑት እጃቸውን ለደርግ ሰጡ፣ መጠነኛ የሆኑት ደግሞ ወያኔን ተቀላቀሉ:: የኢሕአፓም እንቅስቃሴ በጣሙን ተዳከመ:: እነኝህ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት መረጃዎች የተወሰዱት የኢሕአፓ የቀድሞ አመራር አባል የነበረው ክፍሉ ታደሰ «The Generation, Part II» በሚል ከጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ነው::

የኢሕአሠ አባላት በ1972 ዓ.ም. የተበታተኑት በጊዜው የነበሩትን እምባገነን አመራሮች በመቃወም ነበር ሲሉ በአንጻሩ በዚያን ጊዜ ያጋጠሙትን ችግሮች በመታደግ ድርጅቱን አሁን እደረሰበት ደረጃ ያደረሱት ነባር የአመራር አባላት በዚህ አይስማሙም:: ከድርጅቱ የተለዩትን አባላትም ለሕግና ደንቦች የማይገዙ ከፋፋዮችና በታኞች በማለት ድርጅቱን ሜዳ ላይ ጥለው የጠፉ አድርገው ይቆጥሯቸዋል:: የክፍሉ ታደሰንም መጽሐፍ በጥርጣሬ ይመለከቱታል:: (30)

ኢሕአሠ በ1969 ዓ.ም. በአሲምባና በ1970 ዓ.ም በጎንደር የአርማጭ ንቅናቄ ባካሄደበት ወቅት ሠራዊቱ የሚተዳደርበትን ሕግና (Constitution) የውስጥ ደንቦች (Bye-Laws) አውጥቷል:: (31) አባላቱም ለእነኝህ ደንቦች ተገዢ እንዲሆኑ ይፈልጋል:: ሆኖም በሂደት ብዙዎች የእነኝህ ደንቦች ሰለባ ሆነዋል:: ሌሎች ደግሞ የእነኝህን ደንቦች አፈፃፀም ትክክለኛነት በመጠራጠር ከሠራዊቱ ለቀዋል:: ለነይርጋ ተሰማና ለ14 አባሪዎቹ መገደልና ከዚያም በኋላ ብዛት ያላቸው የኢሕአሠ አባላት መበታተን የሚቀርቡት ምክንያቶች እነኝሁ ከደንቦቹና ከአፈፃፀሙ ጋር የተያያዙ ናቸው::

ሕግና ደንብን የሚቀርጹት ሰዎች ናቸው:: ደንቡን ማክበርና ለአጸደቁትም ደንብ ተገዢ መሆን ያለባቸው ደንቡን የተቀበሉት ናቸው::

ደንቡን የሚጥሱትም እነሱው ናቸው:: የሚታሰሩ፣ የሚፈቱና የሚገደሉም እነሱው ናቸው:: በኢሕአፓ ድርጅት ውስጥ በተለያየ ጊዜ የተከሰተው ይኸው ነበር:: ሌላው ቢቀር ከታች ያሉት ተራ የድርጅቱ አባላት እንደሚገነዘቡት ኢሕአፓ እንደተመሰረተ በአባላቱ መካከል የነበረው መፈቃቀር፣ መከባበር፣ መተማመን፣ አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ መባባሉና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለሚተላለፉ ውሳኔዎች የነበረው ተገዢነት የሚያስቀና ነበር:: ታዲያ ያ ሁሉ እንዴት እንደ እንቧይ ካብ በአንድ ጊዜ ሊናድ ቻለ? ችግሩ ከደንቡ ነበር ወይስ ከአስፈጻሚው ወይስ ደንቡን ከጣሱት? በዚህ ጉዳይ ላይ የቀድሞም ሆነ የአሁን ጊዜ የኢሕአፓ አባላት ራሳቸውን መጠየቅና መመርመር ይገባቸዋል::

ኢሕአፓን እንቅልፍ የሚነሱ (Haunt) አራት የተወሳሰቡ ችግሮች አጋጥመውታል:: ከእነኚህ ዙሪያ ጥምጥም ችግሮች (Vicious Circle) ለመላቀቅ ሲውተረተር አንዳንዶች በተደጋጋሚ ጠልፈው ጥለውታል፣ ብዙዎቹም ተፈታትነውታል::

1. በቀይ ሽብርና በከተሞች አካባቢ ለተፈጠረው ችግር ማምለጫ ሰበብ መፈለግ (Scapegoat):- በቀይ ሽብር ጊዜ ለተካሄደው ፍጅት ተጠያቂው የደርግ መንግሥት ቢሆንም ኢሕአፓም የራሱ ድርሻ እንዳለው ቀደም ብሎ ተገልጿል:: ለዚህ ስህተት የተወሰኑት የአመራር አባላት ወይም አዲስ አበባ የነበሩት ብቻ ወይም በቀይ ሽብር ሕይወታቸው ያለፈው ብቻ ተጠያቂ አይሆኑም:: በጊዜው ለተፈጠረው ድክመት ሁሉም የኢሕአፓ አመራር አባላት ተጠያቂ ናቸው:: ይህም በአመራር ሰጪነታቸው ሲሆን በተሳትፎአቸው ደግሞ ሁሉም አባላት ስህተቱን ይጋራሉ::

2. የአንጃው ጥላ:- በኢሕአፓ ድርጅት ውስጥ አንጃ ባይፈጠርና መከፋፈል ባያጋጥም ኖሮ ችግሮች አይባባሱም ነበር:: በአንድ ድርጅት ውስጥ መከፋፈል ሲያጋጥም ኢሕአፓ የመጀመሪያው ድርጅት ባይሆንም የመከፋፈል አደጋውን ከባድ ያደረገው ከደርግ የቀይ ሽብር እርምጃ ጋር የተያያዘ በመሆኑንና የኢሕአፓ ክፍልፋይ አንጃም ከደርግ ጋር በመወገኑ ነበር::

በነብርሃነ መስቀል ረዳ የተፈጠረው አንጃ ሦስት አከራካሪ የልዩነት ጥያቄዎችን አነሳ:: አንደኛው ከደርግ ጋር መሥራት ይቻላል፣ የግንባር ጥሪውን ኢሕአፓ መቀበል አለበት የሚል ሲሆን በሂደት እንደታየው ግን ደርግ ከኢሕአፓ ጋር ቀርቶ አብረውት የነበሩትንም ድርጅቶች አጥፍቷል:: በጊዜው የደርግ የግንባር ጥሪ የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ደጋፊ የነበሩትን ድርጅቶች አጋርነታቸውን እንዲያጠናክሩ ለማድረግ እንጅ ኢሕአፓን የሚመለከት እንዳልነበረ መኢሶን አረጋግጧል(32):: ሁለተኛው ደግሞ የከተማው የትጥቅ ትግል መካሄድ የለበትም የሚል ነበር:: ይህም ቢሆን ኢሕአፓ ራሱን ለመከላከል በመገደዱ የተወሰደ እርምጃ ሲሆን መመለሻውን ባለማወቁና በአንጃውም የውስጥ አርበኝነት ድርጅቱን ጉዳት ላይ ጥሎታል:: ሌላው በዝቅተኛ ደረጃ የተነሳው ሦስተኛው የልዩነት ነጥብ ደርግ ፋሽስት ነው አይደለም በሚለው አባባል ነበረ:: የደርግ መንግሥት የፋሽስት መንግሥት ተደርጎ ይቆጠር የነበረው ከድርጊቱና ከአንዳንድ ባህርያቱ ጋር በተያያዘ እንደነበር ይታወሳል:: በዚህ የተነሳ ምንም የዴሞክራሲ መንገድ በማይከተልና የፋሽስት ድርጊት ከሚፈፅም መንግሥት ጋር ግንባር መፍጠር የኢሕአፓ ድርጅትን ለከፋ አደጋ ማጋለጥ ነው በሚለው ወገንና በተቃራኒው በቆሙት መካከል ልዩነቱ እየሰፋ መጣ::

እነኝህ ልዩነቶች የተፈጠሩት በተዋረድ እንደተጠቀሱት ደረጃ በደረጃ እንጅ አንዳንዶች እንደሚያቀርቡት በአንድ ጊዜ አልነበረም። በጊዜው የተፈጠረውን ብዥታ ለማጥራት ኢሕአፓ መጠነኛ ማብራሪያ በተለያየ ጊዜ ሰጥቷል፤ በተለይም ስለ ፋሺዝም አነሳስ አጠቃላይ ይዘትና የኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ፣ የውስጥ ፓርቲ ትግል፣ የጋራ ግንባር አመሰራረት፣ የኢትዮ ሶማሌ ጦርነት፣ ሶሻል ኤምፔሪያሊዝም ያቀረበውን እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል።

በጊዜው አነብርሃነ መስቀል ረዳ ሃሳባቸው በአብዛኛው የኢሕአፓ አመራር አባላት ተቀባይነት ሲያጣ የወሰዱት እርምጃ ለዴሞክራሲ ተገዢ ባለመሆን ድርጅቱን መከፋፈልና አንጃ መፍጠር ነበር። የአንጃው አባላት እራሳቸውን «የእርማት ንቅናቄ» የሚያራምዱ አድርገው ቢቆጥሩም ድርጊታቸው ግን እንደ ጥላ ወጊ ነበር። በዚህ የተነሳ የኢሕአፓን እንቅስቃሴ እያደቡ በይፋም ሆነ በድብቅ በከተማም ሆነ በገጠር አዳክመውታል። ዝርዝሩ በምዕራፍ ስድስት ይቀርባል። በኢሕአሠም ውስጥ የነበሩት ደጋፊዎቻቸው በሠራዊቱ ውስጥ ለተፈጠሩት ሆኔታዎች መካረርና ለአንዳንዶቹ ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆነዋል። የአንጃው አስተሳሰብ በጥቂት የኢሕአፓ አመራር አባላት ከተጠነሰሰ በኋላ ወደ ብዙኂኑ ለመሰራጨት እንደሞከረ ይታወቃል። ብዙም መስፋፋት ባይችልም በአንጭጩም መቀጨት አልቻለም። ይህ ከስንዴው መካከል የተዘራ እንክርዳድ ስንዴው እበቀለበት ቦታ ሁሉ አብሮ በቅሏል። ስንዴውን ከእንክርዳዱ በአግባብ መለየት ባልተቻለበት ቦታም «ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ» አይነት አጋጥሟል። በዚህ የተነሳ አስመሳዩን ከሌላው መለየት ባልተቻለበት አጋጣሚዎች አንዳንድ የድርጅቱ እውነተኛ ደጋፊዎች ሳይጎዱ አይቀርም።

ከአንጃው አመራሮች መካከል አንዳንዶቹን በውይይትና ድርድር የሚያምኑ አድርጎ ለማቅረብ የሚሞከረውም ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ነው። በውይይትና ድርድር የሚያምን ድርጅቱን ከፋፍሎ በድርጅት ውስጥ ድርጅት አይመሰርትም፣ ከኢሕአፓ ድርጅታዊ አሰራር ውጭም እንቅስቃሴ አያካሂድም። ከደርግም ጋር በድብቅ አይወግንም።

3. የብሔርተኞች ተጽኖ፡- ከቀይ ሽብር በኋላ የብሔርተኛና ጎጠኛ ድርጅቶች ገነው መውጣት ኢሕአፓን በጣሙን ጎድቶታል። በመጀመሪያ ደረጃ ከቀይ ሽብር በትር ብዙም ሳያገግም በ1970 ዓ.ም. ከወያኔ ጋር ባካሄደው ጦርነት በመሸነፉ እቋሙን እናግቶበታል። የኃይል ሚዛን በአስተሳሰብ ሚዛን ላይ ተጽኖ ያደርጋል። ኢሕአፓና ኢዱህ ከመዳከማቸው በፊት የሕብረ ብሔሩ ጎራ ተቀባይነት ነበረው። ነገር ግን በዚያው ሊቀጥል አልቻለም። ከበለሳ ከድተው ወያኔን የተቀላቀሉት የኢሕአሠ አባላትም የዚሁ የኃይል ሚዛኑ መናጋት የቀሰቀሰው ማእበል የጠለፋቸው ነበሩ። ከኢሕአፓ ከድተው ወያኔን ተጠግተው ብአዴንን ቢመሰርቱም የብሔርተኝነት ሰለባ ሆኑ እንጅ በራሳቸው በመቆም የህብረ ብሔሩን ጎራ በማጠናከር አልታገሉም።

በአንድ በኩል የብሔርተኞችን ተንኳሽነት፣ በሌላው በኩል የደርግን ጥቃት የሚከላከለው ኢሕአፓ በሠራዊቱ ውስጥ ጥብቅ ወታደራዊ ሥነ ሥርአት እንዲሰፍን ይፈልግ ነበር። የሥነ ሥርአት መጥበቅ ደግሞ ተቃውሞን ያስነሳል። በሌላ መልኩ የሥነ ሥርአት መንደልም የብዙዎችን ሕይወት አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል። በዚህ የተነሳ የኢሕአፓ ድርጅት በሁሉም መልክ ተወጥሮ አሳልፏል። የብሔርተኞች ተጽኖም እየቀጠለና እያደገ መጥቶ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች አገሮችም ብዙ ጉዳትና መከፋፈል

አድርሷል። የብሔርን ጥያቄ ከሌላው ለይቶ በማጉላት የዘመኑ የብሶት መግለጫ ሆኗል።

የደርግ መንግሥት የፊውዳሉን የመሬት ይዞታ ቢለውጥም የአገሪቷ የዴሞክራሲ ሁኔታዎች ስለአልተቀየሩ የብሔር ጥያቄን አንግበው የተነሱትን ድርጅቶች ትግል እያጎላው መጣ። በዚህ የተነሳ ኢሕአሠ አሲምባ ለመቆናጠጥ ከሞከረ ጀምሮ ተደጋጋሚ ችግሮች ገጥመውታል። ታዲያ ከዚህ ትምህርት በማግኘት ከወያኔና ሻዕቢያ ጋር በ1970 ዓ.ም. ትግራይ ውስጥ ከመፋጠጥ ለምን ለቆ አልወጣም ነበር? ይህም ከጠባብ ብሔርተኞች የሚሰነዘረውን አደጋ አለመገንዘቡን ያመለክታል። ከዚህ መሰል ሽኩቻ ለመዳን ቀደም ብሎ አካባቢውን ለቆ ጎንደር ፀለምት በ1968 ዓ.ም. ወደ መሰረተው የመንቀሳቀሻ ቦታ ተጠቃሎ ቢሆን ኖሮ ኃይሉን በመቆጠብ ለተሻለ ፍልሚያ መዘጋጀት ይችል ነበር። ይህ ባለመሆኑ በትግራይም በወልቃይትም የጥቃት ሰለባ ሆነ።

4. የሠራዊቱ ስብጥር፦ ለትጥቅ ትግል ከከተማና ከገጠር የተሰባሰበው የኢሕአሠ ሠራዊት ስብጥር አስተሳሰብና የንቃት ደረጃ የተለያየ ነበር። በተለይ በገጠሩ የትጥቅ ትግል የቆዩትና አዲስ የተደባለቁት የድርጅቱ አባላት እስኪላመዱና ተቀራራቢ አስተተሳሰብ እስኪያዳብሩ ድረስ ልዩ ክትትል ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህ ካልሆነ ግን ስብጥሩ ዝብርቅርቅ እንደሆነ ይዘልቃል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ የሠራዊቱ አባላት የታየው ተስፋ መቁረጥ፣ ደርግን ማሸነፍ አይቻልም እስከ ማለት መድረስ፣ ደርግን በትጥቅ ትግል ለማሸነፍ መሞከር ሰማይን እንደመቧጠጥ ይቆጠራል የሚል አባባል መሰንዘር፣ ገበሬው ተገዶም ይሁን በኋላ ቀርነት ከደርግ ጋር አብሮ ኢሕአሠን አንዳንድ ቦታ ሲወጋ የሚያጋጥመው ተስፋ መቁረጥ፣ የመሬት ጥያቄ ስለተመለሰ የገጠሩን የትጥቅ ትግል ገበሬውም አይደግፈውም ብሎ መጠራጠር፣ የገጠሩን ሕይወት አለመቋቋም፣ ከደንብ ውጪ መዳራት፣ ከወታደራዊ ሥነ ሥርአት ውጪ አልዋጋም ማለት፣ ወዘተ. (33) የስብጥሩን ድክመት የሚያመለክቱ ነበሩ።

እነኝህና ሌሎችም በክፍሉ ታደሰ መጽሐፍ ውስጥ በስፋት የተጠቀሱት ድክመቶች የሚያሳዩት ያ ስብጥር በገጠር አብሮ መዝለቅ እንደማይችል ነበር። በዚህ ግርግር ወቅት ለትግሉ ቅን አመለካከት የነበራቸው አንዳንድ ታጋዮች በሁኔታው ተስፋ እየቆረጡ ኢሕአሠን ጥለው መሄዳቸው ይታወቃል። በዚህ ጊዜ ከለቀቁት መካከል የኢሕአፓ መሥራች፣ የትጥቅ ትግሉ ፊር ቀዳጅና ከመጀመሪያው ጀምሮ የኢሕአሠ ወታደራዊ ኮማንደር የነበረው አብዲሳ አያናና የሠራዊቱ ጠቅላይ አመራር አባል የነበረው ገብሩ መርሻ በፍቃዳቸው መሰናበት የሚያስቆጭ ነበር።

በዚያን ወቀት ኢሕአፓ ከተጋረጠበት የመበታተን አደጋ አገግሞ በቀጣይነት ትግሉን ለማካሄድ እንዲረዳው ከጊዜው ጋር ሊራመድ የሚያስችል የፕሮግራም ለውጥ በማድረግ ወደፊት ለመጓዝ ሞክሯል። ይህንንም ያደረገው የትግል አቅጣጫውን እየመረመረ፣ የተሳሳተውን መስመር እያስተካከለ፣ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሊዛመድ የሚችል ፕሮግራም እየነደፈና ደረጃ በደረጃ እራሱን እየቀየረ በመጓዝ እንጅ በ1973 ዓ.ም. ሱዳን ውስጥ በተካሄደው የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ አንዳንድ የአመራር አባላቱ እንዳቀነቀኑት ድርጅቱን አፍርሶ እንደገና በመገንባት ወይም በሌላ የግራ ዝንባሌ ባለው አንቅስቃሴ በመተካት አልነበረም። (34)

ምዕራፍ ሦስት

የቀይ ሽብር አስከፊ ትዝታ

1. የማይረሳ ቀን

«በአንድ ህብረተሰብ የአመፅ መንፈስ ሊፈጠር የሚችለው በአኩልነት ሽፋን ትልቅ ልዩነቶች ሲፈጸሙ ነው።» (The spirit of revolt can only exist in a society where a theoretic equality conceals great factual inequalities). (1)

ልጅ ሆኘ ከትምህርትና ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ የገጠሙኝ ነገሮች ትዝታቸው አሁንም ይመጡብኛል። የሩቁንም የቅርቡንም ያስታውሱኛል። ወላጅ አባቴ የቄስ ትምህርት ተምሬ የሚወደውን የቅዱስ ገብርኤል ታቦት አገልጋይ ብሆን ደስታውን አይችለውም ነበር። ሆኖም መሰረታዊ የቄስ ትምህርት ከተከታተልኩ በኋላ በቤተዘመድ ግፊትና በአካባቢውም ተጽኖ በጊዜው አጠራር የመንግሥት ትምህርት ቤት አስገባኝ። ተምሬ ምን እንደምሆን አባቴ እርግጠኛ ባይሆንም እኔን በትምህርት ማትጋትና አንዳንድ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች መግዛት የዘወትር ተግባሩ ነበር። እንደምገምተው አባቴ ይህንን የሚያደርገው ትምህርት ቤት አብሬ ከምውላቸው ጓደኞቼ እንዳላንስ ፈልጎ እንጅ የትምህርትን ጥቅም ተገንዝቦት አይመስለኝም። እኔም አሁን ወደኋላ ተመልሸ ከትምህርት ያገኘሁትን ጥቅም ስመዝነው ባዶነት ይሰማኛል። የተማረው ትውልድ እርስ በርሱ ሲተላለቅ እንጅ የአገርንም ሆነ የራሱን ሕይወት ሲቀይር አይታይም፣ ሁለቱን ለይቶ ማየትም አይቻልም። ታዲያ ትምህርት ለዚህ የሚጠቅም ካልሆነ ምን ፋይዳ አለው?

የአሁን ዘመን ልጆች በቄስና በመንግሥት ተማሪዎች መካከል ጥንት የነበረውን ስድብና ፉክክር አያውቁትም። ከሰፈር ልጆች ጋር የቄስና የመንግሥት ተማሪዎች ወገን እየለዩ መሰዳደብ የሚታወስ የልጅነት ትዝታ ነው። «የመንግሥት ተማሪ ምን ይበላል ዓሣ ሁሉ ኮሳሳ»፣ «የቄስ ተማሪ ምን ይበላል ፍርፋሪ ሁሉም ሆነ ፈሪ» እየተባባሉ ለድብድብም መገባበዝ ነበር። ለነገሩ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚማሩት በእድሜ ትላልቆች በመሆናቸው በቄስ ተማሪዎች ይፈራሉ። ችግሩ የመንግሥት ትምህርት ቤት ከተገባ በኋላ በክረምት ትምህርት ቤት ሲዘጋ የቄስ ትምህርቱ እንዳይረሳና እንዳይዘነጋ ቄስ ትምህርት ቤት ለመከለስ ተመልሶ ሲገባ የትኛውን ወገን መስደብ እንደሚገባ ይጨንቅ ነበር።

ሌላም፣ ሁልጊዜ ገብርኤል በሆነ ቀን የማልረሳውና የማስታውሰው ትዝታ አለኝ። አንዳንድ ጊዜ ገብርኤልና አባቴ ይመሳሰሉብኛል። እንደ አሁን ዘመን የአምበሬ ጭቃ (እስክሪፕቶ) ባልተለመደበት ጊዜ ዱሮ ተማሪ እያለን በቀለም ጠብታ ብዕር መጻፍ እናዘወትር ነበር። ታዲያ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ አንድ በትንሽ ገንዘብ ከልጆች የገዛኋት የምወዳት ጥሩ ብዕር ነበረችኝ። በቀለም አወራረዷና በአጻጻፏ በጣም እወዳት ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ያች ብዕር ጠፍታብኝ በልጅነት አእምሮ በጣም ተናድጀ አምርሬ ሳዝን አባቴ እኔን ለማጽናናት «አይ ዛሬ ቀኑ ምንድነው? ለካስ ገብርኤል ነው፣ የኔ ገብርኤል ምን ሰርቸ ነው ልጄን ሃዘን ላይ የጣልከው» ብሎ ሲጸጸት በጣም ደነቀኝ።

አባቴ ገብርኤልን በጣም ያከብራል፣ ይዘክራል፣ በቀኑም ሥራም አይሰራ:: በዕለተ ቀኑ አንድ ችግር ከደረሰበት ምን አድርጌ ይሆን በማለት እራሱን ይጠይቃል:: እኔም አሁን አድጌ የሱን ያክል የእምነት ጽናት ባይኖረኝም በመንገድም ሳልፍ የኔብጤ ስለ ገብርኤል ሲል የአባቴም ሆነ የቀኑ ትዝታ ይመጡብኛል::

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ በ1969 ዓ.ም. እና በ1970 ዓ.ም. የተካሄደው የቀይ ሽብር ትርምስ ብዙ አስደንጋጭ ትዝታ ትቶ አልፏል:: በዚያን ጊዜ ደርግ ብዙ ወጣቶችንና ምሁራንን ለስር፣ ለስደትና ለግድያ ዳርጓል:: (2) እኔም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ የዚሁ ሰለባ ሆኛለሁ:: ሚያዝያ 19 ቀን 1970 ዓ.ም. ከማስተምርበት ከደብረ ዘይት የረዳት የእንስሳት ሐኪሞች ማሰልጠኛ ተቋም በጠዋት ተነስቼ ከተቋሙ ተጠባባቂ ርዕሰ መምህር ጋር ወደ አዲስ አባበ በረርኩ:: በቀኑ አንድ የተቋማችንን ትንሽ ሬኖ መኪና እያሽከረከርኩ አንዳንድ ነገሮችን ለተቋሙ ለመግዛትና ሌሎች ገዳዮችን ለመፈጸም ወደ አዲስ አባባ ሁለት ሆነን አመራን:: የቀይ ሽብር ዘመን ስለነብር በየመንገዱ የሚደረገው ፍተሻ እንዳለ ቢሆንም የሽብር እርምጃ እየተባለ በየመንገዱ፣ በየአደባባዩና በየሰው መኖሪያ ደጃፍ የሚጣለው ግዳይ ጋብ ብሏል:: «ፀረ አብዮተኞችን» ማደኑ ግን እንደቀጠለ ነበር::

የደርግ የሽብር አራማጆች ሲያሰኛቸው ቁም ሳይሉ ከሩቅ ተኩሰው መግደል ወይም ከነመኪናው መደምሰስ አሁንም አልፎ አልፎ ያጋጥማል:: ስለዚህ ማንም የቆመበትን አያምንም፣ የስጋትና የጥርጣሬ ሕይወት ይመራል:: የፖለቲካ ተሳትፎ ያለው ከዛሬ ነገ ተያዝኩ ወይም በነፃ እርምጃ ተደመሰስኩ እያለ ሲያሰላስል ምንም የማያውቀውና ትግሉ ግራ ያጋባው ደግሞ እሱንም ጠርጎ ይዞት የሚሄድ ስለሚመስለው ይጨነቃል:: በዚህ ምስቅልቅል ሕይወት ውስጥ ጥርጣሬ የገባው መዋያና ማደሪያ ቦታውን መቀያየር፣ የፀጥታ ኃይሉን እንቅስቃሴ መሰለል፣ ማን ተይዞ ማን ተገደለ ብሎ ለማጣራት መሞከር፣ ሌላው ቀርቶ በሚውልበት አካባቢ ማን ሊፈልገኝ መጥቶ ነበር ብሎ መጠየቅ፣ ሳይቀደሙ ለመቅደም በጣም አስፈላጊ ነበር::

ከሚኖሩበት አካባቢም ጠፍቶ መሰወር፣ አገር ለቆም መሰደድ ያለ ነበር:: ወደ ውጪ አገር የሚያስኬድ ምክንያት ከተገኘማ ማንም ደስታውን አይችለውም ነበር:: ለምሳሌ በቁጥጥር ስር ከመዋሌ ከአንድ ወር በፊት ይህን መሰል እድል አጋጥሞኝ ገብርኤል አልፈቀደም መሰለኝ ከሸፎብኛል:: የአፍሪካ የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር ለማቋቋም የጋና የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር የኢትዮጵያን የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር ይጋብዛል:: በጊዜው እኔም የሙያ ማህበራችን ዋና ፀሐፊ ስለነበርኩ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተመርጬ ጋና ለመሄድ ስዘጋጅ የጊዜው ፈቃጅ የእርሻ ሚኒስቴር ሊያሳካልኝ ሳይችል ቀርቷል::

2. የከፍተኛና የደርግ ጽሕፈት ቤት ምርመራ

ታዲያ ሚያዝያ 19 ቀን 1970 ዓ.ም. ገብርኤል መሆኑን እንደተለመደው የኔብጤዎች በየመንገዱ እያስታወሱን ከደብረ ዘይት ወደ አዲስ አባባ ገሰገስን:: አዲስ አበባ ጉዳያችንን ከውነን እንደ ልማዳችን ወደ እርሻ ሚኒስቴርና ከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ጎራ ሳንል በችኮላ ወደ ደብረ ዘይት ጉዞ ቀጠልን:: ጓደኛዬም ለሥራ ቸኩሏል፣ እኔም ከጥቂት ቀናት በፊት

ከማስተምራቸው ተማሪዎቼ ጋር ሆኜ አንድ በሽተኛ ወይፈን ስመረምር ለአብድ ውሻ በሽታ ተጋልጬ ስለነበረ ውጤቱ ከተረጋገጠ በኋላ ራሴን ለመከላከል ክትባት እየወሰድኩ ነበር:: ይህ በሽታ በቀንድ ከብት ላይ ሲያጋጥም ከሌሎች መሰል በሽታዎች ለመለየት በጣም ስለሚያስቸግር (3) ተማሪዎቼን የታመመውን ወይፈን እንዳይነኩ በመከልከል ራሴ ስከታተል ቆይቸ ከሞተ በኋላ ለተጨማሪ ምርመራ ናሙና የኢትዮጵያ የጤና ተቋም (ፓስተር) ተልኮ ስለተረጋገጠ መከላከያ ክትባት ጀምሬ ያን ቀንም የክትባት መርፌ ለመውሰድ ቀጠሮ ነበረኝ::

የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበው ያጋጥማል ሆነና ነገሩ እኔና ጓደኛዬ አዲስ አበባ ለመንግሥት ሥራ ጉድ ጉድ ስንል የደርግ ጋሻ ጃግሬዎች ከአዲስ አበባ ደብረ ዘይት በጠዋት መጥተው ሊይዙኝ ያጡኛል:: አዲስ አበባም መሄዴ ሲነገራቸው ተመልሰው በየቦታው እያሰሱ ይፈልጉኛል:: እላይ እንደጠቀስኩት ወደ እርሻ ሚኒስቴር ብቅ ብንል የሰማ ሰው ካለ ሹክ የሚለኝ አይጠፋም ነበር:: ደብረ ዘይትም ብሆን የማምለጥ እድሌ የሰፋ ነበር:: አሁን ግን ያልጠረጠረ ተመነጠረ ሆነ:: ደብረ ዘይት ስንመለስ በመኪና በጎናቸው ያለፍናቸው የደርግ የሽብር አራማጆች ቃሊቲ ለፍተሻ ቆመን ተራ ስንጠብቅ በደረቴ ላይ መሣሪያ ደቅነው እጅ ወደላይ በማለት በቁጥጥር ስር አዋሉኝ:: ከዚያም እጄን በካቴና ጠፍረው ኪሴንና የሸሚዜን ኮሌታ ፈትሸው «መድሐኒት እንዳይውጥ በደንብ ጠብቀው» እየተባባሉ መኪናቸው ውስጥ አስገብተው በተለያዩ መሣሪያዎች አጅበው ወደ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት ወሰዱኝ::

እስር ቤቱ ስንደርስ ስምንት ሰዓት ይሆናል:: የደርግ የቀይ ሽብር አራማጆች ለመያዝ ያስቸገራቸውን «ፀረ አብዮተኛ» በቁጥጥር ስር በማዋላቸው በጣም ተደስተዋል:: «መኪና ሲነዳ እንዴት ይፈጥናል» ይባባላሉ፣ «ፍተሸው ቦታ ሌሎች መኪኖች ባይኖሩ ኖሮ ወደ ደብረ ዘይት በመብረር ያመልጠን ነበር» ይባባላሉ:: የማልሰማው ነገር የለም:: ነገሩ ያጋጣሚ ጉዳይ እንጅ ሲፈልጉኝ በቀላሉ ልያዝም ወይም ላመልጥም እችል ነበር::

በደርግ ሰዎች በቁጥጥር ስር ስውል የመጀመሪያ ጊዜዬ ቢሆንም የሚመጣውን ነገር በፀጋ ለመቀበል ስጠባበቅ እየረገጡና እየጎሸሙ አንድ ትንሽ የምርመራ ክፍል ውስጥ አስገቡኝ:: እንደገባሁ ሦስት ጠረንገሎ ጎረምሶች በጠረባ ጠልፈው መሬት ላይ ዘረሩኝ:: ከዚያም እግሬና እጄን ካሰሩ በኋላ ገልብጠው በጉማሬ፣ በጎማ ጉማጅና በኤልክትሪክ ገመድ ይገርፉኝ ጀመር:: እነኝህ ሦስት ገራፊዎችና መርማሪዎች ቀደም ብለው የኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ አባላት የነበሩ ናቸው:: አንዱ ቴዎድሮስ ይርጉ የሚባል «ኮማንደር» የነበረ ሲሆን ሁለቱ ደግሞ ሳሙኤል ይፍሩና ብንያም መንግሥቱ የሚባሉ «የስኳድ» አባላት ነበሩ:: የበሬ አራጆች በበሬ ጠለፋ፣ ቆዳ ገፈፋና የሥጋ ብልትም በማውጣት እንደሰለጠኑ ሁሉ እነኝህ ገራፊዎችም በጠረባ በመጣል፣ እግር ተወርች በማሰር እያገላበጡ በመግረፍ የተካኑ ነበሩ:: ላባቸው እስቲንቆረቆር ስውን እንደ ኳስ እያንን ሲገርፉ ለነሱ ጨዋታ እንጅ ሌላ ምንም አይመስላቸውም:: ታማኝነታቸውን የሚገልጹበት መንገድ ስለሆነ ምንም አይሰማቸውም:: ክፋቱ አንዳንድ ጊዜ በዚህ መልክ ከተጠቀሙባቸው በኋላ ከሌሎች ጋር ደባልቀው የቀይ ሽብር ያፋፍሙባቸዋል:: ይህን መሰል ድርጊት በዚህም ሆነ በሌሎች ከፍተኞች አጋጥሟል::

በዋነኛነት ቆሞ እኔን የሚያስገርፈውና መመሪያም የሚሰጠው ሲያሰኘው ም ራሱም በድብደባው የሚሳተፈው፣ የተያዝኩበት ቀበሌ ሊቀመንበርና

የከተማ ልማት የቀይ ሽብር ተወካይ ከሰተ አብራኒዮስን (ከሰተብርሃን ወልደፀዮን) በሚገባ አውቀዋለሁ:: በዚህ አጋጣሚ በእንዲህ ዓይነት ችግር ጊዜ የሚያውቁት ሰው እጅ መውደቅ መጥፎም ጥሩም ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ:: እንደዚያ እየተረባረቡብኝ ተክልዬ ሌላ ነገር ሳይከተል እንደሰለጠነ ሰው እንግባባና ስለ ኢሕአፓ የምታውቀውን፣ የመለመልከውን፣ የአመራር አባል መሆንክን፣ ያስገደልከውንና የሠራኸውን በሙሉ አንድም ሳይቀር እንድትነግረን ሲል ጮኸብኝ:: በዚህ ጊዜ ከሰተን በልጅነቱ ከማውቀው ባህሪው እንዳልተቀየረና በሱ እጅ መውደቁ መጥፎ እንደሆነ ጠረጠርኩ::

ይህ እንደ ሰለጠነ ሰው የሚለው አባባል እስከ አሁን ድረስ በስሜቴ ተተክሎ ይኖራል:: ለካ የመግረፊያ ክፍል (በነሱ አባባል የምርመራ ክፍል ይሉታል) አዘጋጅቶ በጠረንገሎ ጎረምሶች ገራፊዎች (በነሱ አባባል መርማሪዎች) ሰውን እንደ ኳስ እያንነ ለማያቋርጥ ሰዓታት መግረፍ፣ ሰዎችን ጠባብ ክፍል ውስጥ ማሰርና እየገደሉ በየሜዳው መጣል መሰልጠን ኖሯል::

ግርፋቱ እየቀጠለ ሄደ፣ መጯጯህ ሆነ:: ራሴን እስክስት ዘቅዝቀው በውሃ እያራሱ ምንጥር አድርገው ገረፉኝ:: ስቶቃው ሲበዛብኝ ከልጅነቴ ጀምሮ የማታውቀኝ መስለህ ከሰተ ታስገድለኛ እያልኩ ስማፀን በሊቀመንበሩ ላይ ጥቆማ መጣበት እያሉ ሁሉም ተሳለቁብኝ:: ከእንደዚህ መሰል ስቃይ ለመዳን አንድ ሰው ምን መናገር እንዳለበት ይጨንቀዋል፣ ሁሉም ነገር ይጠፋበታል:: ከድብደባና የሠራኸውን አውጣ የሚል መጯጯህ በስተቀር መደማመጥ የለም:: አንዱ ወገን ቀላል ነው ብሎ ዘንግቶ የሚተወውን ወይም እንደ ዋዛ የሚናገረውን ሌላው ያጋንነዋል:: እውነትም ሆነ ውሸት ቢነገርም ግርፋቱ አይቆምም:: ትንሽ ተንፈስ የሚባለው ላባቸው እስኪንጠባጠብ እየተፈራረቁ ገርፈው ሲደክማቸው ቁና ቁና እየተነፈሱ ገራፊዎቹ ውሃ ለመጠጣት ሲያርፉ ብቻ ነበር:: የአንዱ ስቃይ የሌላው ደስታ በሆነበት በዚያን ወቅት ውሃ ሲጠጡ በሰው ሰውነት ላይ እያንጠባጠቡ ለማራሻና ለተጨማሪ ግርፋት ያዘጋጁታል::

ግርፋቱና ስቃዩ እንደቀጠለ «ይህ ፀረ አብዮተኛ እንዲህ ፀጥ ያለው የአመራር አባል ቢሆን ነው እዚሁ እርምጃ እንውሰድበት» በማለት ከሰተ የጠመንጃ ቃታ ብጤ አንቋቋና ጆሮ ግንዴ ስር ተኮሰብኝ:: እኔም በጣም ብደነግጥም ራሴን ተቆጣጥሬ ሰውነት ስገዛ የውሸት ሽጉጥ መሆኑን ተረዳሁ:: «በዚህ የትምህርት ደረጃው የማዕከላዊ ኮሚቴ ይሆናል» እያሉ እየተፈራረቁ ይቀጠቅጡኛል፣ ይተኩሱብኛል፣ ይሰድቡኛል፣«ዛሬ ማታ መንገድ ላይ አውጥቶ ማጋደም» ነው ይሉኛል:: ይህ ሁሉ ሲሆን እኔን ለመያዝ ሲያድኑኝ ከነበሩት መካከል ብዙዎቹ ስንገፍ ቆመው ተመልክተዋል፣ ተሳትፈዋልም:: እኔን በቁጥጥር ስር ለማዋል ያስፈለገውን የሰው ኃይል ባላውቅም ከላይ የጠቀስኳቸው የቀበሌ ሊቀመንበርና ሦስቱ ገራፊዎች፣ የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር የነበረው የሃምሳ አለቃ ኃይለማርያም፣ ሌሎች ሦስት የአብዮት ጥበቃዎች ደምሴ ኃይሌ፣ ነጋ በረካ፣ አለሙ ደበሌና አንድ ምንነቷ የማይታወቅ የትራንስፖርትና መገናኛ ድርጅት ካድሬ/የአብዮት ጥበቃ መሆኗ የሚነገርላት ወ/ሮ ትንሣኤ የምትባል በምርመራው መሳተፋቸው ትዝ ይለኛል::

ድብደባው ቀጥሎ እኔም እየተዳከምኩ ስሄድ እኔ ኢሕአፓን የምደግፍ የድርጅቱ አባልና በገንዘብ የምረዳ መሆኔን ባምንላቸውም እየባሰባቸው ሄደ አንጅ አላስታገሳቸውም:: የቀይ ሽብር ግርፋት ከሆንኩው በላይ እንድትሆን የሚጠይቅና ብታምንም ባታምንም ግርፋቱ የማያቋርጥ ነበር:: እውነትም ስለ ድርጅቱ የማውቀውን ተናግሬአለሁ:: ከዚህ የሰፋ ተሳትፎ የለኝም፣

ያልሆንኩትን መሆን አልችልም። ስለ ድርጅቱ የማውቀውንና ከእኔም ጋር ግኑኝነት የነበራቸውን ተናግሬአለሁ። ነገር ግን ዱላና ድብድቡ እየበረታ ሄደ እንጅ አላቋረጠም። ከዚህ በኋላ አንድ የማላውቀውን ስው ጠርተው እሱ ነው የጠቆመህ ታውቀዋለህ ወይ ብለው እንደታሰርኩ ጠየቁኝ? እኔም አላውቀውም አልኩኝ፣ በእውነትም አይቸው አላውቅም። በኋላም እንደተረዳሁት የችግሬ መነሻ የሆነው ይኸው እኔን በቅጥ የማያውቀኝ ግለሰብ ባደረገው ጥቆማ መሆኑን ሌላ ጊዜ ልረዳ ቻልኩ። ካልታሠሩ የሥራ ባልደረቦቸ በሌላ ጊዜ እንደተረዳሁት በዚያን ቀን እኔን ለመያዝ የመጡት ሰዎች ደብረ ዘይት ከሚገኘ ት የእንሰሳት ሐኪሞች መካከል ሱዳን የተማረው ማን ነው በማለት ጥያቄ ማቅረባቸውን ስሰማ በጣም ገረመኝ።

ቀጥሎ አንድ ሌላ ግለሰብ ጠርተው እኔን ጠቁሞብሃል አትተዋወቁም ወይ ብለው ጠየቁት? አይኔን ግንባር ያድርገው አለዛሬም አላየሁት ብሎ ማለ። እኔም አላውቀውም የጠቆምኩትም ነገር የለም ስል አንተን ማን ጠየቀህ ብለው ዝለጥ አደረጉኝ። ከዚያ አዲስ የጠሩትን ስው እኔን እንዲመታኝ ቢጠይቁት አላደርገውም አለ። እንደ ቆመ እንደ ሕጻን ልጅ ሾጥ ሲያደረጉት በጥፊ ብጤ ሳይወድ ነካ አደረገኝ። እኔም ሊያስፈራሩት የጠሩት ሰው ይሆናል ብዬ ገመትኩ። ጊዜ ካለፈ በኋላ እንደተረዳሁት እንዲሁ የታሰረ አቶ ሥ. የሚባል የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ የሆነ የህግ ባለሙያ መሆኑን ተረዳሁ።

ከዚያም የረሱትን ያስታወሱ ይመስል አብሮህ የነበረውን የሥራ ባልደረባህን መልምለኸዋል ወይ? የኢሕአፓስ አባል ነው ወይ? የሚል አሰጥ አገባ ተጀመረ። እስከዚህ ድረስ ብዙ ተደብድቤ ብደክምም ራሴን እቆጣጠር ስለነበረ ከሙያ ባልደረብነት ውጪ ሌላ ምንም ግኑኝነት እንደሌለን ብገልጽም ሊያምኑኝ አልቻሉም። በዚህ ንትርክ የተነሳ ብዙ ተደበደብኩ። ሌሎች ጓደኞችህም የኢሕአፓ አባል የሆኑ ካሉ አውጣ በሚል ብዙ ውርጅብኝ ደረሰብኝ። ከዚያም እንደገና ወደራሴ ተመለሱና በፊት የጠቆመኝ ግለሰብ በደብረ ዘይት የድርጅቱ ተጠሪ ነው፣ ከጎንደርም በቅርብ ተዛውረህ መምጣትክን ያውቃል፣ ከኢሕአፓ ጋር ያገናኝህ ነበር። አንተ ምን ትላለህ በሚል ሙግት ድብደባው ቀጠለ። ምንም እንኳን ውጥረት ቢበዛም እነሱ ከሚቀባጥሩት ምን መልስ መስጠት እንደሚቻል መንገዱን ይመራል። በዚህ ጊዜ ጥሩ መንገድ ስላገኘሁ ከበላይ ሆኖ የሚያውቀኝ ከሆነ ራሱን ጠይቁት እኔ በአባልነት ገንዘብ ማዋጣቴን ነው የማውቀው ብልም ጎንደር ምን ሰርተሃል አውጣ እያሉ ብዙ አንገላቱኝ።

ጎንደርም ቢሆን እኔም ሆንኩ የማውቃቸው ጓደኞቸ ከዚህ የተለየ ምንም አልሰራንም፣ ምናልባት ለመንግሥት ሥራ በየቦታው ስንዘዋወር ለአንዳንድ የማናውቃቸው የኢሕአፓ አባላት የመገናኛ ድጋፍ ሰጥተን ይሆናል ስል እኔ ምንም ክብደት ባልሰጠሁት በዚህ አባባል ሰዎቹ እነማን እንደሆኑ ስማችውን እንድሰጥ በጣም ተደበደብኩ። እኔም የማላውቀውን መንገዳኛ ሰው ስም መስጠት አልችልም በሚል ህሊናዬን እስክስት ተገርፌ በደም ተጨማልቄ ሰውነቴ በሙሉ ቁስል ሆኖ መቆምና መቀመጥ በማያስችል ሁኔታ አንድ ሰደሬ የሚባል 2 ሜትር x 3 ሜትር የሚሆን ጠባባ ክፍል ውስጥ ከሌሎች ብዙ እስረኞች ጋር ተዳባዬ ነቃሁ። በዚህ ጠባብ ክፍል ውስጥ ከሃያ የማያንሱ እስረኞች ነበሩ። ከሌሎች እንዳረጋገጥኩት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ እየተሳደቡ አምጥተው እዚህ ክፍል ወርውረውኝ እንደሄዱ ልረዳ ቻልኩ።

ጠዋት እንደተነሳሁ ለማምለጥ ቀርቶ ለመንቀሳቀስ በማልችልበት ሁኔታ እያለሁ አጀ በካቴና ተጠፍሮ ወደ ደርግ ጽ/ቤት (ምኒልክ ቤተ መንግሥት) ተወሰድኩና ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የሚባል የደርግ የምርመራ ክፍል ሹምና የቀይ ሽብር ዋና ተዋናይ (4) ፊት ቀረብኩ፡፡ እንደገመትኩት እኔን የጠቆመኝ ግለሰብ ከተሸሸገበት ከጎንደር ክፍለ ሃገር ወሮታ ከሚባል ቦታ ምንም ችግር ሳይገጥምው እጁን ሰጥቶ የገባ ስለነበረ የተባለው ሹም ጉዳዩን እንዴት ያለ ክብደት እንደሰጠው ባላውቅም እኔን ለከፍተኛ ምርመራ ወደ ጽ/ቤቱ እንድቀርብ ፈልጓል፡፡ ምናልብት ወደ ደርግ ጽ/ቤት የተወሰድኩት አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድብኝ ሊሆንም ይችላል፡፡ በእኔ ላይ ጥቆማ ያካሄደው ግለሰብም እዚህ ከፍተኛ እስር ቤት በምን ምክንያት እንደመጣ እስከ አሁን ድረስ ግልጽ አልሆነልኝም፡፡ ምናልባት እሱ ተደብቆ እያለ ሌሎች እዚሁ ጠቁመውበት አልፈው እንደሆነም አላውቅም፡፡

ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ፊት ታስሬ እንደቀረብኩ ይነሱ የነበሩት ጥያቄዎችና መልሶች ከኔ ጋር ሳይሆን ይዘውኝ ከሄዱት ሰዎች ጋር ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ በጣም አጭር የሆነው አስፈሪው ሻለቃ ቀጭ ብድግ እያለና በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ ዙሪያውን እየተሽከረከረ ዶ/ር ከነ አክሊ ጋር ይገናኛል እያለ ቢጠይቅም ይዘውኝ የሄዱት ሰዎች የለም የሱ ጉዳይ ከማንም አይገናኝም የሚል መልስ ሆነበት፡፡ ሻለቃውም ምንም የሚያስደስተው መልስ ስላጣ የት ነው አገርህ ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ደብረ ብርሃን መሆኑን ስመልስ፣ አንተማ ነፍጠኛ ነህ አለኝ፡፡ መቸም አሽሙር እንዳይመስልብኝ ሰግቶ እንጅ የለም ጌታዬ የኔ ዘመዶች አካባቢያቸውን አለቀቁም የሚል መልስ ለመስጠት ቃቶኝ ነበር፡፡(5) የምርመራ ክፍል ሹሙ በጊዜው ከወታደራዊ ክፍል ነፍጠኞችን በብዛት ያሰባስብ የነበረው የወዝ ሊግ (6) አባል መሆኑን በሚገባ አውቃለሁ፡፡ ከዚያም እኔን ውጭ አስወጥተው በሌለሁበት በሚስጥር ምን እንደተነጋገሩ ባላውቅም ወደ መጣሁበት እስር ቤት ይዘውኝ ተመለሱ፡፡

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ከስተ አብራኒዮስን እንዳሁን ሳይሆን ልጆች ሆነን አውቀዋለሁ፡፡ ከትግርኛ ተናጋሪ ቤተሰብ ቢወለድም ያደገው ደብረብርሃን ከተማ ነበር፡፡ አባቱ በመንግሥት ሥራ ምክንያት እዚያው ስለኖረ ከስተ እንደ አካባቢው ተወላጅ ይቆጠራል፡፡ ልጆች ሆነን ከስተ ችኩልና ሁሉን እኔ ነኝ የማውቀው ባይ ነበር፡፡ መጀመሪያ ከደብረ ብርሃን ት/ቤት ጎንደር ሄዶ የጤና ተቆጣጣሪ (Sanitarian) ትምህርት እንደተከታተለ፣ ከዚያም ደብረዘይት ረዳት የእንስሳት ሕክምና ማሰልጠኛ ገብቶ ረዳት የእንስሳት ሐኪም መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ከሥራው ጋር በተያያዘ የአጭር ጊዜ የሥጋ ምርመራ ስልጠና ውጭ አገር ድረስ ተልኮ ተምሯል፡፡ አንዳንድ ሰዎችን ትምህርት፣ እድሜና የሥራ ልምድ ባህሪያቸውን እንደማይቀይር ከሱ መረዳት ይቻላል፡፡ ከስተ እጁ በደም የተጨማለቀ የደርግ ጨፍጫፊዎች ከሚባሉት ግለሰቦች አንዱ ነው፡፡

ከስተ በቅድሚያ ያመኢሶን አባል የነበረ ቢሆንም የዚህ ድርጅት አመራር አካላት አኩርፈው ደርግን ጥለው ሲከዱ አቋሙን ለመቀየርና ከሌሎች ጋር ለመለጠፍ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ እንደ ማንኛውም የመኢሶን አባል፣ አመራሩ ከፈረጠጠ በኋላ በሌላ ድርጅት ለመተካትና ነፍስ ለመዝራት በተሞከረው «በቀይ ፋና» ድርጅትም (7) ሳይታቀፍ አይቀርም፡፡ የከተማ ልማት ሠራተኛና የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ሊቀመንበር በመሆኑ የደርግ የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባል ለመሆን አመቺ ሁኔታ ተፈጠረለት፡፡ ይህም ኃላፊነት ከሻለቃ ብርሃኑና ሌሎች የወዝ ሊግ አባላት ጋር ለመተሳሰርና የሻለቃው የገዳይ ቡድን

(ስኳድ) ለመሆን አበቃው። የበላዩ የከፍተኛ 22 ሊቀመንበር የነበረውን የመቶ አለቃ ደስታ አውላቸውና ሌሎች የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባላትን ሥልጣን ጠቅልሎ በመያዝ አድራጊ ፈጣሪ ሆነ። የተማርኩ ነኝ ባይ ነው፣ ሁሉን አውቃለሁ ባይ ነው፣ የከፍተኛው ማዕከላዊ እስር ቤት በርሱ ቀበሌ ውስጥ ነበር፣ የሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ቀኝ እጅ ነበር፣ የቀይ ሽብር ኮሚቴው የከተማ ልማት ተወካይ ነበር። ታዲያ ከሰተ ይህንን ሁሉ ድርብርብ ሥልጣን አግኝቶ ማን ሊችለው፣ ማንስ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆኖ ሊተርፍ። ከሰተ ከግብረ አበሮቹ ጋር ብዙ ሰዎችን በቀይ ሽብር በመፍጀት (በመግደል) የሚጠየቅ የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ሊቀመንበር ነበር።

ሌላ እዚህ ላይ መጠቀስ ያለባት አንዲት ወዶ ገብ የነበረች ወ/ሮ ትንሣኤ በልሁ የምትባል የተሟላ ሥልጣን የነበራት ካድሬ/አብዮት ጥበቃ እንደነበረች ነው። ትንሣኤ የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባል አልነበረችም፣ ወይም በማሰርና በመፍታት ጉዳይ በቀበሌው ሥልጣን የላትም፣ ነገር ግን የፈለገችውን የትራንስፖርትና የመገናኛ ሳብ አደር እያሳሰረች የምታስገርፍ ነበረች። ከዚህም አልፎ ሌሎችም በቁጥጥር ስር ሲውሉ በማያገባት ገብታ አጋፋሪ ትሆን ነበር።

የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤትን ለመጀመሪያ ጊዜ ትንሽ ልብ ገዝቸ የተመለከትኩት ከደርግ ጽ/ቤት ስመለስ ነበር። ቀበሌው የሚገኘው የትንባሆ ሞኖፖል አካባቢ ሲሆን የቀበሌው ጽ/ቤት እንዳለ ወደ እስር ቤት ተቀይሯል። እስር ቤቱን ለመግለጽ ያክል አንድ የተወረሰ የዱሮ የጭቃ አሮጌ ቪላ ቤት ውስጥ ነበር። ቤቱ ውስጥ ሲገቡ አንድ ሳሎን፣ አንድ ለምርመራ (ለመግረፊያ) የሚጠቀሙበት ክፍል፣ ሌላ ለቢሮ የሚያገለግል ክፍልም የነበርው ይመስለኛል አርግጠኛ አይደለሁም፣ ከምርመራ ክፍሉ ጎን አንድ ሶደሬ የሚል ስያሜ የተሰጠው ለእስር ቤት የሚያገለግል ክፍልና አንድ ሽንት ቤት ነበረው። ግቢው ዙሪያውን የታጠረ ዋርድያም የሚቆምበት ቦታ የነበረው ነው። በተጨማሪም እየቆየሁ ስሄድ እንደተገነዘብኩት በጽ/ቤቱ በቀኝ በኩል ከቤት ሲወጣ አንድ የይድረስ የይድረስ ለእስረኛ ማቆያ የተሰራ ሰፊ አዳራሽ ነበር። አዳራሹን ተከትሎ ዙሪያውን ሲዞር ለሴቶች እስር ቤት የሚገለገሉባቸው የሰርቪስ ቤቶችና የጉርጓድ ሽንት ቤትም ይገኙ ነበር።

ደርግ ጽ/ቤት ደርሽ ሶደሬ እስክመለስ በግርፋት የተጎዳ እግሬን ነጠላ ጫማ አድርጌ ስለተንቀሳቀስኩበት የእግሬ ቆዳ ሙሽልቅ ብሎ ተገፎ ተነሳ፣ የውስጥ እግሬም ፈነዳ። ከመንፏቀቅ በስተቀር ቆሞ መሄድ ተሳነኝ። ክራንች በሌለበት ሁኔታ ከተጋደምኩበትም ሆነ ከተቀመጥኩበት ቦታ የምነሳው ግድግዳ በመታከክ ወይም በሰዎች ድጋፍ ነበር። ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስም በሰዎች ዕርዳታ ነበር። በዚህ ምክንያት ሕክምና በሌለበት ሁኔታ ቁስሉ ጠገግ ለማለትና እኔም ራሴን ችዬ ለመንቀሳቀስ ብዙ ጊዜ ፈጀብኝ። የእግሬ ቁስል ከሶደሬም አልፎ ክርቸሌም ከአስር ወር በኋላ ሳይድን ዘልቋል። አሁንም ይህንን ማስታወሻ ስጽፍ የግራ እግሬ ቁስል ጠባሳ መልኩ ሙሉ በሙሉ ሳይቀየር ከ22 ዓመት በኋላ ይታየኛል። አሁን ሳስበው ወደ «ጋንግሪን» ተለውጦ አለመሞቴ ወይም እግሬ አለመቆረጡ ይደንቀኛል።

በአፍላ የቀይ ሽብር ጊዜ እንደማንኛውም የአዲስ አበባ ከፍተኛና ሌሎች እስር ቤቶች በከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤትም በመቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ይገኙ ነበር። እነኝህ እስረኞች ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ልዩ ልዩ የእስር ክፍሎች ማለትም በአዳራሽ፣ በሶደሬና በሰርቪስ ቤቶች ይታሰሩ ነበር። ሶደሬ

የአዲስ ገቢ እስረኞች፣ ጉዳያቸው ጠበቅ ያለ እስረኞችና የግድያ እርምጃ የሚወሰድባቸው እስረኞች መቆያ ሆኖ እስከ መጨረሻው ዘልቋል:: በዚህ የተነሳ ሶደሬ በከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት ልዩ ስፍራ የሚሰጠው ስለሆነ በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፋት ይቀርባል:: ትንሹ የእስር ክፍል ትልቁን ችግር የተሸከመ እንደነበረ አንባቢ ይገነዘባል::

በሶደሬ እየቆየሁና እየተለማመድኩ ስመጣ ከዚህ በፊት በቀይ ሽብር በተገደሉት እስረኞችና በኛም ህይወት ላይ ወሳኝ የነበሩትን አንዳንድ የከፍተኛ 22 የአብዮታዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ (የቀይ ሽብር ኮሚቴ) ማንነት ማወቅ ቻልኩ:: ከእነሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙበት ነበር::

1. መ/አ ደስታ አውላቸው የከፍተኛ 22 ሊቀመንበር-- የኮሚቴው ሰብሳቢ
2. ከሰተ አብራኒዮስ (ከሰተብርሃን ወልደፅዮን) የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ሊቀመንበርና የከተማ ልማት ተወካይ--አባል
3. ነጋ በረካ የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ም/ሊቀመንበር-- አባል
4. የአምሳ አለቃ ኃይለማርያም የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር-- አባል
5. ወታደር ይገረም አየለ የፖሊስ ተወካይ--አባልና ፀሐፊ
6. ውቤ በቀለ የከፍተኛ 22 ካድሬ የህዝብ ድርጅት ተወካይ--አባል
7. አለሙ ደበሌ የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 አብዮት ጥበቃ-- አባል
8. ደምሴ ኃይሌ የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 አብዮት ጥበቃ-- አባል
9. ከልክሌ ማንደፍሮ የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ተመራጭ-- አባል

ሶደሬ ለነበርነው እስረኞች የከፍተኛው ሊቀመንበር ተሳትፎ ግልፅ አልነበረም:: አንድ ጊዜ ብቻ ሶደሬ በር ላይ ቆሞ እንደተመለከተን ትዝ ይለኛል:: የኮሚቴ አሰራራቸውን በውል ባናውቅም ሁሉንም እስረኞችን የሚመለከት ጉዳዮች የሚከታተሉት ከሰተና በሱም መመሪያ መሰረት በዙሪያው የነበሩት አብዮት ጠባቂዎችና ገራፊዎች ነበሩ:: ከከፍተኛው ሊቀመንበሩ ይልቅ ሌሎች የማናውቃቸው የሌሎች እስር ቤቶች የቀይ ሽብር አራማጆች ይጎበኙንና ያስፈራሩን ነበር:: አንዳንዶች ለምርመራ የመጡ ይመስል የአንተ ተሳትፎ ምንድን ነው? በምን ደረጃ ነው የሰራኸው? እያሉ የሚያስበረግጉን ጊዜ ነበር::

ምዕራፍ አራት

እስር በሶደሬና በሌሎች እስር ቤቶች

1. ሶደሬ ምንድን ነው?

ሶደሬ አንድ ጠባብ ክፍል ሲሆን አደገኛ የተባሉና አዲስ እስረኞች ይታጎሩበታል:: በአንድ በኩል የሚከፈት መስኮት ቢኖረውም ሁል ጊዜ እንደተዘጋ ነበር:: መግቢያ በሩ በውስጥ በኩል ወደ ሳሎኑ ነበር:: ምናልባት በጣም ተቸግሮና ተጠጋግቶ አስር ሰዎች ብቻ ማስተኛት ቢችልም እስረኛ ከበዛ ከ20-30 ሰዎች ይጠቀጠቁበታል:: በሶደሬም ሆነ በሌሎች እስር ቤቶች እስረኞች በጨቤ ስክ አስተኛኘት ተጣበው ይተኙ ነበር:: ይህም የቦታ ጥበትን ለመቋቋም በጣም ተጠጋግተውና ተሳስረው የአንዱ ጭንቅላት ወደሌላው እግር ተደርጎ መተኛት ነበር:: አሳሪዎቹ እስረኛው ቆሞ ቢያድርም ደንታ አልነበራቸውም:: ሶደሬ በጣም ከመጥበቡም ሌላ የእስረኞች የሽንት መከፊያ አነስተኛ የበርሜል ጉማጅ ቀንም ማታም እዚያው ክፍል ውስጥ ይቀመጣል:: በዚያን ጊዜ ሽታው ማስፈለጉ ነበር:: የምግብና የውሃ ዕቃዎችም ማታ ማታ ቢወጡም ቀን ቦታ ማጣበባቸው አልቀረም::

የሶደሬ እስረኛ አንዳንድ ጊዜ ቁጥሩ በየቀኑ ሊጨምርና ሊቀንስ ቢችልም ሚያዝያ 19 ቀን 1970 ዓ.ም. አካባቢ ከ20 የማያንሱ እስረኞች እንደነበሩ ይገመታል:: በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ እስረኞች ኢሕአፓዎችና ቢሮክራት ተብለው የተጋለጡ የአውራ ጎዳና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ነበሩ:: ቢሮክራት ተብለው ከታሰሩት የአውራ ጎዳና ባለሥልጣኖች መካከል የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ የሆኑ የፔርሶኔል ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ የህግ አማካሪና ሌሎችም ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ነበሩባቸው:: ከነሱ መካከል የጎጃም የአውራ ጎዳና መሥሪያ ቤት ባልደረባ የነበረው በኢሕአፓ ሊግ አባልነት የታሰረው ወጣት ወ. ገብረሂና(ወ.ገ.) በጣም ቀልደኛና ተግባቢ ስለነበረ አለቆቹን እነሱ «የከተማ ቢሮክራት» ሲሆኑ እኔ «የገጠር ቢሮክራት» ነኝ እያለ ያስቀን ነበር::

የሶደሬ እስረኞች እግራቸው ተጎድቶ ለመንቀሳቀስ የማይችሉትን ጓደኞቻቸው እየተሸከሙና እየደገፉ ሽንታቸውን እንዲሸኑና እንዲፀዳዱ በማድረግ የማይረሳ ውለታ ዋለውባቸዋል:: ደርግ ቢሮክራት ብሎ አዋርዶ ያሰራቸው የአውራ ጎዳና ባለሥልጣኖችም እንኳን ሳይቀሩ ምን ያክል ሰውን በማገዝ በኩል ከሌሎች እንደማይለዩ፣ አብረው እንደሚበሉና ከቤታቸው የሚላክላቸውን ለሌሎች እንደሚያካፍሉ ሶደሬ የነበሩት በሙሉ ያስታውሳሉ::

በመሰረቱ የሶደሬ እስረኛ ሽንቱን እክፍሉ ውስጥ ለሰው መከፊያ ውስጥ እንዳሻው መሽናት ቢችልም አዳሪ ለመውጣት የሚፈቀድለት በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ በአጃቢ ሆኖ ነበር:: የሚናፈሰውና ፀሐይ እንዲሞቅ የሚፈቀድለት በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን እሱውም ብዙ ጊዜ በተግባር አይውልም:: ከዚህ ሌላ ታፍኖ ሶደሬ መዋልና ሌሊትም ለግድያ ጠሩኝ አልጠሩኝ እያለ በስጋት መጠባበቅ የተለመደ ነበር:: አንዳንዱ እንቅልፍም ሳያሸልብ ያድራል:: የሶደሬ በር መዝጊያ ቀን ካልተከፈተ ሙቀቱ ከባድ ነበር::

በዚህ ጠባብ ክፍል ውስጥ 30 የሚሆኑ እስረኞች ታጉረው በሩ ተዘግቶባቸው በሚውሉበት ጊዜ በሚፈጠረው ሙቀት፣ ላባቸው ሲንቆረቆር

በላባቸው ስለሚታጠቡ ሶደሬ የሚል ስም አወጡለት። እንግዲህ በዚህ ዓይነት በቁማቸው ከተሰቃዩ በኋላ ነበረ እየተወሰዱ የሚገደሉት። ከደብደባው፣ ከዋይታውና ከሰቆቃው በተጨማሪ አየር ተነፍገው በሙቀት ተለብልበው በተለያየ ጊዜ ከ100 ሰዎች በላይ ከሶደሬ እየተወሰዱ የጥይት እራት ሆነዋል። የሶደሬ ችግር ሙቀት ብቻ አልነበረም። የእስረኛው ቁጥር ካነሰም ወለሉ ሲምንቶ ስለሆነ ሌሊት ለብርድ በሽታ ያጋልጣል። ምክንያቱም የሚለበሰው የቀበሌውን አስተዳደር አስፈቅዶ ከቤተ ዘመድ የሚገባው አንድ ጋቢ ብቻ ስለነበረ ነው። ጋቢው የሚፈቀደውም በአገራችን ባህል ሰው ሲሞት የከፈን ጨርቅ ስለሚያስፈልግ ከዚያ ጋር በተያያዘ ሳይሆን አይቀርም። በምዕራፍ ስድስት ስለ ጋቢና ዋራንት በሰፋት ይወሳል:

ታዲያ በዚህ ዓይነት የወጣው ስም መታወቂያው ሆነና አሳሪዎቹም ሳይቀሩ ይህን እስር ቤት ሶደሬ እያሉ ይጠሩት ጀመር። ለምሳሌ የአውራ ጎዳና ቢሮክራቶች በሚል ከታሰሩት መካከል አቶ ደ. ከምርመራ በኋላ «ወደ ሶደሬ ውሰዱት» ሲባል «አዎን ሽማግሌና በሽተኛ ስለሆንኩ ለኔም ሙቀቱ ይሻለኛል» እንዳለ ዛሬም በሕይወት ያሉ የሶደሬ እስረኞች እያስታወሱ ይስቃሉ።

የሶደሬ እስር ቤት ችግሮች ብዙ ነበሩ። ቀን ቀን ሙቀቱ፣ በሩ ከተዘጋ በትናንሽ ቀዳዳዎች አየር ለማግኘት መሻማቱ፣ የሲጋራ ጭስ እንዳያፍን አጫሾች በተራ እንዲያጤሱ ተራ ማውጣቱ፣ ከምርመራው ክፍል ብዙም ስለማይርቅ ሰዎች ሲገረፉ የሚያሰሙትን ጩኸትና ዋይታ ማዳመጡ፣ ንቃት እየተባለ የካድሬዎችን ልፍለፋና ስድብ መታዘቡ፣ ኢሕአፓን፣ ኢዴህንና ጀበሐን የሚራገም መፈክር ለማውረድ መገደዱ፣ የንቃት መዝሙር መዘመሩ፣ ከአሁን አሁን ሊገድሉኝ መጡ በሚል ሌሊት እንቅልፍ ማጣቱ፣ አንዳንድ እስረኞች በመንፈስ ጭንቀት የተነሳ ሲዘባርቁ መስማቱ በሙሉ የማይረሱ ትዝታዎች ናቸው። ሌሊት ቁስሌን ረገጥከኝ ብሎ እሪ ማለትም የተለመደ ነበር። እንዲያውም እዚያ ጠባብ ክፍል ውስጥ ተደራርቦ ሲተኛ በአንዳንዶቻችን ቁስል ላይ ችግር እንዳይፈጠር በጣም አዛኝ የሆኑ ግለሰቦች የተጎዳውን እግር ተሸክመው ይተኙ ነበር።

እስር ቤት ለብዙ ጊዜ ሲቆይ የውጭው ዜናም ይናፍቃል። ለመናገር ፍቃደኛ ከሆኑ አንዳንድ አዳዲስ እስረኞች ከሚገኘው መረጃ በስተቀር በመጀመሪያው የእስር ወቅት ምንም ወሬ መስማት አልተቻለም ነበር። እስረኛ ለመጠየቅ ከሚመጣ ቤተ ዘመድም ሆነ ሌላ ወዳጅ ጋርም በገጽ መገናኘት ስለተከለከለ ታሳሪው መኖሩን ወይም መሞቱን የውጪው ሰው የሚያረጋግጥበት መንገድ አልነበረውም። እንዲያውም አንዳንድ ጠያቂዎችን እንዴት ፀረ አብዮተኛ ትጠይቃላችሁ ብሎ ማስፈራራቱ፣ ሕክምና መከልከሉ፣ ከጠያቂ የሚላክ ምግብ ባይኖር ኖሮ ለረሃብ መጋለጡ፣ እነኝህ ሁሉ ተዘርዝረው የማያልቁ የሶደሬ ጉዶች ነበሩ። እነኝህ ሁሉ ሁኔታዎች እስሩ በጣም ጥብቅ በነበረበት ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች ናቸው።

በአፍላ ቀይ ሽብር ጊዜ ከደርግ ጽ/ቤትና ማዕከላዊ በስተቀር ማንኛ ቸውም የቀበሌም ሆነ የከፍተኛ እስር ቤቶች ሌሊት እያወጡ ሰው የሚገድሉት በራሳቸው ውሳኔ ነበር። በዚያን ጊዜ ሁሉም የራሱ የቀይ ሽብር ኮሚቴ ስለነበረው ሁሉም እንዳሻው እርምጃ ይወስድ ነበር። በዚህ ዓይነት በከተማም በገጠርም ያለምንም ቁጥጥር ግድያ ተፈጽሟል። ይህም ሊሆን የቻለው ደርግ የቀይ ሽብር ጦርነት በኢሕአፓ ላይ እንዲካሄድ ስለፈቀደ መሆኑን በምዕራፍ

ሁለት ተገልጿል:: ሌላው ቀርቶ ይህን ግድያ በመፍራት በጊዜው ጤፍና ሌሎች ቁሳቁሶች ከገጠር ወደ አዲስ አበባ ለሺያጭ ለማስገባት ሕዝቡ ፍራቻ ውጦት እንደነበር ይታወቃል:: (1) በኋላ ግን ከሚያዝያ 1970 ዓ.ም. ጀምሮ ግድያው በማዕከላዊ አሰራር በደርግ የምርመራ ክፍል ሹም በሻለቃ ብርሃኑ ከበደ አማካኝነት እንዲፈጸም ስለተወሰነ ትንሽ ጋብ ሊል ቻለ:: የእስረኛውም ስጋት ከበፊቱ ቀነሰ:: ይህ ውሳኔ ተላለፈ የሚባለው የአዲስ አባባ ቋሚ የደርግ አባል ተጠሪ የነበርው ኮለኔል ደበላ ዲንሳ የከፍተኛና ቀበሌ ቀይ ሽብር ገዳዮችን ቅጥ ያጣ ጭፍጨፋ ስለተቃወመ ነበር::(2) በአንፃሩ ዶ/ር አለሙ አበበ ይህንን በመቃወም ቀይ ሽብርን ለማዳከም ተጋኖ የሚነገር ነው ይል ነበር::

ቢሆንም እንደ ከሰተ አብራኺዮስ የሻለቃ ብርሃኑ የቀኝ እጅ የነበሩት የሚፈልጉትን እርምጃ ለማስወሰን ፍቃድ ማግኘት አይከብዳቸውም ነበር:: ለዚህ መሰል እርምጃ የተዘጋጀን የሶደሬ እስረኞች እንደነበርን አይጠረጠርም:: በሶደሬና በሌሎች ከፍተኞችም የነበሩ የሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ወዳጆች በብዙዎች ላይ እርምጃ ለማስወሰን አቆብቁበው እያለ የኮለኔል ደበላ ዲንሳን ተቃውሞ ተከትሎ በሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ላይ የተወሰደው እርምጃ ደጋፊዎቹን እንዴት አንገታቸውን ሊያስደፋቸው እንደቻለ ወደፊት ይገለጻል:: ከዚህ አጋጣሚ በኋላ አላይ የተዘረዘሩት የሶደሬ ችግሮችም ደረጃ በደረጃ እየተሻሻሉ መጡ:: ልዩ ልዩ ከፍተኞችም በቀይ ሽብር ስም ካሰሯቸው መካከል «የፖለቲካ ንቃት» እየሰጡ መፍታት ጀመሩ::

ብዙ ጊዜ አዲስ እስረኛ ሲመጣ ሶደሬን ሳይረግጥ ወደ ሌሎች እስር ክፍሎች አይዛወርም:: ለማስፈራራት ወይም ለሌላም ነገር አሳሪዎቻችን ሶደሬን ይጠቀሙበታል:: በዚህ የተነሳ የሶደሬ እስረኞች ቁጥር አንድ ጊዜ ይጨምራል ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ውጪ ወዳሉት ክፍሎች እስረኞች ሲዛወሩ ቀጥሩ ይቀንሳል:: አንዳንድ ጊዜ በአዳራሽ ውስጥ ካሉት እስረኞችም መካከል እስራቸውን ለማጥበቅና ለማስፈራራት ሲያስፈልግ ወደ ሶደሬ የሚመለሱ አይጠፉም:: እድሉ በጣም ጠባብ ነው እንጅ በአዳራሽ የሚገኙ እስረኞችም አንዳንድ ጊዜ ሰው ሳያያቸው ሶደሬ መጥተው ያሉትን እስረኞች ጎብኝተው ይመለሱ ነበር::

ከሚያዝያ 1970 ዓ.ም በኋላ በሌሎች ከፍተኞች የነበሩ እስረኞች መፈታት ሲጀምሩ አዳራሽ ከታሰሩት መካከል ደረጃ በደረጃ ከፍተኛ እየተወሰዱ «የፖለቲካ ንቃት እየተሰጣቸው» መለቀቅ ጀመሩ:: በሰርቪስ ቤትም ከታሰሩት ሴቶች መካከል በየጊዜው ብዙዎች ተለቀቁ:: ከሶደሬ ግን ከአውራ ጎዳና ሠራተኞችና ከጥቂቶች በስተቀር ሌሎች የመፈታት እድል አላጋጠማቸውም:: በጊዜው የቆዩ እስረኞች መፈታት ብቻ ሳይሆን አዳዲስ እስረኞችም ይጨመሩ ነበር:: ይህን መሰል ማሰርና መፍታት በሚካሄድበት ወቅት በከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 የታሰሩትን የተለያዩ እስረኞች መዘርዘር ቢያስቸግርም ከሞላ ጎደል ሶደሬ በተባለው የእስር ክፍልና በሌሎችም ክፍሎች ለብዙ ጊዜ የቆዩት እስረኞች እዚህ ላይ ይጠቀሳሉ::

1.1 የኢሕአፓ ደጋፊ ስረኞች በሶደሬ

ሰ. ኃይሉ(ሰ.ኃ.) የኢሕአፓ አባል ሲሆን እጁን ሰጥቶ በዚህ ከፍተኛ ቀደም ብሎ ታሰሯል:: ከሰዎች ጋር መደባለቅ ብዙም ስለማይወድ ከጓደኞቹ ጋር ያለው ግኑኝነት ሻካራ ነበር:: በዚህ የተነሳ ብዙ ጊዜ ጋቢውን ተከናንበ

እራሱን በማግለል መተኛት ያዘወትር ነበር። በጋቢው ውስጥ ተጠቅልሎ ከየት እንዳገኛቸው የማይታወቅ የፖለቲካ ጽሑፎችን ለብቻው ሲያነብ አንዳንዶች ያፌዙበታል፣ ሌሎች ደግሞ ይታዘቡታል። እስሩ እየገፋ ሲሄድና ሁኔታዎች ሲቀያየሩ እየሟሸሸ መጣ አንጅ ሰ.ኃ. አንድ የተለየ ግኑኙነት ከአሳሪዎቻችን ጋር እንደፈጠረ የሚያሳይ ምልክት ነበር። ከርሱ በስተቀር ሌሎች የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች ብዙም የባህርይ ልዩነት አልነበራቸውም። ተ. በቀለ(ተ.በ) የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊም እዚሁ መታሰሩ ቀደም ብሎ ስለተገለፀ መታወስ አለበት።

ውብሸት አለማየሁ የኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ ቡድን አባል ሲሆን ቀደም ብሎ ታስሮ ከቆየበት ከአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ወደ ቀበሌው እስር ቤት የተዛወረ ነበር። ሌላው ደግሞ አለማየሁ ለማ የሚባለው ከመታሰሩ በፊት የዚሁ ቀበሌ ነዋሪና በቀበሌው ጽ/ቤትም የሚሰራ ነበር። አለማየሁ ለማ በኢሕአፓ ሊግ ደጋፊነት ተጋልጦ የታሰረ በመሆኑና በፊትም እዚሁ ቀበሌ ይሰራ ስለነበረ የቀበሌ ባለሥልጣኖች ሲያዩት አይናቸው ደም ይለብሳል። አለማየሁ ለማን የሚጠሉበት ዋናው ሚስጥር እሱና ለጊዜው ያልተያዘው በኋላ ግን ከርቸሌ ከተዛወርን በኋላ እጁን ሰጥቶ ታስሮ የመጣው አብይ ኃይሉ የሚባለው ጓደኛው በዚህ ቀበሌ ነዋሪ የነበረ ግለሰብ አንዲገደል ጥናት አቅርባችኋል በሚል ስለተወነጀሉ ነበር።

ሰውዬው በኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ እርምጃ ከተወሰደባቸው ግለሰቦች አንዱ እንደነበረ ይነገራል። ኢሕአፓ በሰውየው ላይ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያመቸው የግለሰቡን የዕለት ተለት እንቅስቃሴ መከታተልና መረጃዎችን ማሰባሰብ ስለነበረበት እነ አለማየሁ በሰፈር ነዋሪነታቸው ተባብረዋል በሚል ተከሰዋል። በመሰረቱ አለማየሁና ጓደኛው ማንም የሰፈር ሰው ቢጠየቅ ሊናገር የሚችለውን የዚህን ሰውዬ የግል ሕይወት ሲጠየቁ ተናገሩ እንጅ ከዚህ ሌላ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ለዚህ ተገደለ ለተባለው ሰውዬ በቀል አለማየሁ፣ ውብሸትና ሌሎች ዝቅ ብሎ የሚጠቀሱት የቀይ ሽብር እርምጃ ሲወሰድባቸው ተሸሽጎ ከርሞ ከርቸሌ ከተዛወርን በኋላ እጁን ሰጥቶ የታሰረው አብይ ኃይሉ ብቻ ሊድን ችሏል። በዚህ መልክ ጓደኞቹ ሲሞቱ የተረፈው አብይ ኃይሉ በ1991 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

ደርግ የአንድን «ታጋይ ሞት በሺህ እንበቀላለን» ባለው መሰረት በዚህ ሰውዬ ጦስ የተነሳ ከላይ ሆነው ውሳኔ የሰጡት፣ ድርጊቱን ፈጸሙት የተባሉት፣ ሽፋን የሰጡትና በጥናት ስበብ ተራ መረጃ አቀብላችኋል ተብለው የተከሰሱት ሳይቀሩ በጅምላ ተገድለዋል። እንግዲህ ቀይ ሽብር ይህን መሰል በቀል ያዘለ የጭፍጨፋ እርምጃ ነበር። ምናልባትም ሰውየው የተገደለበትን ጠመንጃና ጥይትም ያቀበሉ ሁሉ ተገድለው ሊሆን ይችላል። በደርግ ጭፍን አሰራር ሰውዬው በተገደለበት አካባቢ የነበሩት አላፊ አግዳሚም በተባባሪነት አለመገደላቸው ሰዎቹን መለየት ስላቃተው ሳይሆን አይቀርም።

ከእነኝህ የኢሕአፓ እስረኞች በተጨማሪ ከዚህ በፊት የተጠቀሰው ከጎጃም የአውራ ጎዳና መሥሪያ ቤት የታሰረው የኢሕአፓ ሊግ አባል ወ. ገብረሂዎት(ወ.ገ.)፣ ከከተማ ልማት የታሰሩት ባልና ሚስት ብ. እና ጽ. ደባስ(ጽ.ደ.) የሚጠቀሱ ነበሩ። ጽ.ደ. ጠንካራ የኢሕአፓ አባል ስትሆን ብ. ብዙ ተሳትፎም አልነበረውም። እነኝህን የመሥሪያ ቤቱ ባልደረባ የሆኑ ባልና ሚስት ከሰተ ከፖለቲካ ልዩነት ባሻገር እንደ ባላንጣ ይመለከታቸው ነበር። ከሰተ በተለይ ብን. የሚጠላበት የራሱ የሆነ ልዩ ምክንያት እንደነበረው ከባልና ሚስቱ ልንረዳ ቻልን። ብ. እና ከሰተ በከተማ ልማት መሥሪያ ቤት በሰጡት አገልግሎት

ለአንድ የስልጣን አርከን አሸናፊ ለመሆን ተወዳድረው ስለነበረ በመካከላቸው ስምምነት አልነበረም:: በዚህ የተነሳ ከሰተ በኢሕአፓ አባልነት አሳቦ በብ. ላይ የነበረውን የቆዬ ቂም በቀል ይወጣበት ነበር::

ሶደሬ ከነበሩት የኢሕአፓ እስረኞች ውጪ አብዛኞቹ አዳራሽ የነበሩት ስለተፈቱ ስለነሱ ብዙም ማለት አይቻልም:: የሴት እስረኞችም ጉዳይ እንደዚሁ ነው:: ምናልባት አዳዲስ እስረኞች እስኪመጡ ድረስ ሌሎች ተፈተው ጽ.ደ. ብቻዋን መቅረቷን መጥቀሱ በቂ ነው:: እንዲያውም ብዙ ሲቆጭ የነበረው የጽ.ደ. ባለቤትም ከተፈታ በኋላ እሷ ብቻዋን ቀርታለች:: በመጨረሻ ሊጠቀስ የሚገባው የአዳራሽ እስረኞች በሙሉ ከተፈቱ በኋላ ከነሱ ተነጥሎ ሶደሬ ከሌሎቻችን ጋር የተደባለቀው ከአንበሳ መሥሪያ ቤት የታሰረው የኢሕአፓ ደጋፊ ላብአደር ተ. ነው:: ይህ ግለሰብ እስሩ ሊጠነክርበት የቻለው ወዳጁ የነበረችው ትንሣኤ የተባለችው የመገናኛ ካድሬ ስለምትጠላው መሆኑ ይታወቃል:: ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በሶዴሬ የቆዩት የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች ሲሆኑ ሌሎች በየጊዜው እየተደባለቁቸው የእስረኛውን ቁጥር ከፍ አድርገውታል::

ደርግ በቀይ ሽብር ዘመቻ በቀበሌና በከፍተኛ የኢሕአፓን መዋቅር ካፈራረሰ በኋላ በሌላም ቦታ ያሉ ተሸሽገው እንዳይቀሩ ማሳደዱ ይታወቃል:: በገጠር ሁሉ ተደብቀው የነበሩትን በገበሬ ማህበራት አማካኝነት እያሳደደ በቁጥጥር ስር አውሏል:: በዚህ የተነሳ ቀደም ብለው በአፈሳም ሆነ በሰላማዊ ሰልፍ ወይም በተለያዩ ጥርጣሬዎች በአዲስ አበባ ወህኒ ቤትና በሌሎችም እስር ቤቶች ታስረው የነበሩትን የድርጅቱን አባላት ለማጋለጥና መንጥሮ ለማውጣት በየቀበሌው የታሰሩት ጓደኞቻቸውን እንዲጠቁሙ ግፊት አድርጓል:: በወህኒ ቤት የሚገኙ እስረኞች ወደ ቀበሌዎችና ከፍተኛዎች ተወስደው ምርመራቸው በድጋሚ እንዲጣራ የአብዮት ጥበቃ ሊቀመናብርት በስብሰባ ወስነው ነበር::

ከዚህ ያመለጡትን በማታለልና በማግባባት «የኢሕአፓ ድርጅት ፈርሷል»፣ «ቀይ ሽብርም ቆሟል»፣ «እራሳችሁን አያጋለጣችሁ ተፈቱ» በማለት ይገፋፋል:: በዚህ ስብከት የተነሳ አንዳንዶች ሲታለሉ ሌሎች ጥርሳቸውን ነክሰው ተደብቀው ለማሳለፍ ችለዋል:: በከርቸሌ እስር ቤትም ቢሆን ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የመለመላቸው አንዳንድ ግለሰቦች የኢሕአፓ እስረኞችን «አጋልጥ፣ ተጋለጥ» እያሉ ያተራምሱት ነበር:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በ1970 ዓ.ም. በሚያዝያና ግንቦት በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ቀንደኛ አተራማሾች የነበሩት «ግንቦቴዎች» በሚል መጠሪያ የሚታወቁት የሚረሱ አይደለም::

ያን ጊዜ የከርቸሌ እስረኛ ስሙ እንኳን እንዳይታወቅበት የሚደበቅበት ጊዜ ነበር:: ከእነዚህ «ግንቦቴዎች» መካከል አንዳንዶቹ በእስር ላይ የነበሩትን ጓደኞቻቸውን ከማተራመስ አልፈው በመገናኛ ብዙሐን መግለጫ በመስጠት የኢሕአፓን ድርጊት ለማጉደፍ ብዙ ሞክረዋል:: የኢሕአፓ ድርጅት ፀረ ሕዝብ በሆኑ የደርግ ደጋፊዎች ላይ የግድያ እርምጃ ሲያካሂድ የነበረው በገንዘብ በተገዙ ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች አማካኝነት እንደነበረ በማስመሰል በቴሌቪዥን የተሳሳተ መግለጫ ሰጥተዋል:: የከፍተኛ ቀይ ሽብር አራማጆችም በማዕከላዊ፣ በከርቸሌና በሌላም ቦታ ታስረው የነበሩ የየከፍተኞቻቸውን ወጣቶች እያሳደዱ ይወስዱ ነበር::

ታዲያ በዚህ መካከል ነበር ውብሸት ከከርቸሌ ወደ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት የመጣው:: እንደመጣም የኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ አባል የነበሩትን መርማሪዎች ያገኛል:: ለነሱም የሚያውቀውን ይናገራል:: ከአንደኛ

ው መርማሪም ጋር አንድ የጥቃት መከላከያ ቡድን («ስኳድ») ውስጥ አብረው ይሰሩ ስለነበረ ይተዋወቃሉ። ስለዚህ የበላያቸው የነበረው «ኮማንደር» አብሮት ከርቸሌ በእስር ላይ እንዳለ ይናገራል። ከፍ ብሎ በዚህ ቀበሌ በኢሕአፓ አርምጃ የተወሰደበት ግለሰብም የተገደለው ይኸው «ኮማንደር» በሚመራው «ስኳድ» መሆኑን ተጨማሪ ማረጋገጫ ይሰጣል። በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው የዚህ ጥቆማና ማጋለጥ ሁኔታ ከሌሎች ድርጊቶች ጋር የተወሳሰበ ስለሆነ ፀሐፊው ሳይወድ በግድ ማን ማንን እንደጠቆመና ማን ጥናት እንዳቀረበ ለመግለፅ ተገዷል።

ሚያዝያ መጨረሻ 1970 ዓ.ም. አካባቢ ደሳለኝ በረድ ሶደሬ ይመጣል። ደሳለኝ በረድ እንደ ውብሸት ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ ወህኒ ቤትና በማዕከላዊ ለአንድ ዓመት ጊዜ በእስር ላይ ያሳለፈ ነበር። የስር ጊዜውን ጨርሶ ሊፈታ ትንሽ ሲቀረው ከዚህ በፊት የሚያውቀው ቀደም ብሎ ወደ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 በመምጣቱ ሊያስጠራው ችሏል።

የደርግ ዘመን የፖለቲካ እስረኛ ሆኖ የሚያጋጥመውን የግርፋት ውርጅብኝና ስቃይ ለመቋቋም ልዩ የመንፈስ ጽናት ይጠይቃል። ደሳለኝና ጓደኛው በ1969 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ ሲያጅቡ በቁጥጥር ስር ይውሉና ማዕከላዊ ይታሰራሉ። በዚህ የሰላማዊ ሰልፍ ጊዜ ብዙ የአዲስ አበባ ወጣቶች እንደተገደሉና እንደታሰሩ ይታወቃል። ደሳለኝና ጓደኛው ማዕከለዊ ታስረው በምርመራ ላይ እያሉ ብዙውን ስቆቃ ጓደኛው ቢቋቋምም፣ ሲጨንቀው የበላዩ ሁሉንም ነገር የሚያውቀው ደሳለኝ መሆኑን ይናገራል። ደሳለኝም ጭራሽ እንደማይተዋወቁ ይክዳል። በዚህ የተነሳ ደሳለኝ ማዕከላዊ ፍዳውን ያያል። ደግነቱ ደሳለኝን ጓደኛው የሚያውቀው በትግል ስሙ (ኮድ ስም) ስለነበረ የማዕከላዊ መርማሪዎች ቢረባረቡበትም ጭራሽ አላውቀውም በሚል ይክዳል። የደሳለኝ መጠሪያ ስምና ጓደኛው የተናገረው ሰው ስም ስላልገጠመ የማዕከላዊ መርማሪዎች ምንም ማድረግ አልቻሉም ነበር። እዚህ ላይ የድርጅቱ የጥቃት መከላከያ መዋቅር አሰራርም ደሳለኝን እንዳዳነው መገንዘብ ይገባል። ደሳለኝ የስኳዱ መሪ (ኮማንደር) በነበረበት ጊዜ የመጣው ከሌላ ክፍተኛ ሲሆን በስሩ የሚገኙት የከፍተኛ 22 ነዋሪ ነበሩ። ለድርጅቱ ሥራ በኮድ ቢገናኙም በሌላ ነገር ሁሉም አይተዋወቁም። ማዕከላዊም የደሳለኝንና ጓደኛውን ነገር መፍታት ስላልቻለ ሁለቱንም ለአንድ ዓመት አዲስ አበባ ወህኒ ቤት እንዲቆዩ ይልካቸዋል። እንግዲህ ጓደኛው ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 መጥቶ ነገሩን ሁሉ አበለሻሸው።

ደሳለኝ በኢሕአፓ የወጣት ሊግ ውስጥ መሳተፍ ሲጀምር የአሥራ አንደኛ ክፍል የምኒልክ ትምህት ቤት ተማሪ ቢሆንም የነበረው የፖለቲካ ንቃትና ያካበተው የትግል ልምድ ቀላል አልነበረም። ማዕከላዊ እንደ ኳስ እያጓኑ ሲደበድቡት፣ «ጉራጌ ብሎ ፖለቲከኛ እያሉ ሲያሽሟጥጡት» ማንነቱን ጨርሶ አላወቁትም ነበር። ደሳለኝ በጥቃት መከላከያ ሥራ የፈጸማቸውን ድርጊቶች በሌላ ክፍተኛ የነበሩ ጓደኞቹ ሊጋሩት ቢችሉም እንኳን ከርቸሌ እያለ ማንነቱንና አሁን የት እንዳለ ማወቅ አይችሉም ነበር። ነገር ግን ከርቸሌ አብሮት የነበረው ጓደኛው በሠራው ትንሽ የግምት ስህተት ደሳለኝንም እራሱንም ለከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 አጋልጦ ሰጠ። ደሳለኝ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት እንደመጣ እንደ በፊቱ እራሱን መደበቅ አልቻለም። ከመርማሪዎችም መካከል የሚያውቁት አሉ፣ ጓደኛውም ከርቸሌና ማዕከላዊ አብሮት ቆይቷል። ከሌላ በታም ሊመጣበት የሚችለውን ጥቆማ መሸፈን አይችልም። እንግዲህ

ተያይዘን አናልቃለን ብሎ አረፈ:: ሊገርፉት ሲሞክሩም ሳቀባቸው:: ከርቸሌ አያለ የሚያደርገው ነጠላ የጎማ ጫማ (በረባሶ) ስለነበረ ሶደሬ ሲመጣ የእግሩ ንቃቃት የአገር ቤት ገበሬ ይመስል ነበር:: ስለዚህ ዱላና ግርፋቱ እንኳን ምንም አልተሰማውም:: ነገር ግን ከሚያውቃቸው ጋር መፋጠጥ አልሆነለትም:: ከመርማሪም ከመስካሪም ጋር መፋጠጥ አላዋጣውም::

ደሳለኝ ሶደሬ ከመጣ በኋላ ለብዙ ጊዜ በካቴና ታስሮ አሳልፏል:: ሲበላም ሲተኛም አይወልቅለትም ነበር:: ሌላው ቀርቶ የሶደሬ የእስር ሁኔታ ከላላና ብዙ እስረኞች ከተፈቱም በኋላ እንኳን የቀሩት በግቢው ውስጥ መዝናናት ሲፈቀድላቸው ደሳለኝ ከሶደሬ ውጪ አይወጣም ነበር:: አንዳንዶቻችንም የእግር ቁስላችን ያልዳነው ብዙ ጊዜ ሶደሬ ተቀምጠን ስለምንውል ሁኔታው ከደሳለኝ ጋር ሊያቀራርበን ቻለ:: ደሳለኝ ብዙ መናገር ባይወድም ከላይ የሰፈረውን የትግልና የእስር ሕይወቱን ሊያካፍለን ቻለ:: ደሳለኝ የጓደኛው ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 መምጣት የሁለቱንም ሕይወት አደጋ ላይ እንደሚጥለው ተናግሯል:: ያለውም አልቀረም ሁለቱም በቀይ ሽብር ከነአለማየሁ ጋር መገደላቸውን ወደፊት እንደርስበታለን::

ከደሳለኝ ቀጥሎ ሶደሬ ታስሮ የመጣው መ. ነበር:: መ. የድሬደዋ ባቡር መንገድ ሠረተኛ ቢሆንም የአዲስ አበባ ልጅ ነው:: በኢሕአፓንነት ተጠርጥሮ ድሬደዋ ብዙ ተሰቃይቷል:: ከዚያም ከአዲስ አበባ የመጣ ነው በሚል ወደ ዋና ከተማው ስለተላከ ትንሣኤ አንከብክባ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት ታመጣዋለች:: እዚህም ሲደርስ ከግርፋትና ከምርመራ አላመለጠም:: አንዳንድ ሰው አንድ ጊዜ ለችግር ከተጋለጠ እየለመደው ስለሚመጣ እየተረጋጋ ይሄዳል:: ሌላው ደግሞ ለተደጋጋሚ ችግር ሲጋለጥ መንፈሱ እየደከመ ይመጣል:: ራሱንም መቆጣጠር ያቅተዋል:: መ. ለተደጋጋሚ መዋከብና ምርመራ በመጋለጡ መረጋጋት አቅቶት የመረበሽና የመንፈስ ጭንቀት ደርሶበታል:: ራሱን መቆጣጠር ባይሳነውም፣ ከሰው ጋር መናገር አይወድም፣ ዝምታን ያበዛል፣ ተደብሮ ብቻውን መቀመጥን ይወዳል:: ከሌሎች ጋር እምነት ጥሎባቸው ተረጋግቶ ለመደባለቅ ጊዜ ፈጅቶበታል:: ከድሬደዋ እንደመምጣቱ ከዘመዶቹ ተቀያሪ ልብስና ስንቅ ለማግኘት ጊዜ ፈጅቶበታል:: እየቆየ ሲሄድ እነማንን መቅረብ እንዳለበት እየገባው ቢመጣም የማይመስሉትን መጥላቱ እየጨመረ ሄደ:: ይህንን ጥላቻውን ከርቸሌ እንኳን ከመጣን በኋላ በሰ.ኃ. ላይ በአደባባይ ያንፀባርቅ ነበር::

ከዚህ በኋላ በኢሕአፓ ደጋፊነት እየታሰሩ የመጡትን ቀደም ተከተል በውል ማስታወስ ባይቻልም ጉራጌ አገር ተደብቆ ከርሞ እጁን የሰጠው ኢንጅነር ሱ. መሐመድ(ሰ.መ.)፣ ጁሩ አገሩ ተሸሽጎ ከርሞ እጁን የሰጠው የኢላማ አባል የሆነው ተ. ታደሰ(ተ.ታ.) እና የሊግ አባል የነበረችው ተማሪ ዘ. ወርቁ(ዘ.ወ) የሚጠቀሱ ናቸው:: ሱ.መ. በጣም ብልጣብልጥ ባህርይ ያለው ከሰዎች ጋር በቀላሉ የሚደባለቅ ግለሰብ ነው:: የሱ በጉራጌ አገር ተደብቆ ማሳለፍ የራሱን ሕይወት ብቻ ለማዳን የወሰደው እርምጃ ይሁን ወይም ከሌላ ከድርጅቱ ሥራ ጋር ይገናኝ የሚያውቀው እሱ ብቻ ነበር:: ተ.ታ. የደርግን የሽብር እርምጃ ለማምለጥ ተደብቆ ከነበረበት አካባቢ እጁን ሰጥቶ ታስሮ እንደመጣ ልክ ያገሩን የጁሩ ገበሬ ይመስል ነበር:: ነዋሪነቱ በዚሁ ቀበሌ ስለነበረ ራሱን ለመለወጥና ተመልሶ ከተሜ ለመምሰል ጊዜ አልፈጀበትም:: ቢሆንም ለብዙ ጊዜ «ፔዛንት» (Peasant) የሚል የቅጽል ስም ሰጥተነው መጠሪያው ሆኖ ነበር:: ተ.ታ. ፖላንድ ድረስ ተልኮ የቴክንክ ትምህርት የተማረና የውጭውንም የተማሪ

ፖለቲካ ቀመስ የነበረ የፋብሪካ ሠራተኛ ነበር። ዘ.ወ. የዚሁ ከፍተኛ ነዋሪ
ስትሆን ከመታሰሯ በፊት ከደርግ የሽብር እርምጃ ለማምለጥ ከቦታ ቦታ
እየተዘዋወረች እራሷን እየቀያየረች ተቀምጣለች። ሌላው ቀርቶ ። በቤት
ሠራተኝነት እንኳን ራሷን ለመደበቅ አገልግላለች። ይህ የሚያመለክተው
የደርግን አስከፊ የጭፍጨፋ ዘመን ለማሳለፍና ራስን ለመደበቅ የሚደረገው
ሙከራ ቀላል እንዳልነበረ ነው። እንደ ማንኛውም ወጣት የዘ.ወ. ባፍላው የቀይ
ሽብር ጊዜ ከአካባቢው መሰወር ለሕይወቷ መዳን አስተዋጽኦ አድርጓል።
በመጨረሻ ታስሮ የመጣው የሊግ አባል የሆነው ነ. ስዩም(ነ.ስ.) ነበር።
ነ.ስ. የደንቡን ግርፋት ካሚላ በኋላ ሶደሬ የገባው ካልሲውን ባፉ እንደጎረሰ
ነበር። መርማሪዎቹ የጥጋባቸው ብዛት ሲደበድቡት ካልሲውን በአፉ
አጉርሰውት ስለነበረ ሶደሬም ሲያስገቡት ጭራሽ እንዳያወጣ በማስጠንቀቅ
ጥለውት ሄዱ። የሶደሬ እስረኞች እንዲረጋጋና ካልሲውን ካፉ እንዲያወጣ
ቢያግባቡትም እያጉመተመተ መርማሪዎቹ የመጡ እንደሆነ ታስገድሉኛላችሁ
በማለት አሻፈረኝ አለ። ነገሩ እስረኛውን ስላሳዘነው «አይዞህ አሁን አውጣውና
የሰው ኮቴ ድምፅ ስንሰማ መልሰህ ትጎርሰዋለህ፣ እነሱ ሌላ የሚገርፉት
ከሌላቸው ማታ አይመጡም» በማለት በማግባባት ሲረጋጋ ካፉ አውጥቶ
ሊጥለው ቻለ። እንግዲህ ሶደሬ ማለት ይህን መሰል የእስረኛው ስቃይና ሰቆቃ
ለአሳሪዎቹና ለገራፊዎቹ ደስታና መዝናኛ የሚፈጥርበት ቦታ ነበር።
በሶደሬ ስለተጠቀሱት የኢሕአፓ እስረኞች ማለት የሚቻለውን
በለሆሳስ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በዚህ ጽሑፍ ምስክርነት መስጠት
የሚቻለው በጊዜው የሰሙትንና የተገነዘቡትን እንጅ ከዚያ አልፎ ያለውን
ማስቀመጥ ያስቸግራል። በምርመራ ጊዜ በውጥረት የተሰጠ ቃል ሊገንም፣
ሊያጥርም ወይም ሙሉ በሙሉ ውሸት ሊሆን ይችላል። ለዚህም ቢሆን
እነኝህን ሰነዶች ካልጠፉም በአሁን ጊዜ ለማግኘት ያስቸግራል። በአንዳንድ
ጉዳዮች ላይ በጊዜው በሶደሬ የነበሩትንና አሁን በሕይወት ያሉትን ለማነጋገርና
ለማመሳከር ሙከራ ተደርጓል። በሶደሬ ቀደም ብሎ የታሰሩትን እስረኞች
ዝርዝር ታሪክና ከመቶ የሚበልጡ የግድያ ሰለባ የነበሩትን ሰዎች በጅምላ
ከመዘከር በስተቀር እዚህ ታሪክ ውስጥ ለማካተት አልተሞከረም።
የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች በእስር ላይ በነበሩበት ጊዜ እርስ በርሳቸው
በመረዳዳትም ሆነ ሌሎችን በመርዳት ይታወቃሉ። በይፋ መናገር ባይቻልም
በሹክሹክታም ሆነ በአይን ምልክት አዲስ እስረኛ ሲቀላቀላቸው የቆዩት ለአዲስ
መጪዎች ምክር ያካፍላሉ። ምርመራውንም እንዲቋቋምና የስር ቤቱን
ሕይወት እንዲላመድ ያደርጋሉ። ይህንን ሲያደርጉም ከምልክት ጠላፊና ከቀይ
ሽብር አራማጆች ወሬ አቀባባይ መጠንቀቅ ነበረባቸው። ደግነቱ በሌሎች ብዙ
እስር ቤቶች እንዳጋጠሙት በሶደሬ በነበሩት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊ እስረኞች
መካከል የጎላ የአስተሳሰብ ልዩነት አላጋጠመም። ሁሉም ለነፍስ አድን
መልዕክት ይተባበር ነበር። ከደርግ ወገን ከቆሙት ሦስት
ገራፊዎች/መርማሪዎች በስተቀር በመካከላችን በይፋ ከቀይ ሽብር አራማጆች
ጋር የወገነ፣ አጋጣሚውን በመጠቀም አካኪ ዘራፍ በማለት ለመጎዳኘት የሞከረ
ወይም የአንጃውን አቋም የሚከተል አልነበረም። ከሦስቱ መርማሪዎች መካከል
ሳሙኤል ይፍሩ የአንጃ አባል እንደነበረ ይታወቃል።
በሶደሬም ሆነ በሌሎች እስር ቤቶች በቀይ ሽብር ጊዜ የሚበዙት
ኢሕአፓዎች ነበሩ። በቁጥር እንደመብዛታቸው ሁሉ ከሌሎች ጋር መልካም
ግኙኝነት በመፍጠር፣ በምርመራ ጊዜ የተጎዱ እስረኞችን በመንከባከብ፣

ከተቃዋሚ የፖለቲካ እስረኞች ጋር በመቻቻል፣ በአጠቃላይ በእስር ላይ በቆዩበት ጊዜ መልካም ሥነ ምግባር በማንፀባረቅ እንደ አርአያ የሚቆጠሩ ነበሩ:: እውነተኛ ኢሕአፓ'ዎች ካልደረሱባቸው አይደርሱም፣ ካልነኳቸው አይነኩም፣ በአሳሪዎችና በታሳሪዎች መካከል እየገቡ ወሬ አያቀብሉም፣ ወሬኛም አይወዱም፣ አያስጠጉም:: ችግራቸውን በመቋቋም በመንፈስ ጠንካራነት የደርግን ሰቆቃ ተጋፍጠዋል፣ ለመሰዋእትነትም ዝግጁ ሆነዋል:: ይህም ሲባል ለሞት ግድ አልነበራቸውም ለመዳንና በሕይወት ለመኖር አይፈልጉም ማለት አይደለም:: ያለአድሜው ለመሞት ማንም አይፈልግም:: ከኢሕአፓዎች መካከል መንፈሰ ጠንካሮች እንደመኖራቸው ሁሉ መንፈሰ ደካሞችም ነበሩ::

የሶደሬ እስረኞች ከውጪ ጠያቂ የሚያገኙትን ምግብ በጋራ ይመገቡ፣ ሱስ የነበረባቸውም የሲጋራ ቁርጥራጭ እየተካፈሉ በጋራ ያጨሱና በድብቅ ያስገቡትን ማንኛውንም ገንዘብም ሆነ መድኃኒት በጋራ ይጠቀሙ ነበር:: የእስረኛው ማህበራዊ ሕይወት ያስቀና ነበር:: የቀኑ ተራኛ የምግብ አስተናጋጅ ሳህን አጥቦ ከየቤቱ የመጣውን ምግብ ደባልቆ ለሁሉም ያቃምሳል፣ ሻይም ያካፍላል፣ የቤቱን ጽዳት ይቆጣጠራል:: አንዳንዶች እስረኛው እንዳይቆዝም የሚያውቁትን ተረቶችና ቀልዶች ያወራሉ:: ከዚያ ውጪ ሁሉም ቀንም ማታም የሚፈጠረውን መጠባበቅ ነበር::

ከኛ በፊት ብዙዎች ከሶደሬ እየተወሰዱ ተገድለዋል:: እነኝህ ከሶደሬ በየጊዜው እየተወሰዱ የተገደሉት እስረኞች ከእኛ የበዛ ወይም ያነሰ ወንጀል አልነበራቸውም:: ወንጀላቸው እንደኛው የኢሕአፓ አባልና ደጋፊ መሆናቸው ወይም በደርግ «ፀረ አብዮተኛ» ተብለው መፈረጃቸው ነበር:: እንደ ሌሎች የደርግ እስር ቤቶች ሁሉ በሶደሬም በአፍላው የቀይ ሽብር ጊዜ የግድያ ምርጫ አልነበረም ማለት ይቻላል:: የዚያን ጊዜ የኢሕአፓ ድርጅት ደጋፊም ሆነ አባል፣ ዝቅተኛም ሆነ በተለያየ እርከን ላይ ያለ የአመራር አባል፣ የዴሞክራሲያ ጋዜጣ ያነበበም ሆነ ያሰራጨ፣ ወረቀት የበተነ፣ ግድግዳ ላይ የፃፈ፣ የጥቃት መከላከያ አባልም ሆነ ሌላ፣ ሰው የገደለም ሆነ ሰውየውን የጠቆመ፣ ወዘተ. ልዩነት ሳይደረግ ተረሽነዋል:: በጊዜው ማንኛውም በኢሕአፓ አባልነት የተጠረጠረ ወይም የተጠቆመበት ግለሰብ ሲያዝ የሚቀረቡለት ጥያቄዎች ስንት ገድለሃል? ስንት መልምለሃል? ስንት ይከፈልሃል? የሚሉ ነበሩ:: በዚህ የተነሳ ያለምርጫ በእድሜ አነስተኞችም ሆኑ ከፍተኞች ተገድለዋል፣ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ያለርህራሔ ተረሽነዋል፣ ከምንም የሌሉበትም ቀይ ሽብር በልቷቸዋል:: በከፍተኛ 22 የቀይ ሽብር አራማጆች ከተገደሉት ሁለት ወንድማማቾችና አንድ እህታቸው መካከል እንግዳወርቅ ከበደ፣ የግል ወርቅ ከበደና ንጉሤ ከበደ ይገኙበታል::

ምንም እንኳን ሶደሬ ታስረው በቀይ ሽብር የተገደሉትን በሙሉ እዚህ ላይ ማካተት ባይቻልም የሚከተሉት ለአብነት ቀርበዋል::

ሀ) 1. እንግዳወርቅ ከበደ
2. የግልወርቅ ከበደ
3. ንጉሤ ከበደ
4. ሳባ ጣሰው
5. አገኘሁ አያሌው
6. ዘገዬ ኃይሉ
7. ዳንኤል ዘውዴ
8. ነብዩልዑል

9. ክፍሌ ገብረአምላክ
10. ደበበ ታደሰ
11. ሺመልስ ኃይሉ
12. ሙሉጌታ በሱፈቃድ
13. አብርሃም በርሄ
14. ሰሙንጉሥ ከበደ
15. ግርማ አበበ
16. ሞገስ ተፈራ
17. አበበ አለማየሁ
18. ደሳለኝ ቦረጅ- ሶደሬ ታስሮ በ1971 ዓ/ም. በደርግ የተገደለ
19 ውብሸት አለማየሁ- ሶደሬ ታስሮ በ1971 ዓ/ም. በደርግ የተገደለ
20. አለማየሁ ለማ- ሶደሬ ታስሮ በ1971 ዓ/ም. በደርግ የተገደለ
21. አየለ ዘለለው የጆሆቫ እምነት ተከታይ
22. ኃይሉ የምሩ የጆሆቫ እምነት ተከታይ
23. ውቤ አየለ የጆሆቫ እምነት ተከታይ

ለ) በ5/5/70 በከፍተኛ 22 ልዩ ልዩ ቀበሌዎች 15 ሰዎች ተገድለዋል::

በ1970 ዓ.ም. ከታህሳስ እስከ ሰኔ ባሉት ጊዜያት በተለያዩ የአዲስ አበባ ቀበሌዎች የኢሕአፓና ኢድህ አባላትና ደጋፊዎች በሚል የተፈረጁ 286 ሰዎች በቀይ ሽበር እንደተገደሉ የደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ያመለክታል::(3) ከፍ ብሎ የተጠቀሱት በከፍተኛ 22 የተገደሉትም በዝርዝሩ ተካተዋል::

በሶደሬም ሆነ በሌሎች እስር ቤቶች ለደርግ ታማኝነታቸውን የገለጹ አንዳንድ የኢሕአፓ አባላት የምርመራውን ተግባር ጠቅልለው ከያዙት በኋላ ግድያውና የጅምላ እስሩም የበለጠ ጨመረ እንጅ አልቀነሰም:: እነኝህ ወዶ ገቦች በሚያውቁት ቤት ብዙ ጥፋት አደረሱ:: የድርጅቱን አሰራርና መዋቅር ለመተርተር ጊዜም አልፈጀባቸው:: በዚህ የተነሳ የተተረተረውን ገመድ ውሉን ፈልጎ ለመቋጠር አስቸገረ፣ ሚስጥር መደበቅም ተሳነ፣ በከተማም በገጠርም የተዘረጋው የኢሕአፓ መዋቅር ፈረሰ፣ ሁሉም በነበር ትዝታ ሆኖ ቀረ::

ምናልባት መዋቅራቸው ከመፍረስ ያመለጡት በአካባቢያቸው የሚካሄደውን የኢሕአፓ የትጥቅ ትግል የተቀላቀሉት የጎንደር የኢሕአፓ አባላት ሳይሆኑ አይቀርም:: (4) የጎንደር የኢሕአፓ መዋቅርም ቢሆን ከመፈራረስ ድኗል ለማለት አይቻልም:: ምክንያቱም የአካባቢው ከፍተኛ አመራርና ጎንደርና ጎጃምን ከማዕከላዊ ኮሚቴ ጋር ያገናኝ የነበረው ኢንተርዞን ሐላፊ መንግሥቱ ቀፀላና የተለያዩ አባላት ጭምር የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነዋል:: ጥቂት ግለሰቦች አምልጠው የትጥቅ ትግሉን ስለተቀላቀሉ ብቻ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የተሻለ ነበር ለማለት አያስደፍርም::

በእስር ላይ የነበሩ የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች የድርጅታቸውን የውጭ እንቅስቃሴ እያስታወሱ ይቆዝሙ ነበር:: ስህተት የት ላይ እንደተፈፀመና ለእስር እንደተዳረጉ ከስሜታቸው ጋር ይሟገቱ ነበር:: የኢሕአፓ አባል የሆኑ ሁሉ በተለያዩ የድርጅቱ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ የትግሉ ሁኔታ የግድ ይጠይቃል:: ማንኛውም የድርጅቱ አባልም ሆነ ደጋፊ ሊያበረክት የሚችለው እንደነበረበት አካባቢና እንደ ተሳትፎው ይለያያል:: በጊዜው የኢሕአፓ ድርጅት መዋቅር ያልተዘረጋበትና ያልደረሰበት አልነበረም:: በዚህም የተነሳ የድርጅቱ አባል የሆነ ሁሉ ድርጅቱን ሊደግፉና ሊጠቅሙ የሚችሉ ግለሰቦችን መመልመልና ማቅረብ ተቀዳሚ ግዴታው ነበር:: ከዚህ ባሻገር ድርጅቱን በገንዘብ ለማጠንከር ከሚያገኘው ገቢ እየከፈለ

ወርሃዊ መዋጮ መስጠትም ይጠበቅበታል:: በተጨማሪም በተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ እየመረመረ አቋም ይወስድ ነበር:: ከነዚህም መካከል አንጻው ያነሳቸው ጥያቄዎች፣ በኤርትራ ጥያቄ ላይ የተወሰደው አቋምና ያጋጠመው ችግር፣ የኢትዮ-ሱማሌ ጦርነት፣ ሶሻል አምፔሪያሊዝም፣ ወዘተ. ወሳኝ ነበሩ::

ከከተማው ትግል ጎን ለጎን የገጠር የትጥቅ ትግል ለማካሄድ የተሞከረባቸው የትግራና የጎንደር አካባቢዎች የመጀመሪያዎቹ ነበሩ:: በዚህ የተነሳ ከተማ ውጥረት ሲበረታ የትጥቅ ትግል የተጀመረባቸው ጸለምትና አሲምባ የኢሕአፓ አባላት ነፍስ መግዣ ቦታ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር:: ይሁንና በ1969 እና በ1970 ዓ.ም. ለኢሕአፓ አባላት ቀርቶ ለማንኛውም የሚጠረጠር ወጣት እነኚህ አካባቢዎች በቀላሉ ለመድረስ ቀርቶ ጎንደርና ትግራይም መሄድ አዳጋች ነበር::

የጎንደር አካባቢ የኢሕአፓ እንቅስቃሴ ሁለቱንም ተደጋጋፊ የሆኑ ትግሎች አካሂዷል:: በ1968 ዓ.ም. አንድ ክንፍ የገጠር የትጥቅ ትግል የሚያካሂድ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሕዝባዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ከትግራይ ወደ ጸለምት የገባበት ጊዜ ስለነበረ ከአዲስ አበባና ከሌሎች ቦታዎች የተጋለጡም ሆነ በድርጅቱ የሥራ ምደባ ቡድኑን ለመቀላቀል የሚወረወሩት ከጎንደር ከተማ ነበር:: እነሱንም በቅብብሎሽ ጸለምት ለማሻገር በጎንደር ክፍለ ሐገር ወደ ገጠር የሚንቀሳቀሱ የኢሕአፓ አባላት የሚገለገሉባቸውን የመንግሥት ተሽከርካሪዎች መጠቀም አስፈላጊ ነበር:: ለዚህ ጉዳይ በጎንደር የርሻ ሚኒስቴር፣ «የኤፒድ»፣ የአውራ ጎዳና፣ የመሬት ይዞታ፣ ወዘተ. መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ የድርጅቱ አባላት ከሚጠቀሙባቸው የገጠር ተሽከርካሪዎች ጋር በጣም ጠቃሚ አገልግሎት እንዳበርከቱ ፀሐፊው ያስታውሳል:: አሲምባም በመቀሌ በኩል እንደዚሁ ይደረስ ነበር:: እየቆየ ሲሄድ ይህ እድል እየጠበበ መጣ::

በ1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አብዮት ከመካሄዱ በፊት በተማሪ ድርጅቶች መካከል የተከሰተው የፖለቲካ ልዩነት መከፋፈል እንዳስከተለ አይዘነጋም:: በዚህ መለያየትም የተነሳ ሁሉም ወገኖች ጉዳት ደርሶባቸዋል:: የመለያየትን አደጋ ሁሉም ቢገነዘቡም ካለፈው ትምህርት በማግኘት እርማት ሲያደርጉ አይታዩም:: ይህ ጉዳይ በተደጋጋሚ በኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ህይወት ተከስቷል:: ከዚህ ልምድና ትምህርት ያልገበየው የኢሕአፓ አመራርም ባጋጠመው መከፋፈልና አንጃ መፈጠር ብዙዎችን አስደንግጧል፣ አሳዝኗል:: በዚህም የተነሳ በ1969 ዓ.ም. ስለተፈጠረው ልዩነት በድርጅቱ ልሳኖች የሚቀርቡትን ዘገባዎች መርምሮ አቋም መውሰድ የድርጅቱ አባላት መብትና ግዴታ ነበር:: ይህም በጭፍን በአንድ ወገን ላይ ብቻ ከመፍረድ ያድናል::

ከዚህ ሌላ የኤርትራም ጥያቄ ብዙ ጊዜ አነታራኪ ሆኖ ቆይቷል:: በ1969 ዓ.ም በዴሞክራሲያ ላይ ስለ ኤርትራ ጉዳይ አንድ አጨቃጫቂ ዘገባ ቀርቦ ነበር:: ዘገባው በኤርትራ ሕዝብ ላይ እየተወሰደ ያለውን የጭፍጨፋ እርምጃ የኤርትራን ሕዝብ በሙሉ ወደ ትጥቅ ትግልና የብሔር ትንቅንቅ ስለገፋፋው የመደብ ትግል ለማካሄድ አለመቻሉን ይገልጽና ኤርትራ ነፃ እንድትወጣ ይደግፋል:: (5) ነፃነትም ለመደብ ትግሉ መፋፋም ጥቅም እንዳለው ያመለክታል:: ይህንኑ አቋም በ1971 ዓ.ም. በጎንድር የተካሄደው የአራተኛው ማዕከላዊ ኮሚቴ ጠቅላላ ስብሰባ በድጋሚ አጽድቆታል:: (6)

በመሰረቱ ይህ አባባል በሌላው የአገሪቱ አካባቢዎች የሚካሄደውን ጭፍጨፋ ጭራሽ የዘነጋ ነበር:: የደርግ ጭፍጨፋ በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሀሉም ቦታ የሚካሄድ ስለነበረ ኢሕአፓ ይህን ተቋቋሞ በሌሎች የኢትዮጵያ

ክፍሎች የመደብ ትግል ኢያካሄደ በኤርትራ ብቻ ማካሄድ አቃተኝ የሚል እንደምታ ነበረው:: በጊዜው ይህን መሰል ተቃውሞ አልተነሳም ለማለት ያስቸግራል:: ሌላው ቀርቶ በክፍሉ ታደሰ መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ በዴሞክራሲያ ከመታተሙና ይፋ ከመሆኑ በፊት በፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት በቅድሚያ ተሰራጭቶ ያለ ተቃውሞ ማለፉም ያጠራጥራል:: (7) ስለዚህ የኢሕአፓ አመራር በግልም ይሁን በጋራ በኤርትራ ጥያቄ ላይ በተለያየ ጊዜያት የወሰዷቸው ተለዋዋጭ አቋሞች ብዙዎችን አወዛግበዋል::

በመሰረቱ ሁኔታው በጊዜው የተድበሰበሰ ቢሆንም የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የካቲት 1969 ዓ.ም. በኤርትራ ላይ የወሰደው «የኤርትራ ጥያቄ የነፃነት ጥያቄ ነው» የሚለው አቋም (8) ትክክል ነበር ለማለት ያስቸግራል:: ጭቁን ሕዝቦች መብታቸውን ለማያስከብሩበት ወጤት አልባ ትግል የኤርትራ ተዋጊዎችን ለማስደሰት ሲባል ሊድበሰበስና ዝቅተኛ ግምት ሊሰጠው አይገባም ነበር:: ኢሕአፓም በኤርትራ ጥያቄ ላይ በወሰደው አቋም ተጎጂ እንጅ ተጠቃሚ እንዳልነበረ በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል::(9) በተጨማሪ የታሪክ ሂደትም እንዳሳየው የኤርትራ ነፃ መውጥትና በራስ መቆም በሁለቱ መካከል የሚካሄደውን ጦርነት ለጊዜው ጋብ ቢያደርገውም ውሎ አድሮ በሌላ መልክ ከመቀስቀስ አላዳነውም::

1.2 የተለያዩ እስረኞች በሶደሬ

በዚህ አርእስት ስር የተካተቱት እስረኞች ከአውራ ጎዳና ቢሮክራቶች ተብለው የታሰሩትን፣ ፀረ አብዮተኛ ልጆቻችሁንና የቤተሰብ አባሎቻችሁን ደብቃችኋል በሚል የታሰሩትን፣ መሣሪያ ደብቃችኋል በሚል የተገረፉትንና በእምነታቸው የተነሳ የታሰሩተን ያጠቃልላል:: ቀይ ሽብር ሲጀምር በዚህ መሰል ወንጀል ከተከሰሱትም መካከል አንዳንዶቹ የተገደሉ ቢሆንም አብዛኞቹ በአጭር ጊዜ ስለሚፈቱና በእስር ላይ ስለማይቆዩ ሁሉንም እዚህ ላይ መዘከር ያስቸግራል:: ቢሆንም በጊዜው በአገሪቷ በሙሉ በነበረው ተቃውሞ ግራ የተጋባው የደርግ መንግሥት ከግራም ከቀኝም ይላተም ስለነበር እስርና ሰቆቃው እንዴት እንደፀበል ለሁሉም እንደተዳረሰ ለማሳየት የጥቂቶቹን በመረጃነት እንዲያገለግል እዚህ ላይ ሊቀርብ ችሏል::

የአውራ ጎዳና ቢሮክራቶች በሚል ከታሰሩት መካከል የአስተዳደር ሥራ አስኪያጁ አቶ ኢ.፣ ምክትል ሥራ አስኪያጁ አቶ ገ.፣ የፋይናንስ ሹሙ አቶ ገ.፣ የንብረት ክፍል ሹሙ አቶ ደ. እና ሌሎችም የሚታወሱ ናቸው:: በእምነታቸው የታሰሩት ደግሞ በጊዜው የነበረውን የኢትዮጵያና የሱማሌ ጦርነት የማይደግፉ፣ ሃይማኖታቸው ስለማይፈቅድላቸው ለጦርነት መዝመት የማይፈልጉ፣ ኢሕአፓን፣ ኢዴህንና ጀበሐን እናወድማለን የሚል መፈክሮችን ማሰማት የማይወዱ ተብለው ከአንዳንድ መሥሪያ ቤት ተጋልጠው የመጡ ነበሩ:: ከእነኝህ እስረኞች ለየት የሚለው አቶ ሥ. በሚል ስም የሚታወቀው የህግ ባለሙያ ሶደሬ ለትንሽ ጊዜ ታስሮ ከቆየ በኋላ ወደ አዳራሽ ተዛውሮ በመጨረሻ ሊፈታ ችሏል::

ደርግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትጥቅ ለማስፈታት በከተማም በገጠርም ተከታታይ አሰሳ በማካሄድ በሃገሪቷ ይገኝ የነበረውን መሣሪያ ሁሉ ለመሰብሰብ ሞክሯል:: ከሱም ፈቃድ ውጪ ማንም መሣሪያ እንዳይዝ ከልክሏል::

አላማውም የደርግ ዋና ተቀናቃኝ የነበርው ኢሕአፓ ምንም አይነት መሣሪያ በእጁ እንዳይገባ ለመቆጣጠር ነበር:: በዚህ የተነሳ በጊዜው አንዲት አሮጌ ሽጉጥ ደብቆ የተገኝ የሚያገኘው አባዜ በጣም የከፋ ነበር:: አቶ በ. ተምትሜ የሚባል ከ58-60 ዓመት የእድሜ ክልል የነበረ አዛውንት አንዲት የማትረባ አሮጌ ሽጉጥ መደበቁ በቤተሰቡ አባል አማካኝነት ለቀበሌው ጥቆማ ስለደረሰው «ቀደም ብለህ እንዴት አላስረከብክም» በሚል ታሰሮ ክፉኛ ተደብድቧል:: ሌላው ደግሞ ከዚሁ ከመሣሪያ ጋር ታስሮ በተደጋጋሚ ክፉኛ የተደበደበው የዚሁ ቀበሌ ነዋሪና የፖሊስ ሠራዊት አባል የነበርው ኮለኔል ደ. ፍላቴ ነበር:: ይህ ኮለኔል በዚህ ጉዳይ ክፉኛ ተገርፎ ስደሬ ሲመጣ የነበረው እስረኛ በሙሉ ማመን አቃተው:: ምክንያቱም አንድ በማገልገል ላይ ያለ የፖሊስ መኮንን መንግሥት ያስታጠቀው መሣሪያ እያለው እንዴት ሌላ መሣሪያ ደብቆ ተገኘ ሊባል እንደቻለ ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ነበር:: ኮለኔሉ እንደሚለው መንግሥት ካስታጠቀው መሣሪያ ሌላ በድብቅ ያስቀመጠው የራሱ እንደነበረውና አንድ የተጣላው የእህቱ ልጅ እንደጠቆመበት ገልጿል::

ከአንዳንድ የቀዩ የፖሊስ መኮንኖች መረዳት እንደተቻለው ኮለኔል ደ. ፍላቴ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የምርመራ ክፍል ሹም እያለ ከመሳሪያ ጋር የተያያዘ የምርመራ ሥራ ስላካሄደ ምናልባት ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ለራሱ መሣሪያ ሳይወስድ አይቀርም የሚል ሐሜት ነበር::(10) ይህንን ጉዳይ የዱሮ ባላንጣው የነበረው ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ስለሚያውቅ ኮለኔል ደ. ፍላቴን ለመበቀል በተቀነባበረ ሴራ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ያሳስርና ያስገርፈዋል:: ሁለቱን የፖሊስ መኮንኖች ሊያጣላና ይህንን በቀል ሊያስከትል የቻለው ሁለቱም ዝቅተኛ መኮንኖች እያሉ በአንድ ፖሊስ ጣቢያ አንዱ አለቃ ሌላው ምንዝር ሆነው አብረው በሚሰሩበት ጊዜ የተፈጠረ ችግር ነው:: የበፊቱ የበታች ብርሃኑ ከበደ በፖሊስ ሠራዊት ለእድገት ሲጠራ የበላዩ የነበረው ደ. ፍላቴ ያባከነውን ንብረት ሳያስረክብ መሸኛ እንዳይሰጠው ይከለክለዋል:: እንግዲህ ጊዜና ስልጣን ሲቀያየር ይች ቁርሾ ጊዜ ጠብቃ ኮለኔል ደ. ፍላቴን ለጥቃት ታጋልጣለች:: ከዚህ እንደምንረዳው ቀይ ሽብር የቂም በቀል መወጫም እንደነበረም ነው:: እንዲያውም በአንዳንድ ከፍተኞች የሃብታም ነጋዴዎችን ንብረት ለመዝረፍ፣ መልከ መልካም ሚስት የነበረችውን ለመንጠቅና ቤት ንብረት ለመቀማት ሲባል ሰዎች በግፍ ታስረዋል፣ በቀይ ሽብርም ተገድለዋል::

እንደ ኮለኔል ደ. ፍላቴ ሁሉ የአንዳንድ ግለሰቦችም ለስርና ለግርፋት መዳረግ በጣም ይገርማል:: አንድ ጊዜ ከአንበሳ አውቶቡስ መሥሪያ ቤት አንድ በአምሳዎቹ የእድሜ ክልል የነበረ ግለሰብ ይታሰራል:: ሰውየው በጣም ከተደበደበ በኋላ ስደሬ አምጥተው ከነበርነው ጋር ይደባልቁታል:: እንደተለመደው በግርፋት የተጎዳ እግሩ እንዳያብጥና ውሎ አድሮም መግል እንዳያቀተው ቆሞ ዱብ ዱብ እያለ መሬቱን እንዲረግጥ ምክር ከሰጠነው በኋላ ወ.ገ. አንዳንድ የህክምና እርዳታ ያደርግለታል:: ከዚያም ሰውየው ከተረጋጋ በኋላ ከየት እንደመጣና ለምን በዚያን እስር ጋብ ባለበት ወቅት እንደታሰረ ሲጠየቅ «ተውኝ ወዳጆቼ ታስገድሉኛላችሁ» ብሎ ጭራሽ አልናገርም አለ:: ከዚያም የቤቱን ሰዎች እየለመደ ሲሄድ ከአንበሳ አውቶቡስ መሥሪያ ቤት እንደታሰረና በዚህ ከፍተኛ ወደገብ የሆነችው ትንሣኤ የምትባለው የመገናኛና ትራንስፖርት ካድሬ/የአብዮት ጥበቃ «መሥሪያ ቤት ወደኔ ጣትህን ጠቁመህ ለሰዎች አመልክተሃል፣ ምን እያልክ ነበር እውነቱን አወጣ? ተብዬ ይኸው

ፍዳየን አየሁ፣ እናንተንም እዚህ የምትሰቃዩትን እግዚአብሔር አሳየኝ። አደራ ልጆች በዚህ ደግሞ ምን ብለህ አወራህ ተብዬ በድጋሚ እንዳልገረፍ» ሲል ተማጸነ። ድርጊቱ በጣም ቢያሳዝነንም እየቆየንና እየተቀራረብን ስንሄድ ሰውየው እስኪፈታ ድርስ ጣታችንን ወደስው እየጠቆምን እናስቀው ነበር።

1.3 የሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ደጋፊ እስረኞች በሶደሬ

እስከ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ በዋነኛነት በጠላትነት የተፈረጁት የኢሕአፓ፣ የኢዴህና የጀበሐ ድርጅቶች ብቻ ቢሆኑም ሌሎች ወዳጅ ነበሩ ማለት አይደለም። ከደርግ ጋር ወዳጅ የነበሩትም እንኳን ሳይቀር በተለያየ ጊዜ ልዩነት እየፈጠሩ አባላቱ ወይ ከስልጣን አካባቢ ተገለዋል አለበለዚያም ታስረዋል። ሶደሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የሌሎች ድርጅቶች እስረኞች የመጡት ግንቦት 1970 ዓ.ም. አካባቢ የመኢሶን አባሎች ነበሩ። በመጀመሪያ ታስረው ከመጡት መካከል የከፍተኛ 14 የአዘአኮ አባል የነበረው አ. ጉድንፋ(አ.ጉ.)፣ ቡ. ነጋሳ(ቡ.ነ.) የተባለው የአየር መንገድ ሠራተኛና የ. የተባለው መምህር ይገኙባቸዋል። አ.ጉ. ውጪ አገር ከፍተኛ ትምህርት የተማረ የጤና ባለሙያ ሲሆን ቡ.ነ. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የማታው ትምህርት የዲግሪ ምሩቅ ነበር። እነዚህ ሦስቱ ከመጡ በኋላ በተለያየ ጊዜ ሌሎች የመኢሶን አባላት የቀበሌ አመራር የነበሩ አንደኛው ደ. ተሾመ(ደ.ተ.) ሌላው ስሙ የተዘነጋ፣ አንድ ተ. የሚባል በደብረ ዘይት ካደሬ የነበረ፣ አንዲት ሴት ካድሬ ዘ. የምትባልና ሌሎች ወጣቶች ጭምር እንደታሰሩ ይታወሳል። ሌሎች ደግሞ ከመርካቶ አካባቢ ታስረው የነበሩ የመኢሶን ይሁን የሌላ ድርጅት አባላት መሆናቸው የማይታወቅ በቁጥጥር ስር ውለው ነበር።

ብዙዎቹን የወዳጅ ግርፋት በመጠኑ ቸብ ቸብ ቢያደርጓቸውም ብዙም አልጨከኑባቸውም። ቡ.ነ. ብቻ ጨክነውበት በጣም ተገርፏል። ከመርካቶ ተይዘው የመጡት ከነከሰተ አብራኒዮስ ጋር ቀደም ብለው በቅርብ የሚተዋወቁ ጓደኞች ነበሩ። እንዲያውም «እስኪ ተራማጅ ከሆናችሁ አነጋግሩን»፣ «ችግራችንን በውይይት አንፍታው» ሲባባሉ በመካከላቸው አንድ ነገር እንዳለ ያስጠረጥር ነበር። የነኝህ ከመርካቶ አካባቢ የታሰሩት ግለሰቦች ጉዳይ የሶደሬን እስረኛ በየጊዜው እየመጣ ሲያስፈራራ ከነበረውና የከሰተ ጥብቅ ጓደኛ ከሆነው ከኤልያስ ኑር ጋርም ሳይያያዝ አይቀርም። ኤልያስና ከሰተ የሰሩትን የተደበቀ ሚስጥር እነኝህ ሰዎች ስለሚያውቁ ያንን ለመሸፋፈን ወይም ሰዎቹ ሚስጥሩን እንዳያወጡ ለማስፈራራት የታሰሩ ይሆናሉ ተብሎ ይጠረጠራል። በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት እስረኞች መካከል ብዙዎቹ ሲፈቱ ጥቀቶች ብቻ ከሌሎቻችን ጋር ከርቸሌ ተወስደዋል።

የጋራ ችግር ጠበኞች የሆኑ ግለሰቦችንም አንዳንድ ጊዜ ያፋቅራል። ምንም እንኳን የኢሕአፓና የመኢሶን ደጋፊዎች በውጪ አለመግባባት ቢኖረንም ስምንት ወር አብረን አንድ ቤት ስንታሰር የጎላ ልዩነት አልነበረንም። የፖለቲካ ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው ተቻችለን ጠባብ ክፍል ውስጥ በጋራ ታስረናል። መቻቻል ቢኖርም አብረን ስንቆይ አንዳንድ የሰማናቸው መጥፎም ጥሩም ነገሮች ነበሩ። ለምሳሌ ስለ አ.ጉ. በሰማነው እንጀምር። አንድ ከአስራ ስድስት ዓመት የማይበልጥ ታ. አስራት የሚባል ወጣት በአዳራሽ ውስጥ ከታሰሩት መካከል ሳይፈታ የቆየ ወደ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እስር ቤት ከመዛወሩ በፊት አ.ጉ. የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በነበረበት ከፍተኛ 14

ታስሮ ነበር:: በጊዜው ለተለያየ ምርመራ ከአንዱ እስር ቤት ወደ ሌላው ማዛወር አሳሪዎችም እየተዘዋወሩ የሚፈልጉትን ማደን የተለመደ ነበር:: ታዲያ በዚህ ምክንያት ነበር ታ. አስራት ከከፍተኛ 14 አሁን አለበት እስር ቤት የመጣው:: ይህ ወጣት የአንድ ኮሎኔል ልጅ ሲሆን የአባቱን ሽጉጥ ከቤት ወስዶ ለኢሕአፓ ያስረክባል:: በዚህ ድርጊት በመጋለጥ ከፍተኛ 14 ታስሮ በነበረበት ጊዜ በቀይ ሽብር ሊገደል መኪና ላይ ከሌሎች እስረኞች ጋር ከተጫነ በኋላ ኢ.ጉ. እየተዘዋወረ ሲመለከት የልጁን የእድሜ ለጋነት በመገንዘብ ከመኪና አስወርዶ ያዳነው መሆኑን በመግለጥ ኢ.ጉ. ታስሮ እንደመጣ «ነፍሴን ያዳነው መጣ» እያለ አጫውቶናል::

እንደ ዝናም ይሁን እንደ አሸናፊነት እየቆጠሩት በቀበሌ አካባቢ ሲሰሩ የነበሩት የመኢሶን አባላት በቀይ ሽብር የፈጸሙትን አጫውተውናል:: አንዳንዶቹ እንደ ቧልት እያደረጉ የሚናገሯቸው የሚያስቀም ትዕግስት የሚፈታተኑም ነበሩ:: ለምሳሌ የ. የተባለው አስተማሪ በጣም ቧልተኛ ነበር:: ደግነቱ ከኢሕአፓዎችም በኩል እንደ ወ.ገ. ያሉት ለዚህ የሚሰንፉ አልነበሩም:: ደ.ተ. የሚባለው ቀበሌ አካባቢ ሥልጣን የነበረው የመኢሶን አባል አንድ ጊዜ የቀይ ሽብር እርምጃ ሲያካሂዱ አንዱን በሰባት ጥይት ከመቱት በኋላ እንኳን ሳይሞት በርከክ ብቻ ሲል መመልከቱን አሁንም ድረስ እፊቴ ይመጣብኛል በማለት አጫወተን:: ሌላው አብሮት የመጣው ስሙ የተዘነጋው ኳደኛው ደግሞ ኢሕአፓን በጣም ከመፍራቱ የተነሳ እንኳን ሰው ጥላውንም ቢሆን የማያምን እንደነበረ አወጋን:: እንዲያውም አንድ ጊዜ ሰው የተከተለው መስሎት የገዛ ጥላውን በታጠቀው ሽጉጥ ተኩሶ የመታው መሆኑን ሳይደብቅ ነገረን:: ብዙ የኢሕአፓ ወጣቶችን በቀይ ሽብር ገድለው ጥቂቱን ብቻ በየአደባባዩ ሬሳቸውን ከጣሉ በኋላ ሌሎች እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑ እንዳይታወቅ ለልማት ወደ ሌላ እስር ቤት መንግሥት ወስዷቸዋል እያልን እናስወራ ነበር ያለን የደብረ ዘይቱ ካድሬ ተ. ነበር:: ይህንን ጉዳይ ተክልዬ ከመታሰሩ በፊት ደብረ ዘይት እያለ የሰማ መሆኑን አረጋግጧል::

እንደ ኢሕአፓ ሁሉ የመኢሶን እስረኞችም አንዱ አንዱን በመጠቆምና በመሳሳብ የታሰሩ መሆናቸው ውስጥ አዋቂነት አይጠይቅም:: ቢሆንም አጠቃላይ ግምት ከመውሰድ በስተቀር በውስጥ ድርጅታቸው ሚስጥር ዘልቆ መግባት አይቻልም::

1.4 የሶደሬ የእስር ሁኔታ መሻሻል

ከመኢሶን ሰዎች ጋር በጣም እየተላመድንና እየተግባባን ስንመጣ በዚያን ጊዜ በደርግና በደጋፊዎቹ ቡድኖች መካከል የተፈጠረውን ሽኩቻ፣ የወዝ ሊግ የመኢሶን አባላት በነበሩት ላይ የሚፈጽመውን ደባ፣ የወዝ ሊግ አመራር አባላት «በኩደታ ደርግን ለመገልበጥ አያሴሩ» እንደሆነና ደርግም ነገሩን ደርሶበት እያጣራ መሆኑን በቁጭት ሹክ አሉን::

በመሰረቱ የመኢሶን ድርጅት ከደርግ ወዳጅነት አፈንግጦ የወጣ ስለሆነ ይህ አባባል በቁጭት የተሰነዘረ ስለመሰለን እውነትነት ይኖረዋል ብለን አልገመትንም:: በሌላ መልኩ በኢማሌድህ ዙሪያ ያለው ሽኩቻ የተለመደ መሆኑን ስለምንረዳ ብዙም ክብደት ባንሰጠውም የአሳሪዎቻችንን ግንኙነት ስለሚበጥሰውና አፎይታ ስለሚሰጠን በጥሞና መከታተል ጀመርን:: የተወራው አልቀረም መጀመሪያ የወዝ ሊግ አመራር አባል የነበረው የደርግ የምርመራ

ክፍል ሹም ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ለሥራ ወደ ትግራይ ተላከ ተባለ፣ ከዚያም
ሲመለስ ከሥልጣን ተነሳ፣ ቀጥሎ ታሰረ እየተባለ ወሬው ሶደሬ ሾልኮ ገባ።
የገመትነውም አልቀረ የኛም አሳሪዎች እየተለሳለሱ መጡ፣ ለአየርም ለነፋስም
እንደፈለግን እንድንወጣና እንድንዝናና ፈቀዱ። በግቢው ውስጥ እየወጣን የእጅ
ኳስ መጫወት በእስር ክፍላችንም የተለያየ የጊዜ ማሳለፊያ መጫዎቻዎች
እያዘጋጀን መጫወት ጀመርን። ሶደሬ የተሰሩ የዳማ፣ የቼዝ፣ የሞኖፖሊና
የካርታ መጫዎቻዎች ጥሩ የጊዜ ማሳለፊያ ሆኑን።

እንደበፊቱ በርከት ያሉ የፖለቲካ እስረኞች ስለማይታሰሩ የሶደሬ የቦታ
ጥበትም ተቃለለ። ሳይነባባሩ ተሰፋፍቶ መተኛት ተቻለ። ዘመድም ለጥየቃ
ሲመጣ በሩቅ የእጅ ሰላምታ መስጠት ጀመርን። ሌላው ቢቀር በሕይወት
መኖራችን ታወቀ። በድብቅ የምናስገባቸውን ጋዜጣ፣ መጽሐፍ፣ መድኃኒትና
ሌሎች ቁሳቁሶች በይፋ ማስገባት ጀመርን። በአጠቃላይ የእስሩ ሁኔታ ከ1970
ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ እየቀለለ መጣ። ነገር ግን የመሞት ስጋቱ አሁንም
እስረኛውን አለቀቀውም ነበር።

ቀደም ብሎ በድብቅ በመከራ የምናስገባቸው የሚዋጡ እንክብሎች፣
የቁስል ማጠቢያ መድኃኒቶችና ፋሻዎች በይፋ ይገቡ ጀመር። የተጎዱ
እስረኞችን በመርዳት በኩል ወ.ገ. ቁስላቸውን ሳይጠየፍ በማጠብና የተነገረውን
በማድረግ በኩል ያሳይ የነበረው ርህራሔ ምንጊዜም አይረሳም። ለሕክምናው
ተግባር ተክልዬ ቢቀርብም በእግሩ ቁስል አለመዳን ምክንያት እንደልቡ
መንቀሳቀስ ስለማይችል ወ.ገ. እሱን ተክቶ እርዳታ ይሰጥ ነበር። ስለ ሕክምና
ሲነሳ በአሳሪዎቻችን በኩል አንድ በቀበሌው ነዋሪ የሆነ የማዕከላዊ እዝ
ሆስፒታል የሕክምና ባለሙያ አንዳንድ ጊዜ እየመጣ የእስረኛውን ቁስል
ሳይታጠብና ሳያፀዳዳ የቁስል ማድረቂያ ከሚቀባ በስተቀር ሌላ እርዳታ ለማንም
ተደርጎ አያውቅም። ይህንንም አሳሪዎቻችን የሚያደርጉት እስረኞች
ከመገደላቸው በፊት ቁስላቸው ተልቶ እንዳይሸትና እንዳይረብሻቸው የፈጠሩት
ብልሃት እንጅ እርዳታ በመስጠቱ እምነውበት አልነበረም። ምክንያቱም ከ8-9
ወራት የእግራቸው ቁስል ሳይጠግ በመጀመሪያ በሰው ድጋፍ ከዚያም
እየተንፏቀቁ ስንቶች ሲሰቃዩ ተገቢ የሕክምና እርዳታ እንዲያገኙ ባደረጉ ነበር።

የሶደሬ የእስር ሁኔታ መቀያየር የጊዜውን የፖለቲካ ሁኔታ
ተለዋዋጭነት ያመለክታል። ደርግና በደርግ ዙሪያ የነበሩት ድርጅቶች አንድ
ወጥ ባለመሆናቸው የቀይ ሽብሩን ሁኔታ የሚመለከቱት በራሳቸው የፖለቲካ
ጥቅም አኳያ ነበር። ቀይ ሽብር ሲጀመር ሁሉም በአንድ ነገር ማለትም
ኢሕአፓን በመምታት፣ መዋቅሩን በማፈራረስና በማዳከም ስምምነት
ነበራቸው። ነገር ግን በሂደት አንዳንዶች ያለሙት ባለመሳካቱ እየተለያዩና
አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ማሴሩ ይፋ እየወጣ መጣ። በዚህ የተነሳ እርስ
በርሳቸው የተጧጧፈው ሹኩቻ በጋራ ጠላቶቻቸው ላይ መጠነኛ እፎይታ
ሊያወርድ ቻለ። የቀይ ሽብርም እርምጃ ጋብ ሊል ቻለ። ቢሆንም በድርጅቶች
መካከል የነበረው ፉክክር ከአንዱ ወደ አንዱ እየተሸጋገረ ከህብረተሰቡም ጋር
የነበረው ቅራኔ ውስብስብ እየሆነ ስለመጣ ደርግ የቀይ ሽብርን ሙሉ በሙሉ
ሳያጥፍ እንደማስፈራሪያ ይጠቀምበት ጀመር። ስለዚህ የቀይ ሽብር ደረጃ
በደረጃ አድጎና ገርጅፎ ቢቀንስም ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ ደርግ እስከወደቀበት
ድረስ ሙሉ በሙሉ ተነስቶ ነበር ማለት አይቻልም።

1.5 የመጨረሻዎቹ የሰደራ የእስር ሁኔታ

በሰደራ፣ በአዳራሽና በሴቶች ክፍል የነበሩት እስረኞች ደረጃ በደረጃ ከፍተኛ እየተወሰዱ «የፖለቲካ ንቃት» እየተሰጣቸው ሲፈቱ ጥቂት ብቻ ቀረን:: ከቀረነው መካከል በዛ ያልነው የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች ስንሆን አራት የመኢሶን ደጋፊዎች አብረውን ነበሩ:: በዚህ ጊዜ ሴትና ወንዱ ተደባልቆ በግቢው ውስጥ ሲንሸራሸር፣ ኳስ ሲጫወትና በቤትም ውስጥ ባሉት መጫዎቻዎች ሲዝናና ይውላል:: ከሴት እስረኞች የቀሩት ጽ.ደ. እና መጨረሻ የታሰረችው ዘ.ወ. ብቻ ነበሩ:: አብረው ከወንዶች ጋር ሲጫወቱና ምግብም አብረው ተመግበው ካመሹ በኋላ ሲመሽ መኝታ ክፍላቸው ሄደው ይተኙ ነበር:: ጽ.ደ. ባላቤቷ ተፈቶ እሷ ብትቀርም ለህጻናት ልጆቻችን እንኳን እንዳችን ዳንን እያለች የምታሳየው ቆራጥነት የሚደነቅ ነበር::

ከአሳሪዎቻችንም በኩል የነበረው ጣልቃ ገብነት በጣም ቀነሰ:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ መኖራችንንም አረስተው በራሳቸው የማናውቀው ጊዜያዊ ችግር የተጠመዱ ይመስሉ ነበር:: አዲስ እስረኛ መምጣት ካቆመ ቆይቷል:: አኛ ብቻ ይጠብቃሉ:: የውጪ ጠያቂም ካለፈው ጊዜ በተሻለ ይጎበኘናል፣ መቀራረብ ባይኖርም ከሩቅ መኖራችንን አረጋግጦ ይሄዳል:: የሚያስገቡት የቆዩ እስረኞች ወይም ሴቶች ነበሩ:: አሁንም ሁኔታው ከበፊት ጀምሮ ጠያቂ የሚያመጣውን ስንቅና ልብስ ከተፈተሸ በኋላ ባይለወጥም ምግብ አመላላሽ የነበሩት ጽ.ደ. እና ዘ.ወ. ከቤት ዘመዶቻችን ጋር በቀላሉ ለመተዋወቅና መልእክት ይዘው ለመምጣት ቻሉ:: ያለነው ጥቂት እስረኞች በመሆናችን ዘወትር እየመጡ የሚጠይቁንን ሰዎች ለማጥናት ጊዜም አልፈጀባቸው:: ቤተ ዘመድ ሲመጣ የት ቦታ ብንቆም ለአይታ እንደሚያመች ስለሚነግሩን በቀላሉ የእጅ ሰላምታ ለመለዋወጥ ቻልን:: አንዳንድ ጊዜ ብቻ የቀበሌው ሊቀመንበር የነበረው ከስተ አብራኒዮስ ድንገት ከተፍ ካለ አብዛኛው እስረኛ፣ ዕቃ የሚያመላልሱትና ከውጪም ጠያቂ የሆነው ቤተ ዘመድ መደንገጣቸው አይቀርም ነበር::

ከውጪ ጠያቂዎቻችን ምግብ፣ ልብስ፣ ሲጋራ፣ ገንዘብና ሌሎችም ነገሮች ይልኩልናል:: አሁን ካለፈ በኋላ ከቤተ ዘመድም ሆነ ከጓደኞቻችን የተደረገልንን ድጋፍ ከማማስገን በስተቀር ውለታቸውን የምንከፍልበት መንገድ ባይኖርም ለየት ያሉ አጋጣሚዎችን ግን እዚህ ላይ ማስታወስ ያስፈልጋል:: አቅመ ደካማ የሆኑት በምርኩዝ ድጋፍ የሚራመዱት እናት አባቶቻችን ከአዲስ አበባ ውጪ ከርቀት እየተመላለሱ ሲጠይቁን በጣም እናዝን ነበር:: በዚህ አድሜያቸው እኛ አነሱን መርዳት ሲገባን የወላጅ አንጀት አልችል ብሏቸው እኛን ለማየት መጥተው በቅርብ ሳናናግራቸው መመለሳቸው በጣም ይቆረቁረን ነበር::

በጊዜው የቀይ ሽብር አርምጃ በሰዎች ላይ ሽብር ለቆባቸው እንደነበረ ይታወቃል:: እስሩም ግድያውም በጅምላ የሚካሄድ ስለነበረ ሁሉም ለራሱ በሚል ይሰጋል:: ማንም ራሱን ለችግር ማጋለጥ አይፈልግም:: የጅምላው አስርና ግድያ እንዱ አላማም የፖለቲካ ተሳትፎ ያለውን ብቻ ለማንበርከክ ሳይሆን በሌላውም ላይ ፍርሃት ለመልቀቅ መሆኑ አይጠረጠርም:: አንዳንዶች ግን ይህን ማስፈራራት ከምንም ሳይቆጥሩ ከኛ ጎን ቆመዋል:: ተክልዬ ሲታሰር ለአብድ ውሻ በሽታ ተጋልጦ መከላከያ ክትባት እየወሰደ እንደነበር ከዚህ በፊት

በምዕራፍ ሦስት ተጠቅሷል። በዚህም የተነሳ ደብረ ዘይት ያሉት የሙያ ባልደረቦቹ በእስር ላይ እያለ ተጨማሪ ክትባቱን እንዲወጋና እንዲጨርስ ከሰተን እንዲፈቅድ ቢጠይቁት ለዚህ ፀረ አብዮተኛ ርህራሄ የለኝም በሚል እንደከለከላቸው ጊዜው ካለፈ በኋላ ልንረዳ ችለናል። ከሰተ ረዳት የእንስሳት ሐኪም በመሆኑ የበሽታውን አደገኛነት ጠንቅቆ ያውቃል። አንድ እስረኛ በፍርድ እርምጃ እስኪወሰድበት ድረስ መሰረታዊ መብቱ መነካት የለበትም። ታዲያ እንዴት ተደርጎ እንዲህ አይነት ጥያቄ ሲቀርብለት ከሰተ አሻፈረኝ ሊል ቻለ? በጣም የሚገርመው ክትባት እንዳይወጋ የተነፈገው ሰውዬ በእስር ላይ እያለ ያስተማራቸውን ተማሪዎች ፈተና አውጥቶ እንዲፈትን ተጠይቆ ከእስር ቤት ሳይወጣ ፈተና አዘጋጅቶ ፈትኗል። አንዳንድ ተማሪዎቹም በመልስ መስጫ ወረቀታቸው ላይ የመልካም ምኞት መግለጫና የእግዚአብሔር በደህና ያስፈታህ መልዕክት ልከውለታል።

በፊት እስረኛው እየተገደደ የሚያዜመው መዝሙርና የሚያካሂደው የፖለቲካ ንቃት ውይይት ምን መልክ እየያዘ እንደመጣ እዚህ ላይ መጠቀስ ይገባዋል። አንዳንዶቻችን ከመታሰራችን በፊት የኢሕአፓን የመቀስቀሻ መዝሙሮች አናውቅም ነበር። ወጣቱ ግን በደንብ ያውቃቸዋል። ብዙዎቹ ጉሮሮአችን እስኪሰነጠቅ ድረስ ስንዘምራቸው የነበሩት ዜማዎች ግጥማቸው ይቀየር እንጅ የኢሕአፓም የጋራ ዜማዎች መሆናቸውን ወጣቶቹ አሳምረው ያውቁ ስለነበር፣ ለማናውቀው ያስተዋውቁን በፊት በለመዷቸው ግጥምም ይዘምሩልን ጀመር። ከኢሕአፓ ዜማዎች መካከል ያልተወረሰውና እንደተከበረ የቀረው መዝሙር «የትግሉ ነው ህይወቱ» የሚለው ብቻ ነበር። ምናልባት ምንም እስር ላይ ቢሆኑ ዜማውም አባላቱን ይቀሰቅሳል በሚል ተፈርቶ ይሆናል።

የፖለቲካ ልዩነት ያላቸው እስረኞች አንድ ላይ ተሰብስበው ውይይት ያካሂዳሉ ማለት ዘበት ነው። ስለዚህ ቀደም ብሎ አንዳንድ ካድሬዎች ወይም ታማኝ እስረኞች የተዘጋጀ የፖለቲካ ማስተማሪያ ጽሑፍ ሲያነበንቡ ከማዳመጥ በስተቀር ብዙዎቻችን ምንም ተሳትፎ አልነበረንም። አወዛጋቢ ባልሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ሃሳብ መስጠት ይቻል እንደሆነ እንጂ ሌላ ምንም ማድረግ አይቻልም ነበር። ቢሆንም ዝምታውም ሌል ትርጉም እንዳይሰጠው አልፎ አልፎ ማስመሰል ነበረብን። ወደ ኋላ የስር ሆኔታ እየተቀያየረና እየላላ ሲመጣ በአሳሪዎቻችን ግፊት ሲካሄድ የነበረው የፖለቲካ ውይይት ተቋርጦ የራሳችንን የግል ንባብና ምርምር ተያያዝነው። ይህም ማታ ማታ ካልሆነ በስተቀር ታፍነን ስለከረምን ቀን በግቢው ውስጥ ወይም በቤት ውስጥ የሚካሄደው ጨዋታ አብዛኛውን ጊዜ ይወስድ ነበር።

አንድ ቀን እንደ ልማዳችን ሁሉም እስረኛ ተበታትኖ በየፊናው ውጪ ሲጫወት ማንም የሚሰማን የለም በሚል ይሁን ወይም በጅብደኝነት የቀበሌው የአብዮት ጠባቂዎችና የቀይ ሽብር አራማጆች ሰውን በመግደል ምን ያክል የሰከሩ እንደነበሩና ከምንም በላይ ደስታ እንደሚሰጣቸው እርስ በርሳቸው ከሚነጋገሩት ልንገነዘብ ቻልን። በቀይ ሽብር ሲያደርጉ የነበሩትን እርስ በርሳቸው እንደዝና ሲያወሩ ሰማናቸው። የታሰረን ሰው መግደልን እንደ ዝና በመቁጠር «ቀይ ሽብር እኮ ታገደ እንጂ አንድ ሰው ወይም ሁለት ሰዎችን በመግደል አበልጥሃለሁ» እየተባባሉ ሲፏከሩ መስማቱ ለጆሮ የሚቀፍ ነበር። በመገረምና በቃል የሰማነው ስለሆነ እያንዳንዳቸው የገደሉትን ቁጥርና በስንት

እንደሚበላለጡ አሁን በትክክል ማስታወስ ባይቻልም በእነኝህ ሰዎች ግምት ቀይ ሽብርን እንዲያካሂዱ በተሰጣቸው ህጋዊ ስልጣን ማን ከማን የበለጠ መግደሉን አይክዱም፣ አይደብቁም:: ምክንያቱም ደርግ የፈቀደው ህጋዊ አሰራር ነበርና:: እኔ አበልጣለሁ እያተባባሉ ሲፎካከሩ ከነበሩት መካከል የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር የነበረው የሃምሳ አለቃ ኃይለማርያም በአሁን ጊዜ በህይወት ባይኖርም ሌሎቹ ሁለቱ ነጋ በረካና አለሙ ደበሌ በዚያን ጊዜ በሰሩት ወንጀል ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በድጋሚ መታሰራቸውን እንዳንዶቻችን በመገናኛ ብዙሐን ተመልክተናል:: ፍርድ የሚሰጥ ካለ ሥራቸው ያውጣቸው::

ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የእስር ጊዜ የዘለቀ አንድ ነገር ነበር:: ይኸውም አልፎ አልፎ የሚካሄደው የእስረኞች ዝርዝር ምዝገባ አለመቋረጥ ነበር:: ይህ እንደ ዕቃ ዝርዝር የእስረኛ ምዝገባ ከርቸሌም ተከትሎን ዘልቋል:: ምዝገባው በየዕለቱ ከሚካሄደው የእስረኛ ቆጠራ በተጨማሪ የሚከናወን ነበር:: በዚህ መሰል ምዝገባ የሚያልቀው ወረቀት የአንድ መሥሪያ ቤትን የወረቀት የዓመት ባጀት ሳይሸፍን አይቀርም:: ምናልባትም ያለውን የእስረኛ ዝርዝር ከማወቅ ባሻገር የሚፈለግ እስረኛ የት እንዳለ ለመከታተል፣ የተለያዩ ጥቆማዎችን ለማገናኘትና የተደበቁ እስረኞችን ለማጋለጥ ያገለግል ይሆናል:: ይህም ቢሆን በኮምፒዩተር የተደራጀ ካልሆነ ለማመሳከር ያስቸግራል:: ከዚህ ይልቅ በግለሰብ ደረጃ ሲደረግ የነበረው ማመሳከር ደርግን የበለጠ ጠቅሞታል:: አንዳንድ በከፍተኛ የአመራር ደረጃ የነበሩ የድርጅት አባላት በአንዳንድ ቀበሌና ከፍተኛ የታሰሩትን ማንነት ከማረጋገጥ አልፈው ከርቸሌም ተወስደው ያልተጋለጡ የኢሕአፓ አባላት መኖር አለመኖራቸውን እንዲሰልሉና እንዲያረጋግጡ ተደርገዋል:: ደርግ የሚተባበረውን ቀንደኛ አባል የሚጠቀምበት መንገዱ ብዙ ነበር:: ከተጠቀመባቸው በኋላ ከከርቸሌ ተወስደው ሌላ እስር ቤት ቆይታ አድርገው ወይ ይፈታሉ አለበለዚያም ይመታሉ:: (11)

የእስረኛውን ዝርዝር በየጊዜው ከመመዝገብ ባሻገር አሳሪዎቻችን ሲላቸው እንደገና ቃል ስጡ ማለትም የተለመደ አሰራራቸው ነበር:: ለዚህ የሚሰጡት ምክንያት ብዙ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ የሰጣችሁት ቃል ጠፋ ወይም ተጨማሪ ጥቆማ መጣባችሁ እያሉ ማስፈራራትን ይጠቀማሉ:: በመጨረሻው የሶደሬ ቆይታችን እንኳን ሁለት ተዘዋዋሪ የደርግ መርማሪዎች መጥተው ቃል እንድንሰጥ ተደርገናል:: በዚህ ጊዜ ተዘዋዋሪ የደርግ መርማሪዎች የተሰማሩት በሁሉም የአዲስ አበባ ከፍተኛ እስር ቤቶች ነበር:: በየከፍተኛው እየተዘዋወሩ ቃል ከተቀበሉት የደርግ መርማሪዎች መካከል ካሣሁን፣ ባድማ፣ ባሳዝነውና ሌሎችም ነበሩበት::

የደርግ አሰራሩ ዝብርቅርቅ በመሆኑ ለምን ዘዋሪ መርማሪዎች እንደተላኩ መገመት ያስቸግራል:: ምናልባት ይህ ሊደረግ የቻለው ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ታስሮ ከተገደለ በኃላ ከሱ ጋር ግኑኝነት የነበራቸው ከፍተኞች እምነት ሳይጣልባቸው ስለቀረ ሊሆን ይችላል:: እንዲያውም በዚሁ ጊዜ የሱ ተባባሪ የነበሩት ከነገ ዛሬ እንታሰራለን እያሉ ስጋቱ ሰውነታቸውን ጨርሶት ነበር:: ደርግም እነሱን በቁጥጥር ስር ለማዋል እንዳቆበቆበ ይታወቃል:: የኛ ከፍተኛ አሳሪዎችም የዚሁ ስጋትና ፍራቻ እንደነበራቸው ቢታወቅም እስከ አሁን ከመደንገጣቸውና ጥጋባቸው ጋብ ከማለቱ በስተቀር በይፋ ያጋጠመ ምንም ነገር አልነበረም:: በዚህ ሁኔታ እያለን ነበር ከሶደሬ ወደ ከርቸሌ እስር ቤት ከደርግ በመጣ ትዕዛዝ የተዛወርነው:: ከርቸሌ የተዛወርነው የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች ሁለት ሴቶችና አስር ወንዶች በድምሩ 12 ስንሆን የመኢሶን

ደጋፊዎች ደግሞ አራት ወንዶች ብቻ ነበሩ:: ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ከኢሕአፓ
ደጋፊ እስረኞች መካከል ነ.ሰ. ከሶደሬ ወደ ከፍተኛ 22 ከዚያም ወደ ደርግ
ጽ/ቤት ተወስዶ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ በጥቅምት ወር 1971 ዓ.ም. ከርቸሌ
ተልኳል::

2. እስር በሌሎች እስር ቤቶች

በአገሪቷ በሞላ ሶደሬን መሰልና ከሶደሬም የባሱ የተለያዩ እስር ቤቶች
በቀይ ሽብር ጊዜ ይገኙ ነበር:: የነኝህን የእያንዳንዱን እስር ቤቶች እዚህ ላይ
መዘርዘር ባይቻልም በጅምላ እንዴት በደርግ እንደተቋቋሙ፣ በማን
እንደሚመሩና ሰቆቃው ምን እንደሚመስል ባጭሩ ለመግለፅ ተሞክሯል::

ደርግ የሕግ የበላይነትን ስለማይቀበል ተቀዋሚዎች የሚላቸውን
በሕግ አግባብና በፍርድ ቤት ከመቅጣት ይልቅ ሰዎችን ለመጨፍጨፍ
እንዲያመቸው በተለያየ ጊዜ የተለያዩ መግለጫዎችን፣ መመሪያዎችን፣
የመንጥር ዘመቻ ትዕዛዞችንና አዋጆችን ይጠቀም ነበር:: በመጀመሪያ መስከረም
1969 ዓ.ም. የነደፈውን ኢሕአፓን የማጋለጥና የማጥፋት ዘመቻ በመጋቢት 9
1969 ዓ.ም. ባስተላለፈው የዘመቻ መንጥር ትዕዛዝ አጠናከረ:: ሌሎች የዘመቻ
መንጥር ትዕዛዞችም በተከታታይ ተላልፈዋል:: ከዚያም ነሐሴ 21 ቀን 1969
ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 129 «ብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ» የሚል የአፈና
ተቋም አቋቋመ:: ምንም እንኳን ይህ አዋጅ ለክፍለ አገር፣ አውራጃ፣ የከተማ
ነዋሪዎች ማህበር፣ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ አጠቃላይ
ምክር ቤት፣ የፖሊስና የጦር ክፍሎች የአብዮታዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ
(አዘአኮ) እያቋቋመ ፀረ አብዮት፣ ፀረ አንድነትና ፀረ ልማት የሚፈፅሙ
ግለሰቦችን እያደኑ ከሦስት እስከ ስድስት ወር የማሰርና አስተማማኝ መረጃ
ካገኙም ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ ቢያመለክትም በአፈፃፀም
ግን በየደረጃው የተዋቀሩት አዘአኮ የቀይ ሽብር እርምጃ በሥልጣናቸው ያካሂዱ
እንደነበረ ነው:: አዘአኮ የሚፈለግባቸው የቀይ ሽብር እርምጃ ከወሰዱ በኋላ
የገደሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር ማሳወቅና በቁጥጥር ላይ ያዋሉትን እስረኛ
ብዛት ለደርግ ማሳወቅ ነበር::

ከዚህ አዋጅ በፊት የነበሩት እስር ቤቶች እንደ ደርግ ምርመራ፣
ማዕከላዊ፣ የፖሊስ ወንጀል ምርመራና ሌሎች በእነሱ ስር የነበሩትም
ሥራቸውን የሚያከናውኑት ለደርግ እያሳወቁና እያስወሰኑ ነበር:: ከአዋጁ በኋላ
የተቋቋሙት እስር ቤቶች ግን በራሳቸው አብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ
እየተመሩ የራሳቸውን የቀይ ሽብር እርምጃ ለመወሰድ እንዲያመቻቸው
አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ:: በዚህ የተነሳ በከተማ ነዋሪዎች ማህበር
(ከፍተኛና ቀበሌ)፣ በአርሶ አደሮች (አውራጃና ወረዳ)፣ በክፍላተአገር፣ በከተማ
ልማትና ቤት ሚኒስቴር፣ በአዲስ አበባ አጠቃላይ ምክር ቤት፣ በተለየዩ የጦር
ክፍሎች፣ በሌሎችም ድርጅቶች እስር ቤቶች ተስፋፉ:: ከፖሊስ ሠራዊትና
ከሌሎች ወታደራዊ ክፍሎች ጋር በመተባበርና በቅንጅት እንዲሰሩ ተወሰነ::

ይህንንም ተከትሎ በአገሪቷ በሞላ እስር ቤቶች እንደ አሸን
እንደተስፋፉ ዝቅ ብሎ ቀርቧል:: ከፍ ብሎ እንደተገለፀውም እርምጃቸውን
ለበላይ ማሳወቅ ሳያስፈልገቸው በራሳቸው ኮሚቴ በመወሰን ማሰር፣
መመርመርና መግደል ወይም መፍታት ይቻላቸው ጀመር:: አስፈላጊ ሆኖ

ሲገኝ ብቻ አስረኛ ለከፍተኛ ምርመራ በተለይም ወደ ደርግ ምርመራ ክፍልና ወደ ማዕከላዊ ይልኩ ነበር::

2.1 የእስር ቤቶች መበርከት

ደርግ አፍላ የቀይ ሽብር በሚያካሂድበት በ1970 ዓ.ም. ብዛት ያላቸው እስረኞች በአገሪቷ በሞላ በነበሩት እስር ቤቶች ታስረው እንደነበረ ይታወቃል:: በዚህ የተነሳ በጊዜው የነበሩት የእስር ቤቶች ቁጥር ከትምህርት ቤቶች ወይም ከፍርድ ቤቶች ቢበልጥ እንጅ አያንስም ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ቀደም ብሎ ከሚታወቁት መደበኛ ወህኒ ቤቶችና የፖሊስ ጣቢያዎች በተጨማሪ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች ጽ/ቤቶች፣ የወታደር ካምፖች፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የማምረቻ ድርጅቶች፣ የቤተ መንግሥቶችና አንዳንድ የትምህርት ቤቶችም ጭምር በእስር ቤትነት አገልግለዋል::

ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከተማ በነበሩት በሃያ አምስቱም ከፍተኞች በአንዳንዶቹ በስራቸው በሚገኙት ቀበሌዎችም ጭምር፣ በተለያዩ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ በአራተኛ ክፍለ ጦር፣ «በሚሊተሪ» ፖሊስ፣ የደርግ ጽ/ቤት በነበረው በምኒልክ ቤተ መንግሥት፣ በማዕከላዊ፣ በልዩ ወንጀል ምርመራ፣ በቃሊቲና በከርቸሌ ወህኒ ቤቶች በሞላ የፖለቲካም ሆነ ሌሎች እስረኞች ይታጎሩባቸው ነበር:: በተጨማሪም ሌሎች ከኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች የተወረሱት ስውር ትላልቅ ቤቶች እንደ «ቤርሙዳ» (Bermuda) በሚል መጠሪያ በከፍተኛ 23 የሚታወቀውና የልዑል አሥራተ ካሣ ቤት የነበረው አንደ ድብቅ እስር ቤቶች አገልግለዋል::

በርከት ያሉ የላብ አደር ሠራተኞች የነበሯቸው አንዳንድ ፋብሪካ ዎችም የራሳቸው ጊዜያዊ ማቆያ እስር ቤቶች እንደነበሯቸው ይታወቃል:: የከተማ ልማት ሚኒስትር የነበረው አቶ ዳንኤል ታደሰ በዋና መሥሪያ ቤቱ የፎቅ ህንጻ ስር በሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ከመሬት በታች (Sub-basement) የራሱ እስር ቤት ነበረው:: በዚህ እስር ቤት የተለያዩ የመሥሪያ ቤቱን አባላት አያሰረ ሲያሰቃይ የነበረው የከተማ ልማት ኦዲትና እንስፔክሺን አገልግሎት ኃላፊ ሻለቃ ሮንዴሳ ቢራቱ (የመሥሪያ ቤቱ የመለዮ ለባሽ ተወካይም ነበር) የሚረሳ አይደለም:: (12)

የከተማ ልማት መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ በተቋቋሙት የከፍተኞች የቀይ ሽብር ኮሚቴዎች በሞላ ከመወከልና ከማስፈጸም አልፎ የራሱም እስር ቤት ነበረው ማለት ነው:: ለግንዛቤም እንዲረዳን በዚያን ጊዜ የነበሩት የከፍተኞች የቀይ ሽብር ኮሚቴዎች ወይም በራሳቸው አጠራር «የአብዮታዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች» የሚዋቀሩት 1) ከቀበሌዎችና ከከፍተኞች ሊቀመናብርት፣ 2) ከሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት፣ 3) ከከተማ ልማት መሥሪያ ቤት፣ 4) ከመላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር፣ 5) ከኢማሌድህ፣ 6) ከፖሊስ ሠራዊት፣ 7) ከአብዮት ጥበቃና 8) አንዳንድ ቦታም ከመከላከያ ሠራዊት በተወጣጡ ተወካዮች ነበር:: ከእነኝህ ተቋማት የሚወከሉት ግለሰቦች የጊዜው የፖለቲካ ቡድኖች አባላት እንደነበሩም መገመት አያዳግትም::

የከተማ ልማት ከነማትን በማጠናከር በቀይ ሽብር እንዲሳተፉ አድርጓል:: በ1969 ዓ.ም. የከፍተኛና የቀበሌ አብዮት ጥበቃዎችን በመሳሪያ

በማስታጠቅና «ፀረ አብዮተኞችን» እንዲመነጥሩ መመሪያ በመስጠት የመኢሶን አመራርና የአዲስ አበባ የሕዝብ ድርጅት ኃላፊ ከበደ መንገሻ፣ የመኢሶን ከፍተኛ አመራርና የከተማ ልማት ሚኒስቴር የማህበራት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ አበራ የማነአብና ሻለቃ ሮንዴሳ ቢራቱ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

የዚህ የቀይ ሽብር ኮሚቴ አወቃቀርና አሰራር ከላይ የስርአቱን አራማጆችና ከታች የድርጊቱን አስፈጻሚዎች መተሳሰር ያመለክታል። ይህም በመሆኑ በጊዜው ሰዎች እንዲታሰሩም ሆነ እንዲገደሉ የሚወስኑት ኮሚቴዎችም ሆነ ከላይ ሆነው እነኝህን ኮሚቴዎች የሚያዋቅሩት በሞላ በቀይ ሽብር ወንጀለኝነት ተጠያቂዎች ናቸው። ከቀይ ሽብር ኮሚቴዎችም ሌላ በየመሥሪያ ቤቱ የሚገኙት ካድሬዎችና የኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅቶች ማንኛውንም የጠረጠሩትን የመሥሪያ ቤታቸውን ባልደረባ ማሳሰር፣ ማስገረፍና ማስገደል ይችሉ ነበር። (13) በተለይም እነኝህ ካድሬዎች ተደራቢ የቀበሌ ወይም የከፍተኛ ሊቀመንበርነት ሥልጣን ካላቸው የጊዜው ንጉሦች ነበሩ።

ከአዲስ አበባ ውጪ የነበረውን ሁኔታ ከዚህ የተለየ ባያደርገውም በዚህ ተጨማሪ የእስር ቤቶችን አስፈላጊነት የታሳሪው ብዛት ይወስነው ነበር። በዚህ የተነሳ በአንዳንድ እስረኞች በበዙባቸው ከተማዎች የከተማ ነዋሪዎች ጽ/ቤቶችና በገጠርም የገበሬ ማህበራት ቢሮዎች ለእስር ቤት አገልግሎት ውለዋል። ይህ እንግዲህ ከመደበኛ የፖሊስ ጣቢያዎችና ከነባር የወህኒ ቤቶች በተጨማሪ ወደ ጊዜያዊ እስር ቤትነት የተለወጡትን ተቋማት ብዛት ያመለክታል። የአካባቢው ፀጥታ የደፈረሰና አስቸጋሪ በነበረባቸው በኤርትራ፣ በትግራይ፣ በጎንደር፣ በሐረርና በሲዳሞ አብዛኛው እስረኞች የሚታሰሩትና የሚጠበቁት በወታደራዊ ካምፖች ነበር። ከእነኝሁ አስቸጋሪ የፀጥታ ክልሎች እስረኞች ለከፍተኛ ምርመራና ለተሻለ ጥበቃ ወደ አዲስ አበባ ይላኩ ነበር።

2.2 የቀይ ሽብር ሰቆቃ

ለመሆኑ የነኝህ ሁሉ እስር ቤቶች አመጣጥና እድገት እንዴት ነበር? ቀይ ሽብር በይፋ ተዋናዮቹስ እነማን ነበሩ? ሰቆቃውስ እንዴት ተፈጸመ? ከመጀመሩ በፊት አብዛኛው የፖለቲካ እስረኞች የቀድሞ የኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች እንደነበሩ ይገመታል። ከዚያም ትግሉ ውስብስብ እየሆነ ከደርግም ጋር የነበረው ፍጥጫ በየጊዜው እየጨመረ ሲመጣ የታሳሪዎቹ ዓይነትና ብዛትም እየበረከተ መጣ። በዚህ የተነሳ እስር ቤቶችም እየተጣበቡ የምርመራው ስልትም ጭካኔ እየተሞላበት መጣ። በማዕከላዊና በደርግ ጽ/ቤት የሚካሄደው አሰቃቂ ምርመራ፣ ግፍ የተሞላበት ድብደባና ግድያ ደረጃ በደረጃ እያደገ መጣ። ደርግ ተቀዋሚ የሚላቸውን በቁጥጥር ስር የዋሉ እስረኞች ማታ ማታ እያወጣ መረሸኑን ቀጠለበት። ሆኖም ይህ ድርጊት ከህዝብ የሚቀርብበትን ተቃውሞ ሊገታው አልቻለም። እስሩና ግድያው በጨመረ ቁጥር የህዝቡ ተቃውሞ በአዲስ አበባም ሆነ በየክፍለ አገሩ እያየለ መጣ። በየአካባቢው የሚካሄደው የፖለቲካ ተቃውሞና ሰላማዊ ሰልፍ የእስሩን፣ የምርመራውን፣ የግድያውንና በአጠቃላይ ደርግ የሚፈጽመውን የወንጀል መጠን ከልክ በላይ አበራከተው።

የነበረው ፍጥጫ በጣም ሲካረር ደርግ ተቀዋሚዎችን ከህብረተሰቡ መንጥሮ ለማውጣት የጅምላ እስር፣ ነፃ እርምጃ፣ የመንጥር ዘመቻና

ተደጋጋሚ አሰሳ አካሄደ:: በተለይም በደርግ ውስጥ የነበረው መከፋፈል በአክራሪዎቹ የመንግሥቱ ኃይለማርያም ቡድን አሸናፊነት ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. ከተጠናቀቀ በኋላ ጥቃቱ በጣም ጨመረ:: ከዚያም በ1970 ዓ.ም. የተለያዩ ማጠናከሪያ መመሪያዎች እየታከሉበት ዋናው የቀይ ሽብር ሰቆቃ ተካሄደ:: በዚህ ድርጊት ማንኛውም ከደርግ ወገን የቆመ ሁሉ የአብዮቱ ተቀዋሚዎች ተብለው የተፈረጁትን ኢሕአፓን፣ ኢዴህንና ጀበሐን በማሰርና በመግደል የፈለገውን እርምጃ እንዲወስድ በተፈቀደው(14) መሰረት የከነማ፣ የመኢገማ፣ የፖሊስና የወታደሩ ክፍል ከባድ ጉዳት አድርሰዋል:: ኢሕአፓም ይህንን አስከፊ የሽብር እርምጃ ለመቋቋም ቢሞክርም አቃተው::

በዚህ ፍጥጫ የአብዮቱ ጠላት በመባል የተፈረጁት ወገኖች ደጋፊዎቻቸው ከፍተኛ ቁጥር ስለነበራቸው ተጨማሪ እስር ቤቶች በግድ አስፈለጉ:: እነሱንም ለማደንና በቁጥጥር ስር ለማዋል ከተለመደው የፀጥታ አስከባሪዎች ሌላ በከተማና በገጠር የሚገኙ የቀበሌና የገበሬ ማህበራት በቀይ ሽብር ዘመቻ እንዲሳተፉ የታጠቁ አብዮት ጠባቂዎችን መመልመል በስፋት ተያያዙት:: ነገር ግን የነሱ መዋቅሮች ለዚህ የተዘጋጁ ስላልነበሩ በጊዜው የነበራቸውን ጽ/ቤቶች፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ የህብረት ሱቆች፣ ወዘተ. ለዚህ ተግባር ለማዋል ተገደዱ:: አንዳንዶች የይድረስ የይድረስ ጊዜያዊ እስር ቤቶችና መጠለያዎች አሰሩ:: በጣም የተቸገሩት ደግሞ በድንኳንና በዛፍ ጥላ ስር እስረኞችን ለማሰር ተገደዱ::

ደርግ ጠመንጃና ጥይት ከሶቬት ህብረት በገፍ ስለሚያገኝ የኢሕአፓ አባላትን ለማሳደድና ለመግድል የከተማም ሆነ የገበሬ ማህበራትን ለማስታጠቅ ችግር አልነበረበትም:: በዚህ መልክ በአዲስ አበባ ከተማ ከ1969 ዓ.ም. መጨረሻ በኋላ በሃያ አምስቱም ከፍተኞች የእስር ቤቶች ሊዘጋጁ ቻሉ:: በ1970 ዓ.ም. በአብዛኛው የቀበሌዎችና የከፍተኞች የሥራ እንቅስቃሴ የኢሕአፓ አባላትን ማሳደድና ማሰር፣ ከተያዙም በኋላ ቁም ስቅላቸውን በምርመራ ማዋከብ ከዚያም በጅምላ እያወጡ በየአደባባዩ በቀይ ሽብር መረሸን ሆነ:: ለመያዝ አደገኛ ተብለው የተጠረጠሩትን ከሩቅ በአነጣጣሪ ተኳሾች በየአደባባዩ መግደል ነፃ ርምጃ የሚል ስያሜ ተሰጠው:: በአንዳንድ ቦታ የነፃ እርምጃ የሚፈጽሙት የሰለጠኑ ፀጥታ አስከባሪዎች ከወታደሩ ክፍል የተመለመሉ ገዳዮች ነበሩ:: (15)

በጊዜው በመቶዎች የሚቆጠሩ የሚፈለጉ «ፀረ አብዮተኞችን» ያያቸው ሁሉ እንዲጠቁም በመላው አዲስ አበባ ፎቶግራፋቸው ተለጥፎ እየታደሉ ነበር:: ከእነኝህ መካከል ከ70% በላይ የሚሆኑት የኢሕአፓ አባላት ሲሆኑ በተገኙበት ቦታ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ስለተላለፈ በአንጃዎች ጠቋሚነት በነፃ እርምጃ ብዙዎች ተረሽነዋል:: በአ/አ ከተማ በተደጋጋሚ በተካሄዱት አሰሳዎች እነዚህ የሚፈለጉ ግለሰቦችና ሌሎች የነፃ እርምጃ ኢላማዎች ሆነዋል::

የሁሉም ከፍተኞችና እስር ቤቶች የቀይ ሽብር አሰራር ይመሳሰላል:: ቀደም ብሎ በከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 በሚገኘው ሶደሬ በሚባለው እስር ቤት እንደተገለጸው ይነስ ይብዛም በሁሉም የአዲስ አበባ ከፍተኞች ተመሳሳይ ድርጊቶች ተፈጽመዋል:: በዚያን ጊዜ በከፍተኛ 25 እስር ቤት የተፈጸመውን የግፍ እርምጃ በመዘርዘር «የሰቆቃ ትውስታ ከ22 ዓመት በኋላ» በሚል አንድ የሽብሩ ሰለባና የአይን ምስክር በጦማር ጋዜጣ ላይ አቅርቦታል:: (16) በከፍተኛ 1፣ ከፍተኛ 2፣ ከፍተኛ 4፣ ከፍተኛ 5፣ ከፍተኛ 7፣ ከፍተኛ 8፣ ከፍተኛ 9፣

ከፍተኛ 12፣ ከፍተኛ 14፣ ከፍተኛ 15፣ ከፍተኛ 16፣ ከፍተኛ 18፣ ከፍተኛ 21፣ ከፍተኛ 22፣ ከፍተኛ 23፣ ከፍተኛ 25፣ ወዘተ. ከዚህ ድርጊት የማይተናነስ ተፈጽሟል። በማዕከላዊና በደርግ ጽ/ቤትም በምርመራ ጊዜ እግርን እስከ መቁረጥና ጥፍርን እስከመንቀል ድረስ ተደርሷል። (17)

የደርግ እስር ቤቶች የግፍ የምርመራ ዘዴዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሰዋል። ከእነኝህም መካከል ሰውነትን በእሳት ማቃጠል፣ በፈላ ውሃና ዘይት መጥበስ፣ በወረንጦ ጥፍር መንቀል፣ በፋስ የእግር ጣት መቁረጥ፣ በአፍ ውስጥ ኳስ መክተት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል መንዘር፣ ለብዙ ሰዓት ያለማቋረጥ መግረፍ፣ ለብዙ ሰዓት ዘቅዝቆ መስቀል፣ በእጅም ሆነ በገመድ አንቆ መግደል፣ በውሃ የተሞላ በርሜል ውስጥ መዝፈቅ፣ ሌሎች ሌሎችም የጭካኔ ተግባራት በተለያዩ እስር ቤቶች ተፈፅመዋል። ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪም በየክፍላተ አገሩና በየአውራጃው የተፈጸመው ስቃ ይህንኑ የሚመስል ነበር።

በምርመራ ጊዜ ከሚካሄደው ሰቆቃ በተጨማሪ የቀይ ሽብር ግድያውም ግፍ የተቀላቀለበት ነበር። ከተለመደው በጥይት ደብድቦ ከመግደል ሌላ ለብዙ ሰዓታት በምርመራ አሰቃይቶ እንዲሞት ማድረግ፣ በእጅና በገመድ አንቆ መግደል፣ ወንዝ ውስጥ ወርውሮ ውሃ እንዲወስደው ወይም አዞ እንዲበላው ማድረግ፣ በመርዝ መግደል፣ ነፍስ ሳይወጣ መቅበርና ሌሎች የተለያዩ የግድያ ዘዴዎች ይካሄዱ ነበር። ኦሞ ወንዝ ከነህይወታቸው ተጥለው በውሃ የተወሰዱና በአዞ የተበሉትን 1. ስለሺ አበራ፣ 2. ጥላሁን ኃይሉ፣ 3. ጴጥሮስ ፈረደ፣ 4. ወንድሙ በቀለ፣ 5. ተስፋዬ አግደው፣ 6. በቀለ ከበደና 7. ኢንጅነር ፀጋዬን እዚህ ላይ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ሰዎችን ከገደሉ በኋላ ዘመድ አዝማድንና ህብረተሰቡን ለማስፈራራትና መቀጣጫ ለማድረግ አስከሬኖች ላይ «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚል ፅሁፍ በመለጠፍ ለትርኢት በየቦታው መጣል፣ ቤተዘመድና ሌሎች ሰዎች እየረገጧቸው እንዲያልፉ ማድረግ፣ በመኪና መጎተት፣ በየቦታው ጥሎ ወይም በጅምላ የይድረስ የይድረስ አፈር አልብሶ ጅብ እንዲበላቸው ማድረግ የሚዘገንኑ የሬሳ ማስቃየት ነበሩ። በጨቦና ጉራጌ አውራጃ በቸሃ ወረዳ እነ ወልደአብ ደንቡና ሌሎችም በቀይ ሽብር ከተገደሉ በኋላ አስከሬናቸውን ቤተ ዘመዶች፣ የትምህርት ቤት ተማሪዎችና ገበያተኞች እየረገጡ እንዲያልፉ ተደርጓል፣ ከተጣሉበት ቦታዎች ሳይነሱ በጅብ ተበልተዋል።

2.3 የሰቆቃው አብይ ተዋንያን

በእነኝህ ሰቆቃ በተፈጸመባቸው ቦታዎች ሁሉ ጨካኝ የሆኑ የቀይ ሽብር አራማጆች ተሳትፈዋል። እዚህ ላይ የሁሉንም ስም ማንሳት ባይቻልም አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያክል በአዲስ አበባ የከፍተኛ አንዱ አርገጤ መድበው፣ የከፍተኛ ሁለቶቹ ኤልያስ ኑር፣ ስሙንጉሥ ሐብቴና ሐጂ በድሩ፣ የከፍተኛ አራቱ አንዳለ ጎሳዬ፣ የከፍተኛ አምስቶቹ ጠንክር፣ ግርማና ቡልቲ ለሙ፣ የከፍተኛ ሰባቱ ፍቃዱ አስቻለው፣ የከፍተኛ ዘጠኙ ቀልቤሳ ነገዎ፣ የከፍተኛ 21 ፀሐዬ፣ የከፍተኛ 22 ከሰተ አብራኒዮስ፣ የከፍተኛ 23 በርሄ፣ የከፍተኛ 25 ፈቃደና መኮንን፣ የአቃቂ ልዩ ከፍተኛው ጣምያለው እሸቴ፣ የከፍተኛ 12 ሰለሞን ይመስገን፣ የከፍተኛ 15 ባሳዝነው ባይሳ፣ የከፍተኛ 14 አባተ ጉድንፋ፣ የከፍተኛ 16 ቺፍ ተስፋዬ ገብረጊዮርጊስ፣ የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር

ምክትል ፕሬዜዳንት ተመስገን ማዴቦ፣ የጉራጌ አገሩ ገስግሥ ገብረመስቀል፣ የባህር ዳሩ ዶ/ር ሙሉጌታ ሰምሩ፣ የአዲስ አባበ ከተማ ከንቲባው ዶ/ር ዓለሙ አበበ፣ የደብረ ብርሃኑ አበበ መላኩ፣ የወላይታው ስምኦን ጋሎሬ፣ ወዘተ ሁሉም አገር ያወቃቸው ስማቸው ሲጠራ እንኳን የሚያስደነግጥ የቀይ ሽብር ተዋንያን ነበሩ:: (18)

አንዳንዶቹ ከሚያዙበት ከፍተኛ ውጪ በሌላም ቦታ የታሰሩ የማይመለከታቸውን እስረኞች በውስት እየወሰዱ በከፍተኛቸው የቀይ ሽብር ያካሂዱ እንደነበር ይተወቃል:: በዚህም የተነሳ ራሳቸው ያሰሯቸውን እስረኞች ጨርሰው ወደፊት ከሚያስሩት ለመክፈል በብድር ከሌላ ቦታ እያመጡ ይገድሉ እንደነበር በጊዜው በስፋት ተነግሯል::

የደርግ ጽ/ቤትና የማዕከላዊ መርማሪዎችና የቀይ ሽብር አራማጆች እነ ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ፣ ቺፍ ካሣዬ፣ ሻ/ል ዋቀዮ ጃራ፣ የሃምሳ አለቃ ተሸመ ባዬ፣ መ/አ ተስፋዬ ጉርሙ፣ የሃምሳ አለቃ ባዬ በለጠ፣ አደመ መኮንን፣ ካሣሁን፣ ባድማ፣ መስለ ገብሬ፣ የተለያዩ የየክልሉ መርማሪዎች፣ ከእነኚሁ ጋር የሚደመሩ ነበሩ:: (19) በተጨማሪም ልዩ ኃይል እየተባለ ከሚጠራው የደርግ ሠራዊት ተመለምለው እስረኞችን አፍነው ሲገድሉ የነበሩት እነ ኮ/ል ዘሪሁን አጋፋሪ፣ ኮ/ል አርጋው እሸቱ፣ መቶ አለቃ ሽመልስ ዋለልኝ፣ ወታደር አበበ እሸቱ፣ ልሣኑ ሞላ፣ በርይሁን ማሞና ሌሎች አጋሮቻቸው የሚታወሱ ናቸው:: ቀይ ሽብርን ከላይ ሆነው እነ ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፣ ሻለቃ ፍስሐ ደስታ፣ ሻምበል ለገሠ አስፋው፣ ኮ/ል ተካ ቱሉ፣ ኮ/ል ካሣሁን ታፈሰ፣ ኮ/ል ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ፣ ጀኔራል ለገሰ በላይነህና ሌሎችም የማዕከላዊ መንግሥት ባለሥልጣኖች እንደሚመሩ ሁሉ በክፍላተአገርም ሻለቃ መላኩ ተፈራ፣ ሻለቃ አሊ ሙሳ፣ ሻምበል በጋሻው አታላይ፣ ሻምበል ካሣዬ አራጋው፣ መ/አ እሸቱ ዓለሙ፣ መ/አ ጴጥሮስ ገብሬና ሌሎችም የየአካባቢው የኢሠፓ ተጠሪዎች ታላቅ ሚና ተጫውተዋል::

በተለይ ሻለቃ መላኩ ተፈራ በጎንደርና ሻለቃ አሊ ሙሳ በደቡብ ኢትዮጵያ ያካሄዱት የቀይ ሽብር ጭፍጨፋ ከሁሉም የከፋ ነበር:: ሻለቃ መላኩ ተፈራም ሆነ ሻለቃ አሊ ሙሳ ያሰኛቸውን ለመግደል ከልካይ አልነበራቸውም:: በጎንደር ከተማ ተገድለው በየአደባባዩ ለትርኢት የተጣሉት፣ በአባ ሳሙኤል (ሳሙና በር)፣ በሎዛ ማርያምና በአደባባይ እየሱስ እየተጨፈጨፉ አፈር የለበሱት በሺዎች የሚቆጠሩ የኢሕአፓ ሰማዕታት የሻለቃ መላኩ ተፈራን አረመኔያዊ ድርጊት የሚመሰክሩ ነበሩ:: የሻለቃ መላኩ ተፈራ ገደብ የለሽ ጭፍጨፋ ያስመረራት ጎንደሬ እናት ቢጨንቃት፣

«ሻለቃ መላኩ የእግዜር ታናሽ ወንድም፣
የዛሬን ማርልኝ (ልጄን ማርልኝ) ሁለተኛ አልወልድም::»

ብላ አለቀሰች ይባላል::

እነ ሻለቃ መላኩ ተፈራም ሆነ ሌሎች የሰደድና በኋላም የኢሠፓ አመራር አባላት ሁሉንም ድርጊት ብቻቸውን አልፈጸሙትም:: በሥራቸው በነበሩት የመኢሶን፣ የወዝ ሊግ፣ የማልሬድ፣ የኢጫትና የኢሕአፓ አንጃ ቀንደኛ ካድሬዎችና የቀይ ሽብር አራማጆች ይታገዙ ነበር:: ምንም እንኳን ጊዜው ካለፈ በኋላ ከደሙ ንጹህ ለመምሰል ቢሞክሩም አብዛኞቹ የእነኚህ ድርጅቶች አባላት የቀይ ሽብር አብይ ተዋናይ እንደነበሩ መካድ አይቻልም::

አንዳንድ የከፍተኛ እስር ቤቶች የሚጠሩበት የተለየ ስም እንደነበራቸው የሶደሬ እስር ቤት ስም አወጣጥ ያመለክታል:: ሌሎችም

እንደዚሁ የራሳቸው ልዩ መጠሪያና መታወቂያ ነበራቸው:: ለምሳሌ እስረኞችን ከመደብደብ፣ ከማሰቃየትና ከመግደል አልፈው በእሳት በማቃጠል የከፍተኛ 7 እና ከፍተኛ 14 የቀይ ሽብር አራማጆች የተካኑ እንደነበሩ ይታወቃል:: የከፍተኛ 7 እስር ቤት እንደ «ካታኮምብ» (Catacomb) ስለሚቆጠር እስረኞችም «የካታኮምብ ሰማዕታት» ይባሉ ነበር:: «ቤርሙዳ» በሚል የሚታወቁት የድብቅ እስር ቤቶች ጉዳይ ከፍ ብሎ ተጠቅሷል:: እንግዲህ እዚህ ላይ የብዙዎችን መዘርዘር ባይቻልም የተለያዩ እስር ቤቶች የራሳቸው መለያ እንደነበራቸው መረዳት ይቻላል:: በከፍተኛ 23 የነበረው «ቤርሙዳ» የሚባለው እስር ቤት የማዕከላዊ ምርመራ አካል ሲሆን እስረኞችን አሰቃይቶና በገመድ አንቆ መግደያ ቦታ ነበር:: ሌላው የልዩ ኃይል «ጥይት አናባክንም ግቢ» (Garotting Quarter) ደግሞ የልዑል አስራተ ካሣ ቤት የነበረው በደርግ የልዩ ኃያል የሚታዘዙ ገዳዮች እስረኞችን በገመድና በእጃቸውም በማነቅ የሚገድሉበት ቦታ ነበር:: በተመሳሳይ በገመድ እያነቁ ግድያ በጎንደር፣ በደብረ ማርቆስ፣ በሌሎች እስር ቤቶች ተካሂደዋል::

ከሚያዝያ 1970 ዓ.ም. በኋላ ከደርግ ሳያስፈቅዱ ቀይ ሽብርን እንደበፊቱ በየከፍተኛው አብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ውሳኔ ማካሄድ ተከለከለ ከተባለ በኋላ አንዳንድ ከፍተኞች ድርጊቱን ለመፈጸም ሙከራ አድርገው ሲከሽፍባቸው አንዳንዶች ተሳክቶላቸዋል:: ከእነዚህም ከፍተኞች መካከል የከፍተኛ 2፣ የከፍተኛ 5፣ የከፍተኛ 7፣ የከፍተኛ 8 እና የከፍተኛ 18 የቀይ ሽብር አራማጆች ይገኙባቸዋል:: የከፍተኛ ሁለት የቀይ ሽብር አራማጆች እርምጃ ሊወስዱባቸው የነበሩትን የኢሕአፓ እስረኞች እንደበፊቱ በአደባባይ ለመጣል ጊዜው አመቺ አለመሆኑን ከተረዱ በኋላ በእስር ቤት ግቢያቸው ትልቅ ጉድጓድ አስቆፍረው ገድለው ለመቅበር ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል:: (20) በከፍተኛ 7 እና 18 በተመሳሳይ ወቅት ለማካሄድ የታሰበው ያልተሳካ ሙከራም ከሽፏል:: (21) በነኝህና በሌሎች ከፍተኞች ድርጊቱ ባይፈጸምም በከፍተኛ 5 እና ከፍተኛ 8 በግንቦት ወር 1970 ዓ.ም. 10 ወጣቶች በቀይ ሽብር ተገድለዋል:: (22) የዚህ ዝርዝር በምዕራፍ ስድስት ይቀርባል:: ከአዲስ አባበ ውጭ አብዛኛው የቀይ ሽበር ግድያ የተካሄደው በ1970 ዓ.ም. መጨረሻ ነበር::

ቀይ ሽብር በበረታበት ጊዜ በየክፍላተ አገሩና በየአውራጃዎቹ በሚገኙ ወህኒ ቤቶች በዛ ያሉ የኢሕአፓ እስረኞች ይገኙ ነበር:: በጊዜው በቀበሌም ሆነ በገበሬ ማህበራት የተለያዩ እስር ቤቶች አሰቃቂ ምርመራዎችና የግድያ ወንጀሎች መፈጸማቸው ቢታወቅም አባዛኞቹ የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑት የኢሕአፓ ደጋፊ እስረኞች የተገደሉት ከታሰሩበት የፖሊስ ጣቢያዎችና ከመደበኛ ወህኒ ቤቶች እየተወሰዱ ነበር:: (23) በዚህ መልክ ከጎንደር፣ ከደብረ ታቦር፣ ከደብረ ማርቆስ፣ ከመተከል፣ ከባህር ዳር፣ ከዳንግላ፣ ከደብረ ብርሃን፣ ከጂማ፣ ከደሴ፣ ከአሰላ፣ ከሐረር፣ ከአዋሳ፣ ከድሬደዋ፣ ከናዝሬት፣ ከደብረ ዘይት፣ ከወሊሶ፣ ከጨቦና ጉራጌ፣ ከፍቼ ወህኒ ቤቶች እየተወሰዱ ብዙዎች ተገድለዋል:: ምንም እንኳን የተሟላ መረጃ ነው ባያባልም በ1970 ዓ.ም. በደብረ ማርቆስና በመተከል 98፣ በባህር ዳርና በዳንግላ 68፣ በደሴ 86፣ በደብረ ብርሃን 39፣ በአሰላ 38፣ በጅማ 34፣ በፍቼ 61፣ በአዋሳ 42 እና በጎንደር 104 እንደተገደሉ በጊዜው በቦታው ታስረው የነበሩ ያረጋግጣሉ፤ በደርግ የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» ውስጥም ስማቸው ተካቷል::(24)

በአስመራና በመቀሌ ከተሞችም በርከት ያሉ የተቃዋሚ ደጋፊዎች እየተባሉ በተለያዩ እስር ቤቶችና ወታደራዊ ካምፖች እንደታሰሩ፣ እንደተገደሉና የሽብር ዘመቻም በስፋት እንደተካሄደ ይታወቃል:: (25) ሌላው ቀርቶ ከወታደራዊ ክፍሉ እንኳን 66 የሚሆኑ የሠራዊቱ አባላት የኢሕአፓ፣ የኢዴህና የጀበሐ ደጋፊዎች በመባል በ1970 ዓ.ም በአስመራ እንደተገደሉ ከዚያው ታስረው ከርቸሌ የመጡ ወታደሮች አረጋግጠዋል፣ በደርግ ባለሥልጣኖች ክስ ውስጥም ተመዝግቦ ይገኛል::(26) ከእነኝህ መካከል ጥቂቶቹ ከፍተኛ መኮንኖች ሲሆኑ አንዳንዶች ባለ ሌላ ማዕረጎችና በዛ ያሉት ደግሞ መደበኛ ወታደሮችና «የሚሊሺያ» አባላት ነበሩ:: በሐረርጌ በምስራቅ ግንባርም እንዲሁ ከወታደራዊው ክፍል ተገድለዋል:: እነኝህና ሌሎች የተለያዩ ግድያዎች የተፈጸሙባቸው የጅምላ የቀብር ቦታዎች ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ እየተቆፈሩ አፅማቸው ሊወጣ ችሏል::

እነኝህ ሁሉ የቀይ ሽብር አስከፊ ገጽታዎችን የሚያስታውሱ ሰቆቃዎች ሲሆኑ በውጥረቱ ጊዜ በእስር ላይ ያልነበሩት የኢሕአፓ አባላትም ቢሆኑ ነፍሳቸውን ለማዳን ከቦታ ቦታ በመዘዋወር መሸሸግ የግድ ነበረባቸው:: ሌላው ቀርቶ የገጠር ዘመድ ያላቸው ከከተማ እየተሰደዱ በመሄድ ለመጠለል ቢሞክሩም በገበሬ ማህበርና በፖሊስ አባላት እየታደኑ ሊያዙ ችለዋል:: አንዳንዶች ለተወሰነ ጊዜ መሰወር ቢችሉም ለብዙ ጊዜ መደበቁ እንደማያዋጣቸውና የተጠጉባቸውም ዘመዶች ለችግር እንደሚጋለጡ በመረዳት እጃቸውን ለመስጠት ተገደዋል:: ያጋጠሟቸውን ችግሮች ሁሉ ተቋቁመው እራሳቸውን በመደበቅ ያንን አስከፊ ጊዜ ያሳለፉም ይገኛሉ::

አንዳንዶች ከአዲስ አበባና ከተለያዩ ክፍላተ አገር ከተሞች ተነስተው ጾለምት ኢሕሠን ለመቀላቀል ያደረጉት ጉዞ የተሳካ ቢሆንም ሌሎች ግን ከመንገድ እየተያዙ የሰቆቃ ሰለባ ሆነዋል:: በዚህ ዓይነት የነፍስ አድን ጉዞ ተሰማርተው ሳይሳካላቸው በመቅረት ከሸዋ አውራጃዎች የተያዙና ህይወታቸውን ያጡ ብዙ ነበሩ:: ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ከተሳተፉት መካከል አንዱ ወደ ጾለምት ለመንዝ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት በመቅረቱና መንዝ ተከቦ በመያዙ የሱንም ቀደም ብሎ ሳይጋለጡ ታስረው የነበሩ የአባሪዎቹንም ህይወት ለአደጋ አጋልጧል:: (27)

ለአንዳንዶች ደግሞ ወደ ውጪ አገር ለመሸሽ ያደረጉት ሙከራ የተሳካ ቢሆንም ጥቂቶቹን ግን ለስርና ለግድያ ሰለባ ዳርጓቸዋል:: አንዳንዶች በሸዋ አውራጃዎች ሊካሄድ በታቀደው ያልተሳካ የትጥቅ ትግል ሙከራ ከተሳተፉ በኋላ መፈናፈኛ ሲያጡ ወይ ወደ ጾለምት ተጉዘዋል አለበለዚያም ወደኋላ በመመለስ እጃቸውን ለደርግ ሰጥተዋል:: በዚህ የትጥቅ ትግል ሙከራ ጭራሹን ከግንኙነት ውጪ የሆኑና ለዕለት ተዕለት የኑሮ ችግርም የተዳረጉ ነበሩ:: አንዳንዶች ከድርጅቱ ጋር የሚያገናኛቸው መዋቅር ሲበጠስ ወይም አባላቱ ለእስር ሲዳረጉ በራሳቸው ጥረት ከሸዋ አውራጃዎች አዲስ አበባ ድረስ በመምጣት ግንኙነቱን ለመቀጠል የሞከሩም ይገኙበታል:: በአጠቃላይ ሁኔታው በጣም ዝብርቅርቅ ያለ የአሳሪና የታሳሪ መሳደድ፣ የገዳይና የተገዳይ ፍልሚያና ሩጫ የሚታይበት ወቅት ነበር::

ምዕራፍ አምስት

እስር በከርቸሌ

1. ከርቸሌ ምን ይመስላል?

ከርቸሌ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ የኢትዮጵያ ዋናው ወህኒ ቤት ነበር:: ይህ እስር ቤት የተለያዩ ክፍሎች (ክልሎች) ቢኖሩትም በዋነኛነት የሚታወቀው ዓለም በቃኝ ነበር:: ዓለም በቃኝ ውስጥ ገብተው ካላዩት በስተቀር ከውጪ ሲጠራ ስሙም አስራሩም አስፈሪ ነበር:: ዓለም በቃኝ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ የተሠራ ወህኒ ቤት ነበር:: ነገር ግን የአዲስ አባበ ከተማ እየሰፋ ሲሄድ በመሃል ከተማ እንዲገኝ አድርጎታል:: በፈረንሳይ አናጺዎች እንደተሰራ የሚነገርለት ጥንታዊው ዓለም በቃኝ ውጪው በግንብ የተከበበ ውስጡ ከዚሁ ግንብ ጋር የተያያዘ አንድ ዙሪያ ግጥም ፎቅ ያለው፣ ፎቅና ምድር ቤቱ በ57 ክፍሎች የተከፋፈሉ ነበሩ:: ክፍሎቹ ጠባብ ሆነው መጸዳጃ የሌላቸው ጥቂት እስረኛ ለማኖር የተሰሩ ቢሆኑም የእስረኛ መብዛት ከአስርም ሰዎች በላይ በአንድ ክፍል እንዲጣበቡ ሁኔታው ያስገድድ ነበር:: እስረኛ በጣም ሲበዛና ሲጨናነቅ የላስቲክ ድንኳኖች ግቢው ውስጥ ተሰርተው እንደ ጊዜያዊ መጠለያ ያገለግሉ ነበር:: ዓለም በቃኝ በጣም በተጣበበ ጊዜ አዲስ እስረኞች ሲመጡ በየክፍሉ ከመደልደላቸው በፊት በእነኝህ የላስቲክ መጠለያ ድንኳኖች ውስጥ ለመቆየት ይገደዳሉ:: እነኝህ የመጠለያ ላስቲኮች በግለሰቦች ስለተሰሩ አዲስ ገቢ እስረኞች መጠለያ ለማግኘት የሚከፍሉበትም ጊዜ ነበር::

የዓለም በቃኝ ግንብ ረጅምና ቀጥ ብሎ የተሰራ ሲሆን አናቱ ላይ ጠባቂ ፖሊሶች ይዘዋወሩበት ነበር:: ግቢውና ወለሉ በሙሉ በሲሚንቶ ሊሾ የተሰሩ ስለሆኑ ጽዳቱ ከሌሎች ክልሎች የተሻለ ነበር:: ስሙ ቢያስፈራም የውስጡ ጽዳት ለመኖር ያመች ነበር:: የመግቢያው ትልቅ በር በፖሊስ የሚጠበቅ ሲሆን «ፖርታ» በመባል ይታወቅ ነበር:: «ከፖርታው» ወደ ውጪም ሆነ ወደ ውስጥ ለማለፍ ፍቃድ ያስፈልጋል:: በሌላ ክልል ያሉ እስረኞች፣ ከሴቶች በስተቀር፣ እንደ ልብ ለመዘዋወር ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ለመሄድ ሲችሉ ከዓለም በቃኝ ግን ያለፍቃድ መውጣት የተከለከለ ነበር:: በዚህ የተነሳ የዓለም በቃኝ ጽዳት ለመኖሪያ ተስማሚ ቢሆንም «የፖርታውን» ቁጥጥር እስረኛው አይወደውም ነበር:: በዓለም በቃኝ፣ ከጊዜ በኋላ ተደፈነ እንጅ፣ ለቅጣት እንዲያገለግል ተብሎ ከመሬት በታች የእስር ክፍሎችም እንደነበሩት ይነገራል:: በመሰረቱ በፈረንሳይ አናጺዎች የተሰራ በመሆኑና እነሱም ከእስር ጋር በተያያዘ በታሪካቸው ያላቸውን አስከፊ የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ሰውን አንገት የመቅላት (Guillotine) ልምድ ስናስታውስ እውነተኛነቱን መቀበል አያጠራጥርም:: «ፓፒዮን» (Paillon) የተባለው የልብ ወለድ መጽሐፍ ታሪክም የሚያመለክተው ይህንን ነው:: (1) እንዲያውም በዚያ ከመሬት በታች በነበረውና እንደተደፈነ በሚነገርለት ዓለም በቃኝ እስረኞች ታስረው ቆይተው ወደላይኛው ሲሸጋገሩ ፀሐይ በማየታቸው ወደ «ዓለም ፀሐይ» ተዛወርን የሚሉበት ጊዜ እንደነበረ ይወሳል::

ከዓለም በቃኝ ውጪ በጣሊያን ጊዜ ለፈረስ ቤት፣ ለቢሮና ለመኖሪያ ቤት የሚያገለግሉ ተጨማሪ ቤቶች ተሰሩ:: በአሁን ጊዜ የዋናው

ዓለም በቃኝ ተቀጥላ በመሆን የቀጠሮ እስረኞች ክልል፣ የፍርድ እስረኞች ክልል፣ የፍትሐብሔር እስረኞች ክልልና የሴት እስረኞች ክልል በመሆን ያገለግሉ ነበር። ዓለም በቃኝ የከባድ እስረኞች ማሰሪያ ቦታ ሲሆን ሌሎች ስማቸው እንደሚያመለክተው በቀጠሮ ላይ ያሉ፣ የፍርድ እስረኞችንና ሴቶችን ለያይቶ ለማሰር የሚያገለግሉ ነበሩ። አጠቃላይ ግቢውም ከርቸሌ የሚል መጠሪያ ተሰጠው። እንግዲህ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤት ባሻገር ይገኝ የነበረው ከርቸሌ በተለያዩ ክልሎች በዛ ያሉ እስረኞች የሚታሰሩበት ሲሆን ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያን፣ መስጊድ፣ የኳስ ሜዳ፣ የርሻ ቦታ፣ የእንጨት ሥራና ጋራዥ ነበረው።

ከደርግ የቀይ ሽብር ዘመቻ ጀምሮ የእስረኛው ቁጥር በጣም እየጨመረ ስለመጣ የከርቸሌ እስር ቤት የሚይዘውን የእስረኛ ቁጥር ለመገመት ያስቸግራል። እንደ አመቺነቱ ከ3000-10000 እስረኞች ይታጎሩበታል ማለቱ ይቀላል። የእስረኛው ቁጥር ሲጨምር የግቢው ቦታ እንደፈቀደ ተጨማሪ ቤቶች በየጊዜው ይሰሩ ነበር። እስረኞችም ወደ ሌላ እስር ቤት ወደ ቃሊቲና ወይም ወደ ሌሎች ክፍላተ አገር እስር ቤቶች ማዛወር የተለመደ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ የፍርድ እስረኞች በራሳቸው ጥያቄም ሆነ በአስተዳደሩ ግፊት የርሻ ልማት በስሩት ወደ የሚካሄድባቸው ወደ ሮቢት፣ ዝዋይ፣ ሲዳሞና ሌሎች እስር ቤቶች ይዛወራሉ።

2. የፖለቲካ እስረኞች መሰባሰብና የከርቸሌን ሕይወት መጀመር

ከ1971 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ ምርመራቸውን የጨረሱ የተለያዩ የፖለቲካ እስረኞች ወደ ከርቸሌ ይላኩ ጀመር። ምርመራቸውን የጨረሱ የወንጀልም ሆነ የፖለቲካ እስረኞች ወደ ከርቸሌ መላክ ከዚህ በፊትም የነበረ ቢሆንም ከአፍላ የቀይ ሽብር ዘመቻ በኋላ ቁጥሩ ሊጨምርና ወህኒ ቤቱም ሊጣበብ ችሏል። ከቀበሌና ከከፍተኛ እስር ቤቶች፣ ከፖሊስ ጣቢያዎች፣ ከማዕከላዊ፣ ከድርግ ጽ/ቤት፣ ከወታደራዊ ካምፖችና ከተለያዩ ክፍላተ አገር ወደ ከርቸሌ እስረኞች ይጎርፉ ጀመር።

ምናልባት ከከፍተኛ በተናጠል ከሚላኩት ሌላ በብዛት ከመጡት እስረኞች መካከል ከሶደሬ እስር ቤት የመጣነው ከከፍተኛ 23 እስረኞች ቀጥሎ ብሎ ከሚገኘው የአስተዳደር ጽ/ቤት ተመዘገብን። ይህ ምዝገባ ቀበሌ በየጊዜው ካሳለፍን ለየት ያለ የሕይወት ታሪክን የሚመለከት ነበር። የፖለቲካም ሆነ የወንጀል እስረኛ ታስሮ ወህኒ ቤት ሲገባ በባሕር መዝገብ ላይ ይመዘገባል። የእስረኛው ስም፣ የእናትና የአባት ስም፣ የትውልድ ቦታ፣ የትውልድ ዘመን፣ ሃይማኖትና ሌሎችም መረጃዎች ይጠቀሳሉ።

ከዚያም ምዝገባው እንዳበቃ ዕቃችንን ሸክፈን በፖሊሶችና በአስተናጋጅ (ደልዳይ) እስረኞች ታጅበን ሺ ገዳይ ተወሰደን ልብሳችን በፀረ-ተባይ መድኃኒት ባይረጭም ፀጉራችንን ከተላጨን በኋላ ወንዶች ወደ ዓለም በቃኝ ስንወሰድ ሴቶች ደግሞ ወደ ሴቶች ክልል እንዲወሰዱ ለሴት ጥበቃ ፖሊሶች ተሰጡ። አንዳንዶቻችን ቀበሌ እስር ቤት በነበርንበት ጊዜ የራስ ፀጉራችን በማደግ ለተባይ እንዳያጋልጠን በሚል ቀደም ብለን ተላጭተነው ስለነበርን ለዚህ አልተዳረግንም። ሺ ገዳይ አዲስ እስረኞች ለመጀመሪያ ጊዜ

ከርቸሌ ሲገቡ በፀረ-ተባይ ማጥፊያ ልብሳቸው የሚረጭበት፣ ፀጉራቸውን የሚላጩበትና ለአንዳንድ በሽታዎች መከላከያ ክትባት የሚሰጥበት ቦታ ነበር::

ከዚህ በኋላ ከርቸሌ በቆየንበት ጊዜ ከሴት እስረኞች ጋር አንዳንድ ጊዜ በሩቅ ከመተያየት በስተቀር ተቀራርበን ተነጋግረን አናውቅም:: እነሱም የኛን እኛም የነሱን የእስር ሕይወት በወሬ ከምንሰማው በስተቀር ማንኛችንም አናውቅም:: የከርቸሌ እስር ቤት ሴትና ወንድ እስረኞች እንዳይገናኙ በጥብቅ ይከለክላል::

ወደ ዓለም በቃኝ ብንወሰድም በዚህ ክልል አልተደለደልንም:: ከርቸሌ የደረስንበት ጊዜ ከሰዓት በኋላ ምሽቱ ሊቃረብ ሲል ነበር:: ዓለም በቃኝ ያደረሱን ፖሊሶች ለደልዳይ ኮሚቴ አስረክበውን ሲመለሱ አንዳንዶቻችን ቆመን ዙሪያ ገባውን ስንመለከትና በእስረኛው ብዛት ስንደነቅ ከመካከላችን ከርቸሌን በፊት የሚያውቁት ጓደኞቻችን ዓለም በቃኝ ላለመግባት ሌላ አማራጭ አያስናዱ ወደ ቀጠሮ ክልል ለመሄድ ማመቻቸት ቻሉ:: በዚህም የተነሳ ለከርቸሌ እንግዳ የሆነው ብቻ ስለቀረን ደልዳዮች እስረኞችን እየቆጠረ ያስገባ ከነበረው የዕለቱ ተረኛ መኮንን ባሻ ጋር ተነጋግረው የሰው መረጣ ሳይደረግ ሁላችንም ቀጠሮ ክልል እንድንገባ ተወሰነ::

የቀጠሮ ክልል ግቢው በዘልማድ የባሪያ ድንጋይ በሚባለው ጥቁር ድንጋይ የተነጠፈ አባጣ ጎርባጣ ሲሆን በውስጡም 11 ሰፋፊ የወታደር ከረማታ የመሰሉ እስር ቤቶች ነበሩት:: በአሰራር ቀደምት የሆኑት 6 ቤቶች ማለትም የተያያዙት 1፣ 2፣ 3 እና 5፣ 6፣ 7፣ ከድንጋይ የተሰሩ ነበሩ:: ሌሎች አብዛኞቹ ከቆርቆሮ የተሰሩ ሲሆን ዘጠንኛ ቤት ከአስቤስቶስ የተሰራ ነበር:: ከነኝህም መካከል 9፣ 10 እና 11ኛ ቤቶች እኛ ከርቸሌ ከመጣን በኋላ እስረኛ እየበዛ ሲሄድ የተሰሩ ነበሩ:: ከቀጠሮ ክልል መካከል 3፣ 6፣ 10 እና 11ኛ ቤቶች በጣም ትላልቆች በመሆናቸው እያንዳንዳቸው ከ300 እስረኞች በላይ መያዝ የሚችሉ ነበሩ::

ከቀጠሮ ክልል ቀጥሎ ከፍተኛውን የእስረኛ ብዛት የሚይዘው የፍርድ ክልል 8 ቤቶች ሲኖሩት፣ ከዓለም በቃኝ የሚያንሱት የፍትሐብሔርና የሴቶች ክልሎች እያንዳንዳቸው 5 ቤቶች ነበሯቸው:: በሴቶች ክልል ከነበሩት ሦስት የተያያዙ ቆርቆሮ ቤቶች መካከል አንድ ለሕግ እስረኞች፣ አንድ ለፖለቲካ እስረኞችና ሌላ አንድ ከስሜን ለሚመጡ ሴት እስረኞች ማሰረያ ይጠቀሙባቸው እንደነበር ይታወቃል:: ከዚህም ሌላ አንድ አዳራሽ የሚባል የንጉሣውያን ቤተሰቦች የሚታሰሩበትና አንድ ቆርቆሮ ቤት ለአመጫትና ልጅ ላላቸው ሴቶች መታሰሪያ የሚያገለግሉ ይገኙ ነበር:: አንዳንድ ልጅ የነበራቸው የሴት እስረኞች የልጆቻቸው እድሜ ከፍ እስኪልና ውጪ ያለ አሳዳጊ ወይም የቅርብ ዘመድ እስኪረከባቸው ድረስ አብረው ታስረው ተንገላተዋል:: የእስረኛው ቁጥር እየበረከተ ሲሄድ በፍርድ ክልልም አንድ ትልቅ ቤት ተሰርቶ ሲጨመር ከሴቶች ክልል አጎራባቹ የነበረ አንድ አነስተኛ ቤትም ለሴቶች መኖሪያ ተሰጥቶ ሦስቱ የተያያዙ ቆርቆሮ ቤቶች እንዲፈረሱ ተደርገዋል::

በቀጠሮ ክልል በፍላጎታችንም ባጋጣሚም መ. እና ሰ.ኃ. ስምንተኛ ቤት፣ ወ.ገ. እና ተ.በ. ሰባተኛ ቤት፣ ደ.ቦ. እና ተ. ስድስተኛ ቤት፣ ተ.ታ.፣ ው.አ. እና አ.ለ. አምስተኛ ቤት፣ የመኢሶን አባላት ሦስተኛ ቤትና ስ.መ. ሁለተኛ ቤት ተደለደልን:: የተደለደልንበት ቤት የገባነው የእስረኞች ቆጠራ ከተጠናቀቀ ከአሥራ አንድ ሰዓት በኋላ ነበር::

የቀጠሮ ሰባተኛ ቤት ከ150-200 እስረኞች በመጣበብ ሊያኖር የሚችል ሲሆን ውስጡ ሲገቡ የእስረኞች መኝታ ዲሪቶዎች (የተደረቱ ፍራሾች) ተደርድረው ተነጥፈው ይታያሉ:: በክፍሉ መካከል ከአጠናና ከጣውላ የተሰራ ፎቅ የሚባል ቆጥ በላዩ ላይ በሁለት መስመር የመኝታ ዲሪቶዎች የተነጠፉበት ይገኛል:: በብዙ ቤቶች የሚገኘውን ይህንን ፎቅ የሚባለውን ቆጥ ያሰራው ዱሮ ታስሮ የነበረው ቀኛዝማች ማሞ ካቻ መሆኑ ይነገራል:: በቤቱ ዳርና ዳር ሴኔቻ በሚል ስም የሚጠራ ቦታም እንዲሁ የመኝታ ዲሪቶዎች ተነጥፈውበት ይገኛል:: ከፎቅ ስር ያለው የመኝታ ቦታ ደቦቃ ይባል ነበር::

በቤቱ የሚገኙት እስረኞች እንዳመጣጣቸው ቅደም ተከተል እየተወዳደሩ አንድ ስፋቱ 60 ሴንቲሜትርና ቁመቱ ከሁለት ሜትር የማይበልጥ ዲሪቶ ማሳረፊያ ቦታ ይመራሉ:: በጎረቤታሞች መካከል ምንም ክፍተት ሳይኖር ግጥግጥ አድርገው ማንጥፍ ነበረባቸው:: ሴኔቻ በአንደኛ ደረጃ፣ ፎቅ ደግሞ ምንም እንኳን ኮርኒስ በሌለው የቆርቆሮ የቤት ክዳን ስብርድ ቢያጋልጥም በሁለተኛ ደረጃ የተሻሉ ቦታዎች ተደርገው ሲቆጠሩ ደቦቃ ግን የፎቅ ቆሻሻ፣ ብናኝና አንዳንድ ጊዜም የውሃ እጣቢ ስለሚፈስበት ዝቅተኛ ደረጃ የሚሰጠው ቦታ ተደርጎ ይቆጠራል:: ዲሪቶዎች የመኝታ ቦታ ብቻ ሳይሆኑ ቀን ለጠረጋ ጊዜ ብቻ ከታጠፉ በኋላ ተዘርግተው ለምግብ መመገቢያና ለመቀመጫም ጭምር የሚያገለግሉ ነበሩ::

ከእስረኛው መብዛት የተነሳ አዲስ ገቢ የሆነ ተወዳድሮ የዲሪቶ መዘርጊያ ቦታ ማግኘት አይችልም ነበር:: አንድ እስረኛ ተፈቶ ቦታ ሲለቀቅ ቦታውን ተወዳድሮ እንዲይዝ ቅድሚያ የሚሰጠው በቤቱ ውስጥ ለቆየ እስረኛ ስለሆነ አዲስ መጤዎች ለሽንት ቤት መሄጃና ወደ ውጪ ሲወጡ የእግር መረማመጃ ተብለው የተተው መንገዶች ላይ ሌሎች ከተኙ በኋላ እየተጋፉ መተኛት የግድ ነበር:: ብዙዎቻችን በቀበሌ እስር ቤት ከዚህ የባሰ ችግር ተቋቁመን ስላሳለፍን የትም ብንጋደም ጉዳያችን አልነበረም:: ሆኖም በሰውነታችን ላይ ቁስል የነበረብንን ተመልክተው የመረማመጃ መንገድ ላይ ብንተኛ መረጋገጥ የማይቀርልን መሆኑን በመገመት አንዳንድ ግለሰቦች ፎቅ ላይ ደባል ሆነን እንድንተኛ ፈቀዱልን::

እንደ ከፍተኛ ሁሉ የከርቸሌ እስረኛም ይረዳዳል፣ አንዱ ለሌላው ያዝናል:: የሰባተኛ ቤት ዳኝነት የነበረው ሰይፉ ጁሩ ከቀበሌ አብረን ከመጣነው መካከል ከወ.ገ. ጋር ስለሚተዋወቁ ሰባተኛ ቤት እንደገባን ከማግዝ ጀምሮ የተሻለም መኝታ እንድናገኝ ረድቶናል:: በዚህም የተነሳ ሰባተኛ ቤት ከገባን ቀን ጀምሮ ባንድ ማዕድ የምንቆርስ የመቁርስ አባል ሆንን:: ሰይፉ ጁሩ፣ ወታደር ቢተው አይቸህ፣ አብርሃም ደምሴና ሌሎችንም የሚያካትተውን መቁርስ ተቀላቀልን:: የመቁርስ አባሎቻችን እየተፈቱ ሲሄዱ ከሌሎች ጋር እየተቀላቀልን እስከ መጨረሻ ዘለቅን:: የሰባተኛ ቤት ከረማታ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሁለት ታዛዎች ነበሩት:: አንዱ ታዛ የሽንት ቤት ጉድጓድ ሲኖረው በሌላው ደግሞ ከውጪ ሙቅ ውሃ እያስመጣን ወይም እየገዛን አልፎ አልፎ ገላችንን የምንታጠብበት ሥፍራ ነበረው::

ከቀኑ 11 ሰዓት ጀምሮ በሁሉም ክልል ያሉ እስረኞች በዕለቱ ተረኛ መኮንን ባሻ እየተቆጠሩ በየቤታቸው ይገባሉ:: የጠፋ ወይም የጎደለ እስረኛ ካለ ፍለጋው ይካሄዳል:: አዲስ እስረኞችም ካሉ በየቤቱ እየተደለደሉ ይገባሉ:: እስረኞች ተቆጥረው በየቤቱ ከገቡ በኋላ በሮች ከውጪ በቁልፍ ይዘጋሉ:: አንድ

ጊዜ በሩ ከተቆለፈ በኋላ ሰው ቢታመም፣ እሳት ቢነሳ፣ ወይም ሌላ ችግር ቢያጋጥም ዘቦችን ድረሱልን እያሉ ከመጣራት በስተቀር ምንም ማድረግ አይቻልም ነበር። ዘቦችም ካዘኑ ጠጋ ብለው ይጠይቁና እንደ አስፈላጊነቱ እርዳታ ሊያደርጉ ይችላሉ፣ አለበለዚያ እስኪነጋ ድረስ መስቃየት የግድ ነበር።

ለእስረኛ የሚቀርበው ምግብ አጥጋቢ ባይሆንም በቀን ሦስት ጊዜ ጠዋት፣ ቀንና ማታ በ10 ሰዓት ቁርስ፣ ምሳና እራት ይሰጣል። ጠዋትና ማታ ሻይ በበርሜል ተፈልቶ አንድ ኩባያ ሻይ ከአንድ ዳቦ ጋር ለአንድ እስረኛ ይሰጥ ነበር። ቀን የሽሮ ወጥና ዳቦ ይቀርባል። በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ እሁድ ቀን አንድ መዳፍ የማትሞላ ቅቅል ሥጋና አንድ ኩባያ ሾርባ ይታደላል። ሻይ፣ ወጥና ሾርባ ከበርሜል እየተቀዳ ቢታደልም የመጠጫና የመቀበያ ዕቃዎችን እያንዳንዱ እስረኛ የራሱን ማዘጋጀት ነበረበት። እንግዲህ እስረኛው በውጪ ጠያቂ ባይደጎም ኖሮ የሚሰጠው ምግብ ሕይወትን ለማቆየት በብዛትም ሆነ በጥራት በጣም ዝቅተኛ ነበር። ቢሆንም ምንም ነገር መንግሥት ከማይሰጥበት ከከፍተኛ፣ ከማዕከላዊና ከደርግ ጽ/ቤት እስር ቤቶች ከርቸሌ እስር እጅ ይመረጥ ነበር።

እስረኞች ማታ ተቆጥረው ከገቡ በኋላ እስኪተኙ ድረስ የራሳቸው የተለያዩ ጊዜ ማሳለፊያዎች ነበሯቸው። አንዳንዱ ያነባል፣ ሌላው ክራር ይጫወታል፣ ግማሹ ያጉጎራጉራል፣ አንዳንዶች በድብቅ ባስገቡት ሬዲዮ ዜና ያዳምጣሉ፣ ሌሎች ተሰብስበው ያወጋሉ። ባጭሩ ቁም ነገሩም፣ ጨዋታውም፣ የደራ ነበር። ለእስረኞች የሚነበቡ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍት ከውጪ የሚያቀብላቸው ሰው ካለ በህጋዊ መልክ በእስረኞች አስተዳደር በኩል እየተፈተሹ ማስገባት ይቻል ነበር። አንዳንድ እስረኞች በድብቅ ያስገቡትን ጫትም ሆነ መጠጥ ሲያጣጥሙ ያመሻሉ። ምንም እንኳን የወህኒ ቤቱ የራት ጊዜ ከቀኑ አስር ሰዓት ቢሆንም ብዙ እስረኞች ድርሻቸውን አቆይተው ከወጪ ጠያቂ ከተላከላቸው ጋር ደባልቀው የሚበሉት ማታ ከቆጠራ በኋላ ነበር። የተለያዩ መቁረሶች እራታቸውን ሲበሉ እራት የሌለውን መጋበዝ የተለመደ ድርጊት ነበር። በተለይ በምሳ ሰዓት በሌላ ቤት ወይም ክልል ከሚኖሩ ጓደኞች ጋር መገባበዝ ይዘወተራል።

እስረኞች በግል ከሚያካሂዷቸው ድርጊቶች ሌላ የወህኒ ቤቱ አስተዳደርም ሆነ ሌሎች መልእክቶች በኮሚቴዎች አማካኝነት የሚተላለፉት ማታ ማታ ነበር። ለምሳሌ በሚቀጥለው ቀን የፍርድ ቤት ቀጠሮ ያላቸው፣ ለሥራ የሚሰማሩ፣ የታመሙ ቀደም ብለው ተመዝግበው ከርቸሌ ክሊኒክ ወረፋ የተያዘላቸው፣ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ውጪ ሐኪም ቤት የሚላኩ፣ ወዘተ. መልዕክት ይነገራቸዋል። የወህኒ ቤቱን አስተዳደርና እስረኛውን እንደ ድልድይ ሆነው የሚያገናኙ የተለያዩ ኮሚቴዎች ከየቤቱ ይመረጣሉ። እነኝህ ኮሚቴዎች በእስረኞች አማካኝነት ከየቤቱ እየተመረጡ እንዲቋቋሙ ከመደረጉ ከ1967 ዓ.ም. በፊት የወህኒ ቤቱ አስተዳደር የራሱን ካቦዎች እየመረጠ እስረኞችን ይቆጣጠር ነበር። የየቤቱ ካቦዎች ፈላጭ ቆራጭ ከመሆናቸው የተነሳ ከእስረኛው ጉቦ ሳይቀር እየተቀበሉ የሚያስተዳድሩ፣ ለወህኒ ቤቱ አስተዳደርም አጋልጠው የሚሰጡና ወሬ የሚያቀብሉ እንደነበሩ ይነገራል። ይህን መሰል አስከፊ እስረኞችን በካቦ ማሰቃየት እንዲቀርና እስረኛው ራሱ በመረጠው ኮሚቴ ራሱን እንዲያስተዳድር የተደረገው በ1967 ዓ.ም. በእድገት በህብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ጊዜ ነበር።

ደርግ ሥልጣን እንደያዘ በአገሪቷ በሙላ ከአሥራ አንደኛ ክፍል በላይ የሚማሩት ተማሪዎች በገጠር ዘመተው የገበሬውን ሕይወት እንዲቀይሩ በማሰብ ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ዘመቻ አካሂዷል:: (2) በዘመቻው ጊዜ እነኝህ ተማሪዎች በአንዳንድ የመሰረተ ልማት በመሳተፍ፣ የመሰረተ ትምህርት በማስተማር፣ የገበሬ ማህበራትን በማደራጀትና የመሬት ይዞታም በመንግሥት እንዲሆን ከታወጀ በኋላ (3) አዋጁን በማስፈጸም አገልግለዋል:: የከርቸሌ እስረኞች ከካቦ አስተዳደር ተላቀው ራሳቸው በመረጡት ኮሚቴዎች እንዲመሩ ያደረጉትም እነኝሁ ከከተማ አካባቢ የዘመቱት የእድገት በህብረት ዘማቾች መሆናቸው ይነገራል:: ከዚህም በተጨማሪ በከርቸሌ የመሰረተ ትምህርት እንዲጀመርና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም እንዲቋቋም መሰረት የጣሉት እነኝሁ ዘማቾች እንደሆኑ ይገመታል::

በእነኝህ ኮሚቴዎች አማካኝነት እስረኞች በአስተዳደሩ ቁጥጥር ስር እራሳቸውን ለማስተዳደር፣ ለማስተማር፣ ለማዝናናት፣ ለመመገብ፣ ጤናቸውን ለመንከባከብና ለወህኒ ቤቱም የልማት ሥራ ለማበርከት ተሳትፎ ያደርጋሉ:: በአጭሩ ኮሚቴዎች ለእስረኞችም ለአስተዳደሩም የደም ስር ነበሩ:: ስለዚህ በየቤቱ የሚገኙት እስረኞች በድምፅ ብልጫ ለሚከተሉት የኮሚቴ ዘርፎች አንዳንድ አባል ከመረጡ በኋላ የቤቱም ሆነ አጠቃላዩ የከርቸሌ ግቢ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ:: በዚህ መሰረት፣

1. የዳኝነትና የስነ ስርአት ኮሚቴ፣
2. የደልዳይ ኮሚቴ፣
3. የጤና ኮሚቴ፣
4. የትምህርትና የሥራ ኮሚቴ፣
5. የምግብ ኮሚቴ፣
6. የመዝናኛ ኮሚቴ፣

የሚባሉ ኮሚቴዎች ነበሩ::

እነኝህ ከላይ የተጠቀሱት ኮሚቴዎች የሚሰጡት አገልግሎት እንደስማቸው የተለያየ ሲሆን በቤት ደረጃ እንደ አንድ ኮሚቴ በጋራ ሲሰሩ ከየቤቱ የተወጣጡት የከርቸሌን የተለያዩ ስድስት ኮሚቴዎች ይመሰርታሉ:: ከእነኝህ ኮሚቴዎች በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ የህብረት ሱቅ አማራር የሚሰጡ ኮሚቴዎችና ግለሰቦች ይመረጡ ነበር:: ለመላላክና ከውጪ ጠያቂ ወደ ውስጥ ስንቅ ለማቀበል የሚያገለግሉ ታማኝ እስረኞች በቤቱ የዳኝነትና የስነ ስርአት ኮሚቴ ዘርፍ አማካኝነት ተመርጠው ስማቸው ለአስተዳደሩ ይተላለፋል:: እነኝህ ተላላኪዎች ከአስተዳደሩ ወደ እስረኞች የሚላኩ መልዕክት ያደርሳሉ:: ለምሳሌ ከከፋተኛ ከርቸሌ የመጣነው ጥቂት ከሰነበትን በኋላ አንድ ቀን ቀጠሮ ክልል ግቢ ውስጥ ተጠርተን በሲጋራ ወረቀት ቁራጭ ላይ የተጻፈ ስማችንንና የወህኒ ቤት መዝገብ ቁጥር የያዘ ዋራንት የሚባል መታወቂያ ወረቀት የተሰጠን በእነኝህ ተላላኪዎች አማካኝነት ነበር:: ከርቸሌ ገብተን ከእስረኞች ከተደባለቅን በኋላ በኮሚቴ ወይም በተላላኪዎች አማካኝነት ከሚደርሰን መልዕክት በስተቀር ብዙዎቻችን የአስተዳደሩን በር እረግጠን አናውቅም:: ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በአዘቦት ቀን ምግብ ከውጪ ለእስረኛው ሲላክ በፖሊስ ከተፈተሸ በኋላ ወደሚኖርበት ክልል የሚያመላልሱት፣ መጻሕፍትና ሌሎች ነገሮችንም በፖሊሶች ከተፈተሹ በኋላ ወደ ግቢ የሚያስገቡት እነኝሁ

ተሳላኪዎች ነበሩ፡፡ እሁድ የእስረኞች አጠቃላይ የጥየቃ ቀን ስለሆነ ወደፊት በዝርዝር የሚቀርብ የራሱ የተለየ ታሪክ አለው፡፡

በየቤቱ የኮሚቴ ምርጫ ብዙ ትንቅንቅ ነበረበት፡፡ የሚመረጠው ግለሰብ የእስረኞች አስተዳደር ድብቅ ሰው እንዳይሆን ብዙ ጥረት ይደረጋል፡፡ አጉል ሰው ከተመረጠ ሁሉም እስረኞች በየምክንያቱ መበጥበጣቸውና መከሰሳቸው ስለማይቀር የግድ ጥንቃቄ ያስፈልግ ነበር፡፡ ለነገሩ ነው እንጅ የኮሚቴ አባልም ባይሆን አስተዳደሩ የራሴ የሚላቸውን ስውር ጠቋሚዎች በየቤቱ መመልመሉ አይቀርም፡፡ በፖለቲካና የአስተሳሰብ ልዩነቶች የተነሳ በኮሚቴ አባላት አማካኝነት በደል እንዳይፈጸም አስተዳደሩም መጠንቀቅ ነበረበት፡፡ ስለዚህ የፖለቲካ እስረኞች በአንዳንድ ቤቶች በብዛት ቢበልጡም አንድ ወጥ ስላልሆኑና ስለማይስማሙ በኮሚቴ ምርጫና አሰራር ጭቅጭቅ መፈጠሩ አልቀረም፡፡ ከርቸሌ ስንደርስ የብዙ ኮሚቴ አመራር አባላት የፖለቲካ እስረኞች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ይህ አካሄድ ሊዘልቅ አልቻለም፡፡

አስተዳደሩ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት እስረኞች የነበራቸውን አለመግባባት በኮሚቴ አሰራር ላይ እንዳያንፀባርቁ በማለት የፖለቲካ እስረኞች በኮሚቴ አባልነት እንዳይሳተፉ አገደ፡፡ ይህ እገዳ ከሴቶች ክልል፣ ከልማትና ከህብረት ሱቅ ኮሚቴዎች በቀር በሁሉም በኩል ተግባራዊ ሆኗል፡፡ እንግዲህ ብዙሃኑ የመምረጥ መብታቸው ቢጠበቅም መመረጥን ተነፍገው ነበር ማለት ነው፡፡ ሆኖም ይህ አሰራር በእስረኛው መካከል የነበረውን ሽኩቻ ሊያስቆመው አልቻለም፡፡ ከኮሚቴም አልፎ በሌሎች የወህኒ ቤቱ እንቅስቃሴዎች ላይ የፈጠረውን እንቅፋት ወደፊት እንመለከታለን፡፡

የእስረኞች በከርቸሌ መሰባሰብ እየቀጠለ ሲመጣ በርካታ የከፍተኛ እስረኞች በየቀኑ ይጎርፉ ጀመር፡፡ ከአንዳንድ ከፍተኞች ከርቸሌ የተላኩት አነስተኛ ሲሆኑ ከከፍተኛ 3፣ 5፣ 7፣ 8፣ 13፣ 15፣ 25 እና ሌሎችም በዛ ያሉ እስረኞች መጡ፡፡ ከአንዳንድ ከፍተኞች ወደ ከርቸሌ ከተላኩት ሌላ በከፊል ወደ ማዕከላዊም የተወሰዱ ነበሩ፡፡ ከከፍተኛ ሌላ ከሌሎች እስር ቤቶችም ወደ ከርቸሌ ተልከዋል፡፡ በዚህ የእስረኞች በከርቸሌ መሰባሰብ የተነሳ የኢሕአፓ፣ የኢዴህ፣ የመኢሶን፣ የማሌሪድ፣ የወዝ ሊግ፣ የኢጭአትና የአንዳንዶች ክፍልፋይ አንጃ አባላትም ከርቸሌ ተፋጠጡ፡፡ አሳሪና ታሳሪ የነበሩ ሁሉ የስር ተቋዳሽ፣ ሁሉም የጋቢና ዋራንት ጥሪ ጠባቂ ሆኑ፡፡

የብሔርና የገንጣይ ድርጅቶች አባላትም እንደ ኦነግ፣ ጀበሐ፣ ሻዕቢያና ወያኔም ጭምር ደረጃ በደረጃ በከርቸሌ ተሰባሰቡ፡፡ ከአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከአስመራ፣ ከመቀሌ፣ ከናዝሬትና ከሌሎችም ከተሞች እስረኞች ወደ ከርቸሌ ተመሙ፡፡ ከደርግ ጋር አብረው አድራጊ ፈጣሪና የቀይ ሽብር አራማጆች የነበሩትም የእስሩ ሰለባ ሆኑ፡፡ ብዙዎች ወደ ከርቸሌ ተነዱ፡፡ አያንዳንዳቸው ብዙ ሰዎች በቀይ ሽብር እንደገደሉ የሚታወቀት ገስግስ ገብረ መስቀል፣ ቀልቤሳ ነገም፣ አንዳለ ጎሳዬና ሌሎችም ከርቸሌ ተጠራቀሙ፡፡ ከዚህ በፊት ድርጊታቸው የተጠቀሰው የከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 የቀይ ሽብር አራማጆች ከሰተ አብራኒዮስ፣ የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር የነበረው የሣምሳ አለቃ ኃይለማርያም፣ ሦስቱ የአብዮት ጥበቃዎች ደምሴ ኃይሌ ፣ ነጋ በረካና አለሙ ደበሌ፣ ሁለቱ ገራፊና መርማሪዎች ሳሙኤልና ብንያም ከኛው ጋር ተደባለቁ፡፡ የደርግ ወዳጅም ጠላትም የነበሩት ሁሉ እኩል የከርቸሌ ሰለባ ሆኑ፡፡

የተለመደው የደረቅ ወንጀል እስረኞችም ምርመራቸውን በየፖሊስ ጣቢያው ሲጨርሱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደ ከርቸሌ ማረፊያ ቤት ይላኩ ነበር:: ሆኖም በየጊዜው ከሚጎርፉት የፖለቲካ እስረኞች ጋር ቁጥራቸው ሲወዳደር በጣም አነስተኛ ነበር:: በዚህ የተነሳ የፖለቲካ እስረኞች በሁሉም ክልሎች ግቢውን አጥለቀለቁት::

በጉቦ ቅሌት፣ የመንግሥት ገንዘብ በማባከንና በኤኮኖሚ አሻጥር ሰበብ የታሰሩ የተለያዩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ ነጋዴዎች፣ ወታደሮችና የፖለቲካ ካድሬዎች «የኤኮኖሚ አሻጥር እስረኞች» በሚል ከርቸሌ የተሰባሰቡትም ሌሎች ዓይነት እስረኞች ነበሩ:: በመቶ ሺዎችና በሚሊዮን የሚቆጠር የመንግሥት ንብረት ያባከኑ የመንግሥት ሠራተኞችና አንዳንድ ባለሥልጣኖች ጭምር ሁሉም ከርቸሌ ተሰብስበው ነበር:: (4) ከርቸሌ የሰጡትን ይቀበላል:: በቅርብ ጊዜ በመንግሥት መንበረሥልጣን ላይ ከተቀመጡት የደርግ አባላት መካከል ኮሎኔል አባተ መርሻ፣ ኮሎኔል ደምሴ ዱሬሳና መቶ አለቃ ደምሰው ካሣዬ የከርቸሌ እስረኞች ነበሩ:: በሻዕቢያ ተማርከው የተለቀቁ ሚሊሻዎችና ቋሚ ወታደሮች የነበሩበትን ወታደራዊ ክፍል እንዳይደባለቁና የሻዕቢያን ፕሮፓጋንዳ እንዳያሰራጩ በሚል ከርቸሌ በእስር የተላኩም ነበሩ:: በኢትዮጵያና ሱማሊያ ጦርነት የተነሳ የሁለቱ አገሮች ዲፕሎማቲክ ግኑኝነት ሲቋረጥ በኢትዮጵያ የሱማሌ ኤምባሲ ዝቅተኛ ሠራተኞች የነበሩት አንድ ሾፌር፣ አንድ ዘበኛና አንድ የምግብ ቤት ሠራተኛ ታስረው ነበር:: እነኝህ ዝቅተኛ የሱማሌ ዜጎች ለእስር ሲዳረጉ እምባሳደሩ የዲፕሎማቲክ ደህንነቱ ተጠብቆ በክብር ወደ አገሩ ተሸኝቷል::

በከርቸሌ የተሰበሰቡት የሴትና የወንድ የፖለቲካ እስረኞች አብዛኞቹ በእድሜ ለጋ የነበሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቢሆኑም ሌሎች በተለያየ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ ወታደሮች፣ ገበሬዎችና ከፍተኛ ምሁራን ጭምር ነበሩባቸው:: እድሜያቸው ከ15 ዓመት ታዳጊው ከከፍተኛ 23 የመጣው የሦስት ዓመት ፍርደኛው ሣሙኤል አድማሱ፣ ከጨርቆስ አካባቢ አንድ ላይ ከታሰሩት ታዳጊዎችና ሌሎችም በእድሜ ለጋ ከሆኑት ወጣቶች ጀምሮ እስከ ጡረታ የወጡ አዛውንቶች ድረስ ያዛንቃል:: በፖለቲካ አቋማቸው የደርግ ደጋፊም ተቃዋሚም የነበሩ፣ በማህበራዊ ሕይወታቸው ከተራ ሰው እስከ ደርግ ባለሥልጣንና የኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ልኡላንና መሣፍንትም ጭምር ሁሉም አንድ ላይ ታስረዋል:: የእስረኛውን ብዛትና የታሳሪውን ዓይነት ስንመረምር ብዙ ነገሮች በህሊናችን ይቀረጻሉ:: ምንም እንኳን ብዙዎች በቁጥጥር ስር የዋሉት በፖለቲካ ሰበብ በፀረ አብዮተኛነት ተፈርጀው ነበር ቢባልም በጊዜው ሰዎችን ለማሰር ጥፋት ሳይሆን ምክንያት የሚፈለግ መሆኑን ያሳያል:: ሌላው ደግሞ ደርግ የፖለቲካ ልዩነቶችን የሚፈታበት መንገድ በመቻቻል ሳይሆን በማግለል፣ በማሰርና በመግደል እንደነበረ ያመለክታል::

ከርቸሌ የሰጡትን እስረኞች ውጠ የሚያስቀር ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቹንም ያስወጣ ነበር:: የፍርድ ጊዜያቸውን የጨረሱ እስረኞች ይፈታሉ፣ በቀጠሮም ላይ የነበሩ ፍርድ ቤት የሚመላለሱ እስረኞችም በነፃ ወይም በበቂ ይፈቱ ነበር:: የፖለቲካ እስረኞችም በጋቢና ዋራንት አንዳንዶቹ ለፍቺ፣ ሌሎች ለቺቺ፣ አንዳንዶች ደግሞ ለተጨማሪ ምርመራ ወይም ወደ ሌላ እስር ቤት ለመዛወር ይወሰዳሉ::

ከርቸሌ ከመጡ አንዳንድ የኢሕአፓ የከፍተኛ እስረኞች መካከል የከፍተኛ 2፣ 3፣ 12፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ እና 23 እስረኞች ህግ ፊት ሳይቀርቡ ከ1-20 ዓመት እስራት ተፈርዶባችኋል የሚል የፍርድ ዋራንት ተቀረጠባቸው፤ ከመካከላቸው አንዳንዶቹም እየተወሰዱ ተገደሉ:: ለምሳሌ ከከፍተኛ 22 አንድ ላይ ከመጣነው የኢሕአፓ እስረኞች መካከል ሦስቱ ደርግ ጽ/ቤት ተወስደው ሲገደሉ የቀሩት ከአንድ እስከ 10 ዓመት ተፈረደባቸው:: ከሌላ ከፍተኛ የመጡት ከዚህ በላይም ተፈርዶባቸዋል:: ዝርዝሩ ወደፊት ስለሚቀርብ እዚህ ላይ በስፋት ማስቀመጡ አስፈላጊ አይደለም:: ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ እዚህ ላይ መጠቀስ አለበት:: ከከፍተኛ ከመጡት መካከል ከኢሕአፓ እስረኞች በስተቀር ሌሎች ፍርድ አልተጣለባቸውም ነበር::

ደግሞም የደርግ አሰራሩ ቅዕበታዊ በሆኑ ግፊት እንጅ ታስቦበት አለመሆኑ የሚያሳየው በዚህ ጊዜ ከተሰጠው የእስር ፍርድ ሌላ በቀጣይነት አልታየም:: ሌላው ቢቀር በይፋ አልተነገረም:: ሌላው ከዚህ ጋር መጠቀስ ያለበት ጉዳይ የአንዳንድ ከፍተኛ እስረኞችን መጀመሪያ ከከፍተኛ ወደ ማዕከላዊ ተወስደው ካቆዩአቸው በኋላ ሲፈረድባቸው ወደ ከርቸሌ እንዳመጧቸው መታወቅ አለበት:: በዚህ መልክ ማዕከላዊ ተወስደው ሲፈረድባቸው ወደ ከርቸሌ የተላኩት የከፍተኛ 2፣ 3፣ 19 እና 20 እስረኞች ነበሩ::

ከዚህ ሌላ የአንዳንድ ከፍተኛ እስረኞችን እየከፋፈሉ ግማሹን ከርቸሌ ሲልኩ ግማሹን ደግሞ ማዕከላዊ ወስደው እንዳቆዩአቸው ይታወቃል:: በዚህ መልክ ከተከፋፈሉት የከፍተኛ 7፣ 8፣ 13፣ 14 እና 15 እስረኞች መካከል ከፊሉ በ1971 ዓ.ም. ከርቸሌ ሲላኩ ቀሪዎቹ ማዕከላዊ የቆዩት ደግሞ በ1972 ዓ.ም. ተጠቃለው ከርቸሌ ተሰበሰበዋል:: አሰራሩ ዝብርቅርቅ ቢመስልም የደርግ ባለሥልጣኖች ወደ ማዕከላዊ የወሰዷቸውን እስረኞች ለምን እንዳሰቧቸው መገመት አያዳግትም:: ከከፍተኛ እስረኞች ሌላ ብዛት ያላቸው ከማዕከላዊ፣ ከደርግ ጽ/ቤትና ከሌሎችም እስር ቤቶች ከርቸሌ የተላኩ ያልተፈረደባቸው የኢሕአፓና ሌሎች እስረኞች እንደነበሩ መታወቅ አለበት::

3. የእስረኞች ጥየቃ በከርቸሌ

አልፎ አልፎ የእስረኞች አስተዳደርን እያስፈቀዱ በአዘቦት ቀን ከሚደረገው ጉብኝት በስተቀር ማንም እስረኛ ከውጪ ጠያቂ መጥቶ ሊገናኘው የሚችለው እሁድ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ባለው ጊዜ ብቻ ነበር:: የቤተ ዘመድና የሚያውቁት ጓደኛ ጉብኝት ለእስረኛው የሚሰጠው መፅናናትና ደስታ ከፍቺ መለስ ምንም ወደር አልነበረውም:: ምክንያቱም እስረኛው ከመጠለያና መጠነኛ ምግብ በስተቀር ለእለት ተእለት ኑሮው እንደ ስንቅ፣ ልብስ፣ የመኝታ ቁሳቁሶች፣ መጻሕፍት፣ መድኃኒትና ሌሎች ማንኛ ቸውንም አስፈላጊ ነገሮች የሚያገኘው ከውጪ ጠያቂው ነበር:: ምንም እንኳን ለሕይወት ማቆያ የማያበቃ ምግብ ቢሰጥም ልብስና ሌሎች አስፈላጊ መሰረታዊ ነገሮች ከወህኒ ቤቱ ማግኘት ለአብዛኛው እስረኛ የተለመደ አልነበረም:: በእርሻ፣ እንጨት ሥራ፣ ጋራዥና ምግብ ማብሰል ለሚሰማሩ ጥቂት እስረኞችና አንዳንድ ከባድ ፍርደኞች አልፎ አልፎ ቱታ ወይም የአቡዝዴ ቁምጣና ጥብቆ ይሰጥ ነበር:: ምናልባትም በዓለም ላይ ለሰው ልጅ መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን እንደ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ያሉት በአግባብ ሳይሟሉ እስረኞች

የሚታጎሩበት እስር ቤት ከርቸሌና የሱን መሰል በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙት እስር ቤቶች ብቻ ሳይሆኑ አይቀርም:: እንግዲህ እስረኛው በሕይወት ለመቆየትና በአንዳንድ እንቅስቃሴዎችም ለመሳተፍ ከውጪው ማህበረሰብ የሚያገኘው ድጋፍ ወሳኝነት ነበረው::

እሁድ የከርቸሌ እስረኞች በውጭው ህብረተሰብ በሚጠየቁበት ቀን ከማለዳ ጀምሮ በየክልሉ ያሉ እስር ቤቶች በራቸው ቢከፈትም እስረኞች ሳይጠሩ ከቤት መውጣት አይፈቀድላቸውም ነበር:: በዚህ ቀን በክልል ደረጃ አንድ ቤት የዕለቱ የዘመድ ጥየቃ አስተናጋጅ ወይም ጠሪ ተብሎ ይሰየማል:: የቤቶች ነዋሪ ቁጥር አነስተኛ በሆነበት ክልል ብዙ ቤቶችም አንድ ላይ የቀኑ ጠሪ ለመሆን ይገደዱ ነበር:: ለዘመድ መጠየቂያ እንዲያገለግሉ የተሰሩ ከሰው ቁመት አጠር የሚሉ ማዶ ለማዶ የሚተያዩ አጥሮች በሁሉም ክልሎች የተሰናዱ ነበሩ:: በሁለቱ በወጪና በውስጥ በኩል ባሉት አጥሮች መካከል ያለው ርቀት ከአንድ ሜትር ተኩል አይበልጥም ነበር:: በእነኝህ በሁለቱ አጥሮች መካከል የወህኒ ፖሊሶች ፈንጠር ፈንጠር ብለው ቆመው በጠያቂዎችና በእስረኞች መካከል ሥራቸውን ያከናውናሉ::

ፖሊሶች ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ከውስጥ በኩል ባለው አጥር እንደ ፖሊሶቹ ፈንጠር ፈንጠር ብለው አስተናጋጅ ከሆነው ቤት የተመረጡ እስረኞች ቁጥር ተስጥቷቸው ወረቀትና መጻፊያቸውን አሹለው ይጠባበቃሉ:: ሌሎች ደግሞ ወረቀት ለማመላለስና የተጻፈውን የእስረኛ ስም ለመጥራት የተመደቡ ከዚሁ ተረኛ ከሆነው ቤት ተሰልፈው ይጠባበቃሉ:: የጥየቃው ሰዓት ሲደርስ ከከርቸሌ ውጪ እንደ አመጣጣቸው ተሰልፈው የሚጠባበቁት ጠያቂዎች በተራ እየተፈተሹ፣ የያዙትን ምግብና ልብስ እየቀመሱና እያስፈተሹ ይዘው መግባት ሲፈቀድላቸው፣ መጻሕፍትና የሚነበቡ ነገሮች የሚያስገቡት ካለ የሚልኩለትን ሰው ስምና ክልል እየጻፉ ለፖሊሶች ያስረክባሉ:: መጻሕፍትን ፖሊሶች በሌላ ጊዜ ከመረመሩ በኋላ በተላላኪዎች አማካኝነት ወደ መጻሕፍት ቤት እንዲደርሱ ያደርጉ ነበር::

ማንኛውም ጠያቂ የሚጠይቀውን እስረኛ የሚኖርበትን ክልል ማወቅ ነበረበት:: አለበለዚያ የሚፈልገውን እስረኛ ለማግኘት ትንሽ ጊዜ ሊፈጅበት ይችላል:: የሚፈልገው ክልል መጠየቂያ እንደደረሰ የሚጠይቀውን የእስረኛ ስም ያስመዘግባል:: ከውስጥ በኩል ያለው መዝጋቢ ስምና ቁጥሩን ይጽፍና ተሰልፈው በመጠባበቅ ላይ ላሉት ወረቀቱን ያቀብላል:: እነሱም በቅብብሎሽ ወረቀቱን መጥሪያው ቦታ ሲያደርሱ ጠሪው የእስረኛውን ስምና ጠያቂው የሚገኝበትን ቁጥር ይጠራል:: ከዚያም በየቤቱ በር የሚጠባበቁት ጠሪዎች ስሙና ቁጥሩን ወደ ውስጥ ሲያስተጋቡ እስረኛው ሰምቶ ከጠያቂው ጋር ይገናኝ ነበር:: ምንም እንኳን በመካከላቸው የሚቆመው ፖሊስ ማዳመጥ ቢችልም ጠያቂና ተጠያቂ የሚፈልጉትን ያወራሉ፣ ጠያቂው ያመጣውን ስንቅ፣ ልብስና ገንዘብም በፖሊሱ አማካኝነት ይቀባበላሉ:: ከዚያም እስረኛው ዕቃውን ገልብጦ ያመጣና ሌላም የሚመልሰው ዕቃ ወይም የቆሸሸ ልብስ ካለው በፖሊሱ አማካኝነት ያቀብላል:: በመካከላቸው ከአንድ ሜትር ተኩል በላይ ርቀት ስላለ ማውራትና መግባባት ቢችሉም አይገናኙም፣ ለመገናኘት ደንቡም አይፈቅድም:: በዚህ መልክ በሁሉም ክልሎች ጠያቂዎችና እስረኞች ይስተናገዳሉ:: ሰው ሲበዛ ማዶ ለማዶ ሆነው ሲያወሩና ሲንጫጩ የደራውን የመርካቶ ገበያ ምስጋን ይኑሳው::

የአብዛኛው እስረኛ ጠያቂዎች እሁድ ስለሚመጡ ከሌላው ቀን ቀኑ ልዩ ትዝታ ነበረው። የምግብ መትረፍረፍና ጓደኛሞች በሆኑ እስረኞች መካከል የሚኖረው መገባበዝ እሁድን ልዩ ያደረገዋል። ገንዘብ ከጠያቂ ያገኘው ጓደኞቹን ሻይ፣ ለስላሳና ዙር በኀኔ (በውሃ የተበጠበጠ በሶ) ሲጋብዝ፣ ሲጋራ የመጣለት ለጓደኞቹ ሲያካፍል፣ አንዱ «የሳምንት ጫታችን ተገኝቷል አያሳስብም» ሲል፣ ሌለው ደግሞ ከገጠር የመጣለትን ቆሎ፣ ዳቦ ቆሎና ጥረሾ ሲያድል፣ እሁድን የከርቸሌ ፋሲካ ያደርገዋል። በተለይም የእሁድ ጥየቃ የአገራችን በዓላት እንደ ዘመን መለወጫ፣ መስቀል፣ ገና፣ ፋሲካና የሙሲሊም በዓላትን ተንተርሶ ከመጣ ደስታው ዳርቻ ያጣ ነበር።

ከእሁድ ጥየቃ ውጭም በበዓል ቀን ከአንዳንድ ቤተሰብ የሚላከው ስንቅ የውጭውን ሕይወት ያስታውሳል። ከበዓላት ጋር በተያያዘ የከርቸሌ እስረኞች የተለያዩ ትዝታዎች አሏቸው። የሁዳዴ ጾም የሚፈታው ቅዳሜ ሌሊት በስምንት ሰዓት ቢሆንም ይህንን ለማስታወስ እሁድ ሌሊት በስምንት ሰዓት አንዳንድ እስረኞች ተሰብስበው በመመገብ ወቅቱን ያስቡ ነበር። በበዓላት ቀን እርጥብ ሳር መጎዝጎዝና ዳቦ መቁረስ፣ አንዳንዶችም መጠጥ ገዝተው ወይም ከሙዝና ከብርቱካን ጠጅ ጠምቀው መጠጣት የተለመደ ነበር። እየቆየ ተከልክሎ በድብቅ እንዲሆን እስረኛው ተገደደ እንጂ በሙስሊም በዓላት ቀን ጫት በይፋ ተፈቅዶ ተገዝቶ እየገባ ግቢው በሙሉ ሲቅም ያድር ነበር።

እሁድ ከውጪው ህብረተሰብ ሲገናኙ የተለያየ ዜና መቃረምና መጥፎም ጥሩም ነገር መስማት ያለ ነበር። በመሆኑም ከላይ እንደተዘረዘረው አንዳንዶች በደስታ ጮቤ ሲረግጡ ሌሎች የሚደበሩበት ጊዜም ነበር። መጥፎ ወሬ መስማት፣ ዘመድ ሞቶ መረዳትም ሊያጋጥም ይችላል። ብዙ ጊዜ እስረኛው ዘመድ ሲሞትበት የሚረዳው በቀጥታ ለራሱ በመናገር ሳይሆን በጓደኞቹ አማካኝነት ይሆናል። በአስተዳደሩም በኩል የሚነገራቸው ነበሩ። አስተዳደሩን መቅረብ የሚችል ከባድ ዘመድ እስረኛው ካለው ተፈቅዶለት ወጥቶ የሞተ ዘመዱን ቀብር መመለስም ይቻል ነበር። የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ የአባቱን ማለፍ በጓደኞቹ አማካኝነት ተረድቶ ነበር። ዕሁድ ከውጪው ጠያቂ ጋር መገናኛ ብቻ ሳይሆን የመዝናኛም ቀን እንደነበር ይታወሳል።

ከእስረኞች የጥየቃ ጊዜ ጥሪ ጋር በተያያዘ አንዳንድ መጥፎ አሉባልታዎችም ነበሩ። አንዳንድ በጎ ምግባር የጎደላቸው አስተናጋጅ ፀሐፊዎች ከሚፅፉት ስሞች ጋር ፀያፍ ቅጽል በመለጠፍ ውዝግብ ለመፍጠር ይከጅሉ ነበር። ለምሳሌ አንድ ሰው ከመታሰሩ በፊት ከነበረው ባህርይ በተለይ ሃይማኖቱን አጥባቂ ከሆነ በሱ ላይ ይለጠፍ የነበረው ቅጽል ስብእናን ይነካል። በሌሎችም ላይ እንዲሁ የሚያዋርድ ቅጽል መለጠፍ አልፎ አልፎ ያጋጥማል። እዚህ ላይ አሁን በሕይወት የሌለን ግለሰብ ስም ጠቅሶ ምሳሌ ማቅረብ ባይገባም «ቄስ ገበዝ መሐሪ ዮሐንስ» ተብሎ በየቤቱ ሲጠራ አንዳንዶቹን ፈገግ ቢያሰኝም መሐሪ ዮሐንስን የማይወድ ተንኮለኛ ፀሐፊ የፈጠረው መሆኑ ይታወቃል።

አንዳንድ ስሞች እውነተኛ ይሁኑ ወይም ሌላ መልእክት ለማስተላለፍ ይፈጠሩ አይታወቅም ነበር። ሲሰሟቸው የሚያስበረግጉም ነበሩ። ለምሳሌ ከእነዚህ ዓይነት ስሞች አንዱ «አደፍርስ ነቅንቁ» የሚባለው እየተለመደ ሲሄድ ተናቀ እንጅ በመጀመሪይ ሲጠራ ያናድድ ነበር። እውነተኛ መጠሪያ ስምም ሊሆን ይችላል፣ ብቻ ወደ አልሆነ አቅጣጫ ስሜትን መሳቡ አልቀረም። «አደፍርስ» በ1962 ዓ.ም. በዳኛቸው ወርቁ የተጻፈ የፊውዳሉን ስርአት የህይወት ውጣ ውረድ ገፀ ባህርይ የያዘ ተወዳጅ የልቦለድ መጽሐፍ ስም

ነው። (5) የደርግ ተቀዋሚና ደጋፊ በሆኑት በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል በተካሄደው የፖለቲካ ክርክሮች የኢሕአፓ ወገኖች በጎሕ መጽሔት ላይ ተቃውሞ ሲጽፉ «አደፍርስ» የተባለውን የብዕር ስም ተጠቅመውበታል። (6) (7) ኢሕአፓ በህቡዕ ያሰራጭ የነበረውን የተለያዩ ጽሑፎች ያባዛበት የነበረው በእጅ የሚሰራ ማባዣም «አደፍርስ» የሚል ስም ተሰጥቶት እንደነበር ይታወሳል። እንግዲህ ይህ ስም ከኢሕአፓ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር በጣም የተሳሰረ ነበር። ስለዘህ ይህንን መሰሉ የስም አጠራር የአንድን የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊዎች ስስ ገላ እንደመንካት ይቆጠራል። እነኝህን መሰል ብዙ ቧልቶችና አወዛጋቢ ስሞች በጥሪ ጊዜ ሲተላለፉ መስማት ቅር ያሰኝ ነበር።

4. የእስረኞች ትምህርት በከርቸሌ

አብዛኛው የከርቸሌ እስረኛ በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነበር። ከእነኝህም መካከል በዛ ያለው በፖለቲካ ምክንያት የታሰረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አላጠናቀቀም። አንዳንዶች ደግሞ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ከተለያየ ደረጃ ያቋረጡ ነበሩ። ሌሎች ደግሞ በዲግሪና በዲፕሎም ተመርቀው በማስተማርና በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራ የተሰማሩ ነበሩ። በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ ከዚያም በላይ ባሉ ተቋሞችና በዩኒቨርሲቲም ጭምር ሲያስተምሩ የነበሩ ይገኙባቸዋል።

ከፖለቲካ እስረኛው ሌላ የወንጀልና የፍትሐብሔር እስረኞችን ስንመለከት ከገጠር የታሰሩት ፊደል ያልቆጠሩ ሲበዙበት ከተሜው ደግሞ ትምህርታቸውን ከአንደኛና ከሁለተኛ ደራጃ ያቋረጡ ይበዙበታል። ጥቂት ለወህኒ ቤቱ አገልግሎት ከሚሰጡ የተፈረደባቸው እስረኞች በስተቀር አብዛኛው ፍርድ ያልተሰጠው በቀጠሮ ላይ ያለ እስረኛ ሥራ ፈት ስለሆነ ለጊዜ ማሳለፊያ በእጁ የገባውን መጽሐፍ ሲያነብና ሲያገላብጥ ይውላል። የተለያዩ ቋንቋዎችን ይማራል። ከቤተ ዘመድ የሚላክለትን መጻሕፍት ይመረምራል። በወህኒ ቤቱ አስተዳዳር መሠረት እስረኞችን አጉሮ እያዋከቡ እንዳይጠፉ ከመጠበቅ በስተቀር የቀለምና የሙያ ትምህርት በማስተማር ሲፈቱ ሕይወታቸውን በተሻለ እንዲመሩ ለማዘጋጀት ቀደም ብሎ በዘማቾች እንደተጀመረ የሚነገርለት ትምህርት ቤት ብዙም ትኩረት አልተሰጠውም። የፖለቲካ እስረኞችም በብዛት ከመታሰራቸው በፊት የአስተማሪዎች እጥረት እንደነበረ ይነገራል። በአፍላ የቀይ ሽብር ጊዜም የፖለቲካ እስረኞች ቁጥራቸው ቢበረክትም እንኳን በመማር ማስተማሩ ሊሳተፉ ይቅርና ከዓለም በቃኝ እንዲወጡ አይፈቀድላቸውም ነበር። ፍርድ የተሰጣቸውን እስረኞች ብቻ በእርሻ፣ በእንጨት ሥራ፣ በጋራዥ ሥራ፣ በጥልፍ መጥለፍ፣ በአጥር ማጠር፣ በምግብ ማብሰልና በሌሎች የጉልበት ሥራዎች ማሰማራት የተለመደ ነበር። ከከርቸሌ ወደ ቃሊቲና ሌሎች እስር ቤቶች የፍርድ እስረኞችን ለሥራ መውሰድም የተለመደ አሰራር ነበር። እንግዲህ እያቆየ <u>ሲሄድ</u> ከሰባት ሺህ በላይ እስረኞች ባሉበትና የፖለቲካ እስረኞች ባጥለቀለቁበት ወቅት የእስረኛውን ትኩረት ወደ አንድ አቅጣጫ ለመሳብና ለአስርም እንዳያስቸግር ለመገራት ርስ በርሱ እንዲማማር መፍቀድ የግድ ያስፈልግ ነበር።

ለዚህም እንዲያመች ቀደም ብሎ የተጀመረውን የአንደኛ ደረጃ የቀለም ትምህርት ቤት ማስፋፋት ያስፈልግ ነበር። ይህን ለማከናወን ወህኒ ቤቱ ጥበቃውን ከማጠናከርና ከማስተባበር ሌላ ወጪ አልጠየቀውም። የእስረኞች

የህብረት ሱቅ የነበረው የንግድ ድርጅት ወጪውን እንዲሸፍን ተደረገ:: እስረኛ ው ከውጪ ጠያቂው በሚያገኘው ገንዘብ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ እንደ ሳሙና፣ የሽንት ቤት ወረቀት፣ ሲጋራ፣ ደብተር፣ እርሳስ፣ እስክሪፕቶ፣ ወረቀት፣ ወዘተ. የሚገዛው ከዚሁ የህብረት ሱቅ ነበር:: የህብረት ሱቁን በወህኒ ቤቱ ቁጥጥር ስር የሚያስተዳድረው የእስረኛ የህብረት ሱቅ ኮሚቴ ነበር:: ይህ ሱቅ አንዳንድ ጊዜ ለዘረፋ ቢዳረግም ከፍተኛ ገቢና ትርፍ ነበረው::

ከዚህ ሱቅ በሚገኘው ገቢ በትምህርትና የሥራ ኮሚቴ አማካኝነት ከቆርቆሮና ከአስቤስቶስ ትምህርት ቤቶች ተሰሩ፣ መቀመጫ ዴስኮች ተዘጋጁ፣ ሌላም ሌላም ለትምህርት አስፈላጊ ነገሮች ተደራጁ:: አስተማሪዎች ከእስረኛው ተመርጠው በነፃ ማስተማር ጀመሩ:: ለመምህራን የጽሕፈት መሣሪያ፣ ቾክ፣ ዳስተርና ሌሎች አስፈልጊ ነገሮችም ወጪ የሚደረገው ከዚሁ ከህብረት ሱቅ ነበር:: በዚህ መልክ የተጀመረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየሰፋ ሄዶ የከርቸሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተቋቋመ:: በኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና አጥጋቢ ውጤት ለማምጣትና በተወሰነ ወቅት በአገሪቱ በአንደኝነት ስሙን ሊያስጠራ ቻለ::

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማቋቋም አንዳንድ አጋጣሚዎች ያገዙ ቢሆንም እንቅፋቶችም ነበሩ:: በ1971 ዓ.ም. አንዳንድ በግል ከከርቸሌ ውጭ ይማሩ የነበሩ የወህኒ ቤቱ ባለሥልጣኖች የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ እንዲያመቻቸው በእስር ላይ ከነበሩት መምህራን መካከል ይልማ ኪዳነማርያምን፣ ሠራዊቱ ይመርንና ሌሎችንም እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ይጠይቃሉ:: (8) እነኝህ አስተማሪዎች በዚህ ግኑኝነት በመጠቀም በከርቸሌ ብዙ ምሁራን ታስረው እንደሚገኙ በማስረዳት ቀደም ብሎ ሲሰጥ ከነበረው ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በማስተማር የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ማስፈተን እንደሚቻል የወህኒ ቤቱን አስተዳደር ያሳምናሉ:: (9) የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናን በከርቸሌ ለማስፈተን ትምህርት ቤቱ እንደ አንድ የፈተና ጣቢያ እንዲቆጠር በቅድሚያ ማስፈቀድ ስለሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ፈተና ከሚያዘጋጁት ኃላፊዎች ጋር ለመነጋገርና ስምምነት ለማግኘት ሠራዊቱ ይመር በፖሊስ አጃቢነት ይላካል:: በተልኮውም የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ፈተና ኃላፊ ለነበረው ለዶ/ር መኮንን ይመር የከርቸሌን ወጣቶች የመማር ችግር በማስረዳት ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ::

በዚህ ስምምነት መሰረት የመጀመሪያው የከርቸሌ ተማሪዎች በ1972 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ወሰዱ:: እነኝህ ተፈታኞች አብዛኞቹ ከመታሰራቸው በፊት አሥራ ሁለተኛ ክፍል የደረሱ፣ አንዳንዶቹም ጀምረው ያቋረጡ ወይም ያጠናቀቁ በመሆናቸው ለመዘጋጀት ብዙም ችግር አልገጠማቸውም:: ከነሱ በኋላ በቀጣይነት በተከታታይ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሚደርሱትን ተማሪዎች ለማስፈተን ትምህርት ቤቱ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት እውቅና ማግኘት ስለነበረበት የተለያዩ ተቆጣጣሪዎች እየተላኩ የትምህርቱ ጥራትና የአስተማሪዎች ብቃት እየተገመገመ ማረጋገጫ ሊያገኝ ችሏል::

ትምህርት በከርቸሌ ቢስፋፋም ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥመውታል:: የአገሪቷ መሪ የነበረው ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም «እስር ቤቶች ትምህርትና ሐኪም ቤቶች ይሆናሉ» በሚል ያሰማው መፈክርና ለመሰረተ ትምህርት ዘመቻ የሚደረገው ቅስቀሳ ባያግዘው ኖሮ በእንጭጩ ይቀጭ ነበር::

(!0) ከርቸሌ አንድ ነገር ለመሥራት ሲታሰብ በእስረኛው መካከል መቀናናትና አሻጥር መሸረብ ይጀመራል:: ከአንደኛ ደረጃ በላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመክፈት ሲታሰብ እንዴት ተደርጎ ይታሰባል የሚሉ አንዳንድ የፖለቲካ እስረኞች አስተዳደሩን ግራ ያጋቡት ጀመር:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቢጀመር በአብዛኛው ተጠቃሚ የሚሆኑት ብዛት ያላቸው የኢሕአፓ ደጋፊ ወጣት እስረኞች ነበሩ:: የኢሕአፓ ወጣት ከመታሰሩ በፊት የትምህርት ጊዜውን መሰዋዕት በማድረግ በትግል ያሳለፈ ስለነበረ ባላንጦቹ ይህ «ትምህርት ከድል በኋላ» ሲል የነበረ ወጣት ማመር የለበትም በማለት ተቃወሙ::

በአንዳንድ ከደርግ ወገን በነበሩ እስረኞች አነጋገር የወህኒ ቤቱ አስተዳደር ሳይደናገጥ የሁለተኛ ደረጃው ትምህርት በታሰበው መልክ እንዲቀጥል ፈቀደ:: ለዚህ የብዙ ወጣቶችን የመማር እድል ላጎናፀፈው፣ ከተፈቱም በኋላ የወደፊት ሕይወታቸውን ለለወጠው ቆራጥ ውሳኔ ለሰጡት የወህኒ ቤቱ አዛዥ ለኮለኔል ተሸመ ወለደየስና የጥበቃ ክፍሉ ሹም ለሻለቃ ታደሰ ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል:: በተጨማሪም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱን ከሌሎች ከተፈቱ እስረኞች ተረክቦ በርዕስ መምህርነት እያስፋፋና እያሳደገ መጥቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲጀመር ታላቅ ተጋድሎ ያደረገው አማረ ወልደሥላሴም መመስገን ይገባዋል::

የከርቸሌ የትምህርት ሂደት በውጪ እንደነበረው ዓይነት አልነበረም:: ሴትና ወንድ እስረኞች አብረው አንድ ክፍል አይማሩም:: በግቢው አንድ ችግር ሲፈጠር ወይም እስረኛ ሲጠፋ ትምህርት ቤቱ ቀርቶ እስረኞች በየቤታቸው ቀንም ማታም ይዘጋባቸው ነበር:: የዓለም በቃኝ መውጫና መግቢያ «ፖርታ» በፖሊስ ስለሚጠበቅ አስተማሪም ሆነ ተማሪ እያስፈቀደ መውጣትና መግባት ነበረበት:: ትምህርት ቤቱ እየታወቀና እየተስፋፋ ሲመጣ የወህኒ ፖሊስ አባሎችና ከውጪ የሚመጡ ዘመዶቻቸውን ማታ ለማስተማር መምህራን ከቆጠራ በኋላ ትምህርት ቤት እንዲያመሹም ማስፈቀድ የግድ ነበር::

ማንም እስረኛ ከከርቸሌ ውጪ በፖሊስ አጃቢነት መውጣት ስላለበት አንዳንድ የትምህርት መሣሪያዎች ለመግዛትና ስለ ትምህርትም ጉዳይ ከትምህርት ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችና ተቆጣጣሪዎች ጋር ወጥቶ ለመነጋገር ጣጣ ነበረው:: ለነኝህ ሁሉ ችግሮች መፍትሔ የሚገኘው ከወህኒ ቤቱ አስተዳደር፣ ከጥበቃ ክፍል ሹሙ፣ በግቢው ውስጥ የሚመደቡት የየዕለቱ ጠባቂ ፖሊሶችና በዕለቱ እነሱን በቅርብ የሚያዛቸው ተረኛ መኮንን የሚሆነው ባሻ ጋር በመለማመጥ ነበር:: ታዳያ እነዚህን መሰል ችግሮች ሲያጋጥሙ አንዳንድ ጊዜ በማያውቀው ፖሊስ በዱላ እየተዠለጠም፣ እየተለማመጠም፣ ትምህርት እንዳይቋረጥ፣ አስተማሪዎችና ተማሪዎች መውጣት እንዲፈቀድላቸው የሚያደርገው አማረ ወልደሥላሴ ነበር::

ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት የከርቸሌን ትምህርት የሚያደናቅፉ ችግሮች መካከል የእስረኞች መጥፋትም ዋናው ነበር:: የታሰሩ እስረኞች ደግሞ በየጊዜው ለመጥፋት መሞከራቸው አይቀርም:: በተለይም ወንጀልን ሙያ ያደረጉ እስረኞች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለመጥፋት ይሞክራሉ:: በነሱም የተነሳ የግቢው እስረኛ በሙሉ ይተራመሳል:: በጥየቃ ጊዜ ከውጪ ሰው ጋር ተደባልቆ ለመውጣት መሞከር፣ በአጥር ሾልኮ መጥፋት፣ ቤት ሰብሮ መውጣት፣ በመዝናኛ ጊዜ በሚፈጠረው ግርግር አምልጦ መጥፋት፣ ወዘተ. ያጋጥም ነበር:: ለህክምናም ሆነ ፍርድ ቤት ለመቅረብ በፖሊስ አጃቢነት በሚላኩበት ጊዜ አጃቢውን አሞኝቶ መሰወርም ያጋጥማል::

ከግቢው እስረኛ መጥፋቱ የሚታወቀው በቆጠራ ጊዜ ሲጎድል ስለነበረ ማታ የባውዛ መብራት እያበሩ መፈለግና ከተሸሽገበት አድኖ መያዝ ወይም ሲያመልጥ ሲልም መግደል ያጋጥማል:: አምልጠው ወጥተው ከውጪ ተፈልገው የሚያዙም ነበሩ:: አንድ ጊዜ ቀን በአጥር ሾልኮ አምልጦ ከርቸሌ ማዶ የሚገኘው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤት ገብቶ የተያዘም ነበር:: ሌሊት ቤት ሰርስረው ሰብረው የሚጠፉት የማምለጥ እድላቸው የሰፋ ነበር:: አንድ ጊዜ ከቀጠሮ ሰባተኛ ቤት ሁለት እስረኞች የሽንት ቤት ግድግዳ ሰብረው ስለጠፉ የቤቱ እስረኞች በሙሉ ሳትተባበሩ አትቀሩም በሚል ሰበብ ሦስት ቀን ተዘግቶባቸው ተሰቃይተዋል:: ወንጀልን ሙያ ካደረጉ እስረኞች ሌላ የፖለቲካና ሌሎች የወንጀል እስረኞችም አልፎ አልፎ ያመልጡ ነበር::

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሲጀመር የተለያዩ ተማሪዎች ባላቸው የትምህርት መረጃ መሰረት በያቋረጡበት የትምህርት ደረጃ ስለጀመሩ ከመጀመሪያው ጀምሮ ከ9-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ነበሩ:: ነገር ግን በዛ ያሉት ተማሪዎች 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ነበሩ:: ከርቸሌ የአስተማሪዎች ችግር መጀመሪያው ላይ አላጋጠመውም:: ከዩኒቨርስቲ ምሁራን ጀምሮ ሌሎች በየደረጃው ሲያስተምሩ የነበሩ አስተማሪዎች፣ በሌላ ሥራ ተሰማርተው የነበሩ ባለሙያዎች፣ በዩኒቨርስቲ በተለያዩ ፋኩሊቲዎች ይማሩ የነበሩ የሦስተኛና የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ሁሉም ለማስተማር ዝግጁ ነበሩ:: ትምህርት እየተስፋፋ ሲሄድ በፖለቲካ ልዩነት የተነሳ ሲቃወሙ የነበሩትም ልዩነታቸውን እያቻቻሉ ማስተማሩን ተያያዙት:: ደርግ በሥራ ያልተረጎመውን መፈክር ከርቸሌ በሥራ ላይ አዋለው::

በገቡበት የፖለቲካ ትግል ምክንያት ውጪ ትምህርታቸውን አቋርጠው የነበሩት ተማሪዎችም በትጋት መማር ጀመሩ:: መምህራንና ተማሪዎቻቸው ያላቸው ግኑኝነት በትምህርት ቤት ብቻ ሳይወሰን አብረው ስለሚውሉና ስለሚያድሩ የመማር ማስተማሩ ያልተጠበቀ ውጤት ሊሰጥ ቻለ:: በዚህም የተነሳ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ውጤት ሰመረ:: ለምሳሌ በ1973 ዓ.ም. ከነበሩት አነስተኛ ቁጥር ካላቸው ተፈታኞች መካከል 32 ተማሪዎች በማዕረግ አለፉ:: ለዚህ ውጤት ማማር የወህኒ ቤቱ አስተዳዳር፣ መምህራኑ፣ ከውጪ የማያቋርጥ ድጋፍ ያደረጉት፣ መጻሕፍት ቤት ለማቋቋም የረዱት፣ የማስተማሪያ መጻሕፍትና ቴሌቪዥን የለገሱት፣ በየጊዜው እየመጡ የትምህርት ጥራቱን የሚቆጣጠሩት የትምህርት ሚኒስቴር ተቆጣጣሪዎች፣ ሁሉም የየራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል:: በከርቸሌ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎችም ከተፈቱ በኋላ ከፍተኛ ትምህርት ተከታትለው ሐኪሞች፣ መሐንዲሶች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የእርሻ ባለሙያዎች፣ አስተማሪዎች፣ ወዘተ. በመሆን አገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

የከርቸሌ እስረኞች ብዛት በየጊዜው ይቀያየራል:: የትምህርት ቤቱ ተማሪዎችና መምህራንም እንደዚሁ ይቀያየር ነበር:: በዚህ የተነሳ መምህራን የሚሰጡት ነፃ አገልግሎት እንዳይቋረጥና ትምህርት ቤቱ እንዳይዳከም የሁሉንም ጥረት ይጠይቅ ነበር:: ታዲያ የሚፈታን ሰው ታስረህ ተቀመጥ ማለት ስለማይቻል ሁል ጊዜ ምትክ ማፈላለግ ያስፈልጋል:: ለዚህም በየክልሉ የቆየውንም ሆነ አዲስ መጡን ሊያስተምር የሚችል ግለሰብ ማቅረብ፣ ማግባባትና እንዲያስተምር መመልመል ይጠበቃል:: ይህም የሚደረገው ሰውየውን በሚመስለውና በጓደኛው አማካኝነት በመቅረብ ነበር:: በዚህም የተነሳ ትምህርት ቤቱ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባል የነበሩ ጥራት

ያላቸው መምህራን ለማሰባሰብ ቻለ:: እዚህ ላይ በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ሲያስተምሩ የነበሩትን መምህራን በሙሉ መዘርዘር ባይቻልም ረዘም ላለ ጊዜ በማስተማርና በትምህርት ቤቱ አመራር አገልግሎት ያበረከቱትን መዘከር ያስፈልጋል::

በተደጋጋሚ በመምህራን እየተመረጠ ርዕሰ መምህር በመሆን ሲያገለግል የነበረው አማረ ወልደ ሥላሴ እንደነበረ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል:: የሱ ምክትል በመሆን በመጀመሪያ ሠራዊቱ ይመር ከዚያም ዮሐንስ ክፍሌ ብዙ አበርክተዋል:: ሌሎች በአስተዳደሩ ሥራ የሚያግዟቸው እነ ስለሞን እሸቴ፣ እምሩ ታምራት፣ ገብረወልድ ወልደሰንበት፣ የሱፍ ሐሰን፣ ገብረ ፅዮንና ኤልያስ ኑር የሚጠቀሱ ናቸው:: አማረ ወልደ ሥላሴና ዮሐንስ ክፍሌ ከተፈቱ በኋላ እነሱን በመተካት በመምህራን ተመርጠው ሻምበል አሊ ጋዝ ከበደ በርዕሰ መምህርነትና ጴሬሳ ቂጤ በምክትልነት አገልግለዋል:: የሴቶች ክልል የትምህርት አመራርን በማስተባበር ትልቅ ሚና የተጫወቱት ሳባ ኪዳነማርያም፣ ሮማን ገዛኸኝና ገነት በርሔ ይታወሳሉ:: ከደርግ ጋር በተካሄደው ትግል ሴቶች ከወንዶች የማይተናነስ ተጋድሎ አበርክተዋል:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተለያየ ቦታ እንደተጠቀሰው ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ተገድለዋል:: በእስር ጊዜም ከወንዶች የተለዩ አስከፊ ችግሮች ነበረባቸው:: ይህንን ሁሉ ተቋቁመው ሴቶች በወህኒ ቤቱ በተፈጠረው የትምህርት እድል እንዲሳተፉ በማድረግ ላበረከቱት እነኝህ የሴቶች ክልል የትምህርት አመራሮችና ሌሎችም በማስተማር የተሳተፉ ሴት እስረኞች ከወንዶች በበለጠ ሊመሰገኑና ሊወደሱ ይገባል::

የትምህርት ቤት አመራሮች ምንጊዜም ቢሆን የሚመረጡት ሚስጥራዊ በሆነ የድምፅ አሰጣጥ በድምፅ ብልጫ ነበር:: የተመረጡበት የጊዜ ገደብ ሲያልቅ ወይም ርዕሰ መምህር ሲፈታ የአስመራጭ ኮሚቴ ይመረጣል:: በዚህ ጊዜ ብዙ ፍትጊያ ያጋጥማል:: ለመመረጥ የሚፈልጉ ግለሰቦች ስውር ባህርይ ሁሉ የሚንፀባረቀው በዚህ ጊዜ ነበር:: ርዕሰ መምር ሆኖ ተመርጦ እንደ አመቺነቱ በትምህርት ሥራ ጉዳይ በማሳበብ ከከርቸሌ ውጪ በመውጣት ለሚገኝ ጥቅም ለራስ በማድላት የሌላውን ስም ማጣጣልና ማጉደፍ በምርጫ ጊዜ ይበረታል:: ለምሳሌ አማረ ወልደ ሥላሴ በተደጋጋሚ ቢመረጥም እሱን በማንቋሸሽ የትምህርት ደረጃው ለሁለተኛ ደረጃ ርዕሰ መምህርነት አያበቃውም እያሉ በማስወራት ለመጣል ያልተደረገ ሙከራ አልነበረም:: ነገር ግን በሱ ጥረት ትምህርት ቤቱ ከምን ተነስቶ ምን እንደደረሰ ብዙ መምህራን ስለሚያውቁና በተግባር የተፈተነ ስለሆነ በተደጋጋሚ ሊመረጥ ችሏል:: እሱ ከተፈታ በኋላ ሌላ ርዕሰ መምህር ለመተካት ውስብስብ ችግሮችና አሉባልታዎች ቢያጋጥሙም በጊዜው የተሰየመው አስመራጭ ኮሚቴ እንደ ጌታቸው ኩምሳ ያሉ ጠንካራ ግለሰቦች ስለነበሩበት በአብዛኛው መምህራን ተቀባይነት ሊያገኝ በቻለው በሻምበል አሊ ጋዝ ከበደ መተካት ተቻለ:: ምንም እንኳን የርዕሰ መምህር ምርጫ በተካሄደ ቁጥር የሚናፈሰው ጉምጉም ምርጫው ካበቃ በኋላ እየታመቀ ቢቀርም የአንዳንድ መምህራን የራስ ወዳድነት በህርይ ማንፀባረቅ የሚረሳ አይደለም::

ምንም እንኳን ሁሉንም መጥቀስ ባይቻልም ረዘም ላለ ጊዜ በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች በነፃ በማስተማር አገልግሎት ካበረከቱት መካከል የሚቀጥሉት የሚጠቀሱ ናቸው::

1. ቋንቋ:- ሠራዊቱ ይመር፣ ራሔል መስፍን፣ ታምራት ሳሙኤል፣ ገነት በርሔ፣ ተድላ ጥላሁን፣ አብርሃም ጨጋ፣ ሺፈራው ኪዳኔ፣ ሰይድ ይማም፣ ኃይሌ ሐለፎም፣ ተሾመ ገብረሥላሴ፣ ንጉሤ ሰይፉ፣ አብዲ፣ ዮሐንስ ክፍሌ::

2. ቀጥር:- አሥራት አንዳለ፣ ይተፋ ጆቴ፣ ደብረወርቅ አምደወርቅ፣ ይልማ ኪዳነማርያም፣ ገብረሚካኤል፣ አሰፋ ሐጎስ፣ ግርማ ስሜ፣ ደመላሽ በላይ፣ አለማየሁ ኮንዴ::

3. ኬምስትሪ:- ወርቁ ገብሬ፣ ስለሺ፣ ተክላይ በርሔ፣ ጌታቸው ተሰፋዬ፣ ጋሻው አበበ፣

4. ፊዚክስ:- ሙሉጌታ በቀለ፣ አብርሃም አንግዳ፣ ሰለሞን ቢልልኝ፣ ተሰፋዬ ጥላሁን፣ አለማየሁ አሸቴ፣ ነጋሽ ከበደ፣ አብርሃም ወልደሚካኤል፣ በለጠ፣ አሊጋዝ ከበደ::

5. ባዮሎጂ:- አበራ ገይድ፣ ተክልዬ በቀለ፣ አባተ ጉድንፋ፣ ታወቀ ጉልላት፣ ዳንኤል ገብረየሱስ፣ አስፍሐ፣ ቀለመ::

6. ጂኦግራፊ:- ሺፈራው መልሰው፣ ሳሙኤል ገዛኸኝ፣ መኳንንት አጅጉ፣ ፀጋዬ ደንበባ፣ ዴሬሳ ቀጤ::

7. ታሪክ:- አማረ በዳዳ፣ ጌታቸው ኩምሳ፣ ሰለሞን ወርቅነህ፣ ሞገስ እቁባይ፣ ነፃነት መንግሥቱ፣ ታደለች ኃይለሚካኤል::

8. ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች:- ታደሰ ይበርታ፣ የአቦወርቅ ኃይሌ፣ ሥነ ተፈራ፣ ደለለኝ፣ ፀጋዬ ከምሲ፣ ቡሊ ነጋሳ፣ ኑረዲን፣ ገነት ዘውዴ::

ከመደበኛ ትምህርት ሌላ ለጀማሪዎች የመሰረተ ትምህርት ይሰጥ ነበር:: ለዚህ ተግባር በየቤቱ የነበሩትን ማንበብና መጻፍ የማይችሉትን ግለሰቦች የሚመዘግበው፣ እንዲማሩ የሚገፋፋውና የሚጎተጉተው የትምህርትና የሥራ ኮሚቴ ነበር:: የመሰረተ ትምህርት በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት ድጋፍ በዘመቻ መልክ የሚካሄድ ስለነበረ ለማስፈጸም ችግር አላጋጠመውም::(11) ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ አንዳንድ የሙያ ትምህርትም ለማስተማር ሙከራ ተደርጓል:: ከርቸሌ በእስር ላይ እያሉ የተግባር ትምህርት ልምድ ለመስጠት በማይቻልበት ሁኔታ የሙያ ትምህርት ለማስተማር ያዳግታል:: እንኳን የሙያ ትምህርት ለማስተማር ይቅርና ከመደበኛው የቀለም ትምህርት ዘርፍ እንደ ባዮሎጂና ኬምስትሪ ያሉትን በቃል ብቻ በማነብነብ ማስተማር ከባድ ነበር:: ቢሆንም በሙያ የትምህርት ዘርፍ የንግድ ሥራ፣ የርሻና የመኪና ጥገና (Auto Mechanics) ትምህርቶች ይሰጡ ነበር:: የንግድ ሥራ ትምህርቱ ውጤታማ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንድ እስረኞች ሲፈቱ ሥራ ለማግኘት ጠቀሜታ ነበረው:: የመኪና ጥገና ትምህርቱን በወህኒ ቤቱ ካለው የጋራዥ ሥራ ጋር በማገናኘት ለማስተማር የዚህ ባለሙያ የነበረው ኢንጅነር በለጠ ይጣጣር ነበር:: የሙያው የትምህርት ዘርፍ ሲቋቋም ከመደበኛው ትምህርት ጋር ተፎካካሪ ለማድረግና በአመራሮቹም መካከል የማይገባ ውድድር ለመፍጠር የተደረገው ሙከራ ቀስ በቀስ እየሟሸሸ ሄደ::

ከእነዚህ ሦስት የትምህርት ዘርፎች ሌላ ልዩ ልዩ የግል ጥናቶችና ትምህርቶች ይካሄዱ ነበር:: የፊዚክስ መምህራን አስራ ሁለተኛ ክፍል ላጠናቀቁ ተማሪዎች ከፍተኛ ትምህርት ያስተምሩ ነበር:: እንደ ፈረንሳይኛ፣ አረብኛ፣ ጀርመንኛና ግዕዝ የመሳሰሉ ቋንቋዎች ትምህርት በትምህርት ቤት፣ በቤተክርስቲያን፣ በመስጊድና በየቤቱ ጭምር እንደ አመቺነቱ ይካሄድ ነበር::

የከርቸሌን የትምህርት እድገት ለማስፋፋትና የእስረኛውን የማንበብ ልምድ ለማጎልበት መጻሕፍት ቤት ማቋቋም በጣም አስፈላጊ ነበር:: አንዳንድ እስረኞች ሲፈቱ በስጦታ መልክ ለወህኒ ቤቱ ካበረከቱት በስተቀር ብዛት ያለው የመጻሕፍት ጥርቅም በከርቸሌ አልነበረም:: በዚህ የተነሳ ለተለያዩ የትምህርት ተቋም፣ የመጻሕፍት ቤትና ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ግለሰቦች የመጻሕፍት እርዳታ እንዲያደርጉ ጥያቄ በማቅረብ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ከውጪ በእርዳታ ሊሰበሰቡ ቻሉ:: የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ወመዘክር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች፣ ማዘጋጃ ቤት፣ ኩራዝ የመጻሕፍት አሳታሚ ድርጅት፣ የእንግሊዝ ቤተ መዛግብት («ብሪቲሽ ካውንስል»)፣ ወዘተ. የተለያዩ መጻሕፍት በእርዳታ ሰጥተዋል:: ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል የተወጣጣው እስረኛ ከራሱም ሆነ ከሌሎች ለማስተማሪያና ለንባብ የሚያገለግሉ በርካታ መጻሕፍት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያሰባስብና ትልቅ መጻሕፍት ቤት ሊያቋቋም ቻለ:: በእርዳታ ከተገኙት መጻሕፍት ሌላ ከእስረኛው የህብረት ሱቅ በሚሰጠው ገንዘብ በወቅቱ የሚታተሙ መጻሕፍትን መግዛት ተቻለ:: በየጊዜው የሚታተሙ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማግኘት ተቻለ::

የተቋቋመው መጻሕፍት ቤት ትልቅ ነበር ማለት ይቻላል:: በግምት ከ80-100 የማያንሱ ሰዎች በአንድ ጊዜ ተቀምጠው እንዲያነቡ የሚያስችል ቦታና መቀመጫዎች ነበረው:: ዘወትር በአንባቢ እንደተጨናነቀ ይውላል:: ማታም በየቤቱ ተመዝግበው መጽሐፍ እንዲመጣላቸው ለሚጠይቁ አንባቢዎች በቤቱ የትምህርትና የሥራ ኮሚቴ አማካኝነት ይደርሳቸዋል:: ጠዋት ከመጻሕፍት ቤት በውሰት ለየቤታቸው የወሰዱትን መጻሕፍት ኮሚቴዎች ይመልሳሉ:: በአንድ ቤት የመጻሕፍት ቤት ሠራተኛ ካለ የትምህርትና የሥራ ኮሚቴን ተግባር በመረከብ መጻሕፍት መዋስና መመለሱን ሊሰራ ይችላል:: መጻሕፍት ቤቱ ከእስረኛው በተመረጡ በነፃ የሚያገለግሉ ስለ መጻሕፍት ቤት ሥራ መጠነኛ ልምድ ባላቸው ግለሰቦች ይመራል:: የአንባቢው ብዛት ያሉትን መጻሕፍት በየጊዜው ስለሚያስረጃቸው የመጻሕፍት ቤት ሠራተኞች ትልቁ ሥራቸው በየጊዜው መጽሐፍ መለበድ ነበር:: ቤተ መጻሕፍቱ ከውጪ ለእስረኞች የሚላኩ መጻሕፍትንም እንዲደርሳቸው ያደርጋል:: ማንኛውም የሚነበብ መጻሕፍት፣ ጋዜጣና መጽሔት ከውጪ ከቤተ ዘመድ ወይም ከጓደኞች ለእስረኛው ሲላኩ መጀመሪያ አስተዳደሩ ከመረመራቸው በኋላ በተላላኪዎች አማካኝነት ወደ መጻሕፍት ቤት ይተላለፋሉ:: ከዚያም መጻሕፍት ቤቱ ለተላከለት ግለሰብ እንዲደርሰው ያደረግ ነበር::

5. የእስረኞች መዝናኛ በከርቸሌ

ከእስር ጋር በተያያዘ መዝናናት ያልተለመደ ቢመስልም በከርቸሌ በመጠኑ የመዝናናት ሕይወትም ነበረበት:: ከቤት ውስጥ አነስተኛ መዝናኛዎች ጀምሮ እስከ ውጪ ግቢ አቀፍ መዝናኛዎች ይዘጋጁ ነበር:: ከርቸሌ አቀፍ መዝናኛ የሚዘጋጀው የመዝናኛ ኮሚቴ ከአስተዳደሩ ጋር በመነጋገርና በማስፈቀድ ሲሆን አስተዳደሩም ራሱ አንዳንድ ጊዜ እንደ ገንዘብ ማግኛ ዘዴ ስለሚጠቀምበት ለመፍቀድ አያንገራግርም ነበር:: በመሰረቱ የወህኒ ቤቱ አስተዳደር በጥበቃም ሆነ በገንዘብ ማግኛ ረገድ ከእስረኛው ጥቅም የሚያገኝበት መስሎ ከታየው ምንም ነገር ከመፍቀድ ወደኋላ አይልም:: እስረኛውም ቢሆን የራሱን ስሜት ከማርካት አልፎ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ለሚያካሂደው እንቅስቃሴ

መዝናኛውን እንደ ገንዘብ ማግኛ ምንጭ ይጠቀምበታል:: ስለዚህ በሁለቱም በኩል ሰጥቶ መቀበል ነበር ማለት ነው::

የቤት ውስጥ መዝናኛዎች ውስን ስለነበሩ ብዙም የሚነገርላቸው አይደለም:: ቢሆንም አንዳንድ ጨዋታዎች፣ ቀልዶች፣ በክራር ታጅቦ መዝፈን፣ አነስተኛ ቢንጎ ማጫዎት፣ የመሳሰሉት እሁድ ማታ፣ በበዓላት ቀንና የቆየ እስረኛ ሲፈታ ይዘጋጃሉ:: ይህን መሰል መዝናኛ የሚያገለግለው በጊዜ ማሳለፊያነቱ እንጅ በገንዘብ ማግኛነቱ አልነበረም:: የቤት ውስጥ መዝናኛዎች ሁሉንም የቤት አባላት የሚያሳትፉ የጋራ መዝናኛዎች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በግል ወይም በቡድን በድብቅ የራሳቸውን ጊዜ ማሳለፊያ በመፍጠር፣ ጫት መቃምና መጠጥ አስገብቶ መጠጣት የመሳሰሉት የተለመዱ ነበሩ:: ይህን መሰል የግል ድርጊት የወህኒ ቤቱን ደንብ በመጣስ የሚደረግ ስለሆነ ለቅጣት አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል:: የወህኒ ቤቱ ጥበቃ ከደረሰበት የፖሊስ ዱላና ርግጫ መቅመስ ሊያስከትል ይችል ነበር:: ጠበቅ ካለም ዓለም በቃኝ በቅጣት ሊያስገባ፣ እንደ አዲስ እስረኛና እንደ ልዑካን ለስፖርትም ሆነ ለትምህርት እንዳይወጡ መታገድን ያስከትላል:: ይህን መሰል ቅጣቶች በየትም ክልል ያሉ እስረኞች ሲያጠፉ እንዲታረሙ በአስተዳደሩ የሚወሰዱ እርምጃዎች ነበሩ:: አስተዳደሩ ከዓለም በቃኝ የከፋ በግል የሚያስርበት ጨለማ የቅጣት ክፍልም ነበረው::

የግቢ አቀፍ መዝናኛዎች ብዙ ጊዜ የሚዘወተሩት ቅዳሜና እሁድ ቢሆንም አልፎ አልፎ በሌሎች ቀንም ይካሄዳሉ:: በጣም የሚዘወተሩት የጊዜ ማሳለፊያዎች የእግር ኳስ ጨዋታ፣ የሙዚቃና የቪዲዮ ትርኢቶች ነበሩ:: ለዚህም ሲባል በእስረኛው የተቋቋሙ ስድስት የእግር ኳስ ቡድኖች ዘወትር እሁድና ቅዳሜ ውድድር ያካሂዳሉ፣ ከውጪ ቡድኖችም ጋር ይጋጠማሉ:: ከርቸሌ ከሚገኙት የእግር ኳስ ቡድኖች መካከል አንዳንድ ጊዜ አንድ ቡድን ብቻውን ወይም የተወጣጣ ምርጥ ቡድን በማዘጋጀት ከውጪ ከሚጠሩ የአዲስ አበባ ቡድኖች ጋር በማጋጠም ጨዋታውን እስረኛው ገንዘብ ከፍሎ እንዲመለከተው ይደረጋል:: የከርቸሌ የእግር ኳስ ምርጥ ቡድን ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም:: በ1970 ዎቹ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት አካባቢ በአገራችን ጠንካራ የነበሩትን ክለቦች እንደ ኦሜድላና እርምጃችንን በኋላም ደግሞ የባህር ትራንሲት የመሳሰሉትን ከመቋቋም አልፎ አንዳንድ ጊዜም ያሸንፍ ነበር::

በወህኒ ቤት ታስሮ የነበረው ወጣት የእግር ኳስ ያፈቅራል:: ብዙም ጥሩ ተጫዋቾች ነበሩበት:: በመካከላቸው አንዳንድ ከመታሰራቸው በፊት ታዋቂ የነበሩ የኢትዮጵያ ወጣት ቡድን ተጫዋቾች፣ የእግር ኳስ አሰልጣኞችና የእግር ኳስ ዳኞች ይገኙባቸዋል:: እንዲያውም የእግር ኳስ ስፖርት እየተስፋፋ ሲመጣ የእግር ኳስ ዳኝነትና የአሰልጣኞች ስልጠና ከኢትዮጵያ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን በተጋበዙ ባለሙያዎች የተሰጠበትም ጊዜ ነበር:: ምንም እንኳን የከርቸሌ የእግር ኳስ ቡድኖች የፋይናንስና የማቴሪያል እጥረት ቢኖሮቸውም የወህኒ ቤቱ ጥበቃ በሚፈቅደው መሰረት የነበሩት ቷጫዋቾች ተገቢውን ልምምድ በየጊዜው ያደርጋሉ:: አቅም በፈቀደ መጠንም ደጋፊዎቻቸው ትጥቅ ያሟሉላቸው ነበር:: ለገንዘብ ማግኛ ይረዳቸው ዘንድ ከመዝናኛና ከበጎ አድራጊ ደጋፊዎቻቸው ከሚያገኙት ገንዘብ ሌላ የራሳቸው ሻይ ቤቶች እንደነበሯቸው በከርቸሌ ይካሄድ የነበረው የንግድ እንቅስቃሴ ይመሰክራል:: የከርቸሌ የእግር ኳስ ቡድኖቹ

ለራሳቸው ከሚያስገኙት ገቢ በተጨማሪ ለትምህርትና ለሌላውም የግቢ አቀፍ እንቅስቃሴ ይጠቀሙ ነበር።

ታዲያ እንደ ትምህርት ሁሉ የከርቸሌ የእግር ኳስ ስፖርትም የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት መንፀባረቂያ ለመሆን ይቃጣው ነበር። በተለያዩ የእግር ኳስ ክለቦች የሚጫወቱት ወጣቶች ልዩነት ባይኖራቸውም አንድን ክለብ ካንድ የፖለቲካ ቡድን እስረኞች ጋር በመለጠፍ ሌላውን ደግሞ ከሌላ ጋር በማመሳሰል ገለልተኛ ተመልካችን ያወናብድ ነበር። ይህም የሚመነጨው የእግር ኳስ ክለቦቹ የአመራር ኮሚቴ አባላት ከሆኑት ግለሰቦች ጋር በማዛመድ ወይም ከክለቦቹ ስሞች ጋር በማቆራኘት እንጂ ሌላ ምንም መሰረት አልነበረውም። በዚህ የተነሳ እግር ኳስ የሚጫወቱ አዳዲስ እስረኞች ሲመጡ ለመመልመልና የክለብ አባል ለማድረግ የነበረው እርኩቻ ቀላል አልነበረም። እንዲያውም አንድ ክለብ የተሻሉ ተጫዋቾችን አሰባስቦ አቋሙ እንዳይንርና ሌለው ደካማ እንዳይሆን አዳዲስ ተጫዋቾች ሲመጡ ችሎታቸው እየታየ በየክለቡ እንዲደለደሉ ቢደረግም ልዩነታቸውን ማቀራረብ አስቸጋሪ ነበር። እንኳን የእግር ኳስ ተጫዋች ደጋፊም ለማበርከት የነበረው መጠላለፍ አይጣል ያሰኛል።

የዚህ የኳስ ጭቅጭቅ ከእስረኛው አልፎ አስተዳደሩም ጆሮ ስለደረሰና ከክለቦቹ ስሞች ጋር የተሰጠው ልጣፍ ስላስፈራራው የወህኒ ቤቱ አስተዳዳር ስድስቱንም ክለቦች የቀየ ስማቸውን እንዲቀይሩ አዘዘ። በአስተዳደሩም መመሪያ መሰረት፣ 1) ተግባረእድ ይባል የነበረው ጥቁር አባይ፣ 2) አንድነት ይባል የነበረው ንብ፣ 3) ነፃነት ይባል የነበረው ኒያላ፣ 4) ወዛደር ይባል የነበረው ጉሬዛ፣ 5) ተራማጅ ይባል የነበረው አውራሪስና 6) ነፀብራቅ ይባል የነበረው ዋልያ መባልን መረጡ። ነገር ግን ስም ቢቀይሩም የነበረው ትንቅንቅ ሊቆም አልቻለም። ደግነቱ የከርቸሌ የስፖርት ንትርክ ከጉንጭ ማልፋት አይዘልም ነበር።

ከርቸሌ በተለያዩ የእግር ኳስ ቡድኖች ውስጥ ሲጫወቱ የነበሩት ተጫዋቾች ከተፈቱ በኋላ ከፍተኛ የአገራችን ክለቦች ውስጥ ገብተው ተጫውተዋል። ለብሔራዊ ቡድንም ብዙዎች ተመርጠዋል። ሌሎች ደግሞ እዚያው እያሉ እስር እያደከማቸው ሲመጣ ጨዋታ ለማቆም ተገደዋል። ከርቸሌ ከነበሩት ወጣት የእግር ኳስ ተጫዋቾች መካከል ምንም እንኳን በበሽታና በባህሪው ደካማነት ከተፈታ በኋላ ሊገፋበት ባይችልም ሐቫና በሚል የቅፅል ስም ይጠራ የነበረው አለሙ ታዋቂ ተጫዋች ነበር። ይህ ልጅ ከእድሜው ወጣትነት ሌላ ተክለ ሰውነቱ፣ የኳስ አመታቱ፣ ቴስታውና ግብ የማግባት ችሎታው በጣም የሚደነቅ ነበር። ይህን ኳስ ተጫዋች እንኳን እስረኛው ከውጪ የሚመጡ የክለብ ተጫዋቾችም ሳይቀሩ ያደንቁት ነበር። አለሙ ኩባ ለትምህርት ከተላኩት ታዳጊ ወጣት ተማሪዎች መካከል በስነሥርአት ጉድለት አገራቸው እንዲመለሱ ከተደረጉትና ከርቸሌ ከታሰሩት አንዱ ነበር።

ከእግር ኳስ ጨዋታ ሌላ የሙዚቃና የቪዲዮ ትርኢቶችም ብዙ ተመልካች ይስባሉ። አገር ያፈራቸውን የዘመኑን ሙዚቀኞች ከርቸሌ እየጠሩ በሚያቀርቧቸው ጣዕመ ዜማዎች መደሰት ተለምዶ ነበር። አንዳንድ ጊዜም እንደነ ውብየሻው አይነት የማዕከላዊ እዝ ዘፋኞች ሲመጡ እስረኛውን በገዛ ገንዘቡ በአብዮታዊ ዘፈናቸው ሙልጭ አድርገው ሰድበውት ይሄዳሉ። አንዳንዶች መስደባቸው ቢቆረቁራቸውም ሌሎች ደግ አደረገች ባዮች ደጋፊ አድማጮችም ነበሯት። የሙዚቃ ነገር ከተነሳ ከረቸሌም የእስረኞች የሙዚቃ

ባንድ አቋቁሞ ነበር። አፈሩን ገለባ ያድርግላቸውና አሁን በሕይወት የሌሉት በዚያን ጊዜ ባእስር ላይ የነበሩት ታዋቂዎቹ ተዘራ ሃይለሚካኤልና አበበ ተሰማ ከርቸሌ ካደራጇቸው ሙዚቀኞች ጋር አስረኛውን ያዝናኑ ነበር።

የስፖርትም ሆነ የሙዚቃ ዝግጅት ከወንድ እስረኞች በበለጠ ለሴት እስረኞች ከግቢያቸው ለመውጫያ ሰበብ ይጠቅማቸዋል። የሴት እስረኞች በሳምንት አንድ ቀን መጻሕፍት ለማንበብ ከመምጣትና ለትምህርትም ለብቻቸው ከተሰናዳላቸው መማሪያ ክፍል በመገኘት ከመማር በስተቀር ከግቢያቸው መውጣት አይፈቀድላቸውም ነበር። ምናልባት ለህክምና ወይም የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር እስረኞች ከሆኑ ፍርድ ቤት ለመቅረብ በግቢው ሲያልፉ ይታዩ ይሆናል። ስለዚህ የስፖርት፣ የሙዚቃና የቪዲዮ ዝግጅት ባለ ጊዜ ሴቶች ከግቢያቸው ለመውጣትና የሚያውቁትን የአይን ፍቅር (አይኑካ) የወንድ ጓደኛ በአይን ለመቃኘት መልካም አጋጣሚ ነበር። ከግቢያቸው በሰልፍ ሆነው ወጥተው ከወንዶች ፊንጠር ብለው ተቀምጠው ማየትና መዝናናት የሚችሉት በእንዲህ ያለ ዝግጅት ጊዜ ነበር። ወንድም ቢሆን አይኑካውን ለማሽኮርመም ሴቶች የሚያልፉበትንና የሚቀመጡበትን አመቺ ቦታ ይዞ ይጠባበቃል። እንግዲህ የአይኑካዎች በአይን መጋረፍም እንዲሁ መዝናኛ ክፍል ነበር።

6. የእስረኞች የጤና ችግር በከርቸሌ

ከጤና ጋር በተያያዘ አስረኛው ትልቅ ችግር ነበረበት። የእስረኛው መብዛት፣ በጣም ተፋፍጎና ተጨናንቆ በንጽሕና ጉድለት እንዲኖር ስላደረገው ለተለያዩ የጤና ችግሮች አጋልጦታል። በመሰረቱ አንድ እስረኛ ሲታመም በቤቱ የጤና ኮሚቴ አማካኝነት ተመዝግቦ ክሊኒክ እንዲሄድ ይደረጋል። ክሊኒክም እንደደረሰ በጤና መኮንን ከተመረመረ በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ የመድኃኒትና ሌሎች እርዳታዎች ይደረግለታል። በሽታው ከባድ ከሆነና የቀርብ ክትትልና እርዳታ የሚጠይቅ ከሆነ ለዚህ በተዘጋጁ ጥቂት አልጋዎች ባሉበት ክፍል ተኝቶ ህክምና ይሰጠዋል። ከውጪ የሚመጣውን የጤና መኮንን ከእስረኛው መካከል የተመረጡ የህክምና ባለሙያዎች ያግዙታል።

የክሊኒኩን ጽዳት ለመቆጣጠር፣ መርፌ ለመውጋት፣ በክሊኒኩ የሚገኙትን መድኃኒቶች ለመጠበቅና የተኙ በሽተኞችን ሁኔታ ለመከታተል ከእስረኞች የተመረጡ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የህክምና ባለሙያዎች ያገለግላሉ። ሐኪም የሆኑ እስረኞች የምርመራውንና የህክምናውን ሥራ ከጤና መኮንኑ ጋር በመረዳዳት ይሰራሉ። እነኝህን መሰል ባለሙያዎች በእስረኛው መካከል መገኘት የግቢውን የጤና ችግሮች በማቃለል በኩል ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ለምሳሌ በ1971 እና 1972 ዓ.ም. ዶ/ር መኮንን እና ዶ/ር ይገረሙ ለግቢው ያደረጉትን ውለታ እስረኞች የነበሩ ምን ጊዜም አይረሱትም።

የከርቸሌ የጤና ችግሮች ከአስተዳደሩ አሰራርና ከእስረኛውም ስነምግባር ጋር የተሳሰሩ ነበሩ። በወህኒ ቤቱ አስተዳደር ደንብ መሰረት በከርቸሌ የእስረኞች ክሊኒክ እርዳታ መዳን የማይችል በሽተኛ ወደውጪ ሐኪም ቤት መላክ ነበረበት። ይህ ሊፈቀድ የሚችለው የከርቸሌ የጤና መኮንን ውጪ ወጥቶ መታከም አለበት ብሎ ሲያረጋግጥ ብቻ ነበር። የበሽተኛው ብዛትና የችግሩ ስፋት አንድ በሽተኛ እንኳን ውጪ ሊላክ ይቅርና በጤና ኮሚቴ ተመዝግቦ ጤና መኮንን ዘንድ ለመቅረብ ተራ መጠበቅ ነበረበት። ከ7000 በላይ

እስረኞች የሚስተናገዱት በአንድ ክሊንክ ከመሆኑም ሌላ የግቢው የጤናም ሆነ የእስረኛው ባህርይ ችግሮቹን ውስብስብ አድርገውት ነበር።

አንዳንድ ግለሰቦች የታመሙ በመምሰል ከከርቸሌ ወደ ውጪ ለመውጣት ክሊኒኩን ይጠቀሙበታል። በዚህ የተነሳ ክሊኒኩ ሁልጊዜ ስለሚጨናነቅ የጤና መኮንኑ፣ በተለይም አጋዥ የእስረኛ ሐኪሞች ከሌለው፣ የሥራ ጫና ይበዛበታል። እውነተኛ በሽተኛውን ከአስመሳዩ ለመለየት ራሱን የቻለ ችግር ያጋጥማል። ሌላም ሐሜት ነበር። አንዳንድ እስረኞች በገንዘብም በአማላጅም የወህኒ ቤቱን አስተዳደርና የጤና መኮንኑን የሙጥኝ ይላሉ ይባል ነበር። የውጪው ሕይወት የሚናፍቃቸው እስረኞች በህክምና ሰበብ ለመውጣት የማያደርጉት ጥረት አልነበረም። አስተዳደሩንም ሆነ ጤና መኮንኑን ደልለው እንደሚወጡም ይጠረጠራል። ገንዘብና ባለሥልጣን ዘመድ ላላቸው እስረኞች እስር ቤቱና የውጪው ዓለም ብዙም አይራራቁም። በጊዜው የእነሱን መውጣት ማንም ባይቃወምም በነሱ ምክንያት እውነተኛ ችግር ያለባቸው እስረኞች እርዳታ እንዳያገኙ እንቅፋት ስለሚሆኑ አሰራሩ የሚደገፍ አልነበርም።

በህክምና ምክንያት አንድ ጊዜ ውጪ ከወጡ በኋላ የተላኩበትን ሆስፒታል ሐኪሞች ግራ በማጋባትና ችግር በመፍጠር ተደጋጋሚ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው የሚጎተጉቱም አልጠፉም። በፖሊስ ጥበቃም ሲወጡ በገንዘብ በመደለል ፖሊሱ እንዲለቃቸው የሚያደርጉ፣ የግል ሥራቸውን የሚሰሩና የሚዝናኑም ሞልተው ነበር። የወህኒ ቤቱ አስተዳደር አሰራርም ሌላው የችግር ምንጭ ነበር። ለምሳሌ ለህክምና የተላከ በሽተኛ ሌላ ቀጠሮ ተሰጥቶት ሲመለስ በተባለው ቀንም ላይላክ ይችላል። እንግዲህ በአስተዳደሩ ችግር እስረኛው ሲመላለስ መክረሙ ነው። የወህኒ ቤቱ ለፍርድ ቤት ቀጠሮ፣ ለህክምናና ለሌሎች ሥራዎች ወደ ውጪ የሚወጡ እስረኞችን የሚያጅቡ ፖሊሶች እጥረት ካጋጠመው የማይመስለውን ለማጠፍ ይገደዳል። መቸም የፍርድ ቤት ቀጠሮ አይታለፍም። ሌላው ደግሞ የእስረኛ መጥፋት ካጋጠመ የወህኒ ቤቱ አስተዳደር ፍርድ ቤት ከሚቀርቡት እስረኞች በስተቀር ሁሉንም በየቤታቸው ከርችሞ ያውላል። እንግዲህ በዚህ የተነሳ የህክምና ችግር የህክምና ባለሙያውን፣ እስረኛውንና አሳሪዎችን ያቆላለፈ ውስብስብ ችግር ነበር። በዚህ መሰል ምስቅልቅል ጉድለቶች የተነሳ አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልገው በሽተኛ ውጪ ሐኪም ቤት ሳይደርስ ሊሞት ይችላል። በተለይ ውጪ ሐኪም ቤት መተኛት ካለበት የወህኒ ቤቱ አስተዳደር አብሮት የሚቆይ ጠባቂ ፖሊስ ማዘጋጀት ስላለበት ችግሩን ይበልጥ ያከብደዋል። በተለይም በፖለቲካ እስረኞች ላይ ልዩ ጥርጣሬ ስላለና ክትትል ስለሚደረግ ማንኛውም ሆስፒታል ተልኮ መተኛትም አይቻልም። በዚህ መሰሉና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ የእስረኛ ውንና የአስተዳደሩን ግትኝነትም ሆነ መለያየት በመፍራት በከርቸሌ የሚመደቡትን ፖሊሶችም ሆነ አዛዦች በየጊዜው መቀያየርና መገወዝ ያጋጥም ነበር።

የከርቸሌ ዋና ዋናዎቹ የጤና ችግሮች የሚከተሉትን ያካትት ነበር። በልዩ ልዩ መንስኤዎች እስረኞች አልፎ አልፎ የተቅማጥ ችግር ያጋጥማቸዋል። በግቢው አጠራር «ሽርተቴ» የተለመደ ነበር። «ሽርተቴ» ከምግብና ከንጽሕና ጉድለት የተነሳ ይከሰታል። ከገበያ የሚገዛ እንክርዳድ የበዛበት ስንዴ ዳቦ በሚጋገርበት ጊዜ በላተኛውን በመመረዝ ብዙ እስረኞች ለሚያዞር የራስ ህመምና ሌላም በሽታ ተዳርገዋል። ይህንን ችግር ወህኒ ቤቱ

የራሱን ዳቦ ቤት ካቋቋመ በኋላ ጥራት ያለው የዳቦ ዱቄት በመጠቀም ሊገታው ችሏል:: ሌሎች ከንጽሕና ጉድለትና ተፋፍጎ ከመኖር የተነሳ ከአንዱ እስረኛ ወደ ሌላው የሚተላለፉ በሽታዎች እንደ የሳንባ በሽታ፣ የቆዳ በሽታ (ቋቁቻ፣ እከክ)፣ በቅማልና በሌላም የንጽሕና ጉድለቶች የሚተላለፉ በሽታዎች እንደ Relapsing Fever፣ Typhoid Fever፣ ወዘተ. አልፎ አልፎ ያስቸግሩ ነበር:: የተለያዩ ተባዮችን እንደ ቅማል፣ ቁንጫና ትኋን ያሉትን ለማጥፋት በየጊዜው «ማላታዮን» (Malathion) በየቤቱ ቢረጭም ችግሩን ለጊዜው ይቀንሰው እንደሆን እንጅ ሲያጠፋው አይታይም:: በየቤቱ የሚገኙት ወደል አይጦችም ከርቸሌን የአይጥ መራቢያ ማዕከል አስመስሎት ነበር::

ከኮሌራ በሽታ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ማንኛውም ማስጠንቀቂያ የከርቸሌን እስረኛ ያስበረግጋል:: «የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል» እንደሚባለው የኮሌራ በሽታ በሐምሌና ነሐሴ 1977 ዓ.ም. የከርቸሌን እስረኞች ብዙ ተፈታትኗቸዋል:: ይህ በሽታ በጊዜው በምስራቅ አፍሪካና በኢትዮጵያም ጭምር ተስፋፍቶ እንደነበር ይተወሳል:: የኮሌራ በሽታ ከርቸሌ እንደተከሰተ በጤና ጥበቃና በቀይ መስቀል የተደረገው መረባረብ ከፍተኛ ስለነበረ ብዙዎች ቢታመሙም የሞቱት ከ28 የማይበልጡ እስረኞች ነበሩ:: በጊዜው በበሽተኞች መብዛት ምክንያት የህክምና እርዳታ የሚሰጥበት ቦታ ለማድረስ ወሳንሳ ጠፍቶ በብርድ ልብስ ተሸክሞ መውሰድ ግድ ሆኖ ነበር:: የከርቸሌ ትምህርት ቤትም ለበሽተኞች ማቆያና ማገገሚያ ውሎ በር::

የሁኔታው አሳሳቢነት የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩን ዶ/ር ግዛው ፀሐይንና የደርግ አባል የነበረውን የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩን እንዳለ ተሰማን ግቢውን እንዲጎበኙና የእስረኛውን አኗኗር እንዲመለከቱ አስገድዷቸዋል:: እንዳለ ተሰማ የእስረኞቹን መኖሪያ ከውጪ ሲጎበኝ ዶ/ር ግዛው ፀሐይ በየቤቱ እየገባ የእስረኛውን ተፋፍጎ መኖርና አመጋገብ ጭምር ተመልክቷል::

ቀይ መስቀል የህክምና መድኃኒቶችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ቢረዳም ለእስረኛው እንደታሰበው አልደረሰውም:: የኮሌራን በሽታ የመተላለፊያ መንገድ ለመቀነስ ውሃን አፍልቶ መጠጣት እና የአመጋገብን ንጽሕና መቆጣጠር አስፈልጊ ነው:: በሽታው ወደ ውጪ እንዳይዛመት እስረኛው ከውጪው ህብረተሰብ ጋር እንዳይገናኝ ጠያቂም ተከልክሏል:: በአንጻሩ ነሐሴ ሁለት ቀን 1977 ዓ.ም. በተደረገው የጋቢና ዋራንት ጥሪ በማገገም ላይ የነበሩ የኮሌራ በሽተኞች ተጠርተው ተፈተዋል:: (12) በደርግ ዝብርቅርቅ አሰራር ሌላ ቀን አስታውሶ ከከርቸሌ የሚያስወጣን አይገኝም በሚል በሽተኞች ቢሆኑም በዕለቱ ከጓደኞቻቸው ጋር ለመውጣት ተገደዋል::

በጊዜው እንደተወራው ቀይ መስቀል ለእያንዳንዱ እስረኛ የግሉ የምግብ እቃዎች እንዲኖረው በማሰብ ኩባያ፣ ሳህን፣ ማንኪያ፣ ሹካና በተጨማሪም የብርድ ልብስ ቢሰጥም የወህኒ ቤቱ አስተዳደር በተፈቀደው መሰረት ሳያከፋፍል ቀርቷል:: ለጥቂት ታመው ለተኙ በሽተኞችና ለከባድ ፍርድ እስረኞች ከመስጠቱ በስተቀር ሌሎች አልደረሳቸውም ነበር:: ለብዙ ዓመታት በቀጠሮ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በወህኒ ቤቱ ከከባድ ፍርደኞች የበለጠ መቆየታቸውን በማስረዳት የቀይ መስቀል ከሰጠው ብርድ ልብስ ለነሱም እንዲደርሳቸው ቢጠይቁም ሳይሳካላቸው ቀርቷል:: (13)

በእድሜ መግፋትና በጭንቀት የተነሳ የሚያጋጥሙ በሽታዎች እንደ የደም ብዛት፣ የስኳር በሽታ፣ የመንፈስ ጭንቀት፣ የማየት ችግር፣ የሆድ ዕቃ

በሽታ (Gastritis)፣ ወዘተ. ልዩ እንክብካቤና የውጭ ህክምና እርዳታ የሚጠይቁ ያጋጥማሉ:: የአስምና የኩላሊት በሽተኞችም ስቃያቸው የበዛ ነበር:: ለብርድ በሽታ የተጋለጡ እስረኞችም ለስቃይ ተዳርገዋል::

ከእነኝህ ችግሮች ሌላ አንዳንዶች ከርቸሌ ከመምጣታቸው በፊት በደረሰባቸው ድብደባና ስቃይ ካጋጠማቸው የአካልም ሆነ የመንፈስ ጉዳት ከዓመታትም በኋላ ስላልሻሩ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ነበሩ:: መጀመሪያም ህክምና የተነፈጋቸው ስለሆነ ቁስላቸው ለመዳን ብዙ ጊዜ ፈጅቶበታል:: የዚህ የአካል ጉዳት ሰለባ ከነበሩት መካከል የሚከተሉት ለአብነት ያክል የሚታወሱ ሲሆን የግለሰቦችን ማንነት ለመደበቅ ሲባል ስማቸው በአህጽሮት እንጅ ሙሉ በሙሉ አልተጠቀሰም::

ሀ. በጥይት የተመቱ

1. ክ.ከ. በቁጥጥር ስር በሚውልበት ጊዜ ሳንባው ላይ በጥይት ስለተመታና በጊዜው የተሟላ ሕክምና ስለተነፈገው መተንፈስ እየቸገረው ብዙ የተሰቃየ እስረኛ ነበር::

2. ጎ.ወ. በጥይት ተመቶ ከወገቡ በታች ሽባ የሆነ ያለክራንች ድጋፍ መንቀሳቀስ የማይችል እስረኛ ስለነበረ የደረሰበት ስቃይ የሚረሳ አይደለም::

3. ይ.ወ. እግሩን በጥይት ስለተመታ በደንብ መራመድ የሚሳነው ነበር::

4. አንገቱ ላይ በጥይት የተመታና ለስቃይ የተዳረገም ይገኝበታል::

5. ሙ. በቀልቤሳ ነገዎ በቀይ ሽብር ከተመታ በኋላ «ቀይ ሽብር ተፋፍሞበታል» የሚል መፈክር ለመለጠፍ ስላለቀበት ለማምጣት ሲሄድ የተመታው ስላልሞተ በደረቱ እየተንፏቀቀ በአካባቢው የነበሩት የማዘጋጃ ቤት ዘበኞች እንዲያድኑት ይማፀናል:: ቀልቤሳ ነገዎ መፈክሩን ይዞ ሲመጣ ዘበኞች ልጁን አንስጥም ብለው በመከልከል ለፖሊስ አስረክበው ህይወቱ ተርፎ ከርቸሌ ቢላክም ሙሉ በሙሉ እስኪድን ድረስ ተሰቃይቷል:: በዚህ ዓይነት በቀይ ሽብር ሊገድሏቸው ሲሉ ያመለጡም እንደነበሩ ሁኔታው ያስገነዝባል::

6. አ.ገ. በቀይ ሽብር ሊገድሉት ሲሉ ቆስሎ ካመለጠ በኋላ ታስሮ ብዙ ተሰቃይቷል::

7. ን.ሙ. ሲያዝ በቦንብ ፍንጣሪ ደረቱ ላይ የቆሰለና በድብደባም እጁና ከፊል ሰውነቱ የደነዘዘ በመሆኑ እርዳታ የሚያስፈልገው ነበር::

ለ. በድብደባ ብዛት በእግራቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው

1. እግሩ ከጉልበቱ ጀምሮ እስከ ጣቶቹ ድረስ ከአገልግሎት ውጪ የሆነው ሲ.ሲ.፣

2. የእግሩ ግርፋት ቁስል ለብዙ ጊዜ ያልዳነውና በተለይ ሲተኛ ሰዎች ድንገት ሲነኩት ሲሰቃይ የነበረው ተ.በ.፣

3. የእግር ጣቶቹ በድብደባ በከፊል የተቆረጡትና ጫማ ተጫምቶ ለመሄድ የሚቸገረው ታ.ጥ. እና

4. በድብደባ በደረሰባት ስቃይ የተነሳ ለመራመድ የማትችለውና በእንፉቅቅ ስትሄድ የነበረችው ፀ.ታ. የሚታወሱ ናቸው:: በተለይ ይህች ልጅ ከተፈታችም በኋላ ሰቆቃው ለአእምሮ ጭንቀትና ለቋሚ የህሊና ጠባሳ

ስለዳረጋት ለብዙ ጊዜ ሳትስተካከል ህይወቷን ትመራለች። የሷን መሰል ሌሎችም ብዙዎች ይገኛሉ።

ሐ. በእሳት የተቃጠሉ

1. ከአንገቱ በታች ብዙ የሰውነት ክፍሉ በእሳት የተቃጠለው ታ.፣
2. በምርመራ ጊዜ ጡቷ በእሳት የተለበለበው ሮ.ሙ.፣
3. ጋዜጣ በማቀጣጠል ጀርባው በእሳት የተቃጠለው ተ.፣
4. በምርመራ ጊዜ እጅና ብብቱን በእሳት የተቃጠለው ሲ..ደ. እና ሌሎችም

ተመሳሳይ ኢሰብአዊ የሰውነት ቃጠሎ በከፍተኛ 7 እና 14 የተፈጸመባቸው ለብዙ ጊዜ ሳይድኑ ተሰቃይተዋል። እነኝህና ሌሎች የስቃይ ሰለባዎች ሁሉ የሕክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ነበሩ።

መ. ከአንገት በላይ ችግር ያጋጠማቸው

1. በምርመራ ጊዜ ራሱን ስለተመታ እስኪድን ድረስ የተሰቃየውና እንዲያውም አልፎ አልፎ ሲነሳበት ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ ይሰቃይ የነበረው ተ.ታ. እና

2. አንድ ጆሮውን ክፉኛ ስለተመታ ለብዙ ጊዜ እየመገለ ለመዳንና ለመስማት የተሳነው ብ.መ. ለዚህ ምሳሌ ሆነው የሚቀርቡ ናቸው። ከፍ ብሎ በማቃጠል ጉዳት የደረሰባቸው ከተወሰኑ ከፍተኞች የመጡ እንደነበሩ ሁሉ እነኝህም ከአንገት በላይ ችግር ያጋጠማቸው ከከፍተኛ ሁለት የመጡ እስረኞች ነበሩ። ይህም የመርማሪዎቹን ተመሳሳይ የጭካኔ ድርጊት ያመለክታል።

ሠ. ሌሎች ችግሮች ያጋጠሚቸው

1. ሠ. በድብደባ ብዛት የጀርባ አጥንት ችግርና የአንጀት መታጠፍ ያጋጠመው ነበር። ምናልባትም የአንጀት መታጠፉ የአጋጣሚ ሊሆን ይችላል።

2. ግ.ጌ. ሁለት እጁ ተቆላልፎ ለመመገብ ሳይቀር የሚያስቸግረው ነበር።

3. ው.አ. በድብደባ ብዛት ሽባ የሆነችው ትታወሳለች።

4. ፍ. ከምርመራ በኋላ ሲምንቶ ወልል ላይ ስለተጣለ በብርድ ምክንያት ሽባ ሆኖ ለብዙ ጊዜ በክራንች ድጋፍ ሲራመድ የነበረውና ሌሎችም እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባቸው ብዙዎች ነበሩ።

ከከርቸሌ ወጥቶ የተሻለ ህክምና ለማግኘት በተለያዩ ምክንያቶች እድሉ በጣም ጠባብ እንደነበረ ቀደም ብሎ ተገልጿል። በዚህ የተነሳ እነኝህ ከፍተኛ ችግር የነበረባቸው የስቃይ ሰለባዎችም ሆኑ ሌሎች እስረኞች ከጥቂቶች በስተቀር ውጪ ወጥተው ለመታከም አልተቻላቸውም። ችግራቸውም በአጭር ጊዜ ህክምና የማይስተካከልና ሰፋ ያለ መከታተልን የሚጠይቅ በመሆኑ ለውጪ ህክምና የተላኩትም ደርሰው ከመመለስ በስተቀር አስፈላጊ እርዳታ አላገኙም። ከከርቸሌ ውጪ ባሉ ሐኪም ቤቶች ተኝተው የተሻለ እርዳታ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸውም አልነበሩም።

ከእስር ብዛትና ከመንፈስ ጭንቀት የተነሳ አንዳንዶች የአእምሮ መዛባትና ራስን መጣል አጋጥሟቸው ነበር። ይህም የሚበዛው በቆዩ የከባድ ፍርድ እስረኞች ላይ ቢሆንም አንዳንድ አዲስ መጥ የፖለቲካ እስረኞችም ወፈፍ የሚያደርጋቸው ነበሩ። የአእምሮ መዛባት ካጋጠማቸው የፍርድ እስረኞች መካከል «ባልዲ» በሚል የቅጽል ስም መጠሪያ የሚታውቀው አንዱ ሲሆን ይህ ግለሰብ ማንኛውንም የተጣለ ትርፍራፊ ምግብ፣ የሙዝና የብርቱካን ልጣጭ ሳይቀር ከቆሻሻ ውስጥ እያነሳ ይመገባል። ሌላው ደግሞ የሚታወሰው የሁሌ አዳል ነበር። እንደ «ባልዲ» ባይሆንም በየክልሉ እየዞረ ምግብ እንዲሰጡት ይጠይቃል። መንፈሱ የተረጋጋ ስላልነበረ እስኪሰጡት አይጠብቅም። የሁሌ አዳል በጎንደር ክፍለ አገር በጣም የሚፈራ ሽፍታ እንደ ነበረ ይነገርለታል። አካባቢውን የሚያንቀጠቅጥ ሽፍታ ከመሆኑም ሌላ በተደጋጋሚ ተይዞ ስላመለጠ በመጨረሻ ሲያዝ ቁንጃውን መንግሥት ስለቆረጠው እስከ ወዲያኛው አንክሷል። እነኝህን መሰል እስረኞች ከርቸሌ መኖራቸውን እንጂ እስረኛ መሆናቸውን የሚይውቁም አልነበሩም። ነገር ግን ምንም ሰብአዊነት የሌላቸው አሳሪዎች ዝም ብለው ይመለከቷቸው ነበር።

ሌላው ደግሞ ከናዝሬት የተያዘው «ጃዊሳው» በሚል ስም የሚጠራው ጠዋት ከመኝታው ሲነሳ ጀምሮ አንድ ነገር ማነብነብ ከጀመረ ቀኑን ሙሉ እንደ መፈክር ያንኑ ሲደግም የሚውለው ነበር። «ጃዊሳው» በቅርብ ጊዜ ስለታሰረ አእምሮው ሙሉ በሙሉ የተዛባ ባይመስልም ጤናማ አልነበረም። በየቀኑ አዳዲስ መፈክር መሰል ነገር ሲደጋግም ሲውል እስረኛውን ያስቀዋል። ቀኑን ሙሉ ሲለፈልፍ ውሎ ስለሚደክመው ማታ አንድ ነገር ሳይተነፍስ ተኝቶ ያድራል። ሌሎች ደግሞ አንዳንድ የፖለቲካ ችግር የነበረባቸው፣ ጓደኞቻቸውን ያስገደሉ፣ ከፀረ ሕዝቦች ጋር የወገኑ፣ ወንድም እህቶቻቸውን ያስገረፉ፣ ዘመዶቻቸውን ያስገደሉ፣ ወዘተ. ከእስረኛውም ከራሳቸውም ተጣልተው ብቻቸውን የሚያወሩ፣ ከሰው የማይነጋገሩና ያበዱ ነበሩ። ለእነኝህ የአእምሮ መረበሽ ለነበረባቸው እስረኞች መንፈሳቸውን የሚያረጋጋ ከሐኪም የታዘዘላቸውን መድኃኒት በጤና ኮሚቴ አማካኝነት እንዲውጡ ከሚሰጥ በስተቀር ሌላ እርዳታ አይደረግላቸውም ነበር። በሴቶች ክልልም የመንፈስ መረበሽና መረጋጋት የተሳናቸው ሴት እስረኞች ነበሩ።

የግቢው የጤና ችግር የከፋ ቢሆንም አብዛኛው የፖለቲካ እስረኛ ወጣት በመሆኑ በመድኃኒቱም በስፖርቱም ንፅህናውን በመጠበቁም ራሱን በመንከባከብ ሕይወቱን ሲያተርፍ ችሏል። ከርቸሌ በእስር ላይ በህክምና እጦት በበሽታ የሞቱትን በሙሉ እዚህ ላይ ማስታወስ ባይቻልም ከከፍተኛ 15 ታስሮ የመጣው ወጣት ጥበበ ሣህሌና የሱማሌ ኤምባሲ ምግብ ቤት ሠራተኛ የነበረው መሐመድ የሚታወሱ ናቸው። ምናልባትም ጥበበ ሣህሌ የህክምና እርዳታ በጊዜው ሳይደረግለት ስለቀረ በRelapsing Fever በሽታ ተጠቅቶ ሳይሞት አልቀረም። መሐመድ የሱማሌ ዜጋ በመሆኑ ከሱማልኛና ጣሊያንኛ ቋንቋዎች በስተቀር ሌላ የማይናገር ሲሆን ሆዱን ታሞ ሲሰቃይ ችግሩን እንኳን በቅጡ የሚያስረዳለት አልነበረም። በመጨረሻ ከዘገየ በኋላ ውጪ ሐኪም ቤት ቢላክም በዚያው ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል። ብዙዎቻችን ከርቸሌ ከመሰባሰባችን በፊት አንድ የአለማያ ምሩቅ የርሻ ባለሙያ የሆነ የፖለቲካ እስረኛ እንደሞተም ይታወቃል። የደን ልማት ሠራተኛ የነበረው ሐኒባል ሙላቱም በብርድ በሽታ መሞቱ ይታወሳል። በኮሌራ በሽታ ምክንያት የሞቱት ከ28 ያላነሱ ግለሰቦች

ከፍ ብሎ ተጠቅሷል፡፡ እነኝህ ከብዙዎቹ መካከል የሚጠቀሱ በጊዜው የህክምና እርዳታ ተነፍጓቸው ህይወታቸው ያለፈ ግለሰቦች ነበሩ፡፡

ብዙ ህዝብ ተሰብስቦ በአንድ ላይ የሚኖርባቸው አካባቢዎች ለመጥፎም ሆነ ለጥሩ ነገር የተጋለጡ ናቸው፡፡ አንድ የጤና ተውሳክ ካለ አብረው በሚኖሩና በቅርብ በሚገናኙ ሰዎች መካከል በቀላሉ በመረማመድ ይዛመታል፡፡ ችግሩንም ለመቆጣጠር የሚሞከር ከሆነ በቀላሉ ማገድ ይቻላል፡፡ አንድ ላይ ተሰብስበው በሚኖሩ ሰዎችም ላይ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ያመቻል፡፡ ለምሳሌ በ1973 ዓ.ም. አንድ የጤና ባለሙያዎች ቡድን (ቀይ መስቀል?) የእያንዳንዱን የከርቸሌ እስረኛ ፊትና እግሮች በመመርመር ጥናት አካሂዷል፡፡ ይህ ምርመራ የLeprosy/ Leishmaniasis/ Ergotism/ Torture victims? ችግሮች በእስረኞች ላይ መኖርና አለመኖሩን ለማወቅና ለማጣራት (Screening) የተደረገ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይህ ስለ ጥናቱ የተሰጠ ግምት እንጅ እርግጠኛው ምን እንደነበረ የሚያውቀው በጊዜው ጥናቱን ያካሄደው ብቻ ነው፡፡ ለጥናቱ የመጡት ግለሰቦች የእያንዳንዱን እስረኛ ፊትና እግር በመመልከት የሚፈልጉትን መለያ ምልክቶች ለመፈተሽ ችለዋል፡፡ ከጥናትና ምርመር ሥራቸው ውጪ የእስረኛው ሁኔታ ሳይገርማቸው አልቀረም፡፡ በጥናቱ ላይ ከተሳተፉት ሴቶች መካከል አንዳንዶቹ እግራቸው በድብደባ የተጎዳውንና ጣታቸው የተቆረጠውን እስረኞች በመመልከት እንባ አውጥተው ያለቀሱ ነበሩ፡፡

7. የእስረኞች መደጎሚያ ንግድ በከርቸሌ

በከርቸሌ ሲካሄዱ የነበሩት የንግድ እንቅስቃሴዎች በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ እነሱም በእስረኛው፣ በስፖርት ክለቦች፣ በህብረት ሱቁና በወህኒ ቤቱ አስተዳደር የሚካሄዱት ንግዶች ነበሩ፡፡ የእስረኛው ንግድ ሕጋዊ ባይሆንም ጠያቂ የሌለው እስረኛ ራሱን ለመደጎም የገቢ ምንጭ መፍጠር ነበረበት፡፡ በዚህ የተነሳ በግቢው ውስጥ ሻይና ቡና አፍልተው፣ ምግብ አዘጋጅተውና በሶ በጥብጠው የሚሸጡ በርካታ እስረኞች ነበሩ፡፡ የበሶ ብጥብጥ ዙር በጎኔ የሚል ስም ተሰጥቶት ነበር፡፡ በማንኛውም የእስረኞች መኖሪያ ቤት ደጃፍ ሻይና ቡና የማይሸጥበት አልነበረም፡፡ አንዳንዶች በሻይና ቡና ንግድ ሲያተኩሩ ሌሎች ደግሞ በድብቅ ጫትና አረቄ እያስገቡ በመነገድ ይጠቀማሉ፡፡ የጫትና የአረቄ ነጋዴዎች በወህኒ ቤቱ ዙሪያ በየዋርድያው ቆመው ከሚጠብቁት ፖሊሶች ጋር ግኑኝነትና ሽርክና በመፍጠር የሚፈልጉትን በቀላሉ ያስገባሉ፡፡ ይህን መሰል ንግድ የሚያካሂዱት የፖሊሶቹን ጠባይ በሚገባ የሚያውቁ የቆዩ የተፈረደባቸው እስረኞች ወይም ተመላላሾች ነበሩ፡፡ በጣም ዝነኞች ከነበሩት መካከል ሙኒክ በሚባል ስም የሚታወቀው የግቢው ጫትና አረቄ አከፋፋይ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ በየክልሉ የጫት አከፋፋዮች ከመኖራቸው የተነሳ የዛሬው የጫት መርከብ የትኛው ክልል መልሕቅ ጣለ እስከመባልም ይደርስ ነበር፡፡

ሌሎችም በሌላ የንግድ ዘርፍ የሚታወቁ ነበሩ፡፡ አንድ ዓለም በቃኝ የሚኖር የሞት ፍርድ የተፈረደበት እስረኛ ለከርቸሌ ሹራብና ካልሲ መሥሪያ ቱባ ክር ይሸጥ ነበር፡፡ በሥራው ትጋትና በጥሩ ስነ ምግባሩ ሰው በጣም ስለሚወደው የስቅላት ቅጣት በተፈጸመበት ጊዜ ያለአዘነ አልነበረም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የአንዳንድ የወንጀል እስረኞች ድርጊት ሲሰሙት ቢዘገንንም በእስር ላይ እያሉ የሚያሳዩት መልካም ባህርይ እውነት ይህን መሰል ወንጀል

ፈጽመዋል ወይ? ብሎ የሚያስጠረጥር ነበር። አንዳንዶች ወንጀልን ተገደው ወይም ተገፋፍተው እንደሚፈጽሙ ሳያመለክት ይቀራል?

የከርቸሌ እስረኞች በግቢው ውስጥ ከሚያካሂዱት የንግድ ልውውጥ ሌላ ለውጪ ሰዎችም በጥየቃ ጊዜ የሰሯቸውን የተለያዩ ነገሮች ለሽያጭ ያቀርቡ ነበር። ከእነኝህም ለሽያጭ ከሚያቀርቧቸው መካከል መሰበ ወርቅ፣ በሐር ሥራ ያጌጠ እስክሪፕቶ፣ ከክር የተሰሩ ሹራብና ካልሲ ተወዳጅ ነበሩ። ሌሎች እስረኞች ደግሞ እነኝህን መሰል ዕቃዎች ራሳቸው ሰርተው ወይም ገንዘብ ከፍለው አሰርተው ለጠያቂዎቻቸው ስጦታ ይሰጣሉ። በዚህ የተነሳ አንድ አዲስ ነገር ከርቸሌ ሲጀመር ሁሉም እያዘጋጀ ለጠያቂው ስጦታ ያበረክታል። በአንድ ወቅት ቫርኒሽ የተቀቡ የሚያምሩ እንጨት ላይ የተለጠፉ ፖስተሮች የሚዘወተሩ ስጦታዎች ነበሩ። በሐር ሥራ ያጌጡ እስክሪፕቶዎችም ለየት ያሉ መጻፊያዎች ተደርገው የተቆጠሩበት ጊዜ ነበር።

ምንም እንኳን በንግድ መልክ ባይታይም አንዳንድ የሕግ ባለሙያ የሆኑ እስረኞች ፍርድ ቤት የሚቀርቡ እስረኞችን በማማከርና ማመልከቻም በመጻፍ ገንዘብ ያገኙ ነበር። በዚህ መሰል ሥራ ዳጎስ ያለ ገንዘብ የሚከፈላቸው እንደነበሩም ይታወቃል።

ከግል ንግዶችና ስጦታዎች ባሻገር በወህኒ ቤቱ አስተዳደር የተፈቀደ የእግር ኳስ ክለቦች የራሳቸው ሻይ ቤቶች ነበሯቸው። ምግብም ሳይቀር የሚያዘጋጁ ነበሩ። የክለብ ሻይ ቤቶች በጆንያና በ«ቺፕ ውድ» አምረው የተሰሩ፣ በተለያዩ ቀለሞች ያሸበረቁ፣ ምቹ መቀመጫ ያላቸውና በተለያዩ ሥዕሎች ያጌጡ ነበሩ። በኳስ ለማሸነፍ እንደሚያደርጉት ውድድር በሻይ ቤቶች ውበትም ይወዳደራሉ። እነኝህ ሻይ ቤቶች በጣም ከማማራቸው የተነሳ እስረኛ ውን የውጪውን «ስናክ» ቤቶች ያስታውሱት ነበር። እንዲያውም እስረኞች በነዚህ ሻይ ቤቶች ሲዝናኑ ውለው ወደ ማደሪያቸው ሲመለሱ ምነው ማደሪያችንም እንደ መዋያችን ባማረልን በማለት ይቆጫሉ።

ህብረት ሱቁ ሕጋዊ የእስረኞች ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች የመገበያ ቦታ ነበር። እንደ ማንኛውም በደርግ ዘመን እንደሚገኙ የህብረት ሱቆች የተለያዩ ዕቃዎች ከመንግሥት የጅምላ ማከፋፈያ ተገዝተው ስለሚመጡ ዋጋቸው እርካሽ ነበሩ። እስረኞች የሚያስፈልጋቸውን የጽሕፈት መሣሪያ፣ ለጽዳት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ አነስተኛ ፎጣና አንሶላዎች፣ ለስላሳ መጠጦች፣ የሸላ ወተት፣ ወዘተ. ይገዛሉ። የሸላ ወተተ በጣም ተፈላጊ ስለነበረ ጠዋት ቀድሞ የተሰለፈ ብቻ ነበር ማግኘት የሚችለው። የግቢው ነጋዴዎችም ሆኑ የክለብ ሻይ ቤቶች የሚፈልጉትን ሻይ ቅጠል፣ ቡና፣ ስኳር፣ ወዘተ. የሚገዙት ከዚሁ የህብረት ሱቅ ነበር። አንዳንድ ዕቃ በውጪ እጥረት ካለ ለቤተ ዘመድም ከዚሁ ሱቅ እየገዙ መስጠት ተለምዷል። እስረኛው ከህብረት ሱቁ ገቢ ለትምህርት ቤት፣ ለመጻሕፍት ቤትና ለሌሎች አግልግሎት ስለሚጠቀምበት እንደራሱ ሱቅ ይመለከተዋል። የመዝናኛ በዓልም ሲደረግ ለስላሳ መጠጦች በብዛት የሚገቡት በህብረት ሱቁ አማካኝነት ነበር።

የወህኒ ቤቱ አስተዳደር ንግድና ልማትም ከእስረኛው ሕይወት ጋር የተያያዘ ነበር። ምንም እንኳን የከርቸሌና የቃሊቲ ወህኒ ቤቶች የራሳቸው አስተዳዳሪዎች ቢኖሯቸውም በሁለቱም ቦታ የነበሩትን እስረኞች በጋራ በመጠቀም ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ያካሂዱ ነበር። ከእነኝህም በእስረኞች ነፃ ጉልበት ከሚካሄዱት የእንጨት ሥራ፣ የዶሮ ርባታ፣ የሰንጋ ማድለብ፣ የጓሮ

አትክልትና የጋራዥ አገልግሎት በሽያጭ ከፍተኛ ገቢ ይገኛል:: በተለይ የከርቸሌ የእንጨት ሥራ በአንድ ወቅት በጥራቱና በዋጋ መንቀሱ የተነሳ ብዙ ፈላጊዎች ይሻሙበት ነበር::

የቃሊቲ ወህኒ ቤት ትልቁ ሥራው በጦር ሜዳ ለሚዋጉት የመንግሥት የደርግ ወታደሮች ስንቅ የሚሆን በሶ በእስረኛው ጉልበት ማዘጋጀት ነበር:: ከእነኚህ ከተጠቀሱት ሥራዎች ሌላ የከርቸሌ ወህኒ ቤት በአንድ ወቅት ትልቅ የዳቦ መጋገሪያ አቋቋሞ እስረኛውን የተሻለ ዳቦ ይመግብና ለአካባቢውም ለሽያጭ ያቀርብ ነበር:: በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የዳቦ እጥረት በነበረበት ወቅት ይህ የዳቦ መጋገሪያ ትልቅ ጥቅም አበርክቷል:: የዳቦ መጋገሪያው የተቋቋመው ከእስረኞች በተዋቀረ የልማት ኮሚቴ የቀረበ ጥናት መሰረት ነበር:: ኮሚቴው ሊቋቋም የቻለው የአዲስ አበባ ወህኒ ቤት አዛዥ የነበረው ኮለኔል ተሾመ ወልደየስ የግቢውን እስረኛ ሰብስቦ አንዳንድ ጠቃሚ ልማቶችን ለማካሄድ የወህኒ ቤቱን አስተዳደር ለማማከር የሚችሉ ሥራ ወዳድ ግለሰቦች ከየቤቱ ተመርጠው እንዲላኩ በጠየቀው መሰረት ነበር::

በዚህ ጥያቄ መሰረት ከየቤቱ በተመረጡ አባላት አማካኝነት በበቀለ ገለታ፣ ታደሰ ይበርታና ፀጋዬ ተክሉ የሚመራ ጠንካራ የልማት ኮሚቴ ሊቋቋም ቻለ:: የዚህ ኮሚቴ የልማት እንቅስቃሴና የነደፋቸው የፕሮጀክት አይነቶች በየጊዜው ቢገለጽም የወህኒ ቤቱ አስተዳደር በሥራ ላይ ሊያውል የቻለው ከላይ የተጠቀሰውን የዳቦ መጋገሪያ ብቻ ነበር:: በዚህ መልክ የተሰራው የዳቦ ቤት ለእስረኛውም ጥራት ያለው ዳቦ ለመጋገርና ለሽያጭም ለማቅረብ በቃ:: የወህኒ ቤቶች አስተዳደር በከርቸሌ የእስረኞች ጉልበት በመጠቀም የሚያካሂደው ሌላ ዘመናዊ ዳቦ ቤት በሚል መጠሪያ የሚታወቅ የዳቦ መጋገሪያ በአዲስ አበባ ከተማ ህንጻ ኮሌጅ ፊት ለፊት ነበረው::

8. በአበባ ያሸበረቀው የከርቸሌ የግድያ ቦታ

ከርቸሌ ሰው የሚረሸንበት የግድያ ልዩ ቦታ ነበረው:: ይህ የግድያ ቦታ ግቢው ውስጥ የእግር ኳስ ሜዳው አጠገብ ሲሆን ግድያውን ለማካሄድ እንዲያመች አንድ ቤት መሰል ግንብ ነበረው:: እዚህ ቦታ ላይ 59 የኃይለሥላሴ ባለሥልጣኖችና ሌሎች በ1967 ዓ.ም. ተገድለው በቡልዶዘር በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ በጅምላ ተቀብረዋል:: የደርግ የጅምላ ግድያም የተጀመረው በእነሱው ነበር:: በተጨማሪ አንዳንድ በተናጠል ወህኒ ቤት የተገደሉ ግለሰቦች የሚቀበሩት በዚሁ ቦታ እንደነበረ ይነገራል::

በዚህ የግድያና የቀብር ቦታ ጥሩምባ ቅርፅ ያለው ትላልቅ ነጭ አበባ ያለው ተክል በቅሎበት ይታይ ነበር:: ይህ የአበባ ስፍራ ዘወትር እንክብካቤ የሚደረግለት ይመስል ሁልጊዜ ያጌጠ ነበር::

የከርቸሌን እስረኞች ለማዝናናት ከውጭ የእግር ኳስ ተጨዋቾችና ሙዚቀኞች ሲመጡ እንኳን ደህና መጣችሁ በሚል አቀፍ አበባ ስጦታ የሚበረከትላቸው ከዚሁ ስፍራ አበባ በመሸምጠጥና በመቅጠፍ ነበር:: ይህ ድርጊት ለብዙዎቻችን ህይወት «በፓራዶክስ» የተሞላ መሆኑን የሚያመለክት ነበር:: ከእስር ቤት ውጭ ባልው ህይወት የቀብር ቦታ ይከበራል፣ በቀብር ጊዜም ሆነ ለጉብኝት ሲኬድ ወዳጅ ዘመድ አበባ ያስቀምጣል:: ከርቸሌ ግን ሰዎች ተገድለው በተቀበሩበት ቦታ ያደገውን አበባ እየተቀጠፈ ለእንግዶች ይበረከት ነበር::

ምዕራፍ ስድስት

ጋቢና ዋራንት

1. አንዳንድ የጋቢና ዋራንት ሰለባዎች ሲፈረጁ

በቀይ ሽብር ዘመቻ ደርግና በደርግ ዙሪያ የነበሩት ድርጅቶችና ሌሎች የብሔር ድርጅቶችም ጭምር ተካፍለዋል። በጊዜው ኢሕአፓ፣ ኢዴሀና ጀበሐ እንደ አብይ ጠላት ስለሚቆጠሩ የደርግ ወዳጆች መፈክር «ኢሕአፓ፣ ኢዴሀና ጀበሐን እናወድማለን» የሚል ነበር። ሽብሩም በመጀመሪያ ደረጃ በእነኝህ ላይ ያነጣጠረ ቢመስልም ዋና ሰለባ የሆነው ኢሕአፓ ነበር። የቀይ ሽብር ሲጀመር ኢሕአፓን ያልገደል የማርያም ጠላት የተባለ ይመስል ሁሉም ተረባርበውበታል። የዚህ የቀይ ሽብር ዘመቻ የመግቢያ ታሪክ ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።

ኢሕአፓን በማዳከም ረገድ የራሱ መከፋፈልና አንጃ መፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከአንጃ መሪዎች መካከል ጌታቸው ማሩ በዘመዶቹ አማካኝነት ከደርግ ጋር ቀጥታ ግኑኝነት እንደነበረው ይጠረጠራል። ብርሃነ መስቀል ረዳ ደግሞ በፊት በነበረው ታዋቂነት ስለሚመካ ከኢሕአፓ ተገንጥሎ የራሱን የትጥቅ ትግል ቢጀምር ሁሉም ግልብጥ ብሎ የሚከተለው መስሎት ነበር። እንደ አሁን አቋሙ ሳይሆን ብርሃነ መስቀል ረዳ ከተማሪነቱ ጀምሮ በነበረው የፖለቲካ ንቃት የለውጥ ፈላጊ ተማሪዎችን ትግል በመምራትና አቅጣጫ በማስያዝ፣ ኢሕአፓንም በመመስረት በኩል ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ሁለቱ የኢሕአፓ አመራር አባላት የጀመሩት የእርማት ንቅናቄ፣ በነሱ አባባል መሰረት፣ ተቀባይነት ባያገኝም ድርጅቱን በመከፋፈል፣ በማዳከምና ለደርግም አጋልጦ በመስጠት በኩል የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል።

ምንም እንኳን ከነብርሃነ መስቀል ረዳ ተከታዮች መካከል አንዳንዶቹ በራሳቸው ለመቆም ቢፈልጉም አብዛኞቹ የአንጃው ደቀ መዝሙሮች ለደርግ አድረው በአንዳንድ ከፍተኛና በደርግ ጽ/ቤትም ጭምር ካድሬዎች፣ መርማሪዎችና ገራፊዎች በመሆን በሚያውቋቸው የዱሮ ጓደኞቻቸው ላይ ትልቅ በደል አድርሰዋል። የአንጃ አባላት የኢሕአፓ መዋቅሮች በደርግ እንዲፈራርሱ በማድረግ፣ ለደርግ እየጠቀሙ በማስያዝ፣ የኢሕአፓ አባላትን ያለፍላጎታቸው በማታለል ብርሃነ መስቀል ረዳ በመርሐቤቴ በመሰረተው የትጥቅ ትግል እንዲቀላቀሉ በማድረግ፣ ኢሕአፓ ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ሚስጥራዊ ቤቶች ለደርግ በመጠቆም፣ የድርጅቱን ገንዘብ፣ መሣሪያና ንብረት በመዝረፍ ከባድ ጉዳት አድርሰዋል። (1) የአንጃው መሰሪ ድርጊት ዝቅ ብሎ በዝርዝር ቀርቧል።

የኢሕአፓን ያክል ባይጎዱም በቀይ ሽብር ጊዜ የሌሎች ድርጅቶች ደጋፊዎችና አንዳንድ ግለሰቦችም የሽብሩ ሰለባ ሆነዋል። እየቆየ ሲሄድም አንዳንድ የቀይ ሽብር አራማጆች የነበሩትም ከግድያው አላመለጡም። «አብዮት ልጇን ትበላለች» እንዳሉ ራሳቸውም የሳት እራት ሆነዋል። በኢማሌድህ ስር የነበሩት ወዳጅ ድርጅቶች ርስ በርሳቸው ሽኩቻ፣ መሳሳብ፣ መጠላለፍ፣ አንዱ አንዱን ጥሎ ሥልጣን ለመያዝ መሽረብ፣ አንዱ የድርጅቱን አባላት ለማስፋት ምልመላ ማካሄድና ሌላም ውጥንቅጡ የወጣ ውድድር ነበራቸው።

እንደ ዋና ጠላት የሚፈርጁትን ኢሕአፓን በቀይ ሽብር ካዳከሙ በኋላ በመካከላቸው የነበረው ቅራኔ ይፋ ወጣ። አንዳንድ የኢሕአፓ አመራሮች በቀይ ሽብር ከረገፉና አባላቱም በስር ከተሸማቀቁ በኋላ መኢሶን በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ሌላ የሚወዳደረው ሊኖር እንደማይችል ገመተ። በዚህ የታላቅነት ስነልቦና የተነሳ ሚያዝያ 23 ቀን 1969 ዓ.ም. በተደረገው የላብአደሮች ቀን ሰልፍ ላይ ገኖ ለመታየት «መኢሶን ፓርቲያችን ነው» እና «መኢሶን አስታጥቆናል» የሚሉ መፈክሮችን ይዞ በመውጣቱ ከደርግና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተቃቃረ። የመኢሶን አመራር በነበረው በወርቁ ፈረደ አገላለጽ «አበጠ»፣ ከእንግዲህ አኔ ነኝ፣ ከእኔም ወዲያ ላሳር አለ።(2) ትንሽ በደርግ ወታደራዊ ኃይል ላይ ስጋት ቢኖረውም የሱማሌን ወረራ በአሸናፊነት ይወጣል ብሎ አልጠበቀም። ደርግ በጦርነቱ በአሸናፊነት ቢወጣም እንኳን መኢሶን የዚህ ተባባሪ በመሆን ደርግን የበለጠ ማጠናከር አልፈለገም። ስለዚህ መኢሶን የትግል ስልት በመቀየር ስልታዊ ማፈግፈግ በማድረግ ራሴን ለማዳንና ለመደበቅ መረጥኩ ቢልም(3) ደርግን የከዳው ከደርግ ጋር የፈጠረው ህብረት ከዚህ በኋላ የማያስፈልግ መሆኑን በመተማመን የራሱን የተጠናከረ ትግል ለማካሄድና ሥልጣን ለመያዝ ነበር። በተለይም የመኢሶን አመራሮች ባስታጠቋቸው የአብዮት ጥበቃዎችና ሚሊሻዎች፣ በቢሮክራሲውና በሕዝቡ መካከል በነበራቸው ድጋፍ ተማምነው ነበር።

በዚህ የተነሳ መኢሶን የተለያዩ አባላቱን በሚስጥር በመቀስቀስ በአገሪቱ ያሉት አባላቱ እንዲሰወሩ አንዳንዶቹም በያሉበት የትጥቅ ትግል እንዲያካሂዱ ወሰነ።(4) ከዚህ ውሳኔ በኋላ አብዛኛው የአመራርና ሌሎች አባላቱ በየአቅጣጫው ለመጥፋት ሙከራ ሲያደርጉ ተያዙ፣ አንዳንዶቹም ተከበው ተገደሉ። (5) ከተያዙት የመኢሶን አመራሮች መካከል ታዋቂው ኃይሌ ፊዳ የመኢሶን ዕጣ ፋንታ ተመሳሳይ ስህተት ከሰሩት ከግሪክ፣ ሱዳንና ኢንዶኔዢያ ኮምኒስቶች ጋር ለማነፃፀር ሞክሯል። በሱ ግምት የመኢሶን ሁኔታ ከእነዚህ ፓርቲዎች የሚለየው እነሱ በፋሽስታዊ ጁንታዎች እጅ ሲወድቁ መኢሶን ግን በማርክሲዝም ሌኒንዝም በሚያምን መንግሥት እጅ በመውደቁ የተሻለ ዕድል እንደሚገጥመው ተማምኖ ነበር።(6) ነገር ግን እሱ እንደተመኘው ሳይሆን ደርግ ከእንዶኔዢያው ሱሐርቶ፣ ከግሪክ ኮለኔሎችና ከሱዳኑ ኑሜሪ የሚብስ ፋሽስታዊ ጁንታ እንጅ የማይተናነስ መሆኑን በድርጊት አስመስክሯል። የኢትዮጵያ ጎረቤት አገር የሆነችው ሱዳን በ1960ዎቹ በተለያየ ጊዜ የመንግሥት ግልበጣ ኩደታ ተካሂዶባታል። ኑሜሪ በኩደታ ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ በፊት ይደግፉት በነበሩት የኮምኒስት ፓርቲ አመራር አባላት አንድ ኮለኔልና አንድ ሻለቃ አራሱ በኩደታ ይገለበጣል። እነኝህ ኮምኒስት መኮንኖች በጊዜው የሕዝብ ድግፍ ቢያገኙም በአጭር ጊዜ በግብፅ ወታደራዊ ድጋፍ ተወግደው ኑሜሪ ሥልጣን ላይ ይመለሳል። በመንበረ ሥልጣኑም ላይ ሲመለስ በሱዳን ባልተለመደ መልኩ በኮምኒስቶቻ ላይ የግድያና የማግለል እርምጃ ወሰዷል። ሆኖም ኑሜሪ የወሰደው እርምጃ መንግሥቱ ኃይለማርያም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ካደረሰው ጭፍጨፋ ጋር የሚወዳደር አልነበረም። መንግሥቱ ኃይለማርያም ገዳይ ብቻ ሳይሆን ጨፍጫፊና አራጅ ነበር።

መኢሶን በሲዳሞ፣ በወለጋና በኤሉባቦር ለመሸሸግና ምናልባትም የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ያሰበው ከሸፈ። የሲዳሞ አካባቢ ተወላጅ የነበሩት አ'ነ አበራ የማነአብና አሸቱ አራርሶ (በሱማሌ ዕርዳታ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ሞክሮ የተሰዋ) ከነሱም ጋር የኮበለሉት እንዳርጋቸው አሰግድ፣ ወዘተ

ሲያመልጥ የግምቢ ተወላጅ የነበረውና በወለጋ በአገሩ ላይ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ኃላፊ የነበረው ኃይሉ ገርባባ ለመሸሽግና ለማምለጥ ያደረገው ሙከራ ከሽፎ በሕዝብ ተከቦ ተያዘ። በኤሉባቦርም የአካባቢው ተወላጅ የሆነው የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊና የመኢሶን አመራር አባል የነበረው ዶ/ር ከድር መሐመድ የደርግ ሰለባ ሆነ። ምናልባትም የመኢሶን አመራር ከደርግ ለመሰወር ከመሞከሩ በፊት ለሥራ ጉዳይ አውሮፓ ተልኮ በዚያው ጠፍቶ የቀረው ነገደ ጎበዜ የወሰደው እርምጃ ሳይደነቅ አይቀርም። እንግዲህ መኢሶን በሕዝብ መካከል ገብቶ ለመሥራት ቀርቶ ለመሰወር ሳይችል ቀረ። በከተማም የቀሩት ከደርግ ጋር ለመወገን ያልፈቀዱት አባላቱ እንደ ኢሕአፓ እየተለቀሙ ታሰሩ። የመኢሶን አባላት ለደርግ ድብቅ ባይሆኑም ለአሰራር እንዲያመቸው ኢሕአፓን ለማሳደድ አንጃውን እንደተጠቀመበት ሁሉ የመኢሶንን ውስጥ አዋቂ እነ ዶ/ር አለሙ አበበን ሳይጠቀምባቸው አልቀረም። ለደርግ አሾህን በአሾህ መንቀል በጣም ጠቅሞታል።

መኢሶን በዚህ ጊዜ ከደርግ አጋርነት ቢለይም በአብዮት ስም በአገራችን ለተፈጠሩት ችግሮችና ግድያዎች ተጠያቂ ነው። ምክንያቱም ከደርግ ጋር በነበረበት ጊዜ የደርግን ፖሊሲ ቀያሽና የችግሩም አቀጣጣይ ስለነበረ ከተጠያቂነት አይድንም። የመኢሶን አመራር አባላት ኢሕአፓን ለማጥፋት በተለሙት ተከታታይ የሽብር ዘመቻ የኋላ ኋላ ራሳቸውም ቢጋዩበትም የቀይ ሽብር ጠንሳሽ እንደነበሩ ጥርጥር የለውም። በተደጋጋሚ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሌላ ቦታ እንደተገለጸው የደርግ የሽብር፣ የእስር፣ የግድያና የጦርነት እርምጃዎች ደረጃ በደረጃ እያደጉ መጡ እንጅ በአንድ ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ አልደረሱም። የሕዝብ ተቃውሞ እየጨመረ ሲመጣ ደርግ የሚወስዳቸውም የተለያዩ እርምጃዎችም እየጨመሩ መጡ። እነኝህን የተለያዩ እርምጃዎች በመቀየስ በኩል በደርግ ዙሪያ ከነበሩት ምሁራን መካከል የመኢሶን አባላት እንደ መብዛታቸው ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል። ምንም እንኳን በአፍላ ቀይ ሽብር ጊዜ እነሱም በቆፈሩት ጉድጓድ ቢቀበሩበትም የቀይ ሽብር አመንጪና ጠንሳሽ እንደነበሩ መካድ አይቻልም። ለአንድ ድርጊት ኃላፊነቱን መውሰድ የሚገባቸው ሃሳቡን ያመነጨትና ያስፈፀሙትም ጭምር በጋራ ስለሆነ መኢሶን ከደርግ በማይተናነስ መልኩ በቀይ ሽብር ተጠያቂ ስለመሆኑ የሚከተሉት ተሳትፎዎች ይመሰክራሉ።

1. የመኢሶን አመራሮች በደርግ አባላት እየተጠየቁም ይሁን በራሳቸው አነሳሽነት የሕዝብ ድርጅት እንዲመሰረት፣ በግንባር ጥያቄ ላይ ማን መሳተፍ እንዳለበት፣ ስለ ፖለቲካ ድርጅት አመሰራረት፣ የታጠቀ አብዮት ጥበቃ በየቀበሌው ስለማቋቋም፣ ኢሕአፓን ከህብረተሰቡ መንጥሮ ስለማውጣትና ስለመደምሰስ፣ በኤርትራ ጥያቄ ላይ፣ ወዘተ ደርግን ሲያማክሩና ሲሳተፉ እንደነበረ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የኃይሌ ፊዳ መረጃ ያረጋግጣል።

2. ደርግ ባቋቋመው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት የአንበሳ ድርሻ የነበረው መኢሶን ነው። ይህ በአዲስ አበባ ከተማና በየክፍላተ አገሩ የተዘረጋው የመቀስቀሻ፣ የማደራጃና የተጠረጠሩ ተቃዋሚዎችን የማፈኛ ድርጅት በአብዛኛው የተዋቀረው በመኢሶን አመራር አባላት ነበር።

3. የከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚመራው በመኢሶን አመራር አባል በነበረው በዳንኤል ታደሰ ነበር። የዚህ ሚኒስቴር ሠራተኞች በያሉበት በቀይ ሽብር ኮሚቴነት ተሳትፈዋል፣ አብዛኞቹም በመኢሶን የተመለመሉ ነበሩ። ሌሎች

የመኢሶን የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የላብ አደር መሪዎች፣ የፖለቲካ ት/ቤት ካድሬዎች፣ ተከታዮቻቸውን በመመልመል ተመሳሳይ ድርጊት ፈፅመዋል።
4. አብዮት ጥበቃዎችን ያስታጠቁ የመኢሶን አመራሮች ከበደ መንገሻና አበራ የማነአብ ከሻለቃ ሮንዴሳ ብራቱ ጋር እንደነበሩ በሌላ ቦታ ተጠቅሷል።
5. የቀይ ሽብር አካል በነበረው የቤት ለቤት አሰሳና ግድያ የመኢሶን ከፍተኛም ሆነ ዝቀተኛ ካድሬዎችና አመራር አባላት በሚኖሩበት ቀበሌዎችና ከፍተኞች በአሰሳው ተሳትፈዋል። በአሰሳው ብዙ ሰዎች፣ የኢሕአፓና ሌሎች ድርጅቶች አባላትም ተገድለዋል። አንተስፋዬ ደበሳይ፣ በሪሁን ማርዬና ሌሎች የኢሕአፓ አባላት በዚህ አሰሳ ጊዜ ለሞት የተዳረጉት በመኢሶን ፈታውራሪነት ነበር።
6. የከፍተኛና የቀበሌ ሊቀመናብርትና የአዘአኮ በመሆን በሽብሩ ተሳትፈዋል። የመኢሶን ከፍተኛ አመራሮች ነሐሴ 1969 ዓ.ም. ለመጥፋት ሞክረው ከተያዙ በኋላ ከደርግ ጋር ሲሰሩ የነበሩት አባሎቻቸው በነበራቸው ሥልጣን ላይ ቆይተዋል። በዚህ የተነሳ የቀበሌ ሊቀመንበር፣ የአዘአኮና የቀይ ሽብር አስፈፃሚ በመሆን ተሳትፈዋል። በምዕራፍ አራት እንደተጠቀሰው ደርግ የመኢሶን አባላትን ማግለልና ማሰር የጀመረው ግንቦት 1970 ዓ.ም. አካባቢ ነበር። ምናልባት ደርግ እርምጃ ለመውሰድ ጊዜ ያስፈለገው ከመኢሶን አባላት መካከል የርሱ ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉትን ለመለየት ይሆናል።
7. ቀይ ሽብርን የየአካባቢው የመኢሶን ካድሬዎች ከሌሎች ጋር በመሆን እንደሚያስፈፅሙ ሁሉ የበላዮቻቸውም ከደርግ ጋር መመሪያ ሰጪዎች ነበሩ።
8. የመኢሶን ከፍተኛ አመራሮች ከደርግ ከመለየታቸው በፊት ፀረ አብየተኞችን ማውደምን/ቀይ ሽብርን ማፋፋምን በሚመለከት ያሰሙት ተቃውሞ አልነበረም። በዚህ የተነሳ ከደርግ ጋር ያልወገኑት ተከታዮቻቸው እስኪታሰሩ እስከ 1970 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ የቀይ ሽብር ተዋናይ ነበሩ።

ስለ አንዳንድ በደርግ ዙሪያ ስለነበሩ የፖለቲካ ሰዎች ምን ያክል ኮሎኔል መንግሥቱን እንደሚፈሩና እንደሚሽቆጠቆጡ ሻለቃ ዳዊት በጻፈው መጽሐፍ የሰነዘርው አስተያየት የተጋነነ ቢመስልም አውነትነት አለው። (7) ዶ/ር አለሙ አበበ የመኢሶን አባል የነበረው ጓደኛው ዶ/ር መኮንን ጆቴ በተገደለ ጊዜ ቀብሩ ላይ ከሌሎች የመኢሶን አባላት ጋር ሲያሰማ የነበረው መፈክር ድርጅቱ ደርግን ሲከዳ ከወሰደው አቋም ጋር በጣም ይጋጫል። በዶ/ር መኮንን ጆቴ ግድያ ደርግን በመጠርጠር «ቅጥር ነፍሰ ገዳይ ኢሕአፓ ብቻ ነውን?» የሚል መፈክር ሲያስተጋባ የነበረ ግለሰብ ጓደኞቹ ሲከዱ ከደርግ ጋር ተጣብቆ መቅረቱ ምን ያክል አቋሙ ተለዋዋጭ እንደነበረ ያረጋግጣል።

የመኢሶን ውድቀት በደርግ ዙሪያ ለቀሩት ሌሎች ድርጅቶች ምንም ትምህርት አልሰጠም ነበር። እንዲያውም የሞተውን መኢሶን ተጋግዘው ከቀበሩ በኋላ ሁሉም በየፊናቸው የራሳቸውን የአሸናፊነት መንገድ መትለም ተያያዙት። መኢሶን የሄደበት መንገድ የማያዋጣ መሆኑን ቀድሞ የተገነዘበው የወዝ ሊግ ከውስጥ ሥልጣን በመቆጣጠር የደርግ የፖለቲካ ቡድን በነበረው በሰደድ ላይ ለማየል ማውጠንጠን ጀመረ።

የወዝ ሊግ የደርግ ደጋፊ ከነበሩት ምሁራን መካከል በማቹ በዶ/ር ሰናይ ልኬ የተመሰረተ ሲሆን ነፍጠኞችን (8) ከማሰባሰብ ባሻገር በዛ ያሉ ወታደራዊ መኮንኖች አባላትም ነበሩት። እንዲያውም ከወታደራዊ ክፍል የተመለመሉት አባላቱ በወዝ ድጋፍ ለተመሰረተው ለኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ቡድን ለአብዮታዊ ሰደድም ደጋፊ ነበሩ። (9) የወዝ ሊግ በሌሎች ቡድኖች ላይ እንዲያይል ለማድረግ ወታደራዊ አባላቱና በቀይ ሽብር ጭፍጨፋ

የሚታወቀው የደርግ የምርመራ ክፍል ሹም የነበረው ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ በምርመራ ክፍል ሹምነቱ የተነሳ የቀይ ሽብር ዋና አጋፋሪ በመሆን ብዙዎችን አስጨርሷል። (10) የራሴ የሚላቸውን የሚታዘዙለት የቀይ ሽብር አራማጆችና የግድያ ቡድን (Squad) አዘጋጅቷል። ከየትኛውም «የፀረ አብዮት ድርጅት» ለሱ ታማኝ የሆኑ ግለሰቦች በወዝ አደር ሊግ አባልነት መልምሎ ነበር። ከራሱ ድርጅት ካድሬዎች ሌላ በቀበሌ፣ በከፍተኛ፣ በደርግ ጽ/ቤትና በከርቸሌም ጭምር ከመኢሶን፣ ከኢሕአፓ፣ ከኢሕአፓ አንጃ፣ ወዘተ. ከታሰሩት መካከል የመለመላቸው አዳዲስ አባላት እንደነበሩት ይታወቃል። አብዛኞቹ የቀበሌና የከፍተኛ ሊቀመንበሮችና የቀይ ሽብር አራማጆች የሱው ቀኝ እጆች ነበሩ። በከርቸሌም «ግንቦቴዎች» በመባል የሚታወቁት በ1970 ዓ.ም. የግቢውን እስረኛ ኢሕአፓ የሆናችሁ እራሳችሁን አጋልጡ በሚል ሲያተራምሱ የነበሩት የሱው ሰዎች ነበሩ። በአንዳንድ ከፍተኛና በደርግ ጽ/ቤትም በምርመራ ላይ ተሰማርተው የነበሩት የኢሕአፓ አንጃዎች የሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ጋሻ ጃግሬ ነበሩ። የቀይ ሽብር እርምጃ በየከፍተኛውና በየአካባቢው መወሰኑ ቀርቶ በማዕከላዊነት እንዲሰራ መባሉም ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ በስሩ ካሉት ታማኝ ካድሬዎች ጋር የበለጠ እንዲቀራረብና አድራጊ ፈጣሪ እንዲሆን ረድቶታል።

ነገር ግን ሁሉም ድርጊት ሊዘልቅ አልቻለም። በጊዜው በነበረው መጠላለፍ ደርግ የወዝ ሊግን አካሂድና የሻለቃ ብርሃኑ ከበደን ተንኮል ስለተረዳ የታሰበው ሴራ ሳይሳካ ቀረ። ለሥልጣን ቋምጠው የነበሩት የወዝ አደር ሊግ የአመራር አባላት ኮለኔል ሽታዬ ደስታ፣ ሻለቃ ብርሃኑ ከበደና ሌሎችም በሰርጎ ገብነት፣ የሰደድ ካድሬዎችን በመግደልና ለጠባብ ቡድን ሥልጣን በማድላት ተወንጅለው እርምጃ ተወሰደባቸው። (11)

እዚህ ላይ በጊዜው ስለነበረው ውጥንቅጡ የወጣ ግድያ አንድ ነገር ማስታወስ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን በቀይ ሽብር ጊዜ የነበረው ፍልሚያ በደርግና ራሱን ለመከላከል በተገደደው በኢሕአፓ መካከል ቢሆንም ሌሎች ግርግሩን በእጅ አዙር አልተጠቀሙበትም ማለት አይቻልም።(12) ደርግም ቢሆን ከኢሕአፓ የተሰነዘረ በማስመሰል በራሱ ወገን የቆሙትን የማይፈልጋቸውን ለመግደል ተጠቅሞበታል። ከዚህ ሌላ የወዝ ሊግ አመራር የነበረው ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የኢሕአፓን ግድያ በማስመሰል ግራ ቀኙን ለማፈንና ለፖለቲካ ሥልጣን ደንቃራ ይሆናሉ ብሎ የገመታቸውን ለማጥፋት ተጠቅሞበታል። ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ በቀጥታ በራሱ የሚታዘዙ የድርጅቱ የገዳይ ስኳዶች ከማሰማራት አልፎ የየከፍተኛውን የቀይ ሽብር አራማጆች ተጠቅሞባቸዋል። በዚህ መልክ ብዙዎችን ካስጨረሰ በኋላ ከደርግ አባላት መካከል የጊዜውን የቀይ ሽብር ያለአግባብ ጭፍጨፋ ይቃወም የነበረውን ሻለቃ ደበላ ዲንሳን እንዲገደል ይወስንና ትዕዛዝ ያስተላልፋል። ትዕዛዙ የደረሳቸው በሁኔታው ይደናገጡና ለደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሹክ ይላሉ። .(13) በዚህ የተነሳ እነ ኮለኔል መንግሥቱ ነገሩን ይደርሱበትና ያከሽፉታል።

ከዚያም የሻለቃ ብርሃኑ ከበደን አካሄድ በማጥናት ላይ የነበሩት ነገሩን ለማረጋገጥና ጊዜ ለማግኘት ለምርመራ ሥራ በሚል ሰበብ ወደ ትግራይ ይልኩታል። በሁኔታው ምንም ጥርጣሬ ያልገባው ሻለቃ ብርሃኑ ከበደም እንደለመድው በትግራይ ታስረው የነበሩ የፖለቲካ እስረኞችን በማስገደድ የወዝ ሊግ አባል እንዲሆኑ ቢጠይቃቸው ቀደም ብሎ በሰደድ ስለተመለመሉ የማይሆን መሆኑን ቢያስረዱትም ያለርህራሔ እንዲገደሉ ያደርጋል። ይህን

መሰል ድርጊት መተሐራ ለተመሳሳይ ምርመራ የተላከው ቹፍ ካሣዬ የተባለው ሌላው የወዝ ሊግ አባልም ፈጽሞታል። (14) በዚህ የተነሳ፣ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው፣ የወዝ ሊግ አመራር አባላት በሰድድ በተዘጋጀላቸው ወጥመድ ሊገቡና እርምጃ ሊወሰድባቸው ቻለ።

ከዚህ በኋላ የሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ምልምሎችም ውሃ በላቸው። የቀይ ሽብር አራማጆች የነበሩት በዛ ያሉ የወዝ ሊግ ካድሬዎችና ደጋፊዎች በቁጥጥር ስር ዋሉ። ደርግ በፈቀደው የቀይ ሽብር ዘመቻ በገደሉት የሰዎች ቁጥርም ተጠያቂ ሆኑ። በአንፃሩ የሰድድ አባል የነበሩት የቀበሌና የከፍተኛ ሊቀመናብርትና የቀይ ሽብር አራማጆች እንኳን በቀይ ሽብር ሊጠየቁ ይቅርና ተጨማሪ ግድያ እንዲያካሂዱ የአዲስ አበባ ከፍተኞችን የሚያጠቃልል የተጠናከረ የቀይ ሽብር ኮሚቴ እንዲያቋቁሙ ተፈቀደላቸው። ከደርግ ተዘዋዋሪ መርማሪዎች ጋርም ተቀናጅተው እንዲሰሩ ተወሰነ። ተጠሪነታቸውም ለአዲስ አባባ ከተማ ከንቲባ ለነበረው ለዶ/ር አለሙ አበበ ሆነ። በኢሕአፓና በመኢሶን እንዳጋጠመው ሁሉ የወዝ ሊግን ተንኮልና መዋቅር በማጋለጥ በኩል አንዳንድ አባላቱ ከደርግ ጋር ሳይተባበሩ አልቀረም።

ከዚያም አብዮታዊ ሰደድ የተባለው የደርግ ወታደሮች ቡድን ተጠናክሮ በአሸናፊነት ለመውጣት ችግር አላጋጠመውም። እንዲያውም በየጊዜው ለጠባብ ድርጅታዊ ቡድን ጥቅም የሚደረገውን የሥልጣን እርኩቻ ለማቆም ሁሉንም ያካተተ አንድ ወጥ ድርጅት ለመመስረት ኢማሌድህ ወደ ኢሠፓአኮ በ1972 ዓ.ም. ተሸጋገረ። በሂደትም የደርግ የሠራተኞች ፓርቲ ተመሰረተ። የወዝ ሊግ ከተመታ በኋላ የማሌሬድና የኢጭአት ቡድኖችም እየከሰሙ ሄዱ። ማሌሬድ ከኢሕአፓ አፈንግጠው በወጡ ግለሰቦች የተመሰረተ ድርጅት ስለሆነ ሁልጊዜ የኢሕአፓን አባላትና ደጋፊዎች ለመቀራመት እንዳደባ ነበር።(15) ከዚህ በፊትም እንደለመደው በቀይ ሽብር ዘመንም የእስር ሰለባ የሆኑ ኢሕአፓዎችን በተጽኖ ለመመልመል ቢሞክርም እንደሌሎች እየተነዳ ወደ ክርቸሌ ከመግባት አላመለጠም። በከፍተኛ 12 በማሌሬድ ተመልምለው ወደ አብዮቱ ካምፕ ተመልሰዋል በሚል ከተፈቱ በኋላ በድጋሚ በኢሕአፓነት የታሰሩ ነበሩ። ከደርግ ጋር ከነበሩት የፖለቲካ ቡድኖች መካከል የኢጭአት አባላት ከተለያዩ የጭቁን ብሔረሰቦች የተወጣጡ ነበሩ። በደርግ ባለሥልጣኖች በጠባብነት ስለተፈረጁ እነሱም ከመበታተን አላመለጡም። ከእነኝህ መካከል የኦሮሞ ተወላጅ የነበሩት አነግን ሲደባለቁ፣ የደቡብ ተወላጆች የሆኑት አንዳንዶቹ ሲታሰሩ አንዳንዶቹ ኢሠፓን ተቀላቀሉ። አነግን ከተቀላቀሉት መካከል ብዙዎቹ ውሎ አድሮ የእስር ሰለባ መሆናቸው አልቀረም። በርከት ያሉ የመኢሶን አባል የነበሩ የኦሮሞ ብሔርተኞችም አነግን ተጠግተዋል።

2. የኢሕአፓ ክፍልፋይ አንጃ ድርጊት

የኢሕአፓ አንጃ በ1969 ዓ.ም. እንደተፈጠረ ቀደም ብሎ ያልተስማማባቸውን በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱትን ልዩነቶች በድብቅ ለማስፈፀም የራሱን እርምጃ መውሰድ ጀመረ። እነኝህም በዋናኛነት ከደርግ ጋር ተባብሮ መሥራት፣ የከተማውን የኢሕአፓ የመከላከል የትጥቅ ትግል ማኮላሸትና የራሱን የገጠር የትጥቅ ትግል ማካሄድ ሲሆኑ በውስጠ ታዋቂ የኢሕአፓን መዋቅር ማዳከምና አብዛኛውን የኢሕአፓ አባላት የራሱ ደጋፊ

ማድረግ ይገኙበት ነበር:: እነኝህን ድርጊቶች ለማስፈፀም በከተማ ጌታቸው ማሩና ጓደኞቹ በገጠር ደግሞ ብርሃነ መስቀል ረዳና አባሪዎቹ ተንቀሳቅሰዋል::

በአንጃ የተነሳ በኢሕአፓ ድርጅት ውስጥ ከአመራሩ ጀምሮ የተፈጠረው ስንጥቅ ነፋስ አስገብቷል:: «በሬ ከአራጁ ጋር ይውላል» እንደሚባለው ደርግ ኢሕአፓን ለጭዳ ሲያስብ የድርጅቱን አሰራርና መዋቅር የሚያውቁ የቅርብ ጠቋሚና ተባባሪ ይዞ የተነሳው አንጃውን ነበር:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በ1970 ዓ.ም. የኢሕአፓ አስረኞች የገዛ ጓደኞቻቸው በነበሩት አንጃዎች ሲዋከቡ ያሉትን አገርኛ አባባል እዚህ ላይ ማስታወስ ይገባል::

«አርሜ ኮትኩቼ ያሳደኩት ቀጋ፣
እኔን ሲዘነጥል እሾሁን ዘረጋ::»

ኢሕአፓ የአንጃውን መሰሪ አካሂድ ከተረዳ በኋላ አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ ተገደደ:: ከአንጃው ጋር የገጠመው ግብግብ ከደርግ ጋር እንደሚያካሂደው ፍልሚያ ራሱን ለመከላከል ነበር:: ሆኖም አንጃው ከደርግ ጋር በህብረት የሚያካሂደውን እንቅስቃሴ ለመግታት አልቻለም:: ኢሕአፓ የአንጃውን መሰሪ አካሂድ፤ የተገነዘበው ዘግይቶ ስለነበረ በመዋቅሩና በአባላቱ ላይ ደርግና አንጃው የሚያደርሱትን ጉዳት በቀላሉ ለመጠገን አልቻለም:: ሆኖም በወሰደው እርምጃ በከተሞች አካባቢ የነበሩትን አንጃዎች በከፊል መቆጣጠር ቢችልም ብርሃነ መስቀል ረዳ አምልጦ መርሐቤቴ ኢሕአፓ ለትጥቅ ትግል ያዘጋጀውን ቦታ ቀምቶ የራሱን የትጥቅ ትግል ለመጀመር ቻለ::

ብርሃነመስቀል ረዳ ይህንን ማድረግ የቻለው በአካባቢው ተወላጆችና የአንጃ አባላት በአነደምሴ ኃይለማርያምና መምህር ትዕዛዙ አማካኝነት ነበር:: አንጃው ለትጥቅ ትግል በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስና መሣሪያ ሲያከማች የነበረው ደብረ ብርሃን በሚገኘው መምህር ትዕዛዙ ቤት ነበር:: ትግልም ሲጀምሩ የጦር መሣሪያ፣ መድሐኒት፣ ገንዘብና የተለያዩ ቁሳቁሶች ከኢሕአፓ እንደወሰዱ ብርሃነመስቀል ረዳ ራሱ አረጋግጧል:: በነኝህና በሌሎች ዝቅ ብሎ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ብርሃነ መስቀል ረዳ የእርማት ንቅናቄ ለማካሄድ በሚል በ1971 ዓ.ም. ከመርሐቤቴ በቴፕ ልኮ የሣፈው «የብዙሐን መስመር» መጣጥፍና ከደርግ ጋር ተባብሮ ለመስራት ቃል የሰጠበት ሰነድ እንደ መረጃ ቀርበዋል(16)::

መርሐቤቴ አንጃው የትጥቅ ትግል (በነሱ አባባል «ታጥቆ አንቂና አደራጅ ቡድን») እንዲያካሂድና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ በስብሰባ የወሰኑት አንጃዎች 1) ብርሃነመስቀል ረዳ፣ 2) አብዩ ኤርሳሞ፣ 3) በክሪ (የኮድ ስም ብርሃኔ)፣ 4) መልዕክተ ዮሐንስ፣ 5) መሐሪ፣ 6) ቡሴሪ፣ 7) ደምሴ ኃይለማርያምና 8) ሙላት (የኮድ ስም) ነበሩ:: ብርሃነመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ቀደም ብሎ የተስማሙ ቢሆንም በዚህ ስብሰባ ላይ ጌታቸው ማሩ አልተገኘም ነበር:: አብዩ ኤርሳሞ በሃድያ አካባቢ መጠነኛ የፖለቲካ ሥራ ሰርቶ ስለነበር የትጥቅ ትግሉን በዚያ ለመጀመር በቅድሚያ ቢያስቡም ሰፊ ሽፋን የሚሰጥ የመንቀሳቀሻ ቦታ ስለሌለው ሌላ አማራጭ አስፈለጋቸው:: በዚህ ጊዜ መርሐቤቴ ሌላ አማራጭ መሆን እንደሚችልና ለትጥቅ ትግልም አመቺ እንደሆነ፣ አርሶ አደር የፓርቲ አባላትም እንደሚገኙበትና ከነሱም ጋር ግኑኝነት እንዳለው ተሰብሳቢዎቹን የአካባቢው ተወላጅ ደምሴ ኃይለማርያም እንዳሳመነ ይጠቀሳል::

በመሰረቱ ኢሕአፓ መርሐቤቴ የትጥቅ ትግል ለመጀመር ዝግጅት ሲያደርግ እንደነበረ ጌታቸው ማሩና ብርሃነመስቀል ረዳ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል

በነበሩበት ጊዜ ስለሚያውቁ በቂ መረጃ ነበራቸው። ስለዚህ ደምሴ ኃይለማርያም ሊያደርግ የሚችለው እነብርሃነመስቀል ረዳ በዝና የሚያውቁትን ቦታ ወስዶ ማሳየት፣ መሣሪያዎችንና ሰዎችን ማጓጓዝ እንጅ ራሱ ጠቆመ የሚለው አባባል ተአማኒነት ሊኖረው አይችልም። ደምሴ ኃይለማርያም አላማችንን ከተረዳ በኋላ ሊደግፈን ቃለ እንጅ መጀመሪያ የተቃወቀለን እንቅስቃሴያችንን በማጥናት ብርሃነመስቀል ረዳን ለመግደል ወይም ለማስገደል ነበር የሚለው አባባልም እንዲሁ ጥርጣሬ ላይ የሚጥል ነው። ደምሴ ኃይለማርያም እነብርሃነመስቀል ረዳን መርሐቤቴ ካቆናጠጠ በኋላ አዲስ አበባ ተመልሶ በከተማ ልማት መሥሪያ ቤት በካድሬነት ሲሰራ ቢሮው ውስጥ በአንድ ወታደር ተገደለ ይባላል።

ደብረ ብርሃን ከተማ የሚገኙት የኢሕአፓ ፓርቲና ሊግ አባላት የብርሃነ መስቀል ረዳን እንቅስቃሴ እንዲከታተሉ መልዕክት እንደደረሳቸው ሲያጣሩ ብርሃነ መስቀል ረዳ ሳያውቁ በደብረ ብርሃን ከተማ እየተመላለሰ ሁኔታውን ካመቻቸለት ከአካባቢው ተወላጅ ከደምሴ ኃይለማርያም ጋር በእነዋሪ በኩል ወደ መርሐቤቴ መውረዱን ተረዱ (ከአካባቢው አንድ የኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ የተገኘ መረጃ)። ከጥቂት ጊዜ በኋላም የአንጃ አባላት ባደረጉት ጥቆማ የሰሜን ሸዋ የኢሕአፓ መዋቅሮች ሲጋለጡና በርክት ያሉ አባላቱ የቀይ ሽብር ሰለባ ሊሆኑ ቻሉ።

ብርሃነ መስቀል ረዳ በመርሐቤቴና አጎራባች በሆኑት የመንዝና ግሼ አውራጃዎች ጥቂት ታጣቂዎችን በመያዝ ከአካባቢው አደገኛ ሽፍታ ከመንግሥቴ ደፋር ጋር በፍቃደኝነትም ሆነ በመገደድ (በመታገት) አብሮ ከቦታ ቦታ ቢንቀሳቀስም ከደርግ ጦር ጋር ፍልሚያ አላካሄደም ነበር። እሱና የሱ ሰዎች የታጠቁትን መሣሪያዎች መንግሥቴ ደፋር እንዳይነጥቃቸው ስጋት ነበራቸው። ጌታቸው ማሩ ከሞተ በኋላ ከተማ ከነበሩት አንጃዎች ከመልዕክተ ዮሐንስ፣ ከጌታቸው ስዩምና ከሌሎች አንጃዎች ጋር ቀጥታ ግኑኝነት ነበረው። እነኝህና ሌሎች የከተማ ተባባሪዎቹ የሰደድ ካድሬ በመሆን በየከፍተኛውና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ተመድበው የኢሕአፓ አስረኞችን ያተራምሱ እንደነበረ ዝቅ ብሎ ተጠቅሷል። ከመንግሥትና ከሌሎች ግለሰቦች የዘረፉትን ገንዘብ፣ ጥይትና መሣሪያ በተለያየ ጊዜ ለብርሃነመስቀል ረዳ ሲያቀብሉት መንግሥቴ ደፋርም በስምምነታቸው መሰረት ድርሻውን ይወስድ ነበር።

በመንዝና ግሼ የነበሩት የተለያዩ ሽፍቶች የጋራ ስምምነት አልነበራቸውም። ብርሃነመስቀል ረዳና ጓደኞቹም የታጠቁትን መሣሪያዎች መንግሥቴ ደፋር ወይም ሌሎች ሽፍቶች ገፈው እንዳይገድሏቸው ስጋት ነበራቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ብርሃነመስቀል አንጃውን ሲመሰርት በነበረው እምነት መሰረት ከደርግ ምህረት አግኝቶ ከተማ ለመግባት ከፍተኛ ፍልጎት ነበረው። በዚህ የተነሳ በሁለት መንታ መንገድ ላይ ይገኝ ነበር። በአንድ በኩል ከሽፍቶች ስጋት ለመዳን ከመንግሥቴ ደፋር ጋር አንድ ስምምነት ተፈራርሞ የመሣሪያና ገንዘብ ዕርዳታ እየሰጠ ለመቀራረብ ሲሞክር በሌላ በኩል ከዚህ አጣብቂኝ ለመላቀቅ ከደርግ ጋር እርቅ ለመፍጠር ይላላክ ነበር። እንዲያውም አልተሳካም እንጅ ከመንግሥት ጋር ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ምህረት እንዲደረግለት በመልዕክተ ዮሐንስ አማካኝነት ግኑኝነት ጀምሮ ነበር። በመጨረሻ ይኸ ሁሉ ሳይሳካ ቀርቶ ከነአባሪዎቹ 14 ራሱን ሆኖ በደርግ ጦርና በአካባቢው ነጭ ለባሾች ተከቦ ተይዞ ከታሰረ በኋላ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነ።

ብርሃነመስቀል ረዳ ገጠር እየተንቀሳቀሰ እያለ ሌሎች አባላት በተለያየ ጊዜ ተቀላቅለውታል። የዚያኑ ያክል በመጥፋት፣ በመክዳት፣ ለደርግ እጃቸውን በመስጠትና ባለመስማማት የተለዩት ነበሩ። መ/አለቃ አበበ ጅማ መርሐቤቴ ኢሕአፓ የመሰረተው ዳግማዊ አሲምባ ይገኛል በሚል በነበክሪ በመሞኘት ከደርግ ከወሰደው አውቶማቲክ መሳሪያዎች ጋር የተቀላቀለ ስለነበረ መስማማት አልቻለም ነበር። በዚህ የተነሳ ይከዳና ከመንግሥቴ ደፋር ጋር ይቀላቀላል። ከዚያም እሱ የኢህአፓ ድርጅት ደጋፊና መሣሪያዎቹም የዚያው ድርጅት ንብረት መሆናቸውን በማስታወቅ አነብርሃነመስቀል ረዳ መሣሪያዎቹን ለመንዝና ግሼ ሽፍቶች እንዲያስረክቡ ክስ ያቀርባል። አነብርሃነመስቀል ረዳም አባላችን ነው በሚል ይከራከራሉ። መንግሥቴ ደፋርም ጥሩ መንገድ ስላገኘ ለማስማማት በሚል ሁለቱም መረጃቸውን እንዲያቀርቡ ውሳኔ ይሰጥና መሣሪያዎቹን በአደራ መልክ ይይዛል። መ/አለቃ አበበ ጅማም የሚፈልውን ካሚላ በኋላ ይሰወርና ወደሚፈልገው አካባቢ ይሄዳል። የአካባቢው ሽፍቶችም በደርግ ጥቃት እንደነብርሃነመስቀል ረዳ ተያዙ በከፊልም ተበታተኑ። አንዳንዶቹም በምህረት እጃቸውን ከሰጡ በኋላ ተገደሉ።

ደርግን የተጠጋ ድርጅት ሁሉ በራሱ እስኪመጣበት ድረስ አባላትን ለመመልመልና ደጋፊውን ለማብዛት ጥረት ያደርጋል። የኢሕአፓ ክፍልፋይ አንጃም ከደርግ ጋር ካበረ በኋላ በህይወት ማዳን ስበብ፣ በማስገደድና በማስፈራራት አንዳንድ በቁጥጥር ስር የነበሩ የኢሕአፓ አባላትን ለመመልመልና አቋማቸውን ለማስቀየር ጥረት አድርጓል። «ከምትሞቱ ነፍሳችሁን አድኑ» በማለት አንጃውም በደርግ ዙሪያ እንደነበሩት ድርጅቶች የኢሕአፓ አባላትን እንደ ቅርጫ ሥጋ ለመከፋፈልና አባል ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም ብዙ የኢሕአፓ አባላት ብንሞትም ለምናምንበት ዓላማ እንቆማለን በማለት ተቃውመዋል። አንዳንዶችም ከመሞት መሰንበት በሚል የተቀበሉ መስለው ለጊዜው ተቀላቅለው አንገታቸውን ደፍተው አሳልፈዋል። አንዳንዶች ደግሞ በደርግ ታድነው ሲያዙ የወሰዱት ምርጫ አንጃ ነበርን በማለት ህይወትን ለማዳን መሞከር ነበር። ይህም የእስር ጊዜ አንጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር። የእስር ጊዜ አንጃዎችም የደርግ ወዳጅና ደጋፊ በመሆን መርማሪ፣ ገራፊና ካድሬ በመሆን ታማኝነታቸውን ገልፀዋል። በፈቃዳቸው እጃቸውን የሰጡና የሚያውቁትን ያጋለጡም ከታማኞች ጎራ ይቆጠሩ ነበር።

በቀይ ሽብር ጊዜ የአንጃ አባላት በከፍተኛ 3፣ 5፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 15፣ 18፣ 19፣ 22 እና በሌሎች እስር ቤቶችና በደርግ ጽ/ቤት ጭምር መርማሪ፣ ገራፊ፣ ካድሬና የትምህርትና የቅስቀሳ ኮሚቴ በመሆን የዱሮ ጓደኞቻቸውን አሰቃይተዋል። የኢሕአፓን አሰራር ስለሚያውቁና ከደርግ ጋር ስላበሩ ምርመራ ለማካሄድ ተመራጭ ነበሩ። የከፍተኛ 9 እና 10 መርማሪዎች የአንጃው መሪ የነበረው የጌታቸው ማሩ ወንድምና እህት ነበሩ። በከተማ የነበሩት የነብርሃነመስቀል ረዳ ደጋፊ አንጃዎች አነሙፍታህ ሸሪፍ በከፍተኛ 5፣ መክብብ ተሰማ በከፍተኛ 7፣ አሰበል ድንቁ በከፍተኛ 18ና ሌሎች በተለያዩ ከፍተኞች የሰደድ ካድሬ በመሆን በኢሕአፓ እስረኞች ላይ የነበራቸውን የአዳኝነትም ሆነ የገዳይነት ሥልጣን በመጠቀም በሰደድ ሽፋን የራሳቸውን የአንጃ አባላት ለመመልመል ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል።(17) በጊዜው በነበረው የኢማሌድህ መጠላለፍ ለሰደድ ተአማኒ አለመሆናቸውና ለአንጃው እንደሚሰሩ ሲነቃባቸው ከታጠቁት መሣሪያ ጋር ብርሃነ መስቀል ረዳን ለመቀላቀል ሲጠፉ ተይዘው በ1972 ዓ.ም. ተገድለዋል።

እነኝህ ኮብላዮች በተለያየ ጊዜ ብርሃነመስቀል ረዳን ይገናኙት ገንዘብ፣ መሳሪያና የተለያየ ቁሳቁሶች ያቀብሉት እንደነበረ ክፍ ብሎ ተገልጿል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ብርሃነመስቀል ረዳ የአርማት ንቅናቄ ለማካሄድ አንድ ከደርግ ጋር ወግነው ኢሕአፓን ለማስመታት እንዳልተንቀሳቀሱ ይናገር የነበረው ትክክል አለመሆኑን ነው፡፡ ከደርግ ጋር አብረው ቆይተው ብርሃነ መስቀል ረዳን ለመቀላቀል የወሰዱት እርምጃ የተናጠል ሳይሆን የተቀነባበረ እርምጃ ነበር፡፡ እሱም ቢሆን ከመንግሥት ጋር መታረቅ የሚለው ሃሳቡ እንደማይሳካ ከተረዳ በኋላ ከተማ ከነበሩት ደጋፊዎች መካከል ከፊሎቹ ገጠር ገብተው እንዲያግዙትና ግማሾቹ ደግሞ ለከተማው ሥራ እንዲቆዩ ተስማምቶ ነበር፡፡

የኢሕአፓ አንጃ በብርሃነ መስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ ከተመሰረተ በኋላ ለመስፋፋት የሞከረው በመተዋወቅ፣ በጓደኝነት፣ በግል ግኑኝነት፣ አንዳንድ ጊዜም በማታለልና ታማኝ የኢሕአፓ አባላት ያሉበትን መዋቅር በመጥለፍ ነበር፡፡ (18) ጌታቸው ማሩ ከነወንድሞቹና ከነመስፍን አጎናፍር ጋር በሚኖሩበት በከፍተኛ 8 እና በአጎራባቹ በከፍተኛ 7 በሚገኘው ሰናድር በሚባለው የወጣቶች ማህበር የሚሳተፉ የኢሕአፓ የወጣት ሊግ አባላትን ለማጥመድ ብዙ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ወጣቱም ይህንን ለማፍረስ ብዙ ተቋቁሟል፣ በቀይ ሽብርም ፍዳውን አይቷል፡፡ ጌታቸው ማሩ ከወጣት ሊግ አመራሮች ጋር የነበረውን ግኑኝነት በመጠቀም ወደ አንጃው ለመሳብ ያደረገው ሙከራ አንድ የሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አመራር ለመቀየር ከመቻሉ በስተቀር አልተሳካም ነበር፡፡ ይህ የሊግ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አንጃ በመሆኑ የተነሳ ከሊግ አመራር ተገሎ በነጠላ ግኑኝነት እንዲቆይ ተወስኖበት ነበር፡፡ በእስር ጊዜ በኢሕአፓ አባላት ላይ ብዙ ጉዳት ካደረሱት አንጃ መካከል አንዱ ነበር፡፡

ጌታቸው ማሩ በጣም የተሳካ ፀረ ኢሕአፓ ድርጊት የፈፀመው በሚኖርበት አካበቢ የነበረውን የዞን አንድ የፓርቲ መዋቅር በቀላሉ የአንጃው ደጋፊ ማድረግ መቻሉ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ የአንጃው አባል የነበሩት የአካባቢው የዞን አንድ የፓርቲ፣ የወጣት ሊግና የጥቃት መከላከያ አመራሮች የኢሕአፓን መልዕክት በማዛባት፣ እርምጃ ባለመውሰድ፣ ንብረት ባለማስረከብ፣ በስራቸው የነበሩትን አባላት ባለማሳወቅና እንዲያስተላልፉም ሲጠየቁ ለማስተላለፍ ፍቃደኛ ባለመሆን አፍራሽ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በተለይም በክሪ (የኮድ ስም ብርሃኔ) የተባለው የዞን አንድ ፓርቲ ፀሐፊና ሙላት (የኮድ ስም) የተባለው የጥቃት መከላከያ አመራር ኢሕአፓን ሲያደናቅፉ የነበረው ብርሃነመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ በሚሰጧቸው መመሪያ መሰረት ነበር፡፡ ይህ በሰው ኃይሉና በመሣሪያው ብዛት ከብዙ የአዲስ አበባ ዞኖች ይበልጥ የተደራጀው የመርካቶ አካባቢ ዞን ለተወሰነ ጊዜ በብርሃነመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ ስር ወድቆ ከኢሕአፓ ትዕዛዝ ባለመቀበል እርምጃ መውሰድ አቁሞ ነበር፡፡

መርካቶ ከፍተኛ የንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት፣ ሕዝብ በብዛት የሚዘዋወርበትና ተፋፍጎ የሚኖርበት ቦታ በመሆኑ ለኢሕአፓ እንቅስቃሴ አመቺና ለመሸሸጊያም የሚስማማ ነበር፡፡ ሆኖም አካባቢውን አንጃው ከበረዘው በኋላ የብዙ ኢሕአፓ ወጣቶች ህይወት ሊጠፋበት ችሏል፡፡ በዞን አንድ የጥቃት መከላከያ ከነበሩት መካከል ወደ አንጃነት የተቀየሩት ከመንግሥት ጋር በመወገን ከደርግ አልሞ ተኳሾች ጋር በመኪና እየተዘዋወሩ መርካቶ ኢሕአፓዎች በሚያዘወትሩባቸው ሻይ ቤቶች፣ ሲኒማ ቤቶች፣ ሱቆችና ሌሎች አካባቢዎች የሚያውቃቸውን እየጠቆሙ አስፈጅተዋል፡፡

ጌታቸው ማሩ የአንጃው ደጋፊ ከሆኑት የዞን አንድ አመራሮች በተጨማሪ የኢሕአፓን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ «ሌሎችን ሰዎች ብገናኝስ» (ደርግ/መኢሶን) ይለው እንደነበር ብርሃነመስቀል ረዳ አረጋግጧል:: በተለይም ኢሕአፓ ከቁጥጥራቸው ውጭ የሆነ ሌላ እርምጃ እንዳይወስድ ለመግታት ወይም እነሱ እንደሚሉት «አብዮቱን ከቀኝ ኩደታ» ለማዳን ተጨማሪ ድጋፍ አስፈልጓቸው ነበር:: ለዚህ የወሰዱት እርምጃ በጌታቸው ማሩ አማካኝነት ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤልና ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ የኢ.ሕአፓ አባልና ደጋፊ መሆናቸውን ለደርግ መረጃ ማቀብል ሳይሆን አይቀረም::

እንደ ዞን አንድ ሁሉ በሌሎች ዞኖች የሚገኙ አንዳንድ የጥቃት መከላከያዎች የኢሕአፓን ድርጊት በሰውር የሚያደናቅፉ ነበሩ:: በድብቅ የተፈፀመ ድርጊት በአጋጣሚ ይፋ ይወጣል እንደሚባለው ኢሕአፓ በአንድ የደርግ ባለሥልጣን ላይ ሊወስድ ያቀደውን እርምጃ ያከሸፍኩ እኔ ነኝ እያለ የጥቃት መከላከያውን መዋቅር ከአባሪዎቹ ጋር ቴሌቪዥን ላይ በቻርት በተደገፈ ገለፃ ያቀረበው ቺፍ ኮማንደር የአንጃውን ድርጊት የሚያመለክት አንጅ ሌላ አልነበረም:: እነኚህ የዞን ሦስት የጥቃት መከላከያ አባላት ቴሌቪዥን ላይ አራት ሆነው ቀርበው መግለጫ የሰጡት በቺፍ ኮማንደሩ ግንባር ቀደምትነት ነበር:: ተገደው ቴሌቪዥን ላይ መግለጫ መስጠታቸው ባያሰወቅሳቸውም ከመታሰራቸው በፊት ግዳጃቸውን አለመፈጸማቸው ያስወቅሳቸዋል:: ከአራቱ ሁለቱ በ1978 ዓ.ም. ሲገደሉ ሁለቱ ድነዋል:: በዚሁ በዞን ሦስት የጥቃት መከላከያ አባላት አማካኝነት መስከረም 1970 ዓ.ም. ከአጅኩ የመንገድ ሥራ ድርጅት 80,000 ብር ተዘርፎ ኢ.ሕአፓ ሳይጠቀምበት ኤልያስ የተባለው አንጃ ወስዶታል::

አንጃው በነበረው ድርጅታዊ ግኑኝነትና ጓደኝነት ለመስፋፋት እንደሞከረ ሁሉ የኢሕአፓ ደጋፊዎችንም ለማስፈጀትም ሆነ በኃይል ለማጥፋት በስፋት ተንቀሳቅሷል:: ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. የላብ አደሮች ቀን ከሚከበርበት ሁለት ቀን በፊት በአዲስ አበባ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ደርግ አሰቃቂ የግፍ እርምጃ በመውሰድ ብዙ የኢሕአፓ ወጣቶች ጨፍጭፏል፣ አስር ቤትም አጉሯል:: ለዚህ አስከፊ ድርጊት ደርግ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ በዚያን ቀን ሰላማዊ ሰልፍ እንደሚካሄድ ሚስጥራዊ መረጃ ቀደም ብሎ በማቀበል አንጃው እንደተባበረ ይጠረጠራል:: (19) በዚህ ሰልፍ ምን ያክል እንደተገደሉና እንደታሰሩ በትክክል የተጣራ መረጃ ባይኖርም የደርግ የቀይ ሽብር የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» 57 ወጣቶች እንደተገደሉ የስም ዝርዝራቸውን አካቷል:: (20) በሌላ የደርግን ወንጀል የሚዘረዝር ሰነድ ደግሞ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም በአዲስ አባባ 153 ሰዎች እንደተገደሉ ተጠቅሷል:: ዕለቱ በአዲስ አበባ የዕልቀት ቀን ነበር:: እንዲያውም የምኒልክ ሆስፒታል አስከሬን ምርመራ ክፍል ከወለሉ እስከ ጣራው ድረስ ሰው በሰው ላይ በተከመረ አስከሬን ተሞልቶ ቤተ ዘመዶችም የሚፈልጉትን አስከሬን ለማግኘት መቆሚያ አልነበራቸውም:: ከተገደሉት መካከል አንዳንዶች በእድሜ ለጋ የሆኑ የ15 ዓመትና ከዚያም በታች የሆኑ ታዳጊዎች ይገኙበታል:: ግድያውም በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በክፍላተአገርም ተካሂዷል:: አንድ በዕለቱ አህቱ የሞቱችበት የዚያን ቀን ትውስታ «የአዲስ አበባ ሕዝብ በእንባ ሲታጠብ ደርግ በደስታ ብዛት በሻምፓኝ የተራጨበት ቀን» በሚል ገልጾታል::

ክፍሉ መኩሪያ የተባለው በደርግ ጽ/ቤት መሸጎ የነበረ አንጃ ቀድሞ የሚያውቃቸውን 1) ተፈሪ ቦጋለ፣ 2) አበባው ተፈሪና 3) ተሰማ ንዋይ የተባሉትን ጓደኞቹን ጥር 8 ቀን 1970 ዓ.ም. በነፃ እርምጃ አስገድሏል:: (21)

እነዚህ ሦስት ግለሰቦች በዚያን ቀን በደብረ ዘይት መንገድ ሸዋ ዳቦ ቤት አካባቢ አራተኛ ክፍለ ጦር አጥር ስር ከሚገኘው ከአቶ አበበ ኃይሌ ቡና ቤት ፊት ለፊት የተገደሉት በክፍሉ መኮንኖች ጠቋሚነት ከየቤታቸው ተወስደው ነበር:: ከግድያው በኋላ የሚኖሩበትን ቤት በመፈተሽ፣ የሟች ወንድሞችን ደርግ ጽ/ቤት በመውሰድ ከፀረ አብዮተኞች ጋር ተባባሪ ሳትሆኑ አትቀሩም በሚል አንገላተዋቸዋል:: በዚህ መልክ አንጃዎች የሚያውቋቸውን የሚፈለጉ የኢሕአፓ አባላት ለመንግሥት እየጠቆሙ በነፃ እርምጃ አስገድለዋል::

ከነበክረ በተጨማሪ የጌታቸው ማሩ የቅርብ ጓደኞች የነበሩት አብዩ ኤርሳሞና ገዛኸኝ ስሜ የኢሕአፓን እንቅስቃሴ ከማደናቀፍ አልፈው የድርጅቱን ንብረትና ገንዘብ ለአንጃው በማቀበል፣ አባላቱን በማታለል ብርሃነ መስቀል ረዳን እንዲቀላቀሉ በማድረግና የኢሕአፓን አባላት በፀጥታ ኃይሎች እንዲጠለፉና እንዲገደሉ በመጠቆም አፍራሽ ሚና ተጫውተዋል:: (22) የዞን አምስት የፓርቲ ፀሐፊ የነበረው አብዩ ኤርሳሞም ኢሕአፓን የማደናቀፍ፣ አባላትን ያለማስተላለፍ፣ ንብረትና መሣሪያ የመዝረፍ ድርጊቶች እንደ ዞን አንድ ፈፅሟል:: ሌሎች የአንጃ አባላትም በዚሁ አይነት በቅርብም ሆነ በርቀት ጓደኞቻቸውን በመጠቀም፣ ቀደም ብሎ ሚስጥራዊ ግኑኙነት በማዘጋጀት፣ የኢሕአፓ አባላትን ድርጅታዊ እንቅስቃሴ በመከታተልና የቴሌፎን ንግግሮችን እንዲጠለፉ በማገዝ እንዲገደሉ አድርገዋል::

አንጃው ኢሕአፓን ካስመታ በኋላ ድርጅቱ መታረም ይገባዋል በሚል ያቀረበው «የእርማት ንቅናቄ» የሚያስኬድ አይደለም:: በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱትን የልዩነት ነጥቦች በማድበስበስ፣ «ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል» እንደሚሉት፣ ሌሎች ልዩነቶችን በመጨማመር፣ «የብዙሐን መስመር» በሚል ብርሃነመስቀል ረዳ ከመርሐቤቴ በቴፕ ልኮ በፅሁፍ መልክ ያቀረበው በስድብ የታጀለ መጣጥፍ ብዙ ሃሰቦችን ያነሳል፣ ይጥላል:: በተለይም የሱማሌ ጦርነት፣ የብሔር ጥያቄ፣ የዴሞክራሲ ጥያቄ፣ የማርክሲስት ድርጅቶች ህብረት፣ በኢትዮጵያ አብዮት የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት፣ ቀይ ሽብር የተባለው የደርግ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ፣ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ሕብረት አለ ወይ?፣ ኢሕአፓና የወደፊቱ ጉዞ ተጠቅሰዋል:: ይኸ ፅሑፍ እነብርሃነመስቀል ረዳን ከደርግ ጋር ያቀራርብ እንደሆነ እንጅ ኢሕአፓን ከአንጃው ጋር የሚያስታርቅ አይደለም:: ሁለቱ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የኢሕአፓን ደንብ ባለማክበር፣ ለዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ተገዢ ባለመሆንና በስልጣን ሽኩቻ በፈጠሩት የተሳሳተ የልዩነት አቋም ኢሕአፓ በብዙ መልኩ ተጎጂ ሲሆን የተጠቀሙት ደርግና ደጋፊዎቹ ነበሩ::

ኢሕአፓ በሶሻል ኢምፔሪያሊዝም ላይ፣ በደርግ የፋሽስት ባህርይና ከደርግ ጋር ግንባር መፍጠር የማይታሰብ መሆኑን አስረግጦ የወሰደው አቋም ትክክል ነበር:: ፋሽዝም ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአንዳንድ የካፒታሊስት አገሮች ሶሻል ዴሞክራሲ በኮምኒዝም ላይ በነበረው ጥላቻ የተነሳ ለመደብ ትግል እንቅፋት በመሆን የላብ አደሩን መደብ ሶሻሊስት አብዮት እንዳያካሂድ ስለገደበው በጊዜው የተፈጠረውን የኤኮኖሚና ሌሎች ቀውሶች ተከትሎ የተከሰተ «የቶታሊቴሪያን» (የአንድ ድርጅት ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት) መንግሥት ነበር (23):: ይህንን መንግሥት የመሰረቱት በ1930 ዓ.ም. አካባቢ የጀርመኑ ሒትለር፣ የጣሊያኑ ሞሶሎኒና የስፔኑ ፍራንኮ ነበሩ:: ካፒታሊዝም ባላደገበት ታዳጊ አገሮችም ሌሎች አምባገነኖች በኢንዶኔዥያ ሱሐርቶ፣ በቺሊ ፒኖሽ፣ በካምቦዲያ ፖልፖትና በኢትዮጵያ መንግሥቱ

ኃይለማርያም የአብዮታውያንን ትግል በማኮላሸት «የቶታሊቴሪያን» ባህርይ ያላቸው የፋሽስት መንግሥታት መስርተው ነበር:: ሁለቱን የሚያመሳስላቸው የሚያለያያቸውም ባህርያት አሉ:: ዝርዝሩ አልቀረበም::

በኤርትራ ጥያቄ ላይ ኢሕአፓ ስለነበረው አቋም በምዕራፍ ሁለትና ሦስት ተጠቅሷል:: ነገር ግን ብርሃነመስቀል ረዳ «የብዙሐን መስመር» በሚለው መጣጥፍ ላይ ስለ ኤርትራ ጥያቄ ያነሳው ነጥብ የኢሐአሠን ጥንስስ ሠራዊት (የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት ሠራዊት/የኢሕአፓ ሠራዊት) እየመራ ኤርትራ ከገባ በኋላ ወደ ትግራይ ለመሸጋገር ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ሲደራደር ከወሰደው አቋም ጋር ይጣረሳል:: በዚያን ጊዜ የኤርትራ ነፃነት መደገፍ አለበት ሲል የነበረ(24) እንዴት አቋሙን ቀይሮ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ከሚለው መርህ ውጭ ሌላውን እንደተቃወመ ግልፅ አይደለም::

በሱማሌ ጦርነትም ላይ ኢሕአፓ የወሰደው አቋም ትክክለኛነቱን መርምሮ የወሰደው እርምጃ እንጅ ደርግን ለማስደሰት ብሎ ያደረገው አልነበረም:: ደርግ የብሔር ጥያቄን መፍታት ስላልቻለ የኤርትራ፣ የምስራቅና የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦችን የብሔር እንቅስቃሴ አባብሶት ጭፍጨፋና ጦርነት ይካሄድ ነበር:: ኢሕአፓ ግን የራስን ዕደል በራስ መወሰን በሚለው መርህ መሰረት የጭቁን ብሔር ብሔረሰቦችን ትግል ስለሚደግፍ ደርግ ከጭፍጨፋ እንዲቆጠብ ይጠይቅ ነበር:: የምስራቅና የደቡብ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ትግል በዚያድ ባሬ የመስፋፋት ጣልቃ ገብነት መፍትሄ እንደማያገኝ ኢሕአፓ ያምን ነበር:: በዚህ የተነሳ ሐምሌ 1969 ዓ.ም. የዚያድ ባሬ የመስፋፋት ጦርነት ሲጀመር ኢሕአፓ ተቃውሟል (25)::

«የብዙሐን መስመር» የተባለው መጣጥፍ ባነሳው በአንድ ሃሳባ ላይ መስማማት ይቻላል:: በዚያን ጊዜ በከተሞች አካባቢ ለህዝባዊ አመፅ መገፋፋት መጣጥፉ እንደሚለው ባይሆንም ወቅታዊ አልነበረም:: ኢሕአፓም ይህን ስህተቱን ተገንዝቦ ራሱን ለማረም ስህተት የሰሩትን ባለው ዴሞክራሲያዊ አሰራር ወቅሷል::

እንደማንኛውም የአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኞች ከፍ ብሎ በተጠቀሱት የአንጃ አባላት በመርማሪነትና በካድሬነት በሚሰሩበት ከፍተኞችም በቀይ ሽብር ብዙዎች ተገድለዋል፣ ብዙዎችም ተሰቃይተዋል:: ሌላው ቀርቶ የደርግ የበላይ ባለሥልጣኖችን ሳያስፈቅዱ መግደል ተከልክሏል ከተባለ ከሚያዝያ 1970 ዓ.ም በኋላ ግንቦት 5 ቀን 1970 ዓ.ም. የመጨረሻው የከፍተኛ ስምንት የቀይ ሽብር ግድያ ተካሂዶ 1) አንተነህ ፍርድ አወቅ፣ 2) ፍቅርተ ሞገስ፣ 3) ዳንኤል ይርጉ፣ 4) ዮሐንስ በላይ እና 5) ዱባለ ደምሴ ተገድለዋል::(26) ከእነኝህ መካከል አንዳንዶቹ በከፍተኛ ስምንት ታስረው በነበሩ አንጃ አባላት አለንላችሁ በሚል የተሳሳተ ተስፋ ተገፋፍተው ከተደበቁበት ቦታ በራሳቸው ፍቃድ እጃቸውን ለከፍተኛ ስምንት እንዲሰጡ የተደረገም የግድያው ሰለባ ሆነዋል::

በዚሁ በግንቦት ወር 1970 ዓ.ም. በከፍተኛ አምስት እስር ቤት ታስረው ከነበሩት መካከል 1) መሐመድ አክሊሉ፣ 2) አየለ መንግሥቱ፣ 3) ሰለሞን ጉራራ፣ 4) ወንድሙ ኪዳኔ እና 5) ግርማ ነጋሽ ተገድለዋል:: (27) በከፍተኛ ሰባትም ሰኔ 27 ቀን 1970 ዓ.ም. የቀይ ሽብር ሊካሄድ ከተወሰነባቸው ዘጠኝ ግለሰቦች 1) ዘ. ጉግሳ፣ 2) ካ. ታምሩ፣ 3) መ. ሐሰን፣ 4) ጌቱ ሐጎስ፣ 5) ሰ. መሐመድ፣ 6) ግ. ደቻሳ፣ 7) ታ. ገላን፣ 8) ማ. ጎበና እና 9) ክ. ከፍሌ መካከል ስምንቱ በታምር ድነው ብዙ ጊዜ በከፍተኛ፣ ማዕከላዊና ክርቸሌ በእስር ማቀው ሲፈቱ ከመካከላቸው ጌቱ ሐጎስ ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ወደ ከፍተኛ አራት

በውስት ተወስዶ ስለነበረ አዚያው ተገድሏል::(28) በጣም የሚገርመው የከፍተኛ ሰባት ውሳኔ ሰጭዎች በጌቷ ሐጎስ ላይ ውሳኔ ሲያስተላለፉ የት እንዳለ እንኳን አያውቁም ነበር ማለት ይቻላል:: አያወቁም ከሆነ ይህ ወጣት ሁለቱም በታ ተፈርዶበታል ለማስኘት ያደረጉት ይሆናል::

ከከፍተኛ ሰባት በተገኘ በፀሐፊው እጅ በገባ መረጃ መሰረት በእነኝህ ዘጠኝ ሰዎች ላይ የቀይ ሽብር እርምጃ እንዲወሰድባቸው በፊርማቸው በማፅደቅ ውሳኔ ያስተላለፉት የከፍተኛ ሰባት የአብዮታዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ (የቀይ ሽብር ኮሚቴ) የስም ዝርዝር የሚከተሉት ነበሩ::

1. በርሲሳ በዳዳ የከፍተኛው ሊቀመንበር -- ሰብሳቢ
2. ካሣዬ ወ/ማርያም የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት -- ተ/ም/ሰብሳቢ
3. አዳሙ ንጋቱ የከተማ ልማት ተወካይ -- አባል
4. ወ/ር አበበ አያሌው የፖሊስ ተወካይ -- አባልና ፀሐፊ
5. ደገፋ ወልደሰንበት የከፍተኛ 7 ም/ተወካይ -- አባል
6. አሰፋ በቀለ የመኢሰማ ተወካይ -- አባል
7. ተስፋዬ መኮንን የከፍተኛ 7 የአብዮት ጥበቃ ሊ/መንበር -- አባል
8. ደጉማ ቴኮም የሕዝብ ድርጅት ሁለተኛ ተወካይ -- አባል

ይህ የስም ዝርዝር እንደሚያረጋግጠው በጊዜው ምንም የፍርድ ቤት ስልጣን፣ የሕግ እውቀትና ሰብአዊ ርህራሄ የሌላቸው ግለሰቦች በአብዮታዊ ኮሚቴ ስም ተሰባስበው የኢትዮጵያን የወንጀለኛ መቅጫና ሌሎች ደንቦች ሳያገናዝቡ ደርግ በሰጠው መመሪያ ብቻ በመመርኮዝ በየከፍተኛውና በሌሎች እስር ቤቶች ያጎሯቸውን የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ይጨፈጭፉ እንደነበር ነው::

በመጨረሻ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በደርግ ዙሪያ የነበርው ሽኩቻ ሲጠራ በሱ ከለላ የነበሩት የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ስለተፍረከረኩና አባላቱም ስለታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ በአንድ ወጥ መታየት ጀመሩ:: አሳሪና ታሳሪ፣ ገራፊና ተገራፊ፣ አዳኝና ገዳይ፣ መልማይና ተመልማይ የነበሩት ሁሉ ሁሉም አንድ ሆኑ:: ሁሉም እኩል እስር ቤት ተገናኙ፣ ሁሉም ጋቢና ዋራንት ጠባቂ ሆኑ:: በቀጣዩ የትግል ወቅትም የቀይ ሽብር ከፍተኛ በትር ያረፈባቸው ድርጅቶች ተሽመድምደው ሲቀሩ ብሔርተኞች ገነው ሊወጡ ቻሉ:: ደርግም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በከተማ ያካሄደውን ትግልና ከሱማሌም ጋር የነበረበትን ጦርነት በአሸናፊነት ቢወጣም ከብሔርተኞች ጋር ያደረገው ፍልሚያ ሊቀናው አልቻለም::

3. የአሕአፓ አባላት የርስ በርስ ሁኔታ

በዚሁ በቀይ ሽብር ውርጅብኝም የተነሳ የኢሕአፓ አባላት ርስ በርሳቸው እንዴት ይተያዩ እንደነበር መጥቀስ ያስፈልጋል:: በዛ ያሉት መንፈሰ ጠንካራ የነበሩት የድርጅቱ አባላት ሰቆቃውን በመቋቋም ሊያሳልፉ ሲችሉ ጥቂቶች ራሳቸውን ብቻ ለማዳን ያሳዩት ስስት የሚረሳ አይደለም:: ከመታሰራቸው በፊት ከሚታወቁበት አቋምና ባህርይ ውጪ አንዳንዶች የደርግ ደጋፊ ሆነው ለመቅረብ፣ የአንጃው ደጋፊ ሆነው ለመታየት፣ የኢሕአፓን እንቅስቃሴ ለማጥላላት፣ በቁጥጥር ላይ እያሉ ጓደኞቻቸውን ለመሰለል፣ ወዘተ. ያላደረጉት ሙከራ አልነበረም::

አንዳንዶች ደርግን እንደተቀላቀሉና ወደ አብዮቱ ሠፈር እንደተመለሱ በአደባባይ በመናገር ሌሎች የእነሱን አርአያነት እንዲከተሉ የሚገፋፉ ነበሩ::

ሌላው ቀርቶ ከነበሩበት እስር ቤት አልፎ በሌሎች እስር ቤቶች እየተዘዋወሩ ይህንኑ ይሰብኩ ነበር። ከእነኝህ መካከል ጭልጥ ብለው የደርግ ጋሻ ጃግሬ በመሆን በተለያዩ እስር ቤቶች ገራፊና መርማሪ በመሆን ያገለገሉ፣ ገዳይና አስገዳይ በመሆን የተባባሩ ነበሩባቸው። አንዳንዶች ሁሉንም ነገር በሌሎች ላይ በመደፍደፍ የራሳቸውን ተሳትፎ ለማሳነስ ሞክረዋል። ሌሎች ደግሞ የሚያውቁትን ቀርቶ የማይመለከታቸውን መረጃ ለቀይ ሽብር አራማጆች በመስጠት ታማኝ ሆነው ለመቅረብና ጓደኞቻቸውን ለማሳጣት አጋጣሚውን ተጠቅመዋል። እንዲያውም ጓደኞቻቸውን የተደበቀ ቀሪ ሚስጥር ስላለ ያውጡ በማለት እየገፋፉ አደጋ ላይ ጥለዋቸዋል።

አንዳንዶች ስቃዩ ሲበዛባቸው ከድብደባው ለመተንፈስ ያልሰሩትን በመናገር ለከፋ ችግር ተዳርገዋል። ያልሆኑትን በመሆንና «የኢሕአፓ የጥቃት መከላከያ አባል ነኝ»፣ «እከሌን የገደልኩ እኔ ነኝ»፣ «እከሌን ያስገደልኩ እኔ ነኝ» ወዘተ. በማለት ሕይወታቸውን ያጡም ይገኙበታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ወጣት በከፍተኛ 12 የተፈጸመበትን የምርመራ ስቃይ መቋቋም ሲያቅተው 24 ሰዎችን ገድያለሁ የሚል የማይታመን ቃል በመስጠቱ የቀይ ሽብር እርምጃ ተወስዶበታል። ይህ ወጣት በድብደባ ጥርሱ ረግፎ ሰውነቱ በሙሉ ቁስል ሆኖ መቆም፣ መቀመጥና በደንብ መናገር በማይችልበት ሁኔታ እያለ ቀበሌ የተሰበሰቡ ሰዎች ዘንድ በአቅፍ ተወስዶ በሰለሞን ይመስገን ስማ በለው አማካኝነት 24 ሰዎች መግደሉን እንዲያምን ተገዷል። በተሰበሰቡት ሰዎች ፊት እንደቀረበ የሚናገረው እንኳን ስለማይሰማ አፉ ሲንቀሳቀስ የሚያስተጋባው የቀይ ሽብር አራማጁ ሰለሞን ይመስገን ነበር። ይህ ወጣት ይህን ያክል ሰዎች ይግደል ወይም አይግደል በእርግጠኝነት ለመመስከር የሚያጠራጥር መሆኑን በጊዜው በከፍተኛው በእስር ላይ የነበሩት ያረጋግጣሉ። (29)

ይህን መሰል ተመሳሳይ ሁኔታዎች በክፍተኛ 25 እና በሌሎች ከፍተኞችም አጋጥመዋል። እነኝህ ሁሉ የሚያመለክቱት በቀይ ሽብር ጊዜ ሲካሄድ የነበረው ስቃይ የሰው ፍጡር ሁሉ ከሚቋቋመው በላይ መሆኑንና ከስቃዩም ለመተንፈስ ሲባል ያላደረጉትንም ለመቀበል የሚያስገድድ መሆኑን ነው። ምናልባት የቀይ ሽብር አራማጆች ቃል የተቀበሉበት የምርመራ መዝገብ ቢፈተሽ አንዳንድ በኢሕአፓ ተገደሉ የተባሉ ግለሰቦች ብዙ ገዳይ ሳይኖራቸው አይቀርም።

የተለዩ አጋጣሚዎችም ነበሩ። የብዙዎችን ስቃይ ለራሳቸው በመቀበል ሁሉንም ነገር የሰራሁት እኔ ነኝ በሚል ማንኛውንም ወደራሳቸው በመሳብ የሌሎች ጓደኞቻቸውን ሕይወት ያተረፉና ብቻቸውን መስዋዕት የሆኑም ሞልተዋል። ድብደባውንና ስቃዩን በመቋቋም ፍንክች ሳይሉ ሕይወታቸውን ያተረፉ ደፋሮችም ይገኙበታል። ሌሎች ደግሞ በቁጥጥር ስር በዋሉበት ጊዜ ማንኛውንም አጋጣሚ በመጠቀም ከጓደኞቻቸው ጋር በመነጋገር ምን ምን መረጃ መስጠት እንደሚገባቸው የሚያመቻቹም ነበሩ። ከአባሪ ጓደኞች ጋር መልዕክት በመለዋወጥ በጋራ የሚያውቁትን ሚስጥር በመጠበቅ የጋራ ሕይወትን ለማትረፍ ተችሏል። አንዳንዶች በግል የደበቁትን ሚስጥር ኋላ የሚያውቁቸው ሲታሰሩና ሚስጥር ሲወጣ አደጋ ላይ ወድቀዋል። በአጠቃላይ በቀይ ሽብር ጊዜ የተለያዩ ምስቅልቅል የሆኑ ሁኔታዎች አጋጥመዋል። በዚያን ወቅት በጋራም ሆነ በግል የነፍስ አድን ዘመቻው ከፍተኛ ነበር። አንዱን ከሌላው ለይቶ ለማየት ያስቸግራል። በጋራ ጥረት የዳኑት የሚመስገኑ ቢሆንም በግል ህይወቱን ለማዳን ራሱን አሳልፎ ላለመስጠት የተሟገተውም

የሚናቅ አይደለም። ምንም እንኳን በአንዳንድ ራስ ወዳዶች የተነሳ ያለአግባብ የተጎዱና ሕይወትም የጠፋ ቢሆንም የጊዜው ሁኔታ የፈጠረው መሆኑን ታውቆ ከዚያ ሰቆቃ ተርፈው አሁን በሕይወት ያሉት ይህንን ሁሉ በጥሞና አገናዝበው በሆደ ሰፊነት ይቅር ባይ መሆን ይገባቸዋል።

ደርግ በመገናኛ ብዙሐን እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የህትመት ሚዲያ ላይ የታሰሩ የኢሕአፓ አባላት መግለጫ እንዲሰጡ በማስገደድ ትያትር ይሰራ ነበር። በማሰቃየትና በማስፈራራት የደርግን አቋም አምነው የተቀበሉ በማስመሰል አንዳንድ የፓርቲ፣ የሊግና የጥቃት መከላከያ አባላት «የኢሕአፓ መስመር የተሳሳተ ነው»፣ «ትክክለኛውን የአብዮት መስመር እንከተላለን»፣ ወዘተ እያሉ ይፋ መግለጫ እንዲሰጡ የተገደዱ ነበሩ። አንዳንዶች ኢሕአፓ ያልሰራውን የፈጠራ ወሬ የሚያቀርቡና የአንጃውን አቋም የሚያንፀባርቁ መግለጫዎችን የሰጡ ነበሩ። በጊዜው ከሁለቱም ወገን የሚቀርቡት መግለጫዎች በስር ላይም ሆነ ከእስር ውጭ በነበሩት የኢሕአፓ አባላትና የድርጅቱ ደጋፊዎች ላይ ተስፋ መቁረጥና መጠራጠር አስከትለው ነበር።

4. የጋቢና ዋራንት ጥሪ

በአገራችን ባህል መሰረት አንድ ሰው ሲሞት ከመቀበሩ በፊት አስከሬኑ ይገነዛል፣ ይፀዳዳል፣ ዘመድ ከተሰበሰበ በኋላ ሲቀበር ሲል የከፈን ልብስ እንደ ጋቢ መሰል የአገር ልብስ ወይም አቡጀዴ ለብሶ በሰሌን ተጠቅልሎ ወይም በሳጥን ውስጥ ታሽጎ ይቀበራል። አስከሬንን በሳጥን ውስጥ አሽጎ መቅበር እንደ ሃይማኖቱና እንደ ሀብቱ ይለያያል። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች አስከሬንን በሳጥን አሽጎ መቅበር እምነታቸው ስለሚከለክል በሰሌን ጠቅልለው ይቀብራሉ። ክርስቲያኖች በሬሳ ሳጥን አሽገው መቅበርን ሃይማኖታቸው ባይከለክልም የሳጥን መግዣ ገንዘብ የሌላቸው በሰሌን ጠቅልለው መቅበር የተለመደ ነው።

በደርግ የቀይ ሽብር ዘመን ሰው ሲታሰር መጀመሪያ ከጠያቂ እንዲገባለት የሚፈቀደው ጋቢና ምግብ ነበር። ምግብ የሚፈቀደው ደርግ ከጥይት በስተቀር ሌላ መቀለብ ስለማይችል ሲሆን ጋቢ ደግሞ እስኪገደሉ ድረስ የብርድ መከላከያ ከመሆን አያልፍም ነበር። ምንም እንኳን በአገራችን ባህል መሰረት አንድ ሰው ሲሞት የከፈን ልብስ እንደሚያስፈልገው የኢሕአፓ ወጣቶች ቢያውቁም ለግድያ ሲጠሩ ጋቢ ቀርቶ ብጣቂ እንሶላ እንኳን ሳይቀር በሕይወት ለቀሩ ጓደኞቻቸው ትተው ይወጡ ነበር። ደርግም ቢሆን ከገደለ በኋላ እንኳን በጋቢ ጠቅልሎ ሲቀብር ቀርቶ አንዳንድ ጊዜ አፈር ሳያለብስም ለአውሬ ይሰጥ ነበር።

ምግብ በአንዳንድ እስር ቤት እንዲገባ ቢፈቀድም አስከናካቴውም እንደ ደርግ ጽ/ቤት ባሉ እስር ቤቶች ከውጪ ጠያቂም ለእስረኞች ማስገባት አይቻልም ነበር። የደርግ ጽ/ቤት እስረኞች ህይወታቸውን የሚያቆዩት ለጠባቂ ወታደሮች የሚመጣውን ምግብ ትርፍራፊ በመመገብ ነበር።

ዋራንት የወንጀል ቁጥር፣ የወህኒ መዝገብ ቁጥር፣ የእስረኛው ስምና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች የሰፈሩበት በሲጋራ ወረቀት ላይ ተጽፎ ከርቸሌ ሲገቡ የሚሰጥ የመታወቂያ ወረቀት ነበር። እስረኛው በፍርድ ቤት ወይም በሌላ ባለሥልጣን ትዕዛዝ ለመታሰሩ የወንጀል ቁጥሩ ያመለክታል። ይኸው ዋራንት አብዛኛውን ጊዜ በሲጋራ ወረቀት ላይ ተጽፎ ይሰጥ እንጅ በማንኛውም

ጠንከር ባለ ወረቀት ላይ ተጽፎ ሊሰጥ ይችላል። ይህም ሊሆን የቻለው የወህኒ ቤቱ አስተዳደር የመታወቂያ ወረቀት (ዋራንት) ለማሳተም አቅም ስለሌለው ነበር። ለእስረኛው ይሰጥ የነበረው ዋራንት ቀጥሎ የተመለከተውን መረጃዎች የያዘ ሲሆን ለቀጠሮና ለፍርድ እስረኞች የተለያየ ዓይነት እንደነበረ መገንዘብ አያዳግትም።

<u>የአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ለተፈረደበት እስረኛ የሚሰጠው የመታወቂያ ወረቀት</u>
<u>(ዋራንት)</u>

የእስረኛው ስም---
የወህኒ ቤት መ.ቁ.-------------------የወንጀል ቁ.---------------------
የተፈረደበት ቀን-----------------------የፍርድ ልክ---------------------
----
የወንጀሉ ዓይነት--
የሚፈታበት ቀን---

እንግዲህ አንድ እስረኛ ከከርቸሌ ወደ ደርግ ጽሕፈት ቤት ወይም ወደ ማዕከላዊ ሲጠራ ጋቢና ዋራንት ይዞ እንዲቀርብ ይጠየቃል። የጋቢና ዋራንት ጥሪ ከሦስት ነገሮች ለአንዱ ማለትም ለቺቺ (30)፣ ለፍቺ ወይም ለተጨማሪ ምርመራ ሊዳርግ ይችላል። የተጠራውም ግለሰብ ለየትኛው እንደተፈለገ ስለማያውቅ ጋቢውን አንግቦ ዋራንቱን አንጠልጥሎ መቅረብ ነበረበት። የወህኒ ቤቱ አስተዳደር ዋራንቱን ካለው መዝገብ ጋር ካመሳከረ በኋላ የተጠራውን እስረኛ ከነጋቢው ያስረክባል። ተረካቢውም ለመተንፈስ በሚያስቸግር የአየር እጥረት ባለበት ድፍን መኪና ጭኖ ይወስዳል። የተጠራው ግለሰብ እድል ቀንቶት ከተፈታ እሁድ ከውጪ መጥቶ ጓደኞቹን ይጠይቃል። ለተጨማሪ ምርመራ የተወሰደው ወይ ይመለሳል አለበለዚያም በዚያው ቀልጦ ይቀራል። አንዳንድ ጊዜ ለተጨማሪ ምርመራ የተወሰደው በዚያው ቀልጦ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ ሲባል ከርሞ ሊመለስ ይችላል። ለቺቺ የተዳረገው አለቀለት ማለት ነበር።

በከርቸሌ፣ በማዕከላዊና በደርግ ጽ/ቤት መካከል የእስረኞች መመላለስ ፈጣን በሆነበት ጊዜ በጋቢና ዋራንት ተጠርተው የተመቱ እስረኞች ዜና ወዲያው ይደርሳል። አንዳንድ ጊዜ ከተለያዩ እስር ቤቶች አንድ ላይ አጠራቅመው የገደሏቸው እስረኞች ዜና ጭምር ይደርሳል። አንዳንድ በግል በጋቢና ዋራንት ተጠርተው የተገደሉ ግለሰቦች በተለይም ያለአባሪ (ጓደኛ) የታሰሩ እስረኞች ከሆኑ የተወሰደባቸውን «እርምጃ» (31) ለመስማትም ሆነ ለማወቅ ያስቸግራል። በዚህ የተነሳ ከከርቸሌ በጋቢና ዋራንት ተጠርተው የተገደሉትን በሙሉ እዚህ ላይ መዘርዘር አይቻልም። አንዳንድ ጊዜ ደርግም እርምጃ የወሰደባቸውን ግለሰቦች ስም ዝርዝር በመገናኛ ብዙሐን ያስታውቅ ነበር። ለምሳሌ ብርሃነ መስቀል ረዳ በ1971 ዓ.ም. በሐምሌ ወር ሲገደል የኢትዮጵያ ሬዲዮና ሌሎች የመገናኛ ብዙሐን ስለ ብርሃነ መስቀል ረዳ ሰፋ ያለ መግለጫ አውጥተዋል። ከነብርሃነ መስቀል ረዳ በኋላ ኃይሌ ፊዳና ሌሎች የመኢሶን አመራር አባላት እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

በ1971 ዓ.ም. የከፍተኛ እስረኞች መጀመሪያ ከርቸሌ መሰባሰብ እንደጀመሩ አንድ አስደንጋጭ የጋቢና ዋራንት ጥሪ ተካሂዷል። በምዕራፍ አምስት እንደተጠቀሰው በዚህ ጊዜ ከአንዳንድ ከፍተኞች ከመጡት እስረኞች መካከል በጋቢና ዋራንት ተጠርተው ሲገደሉ፣ ሌሎች ጓደኞቻቸው ደግሞ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የ20 ዓመት እስራት ተፈረደባቸው። ለምሳሌ ከከፍተኛ

22 ከመጣነው መካከል ደሳለኝ፣ ውብሸትና አለማየሁ ከተገደሉት መካከል ነበሩ:: እንግዲህ የቀይ ሽብር ቆሟል እየተባለ ከሚወራለት ከ1971 ዓ.ም. ጀምሮ በጋቢና ዋራንት የተገደሉትን አጠቃላይ ቁጥር ማወቅ ቢያስቸግርም የሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንደ መረጃ እንዲያገለግል ቀርቧል::

ከ1971-1979 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋ፣ በከምባታና ሐዲያና በሌሎች ቦታዎች የተገደሉ እስረኞች ብዛት (32)

የእስረኛው ዓይነት	የተገደሉት ብዛት
የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች	133
የኢዴህ አባላትና ደጋፊዎች	2
የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች	5
የጀበሐ አባላትና ደጋፊዎች	11
የሻዕቢያ አባላትና ደጋፊዎች	23
የኢፒዲኤ አባላትና ደጋፊዎች	5
የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች	7
የወዝ አባላትና ደጋፊዎች	12
ድብልቅ (ኢሕአፓና ወያኔ)	23
ድብልቅ (ኢሕአፓ፣ ኢፒዲኤና ወያኔ)	7
ድብልቅ (ጀበሐና ሻዕቢያ)	26
ድብልቅ (ኦነግና ወያኔ)	30
የኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች	9
የሃይማኖት መሪዎች	2
ሌሎች «ፀረ አብዮተኛ» ግለሰቦች	33
ጠቅላላ ድምር	328

በዚህ ሰንጠረዥ መሰረት ከ1971 ዓ.ም. እስከ 1979 ዓ.ም. ድረስ 328 የተለያዩ ድርጅቶች አባላትና ሌሎች «ፀረ አብዮተኛ» የተባሉ ግለሰቦች ተገድለዋል:: ይህ አሃዝ በደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ላይ ተገድለዋል ተብለው ከተጠቀሱት መካከል በመቶ ሲሰላ 15% ይሆናል:: ከእነኝህ 328 ሰዎች መካከል ግማሹን የሚይዙት የኢሕአፓ አባላትና ደገፊዎች ነበሩ:: ለማስታወስም እንዲረዳ የስም ዝርዝራቸው ዝቅ ብሎ ተካቷል:: እነኝህ የኢሕአፓ አባላት የተገደሉት ከ1971 ዓ.ም. በኋላ ይሁን እንጅ አብዛኞቹ የታሰሩት ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የአዲስ አበባ ከፍተኞችና በሌላም ቦታዎች ነበር:: በነሱ ላይ የተፈጸመው ግድያ የቀይ ሽብር ቀጥያ እንደነበርና ደርግም በ1969 ዓ.ም የጀመረውን እስኪወድቅ እንዳላቆመ ያመለክታል::

ከ1971- 1979 ዓ.ም. የተገደሉ የኢሕአፓ አባላትና ደገፊዎች ስም ዝርዝር (33)

ሀ. የስም ዝርዝር

1. መኮንን ለማ
2. ሰለሞን እጅጉ
3. ስይፈ መንግሥቱ
4. ሰይፈ ወርቅነህ
5. ሱራፌል ካባ
6. ሲሳይ አድማሱ
7. ስዩም በቀለ
8. በቀዬ ፀጋዬ
9. ቢራራ ዮናስ

10. ተረፈ ቶላ
11. ተስፋዬ ለገሰ
12. ተስፋዬ ስዩም
13. ተስፋዬ ሸኝ
14. ቶሾመ ብርሃኑ
15. ታምራት ወ/አማኑኤል
16. ታደሰ ብስራት
17. ትዕዛዙ ብርሃኑ
18. ነብዩ ተፈራ
19. አህመድ መሐመድ
20. አለማየሁ ለማ(በከፍተኛ 22 የታሰረ)
21. አለማየሁ ዘለቀ (በከፍተኛ 20 የታሰረ)
22. አስጨናቂ ብርሃኑ
23. አሸናፊ ጨነቀ
24. ከበደ ሀብቴ
25. ውብሸት አለማየሁ
26. ዑመር መሐመድ
27. ደረጀ ካሣ
28. ደሳለኝ በረጅ
29. ጉልላት ንጉሤ
30. ጋሹ ተሾመ
31. ግርማ ሙላት
32. ግርማ ታደሰ
33. ግርማ ዱባለ
34. ጎይቶም ለባሲ
35. ጤናዬ ተስፋዬ
36. ጤናዬ አለሙ
37. ጥልሁን ካሣ
38. ፍቃዱ ሩጋ
39. ፍቅሩ ወልደማርያም

ለ. የስም ዝርዝር

1. ሀብተሥላሴ ይባስ
2. መኮንን ባይሳ
3. መዝገቡ ከበደ
4. ሙሂዲን ኡመር
5. ሚሮን አሰፋ
6. ሲራክ ተፈራ
7. ባዩ ስዩም
8. ቲቶ ሀሩይ
9. አለማየሁ እግዜሩ
10. ገበየሁ ዳኘው
11. ፍቅሬ ዘርጋው

ሐ. የስም ዝርዝር

1. ሁሴን ኢላላ

2. መሐመድ አህመድ
3. ሙስነህ ፋላስ
4. መ/አ ሙሉጌታ አብርሃ
5. ስለሞን ሺፈራው
6. ተዘራ መኮንን
7. አላዊ አብዱል አህመድ
8. አሸናፊ ግዛው
9. አብዲ ሳና
10. አድማሱ ኃይሌ
11. ይጥና አሸቱ
12. ዲሳሳ ባልቻ
13. ወ/ር ጌታቸው በላቸው
14. ጌታቸው ተ/ማርያም
15. ግርማ አዱኛ

መ. የስም ዝርዝር

1. ተ/ወ ለገሰ ገብረ እግዚአብሔር
2. ተ/ወ ሙላቱ መላኩ
3. ተ/ወ ምህረት አለባቸው
4. ተ/ወ አበራ ባህሩ

ሠ. የስም ዝርዝር

1. ሉሉ ደምሴ
2. መኮንን አዳነ
3. ማቴዎስ ጡመሮ
4. ምንዳ ገ/ሚካኤል
5. ሞገስ ግርማ
6. ስንታየሁ
7. በረከት ዮሴፍ
8. ተስፋዬ ዘውዴ
9. ተሸመ ነጋሽ
10. ታደስ ተሸመ
11. ነጋ ፀደቀ
12. አበበ በዕሐ
13. አቤ ንጉሴ
14. አብዲ አድማስ
15. አባይነህ ንጉሴ
16. አሰፋ በቀለ
17. አስራት አለሙ
18. አስታጥቄ ፈለቀ
19. አስናቀ ካሣ
20. አስጨናቂ ቸኮል
21. አስጨናቂ አብጠው
22. አክሊሉ ፈለቀ
23. አክሊሉ ደቦጭ
24. አድማሱ ወንድሙ

25. አድማሱ ዘውዴ
26. አየልኝ ቢረዳ
27. አንድርያስ ማሴቦ
28. ካሡ ታምሩ
29. ደመቀ ቦጋለ
30. ዶፊ
31. ወርዶ ኤርሳሞ
32. ዮሐንስ ኤርቾ
33. ዮሴፍ ገበየሁ
34. ፋንታሁን መዘምር
35. ፍቅሬ ለገሰ

ረ. የስም ዝርዝር
1. ሙኸዲን ከማል
2. ሰለሞን ግርማ
3. ሱሊማን መሐመድ
4. ተስፋዬ ገብረ ማርያም
5. ተሻለ ውንድሙ
6. ቴዎድሮስ አስፋው
7. ንጉሤ እውነቱ
8. አለም (አለሙ) ኪዳኔ?
9. አምሃ ጌታነህ
10. አስናቀ ጌታቸው
11. አስፋው ረጋሳ
12. ከበረ ኃይሌ
13. ዮሐንስ ግርማቸው
14. ጌታቸው አሰፋ
15. ጌታቸው ኩምሳ
16. ዘሪሁን በንቲ
17. ዘውዱ ኃይለሚካኤል

ሰ. የኢሕአፓ አንጃ አባላት የስም ዝርዝር
1. መልዕክተ ዮሐንስ
2. መሥፍን አጎናፍር
3. መክብብ ክንፈ
4. መክብብ ተሰማ
5. ሚፍታህ ሸሪፍ
6. ሰይፉ ከበደ
7. ብርሃነ መስቀል ረዳ
8. ተስፋሁን መንግሥቱ
9. አለበል ድንቁ
10. ዳኘ አቡዬ
11. ጌታቸው ስዩም

ሸ. ሌሎች 30 የኢሕአፓና የሌሎች ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች አንድ ላይ ተደባልቀው ተገድለዋል::

ደርግ ሥልጣን ላይ እንደወጣ ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. 59 የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖችንና ሌሎችን በፖለቲካ ውሳኔ መግደሉ ይታወቃል:: በተጨማሪ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእስር ላይ ከቆዩት ሌሎች የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች መካከል 9 ሰዎችን በ1971 ዓ.ም. ገድሏል::

ከፍ ብሎ የቀረበው አሃዛዊ መረጃ በምንም መልኩ ደርግ ከ1971 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም. እስከወደቀ ድረስ የገደለውን የሚያጠቃልል አይደለም:: ግድያውም የተካሄደው በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻም አልነበረም:: ደርግ በወታደሩ ክፍል የተከሰተውን ተቃውሞ፣ በትጥቅ ትግል ያጋጠመውን ሽንፈት፣ በአገሪቷ የተንሰራፋውን ሙስናና የኤኮኖሚ አሻጥር፣ በአጠቃላይ በህብረተሰቡ የነበረውን ተቃውሞና ምሬት የሚያፍንበትና አልሁን የሚወጣበት በመግደል ነበር:: ስለዚህ ከሥልጣን እስከተወገደበት እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ድረስ የተለያዩ ግድያዎችን በተለያዩ ቦታዎች አካሂዷል:: በተለይም በመጨረሻዎቹ የሥልጣን ዘመኑ የተፈጠረው ውጥረት የሚይዘውንና የሚጨብጠውን ሰላሳጣው የትግራይና የኤርትራ ተወላጆችን የወያኔ/ኢሕአዴግና የሻዕቢያ ደጋፊ ናችሁ፣ ወታደራዊ ሚስጥር ታቀብላላችሁ፣ በገንዘብ ትረዳላችሁ፣ ወዘተ. በማለት ብዙዎችን ረሽኗል:: ስለዚህ ከ1971-1979 ዓ.ም. በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋ፣ በከምባታና ሐዲያና በሌሎች ቦታዎች የተገደሉት እስረኞች ቁጥር የሚያመለክተው ቀይ ሽብር ከ1971 ዓ.ም. በኋላ መቀጠሉን እንጅ በጠቅላላው የተገደሉትን አለመሆኑን መታወቅ አለበት:: ደርግ በቀይ ሽብር የገደለውን ሰዎች ቁጥር ማረጋገጥ የሚቻለው በሩዋንዳና በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው በአገር አቀፍ ደረጃ ምዝገባ በማካሄድ እንጅ በሌላ መልክ ሊታወቅ አይችልም::

የደርግ ባለሥልጣኖችና ተከታዮቻቸው በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ያደረሱትን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያጣራው የልዩ ዐቃቢ ህግ ጽ/ቤት ሥራውን ወደፊት ሲያጠቃልል በደርግ የተገደሉና የተሰቃዩ የሚባሉትን ሰዎች ብዛት ያቀርባል ተብሎ ይጠበቃል:: ያም ቢሆን አንድ መቶ ሺህ ሰዎች በቀይ ሽብር ተገድለዋል በሚባልበት አገር የመረጃ እጥረትና ክፍተት ስለሚያጋጥም አውነተኛውን አሃዛዊ መረጃ ለማግኘት ያዳግታል:: ይህም ጥቅምት 1987 ዓ.ም. በተዘጋጀው የደርግ የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ቻርጅ ላይ ይንፀባርቃል (34):: ስለዚህ እንኝህን ሁሉ ክፍተቶች ለማሟላት ደርግ ሥልጣን ላይ በቆየበት ጊዜ የቀይ ሽብር የግድያ ሰለባ የነበሩትን ሰዎች ቁጥር ለማወቅ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሰፊ አገር አቀፍ ምዝገባ ማካሄድ የግድ ያስፈልጋል:: ይህንን ለማስፈፀምና ለማጣራት የሚችሉት ሁሉም ይገባኛል የሚሉት በጊዜው የነበሩት ድርጅቶችና ተጎጅ ግለሰቦችና ቤተዘመዶች ተሳትፎ እንጅ ባጋጣሚ ሥልጣን ላይ በወጡት ብቻ አይደለም:: እንዲያውም በአንድ ወገን የተከናወነ ድርጊት በሌሎች በጥርጣሬ ሊታይ ይችላል::

ስለ ደርግ የቀይ ሽብር ድርጊት አንድ ማጠቃለያ ማስቀመጥ ይቻላል:: ቀይ ሽብር የተጀመረው ተቀዋሚዎችን ለማዳከምና ኢሕአፓን ለመምታት ታስቦ ቢሆንም በሂደት ህዝብን ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት እንዲያመች የደርግ የአስተዳደር መሣሪያ ሆኗል:: ስለዚህ ደርግ ቀይ ሽብርን ከጀመረ አንስቶ ቀይ ሽብርን ከደርግ፣ ደርግን ከቀይ ሽብር መለያየት አይቻልም፣ ተለያይተውም አያውቁም:: ይህም ደርግ ያካሄደውን ግድያ ቀይ ሽብር የሚል ስያሜ ከሰጠው ጀምሮ ለማለት እንጅ ከዚያ በፊት ግድያ አልነበረም ለማለት አይደለም::

በ1971 ዓ.ም. በቀይ ሽብር ከተመቱት የኢሕአፓ እስረኞች በተጨማሪ ከከፍተኛ 2፣ 3፣ 12፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22 እና 23 ከርቸሌ

በተሰባሰቡትና ማዕከላዊም በነበሩት እስረኞች ላይ የፍርድ ውሳኔ ተላልፏል:: በዚህ የተነሳ በዛ ያሉ እስረኞች በጊዜው ማን ይፍረደው የማይታወቅ ከአንድ እስከ 20 ዓመት ፍርድ ተከናንበዋል:: ምናልባትም ይህንን የቀይ ሽብርና የፍርድ ውሳኔ የሰጡት ከዚህ በፊት የተጠቀሱት ከሰደድ የድርጅት አባላት የተወጣጡትና በዶ/ር አለሙ አበበ ሊቀመንበርነት የተሰባሰቡት የከተማ ነዋሪዎች የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም:: በተጨማሪም ቁጥራቸው አነስተኛ ይሁን እንጅ ከደርግ ጽ/ቤት፣ ከማዕከላዊና ከሌላም ቦታ የመጡ የተፈረደባቸው የፖለቲካ እስረኞች ነበሩ::

በጊዜው በአንዳንዶች ላይ የተቀለለው ከባድ ፍርድ የሚያስደነግጥ ቢሆንም በደርግ ምስቅልቅል የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ እድሮ ምን እንደሚፈጠር ስለማይታወቅ ከመሞት መሰንበት የአንድም ቀን መኖር እድሜ ስለሆነ ከባድ ፍርድ የተፈረደባቸው ለሞቱት ጓደኞቻቸው ከማዘን በስተቀር ለፍርዱ ቁብም አልነበራቸው:: ከ10-20 ዓመት ከባድ ፍርድ ከተጣለባቸው መካከል 3 ሴቶችና ከ51 በላይ ወንዶች ይገኙባቸው ነበር:: ዝርዝሩን ቀጥሎ የቀረበው ሰንጠረዥ ያመለክታል::

<u>ከ10-20 ዓመት የተፈረደባቸው የኢሕአፓ እስረኞች ብዛት(35)</u>

የታሰሩበት ከፍተኛ	የእስረኛ ብዛት	ማብራሪያ
ከፍተኛ 2	2	
ከፍተኛ 3	5	አንዲት ሴት
ከፍተኛ 12	12	
ከፍተኛ 16	1	
ከፍተኛ 17	8	
ከፍተኛ 18	6	
ከፍተኛ 19	6	ሁለት ሴቶች
ከፍተኛ 20	2	
ከፍተኛ 21	10	
ከፍተኛ 22	2	
ጠቅላላ ድምር	54	

ምንም እንኳን ግድያውም ሆነ ፍርድ አሰጣጡ በዚህ ጊዜም በኢሕአፓ ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም የሌሎች ድርጅቶች እስረኞች ሙሉ በሙሉ አምልጠው ነበር ማለት አይቻልም:: በዚህ የተነሳ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አባላት እስረኞች ሲገደሉ ወይም ሲፈረድባቸው ሌሎችን ያስደስታል ማለት አይቻልም:: የሁሉም እጣ ፋንታ ስለማይታወቅ ከመታሰራቸው በፊት የቀይ ሽብር አራማጆች የነበሩትን እንኳን ድርጊቱ እንደበፊቱ አያስፈነድቃቸውም ነበር:: እንዲያውም የመኢሶን፣ የወዝ ሊግና የሌሎች ድርጅቶች አመራር አባላት መገደል ለተከታዮቻቸውም እንደ ማስጠንቀቂያ ደወል ያቃጭል ነበር:: የደርግ በትር በኢሕአፓ ላይ ቢበረታም ሌሎችንም የሚሸነቁጥ፣ ወዳጅም ጠላትም የማይመርጥ መሆኑን በእስር ላይ የነበሩት በሙሉ ተገንዝበውታል:: ከፍ ብሎ የቀረበው ሰንጠረዥም ይህንኑ ያረጋግጣል::

የደርግ አሰሩም ሆነ አሰራሩ ዝብርቅርቅ ነበር:: ከእስረኞችም መብዛት ይሁን ወይም ከአሰራር ጉድለት ባይታወቅም አንዳንድ እስረኞችን የትኛው እስር ቤት እንዳስቀመጣቸው እንኳን የሚያውቅ አልነበረም:: አንድ የሚፈለግ እስረኛ የታሰረበት ቦታ ሲጠፋ መርማሪዎች ከርቸሌ መጥተው ጋቢና ዋሬንት ጥሪ

ያካሂዳሉ:: ችግሩ ከአሰራር ጉድለት ብቻ ሳይሆን ከእስር ቤቶችና የማቆያ ስፍራዎች መብዛት ማን የት እንደታሰረ ካለማወቅ የተነሳ ሊሆን ይችላል::

ለምሳሌ በ1971 ዓ.ም. መጨረሻ ፍቅሬ ዘርጋውን ከርቸሌ በጋቢና ዋራንት ጥሪ በየክልሉ እየተዘዋወሩ ይፈልጉታል:: በዚህ ጊዜ በቀጠሮ ክልል ጥሪ ሲያካሂዱ እስረኛው ቆሞ ሲያዳምጥ ፍቅሬ ዘርጋውን ከሚፈልጉት የደርግ ሰዎች መካከል አንዱ አንድ እስረኛ እየተመለከተ የምንፈልገው እስረኛ ይህ መሆን አለበት፣ የፍየል ጺም የምትመስለው ጺሙም መልኩም እሱን ይመስላል ብሎ ሙጭጭ በሚልበት ጊዜ የተባለው ግለሰብ ሌላ እስረኛ መሆኑን ቢያስረዱትም ብዙም ሳይደሰት እየተጠራጠረ ሊሄድ ቻለ::

የፍቅሬ ዘርጋውን በከርቸሌ አለመኖር የሚያውቁ እስረኞች የዚያን ቀን ጥሪ በጣም ደንቋቸዋል:: ከርቸሌ ከቆዩ እስረኞችም ይህን መሰል አጋጣሚ ከዚህ በፊት ተፈጥሮ እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል:: አንድ ጊዜ እንደዚሁ የደርግ ሰዎች መጥተው ጋቢና ዋራንት ከተጠራ በኋላ የሚፈልጉት ሰው ስለጠፋ ፍለጋ ይካሄዳል:: በመካከሉ አንድን የደረቀ ወንጀል እስረኛ አፈፍ አድርገው አንተ ነህ በሚል ሊወስዱት ሲሉ «□ረ እኔ የፖሊቲካ እስረኛ አይደለሁም፣ ማንም የሚያውቀኝ ጌታቸው (?) ዜንጦ የምባል የታወቅሁ ሌባ ነኝ» ብሎ በመማፀን አስተዳደሩ ድረስ ደርሶ ዋራንቱ ተመርምሮ በኃይል ከመወሰድና ከመረሸን ድኗል:: የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል የነበረው ፍቀሬ ዘርጋው የተገደለው በዚሁ ጊዜ ነበር::

የተፈረደባቸው የፖለቲካ እስረኞች ፍርዳቸውን ሲጨርሱ እንደ ማንኛውም የፍርድ እስረኛ በወህኒ ቤቱ አማካኝነት ይፈታሉ:: ከዚህ ውጪ ፍርድ የተሰጣቸው የፖለቲካ እስረኞች ወህኒ ቤት እስካሉ ድረስ ምንም ልዩነት አልነበራቸውም:: እንደ ሌሎች ሁሉ በጋቢና ዋራንት ሊጠሩ፣ ለተጨማሪ ምርመራና ለግድያም ሊዳረጉ ይችላሉ:: በዚህ የተነሳ ፍርድ ከተሰጣቸው የፖለቲካ እስረኞች መካከል አንዳንዶች ማዕከላዊ እየተጠሩ ሰንብተው የሚመለሱበት ጊዜ ነበር:: ማዕከላዊ ለምርመራ የሚያስጠሯቸው በአፍላ የቀይ ሽብር ጊዜ ተሸሽገው ከቆዩ በኋላ እጃቸውን ሰጥተው የሚታሰሩ ግለሰቦች ነበሩ:: የዚህ ዓይነቱ የምርመራ ጥሪ መዘዙ ብዙ ነበር:: የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ በ1972 ዓ.ም. በጋቢና ዋራንት ተጠርቶ ማዕከላዊ ሦስት ቀን አድሮ ተመልሷል:: ማዕከላዊ ያስጠራው ድብረ ዘይት ይገናኘው የነበረ በአፍላ የቀይ ሽብር ጊዜ ተሸሽጎ ቀይቶ እጁን ሰጥቶ ስለታሰረ ነበር:: ይህ በአሁን ጊዜ የታሰረ ግለሰብ ምርመራውን ማእከላዊ ሲጨርስ ከርቸሌ ተልኮ በመጨረሻ ሊፈታ ችሏል::

የማዕከላዊ እስር ቤት እንደ ዓለም በቃኝ ቀና ቢሉ ሰማይ ብቻ የሚታይበት የላይና የታች ሁለት ክንፍ እስር ቤቶች ነበሩት:: የላይና የታች ክንፍ እስር ቤቶች በሚገናኙበት አካባቢ እስረኞች ቀን ለጥቂት ጊዜ የሚናፈሱበት ቦታ ነበረው:: የሁለቱም ክንፍ እስር ቤቶች የመግቢያ በሮች ዋርድያ በሚቆሙባቸው ዘበኞች በጥብቅ ይጠበቁ ነበር:: የሁለቱም ክንፍ እስር ቤቶች በሁለት ረድፍ የተሰሩ ጠባብ የእስር ክፍሎች ነበሯቸው:: በሁለቱ ረድፍ ክፍሎች መካከል ጠባብ የእስረኛ መተላለፊያ «ኮሪዶር» ይገኛል:: ዋርድያ ካለበት የመግቢያ በር በተቃራኒ ሽንት ቤት ይገኛል:: የእስር ክፍሎቹ ከመግቢያው በር ጀምሮ እስከ ሽንት ቤቱ ድረስ ማዶ ለማዶ የሚተያዩ ጠባብ ክፍሎች ነበሩ:: እያንዳንዳቸው ከ3x4 ሜትር የማይበልጡ ከአስር ሰዎች በላይ ተጠጋግቶ የማያስተኙ ቢሆኑም እስረኛ ሲበዛ ከዚያም በላይ ይጠቀጠቅባቸው ነበር::

የታችኛው የማዕከላዊ እስር ቤት ከተለመደው ዓይነት ክፍሎች ሌላ ለአንድ ሰው ማሰሪያ ብቻ የሚያገለግሉ «ጨለማ ቤት» የሚባሉ ክፍሎች ነበሩት:: ይህ ክንፍ በኋላ ስለተሰራ ለጥበቃም አመቺ እንዲሆን እንደ ዓለም በቃኝ በላዩ ላይ ጠባቂዎች ዙሪያውን ይዘዋወሩበታል:: በ1969 ዓ.ም. አካባቢ የላይኛው የማዕከላዊ እስር ቤት ብቻ በመኖሩ በእያንዳንዱ ክፍል እስከ 50 ሰዎች ይታሰሩበት ነበር:: እስረኛም በጣም ሲበዛ በጠባቂዎች ፍቃድ አንዳንድ ጉዳያቸው ቀላል መሆኑ የሚታወቅ እስረኞች ከቤት ወጥተው «ኮሪደር» ላይ እንዲተኙ የሚፈቀድበትም ጊዜ ነበር:: ሆኖም አንድ የማዕከላዊ መርማሪ መጥቶ በየክፍሉ አስገብተህ ዝጋልኝ ካለ እስረኛው እየተጣበበ ለመተኛት ወይም ቆሞ ለማደር ይገደዳል::

እንደ ደርግ ጽ/ቤት፣ ቤርሙዳ፣ የፖሊስና ወታደራዊ ካምፖችና ሌሎች የጊዜው ድብቅ እስር ቤቶች የፖለቲካ እስረኞች መጀመሪያ የሚታሰሩት ወይም ከባድ እስረኞች ተብለው የሚጠረጠሩት የሚታሰሩትና እርምጃም የሚወሰድባቸው ከማዕከላዊ ተወስደው ነበር:: በተለይም ቀይ ሽብር በየቀበሌውና በየከፍተኛው ከመጀመሩ በፊት አብዛኛው የኢሕአፓ እስረኞች የሚታሰሩትና እርምጃም ይወሰድባቸው የነበረው ከማዕከላዊ እየወጡ ነበር:: (36) ስሙም እንደሚያመለክተው ማዕከላዊ ዋናው የፖለቲካ እስረኞች ፍዳ ማሳያ ቦታ ነበር::

ባቢሌ ቶላ «አንድ ትውልድ ለመምተር፣ ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፉ እንደጠቀሰው በ19/6/69 በአንድ ምሽት ብቻ 45 ሰዎች ለግድያ ከማዕከላዊ ተወስደው ብዙዎች ሲረሸኑ አንዳንዶች የታሰሩ እጆቻቸውን በመፍታት ከመኪና ዘለው ለማምለጥ ችለዋል:: (37) በዚያን ቀን ከግድያ ካመለጡት መካከል በላይነህ ገብረማርያም፣ ደምሰው ብዙወርቅ፣ ፍቅሩ ዮሴፍ፣ በቀለ መርኔ፣ ካሡ ኩማ፣ ኃይሉ ገብረ እግዚአብሔርና ሌሎችም የድርጊቱ ምስክር ነበሩ::

ማዕከላዊ ከታሰሩበት ቤት የእንዳንዳቸው ስም እየተጠራና እጆቻቸውን በገመድ እየታሰሩ ወደሚገደሉበት ስፍራ በመኪና ተጭነው ሲወሰዱ ብዙዎች ይዘምሩና መፈክር ያሰሙ ነበር:: በዚህ ጊዜ አንዳንዶች በጥርሳቸው የጓደኞቻቸውንና የራሳቸውንም እጆች በመፍታት በጅፕና በሌሎች መኪናዎች የሚያጅቧቸው የደርግ ወታደሮች ሳያዩዋቸው ከመኪና እየዘለሉ ሲያመልጡ አንዳንዶቹም ተገደሉ:: የዚህ ነፍስ አድን የማምለጥ ሁኔታ እንዴት እንደነበር ዝርዝር ታሪኩን አንዳንድ ፀሐፊዎች ለማቅረብ ሞክረዋል:: (38) በዚያን ጊዜ ከሞት ካመለጡት መካከል በላይነህ ገብረማርያም በሌላ ጊዜ በድጋሚ ተይዞ መስዋዕት ሲሆን በቀለ መርኔም በቅርብ ጊዜ ሕይወቱ አልፏል::

በ1972 ዓ.ም. በማዕከላዊ ታስረው ከነበሩት እስረኞች መካከል የኢሕአፓ፣ የኦነግ፣ የማልሬድና የኢጭአት አባላትና ሌሎችም ይገኙባቸው ነበር:: በልዩ ልዩ ከፍተኞች ታስረው ቆይተው ወደ ማዕከላዊ ከተዛወሩት የኢሕአፓ እስረኞች መካከል የከፍተኛ 7፣ 8፣ 13፣ 14፣ 15 እና ሌሎችም በኋላ ከርቸሌ ተጠቃለው የተላኩት እስረኞች ይገኙበታል:: ከግለሰብ እስረኞች መካከል ቀኛዝማች ታዬ መሸሻ «ጨለማ ቤት» ውስጥ ብቻውን ታስሮ በ1973 ዓ.ም. ተገድሏል::(39) ይህ እስረኛ ከውጪ ጠያቂ በብዛት የሚያመጣለትን ምግብ ለሌሎች በማካፈል፣ ለሰዎች ባለው ርህራሄና ሐዘኔታ በማዕከላዊ እስረኞች በሞላ ተወዳጅ ነበር:: በማዕከላዊ በጊዜው የውጪ ዜጎችም ታስረው እንደነበር

ይታወቃል። ከእነኝህ መካከል የዚያድ ባሬ ተቃዋሚዎች የነበሩት አሁን በሰሜን ሱማሊያ በሐርጌሳ የራሳቸውን መንግሥት የመሰረቱት ባለሥልጣኖች እነ ኮለኔል አብዱላሂ የሚታወሱ ናቸው። ደርግ አንዳንድ የዚያድ ባሬን ተቃዋሚዎች በመደገፍና ሌሎችን በማግለል ነበር እነኝህን የሱማሌ መድህን ግንባር (Somalia Salivation Front) አባላት በዚያን ጊዜ ያሰራቸው።

በማዕከላዊ የነበሩት የሱማሊያ እስረኞች ያለ አግባብ ያለ ምግብ መታሰራቸውን በመቃወም ደርግ እንዲፈታቸው ወይም ምግብ እንዲያቀርብላቸው ለማስገደድ የርሃብ አድማ መተው ነበር። በዓለም ላይ ለሰዎች የመኖር ህልውና አስፈላጊ የሆነውን ምግብ ሳያቀርብ የሚያስር መንግሥት ካለ የደርግ መንግሥት ብቻ መሆኑን በመግለጽ በአድማው ማዕከላዊን አፋጠውታል። ከኢትዮጵያውያን የእስር ጓደኞቻቸው የሚሰጣቸውን ምግብ አንበላም የእስረን መንግሥት ምግብ ያቅርብልን በማለት ያካሄዱት የርሃብ አድማ በጊዜው ውጤታማ ሆኖ ሊፈቱ ችለዋል።

5. የግድያ ጥሪ በሌሎች እስር ቤቶች

የጋቢና ዋራንት ጥሪ የሚታወቀው በከርቸሌ እስር ቤት እንጅ በሌሎች እስር ቤቶች አልነበረም። በሌሎች እስር ቤቶች የእስረኞች መለያ ወረቀት የነበረው ዋራንት ስለማይሰራበት የስም ጥሪው የሚካሄደው የእስረኞች ማደሪያ ቤቶች ከተዘጉ በኋላ ነበር። ይህም በመሆኑ አሳሪዎችና መርማሪዎች በአካባቢው ሲታዩና የእስር ክፍሎችም ሲዘጉ ሁሉም እስረኛ እርጭ ብሎ ለግድያ መጠራቱን ይጠባበቅ ከስሜቱም ጋር ይሟገት ነበር። ጥሪው የሚካሄደው ብዙ ጊዜ ወደ ማታ ሲሆን በከርቸሌ ግን በማንኛውም ሰዓት ነበር። አንዳንድ ጊዜ በከርቸሌም የሌለ እስረኛ በጋቢና ዋራንት ሊጠራ እንደሚችል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሌላ ቦታ ተገልጿል፡ በሌሎች እስር ቤቶችም እንደዚሁ በከርቸሌ ያለ እስረኛ ሊጠራ ይችላል።

ከርቸሌ ለግድያ የሚጠሩት እስረኞች ከተወሰዱ በኋላ አንድ ማቆያ እስር ቤት አውለዋቸው ማታ በድጋሚ ተጠርተው ከሌሎች ጋር ተደባልቀው ይገደሉም እንደነበር ይታወቃል። የማቆያው ቦታ በማዕከላዊ፣ ደርግ ጽ/ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያ ወይም በሌሎች ስውር እስር ቤቶች ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ከተለያዩ እስር ቤቶች የተጠሩትን አንድ እስር ቤት አጠራቅመው የሚገድሉበት ጊዜም ነበር።

እስረኞች ለግድያ ከተጠሩ በኋላ እስኪገደሉ ድረስ ብዙ ስቃይ ይደርስባቸዋል። ከአንዳንድ እስር ቤቶች ለግድያ የሚወሰዱትን እስረኞች እንደ እንስሳ በገመድ ጠፍረው መኪና ላይ እንደ እቃ እየወረወሩ በመጫን የሚገደሉበት ቦታ ማድረስ የሚዘወተር ድርጊት ነበር። በማዕከላዊ፣ በደርግ ጽ/ቤት፣ በከፍተኛና በሌሎች እስር ቤቶች እስረኞች ለግድያ እንደተጠሩ እጃቸውን ወደኋላ በመስበር እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግና አስቸጋሪ ሆነው የተገኙትንም እዚያው በቦታው አንቆ መግደል የተለመደ ነበር። በተለይም የሚታገሉ፣ የሚሳደቡና መፈክር የሚያሰሙ እስረኞች ለዚህ አሰቃቂ ግድያ ይዳረጉ ነበር። የዚህ ዓይነት የግድያ ተግባር የሚያዘወትሩት ከደርግ ወታደራዊ ክፍል የተመለመሉት ገዳዮች እንደነበሩም ይታወቃል። ጥይት ለምን እናባክናለን በሚል እስረኞችን አንቀው በመግደል እርካታን የሚያገኙ ገዳዮች እንደነበሩ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል።

6. የአንድ አቅጣጫ መንገድ

የእስር ሕይወት እየተለመደ ቢመጣም ጊዜው እየጨመረ ሲሄድ በጣም ያሰለቻል። ለአንዳንዶች ነጋ ጠባ አንድ ዓይነት ሕይወት መምራት፣ ጠዋት ተነስቶ በግቢው ውስጥ መዞር፣ ከጓደኞች ጋር ሆኖ ለዚህ የዳረገ መንግሥትን መራገም፣ ተግራሪ እስረኞችን በዓይን መገርመም፣ ጋቢና ዋራንት ጥሪ መጠበቅ፣ ተመልሶ ዲሪቶ ላይ መጋደም ሁሉም እጅ እጅ የሚል ነበር። ለሌሎች ደግሞ በመማር ማስተማር ጊዜን ማሳለፍ፣ መጽሐፍ ማንበብና መመርመር ቢታከልበትም ይህም ሲበዛ አሰልቺነቱን መገመት አያዳግትም። ለአማኞች ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ሚካኤልን መሳለም፣ መፆምና መፀለይ፣ ሙስሊም ለሆኑት ደግሞ ለሰላት መስጊድ መሄድ የዘወትር ተግባራቸው ነበር። አንዳንድ እስረኞች ውጪ ከነበራቸው ባህርይ በተለይ ሃይማኖታቸውን አጥባቂዎች የሆኑም አይጠፉም። በእስር መለሸቅ የተነሳ ውጪ አካኪ ዘራፍ ሲል የነበረው አብዮተኛ አክራሪ ሃይማኖተኛ ሆኖ ቢገኝ አያስደንቅም። ለዘብተኛ የነበረው ደንፊ ቢሆን፣ ልታይ ልታይ ሲል የነበረው ቢደበቅና ሲደበቅ የነበረው ባህርይ ግልፅ ቢወጣ የውጥረት መግለጫው የተለያየ ስለሆነ ምንም አያስደንቅም ነበር።

እስር ያንገፈገፋቸው የደቡብ ሱዳንና የጋምቤላ ተወላጅ እስረኞች በከርቸሌ አመፅ አካሂደው ነበር። እነኝህ እስረኞች ባካሄዱት አመፅ የወህኒ ቤቱን አስተዳደር የስልክ መገናኛ በመቁረጥ አመራሩን በቁጥጥር ስር ለማዋልና ወደ አፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤት ሾልከው ለማምለጥ ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል። በዚህ ጥፋታቸው ዓለም በቃኝ በቀጣት ላለመግባት የወህኒ ፖሊሶችንም ድብደባ ለመቋቋም በቀጠሮ ሦስተኛ ቤት ነዋሪ የነበሩት ቤቱን ዘግተው ትልቅ ግብግብ አካሂደዋል። በመጨረሻ በዚህ አሳዛኝ ድርጊት ክፉኛ በፖሊስ ተደብድበው ዓለም በቃኝ ለቀጣት ሊገቡ ተገደዋል።

በከርቸሌ የነበሩት የፖለቲካ እስረኞች ውጪ በነበራቸው ተፃራሪ አቋም የተነሳ ባይጣጣሙም በትምህርቱም፣ በስፖርቱም፣ በመኖሪያ ቤቱም በመቆየት ሊለመድና መቻቻል ሊፈጠር ችሏል። ከመሰላቸትም ይሁን ከመላመድ የእስር ጊዜ እየበዛ ሲሄድ ሁሉም ልዩነቶች እየላሉ መጡ። እትንካኝ አልነካህም፣ አትድረስብኝ አልደርስብህም፣ ዓይነት አቋም ተያዘ። አንዳንድ ነገሮች የሰውን ስሜት በጣም የሚፈታተኑ ቢሆንም እየተለመዱ መጡ። ለምሳሌ ከፍተኛ በእስር በቆዩበት ጊዜ መርማሪ ሆኖ የገረፈን ግለሰብ ቆሞ ማስተማር ትዕግስትን ይፈታተናል። ይህን መሰል ትያትር ያጋጠማቸው በሳል አስተማሪዎች ምንም ሳይሰማቸው ለማስተማር ቢችሉም አንዳንድ ተማሪዎች በሰሩት ድርጊት በመሸማቀቅ ትምህርት ያቋረጡ አልጠፉም ነበር። እየቆየና እየተለመደ ሲሄድ በዚህ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡትም ተመልሰው ገብተው ሊማሩ ችለዋል።

በመቆየት ከቤት መኖሪያ ጀምሮ ሁሉም የሚታወቅበት መለያ ተበጀ። በቀጠሮ የእስር ክልል አብዛኛው የኢሕአፓ እስረኞች በየቤቱ ከወንጀል እስረኞች ጋር ተሰባጥረው ሲኖሩ ሦስተኛ ቤት በአመዛኙ የመኢሶንና የሌሎች በደርግ ዙሪያ የነበሩ እስረኞች የሚኖሩበት ቤት በመሆን ይታወቅ ነበር። በፍርድ ክልል የሚበዙት የወንጀልና ከእነሱም ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩት የኢሕአፓና ሌሎች ቅይጥ እስረኞች ሲሆኑ በዚሁ እስከ መጨረሻው ዘልቋል። የፍትሐብሔርን

ይመርጡት ነበር:: ከእነሱም
ክልል በአብዛኛው «የኤኮኖሚ አሻጥር እስረኞች» ያዘወትሩታል::
ጋር የቅርብ ግኑኝነት ያላቸው በደርግ ዙሪያ የነበሩ እስረኞች ዘልቋል::
ዓለም በቃኝ ብዙ ጊዜ አዲስ መጥ እስረኞች የሚታሰሩበት ቦታ ሆኖ በመቆየታቸውም
ከጊዜ በኋል የቆዩት የፖለቲካ እስረኞች እየለቀቁ በከርቸሌ በሚመጡ
ሌሎች ክልሎች እያማረጡ ሲደለደሉ ዓለም በቃኝ ከስሜን
የሻዕቢያና የወያኔ እስረኞች ተሞልቷል::
በዓለም
ከታሰሩበት ጊዜ ጀምሮ በ1980 ዓ.ም. እስከተፈቱበት ድረስ መኮንን፣
በቃኝ የቆዩት የልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴ ልጆች በዕደማርያም ተናኘ
ሚካኤል መኮንንና ወሰንሰገድ መኮንን ነበሩ:: በሴቶች ክልልም ልዕልት ተወላጆች
ወርቅ ኃይለ ሥላሴ፣ ሌሎች የልዑላን ቤተሰቦችና የመሣፍንት ሁኔታ
ታሰረው ቆይተዋል:: የልዑላኖቹንና የመሣፍንቱን ተወላጆች የእስር ካልወጡ
ከሌላው ለየት የሚያደርገው ከአስተዳደሩ ተፈቅዶላቸው በአጃቢ ነበር::
በስተቀር በሌላው ጊዜ ከግቢያቸው መንቃነቅ አይፈቀድላቸውም አይገኙም
በትምህርት ቤት፣ በመጽሐፍት ቤትና በግቢው የመዝናኛ ስፍራ ወዳድ
ነበር:: ወጣቱ ልዑል በዕደማርያም መኮንን ተግባቢና እግር ኳስም
ስለሆነ የግቢውን እግር ኳስ ጨዋታ በዝና ይከታተል ነበር::
ቢለያይ፣
እንግዲህ ይህን ሃሳብ ለመቋጨት የፖለቲካ እስረኛው ምንም ሁሉም
በእስር ቢሰላችና በፖለቲካም ልዩነት የተነሳ የማይመስለውን ቢጠላም በመጥፎም
ለመፈታት አንድ ነገር በጋራ ይጠብቅ ነበር፣ ጋቢና ዋራንት ጥሪን:: ነበር::
ሆነ በጥሩ ጎኑ እስረኛውን አንድ የሚያደርገው ጋቢና ዋራንት ጥሪ አንድ
በዚህ የተነሳ የተለያየውን የአገራችንን የፖለቲካ ምሁር ደርግ አቀራርቦታል::
አድርጎታል፣ የማይታረቀውን ልዩነታቸውን በጋቢ ዋራንት ጥሪ እንደተለመደው
ታዲያ ጋቢና ዋራንት ወደፊት ህብረት ይፈጥር ይሆን? ወይስ
የአንድ አቅጣጫ መንገድ በመከተል ምሁሩ እንደ በፊቱ ይባዝን ይሆን?

7. የጋቢና ዋራንት ጥሪ በመጨረሻው የእስራት ዘመን

በአብዛኛው ለፍቺ እየሆነ መጣ::
እየቆየ ሲሄድ የጋቢና ዋራንት ጥሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በዛ ያሉ
ጥቂት በጥቂት በየጊዜው ከሚለቀቁት እስረኞች ሌላ የደርግ አብዮት
የቆዩ እስረኞች የተፈቱት መስከረም አንድ ቀን 1975 ዓ.ም. የኃይለ ሥላሴ
በዓል ጊዜ ነበር:: ከከርቸሌና ከአራተኛ ክፍለ ጦር የቀድሞ በርከት ያሉ
መንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የመኢሶን አመራሮችና ካድሬዎች፣ የሚደርሱ
የኢሕአፓ እስረኞችና ሌሎችም በጠቅላላው ቁጥራቸው 716
የፖለቲካ እስረኞች በዚህ ጊዜ ተፈቱ:: (40)
ከአራተኛ ክፍለ ጦር ከተለቀቁት መካከል ከወሎ ክፍለ አገር የተያዘው
በእስሩም ጊዜ ከደርግ ጋር ለመመሳሰል ችግር ያልገጠመውና ከርቸሌ ለአጭር
ጊዜ ቆይቶ አራተኛ ክፍለ ጦር ተወስዶ የታሰረው የሸዋ ክፍለ አገር የኢሕአፓ
አመራር አባል የነበረው ከ. መሐመድ አንዱ ተፈቺ ነበር:: ሌሎች የኢሕአፓ
እስረኞች በብዛት የተፈቱት ከከርቸሌ እስር ቤት ነበር:: በዚያን ጊዜ የተፈቱትን
እስረኞች ደርግ ለፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ አድርጓቸዋል:: ደርግ በዓለም አቀፍ
ደረጃ ሰዎችን በቀይ ሽብር በመግደልና በማሰር ይወገዝ ስለነበር ለዚያ
ማስተባበያ መልስ ለመስጠት እነዚህን የቆዩ እስረኞች በብዛት ሊፈታ ቻለ::
በአራተኛ ክፍለ ጦር ለብዙ ጊዜ ታስረው የቆዩት የኃይለ ሥላሴ
ባለሥልጣኖች፣ የመኢሶን አባላት እስረኞችና ሌሎችም ከተፈቱ በኋላ ክፍለ

ጦሩ ማስሪያነቱ ቀርቶ የበፊቱን ወታደራዊ አገልግሎት ብቻ መስጠት ቀጠለ።
በዚህ እስር ቤት ከነበሩት መካከል በፍቺ ያልተካተቱት ጥቂት የመኢሶን አባላት
እስረኞች ወደ ከርቸሌ ተዛወሩ።

ከ1975 ዓ.ም. የአብዮት በዓል ፍቺ በኋላ የከርቸሌ እስረኞች በያመቱ
ጋቢና ዋራንትን አንጋጠው ይጠብቁ ጀመር። እውነትም በመካከል ከሚፈቱት
አነስተኛ እስረኞች በተጨማሪ በየአብዮት በዓሉ የጋቢና ዋራንት ፍቺ
እየተለመደ መጣ። የሚገደሉት እስረኞች ቁጥርም አነስተኛ ይሁን እንጅ ቀይ
ሽብርም ውስጥ ውስጡን በተለይ በአዲስ እስረኞች ላይ መካሄዱ አላቋረጠም
ነበር። በዚህ ዓይነት የቀጠለው የጋቢና ዋራንት ጥሪ በ1977 ዓ.ም. ከባድ
ፍርድ ተፈርዶባቸው ከነበሩት መካከል ለፍቺ ማካተት ጀመረ። በዚህ የተነሳ
በከርቸሌ የቆየው እስረኛ ስሜቱ በሙሉ ወደ ፍቺና ወደ ውጪው ሕይወት
አዘነበለ።

እንዲህ እያለ ቀስ በቀስ የከርቸሌ እስረኞች በጋቢና ዋራንት ጥሪ
እየተፈቱ ቢሄዱም መስከረም 25 ቀን 1978 ዓ.ም. አንድ አስደንጋጭ የጋቢና
ዋራንት ጥሪ ተካሄደ። ከዘጠኝ ዓመት በላይ በእስር የማቀቁ የኢሕአፓ
እስረኞች፣ የጆሆቫ እምነት ተከታዮች፣ አንዳንድ የወያኔ አባላትና የኢትዮጵያ
ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ቃል ኪዳን (ኢፒዴኤ) አባላት በጋቢና ዋራንት
ተጠርተው ተረሸኑ። በዚህ የተነሳ ከርቸሌ እንደ ልማዱ ተረበሸ፣ የጥንቱ
ትዝታ አገረሸ፣ ለመፈታት የነበረው ተስፋ ሟሸሸ። በዚህ ጊዜ በቀይ ሽብር
ከተመቱት መካከል አብዛኞቹ የቆዩ እስረኞች ከከርቸሌ የተወሰዱ ሲሆን ሌሎች
ደግሞ ማዕከላዊ የነበሩ ናቸው። «አንድነት» በሚል የሚታወቀውን የሬድዮ
ፕሮግራም ከካርቱም፣ ሱዳን ሲያስተላልፍ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ
ዴሞክራሲያዊ ቃል ኪዳን (ኢፒዴኤ) አባላት እነ ደጃዝማች አስጋኸኝና
ሌሎችም የተመቱት ከማዕከላዊ ተወስደው ነበር። የዚህ ድርጅት አባላት
ከውጪ አገር ከሚያሰራጩት ፕሮፓጋንዳ ሌላ በ1970ዎቹ አጋማሽ በአዲስ
አባባ ከተማ ፀረ ደርግ ቅስቀሳ ሲያካሂዱ፣ ወረቀት ሲበትኑና ፅጥታ ሲነሱ
መያዛቸውን ደርግ በጊዜው ገልጿል።

በዚህ ጊዜ ከተገደሉት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

የእስረኛው ስም	የፖለቲካ ድርጅት (41)
1. ሙኸዲን ከማል	ኢሕአፓ
2. ሰለሞን ግርማ	ኢሕአፓ
3. ሱሊማን መሐመድ	ኢሕአፓ
4. ተስፋዬ ገብረማርያም	ኢሕአፓ
5. ተሻለ ወንድሙ	ኢሕአፓ
6. ቴዎድሮስ አስፋው	ኢሕአፓ
7. ንጉሤ እውነቱ	ኢሕአፓ
8. አለም (አለሙ) ኪዳኔ	ኢሕአፓ
9. አምሃ ጌታነህ	ኢሕአፓ
10. አስናቀ ጌታቸው	ኢሕአፓ
11. አስፋው ረጋሳ	ኢሕአፓ
12. ከበረ ኃይሌ	ኢሕአፓ
13. ዮሐንስ ግርማቸው	ኢሕአፓ
14. ጌታቸው አሰፋ	ኢሕአፓ
15. ጌታቸው ኩምሳ	ኢሕአፓ

16. ዘሪሁን በንቲ	ኢሕአፓ
17. ዘውዱ ኃ/ሚካኤል	ኢሕአፓ
18. ወልደገብርኤል ለማ	ወያኔ
19. የማነብርሃን ብርሃኔ	ወያኔ
20. ደጃዝማች አሰጋኸኝ አርአያ	ኢ.ፒ.ዴሎ
21. ውቤ ገብረዮሐንስ	ኢ.ፒ.ዴሎ
22. ማህተመወርቅ ካሣሁን	ኢ.ፒ.ዴሎ
23. አክሊሉ መዋኢ.	ኢ.ፒ.ዴሎ
24. ወ/ሮ ዘይዳ በላይ	ኢ.ፒ.ዴሎ
25. ካሣ ገብረመድህን	የጆሆቫ እምነት ተከታይ
26. ወንድሙ ደመራ	የጆሆቫ እምነት ተከታይ
27. ገብረዮሐንስ አድሃኖም	የጆሆቫ እምነት ተከታይ
28. እሸቱ ምንዳ	የጆሆቫ እምነት ተከታይ
29. አደራ ተሾመ	የጆሆቫ እምነት ተከታይ
30. ካባ አያና	የጆሆቫ እምነት ተከታይ

ምንም እንኳን የመስከረም 25 ቀን 1978 ዓ.ም. ጋቢና ዋራንት ጥሪ ከላይ የተዘረዘሩትን የቆዩ እስረኞች ለግድያ ቢዳርግም ከከርቸሌ ከተጠሩት መካከል ጥቂት የደን ልማት ሠራተኛ የነበሩ እስረኞች ተፈተዋል:: እንደተለመደውም እሁድ በእስረኞች ጥየቃ ጊዜ ከርቸሌ መጥተው የነሱን መፈታትና የሌሎችን ማዕከላዊ መቅረት ተናግረዋል::

በዚሁ በ1978 ዓ.ም. በግንቦት ወር ደርግ ብዛት ያላቸው የቆዩ የፖለቲካና የወንጀል እስረኞች በምህረት ፈታ:: ቢሆንም ምንም እንኳን በዛ ያሉ የቆዩ የፖለቲካ እስረኞችን ቢፈታም ከብሔርተኞችና ከገንጣዮች ጋር የሚካሄደው የትጥቅ ትግል እየጨመረ ስለመጣ በአንድ በኩል የቆዩትን ሲፈታ በሌላ በኩል በአዳዲስ ታሳሪዎች ይተካው ጀመር:: በዚህ ውጥረት የተነሳ ደርግ በኢሠፓ ድርጅት ውስጥ ሠርገው የገቡ የሚላቸውን የወያኔና የኦነግ አባላትንና ሌሎች የተማረኩ ታጣቂዎችን በ1979 ዓ.ም. በቀይ ሽብር ሲገድል ቻለ:: (42) ከዚያም ለ15 ዓመታት በከርቸሌ ታስረው የነበሩትን ልዑላኖችና መሣፍንቶች በ1980 ዓ.ም. በጋቢና ዋራንት ጥሪ ፈታ:: ምናልባትም ከደርግ ዘመን ፍፃሜ በፊት ብዙ ጊዜ የቆዩ እስረኞችን ለመፍታት የመጨረሻው ጋቢና ዋራንት ጥሪ የነሱ ሳይሆን አይቀርም:: ከዚህ ጥሪ በኋላ የቀሩት የፖለቲካ እስረኞች ወያኔ/ኢሕአዴግ የደርግን መንግሥት አሸንፎ አዲስ አበባ ሲገባ ከርቸሌን ሰብረው ከወንጀል እስረኞች ጋር አብረው ራሳቸውን ሊፈቱ ችለዋል:: ከርቸሌን አብዛኛው የደርግ እስረኛ በቁጥጥር ስር በነበረበት ጊዜ ከርቸሌን ያልረገጠ አይገኝም:: እስር የትም ይጀመራል ውሎ አድሮ ወደ ከርቸሌ ያመራል የሚል አባባል ነበር:: ቢሆንም አንዳንድ እስረኞች ከርቸሌን ሳይረግጡ የተፈቱ ወይም የተገደሉ እንደነበሩም መታወቅ አለበት:: ከርቸሌን የረገጡ እስረኞች ደግሞ የጋቢና ዋራንትን ጥሪ በቅጡ ያስታውሳሉ:: ብዛት ያላቸው የከርቸሌ እስረኞች በጋቢና ዋራንት ጥሪ ቢፈቱም አንዳንዶች ከከርቸሌ እየተወሰዱ ብቻቸውንም ሆነ ከሌሎች እስር ቤት ከመጡ እስረኞች ጋር የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነዋል:: ስለዚህ የጋቢና ዋራንት ታሪክ የብዙዎችን እጣ ፋንታ የሚዳስስ የሞትና ሕይወት ታሪክ ነው ማለት ይቻላል::

8. የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የከርቸሌ ጉብኝትና ጋቢና ዋራንት

ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የከርቸሌን እስር ቤት በ1978 ዓ.ም. ጎብኝቷል። ከሱ ጉብኝት ጋር በተያያዘም ይሁን ወይም በአጋጣሚ በ1978 ዓ.ም. በከርቸሌ የተለያዩ ነገሮች ተከስተዋል። ከዘጠኝ ዓመት በላይ በከፍተኛ፣ በማዕከላዊና በከርቸሌ እስር ቤቶች ሲሰቃዩ የነበሩት የኢሕአፓና ሌሎች እስረኞች በቀይ ሽብር ተገድለዋል። ከዚህ ቀደም ብሎ የሚፈራው የኮሌራ በሽታ ከሀያ ስምንት የማያንስ የእስረኛ ሕይወት ቀጥፏል። የከርቸሌ የእስር ቤት እንቅስቃሴ የመንግሥትን ትኩረት በመሳብ የአገሪቷ መሪ ሊጎበኘው ችሏል። ከዚህ ጉብኝት በማስከተልም በዛ ያሉ የፖለቲካ እስረኞች ተፈተዋል።

ቀደም ብሎ በምዕራፍ አምስት እንደተገለፀው በከርቸሌ ጠንካራ ትምህርት ቤት ተቋቋሞ የመማር ማስተማሩ ሂደት በእስረኞች ይካሄድ ነበር። ይህን መሰል እንቅስቃሴ መንግሥትን በማይደግፉ ወገኖች መፈፀሙ የመንግሥትን ትኩረት ይስባል። እስረኛው ላበረከተው መልካም ተግባር እንደ መመዘኛም ተደርጎ ይቆጠራል። ምናልባትም የመንግሥቱ ኃይለማርያም ጉብኝት ዓላማ ይህንኑ ትምህርት ቤት በቅርብ ለመመልከትና ማበረታቻም ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም። የአገሪቷ መሪ በወሬ ደረጃ ስለ እስረኛው የሚሰማውን በጉብኝት ለማረጋገጥ ፈልጎም ይሆናል። ለዚህ ጉብኝት ሲባል የእስረኛው የህብረት ሱቅ የገንዘብ አቅም በሚፈቅደው መሰረት ትምህርት ቤቱ ታድሷል። በጉብኝቱ ወቅት ነፃ አገልግሎት ለሚያበረክቱት አስተማሪዎችም የማበረታቻ ቃል ተችሯቸዋል። ከትምህርት ቤቱ በተጨማሪ ሌሎች በግቢው ውስጥ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችም ተጎብኝተዋል።

ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በጉብኝቱ ወቅት በቅርብ ያጋጠሙትን አንዳንድ እስረኞች በምን ምክንያት ታሰርክ/ታሰርሽ? ስንት ዓመት ታሰርክ/ታሰርሽ? እያለ በመጠየቁ እስረኞችም ተገቢውን መልስ ሰጥተዋል። አንዳንዶች እስር ያንገፈገፋቸው መሆኑን ሳይደብቁ ገልፀው ተናግረዋል። በመጨረሻ እስረኛው በአንድ ላይ ተሰብስቦ በመረጠው ወኪሉ አማካኝነት መንግሥት አሸናፊነቱንና ኃይሉን ማሳየት ብቻ ሳይሆን መሐሪ መሆኑንም ማሳየት አለበት በሚል ምህረት ተደርጎለት እንዲፈታ ጥያቄ አቅርቧል። ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አዳኝም ገዳይም እሱ ብቻ መሆኑን ለማሳየት ከጉብኝቱ በኋላ አብዛኛውን የቆዩ የፖለቲካ እስረኞች በግንቦት ወር 1978 ዓ.ም. እንዲፈቱ ፈቅዷል። እስረኛው ምህረት የተደረገለት መሆኑን በደስታ በመቀበል ከከርቸሌ የመከራና የእስር ሕይወት ቢገላገልም በሞት የተለዩትን ጓደኞቹን ምንጊዜም ማስታወሱ አይቀርም። በተለይ እስከ መጨረሻው አብረው በእስር ተንገላተው በመስከረም 1978 ዓ.ም. ተወስደው የተገደሉትን በልዩ ሁኔታ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

9. የጀኔራሎቹ ወር ተራ

ደርግ የሱማሌን ወረራ በሶቬትና በኩባ ወታደራዊ እርዳታ ቢያሸንፍም ከብሔርተኞች ጋር ያካሄደውን ጦርነት መቋቋም እንዳልቻለ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ይህም ሊሆን የቻለው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ዋናው ግን የደርግ የራሱ ድክመት መሆኑ አያጠያይቅም። «የቀይ ኮከብ ዘመቻ» በሚል በሰየመው ጦርነት ሻዕቢያን ናቅፋ ድረስ ቢያሳድድም በመጨረሻ የታለመውን ድል በራሱ ስህተት መጨበጥ ሳይችል ቀርቷል። ምን ያክል እውነት መሆኑ ባይታወቅም ሻዕቢያን ናቅፋ የከበበው የቀይ ኮከብ ሠራዊት ተገቶ ድሉን

ለኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ታማኝ ሠራዊት ለሆነው ለሦስተኛ ክፍለ ጦር ለመስጠት ታስቦ ከነበረበት ተንቀሳቅሶ ናቅፋ ግንባር እስኪደርስ የተዳከመው የሻዕቢያ ጦር ጊዜ ስላገኘ እንሰራርቶ ሊመክት ችሏል። (43)

በሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች «የቀይ ኮከብ ዘመቻ» ውጤት አልባ ስለሆነ የሻዕቢያ ጦር ሊያይል ችሏል። ከዚህ በኋላ ግዙፍ የሆነው የደርግ መንግሥት ሠራዊት በወያኔና በሻዕቢያ የተቀናጀ ዘመቻ ሽሬ ላይ ከባድ ሽንፈት ሊደርስበትና ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ወታደሮችም ሊማረኩ ቻሉ። ከሰሜንና ከደቡብ ኢትዮጵያ ከተለያዩ ክፍሎች የተሰባሰበው ሠራዊት ሽሬ ላይ በቀላሉ ድል ተመታ። ከሽሬ ሽንፈት በኋላ የደርግ ሠራዊት ምንም ሳይመክት ትግራይን ለቆ በመውጣቱ ወያኔ ትግራይን ነፃ በማውጣት በኤርትራና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ያለውን ሠራዊት እንዳይገናኝ ከፋፈለው። በዚህ የተነሳ በሰሜን የሚገኘው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከአየርና ከባህር ግንኙነት በስተቀር በየብስ እንደልቡ ከመሐል አገር ጋር መገናኘት አልቻለም። የኃይል ሚዛኑም ሙሉ በሙሉ ተቀየረ። ሻዕቢያና ወያኔም የበለጠ ጦራቸውን አቀነጅተው ወደ አዲስ አበባና አስመራ ሲገሰግሱ የሚቋቋማቸው ጠፋ።

ከእነኝህ ወታደራዊ ሽንፈቶች ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚገባው በደርግ ላይ የተደረገው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራና ከሱም ጋር በተያያዘ የተገደሉት ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦችና መኮንኖች ነበሩ። ደርግ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ የዴሞክራሲ አሰራርና ቅራኔዎችን የማስታረቅ ችሎታ ስላልነበረው እኩይ ድርጊቱ ደረጃ በደረጃ አዘቅት ውስጥ ሊጥለው ቻለ። የራሱ የሥልጣን መሰረት የሆነውን ወታደራዊ ክፍል እንኳን በየጊዜው በማፈራረስ ልምድ ያላቸውን አዛዦች በመፍጀት ውድቀቱን አፋጥኗል። ደርግ የሚከተለው ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሰራርና ሁል ጊዜ ጦር መስበቅ የወታደሩን ክፍል ስላማረረው በ1981 ዓ.ም. የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ሊያደርግ ቻለ። (44) ይህ ሙከራ ከብዙዎቹ ሙከራዎች አንዱ ቢሆንም ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው አብዛኛው ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች የተሳተፉበት በመሆኑ ነበር። የዚህ ኩዴታ መክሸፍ የብዙዎችን ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ሕይወት መጥፋት አስከተለ። ብዙዎች ከሞት የዳኑት መኮንኖች ሲታሰሩ፣ ሳይያዙ ያመለጡትም ከአገር ጠፍተው ኮበለሉ። ኩዴታው ወታደሩን የበለጠ ለመከፋፈል ዳረገው፣ ያለበቂ አመራርም አስቀረው። ከዚህ ኩዴታ በኋላ ምንም የወታደራዊ አመራር ልምድ የሌላቸው ዝቅተኛ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ለስርአቱና ለፖለቲካው ባላቸው ታማኝነት ብቻ ከፍተኛ ሹመት ተሰጣቸው። በወታደሩ ክፍል የተሰገሰጉት ካድሬዎችና ኮሚሳሮችም ፈላጭ ቆራጭና ሁሉን ነገር ተቆጣጣሪዎች ሆኑ። በአጠቃላይ በወታደራዊ ክፍሉ የነበረው የእዝ ሰንሰለት ተዋረድና ወታደራዊ ሥነ ስርአት ተናጋ።

የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ የተደረገው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ለጉብኝት ወደ ውጪ አገር በሄደበት ጊዜ ነበር። የኩዴታው አራማጆች የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ መንግሥት ላይ የነበረው ምሬት ከፍተኛ በመሆኑ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን ከሥልጣን መወገድ ሆ ብሎ ይቀበላል የሚል ግምት ስላደረባቸው የጥንቃቄ ጉድለት በመፈፀማቸው የስህተታቸው ሰለባ ሆኑ። በዚህ የተነሳ አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ መሥሪያ ቤቶችንና ኩዴታውን ሊቃወሙ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ የደርግ ታማኝ ወታደሮችንና ባለሥልጣኖችን ለመቆጣጠር የተወሰደው እርምጃ ደካማነት የመንግሥት ግልበጣውን ሊያከሽፈው ቻለ።

ከአስመራ ወይም ከሐረር ወታደሮችን በአየር አስመጥቶ አዲስ አበባን መቆጣጠር ያዳግታል፣ ወይም ብርቱ ጥንቃቄን ይጠይቃል:: ኩዴታውን ያካሄዱት ወገኖች እነኝህን መሰል ስህተቶች በመፈፀማቸው አዲስ አበባ መከላከያ ሚኒስቴር እንደተሰበሰቡ በኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ደጋፊዎችና ባለሥልጣኖች ሲከበቡ አስመራም የነበሩት ደጋፊዎቻቸው በጦሩ ክፍል ሊደመሰሱ ቻሉ:: በወቅቱ በአዲስ አበባም ሆነ በአስመራ ከተገደሉት ጀኔራሎችና የጦር መኮንኖች ሌላ ከልዩ ልዩ ክፍሎች የታሰሩት 12 ጀኔራሎች ጦር ፍርድ ቤት ቀርበው የፍርድ ውሳኔ አየተጠባበቁ እያለ በኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዕዛዝ ተረሸኑ:: ከተገደሉት ጀኔራሎች ሌላ አንዳንድ መኮንኖች የረጅም ጊዜ የፍርድ ውሳኔ ተጥሎባቸው ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ተፈተዋል::

ደርግ የሥልጣን ተቀናቃኞቹን በመንደፍ የሚታወቅ ቢሆንም በዚህ ጊዜ የሰራው ስህተት የራሱን ውደቀት የበለጠ ሊያፋጥንና መቀመቅ ሊያወርደው ችሏል:: በደርግ ጊዜና ከዚያም በፊት በወታደራዊ አመራር ብቃታቸው የሚታወቁት ወታደራዊ አዛዥ መኮንኖች በኩዴታው ጊዜ በመርገፋቸው የኢትዮጵያ ወታደራዊ አቋም ተናጋ:: በዚህ የተነሳ ለብዙ ዓመታት የትጥቅ ትግል ሲያካሂዱ ሥልጣን ለመያዝ ሳይቀናቸው የቀሩት ሻዕቢያና ወያኔ በቀላሉ ድል ሊጎናፀፉ ቻሉ:: ደርግን በኩዴታ ከሥልጣን ለማውረድ የተዶለተው ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይለወጣል ማለት ባይቻልም ምናልባት በአገሪቷ ላይ የደረሰው ወታደራዊ ውድቀት ላይፋጠን ወይም ሌላ አቅጣጫ ሊይዝ ይችል ነበር::

በመጨረሻ ደርግን ለመገልበጥ የኢትዮጵያ ጀኔራሎችና ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ያደረጉት ሙከራ ኩዴታም ተብሎ መጠቀስ የሚገባው አይደለም:: ምክንያቱም ኩዴታ በጥቂት ወታደሮችና አዛዦቻቸው ተዶልቶ የሚካሄድ፣ ፈጣን የወታደራዊ እንቅስቃሴ የሚጠይቅና ከፍተኛ ሚስጥር መጠበቅ የሚያስፈልገው ድርጊት እንጅ ሁሉን አዛዦች አግበስብሶ የሚይዝ ግብዣ አይደለም:: ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ መኮንኖችና ጀኔራሎች ያካሄዱት እንቅስቃሴ በታሪክ መጠቀስ ያለበት እንደ ወታደራዊ አመፅ (Mutiny of the Generals) እንጅ እንደ ኩዴታም መታየት አይገባውም::

10. የከርቸሌ የወንጀልና የፖለቲካ እስረኞች ግኑኝነት

የከርቸሌን የእስር ታሪክ በፖለቲካ እስረኞች ላይ ብቻ በማተኮር የሌሎችን እስረኞች ሁኔታ ሳይዳስስ ማቅረብ ዘገባውን የተሟላ አያደርገውም:: የሌሎች እስረኞች ሁኔታ ሲነሳ ሌሎች ተዛማጅ ማህበራዊ ችግሮችን መመልከት የግድ ያስፈልጋል:: ለአጠራርና ለአያያዝ እንዲያመቻቸው በወህኒ ቤቱ አስተዳደር መሰረት የከርቸሌ እስረኞች በሁለት ይከፈሉ ነበር:: እነሱም የደረቅ ወንጀልና የፖለቲካ እስረኞች (የፀረ አብዮት እስረኞች) በሚል ሲሆን የደረቅ ወንጀል እስረኞች የሕግ እስረኞችም በሚል መጠሪያ ይታወቃሉ:: የሕግ እስረኞችም የሚያሰኛቸው በሰሩት ወንጀል መሰረት ፍርድ ቤት ቀርበው ተከራክረው ውሳኔ ስለሚሰጣቸው ነበር:: የፖለቲካ እስረኞችን ፍርድ ቤት ምንም ስለማያውቃቸውና ደርግ እንዳመቸው ስለሚገድላቸውና ስለሚፈታቸው እንደ ሕግ እስረኞች አይቆጠሩም ነበር::

በአገራችን ሕግ መሰረት አንድ በቀጠሮ ላይ ያለ የሕግ እስረኛ ካልተፈረደበት በስተቀር ወንጀለኛ ሊባል አይችልም:: ይህም በመሆኑ ከርቸሌ እንደገባ የወህኒ ቤቱ አስተዳድር በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት የቀጠሮ እስረኛ ወይም ያልተፈረደበት እስረኛ መሆኑን የሚያመለክት መታወቂያ ወረቀት (ዋራንት) ይሰጠዋል:: ፍርድ ቤት ቀርቦ ከተፈታ በሰላም ይሰናበታል:: ነገር ግን ከተፈረደበት የእስራት ዘመኑ ተጠቅሶ የፍርድ ዋራንት ይቀየርለታል:: ለፖለቲካ እስረኛውም የወህኒ ቤቱ አሰራር እንደዚሁ ነበር::

በደረቅ ወንጀል እስረኛነት የሚጠቃለሉት የከርቸሌ የሕግ ታራሚዎች በራሳቸው የወንጀልና የፍትሐብሔር እስረኞች በሚል በሁለት ይከፈላሉ:: በመጀመሪያው ክፍል ያሉት ስማቸው እንደሚያመለክተው ሕግን በመተላለፍ ከአነስተኛ እስከ ከባድ ወንጀል የፈፀሙ እስረኞች ሲገኙባቸው የፍትሐብሔር እስረኞች ደግሞ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ጥፋትንና ጉድለትን የፈፀሙ እስረኞች ነበሩ:: የወንጀል እስረኞች በራሳቸው ከባድ ወንጀል፣ ቀላል ወንጀልና ተመላላሽ በሚለው ይከፋፈላሉ:: ከባድ ወንጀል የፈፀሙ ናቸው ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት ሽፍታ ሆነው ሰው የገደሉና ቤት ንብረት ያቃጠሉ፣ በአጋጣሚም ሆነ በቂም በቀል የሰው ሕይወት በማጥፋት ነፍስ ገዳይ በሚል የተከሰሱ፣ ማጅራት መቺዎችና ሌላም አስቃቂ ወንጀሎች የፈፀሙ ከባድ ፍርድ የተፈረደባቸውንና ሊያስፈርድባቸው የሚችል ድርጊቶችን የፈጸሙትን ያጠቃልል ነበር:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአምባጓሮ ሰው በመደብድብ፣ በስለት ለመውጋት በመሞከር፣ ወዘተ. የታሰሩ እንደ ቀላል ወንጀል የፈፀሙ ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ::

ሌሎች የእለት ተለት የኑሮ አረንቋ ችግር የገረፋቸው፣ ሥራ የሌላቸው፣ የጎዳና ተዳዳሪ የሆኑ፣ ትምህርት ያቋረጡ፣ አንዳንድ ጊዜም በዝቅተኛ ሥራ የሚተዳደሩት፣ ወዘተ. በአጠቃላይ ቦዘኔ በሚል በህብረተሰቡ ከሚጠቀሱት መካከል በየጊዜው አነስተኛ ወንጀል እየፈፀሙ ከርቸሌ ይመላለሳሉ:: አንዳንዶቻቸው ከወንጀላቸው ዝቅተኝነት የተነሳ የሚጣልባቸው ፍርድ አነስተኛ ስለሆነ በየጊዜው ከርቸሌ ስለሚታሰሩና ስለሚፈቱ ተመላላሽ የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል:: ተመላላሽ የወንጀል እስረኞች በአጠቃላይ ከሌብነት ጋር የተያያዘ ዝቅተኛ ወንጀል ፈፃሚዎች ተደርገው ይቆጠሩ እንጅ የአንዳንዶቹ ድርጊት ከከባድ ወንጀል አይተናነስም ነበር:: ለምሳሌ የታጠቁ የገጠርም ሆነ የከተማ ዘራፊዎች ተራ ሌቦችም ከባድ ወንጀለኞችም ናቸው::

የተመላላሽ ወንጀለኞች ስም ከድርጊታቸው ይመነጭ ነበር:: «ሰተቴ» የሚባሉት የተከፈተ ቤት ሰተት ብለው ገብተው ያገኙትን ተሸክመው ሰርቀው የሚነጉዱ ነበሩ:: «ቀጭ በሉ»፣ በአፍ ብልጠትና ቀልጣፋነት (ወይም አራዳነት) ሸውደው የሌላውን ገንዘብና ንብረት በራስ ፈቃድ ተረክበው አታለው የሚወስዱ ናቸው:: አንዳንድ «ቀጭ በሉዎች» አለባበሳቸውና ጠቅላላ ሁኔታቸው ሲታይ አፈ ጮማ ከመሆናቸው በስተቀር የማታለል ተግባር ይፈፅማሉ ብሎ ለመጠርጠር ያስቸግራል:: ሌሎች የሚጠቀሙበትን ስምና ድርጊት ለማህበራዊ ጥናት ተመራማሪዎች በመተው ቤት ሰርሳሪ (አንክቴ)፣ ኪስ አውላቂ (ቦሩ)፣ ዘንቢል ጠላፊ፣ መኪና ጎርጓሪ፣ ነጥቆ በራሪ፣ በገጠር ደግሞ ጎተራ ገልባጭ፣ የእህል ክምር ዘርጣጭ፣ ከብትና በግ ጠላፊ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ወንጀል ፈፃሚዎች ሁሉ ተመላላሾች ነበሩ::

ተመላላሽ እስረኞች ከርቸሌ የመመላለሳቸውን ያክል የግቢውም ችግር ፈጣሪ ነበሩ:: በቁጥጥር ስር መሆናቸውን ዘንግተው የእስር ቤቱን ደንብ

በመጣስና የውጪውን ሕይወት ከርቸሌ ለማምጣት በመሞከር ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ:: በከርቸሌ ቁማር መጫወትን፣ ጫት መቃምን፣ መጠጥ መጠጣትን፣ ከእስር ለማምለጥ መሞከርንና ሌሎች የተከለከሉ ነገሮችን በመፈፀም ግንባር ቀደም ነበሩ:: እንዲያውም ሃሺሽ ማጨስ በጊዜው የተስፋፋ አይሁን እንጅ የወህኒ ቤቱን አጥር ጥሶ ሳይገባ አይቀርም:: በወህኒ ቤቱና በእስረኛው የተጠላውንና የተወገዘውን የግብረ ሰዶም ድርጊት አንዳንዶች ሲፈፅሙ እየተያዙ በጀርባቸው ላይ «እኔን ያየህ ተቀጣ» የሚል ተለጥፎባቸው በግቢው ውስጥ የሚዞሩትም በአብዛኛው እነሱው ነበሩ:: በመሰረቱ የውጪው ሕይወታቸው ከዚህ የተለየ ስላልሆነ አይፈረድባቸውም:: ተመላላሽ እስረኞች የሚፈፅሙትን መጥፎ ድርጊቶች አንዳንድ ምግባረ ብልሹ የሆኑ ሌሎች እስረኞችም እንደሚጋሯቸው መታውቅ አለበት::

ተመላላሽ እስረኞች የውጪው ሕይወታቸው በሌብነት እንዲስማሩ ቢገፋፋቸውም ከርቸሌ በእስር ላይ በሚቆዩበት ጊዜ ከእስረኛው ምንም ጊዜ ሲሰርቁ አይታዩም ነበር:: በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ይደነቃሉ:: የውጪ ስራቸው የሚቀረው ከእስር ቤት ውጪ እንጅ ተከትሏቸው ከርቸሌ አይገባም:: አንዳንዶች ፍርዳቸው እስኪያበቃ ድረስ ትምህርት ቤት ገብተው ይማራሉ:: ከዚህ ሌላ እንደ ማንኛውም እስረኛ ርስ በርሳቸው ይረዳዳሉ:: በውጪ ያሉ ጓደኞቻቸው ከርቸሌ እየመጡ ይጠይቋቸዋል:: በእድሜ የገፉት ተመላላሾች በመነተፉት ገንዘብ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩና ልጆችም ያሏቸው ነበሩ::

የፍትሐብሔር እስረኞች ወንጀል በመፈፀም ሳይሆን በገንዘብ ማጉደል፣ እደራ በመብላት፣ ተበድሮ ባለመክፈል፣ የመንግሥት ካዝና በመገልበጥ፣ ወዘተ. የታሰሩ ነበሩ:: በጊዜው እነሱንም በሁለት ክፍሎ ለማየት ይቻላል:: በአንድ ወገን ጊዜው የወለደው «የኤኮኖሚ አሻጥር እስረኞች» ሲገኙ በሌላው ወገን ደግሞ የተለመደው የፍትሐብሔር እስረኞች ይገኙ ነበር:: «የኤኮኖሚ አሻጥር እስረኞች» በሚል የሚጠቃለሉት የመንግሥት ካዝና በማራቆት ለራሳቸው የግል ጥቅም በማዋል የታሰሩ ሲሆኑ በመንግሥት ሥልጣንም ላይ የነበሩ በዚህ ቅሌት የታሰሩ ነበሩ:: ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በመመሳጠር በጊዜው ጉቦ በማቀበል፣ ባለሥልጣን በመደለል፣ የሸቀጣ ሸቀጥ እጥረት ለመፍጠር ዕቃ በመደበቅ፣ ከሕግ ውጪ ዕቃ በመግዛት፣ ወዘተ. ብዛት ያላቸው ነጋዴዎች ታስረው ነበር:: ያለአግባብ ለመበልፀግ በሚያደርጉት ሙከራ አንዳንድ የሰመረላቸው ነጋዴዎች በአጭር ጊዜ ሐብታም ለመሆን ሲችሉ የተጋለጡት ደግሞ ለእስር ተዳርገዋል:: ብዙ ሐብት በአጭር ጊዜ ካግበሰበሱት መካከል «የደርግ ልጆች» በሚል መጠሪያ የሚታወቁት ነጋዴዎች የሚታወሱ ናቸው::

ከርቸሌ በእስር ላይ ከነበሩት እስረኞች መካከል ከፖለቲካ እስረኞች ይልቅ የእስር ቤቱ የኑሮ ችግር በደረቅ ወንጀል እስረኞች ላይ ይበረታ ነበር:: የውጪ ጠያቂም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር በየጊዜው አይጎበኛቸውም:: ይህም ሊሆን የቻለው አብዛኞቹ የደረቅ ወንጀል እስረኞች መሰረታቸው ከገጠር ስለሆነ ወዳጅ ዘመዶቻቸው በቅርብ ስለማይገኙ ሊሆን ሲችል ሌላው ደግሞ የተፈረደባቸው እስረኞች ቁርጡ በመታወቁም ሊሆን ይችላል:: እዚህ ላይ ግን በሳምንት ቀርቶ በየቀኑ የሚጠየቁትን «የኤኮኖሚ አሻጥር እስረኞች» ከሌሎች ጋር ደባልቆ ጠያቂ እንደሚያጥራቸው እስረኞች መቆጠር የለባቸውም::

የደረቅ ወንጀል እስረኞች በወህኒ ቤቱ አስተዳደርም የሚደርስባቸው በደል ለየት ያለ ነበር:: በየጊዜው ሲዳሞ፣ ብላቴን፣ ሸዋ ሮቢት፣ ዝዋይ፣

ሎሜራ፣ ወዘተ. ለተለያዩ የእርሻ ሥራ አገልግሎት ይላካሉ:: በከርቸሌ ግቢም ውስጥ ከባድ የእርሻ ሥራ የሚሰሩት እነሱው ነበሩ:: አንድ ጊዜ ብቻ በ1976 ዓ.ም. መንግሥት የአዋሽ አርባን ጥጥ በወቅቱ ለመሰብሰብ የሰው ኃይል እጥረት ስላጋጠመው ድብልቅ የፖለቲካና የወንጀል እስረኞች ለጥጥ ለቀማ ተልከዋል:: በዚህ ጊዜ በከርቸሌ ግቢ ያጋጠመው ትርምስ የሚረሳ አይደለም::

ከፖለቲካ እስረኞች መካከል ፍርድ ያላቸው ነበሩ ለዚህ የተጋለጡት:: ቢሆንም አብዛኛው የተፈረደባቸው የፖለቲካ እስረኞች በግቢው ውስጥ የማስተማርና ሌላም ሌላም ነፃ አገልግሎት የሚያበረክቱ ስለነበሩ ወደ ጥጥ ለቀማው ከመሰማራት ሊድኑ ችለዋል:: እስረኞችን ወደ አዋሽ አርባ ለመውሰድ በታቀደበት ቀን ጠዋት የእስረኞች መኖሪያ ቤቶች ሳይከፈቱ ተጓዦች ብቻ ዕቃቸውን ይዘው ከየቤቱ እንዲወጡ ተጠሩ:: እነኝህ የተጠሩት እስረኞች በኳስ ሜዳ ተሰብስበው የሚወስዷቸውን መኪናች ሲጠባበቁ ዋሉ:: ሌሎች እስረኞች በቤት ውስጥ ተዘግቶባቸው ውለው በዚያው አደሩ:: ተጓዦቹን የሚወስዱት መኪናዎች በዚያን ቀን ስላልመጡ ግቢው ውስጥ ከሜዳ አድረው በማግስቱ ተጭነው ተወሰዱ:: በዚህ ጊዜ ለጥጥ ለቀማ ከተወሰዱት መካከል ብዙዎቹ ተሰቃይተውና ታመው ተመልሰዋል::

እስረኞችን ከአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ወደ ቆላማ ቦታ ማዛወር ለወባና ለተለያዩ ውሃ ወለድ በሽታዎች ያጋልጣል:: ለዚህ መሰል ሥራ ከከርቸሌ የተወሰዱት እስረኞች ተመልሰው ሲመጡ በጣም ተጎሳቅለውና ሰውነታቸው አልቆ ስለሚመጡ ለማገገም ብዙ ጊዜ ይፈጅባቸዋል:: ከዚሁ እስረኞች ከሚሰጡት የጉልበት ሥራ ሳንወጣ የህሊና እስረኞች በአገሪቷ መኖር ሕገ ወጥ ከመሆኑም ሌላ እንደ ተራ ወንጀለኞች ከባድ ሥራ መሥራትም እንደሌለባቸው የደርግ መንግሥት የሚያከብር አልነበረም:: ምናልባትም ከአንድ ጊዜ በስተቀር እንደ ወንጀል እስረኞች የፖለቲካ እስረኞች ልዩ ልዩ ቦታ ያልተላኩበት ምክንያት በወቅቱ በየቦታው በሚካሄደው የተጧጧፈ የትጥቅ ትግል የፖለቲካ እስረኞችን ተቃዋሚዎች እንዳይነጥቁት ደርግ ስለሰጋ ሊሆን ይችላል::

ከርቸሌ በእስር ላይ በነበሩት የወንጀልና የፖለቲካ እስረኞች የሚነሱ ሁለት ጥያቄዎች ነበሩ:: እነሱም አንደኛ የተራ ወንጀልና (Common criminals) የህሊና እስረኞችን (Prisoners of conscious) አንድ ላይ ደባልቆ ማሰር ተገቢ ነው? የሚለው ሲሆን ሁለተኛ በእስር ላይ በቆዩበት ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ? የሚሉት ናቸው:: በእነኝህ ጥያቄዎች ዙሪያ ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች ይሰነዘሩ ነበር::

በአንድ ወገን ያለው ሃሳብ የተራ ወንጀለኞችንና የህሊና እስረኞችን አንድ ላይ መታሰር ትክክል አለመሆኑን በመቃወም የፖለቲካ እስረኞችን ለአገሪቷ ከባድ ወንጀለኞችና መጥፎ ልምድ ላላቸው ቦዘኔዎች አጋልጦ መስጠት ነው በሚል አይቀበሉትም ነበር:: ተራ ወንጀለኞች ከህብረተሰቡ የሚገለሉትና ለብቻቸው በእስር ላይ የሚቆዩት ከጥፋታቸው እንዲታረሙ ስለሆነ ይህን መሰል ጥፋት ያልፈፀሙትን ከእነሱ ጋር ደባልቆ ማሰር ተገቢ አይደለም በማለት ይከራከራሉ:: በተለይም በጊዜው የፖለቲካ እስረኛው ብዛት ባይኖረው ኖሮ የተራ ወንጀለኞችን መጥፎ ድርጊት መቋቋም አይችልም ነበር የሚሉ ወገኖች የመኖራቸውን ያክል በተቃራኒውም የቆሙ ነበሩ::

ሌላው ወገን ደግሞ እስርን ማንም ወዶ አይታሰርም:: በግል ሲመዘን የአንድ ሰው ጥፋት ወንጀለኛ ሊያሰኘው ቢችልም በድምር ሲታይ የፖለቲካም

ሆነ የወንጀል እስረኞች የማህበራዊ ችግሮችና የስርአቱ ሰለባዎች ናቸው። ስለዚህ የህሊና እስረኞች በአገሪቷ የተንሰራፉትን ማህበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመለወጥ የቆሙ እስከሆኑ ድረስ እስርና ሰቆቃን መቃወም እንጅ ለምን ከወንጀል እስረኞች ጋር ታሰርን በሚል ተቃውሞ ማንሳት የለባቸውም ይሉ ነበር።

በዚህ ክርክር የየትኛውም ወገን ትክክል ይሁን በጊዜው ሁለቱ አንድ ላይ በመታሰራቸው የከፋ ችግሮች አላጋጠሙም። ምናልባት ከጊዜው የፖለቲካ ውዥንብር ጋር የተያያዘ ተራ ስድቦችና አለመግባባቶች በግለሰብ ደረጃ አጋጥመው ይሆናል። ከኢሕአፓ ደጋፊ እስረኛ ጋር ሲጣሉ «ወረቀት በታኝ» ወይም «አናርኪስት» ማለት፣ የመኢሶን አባል ከሆነ «ባንዳና ቀኝ መንገደኛ» ብሎ መሳደብ፣ የቀይ ሽብር አራማጅ ከሆነ «ፀረ ሕዝብ» ብሎ መጎንተል፣ የኤኮኖሚ አሻጥር እስረኛ ከሆነ «ካዝና ገልባጭ» መባል፣ ተመላላሽ ከሆነ «ቦዘኔ» ተብሎ መሰደብ፣ ወዘተ. የከፋ ችግር ያስከትላል ማለት አይደለም። ይህን መሰል መናቆር ከእስር ቤት ውጪም ከህብረተሰቡ ጋር ሲኖር ያጋጥማል። ከእነኘህ ስም ለማጉደፍ ከሚለጠፉ ቅፅሎች ወጪ በጊዜው በተካሄደው የፖለቲካ ትግል እያንዳንዱ የራሱን ቀዳ ለማዋደድና ትክክል መስሎ ለመቅረብ ቢሞክርም ህብረተሰቡና በተለይም የነቃው ክፍል ማ ምን እንደነበረ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ከዚህ ሌላ የወንጀል እስረኛው አንዳንድ ጊዜ እርስ በርሱ ሲጣላ በድንጋይ ቢፈናከትና በስለት ቢሸራከትም በፖለቲካ እስረኛ ው ላይ ጉዳት አላደረሰም። ይህን መሰል አምባጓሮ ለመፍጠርም ቢሆን የእስር ቤቱን አስተዳደር ግሳጼና ቅጣት ስለሚፈራ ብዙም አያጋጥምም። ቢሆንም አንዳንድ እንደ ሰማኝ ፈረጃና ግርማ ጃክ ዓይነት ጉልበተኛ የወንጀል እስረኞች በእስር ጓደኞቻቸው ቀርቶ በአስተዳደሩም የሚፈሩ ነበሩ።

በሌላ መልኩ የወንጀልና የፖለቲካ እስረኞች አንድ ላይ ተደባልቀው መታሰራቸው ለአንዳንድ የወንጀል እስረኞች አስተሳሰባቸውን ለማበልፀግና ባህሪያቸውን ለመቀየር ረድቷቸዋል። ከርቸሌ የነበረው ትምህርት ቤትና መጻሕፍት ቤት ምን ያክል አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ በምዕራፍ አምስት ተገልጿል። ይህንን እድል በትምህርታቸው ያልገፉት የፖለቲካም ሆነ የወንጀል እስረኞች ተጠቅመውበታል። ያልተማሩትን ከመሐይምነት ለማላቀቅ፣ መጠነኛ ትምህርት የነበራቸውን ደረጃቸውን ለማሻሻል ረድቷቸዋል። ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኛው የከርቸሌ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች የፖለቲካ እስረኞች ነበሩ። እንግዲህ የፖለቲካ እስረኞች ባይኖሩ ኖሮ የከርቸሌ የመማር ማስተማር ግቡን መምታቱ ያጠራጥራል። ስለዚህ የፖለቲካ እስረኞች በከርቸሌ መኖር ለሁለቱም ወገኖች ትምህርት ለመማርና በአእምሮ ለመበልፀግ አስተዋፅኦ አድርጓል።

በፖለቲካ እስረኞች መካከል በነበረው አለመግባባት የተነሳ የወህኒ ቤቱ አስተዳደር የፖለቲካ እስረኞችን በኮሚቴ አባልነት እንዳይሳተፉ በማገዱ የተነሳ የወህኒ ቤቱን ኮሚቴዎች በሙሉ የሚቆጣጠሩት የወንጀል እስረኞች እንደነበሩ ቀደም ብሎ በምዕራፍ አምስት ተገልጿል። በወንጀልና በፖለቲካ እስረኞች በጋራ የሚመረጡት እነኘህ ኮሚቴዎች ለራሳቸውም ሆነ ለተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በማድላት የፈፀሙት እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው የጎላ ስህተት አልነበረም። ሌላው ቢቀር በይፋ የታየ ነገር አልነበረም ለማለት ይቻላል። ከዚህ ጋር ሊቀርብ የሚችለው ምንም ተጨባጭነት የሌለው አሉባልታ ቢመስልም አንዳንድ የወንጀል እስረኞች በኮሚቴ አባልነት ቢመረጡ

ውጪ አያሉ በአባልነት ለሚደግፉት የፖለቲካ አስተሳሰብ ማድላታቸው አይቀርም ነበር፡፡ ደግነቱ እነኝህን መሰል የወንጀል እስረኞች በየቤቱ በቅጥ ስለሚታወቁ በስህተት አምልጠው ካልሆን በስተቀር የመመረጥ እድላቸው የጠበበ ነበር፡፡

የፖለቲካ እስረኞች በጋቢና ዋራንት ተጠርተው ሲገደሉ በከርቸሌ ግቢ ታላቅ ሐዘን እንደሚሰማ ሁሉ የወንጀል እስረኞችም በሕግ ተፈርዶባቸው በስቅላት ሲቀጡ ተመሳሳይ ሐዘን ያጋጥማል፡፡ የሕግ እስረኞች ወታደሮች ካልሆኑ በስተቀር የሚገደሉት በስቅላት ነበር፡፡ ወታደሮች ጦር ፍርድ ቤት ቀርበው ሞት ከተፈረደባቸው በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ይደረጋል፡፡ የደርግ የቀይ ሽብር ሰለባ የነበሩት የፖለቲካ እስረኞች ግን በጥይትም፣ ታንቀውም፣ በሌላም ለገዳዩ አመቺ በሆነ መንገድ ይገደሉ እንደነበር ቀድም ብሎ በሌላ ቦታ ተገልጿል፡፡ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው የሕግ እስረኞች ስቅላት እስኪፈጸምባቸው ድረስ ብዙ ጊዜ በከርቸሌ ይቆያሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ስቅላቱም የሚፈፀምባቸው ከወህኒ ቤቱ ተወስደው ወንጀል በሰሩበት አካባቢ ነበር፡፡ ከወህኒ ቤቱ ገና ተጠርተው ሲወሰዱ ድርጊቱ እንደሚፈፀምባቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ የተነሳ በሚወሰዱበት ጊዜ በቅርብ የሚያውቋቸው በሙሉ ይረበሻሉ፣ ያዝናሉ፡፡ ሞት የተፈረደባቸው እስረኞች በቁጥር አነስተኛ ስለሆኑና በአንድ ወቅት በስቅላት የሚቀጡትም እንደዚያው አነስተኛ በመሆናቸው አንዳንድ ጊዜ የተሰቀሉትን ሰዎች በቅርብ ከሚያውቃቸው በስተቀር ሌሎች ሳይሰሙ ይችላሉ፡፡

በኢትዮጵያ ከባድ ወንጀል በፈፀሙ ወንጀለኞች ላይ የሞት ፍርድ መፍረድ የተለመደ ነው፡፡ ይህን መሰል ፍርድ በሌሎች አገሮችም ቢዘወተርም አንዳንዶች የሞት ቅጣትን መፈፀም የማይቀበሉም አሉ፡፡ አንድን ወንጀለኛ ከጥፋቱ እንዲታረም ለማድረግ የሚሰነዘረው ቅጣት ለሰውም ለህብረተሰቡም እንደማስተማሪያ ተደርጎ የሚቆጠር ከሆነ የሞት ፍርድ የሚደገፍ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ አንድ ጥፋት የሰራ ሰው ከጥፋቱ ሊታረም የሚችለው በመኖሩ እንጅ በመሞቱ አይደለም፡፡ ሌላው ደግሞ በአንድ ህብረተሰብ የወንጀል ድርጊት ከበረከተና ጥፋት ፈፃሚዎች ብታሰር አልሟሟም በሚል ወንጀል ከመሥራት የማይቆጠቡ ከሆነ የሞት ፍርድ ለማስፈራሪያነቱም ሊያገለግል ይችላል፡፡ ስለዚህ የሞት ፍርድ መታየት ያለበት ከወንጀሉ ከባድነት ብቻ ሳይሆን ከወንጀለኞች መብዛትና ተደጋጋሚ ጥፋቶችን ከመፈፀም ጋር ነው፡፡

የተፈረደባቸው የሕግ እስረኞች የእስር ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ይፈታሉ፡፡ አብዛኞቹ የተፈረደባቸውን 2/3 የእስር ጊዜ ሲያጠናቅቁ አመክሮ ተሰጧቸው ይለቀቃሉ፡፡ ከፍርድ ቤት አመክሮ ለማግኘት የሚቻለው በእስር ላይ በቆዩበት ጊዜ ከጥፋታቸው መታረማቸውን የወህኒ ቤቱ አስተዳደር ሲመሰክር ነበር፡፡ ከእነኝህ በሁለት ደረጃ ከተከፋፈሉት የፍርድ ውሳኔዎች ሌላ ከመንግሥት ምህረትና የእስር ቅናሽ ይደረግላቸው ነበር፡፡ ይህን መሰል እድል የሚያጋጥመው የአብዮት በዓላትን ወይም ሌላ ልዩ ሁኔታን ተንተርሶ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ከኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የከርቸሌ ጉብኝት በኋላ ብዛት ያላቸው የሕግ እስረኞች ምህረትና የእስር ቅናሽ ተደርጎላቸው ተፈተዋል፡፡

ማሳረጊያ

ድህረ ቀይ ሽብር የኢትዮጵያ ፖለቲካ

1. የኢሕአዴግ መንግሥት የፖለቲካ አቅጣጫ

«አንድ የአምባገነን መንግሥት የመሰረተ ግለሰብ ብሩተስን ካልገደለ፣ ወይም አንድ የሪፓብሊክ መንግሥት የመሰረተ የብሩተስን ልጆች ካልገደለ በሥልጣን ላይ ሊቆይ የሚችለው ለአጭር ጊዜ ብቻ ይሆናል::»

(«He who establishes a dictatorship and does not kill Brutus, or he who founds a republic and does not kill the sons of Brutus will only reign a short time.") Machiavelli: Discorsi

በኢትዮጵያ በተከታታይ በሥልጣን ላይ የወጡ መንግሥታትን የፖለቲካ አካሄድ የሚገልፅ ተስማሚ አባባል ነው:: ደርግ በሥልጣን ላይ በቆየበት ጊዜ መሬትን የመንግሥት በማድረግ ፊውዳሊዝምን ከመገርሰሱ በስተቀር ሌላ በጥሩ ጎኑ የሚጠቀስ ታሪክ የለውም:: ኢሕአዴግ በቅርቡ በ1983 ዓ.ም. ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠ ስለሆነ በሂደት የተሳሳተ የፖለቲካ አቅጣጫውን ሊያርም ስለሚችል አጀማመሩን ብቻ አይቶ መተቸት ታሪኩን የተሟላ አያደርገውም:: ቢሆንም አርጌውን ከአዲሱ ጋር ሳያገናኙ መተው ደግሞ የዚህን መጽሐፍ ታሪክ የተሟላ ስለማያደርገው ማሳረጊያው የኢሕአዴግን መንግሥት መመልከት ይሆናል::

በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ዓለም በሁለት ርዕዮተዓለምና በሁለት ኃያላን ጎራ ተከፋፍላ በነበረችበት ወቅት የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የመንግሥት አስተዳደር ከኃያላኖቹ ጋር በነበራቸው ቅርበትና ግኑኝነት ይወሰን ነበር:: በዚህ ጊዜ ከሶቬት ህብረት ጋር ግኑኝነት የነበራቸው ብዙ አገሮች የአንድ ፓርቲ ወይም ወታደራዊ አገዛዝ አምባገነንነት ሰፍኖባቸው ቆይቷል:: ኢትዮጵያም ከሶቬት ህብረት ጋር ወዳጅ በነበረው በደርግ አምባገነን መንግሥት አገዛዝ ስር ስለነበረች የችግሩ ተቋዳሽ ሆናለች:: የሶቬት ህብረት መንግሥት ከተፍረከረከ በኋላ ዓለም ወደ ዴሞክራሲ፣ ወደ መድበለ ፓርቲና ወደ ተሻለ አስተዳደር ስለአመራች የመንግሥት ሥልጣንም በሕዝብ ምርጫ ፍቃድ መወሰን ጀምሯል:: በዚህ የተነሳ የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ዴሞክራሲ የሰፈነበት መልካም አስተዳደር ለመመስረትና ለሕዝባቸውም ብልፅግና ለማጎናፀፍ እየተጣጣሩ ናቸው:: መልካም አስተዳደር ለአንድ አገር የኤኮኖሚ፣ የሶሻልና የፖለቲካ ስርአት ለውጥ ለማምጣት በጣም አስፈላጊ ነው:: አንድ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት ለሚያስተዳድረው ሕዝብ ግልፅነትን፣ ተጠያቂነትን፣ የሲቪል ማህበረሰቡን ተሳትፎ ማጠናከርን፣ የሕግ የበላይነትን ማስከበርን፣ ሰላምና መረጋጋት መፍጠርንና ነፃ ሃሳብ ማንሸራሸርን ካላጎናፀፈ የፖለቲካና የዕድገት ለውጥ ማምጣት አይችልም::

በ1989 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራምና በአፍሪካ የኤኮኖሚክ ኮሚሽን አስተባባሪነት አሥራ አራት ልዩ ልዩ የአፍሪካ አገሮች፣ አሥራ ስምንት የተለያዩ የለጋሽ መንግሥታት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ድርጅቶች በአዲስ አበባ በተሰበሰቡበት ጊዜ የኢሕአዴግ

መንግሥት በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር እንደሚመሰርት አረጋግጦ ነበር:: (1) ነገር ግን ይህ ቃል በተግባር ሲውል አይታይም:: በኢትዮጵያ ሰላም፣ ዴሞክራሲና የኤኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የታለመው መንገድ ብዙ እንቅፋት ያለበት መሆኑን ቀጥሎ እንመለከታለን::

1.1 አሮጌውን ማደስ

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች መካከል «የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል» የሚለውን አንቀፅ 39 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 4 (2) አገርን ለመከፋፈልና ለመለያየት አደጋ ያጋልጣል በሚል ብዙዎች አይስማሙበትም:: ሌሎች ደግሞ የብሔር ብሔረሰቦች ችግር እንደተዳፈነ እሳት ወይም እንደተቀበረ ፈንጂ ስለሚቆጠር ማስተንፈሻው ይህ አንቀፅ መሆኑን ይናገራሉ:: አንዳንዶች የአንድን አገር ችግር ለመፍታት የመቻቻልና የአመራር የፖለቲካ ብስለትን ይጠይቃል እንጅ በሥራ ላይ የማይውል ወይም እንደ ማስፈራሪያ የሚጠቀስ መብት እንደ ሕግ ቀርጾ ማስቀመጡን ይተቻሉ:: በብሔር ብሔረሰቦች መካከል ያለውን ልዩነትና እርስ በርሳቸው መጠራጠር ሊፈታው የሚችለው የመለያየት መብታቸውን በሕገ መንግሥት ደንግጎ ማስቀመጡ ሳይሆን የእኩልነትና የዴሞክራሲያዊ አሰራርን ማጎልበቱ ነው:: አሁን ባለንበት ዘመን በአንድ አገር ሕዝቦች መካካል ቀርቶ በተለያዩ አገሮች መካከል የበለጠ መተሳሰር፣ መተባበር፣ መቻቻልና ዴሞክራሲያዊ ግኑኝነት እየጠነከረ ስለመጣ አንቀፁ አስፈላጊ ነው ለማለት ያሸቸግራል::

በአገራችን ግን የዴሞክራሲያዊ አሰራር ድክመት የኦነግን፣ የአፋር ነፃ አውጪ ድርጅትንና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን ጦር እንዲሰብቁ አስገድዷቸዋል::(3) የመገንጠልን መብት በሕገ መንግሥት ያፀደቀው ኢሕአዴግም ቢሆን ለምን ከእነኝህ መሰል የብሔር ድርጅቶች ጋር በጠመንጃ እንደሚፋለም ግራ ያጋባል:: የህብረ ብሔር ከሆኑት ድርጅቶች መካከል እንደ ኢዴፓቅና መድህን የመሳሰሉት ይህንን ከፋፋይ የሆነ የሕገ መንግሥት አንቀፅና ዴሞክራሲያዊ ይዘት የሌለው አሰራር አይቀበሉትም:: (4) ጦር ካልመዘዙትም መካከል መኢሕድ፣ ኢዴህፓ፣ ወዘተ. በዚህ አንቀፅ ላይ ደስተኞች አይደሉም:: (5) እንዲያውም የአንቀፁን መኖር በከፊል የሚደግፉት አንዳንድ የደቡብ የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶችም ቢሆኑ የመብት አከባባር አፈፃፀሙ ላይ ዴሞክራሲያዊ ይዘት ስላጡበት ከኢሕአዴግ ተራርቀው ከአገሪቷ የፖለቲካ ተሳትፎም ተገልለው ቆይተዋል:: (6) የአምስት ዓመት የሕገ መንግሥቱን አፈፃፀም በመቃኘት በመንግሥት በኩል የቀረበው ዘገባ ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን ችግሮች ሳይዳስስ ሕገ መንግሥቱ የአገር ውስጥ ጦርነቶችን ለማስቀረት መፍትሔ እንደሆነ አስቀምጧል:: (7)

የዓለም አቀፍ ልምድ ስለ «የራስን እድል በራስ መወሰን» ምን ያመለክታል:: የቅኝ ግዛት በዓለም ላይ በተስፋፋበት ዘመን ብዙ አገሮች «የራስን እድል በራስ መወሰን» በሚለው መርህ መሰረት ነፃነታቸውን ለመጎናፀፍ ችለዋል:: የሶሻሊስት አብዮትም ለማካሄድ በተደረገው ትግል ከተለያዩ ብሔሮች የተወጣጡት የጭቁን መደብ አባላት ትግላቸውን ለማቀናጀትና በገገር መደቦች ላይ በጋራ ለመነሳት ይኸው መርህ ረድቷል:: ነግር ግን ከአብዮቱ ግብ መምታት በኋላ «የራስን እድል በራስ መወሰን» ተግባራዊ መፍትሔ ሊሆን አልቻለም:: በዚህ የተነሳ በአሁን ዘመን መልኩን ቀይሮ የብሔርተኞች ብሶት መወጫ፣ የፖለቲካ መጠቀሚያና አገር መከፋፈያ ሆኗል:: ከነማርክስና

ኤንግልስ ቀጥሎ «የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል» የሚለውን ሲያቀነቅኑ የነበሩት ሌኒንና እስታሊን ነበሩ:: (8) እነሱም ሶቬት ህብረትን ሲገነቡ በሥራ ላይ ፈትነውታል:: በህዝቦችም መካከል ሰላም፣ አንድነትና እኩልነት ለማምጠት እንደ ፍቱን መፍትሔ ተደርጎ ይቆጠር ነበር:: በሶሻሊስት ካምፕ ስር የነበሩት ሌሎች የምስራቅ አውሮፓና አንዳንድ የእስያ አገሮችም ይህንኑ እንደሚያመቻቸው ገልብጠው ሲሰሩበት ቆይተዋል:: ነገር ግን በ1983 ዓ.ም. እንደታየው የዚህ መርህ መኖር ሌኒንና እስታሊን የገነቧትን ሶቬት ህብረትን ከመፍረስ አላዳናትም:: የሶቬት ህብረት፣ የምስራቅ አውሮፓ፣ የሩቅ ምስራቅና የአካባቢያችን የፖለቲካ ሁኔታ የሚያመለክተው የመደብም ሆነ የብሔር ትግል ሥልጣን ላይ ለመውጣት ያገለግል እንደሆነ እንጅ ለህዝብ የዴሞክራሲ ለውጥ አለማጎናፀፉን ነው::

የዴሞክራሲ መታፈን፣ የኤኮኖሚ እድገት አዝጋሚ መሆንና በአገሪቷ ታቅፈው የነበሩት ልዩ ልዩ ብሔርችና ሪፓብሊኮች እኩል አለመራመድ ተደማምረው የጥንቱን የሶቬት ህብረት መንግሥት ለመከፋፈልና ለመበታተን ዳርጎታል:: ሶሻሊዝምን ከነቅራኔው ይዞ ወደ ሀያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ላለመሸጋገርና ለማሻሻል የታለመው የጎርባቾብ «ፔሬስትሮይካ» ወይም የተሃድሶ ዴሞክራሲ ሶቬት ህብረትን ሊያፍረከርክ ችሏል:: (9) ከዚህ መከፋፈል የተረፉችው የሩሲያ ፌዴሬሺን «በቾቾን» ተቀዋሚዎች፣ ሌሎች ደግሞ በራሳቸው የውስጥ ችግሮች ተወጥረዋል::

በሶቬት ህብረት የተጀመረው የመከፋፈል አደጋ የሶሻሊስቱን ካምፕ ስላናጋው የቀድሞ የዩጎዝላቪያ ሪፓብሊክ ወደ አራት ትናንሽ አገሮች ተበጣጠሰች:: ቸኮዝላቫኪያም ከሁለት ተጎመደች:: በአካባቢያችንም ሶማሊያ በጎሳ ብጥብጥ ብትንትኗ ወጥቶ ለብዙ ጊዜ ማዕከላዊ መንግሥት የላትም:: ከኢትዮጵያም ኤርትራ ተገንጥላለች:: የሚቀጥለው ተራኛ ማን እንደሚሆን አይታወቅም:: እንግዲህ በሕገ መንግሥት አንቀፅ ላይ መጠቀሱ በራሱ መፍትሔ ሊሆን እንደማይችል ከኛም ሆነ ከሌሎቹ አገሮች ልምድ የታየ ነው:: አንዳንዶች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ታሪካዊ አመጣጥ እላይ የተጠቀሱትን አገሮች ስለማይመስል ለዚህ መሰል የከፋ የመከፋፈል አደጋ አትጋለጥም የሚለው አባባልም አያስኬድም:: የመከፋፍል አደጋ የማያሰጋ ከሆነ የማይጨበጥና የማይዳሰስ ደንብ ሕገ መንግሥት ውስጥ መደንቀር ለምን አስፈለገ? ይልቅ እላይ በተጠቀሱት ልዩ ልዩ አገሮች ያጋጠመውን በማገናዘብ አንድ ማጠቃለያ ማስቀመጥ ይቻላል:: ኢሕአዴግ ጊዜ ያለፈበትን የምስራቅ ፖለቲካ ቅሪት እንደ አዲስ በመልበስ <u>ሊያጌጥበት</u> ቢፈልግም «የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል» ብዙዎችን ለመከፋፈል ስለዳረገ ኢትዮጵያን አይጠቅማትም::

የሶሻሊስት ካምፕ ከተፍረከረከ በኋላ በብዙ አገሮች የመከፋፈል አደጋ ቢያጋጥምም ለውህደት ጋሬጣ የነበረው እንቅፋት ሲቀረፍ ሌሎች ተለያይተው የኖሩም ሊዋሃዱ ችለዋል:: ሁለቱ ጀርመኖችና ተለያይተው የኖሩት የመኖች ሊዋሃዱ የቻሉት ከሶቬት ህብረት ተፅኖ ከተላቀቁ በኋላ ነበር:: ታዲያ እኛስ የቱን እንመርጣልን ህብረት ወይስ መለያየት?

1.2 የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ

የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ፅንሰ ሃሳብ ምንጮች ሕገ መንግሥትና የሃይማኖት ፍልስፍናዎች ናቸው:: በዚህ የተነሳ ብዙ አገሮች እነኝህን መብቶችና ነፃነቶች በሕገ መንግሥታቸው አካተው ይገኛሉ:: ከተለያዩ አገሮች ሕገ መንግሥቶች ሌላ የተባበሩት መንግሥታትም ከ1948 እ.ኤ.አ. ጀምሮ የሰዎችን መሰረታዊ መብቶች ድንጋጌዎች በማውጣት አባል አገሮች ግዴታ እንዲገቡና እንዲያከብሯቸው ማድረጉ ይታወቃል:: በዚህ የተነሳ የሰብአዊ መብቶች እያደጉ ቢመጡም የነኝህን መብቶች መጣስም በተለያዩ አገሮች አጋጥሟል:: የተባበሩት መንግሥታት የ1948 እ.ኤ.አ. መሰረታዊ የሰዎች መብቶች ድንጋጌ ያወጣው ሒትለር ባስነሳው የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ስድስት ሚሊዮን አይሁዶችና 20 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝቦች ከተጨፈጨፉ በኋላ ነበር:: የዚህ ድንጋጌ ዋና ዓላማም ተመሳሳይ እልቂት እንዳይደገም ለመከላከል ነበር:: ሆኖም ከዚያ ወዲህ ሁለት ሚሊዮን ሕዝቦች በካምቦዲያ በፖልፖት ተፈጅተዋል፣ በዩጎዝላቪያ የዘር ማፅዳት ወንጀል ተፈፅሟል፣ በኢትዮጵያ በደርግ የቀይ ሽብር ተካሂዷል፣ በሩዋንዳ የሁቱና የቱትሲ መተላለቅ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነበር፣ ወዘተ.:: እነኝህ ሁሉ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች የተጣሱባቸው አገሮች ሕገ መንግሥት ነበራቸው::

በኢትዮጵያ ባለው የፌዴራል ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ከአንቀፅ 13-28 በሰፊው ተጠቅሰዋል:: (10) ነገር ግን እነኝህ ደንቦች የዜጎችን ያለአግባብ መብታቸውን መገፈፋቸውን፣ ለስርና ለግድያ መዳረጋቸውን፣ ተቃዋሚዎች ከፖለቲካው መድረክ መገለላቸውን፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች እውቅና መነፈጋቸውን ማስወገድ አልቻሉም:: ኢሕአዴግ ደርግን አባሮ አገሪቷን በተቆጣጠረበት ጊዜ ሕግን በማስከበር ስም ሰዎችን እየገደለ ለማስፈራሪያና ለመቀጣጫ በየመንገዱ ሬሳ አጋድሞ ይጥል እንደነበር አይረሳም:: (11)

3000 የሚሆኑ የደርግ ባለሥልጣኖችና የቀይ ሽብር አራማጆች በሰሩት ወንጀል በሕግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ከታሰሩ ብዙ ዓመታት አልፏቸዋል:: ነገር ግን የፍርድ ሂደቱ በጣም አዝጋሚና አሰልቺ በመሆኑ አንዳንድ የታሰሩ ግለሰቦች ከሚጠረጠሩበት ወንጀል ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል መረጃ ቢኖራቸውም የፍርድ ሂደቱ ጊዜ ስለፈጀባቸው በእስር ማቀዋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የጦቢያ መጽሔት የአምነስቲን ዘገባ ዋቢ በማድረግ በ1991 ዓ.ም. እንደዘገበው ለብዙ ጊዜ ታስረው የነበሩ ከ550 የሚበልጡ የደርግ ሰዎች «ክሳቸው ታይቶ ከአፈፃፀም ስህተት ነፃ መሆናቸው ተረጋግጧል::»(12) ሌሎችም በዚህ መልክ ነፃ ሊወጡ እንደሚችሉ አያጠራጥርም:: (13) አንዳንድ ጊዜ ነፃ ናችሁ ተብለው የተለቀቁም እንደገና ይታሰራሉ::

ሌላው ደግሞ ምንም እንኳን ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የዜጎች መብት አይደፈርም ቢባልም በየጊዜው ያለአግባብ የዜጎች መታሰር፣ መሰወርና በአደባባይ መረሸን ያጋጥማል:: የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ለስድስት ዓመታት ማለትም ከህዳር 1984 ዓ.ም. እስከ ህዳር 1990 ዓ.ም. የመዘገባቸውን የሰብአዊ መብቶች መጣስ ዝርዝር በመጽሐፍ መልክ አሳትሞ አውጥቷል:: (14) ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ጎላ ብለው መታየት የሚገባቸው ነበሩ::

- ዜጎች ክስ ሳይመሰረትባቸው ለብዙ ጊዜ በእስር መቆየት፣
- ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መታሰር፣

- ያለፍርድ ያለአግባብ ማቁሰልና መግደል፣
- ከሥራ ማባረርና ስርቶ መተዳደሪያ መንፈግ፣
- ቤት ንብረትን መንጠቅ፣ መዝረፍ፣
- ከቤታቸው ተወስደውና ታስረው የደረሱበት አለመታወቅ፣
- የንግድ ሥራ ፈቃድን ያለአግባብ መቀማት፣
- በሙያ ማህበራት ላይ ጣልቃ መግባት፣
- በመሬት ድልድል ስም የሚያርሱትን መቀማት፣
- እስረኞችን ማሰቃየትና
- በፖለቲካ ቡድኖች ላይ በደል መፈፀም ነበሩ::

ኢሰመጉ ለነኝህ ሁሉ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ ካቀረባቸው አሃዛዊ መረጃዎች መካከል 596 ሰዎች ያለፍርድ በኢሕአዴግ የፀጥታ ኃይሎች የተገደሉና 351 የቆሰሉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል::(15) ይህ ቁጥር የሚሸፍነው ለኢሰመጉ የደረሱትን ሪፖርት ብቻ መሆኑን መታወቅ አለበት:: ከዚህ ውጪ የቀረውን ቤት ይቁጠረው ከማለት በስተቀር መገመት አይቻልም:: በጎሳ ግጭትና በሌላም የተገደሉት በኢሰመጉ ሪፖርት የተጠቀሱ ቢሆንም በዚህ ቁጥር ውስጥ አልተካተቱም:: የግድያ ሰለባ ከሆኑት መካከል በ1989 ዓ.ም በጠራራ ፀሐይ የተገደለው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢሰመጉ አባል የነበረው አሰፋ ማሩ ይገኙበታል::(16)

የኢሕአዴግ መንግሥት የፖለቲካና የአስተሳሰብ ልዩነትን ከማስታረቅ ይልቅ በማስበርገግ እንደሚያምን በጊዜው በአገሪቷ ያለው የእስረኛ ቁጥር ይመሰክራል:: በአገሪቷ በሞላ ከ10000-13000 የሚገመቱ የመንግሥት ተቃዋሚ የፖለቲካ እስረኞች እንደነበሩ ጦቢያ መጽሔት የአምነስቲን ሪፖርት ምንጭ ጠቅሶ አቅርቦታል:: (17) የነፃ ፕሬስ ሕግ በመጣስ፣ ጋዜጠኞችን በማሰርና በማሰቃየት በዓለም ላይ በከፍተኛ ደረጃ ከሚወነጀሉት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ስትሆን የኢሕአዴግ አመራርም በነፃ ፕሬስ ጠላትነት ተፈርጆ ነበር:: (18)

የዜጎች ያለአግባብ ከሥራ መቀነስ፣ አንዳንዶቹም መባረርና መተዳደሪያቸውን ማጣት በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል:: (19) በመዋቀር ማስተካከያና በብሔር ብሔረሰብ ተዋፅኦ ስበብ ከተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቀነሱት ሠራተኞች በማህበራዊ ደህንነት («በሴፍቲ ኔት») እንዲታቀፉ ጥረት ቢደረግም የኑሮ ቀውስ ማስከተሉ አልቀረም:: ከዝቅተኛ ሠራተኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የዩኒቨርስቲ አውቀ ምሁራን በኢሠፓ አባልነት በማሳበብና ሌላም ልዩ ልዩ ምክንያቶች እየተፈለገላቸው የዚሁ ከሥራ የመባረር ሰለባ ሆነዋል:: (20) በአንፃሩ መንግሥት የማይመስሉትን ከሥራ ሲያባርር በምትካቸው የሚቀርቡትን አሰባስቧል:: የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በ1985 ዓ.ም. 42 ምሁራንን ሲያባርር ሌሎችን እንደ አዲስ ለመቅጠር መወሰኑ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነበር:: (21) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ነባር ሠራተኞችን እያባረሩ በሌሎች መተካት የተለመደ ድርጊት ሆኗል::

የመንግሥት ሠራተኞችን ከሥራ ለማባረር ወይም ለመቀነስ መንግሥት የተለያዩ ምክንያቶችን ተጠቅሟል:: በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያን የኤኮኖሚ እድገት ለማፋጠን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉትን ትርፍ አምራች ያልሆኑ አክሳሪ ድርጅቶች ወደግል በማዛወር ስበብ አላስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ከሥራ እንዲቀነሱ አድርጓል:: ለዚህ ጉዳይ የለጋሽ አገሮችም

ግሬት ነበረበት፡፡ በደርግ የሶሻሊስት ስርአት ያለአግባብ የተስገሰጉትን የመንግሥት ሠራተኞች ተሸክሞ ወደፊት መራመድ እንደማይቻል፣ የመዋቅር ማስተካከያም ማድረግ የግድ እንደሚያስፈልግ የዓለም ባንክና ሌሎች የኤኮኖሚ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ያስገነዝባሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የብሔር ብሔረሰብን አስተዋፅኦ ተመጣጣኝ ለማድረግ አንዳንድ የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ ተቀንሰዋል፡፡ ከብሔር ብሔረሰብ አስተዋፅኦ ስንኩል ምክንያት ያልተናነሰው በጡረታ ስበብ ያለአግባብ ከሥራ የተሰናበቱት ሠራተኞች ነበሩ፡፡ የአገራችን የጡረታ የእድሜ ክልል ጣራ ለሲቪል ሠራተኞች 55 ዓመት ቢሆንም በ45 ዓመታቸው ከ20 ዓመት በላይ አገልግላችኋል በሚል በጡረታ እንዲገለሉ ተገደዋል፡፡ በተለይም የኢሠፓ ንክኪ የነበራቸውና የብሔር አስተዋፅኦ የማይደግፋቸው ወገኖች ጡረታ እንዲወጡ ተደርገዋል፡፡ በአንድ ወቅት 45/20 የሚል ማስፈራሪያ በየመሥሪያ ቤቱ ሰፍኖ ወያኔ/ኢሕአዴግ የማይፈልገውን ሠራተኛ ለመቀነስ በሚገባ ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህ ዘዴ ከተወገዱም በኋላ እድሜያቸው 55 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ የጡረታ ክፍያም የተነፈጉ ይገኛሉ፡፡

እንግዲህ ነባር ሠራተኞችን በአዲስ ለመተካት የተለያዩ ምክንያቶች ቢቀርቡም አፈፃፀሙ ከባድ ጥርጣሬንና ተቃውሞን አስከትሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ያጋጠመው ትልቁ ተቃውሞ የተቀነሱትን ማን ተካቸው የሚለው አሳሳቢ ጉዳይ ነበር፡፡ በብሔር ብሔረሰብ አስተዋፅኦና በጡረታ አሳቦ የማይፈልጉትን በማግለል ለስርአቱ ቅርበት ያላቸው ብቻ የመንግሥት መዋቅሩን እንዲቆጣጠሩ ተደርጓል፡፡

አላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በተጨማሪ የኢሕአዴግ አስተዳዳር የምዕራቡን ዓለም «አባርና በሌላ ተካ» (Fire and hire) የሚለውን የአስተዳደር የማስፈራሪያ ዘይቤ በመከተል የመንግሥት ሠራተኞች በፍራቻ እንዲታዘዙና በተፅኖ ለስርአቱ እንዲያጎበድዱ ለማድረግ አመቺ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በዚህ የተነሳ ሠራተኛው (Civil Services) ሰጥ ለጥ ብሎ ሳይጎረብጠው ለስርአቱ ተገገር እንዲሆን የሚያጉረመርመውና ድክመት ያለበት እንዲባረር ተደርጓል፡፡ ይህንን ለማድረግ አንድ የነበረን ስርአት ጥሎ በሌላ የሚተካ መንግሥት የራሱ መመዘኛዎች ቢኖሩትም የራሱንም ድክመት መመርመር ነበረበት፡፡ ይህም ባለመሆኑ ቀድም ብሎ ለአንዳንድ ሠራተኞች መባረርና በሌሎች መተካት ምክንያቶች ተደርገው የተቆጠሩት ጥፋቶች በአዲሱም ስርአት ሲደገሙ ይታያል፡፡ በተለይ የሥራ አፈፃፀም ድክመት፣ ለጊዜው ፖለቲካ ጥላቻ ማንበባረቅ፣ አድላዊነት፣ በሥልጣን ብልግና፣ ሙስና፣ ጉቦኝነት፣ ወዘተ. የመሳሰሉት የህበረተሰባችን ድክመቶች በኢሕአዴግ ጊዜ ብቻ የተከሰቱ ሳይሆን ከበፊትም ጀምሮ የነበሩ ናቸው፡፡ የበፊቱን ብንተወው እንኳን ከኃይለሥላሴ ጊዜ ጀምሮ በየስርአቱ እያደጉ የመጡ የቢሮክራሲው ድክመቶች ናቸው፡፡ በየስርአቱ ምን ያክል በደርግም በኢሕአዴግም ጊዜ የሥልጣን ብልግና፣ የአድልዎ አሰራር፣ ሙስናና ጉቦኝነት እያደጉ እንደመጡ ይታወቃል፡፡ (22) (23) እንግዲህ እነኝህን በየስርአቱ እያደጉና እየተባበሱ የመጡ ችግሮች መቋቋም የሚቻለው የስርአቱ አራማጅ እራሳቸውን ሲቆጣጠሩና የተሻለ የቁጥጥር ዘዴ ሲቀይሱ እንጅ ግለሰቦችን በማግለል፣ ከሥራ በማባረር ወይም በማሰር አልነበረም፡፡ የስርአቱን በሽታ በስርአቱ ላይ በመዝመት ማስወገድ ይቻላል እንጅ በግለሰቦች በማላከክ ማሻሻል አይቻልም፡፡

መንግሥት በቀጥታ ከሚያዝባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውጪ በስቪል ማህበረሰቡ ላይ ተፅኖውን ለማሳረፍ ይሞክራል:: ጠንካራ የነበሩ የሙያ ማህበራት እንደ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ለስርአቱ ስላላጎበደዱ አመራራቸው ለስርና ለስደት ተዳርገዋል:: (24) አንዳንዶቹም አባሎቻቸውን በመከፋፈል ለኢሕአዴግ ታማኝ በሆኑ መሰል ድርጅቶች ተተክተዋል:: እዚህ ላይ የኢሕአዴግ ድርጅት ከሶሻሊስትና ከጎሳ አስተሳሰብ ያልፀዳ በመሆኑ የሙያ ማህበራትን ለመቆጣጠር በራሱ የሚመሩ የመምህራን ማህበር፣ የላብደሮች ማህበር፣ የሴቶች ማህበር፣ የወጣቶች ማህበር፣ ወዘተ. ለማቋቋም ሞክሯል:: በአሁን ዘመን እነኝህና ሌሎች የሙያና የስቪል ማህበረሰብ ክፍሎች የመንግሥትን አሰራር በሚቆጣጠሩበት ጊዜ ይህን መሰል እነሱን የመባረር አካሄድ ተቀባይነት የለውም:: ስለዚህ መንግሥት በምንም መልኩ በነሱ አደረጃጀት ላይ ከማገዝ በስተቀር እጁን ማስገበትና እንቅፋት መፍጠር የለበትም::

በፖለቲካ ድርጅቶችም ላይ ያጋጠሙት ችግሮች ምንም አለመተማመን አለመኖሩን ያመለክታል:: የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) የተቋቋመው ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የአማራ ተወላጆች በኦሮምያ ክልል በተለይም በሐረርና በአርሲ በኦሮሞ የብሔር ድርጅቶች አነሳሽነት ከተጨፈጨፉ በኋላ መሆኑ ይታወቃል:: መአሕድ የተመሰረተው በሰላማዊ መንገድ በመታገል የአማራውን ሕዝብ መብት ለማስከበር ቢሆንም የአመራሩ አባላት የትጥቅ ትግል ለማካሄድ በጎጃምና በደብረ ብርሃን ቅስቀሳ አካሂደዋል በሚል ታስረው ነበር:: በዚህም እስር የተነሳ የድርጅቱ ሊቀመንበር ወቅታዊ ህክምና በመነፈጉ ለሞት ተዳርጓል:: (25)

ኦነግ የወያኔ ተባባሪ ድርጅት እንደነበረ ቀደም ብሎ በምዕራፍ አንድ ተገልጿል:: ነገር ግን ፍቅራቸው ሲዘልቅ ስላልቻለ ወደ ጠብና ጦርነት አምርተዋል:: በርከት ያሉ የኦነግ አባላትም ታስረው ነበር:: (26) ኢሕአፓ ከኢሕአዴግ ጋር የቆየ ቁርሾ እንዳለው ይታወቃል:: የሁለቱ ጠብና ጭቅጭቅ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ እየጨመረ መጣ እንጅ እየቀነሰ አልመጣም:: ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት ከተነሱት ጉዳዮች ሌላ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ያጋጠሙት ችግሮች ምንድን ናቸው?

ደርግ ሊወድቅ አካባቢ የጊዜው ተፋላሚዎች ኢሕአዴግ፣ ኦነግና ሻዕቢያ በእንግሊዝ አገር በሔርማን ኮን አደራዳሪነት ባደረጉት ስብሰባ ኢሕአፓን ገለል አደረጉት:: በጊዜው ለዚህ የተሰጠው ምክንያት ተዋጊ የለውም የሚል ሲሆን አሁን ደግሞ እንደገና ኢሕአዴግ ሊወጋኝ መሣሪያ ከጨበጠ ድርጅት ጋር እርቅ አላደርግም ይላል:: ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠረ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም ባዘጋጀው ኮንፍራንስ ላይ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሳተፉ ሲጋበዙ ኢሕአፓ እንዳይገኝ ተከለከለ::

ሌላው ደግሞ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ከመቆጣጠሩ በፊት ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ ጎንደርና ጎጃም የትጥቅ ትግል ሲያካሂድ የነበረውን የኢሕአፓን ወታደራዊ ክንፍ በመውጋት አንዳንድ አባላቱን ማርኮ በእስር ካቆየ በኋላ በ1985 ዓ.ም. መፍታቱ ይታወቃል:: በዚህ ጊዜ ከታሰሩት መካከል የኢሕአፓ አመራር አባላት የነበሩት ፀጋዬ ገብረመድህን፣ ይስሐቅ ደብረፅዮን፣ በለጠ አምሃና ስጦታው መስፍን እስከ አሁን የት እንደደረሱ አይታወቅም በሚል ኢሕአፓ ይከሳል:: (27) ከዚያም ወዲህ ኢሕአዴግ የኢሕአፓን አባላት ከማሳደድ

ያልተቆጠበ መሆኑን የሚያሳየው በ1985 ዓ.ም. ገብረእግዚአብሔር ኃይለሚካኤልን አዲስ አበባ ከመግደሉም ሌላ (28) ሌሎች የተለያዩ አባላቱ ጭምር ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የት እንደደረሱ አለመታወቃቸውን ኢሕአፓ በየጊዜው ስሞታ ያቀርባል:: (29) ኢሕአፓ ታስሩብኝ ከሚላቸው አባላቱ መካከል እንደ ወ/ት አበራሽ በርታ የመሳሰሉትን የደረሱበት አለመታወቅ ኢሰመጉ በመግለጫው አውጥቶ ነበር:: (30) ከዚህ በተረፈ ኢሕአዴግ ኢሕአፓን ለመከፋፈልም እንደሞከረ ይታወቃል:: ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ ከኢሕአፓ ከድተው ከሱ ጋር በተቀላቀሉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በሚል ደጋፊዎቹ አማካኝነት የኢሕአፓ ወራሽ መስሎ ለመቅረብ ያደረገው ሙከራ ከሽፏል:: (31)

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ለማስፈን ከተፈለገ ሰላማዊ ውድድርን መቀበልና የመቻቻል ፖለቲካን ማዳበር የግድ ያስፈልጋል:: ይህ ከሁሉም ወገኖች የሚጠበቅ ጉዳይ ነው:: ባለፉት ሰላሳ ዓመታት በኢትዮጵያ የተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች በዴሞክራሲያዊ አሰራር ተቻችለው አብረው ለመራመድ የልምድ ማነስ ይታይባቸዋል:: ካለፈው ዘመን እንደወረስነው በፖለቲካው መድረክ ለብቻ ጎላ ብሎ ለመታየት አንዱ ሌላውን ለማጥፋት መሸረብ፣ የሌላውን ስም ማጥፋት፣ ተቀዋሚን እንደ ጠላት መመልከት፣ ሰላማዊ ውድድርን አለመቀበል፣ በኃይል እርምጃ መተማመን፣ ወዘተ. በስፋት የሚንፀባረቁ ድክመቶች ናቸው:: የሕብረ ብሔር ድርጅቶች የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶችን ጠባቦችና ከፋፋዮች አድርገው ይቆጥሯቸዋል:: የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶችም ሕብረ ብሔርተኞችን ራስ ወዳድና የነበረውን እንዳለ ለማቆየት የሚፈልጉ አድርገው ይመለከቷቸዋል:: ተቀራራቢ አቋም ያላቸውም ርስ በርሳቸው አይስማሙም:: ባጭሩ አንዱ የሌላውን መኖር ተገዶ ካልሆነ መቀበል አይፈልግም:: በሌላ መልኩ ሁሉም ያመኑበትን ዓላማ ለማሳካት የሕዝብ ድጋፍ ይፈልጋሉ:: አንዳንዶች የሕዝብ ድጋፍን ለማግኘት የኃይል እርምጃ ይጠቀማሉ:: ሕዝብ ጥቅሙን ሊያስከብርለት የሚችለውን የፖለቲካ ድርጅት ለይቶ ማወቅ ቢችልም በኃይል እርምጃ ተሰንጎ ስለተያዘ የማይፈልገውን ለመቀበል ይገደዳል:: በዚህ የተነሳ የፖለቲካው ውድድር የኃይል እርምጃ የተቀላቀለበት ሆኖ ቆይቷል:: ነገር ግን በዚህ መቀጠል አይቻልም:: ተወደደም ተጠላም ኦነግ የኢሕአፓን መኖር፣ ኢሕአፓ የኦነግን፣ ወያኔ የኢሕአፓን፣ ኢሕአፓ የወያኔን፣ መኢሕድ የኦነግን፣ ኦነግ የመኢሕድን መኖር፣ ወዘተ. መቀበል አለባቸው:: የማንኛውንም ድርጅት ማበብ ወይም መክሰም የሚወስነው የሕዝብ ድጋፍ በማግኘት ወይም በማጣት እንጅ በሌላ ሊሆን አይገባም::

1.3 የአስተዳደር ችግር

ኢትዮጵያ ውስብስብ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች ያላት አገር ስለሆነች ከተማከለ አሀዳዊ መንግሥት ይልቅ የፌዴራል አወቃቀር መመስረት ለችግሮቹ መፍቻ መፍትሔ የሚበጅ ተደርጎ ይቆጠራል:: ሆኖም የፌዴራል መዋቅር በራሱ የአንድ አገር ችግሮችን ይፈታል ብሎ መገመት ያዳግታል:: ብቸኛም አማራጭ ተደርጎ ሊቆጠር አይገባውም:: ምክንያቱም ብዙ በልማት የገፉ አገሮችም አሀዳዊ መንግሥት ስላላቸው:: ለምሳሌ በሥልጣኔ እድገታቸው የሚታወቁት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ስዊድን፣ ጃፓን፣ ወዘተ. አሀዳዊ

መንግሥት አላቸው። የኛን መሰል የብሔር ብሔረሰብ ፌዴሬሽን ባይሆንም አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ጀርመን፣ ስዊዘርላንድ፣ አውስትራሊያ፣ ናይጀሪያ፣ ወዘተ. የፌዴራል መንግሥት መስርተዋል። ከእነኝህ አገሮች መካከል ናይጀሪያ የፌዴራል መንግሥት መዋቅር ቢኖራትም እንደ ኢትዮጵያ በየጊዜው እየተተራመሰች ትገኛለች። በጎሳ ብጥብጥ፣ በሃይማኖት ልዩነት ስበብ፣ በሙስናና በወታደራዊ ኩደታ እንደተናወጠች ነው። ይህ የሚያመለክተው የፌዴራልም ሆነ አሀዳዊ መንግሥት አስተዳደር አስተማማኝ ሊሆን የሚችለው የዴሞክራሲ መሰረት ሲኖር ነው።

የፌዴራል መንግሥት በማዕከላዊና በክልል መንግሥታት መካከል የሥልጣንና የአስተዳደር ክፍፍልን የሚፈቅድ ተደርጎ ይቆጠራል። ከዚህ በመነሳት የኛ አገር ፌዴሬሺን ምን ይመስላል? የሥልጣን ክፍፍልንና የራስን በራስ አስተዳደርን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ በተግባር ያውላል ወይስ አያውልም? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ከአንቀፅ 45 ጀምሮ ስለ ፌዴራል መንግሥት አወቃቀር ያወሳል። የክልሎች አከላለል በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ ማንነትና ፈቃድ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ይገልፃል። (32) በኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦች ተዛንቀው ስለሚኖሩ ይህን መሰል አከላለል ሕዝብን ይከፋፍላል፣ አንዱን ወገን አስደስቶ ሌላውን ያስከፋል። ባጭሩ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ክልል የችግራችን መፍቻ ሊሆን ስላልቻለ ስድስት የተወሳሰቡ ችግሮችን አስከትሏል።

1. በአጎራባች ክልሎች መካከል የሚገኙ የሁለቱንም ክልል ቋንቋዎች ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች ያለፍላጎታቸውና ያለታሪካዊ አመጣጣቸው ተከፋፍለዋል፣ ከማይፈልጉት ጋር በኃይል ተዳብለዋል ይባላል። በዚህ የተነሳ ከጎንደር የፀለምት፣ የወልቃይት፣ የጠገዴና የሁመራ ሕዝብ ከወሎ ደግሞ በከፊል የራያ ቆቦና የወፍላ (የኮረም) ሕዝብ ወደ ትግራይ ክልል መደባለቅ የሕዝቡን ፈቃድ ተጠይቆ የተደረገ ነው ለማለት ያስቸግራል። በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው መሰረት በፈቃዳቸው ከትግራይ ጋር ለመደባለቅ መፍቀዳቸው ያጠራጥራል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በ1992 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ በጎንደር ልማት ላይ ያተኮረ ኤክስፖና ሲምፖዚየም በተደረገበት ወቅት ከተለያዩ አገሮች የተሰባሰቡት የአካባቢው ተወላጆች የኢሕአዴግ መንግሥት ከጎንደር ቆርሶ ያለአግባብ ወደ ትግራይ የደባለቃቸውን ቦታዎች እንዲመልስ ጠይቀው ነበር። (33) ይህን መሰል ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በይፋም ሆነ በድብቅ በሕዝብም ሆነ በተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች በየጊዜው ይቀርባሉ። ተመሳሳይ ችግሮች ተጎራባች በሆኑ ሌሎች ክልሎች በአማራና በኦሮምያ፣ በኦሮምያና በቤንሻንጉል፣ በኤሮምያና በሱማሌ፣ ወዘተ. ይታያሉ።

የሱማሌና የኦሮሞ ክልሎች በሚገናኙበት በባሌና በቦረና አካባቢዎች በተነሳው የይገባኛል ክርክር በ12 ወረዳዎች አስተዳደር ለመመሥረትና ምርጫም ለማካሄድ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር። በዚህ የተነሳ በ1986 ዓ.ም. ከምርጫ ቦርድ ሽምጋዮች ተልከው የሁለቱን ተጎራባች ሕዝቦች አነጋግረው ወረዳዎቹን ለማከፋፈል ሞክረዋል። በጣም የሚገርመው ይህንን ጉዳይ ለመፍታት የተላኩት የምርጫ ቦርድ ሠራተኞች ሕዝቡን ሲያነጋግሩ የሁለቱንም ወገን ቋንቋዎች እንዳይናገሩ በስማ በለውና በአስተርጓሚ እንዲወጡት ተገደዋል። ይህም የተደረገው የአንዱን ቋንቋ ቢናገሩ ሌላው ተደላብኝ ብሎ እንዳያኮርፍና እንዳይቀየም ለጥንቃቄ ነበር። ከምርጫ ቦርድ ከተላኩት መካከል አንድ ኦሮምኛ

ተናጋሪ የነበረ ግለሰብ አስተርጓሚው የፈጠረውን ስህተት አርሞ በኦሮምኛ በመናገሩ የሱማሌው ወገን ተደላብኝ በማለት በተነሳው ግርግርና የተኩስ ልውውጥ የዘጠኝ ሰዎች ሕይወት ሊያልፍ ችሏል:: በዚህ የተኩስ ልውውጥ የፀጥታ አስከባሪዎች ሁኔታውን መቆጣጠር ቢያቅታቸውም በስህተት በኦሮምኛ የተናገረውን የምርጫ ቦርድ ሠራተኛ መልዕክተኛ ከአካባቢው ይዘው በመውጣት ሕይወቱን ለማዳን ችለዋል:: (34)

2. የክልሎች አከፋፈል በሕዝብ አሰፋፈርና በቋንቋ ማንነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያስገነዝበውን የሕገ መንግሥቱን መሰረታዊ የብሔር ብሔረሰብ መነሻ በአንዳንድ ክልሎች ተጥሶ ይገኛል:: በአንዳንድ ክልሎች ካሉት ነዋሪዎች መካከል ብልጫውን የሚይዙት ተወላጆች ቀርቶ የአነስተኛ ተወላጆች ክልል ተፈጥሯል:: የክልሉ መኖርና አስተዳደሩም በሕዝብ ቁጥር አነስተኛ የሆንትን ተወላጆችን ለመጥቀም የታቀደ ይመስላል:: ሕገ መንግሥቱ ለእንዲህ አይነት መፋለስ ምን ትርጉም እንደሚሰጠው ግልፅ አይደለም:: ምናልባት ቦታውን በቅድሚያ የያዙት እነሱ ስለሆኑ አነስተኞችም ቢሆኑ የነሱ ክልል የግድ ያስፈልጋል የሚባል ከሆነ በሌላም አካባቢ የታሪክ ጥያቄ ሊያስነሳ ስለሚችል የማያሻማ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል::

ከክልልም ዝቅ ብሎ ሌሎች የአስተዳደር መዋቅሮች ሲመረመሩ ተመሳሳይ ችግሮች የሚንፀባረቁበት ሆኖ ይገኛል:: በአንዳንድ ክልሎች የንዑሳን ብሔር ብሔረሰቦችን መብቶች ለማስጠበቅ ሲባል በዞን ደረጃ እንዲወከሉ ሲደረግ በሌላው ግን ሁኔታው አያወዛገበ ይገኛል:: ለምሳሌ ያክል በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ውስጥ በሕዝብ ብዛት በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የወልይታ ሕዝብ የራሱን ክልል እንዲኖረው ብዙዎች ቢመኙም የዞን አስተዳደር እንኳን እንዲመሰርት ለብዙ ጊዜ አልተፈቀደለትም ነበር:: በሌላ መልኩ በአማራው ክልል ከሚገኘው ሕዝብ ቁጥር በአነስተኛ ደረጃ የሚገኙት ሃዊያና ኦሮሞዎች የራሳቸው የአስተዳደር ዞን ሲኖራቸው በተመሳሳይ በማናፀር በሌሎች ክልሎች ተዛንቀው የሚኖሩት በርካታ አማሮች የዞን አስተዳደር መመስረት ቀርቶ መብታቸው ሳይከበር ከአንዳንድ አካባቢዎች ነፍጠኛ በሚል ውጡ የሚባሉበት ጊዜ አለ:: ለአንድ ችግር አንድ የመፍትሄ ሃሳብ ሲቀርብ ቀድም ብሎ ከነበረው የተሻለ ሆኖ መቅረብ ይጠበቅበታል:: በፊት የተሰሩ ስህተቶችም መደገም የለባቸውም:: ያለፉትን የገገር መደቦች አስታኮ «ነፍጠኛ» እየተባለ የሚስነዘረው አሉባልታ ከአማራው ክልል ውጪ የሚኖረውን አማራ በጠቅላላ ጨቋኝ አያደርገውም::

3. የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ የሆኑት የደቡብ ሕዝቦች በአንድ ክልል መዳመራቸው ግማሹን ቢያስደስትም አንዳንዶችን አስከፍቷል:: በደቡብ ክልል ውስጥ ከተሰባሰቡት መካከል አንዳንዶች ታሪካዊ አመጣጣቸው፣ የኢኮኖሚ ግኑኝነታቸውና የጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ከደቡብ ጋር የሚያቀራኛቸው ሆኖ ሳላገኙት የራሳቸው ክልል እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ:: (35) በተለይም በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች መካከል በሚደረገው የልማት ማበላለጥ የተነሳ አንዳንዶች የራሳቸው ክልል እንዲኖራቸው ጥያቄዎች አንስተው ነበር::

አንድ ቋንቋም በሚናገሩ የአንድ ክልል ሕዝቦች መካከል ውስብስብ ችግሮች አጋጥመዋል:: የክልሉ አከፋፈል የአስተዳደራዊ ቦታዎችን ርቀት ጭራሽ ያላገናዘበ በመሆኑ ብዙዎች ያማርራሉ:: በዚህ የተነሳ አንዳንድ አካባቢዎች ከክልሉ የአስተዳደር ከተማ ያላቸው ርቀት ሕዝቡን ለችግር ዳርጎት ነበር:: የሰሜን ሸዋ ሕዝብ አንዳንድ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ባህር

ዳር ድረስ ስመሄድ መገደድ፣ የኤልከሬ ሱማሌዎች ጅጅጋ ድረስ መጓዝ፣ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ መቀሌ ድረስ መሄድ፣ የወለጋ ሕዝብ የኦሮምያ ርዕስ ከተማ የሆነውን አዳማን በቅርብ ርቀት መመልከት፣ የጉራጌ ሕዝብ አዋሳ ድረስ መጓዝ፣ ወዘተ. የተገልጋዩን ጊዜና የገንዘብ አቅም የሚፈታተኑ ናቸው:: ከክልልም ዝቅ ብሎ በዞንም ደረጃ ቢሆን በአንዳንድ ዞኖች ተመሳሳይ ችግሮች ይንፀባረቃሉ:: የሰሜን ኦሞ ዞን 24 ወረዳዎች የሚያቅፍ ትልቅ ዞን በመሆኑ ከርዕስ ከተማው ከአርባ ምንጭ በርቀት የሚገኙት የወላይታ ወረዳና የሌሎችም ቦታዎች ነዋሪዎች ተመሳሳይ ፈተና እንዳለባቸው መገመት አያዳግትም::

4. በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የብሔር ብሔረሰብ ፌዴሬሺን በአገራችን የቆዩ ችግሮችን ሊፋታ አልቻለም:: አጎራባች በሆኑ ሕዝቦች መካከል አሁንም አልፎ አልፎ ግጭቶች ይከሰታሉ:: በጉጂና በጌድኦ ሕዝቦች መካከል በ1990 ዓ.ም. በተካሄደው የጎሳ ግጭት ከ3000 በላይ የአካባቢው ሕዝብ እንደሞተ የተነገረው የተጋነነ ቢመስልም የብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት፣ ቤት ንብረት መውደምና በችግሩ ምክንያት ከአካባቢው መሰደድ ማስከተሉ ጥርጥር የለውም:: (36) በሌሎች ቦታዎችም በሐረሪና በኦሮሞ፣ በሱማሌና በኦሮሞ፣ በኦሮሞና በቤንሻንጉል ሕዝቦች መካከል አለመግባባት አጋጥሟል:: (37) በአንድ ክልልም ውስጥ በሚገኙ በአንዳንድ የታጠቁ ቡድኖች ግፊት የተፈጠረው ግጭት አሰቃቂ ግድያዎችና የቤት ንብረት መውደም በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በመተከል አስተዳዳር፣ በከፋና በኢሉባቡር፣ በደቡብ ሸዋ በሐይቆችና በታጅራ፣ በሐረርጌ፣ በጋራ ሙለታ፣ በቦረናና በያቤሎ አጋጥመዋል:: (38)

5. ማንኛውም ብሔሮችና ብሔረሰቦች በቋንቋቸው የመማር፣ ባህላቸውን የማሳደግና እራሳቸውን የማስተዳደር ሙሉ መብት አላቸው ቢባልም የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ተደባልቀው በሚኖሩበት አካባቢ እነኝህን በሥራ ላይ ለማዋል በአንዳንድ ክልሎች ችግር አጋጥሟል:: በኦሮምያ ከተሞች እንደ ናዝሬትና ሻሻመኔ ባሉት ቦታዎች ወላጆች ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ መጠየቃቸው የአካባቢውን ሥልጣን እንደመጋፋት ሳይቆጠር መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባ ነበር:: (39) የወላይታ ሕዝብ የወጋጎዳን ቋንቋ (የወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋና ዳውሮ ቅልቅል ቋንቋ) ተቃውመው ልጆቻቸው በሚያወቁትና በሚገባቸው የወላይታ ቋንቋ እንዲማሩ ያቀረቡትን ጥያቄ መጋፋት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ከመጣስ የሚቆጠር ነበር:: (40)

6. ብዙ ተቀዋሚ የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶች እንደሚያማርሩት የኢሕአዴግ ድርጅት የራሱ ተለጣፊ የሆኑ ታዛኝ ድርጅቶችን በማደራጀት ሌሎችን ከሥልጣንና ከአስተዳደር ተሳትፎ ያገላል:: (41) በብዙ ክልሎች በእውነተኛ ተቃዋሚዎችና ኢሕአዴግ ባዘጋጃቸው ድርጅቶች መካከል አግባብ ያልሆነ ሽኩቻ ይካሄዳል:: በዚህ የተነሳ አንዳንድ የተቀዋሚ ድርጅቶች አባላት ለእስር ለስደትና ለግድያ ተዳርገዋል:: (42) በመሰረቱ ኢሕአዴግ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮምያ፣ በደቡብ ህብረትና በአዲስ አበባ የሚንቀሳቀሱ እህት ድርጅቶች ግንባር ስለሆነ በእነዚህ ክልሎች በቀጥታ በምርጫ ይሳተፋል:: እነዚህ አካባቢዎች ደግሞ የአገሪቷን ሕዝብ ቁጥር ከ85% በላይ ይይዛሉ:: ይህም አልበቃ ብሎት በሌሎች ክልሎችም የሱን አቋም የሚደግፉ ነገር ግን በይፋ ያልተቆራኙ የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶች አዘጋጅቷል:: እንግዲህ ምርጫ በየትም ክልል ሲካሄድ የኢሕአዴግ አባል ወይም የሱ ተለጣፊ የሆነ ተባባሪ

ድርጅት አባል የሆነ ግለሰብ ይመረጣል:: በዚህም የተነሳ አገሪቷን በሙሉ ይቆጣጠራል:: ይህም የሚያመለክተው ከኢሕአዴግ ቁጥጥር ውጪ የራስን እድል በራስ መወሰንና ማስተዳደር ይካሄዳል ለማለት እንደማያስደፍር ነው::

በየትም ክልል ለኢሕአዴግ ወዳጅ ከሆኑት ድርጅቶች ውጪ በምርጫ አሸንፎ የሚያስተዳድር የለም:: ይህ መሰረታዊ ችግር ለሌሎች ውስብስብ ችግሮች ምንጭ ሆኗል:: በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግሥታት በሰው ኃይል አደረጃጀት፣ በፀጥታ አጠባበቅ፣ በልማት እንቅስቃሴና በሌሎችም የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበራዊ ሕይወት ዘርፎች ከኢሕአዴግ ድርጅቶች ቁጥጥር ውጪ ሌሎች አይሳተፉም:: የአገራችንን የቆየ ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ስንመረምር ኃይል ያለው ማስገበሩ፣ የሚስማማውን መሾሙና መሸለሙ የነበረ ነው:: ታዲያ ከዘመነ መሣፍንትና በኋላም ከመጣው በኃይል የማስገበር ስርአት አሁን ያለውን ዘመናዊ ሕገ መንግሥትና ዘመናዊ አስተዳደር ስንመዝነው ልዩነቱ የት ላይ ነው?

የአገራችን የአስተዳደር ችግር ሥልጣን ጠቅልሎ በመያዝ ላይ ብቻ አያበቃም:: ሥልጣን ያለው ሁሉን ነገር የመቆጣጠር ኃይል አለው:: ሥልጣኑን የሚያሽከረክረው ክፍል በኤኮኖሚ ልማት ልዩነት ሊፈጥር፣ በክልሎች መካከል ማበላለጥ ሊያደርግና የማይፈልገውንም ሊያዳክም ይችላል:: የኤኮኖሚ እድገትን ለማምጣት የኢሕአዴግ መንግሥት የነፃ ውድድር መሰረት ቢጥልም፣ የአገርና የውጪ ኢንቨስተሮችን ቢያደፋፍርም በአጅ አዙር ራሱ እየገባ ወድድሩን ሲያዛባው ይታያል:: (43) የአገሪቷን ኤኮኖሚ ለማሻሻል የወሰደው እርምጃ ያሚደነቅ ቢሆንም የሰራውን ራሱ ስለሚያፈርሰው ጥረቱን ከንቱ አድርጎታል:: በነፃ ውድድር ስም የመንግሥት ድጋፍ የተቸራቸው የንግድና የልማት ተቋማት ሁሉንም ለመቆጣጠር እየጣሩ ናቸው:: ከኢሕአዴግ ጋር ግኑኙነት ያላቸው በብዙ ሚሊዮን ብር የሚንቀሳቀሱ ከ23 በላይ የንግድና የልማት ድርጅቶች በአዲስ አበባ፣ በመቀሌና በሌሎች ከተሞች ተመዝግበው ይገኛሉ:: (44) እነኝህ የፖለቲካ ድጋፍ ያላቸው የንግድና የልማት ድርጅቶች ኤኮኖሚውን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን ለኢሕአዴግ ፖለቲካ ዋና መሣሪያ በመሆን ያገለግላሉ:: በእርሻ ልማትና በማዳበሪያ ንግድ ላይ የተሰማሩት ገበሬውን ለምርጫ ማባበያና ማስገደጃነት ሲያገለግሉ ሌሎች ደግሞ የሚፈልጉትን አካባቢ ለማልማትና ለስርአቱ ታማኝ ለሆኑ ግለሰቦች ሥራ ለመፍጠር ይውላሉ:: በዚህ አካሄድ በመሣሪያ ኃይል የተደገፈው የበላይነት ወደ ኤኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት እየተለወጠ ይገኛል::

እነኝህ የፖለቲካው ድጋፍ የተሰጣቸው የንግድና የልማት ድርጅቶች የተቋቋሙት ለተቋቋሙበት አካባቢ ሕዝብ ልማትና በትግሉ ጊዜ ጉዳት ለደረሰባቸው መደጎሚያ በሚል ሽፋን ነበር:: የኢሕአዴግ ድርጅት እንደሚለው እነኝህ የንግድና የልማት ተቋማት በትጥቅ ትግሉ ጊዜ በተገኘ ገንዘብ የተመሰረቱ ስለሆነ የድርጅቱ ንብረት ሳይሆን የታጋዮች መሆናቸውን በማስመሰል ይናገራል:: በመሰረቱ ይህ አባባል ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም:: የኢሕአዴግ ድርጅት የታገለው አንድን ጨቋኝ ስርአትና በጊዜው የነበሩትን አምባገነን መሪዎች ለመጣል እንጅ የኢትዮጵያን ሕዝብ አይደለም:: በጦርነቱ ወቅት የኃይል ጡንቻን በመጠቀም ንብረት ማካበት አይቻልም:: ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት በጦርነቱ ጊዜ የተገኘ ንብረት በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጡራ ሐብት እንጅ የአንድ አካባቢ ሕዝብ ንብረት ብቻ አይሆንም:: በኢትዮጵያ ስም በመታገል ሐብት ማግበስበስ አይቻልም:: ስለዚህ በትግል ጊዜ

ያፈሩት ወይም የዘረፉት ማንኛውም ሐብትና ንብረት ከዚያም ወዲህ የተገነቡት ተቋማት በሙሉ ወይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ አለበለዚያም መፍረስ አለባቸው:: በአንፃሩ በትግሉ ጊዜ ጉዳት የደረሰባቸውን የመንከባከብ ኃላፊነት የኢትዮጵያ መንግሥት ጉዳይ እንጅ የኢሕአዴግ ድርጅት አይደለም::

ከልማት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ክልሎች ወደፊት ሲገሰግሱ ኋላ ቀር የሚባሉት የአፋር፣ የሱማሌ፣ የቤንሻንጉል፣ የጋምቤላና ሌሎች ክልሎች ተገቢውን ትኩረት አልተሰጣቸውም:: (45) በደርግ ጦርነትና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ወደኃላ የቀሩት ከሌሎች ጋር መስተካከል አለባቸው የሚለው አባባል ባያከራክርም አንዳንዶች መከተል የሚችሉትና የሚራመዱት አሁን በልማት ቅድሚያውን የያዙት የት ሲደርሱ እንደሆነ አይታወቅም:: በተጨማሪም ሁሉም ክልል እኩል የተማረ የሰው ኃይልና እኩል የተፈጥሮ ሐብት የላቸውም:: የለብ ለብ ማሰልጠንም ሊያጠናክር የሚችለው የሰው ኃይልን ሳይሆን የፖለቲካ ደጋፊን ነው:: በዚህ የተነሳ በስመ ክልል እራሳቸውን ችለው መተዳደርና በልማቱም ማዝገም አለባቸው የሚለው መስፈርት አያመጣም:: ስለዚህ በክልሎች መካከል የግድ የተመጣጠነ እድገት ያስፈልጋል::

1.4 የ1987 ዓ.ም. ምርጫ ችግር

ማንም ድርጅት ወይም ግለሰብ በአገሪቷ የመንግሥት ሥልጣን ላይ ሊቀመጥ የሚችለው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ተደርጎ የአብላጫውን የሕዝብ ድጋፍ ካገኘ ብቻ ነው ይላል ሕገ መንግሥቱም ሆነ የምርጫ ሕጉ:: ይህንን ለማስፈፀም የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/1987 ከሕገ መንግሥቱ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ታውጇል:: (46) በተግባር የታየው ግን ከዚህ የተለየ ነበር:: በ1987 ዓ.ም. በተካሄደው ምርጫ የኢሕአዴግ ድርጅት ከታማኝ መሰል ድርጅቶች፣ ጥቂት ተቃዋሚዎችና የግል ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድሮ በየክልሉ ከ99% በላይ የድጋፍ ድምፅ በማግኘት አሸንፎ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ቻለ:: (47) በጣት ከሚቆጠሩ የግል ወይም የሌላ ድርጅት ተመራጮች በስተቀር በጠቅላላው የፓርላማ ተወካዮች የኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ሆኑ:: በክልሎችም ቢሆን ሁኔታው ከዚህ የተለየ አልነበረም:: አብዛኛውን የክልል ምክር ቤቶችና የሥልጣን ተዋረድ የሞሉት የኢሕአዴግ አባላትና የሱ ወዳጅ ድርጅቶች ነበሩ:: በዚህ ውጤት የተነሳ በአገሪቷ ኢሕአዴግን የሚወዳደር ጠንካራ ተፎካካሪ ድርጅት እንደሌለ ተቆጠረ:: በሌላ መልኩ በምርጫው ኢሕአዴግ ያገኘው የድጋፍ ድምፅ ብዛት ሲገመገም አንድ ድርጅትን በሥልጣን ላይ ለማስቀመጥ የተካሄደ እንጅ ተቀዋሚ እንዳልነበረና በድርጅታዊ አሰራር የተሸበበ እንደነበረ ያመለክታል::

በምርጫው ጠንካራ ደጋፊ እንዳላቸው የሚታወቁት የኦነግ፣ የመአሕድ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት ፓርቲ፣ የኢዴኃቅና የደቡብ ህብረት ድርጅቶች አልተካፈሉም ነበር:: ከእነኝህ ድርጅቶች መካከል አንዳንዶች የኢሕአዴግን የፖለቲካ መንገድ የማይቀበሉ፣ ግማሾቹ አውቅና የተነፈጉና ሌሎች ደግሞ የምርጫውን ትክክለኛነት የሚጠራጠሩ ነበሩ:: ከኢሕአዴግ ቀጥሎ ምርጫውን በማዳመቅ የሚበዙት የግል ተወዳደሪዎች ነበሩ:: የግል

ተወዳዳሪዎች መብዛት የጋራ ፕሮግራም ስለሌላቸው ቢመረጡም ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም፣ መንግሥትም በግላቸው መመስረት ያዳግታቸዋል:: በጥቂት የግል የፓርላማ ተመራጮች እንደታየው ተቋውሞአቸውን ከማሰማትና ከመንጫጫት አያልፉም:: የዚህን መሰል ሁኔታውን የማይቀይር ጉንጭ አልፋ የፓርላማ ውስጥ ሙግት በንጉሡ ዘመን የሚመረጡ የፓርላማ ተወካዮችም ያሰሙ ነበር::

ምንም እንኳን የምርጫው ሕግ ባይፈቅድም አንዳንድ ያልታወቁ የግል ተወዳዳሪዎች ስውር የኢሕአዴግ ወይም የሌላ ድርጅቶች አባላትም የማይሆኑበት ምንም ምክንያት የለም:: ይህም ማለት በግል ተመራጭ ስም የአንዳንድ የፖለቲካ ቡድን ደጋፊዎች ሊመረጡ ይችላሉ ማለት ነው:: ሌላው ደግሞ በምርጫው የተሳተፉ አነስተኛ ድርጅቶችም ቢሆኑ በክልልም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ አንድም መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል ብዛት ያላቸው ተወዳዳሪዎች አላቀረቡም ነበር:: ይህም የሚያሳየው ጠንካራ ደጋፊ የሌላቸው ድርጅቶቸም ሆነ የግል ተወዳዳሪዎች በምርጫው ተሳተፉም ቀሩም ሁኔታውን መቀየር አይችሉም:: ያምርጫ አዳማቂ ከመሆን አያልፉም:: እንግዲህ እውነተኛ ነፃ ምርጫ ተደርጎ በአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ደጋፊ ያላቸው ድርጅቶች እስካልተሳተፉ ድረስ የ1987 ዓ.ም. ምርጫ ሁኔታ ይቀጥላል::

ከጠንካራ ተፎካካሪዎች ያለመኖር ባሻገር የ1987 ዓ.ም. ምርጫ ተክክል እንዳልተካሄደና በአፈፃፀሙ አድልዎ እንደነበረበት መአሕድ ከዘረዘራቸው ችግሮች መካከል፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ተቀዋሚ ድርጅቶች እንዳይንቀሳቀሱና ከሕዝብ እንዳይገናኙ መከልከል፣ የተቀዋሚ ድርጅቶች ጽ/ቤቶችን በፀጥታ አስከባሪዎች ማዘጋት፣ ካርዶችና የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባብ አለማደል፣ በነዋሪነት መታወቂያ ስበብ እጩ ተወዳዳሪዎችን ማንገላታት፣ በኢሕአዴግና በሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ማድረግ፣ ድምፅ በሚሰጥበት ቀን አንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ከተፈቀደው ሰዓት ቀደም ብለው እንዲዘጉ ማድረግ፣ ታዛቢዎች በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች እንዳይገኙ መከልከል፣ በድምፅ ቆጠራ ማጭበርበር፣ የምርጫ ቦርድና ሌሎችም ምርጫውን የሚያስፈፅሙት አካላት ወገናዊ መሆን ይገኙባቸዋል:: (48)

የምርጫ ቦርድም ከምርጫው ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ በደሎችን በቸልታ መመልከቱን ወቀሳ ቀርቦበታል:: በጊዜው የስልጤ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ አባላት ሲታሰሩ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ የምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ደጋፊዎች ሲሰቃዩና ከምርጫ ሲታገዱ፣ የሮቢ እጩ ተወዳዳሪ ሲገደል፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት ፓርቲ ጽ/ቤቶች ሲዘጉ እርምጃ አልወሰደም ነበር:: (49) በክልል ምርጫ በደል የደረሰባቸው የጋምቤላ ዴሞክራሲያዊ ኮንግረስ አባላት ወደ ፌዴራል መንግሥትና የምርጫ ቦርድ ቢያመለክቱም ችግራችሁ የክልል የውስጥ ጉዳይ ነው በሚል መፍትሔ ሳያገኙ ቀርተዋል:: (50) የአውሮፓ የእርዳታ ለጋሽ አገሮች የምርጫ ተከታታይ ቡድን በምርጫው ጊዜ በከተማና በገጠር መካከል ልዩነት መኖሩን፣ ከኢሕአዴግ ውጪ የሆኑት ተወዳዳሪዎች በገጠር ቅስቀሳ ማካሄድም ሆነ በዕጩነት ለመቅረብ የድጋፍ ፊርማ ለማሰባሰብ አለመቻላቸውን፣ ገበሬዎች ተመዝግባችሁ በምርጫው ካልተሳተፋችሁ ማዳበሪያ አታገኙም በሚል መገደዳቸውን፣ ተወዳዳሪዎች ወይም እነሱ የወከሏቸው በድምፅ ቆጠራ ጊዜ እንዳይገኙ መከልከላቸውንና በቅድሚያ ድምፅ ለመስጠት

ያልተመዘገቡ ሰዎች በምርጫ ቀን ድምፅ እንዲሰጡ መደረጋቸውን ሪፖርት አቅርቧል:: (51) መሬት በመንግሥት ባለቤትነት መያዙም ኢሕአዴግ ገጠሩን እንዲቆጣጠርና በምርጫ ጊዜ ከፍተኛውን ድምፅ እንዲያገኝ ረድቶታል::

ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት የ1987 ዓ.ም. የምርጫ ጊዜ ችግሮች በመነሳት ምርጫው ሕገ ወጥ የሆነ የአድልዎና የድርጅታዊ አሰራር እንደነበረበት መገመት አያዳግትም:: ኢሕአዴግ የነበረውን መንግሥታዊ መዋቅር፣ የቀበሌና የገበሬ ማህበራት፣ የመገናኛ ብዙኃን በሙላ አሸናፊ ለመሆን ለራሱ ተጠቅሞበታል:: ሌላው ቀርቶ የኢሕአዴግ ተወዳዳሪዎች በቀበሌና በገበሬ ማህበራት አማካኝነት፣ ሕዝብ ፊት እየቀረቡ መግለጫ ሲሰጡና ሲገመገሙ ሌሎች ይህን እድል ተነፍገዋል:: በቋንቋ ሰዎችን ለማታለል ካልተፈለገ በስተቀር በምርጫ ጊዜ የሚደረግ ግምገማና በመገናኛ ብዙኃን ከሥራ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ መግለጫ የምረጡኝ ዘመቻ አካል ነበሩ:: ለኢሕአዴግ እጩ ተወዳዳሪዎች የድጋፍ ፊርማ የሚያሰባስቡላቸውና ቅስቀሳ የሚያካሂዱላቸው የመንግሥት ሠራተኞችና የቀበሌና የገበሬ ማህበራት ጽ/ቤት ሠራተኞች ነበሩ:: መንግሥታዊ መዋቅሩ እንዳለ የምረጡኝ ዘመቻ አቀነባባሪ ነበር ማለት ይቻላል::

እንግዲህ ስለ 1987 ዓ.ም. ምርጫ ማለት የሚቻለው ምርጫ መካሄዱንና የምርጫ አስፈፃሚዎችም መኖራቸውን እንጅ ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ በሆነ መልክ ተካሂዷል ለማለት አያስደፍርም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግም በኢሕአዴግም ይህን መሰል የማታለያ ድርጅታዊ አሰራር ሰልችቶታል:: ለሕዝብ አስተያየትና ብሶት ምንም ተጠያቂነት የሌለው ምርጫ ማካሄድ ዋጋ የለውም:: ሕዝብ የማይፈልገውን በማስገደድና በማስፈራራት ወይም በማባበል ድጋፍ ስጥ እያሉ ማጉላላት መቆም አለበት:: ደጋፊ ካድሬዎችን በሕዝብ ስብሰባዎች ሰግስጎ በማስገባት የሕዝብ ድጋፍ እንዳለ ለማስመሰል ማታለል እስከ መቸ ይቀጥላል? ሌላው እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት የምርጫ ቦርድ ራሱ የምርጫ አስፈፃሚና ራሱ የምርጫ ጉድለቶችን ማረሚያ ውሳኔ ሰጪ መሆኑም ምን ያክል አስተማማኝ ሊሆን እንደሚችል መገመት ያዳግታል:: ከ1985 ዓ.ም. በፊት የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የምርጫ ጉድለቶች ማረሚያ ቦርድና የምርጫ ኮሚሽን የተለያየም ተደጋጋፊም ሥልጣን ነበራቸው:: በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የምርጫ ጉድለቶች ማረሚያ ቦርድ ከተለያዩ ክልሎችና ግለሰቦች ስለ ምርጫ የቀረበለትን ተቃውሞዎች መርምሮ የሰጠበትን ውሳኔዎች ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት አድርጎ ነበር:: (52) ከዚህ በኋላ ስለ ምርጫ አፈፃፀምም ሆነ ስለ አጋጠሙት ጉድለቶች ሪፖረት ማቅረቡን የምርጫ ቦርድ ጠቅልሎ ይዞታል::

አንዳንድ እውቅና የተነፈጋቸው ድርጅቶችን በሚመለከት ከኢሕአዴግ ባለሥልጣኖች በኩል የሚሰነዘሩት ትችቶችም አግባብነት አልነበራቸውም:: ለምሳሌ ከኢሕአፓና ከሌሎቹም ጋር ሊያቀራርባቸው ያልቻለው ያለፈው ታሪካቸው መሆኑ እየታወቀ ኢሕአዴግ መሣሪያ ካነሱ የፖለቲካ ቡድኖች ጋር አብሬ መስራት አልችልም የሚል ሰበብ መስጠቱ የማይፈልገውን ለማግለል የታቀደ ዘዴ መሆኑን ያረጋግጣል:: በመሰረቱ ኢሕአዴግ አሁን የመንግሥት ሥልጣን ይዞ ሰላምና መረጋጋት ፈጥሬአለሁ በሚልበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ወገኖች መሣሪያ ጨብጠው በነበሩበት ጊዜም ፍቅር አልነበራቸውም:: እነዚህ ለመዋጋት መሣሪያ ጨብጠዋል የተባሉት ድርጅቶች በሰላም ለመታገል

ቃል ቢሰጡም እርቅ ሊወርድ አልቻለም። (53) ምክንያቱም ለብዙ ጊዜ በጠብና በጭቅጭቅ የኖሩ ቡድኖችን ለእርቅ የማይጋብዝ የአገሪቷን ደንብና ሕገ መንግሥት አክብረው «የጨዋታው ሕግ በሚፈቅደው መሰረት» በፖለቲካው መሳተፍ ይችላሉ ሲል በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አቋሙን በማፅናቱ መቀራረብ አልተቻለም ነበር። (54) ይህ አባባል በሁለቱ መካከል የነበረው የፖለቲካ ልዩነት ከሕገ መንግሥቱና ከጨዋታው ሕግ ጋር የተቆራኘ መሆኑን የዘነጋ ይመስላል። እንዲያውም እኔ የወለድኩትን ልጅ ሳምልኝ የእንተን አታሳየኝ መሆኑን በመንግሥት በኩል የቆሙት ወገኖች አልተገነዘቡትም ነበር። ይህንን አወዛጋቢ የሆነ ሕገ መንግሥትና የጨዋታ ደንብ በሰላማዊ መንገድ ታግሎ ለማስቀየር የፖለቲካ መደላድል በአገሪቷ ካልተፈጠረ ተቃዋሚዎችን የበለጠ እንዲገለሉ ኢሕአዴግ እየገፋፋቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

አሁን የሚሰራበት የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት «የፓርላሜንታሪ» አመራርን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የኢሕአዴግ መሪ በ1987 ዓ.ም. ምርጫ አሸንፎ የአገሪቷ መሪ እንደሆነ ሁሉ በሚቀጥሉት ምርጫዎችም በተደጋጋሚ ሥልጣን ላይ እንደሚቀመጥ ጥርጥር የለውም። እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ይህንን መሰል አመራር የሚከተሉ መንግሥታት በሌሎች አገሮችም ይገኛሉ። ሌሎች ደግሞ «የፕሬዜዳንሻል» አመራርን ይመርጣሉ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ጎረቤት አገሮች «የፕሬዜዳንሻል» አመራርን ይከተላሉ። በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ «የፕሬዜዳንሻል» አመራር የተሻለ ተመራጭነት አለው።

1. የሕግ አስፈፃሚውና የሕግ አውጭው ሥልጣን የበለጠ ይለያያል።
2. «በፕሬዜዳንሻል» አመራር የአገሪቷን መሪ በቀጥታ የሚመርጠው ሕዝብ እንጅ የአሸነፈው ፓርቲ አይደለም። ለዚህም እንዲያመች ከኢሕአዴግ የብሔር ፖለቲካ ቅኝት መውጣትና ህብረብሔራዊ አደረጃጀትን መከተል ያስፈልጋል።
3. «በፕሬዜዳንሻል» አመራር አንድ የአገር መሪ የሚመረጥበት የጊዜ ገደብ አለው፤ ቢበዛ ሁለት ጊዜ በእያንዳንዱ ምርጫ ለአምስት ዓመት ነው።
4. «የፕሬዜዳንሻል» አመራር በኤኮኖሚውና በፖለቲከው የተሻለ አሰራር ለመፍጠር ያስችላል።

1.5 የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና የአካባቢው ፖለቲካ ቅኝት

ኢሕአዴግና ሻዕቢያ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን መንግሥት በመረዳዳት በትጥቅ ትግል የገለበጡና ሥልጣን ላይ የተቀመጡ በመሆናቸው በመካከላቸው ንፋስ ገብቶ ለከባድ ጦርነት ይዳረጋሉ ብሎ የሚገምት አልነበረም። ሆኖም ፍቅራቸው መረን የለቀቀ እንደነበረ ሁሉ ጠባቸውም ለገላጋይ አስቸግሯል። የሁለቱ አገሮች ጦርነት መንስኤ ከኗላው ብዙ ዝባዝንኬ ያለው ቢሆንም የድንበር ግጭት በተለይም የኢትዮጵያ ሉአላዊነት መደፈር፣ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ግኑኝነት መከተል፣ የመናናቅና የታላቅነት ስነልቦና ችግር የፈጠረው ነበር ማለት ይቻላል። የኤርትራ መንግሥት ቀደም ባሉት ጊዜያት ከተለያዩ የአካባቢው አገሮች ማለትም ከሱዳን፣ ከየመንና ከጅቡቲ ጋር በየተራ ሲናከስ ነግ በኔ በሚል ጠንካራ ተቃውሞን ያሰማ አልነበረም። እንዲያውም የጊዜያችን ኃያል መንግሥት የሆነው አሜሪካ የአካባቢውን የእስላም አክራሪ መንግሥታት ለመቆጣጠር እንዲያመቸው ኢትዮጵያን፣ ኤርትራን፣ ዩጋንዳንና ሩዋንዳን በጣም እንዲወዳጁ አድርጓቸው ነበር።

የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት ስልታዊ ግንኙነት ከዓለም አቀፍ ግንኙነት መርህ ውጪ በጋራ ገንዘብ መጠቀምን፣ በኤኮኖሚ መደጋገፍን፣ ወደቦችን በጋራ መጠቀምን፣ በንግድ ልውውጥ ሚዛን ኢትዮጵያ እየተጎዳች ኤርትራን መጥቀምንና የወሰን ክልል ሳይገድባቸው ሕዝቦቻቸው ከአንዱ አገር ወደ ሌላው በነፃ እንዲዘዋወሩ መፍቀድን ያካተት ነበር:: (55) (56) በዚህ ነፃ የንግድ ልውውጥ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የምታገኘውን ለራሷ ከመጠቀም አልፋ ወደ ሌላ አገር አሳልፋ በውጭ ምንዛሪ ትሸጥ ነበር:: ኤርትራ በሰላሙ ጊዜ ከኢትዮጵያ ጋር በነበራት ግንኙነት በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በምታገኘው ጥቅም ኤኮኖሚዋን ትገነባ እንደነበር ዶ/ር ተስፋፅዮን መድሕኔ የዶ/ር አዜብ ዘማርያምን መንደርደሪያ ሃሳብ መሰረት በማድረግ ጳጉሜ 6 ቀን 1991 ዓ.ም. ተደርጎ በነበረው የኤርትራ ሲምፖዚየም ያቀረበውን ጽሑፍ አዲስ ዘመን ዘግቦታል:: (57) ሌላው ቀርቶ በርከት ያሉ ኢትዮጵያኖች በመዋቅር ማስተካከያና በብሔር ብሔረሰብ ተዋፅኦ ሰበብ ከመንግሥት ሥራ ሲቀነሱ ኤርትራውያን በመንግሥት ሥራ ላይ ተደላድለው እንደተቀመጡ፣ በንግድና በዝቅተኛ የስራ መስክ የአገሬውን ዜጋ እንደሚፎካከሩና በምርጫ እንደሚሳተፉ የማይረሱ ትዝታዎች ናቸው:: ይህ የማያዛልቅና ስልታዊ ግንኙነት በሰባት ዓመት መናድና ወደ ጦርነት መሰወጥ ሁሉንም ግራ አጋብቷል:: ግንኙነታቸው ሊደፈርስ የቻለው የሁለቱም መንግሥታት በጋራ ይጠቀሙበት የነበረውን ገንዘብ ቀይረው በየግላቸው ሌላ ገንዘብ በማውጣት ኤርትራ ናቅፋን ኢትዮጵያ ደግሞ አዲስ ብር መጠቀም ሲጀምሩ ነበር:: በዚህ ጊዜ በመካከላቸው የሚደረገ የንግድ ልውውጦች በዓለም አቀፍ ምንዛሪ እንዲሆን የኢትዮጵያ ፍላጎት ሲሆን ኤርትራ ግን ብርና ናቅፋ አንድ ለአንድ እንዲለወጡ ከጀለች:: በተፈጠረውም አለመግባባት ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር የነበራትን የንግድ ግንኙነትና የምፅዋና የአሰብ ወደቦችን መጠቀም ለማቋረጥ ተገደደች::

በዚህ የንግድ ግንኙነት መቋረጥ የተነሳ የኤርትራ መንግሥት በዓመት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በውጪ ምንዛሪ ከወደብ አገልግሎትና ከአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ ከኢትዮጵያ የሚያገኘውን ገቢ ሲያጣ ቻለ:: (58) በንግድ ልውውጥም በኩል ሰባ በመቶ የሚያክለውን ለውጪ ንግድ የሚያቀርበውን ዕቃ ኢትዮጵያ ውስጥ መሸጡ ተቋረጠበት:: (59) ለኤርትራ መሰረታዊ የሆኑ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችና የርሻ ውጤቶች ከኢትዮጵያ መሸመቱ ቀረ:: (60) እነኝህ ሁሉ ያስከተሉት የኤኮኖሚ ችግሮች የአስመራውን መንግሥት ሲያፋጥጡት በኢትዮጵያ ሥልጣን ላይ በድጋፍ ያቆናጠጠውን ኢሕአዴግን በኃይል ለማንበርከክ ወሰነ:: የኢትዮጵያ የቀድሞው ጦር መበታተንና በኢሕአዴግ የጎሳ ፖለቲካ የተነሳ በአገሪቷ አንድነት አይኖርም ብሎ የተሳሳተ ግምት ላይ መውደቅ ሻዕቢያ በጦርነቱ በቀላሉ ድል እንደሚጎናፀፍ የልብ ልብ ሰጠው:: በሻዕቢያው መሪ መሰረት በአካባቢው የሚከሰቱት ልዩነቶችና ችግሮች የሚፈቱት በሕግ ሳይሆን በኃይል ነበር::

በዚህ የተነሳ የሻዕቢያ መንግሥት ከዚህ በፊት በሃኒሽ ደሴት ውዝግብ በየመን ላይ የተጠቀመበትን ስልት በመድገም በይገባኛል ሰበብ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በመድፈር ከግንቦት 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ባድማን፣ ሽራሮን፣ ዛላንበሳን፣ ቡሬን፣ ወዘተ. ወረረ:: ኢትዮጵያም ሉአላዊነቷን ለማስከበር በወሰደችው የመከላከል እርምጃ ብዙ ሰዎች በሁለቱም በኩል የጦርነቱ ሰለባ ሆኑ:: ብዙዎችም ከአካባቢው ተፈናቀሉ፣ በጦርነቱ ጦስም ብዛት ያላቸው የሁለቱም አገር ተወላጆች ወደየአገሮቻቸው ተባረሩ:: በዚህ ጦርነት የተነሳ

ከሁሉቱም በኩል እስከ ጥር 1999 እ.አ.አ. ድረስ 22000 በኤርትራ ይኖሩ የነበሩ የኢትዮጵያ ተወላጆች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ሲደረግ ከ53000 በላይ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የኤርትራ ተወላጆች ደግሞ እንደዚሁ ወደ ኤርትራ እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡ በዚህ መካከል የሰዎች መብት በሁለቱም መንግሥታት እርምጃ እንደተረገጠ አይጠረጠርም፡፡ (61) ከዚያም ወዲህ የማባረሩ ሂደት በሁለቱም በኩል በሰፋት ቀጥሎ ነበር፡፡ አንድ አገር ለአገሩና ለሕዝቡ ደህንነት ሲል የማይፈልጋቸውን የውጪ ዜጎች ማባረር እንደሚችል ብዙዎች ቢስማሙበትም (62) እነኝህ ሁሉ ጉዳያቸው በአግባብ ተጣርቶና ለአገር ደህንነት አስጊ መሆናቸው ታውቆና የውጪ ዜጋ መሆናቸው ተለይቶ የተባረሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡ ወደያገሮቻቸው ከተባረሩት በተጨማሪ ብዙዎች በልዩ ልዩ እስር ቤቶች ታጉረው ነበር፣ አንዳንዶችም የደረሱበት አልታወቀም፡፡ ከሁለቱም በኩል ከግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ቤት ንብረታቸው ወድሞ ተፈናቅለዋል፡፡ የሻዕቢያን ወረራ እንግ በመደገፉ አንዳንድ የኦረሞ ተወላጆች ለስር፣ ለስቃያና ለግድያ ተዳርገዋል፡፡ (63)

ለዚህ ጦርነት ማካሄጃና መሣሪያ መግዣ የወጣው ገንዘብ በኢትዮጵያ በአንዳንድ አካባቢዎች ለረሃብ፣ ለድርቅና ለአህል እጥረት የተጋለጠውን 10 ሚሊዮን ሕዝብ ለመመገብ፣ በመስፋፋት ላይ ያሉትን የጤና ችግሮች ኤድስን፣ የወባና የሳንባ በሽታዎችን ለመቆጣጠርና የማህበራዊ ችግሮች የሆኑትን ድህነትን፣ ሥራ አጥነትንና ልመናን ለመቅረፍ ያገለግል ነበር፡፡

ጦርነት በመጣ ቁጥር የኢትዮጵያ መሪዎች አገር ወዳድ መስለው ይቀርባሉ፡፡ የኢትዮጵያና የኤርትራ ያልተጠበቀ ጦርነትም ኢሕአዴግን በአንድ ጊዜ አገር ወዳድ አስመስሎታል፡፡ ለአገርና ለሉአላዊነት ተቆርቋሪነቱና ሕዝብን ለጦርነት እንዲነሳሳ የሚያደርገው ግፊት ከዚህ በፊት ከነበሩት መንግሥታት ተመሳሳይነት ነበረው፡፡ ደርግ በሱማሌ ወረራ ጊዜ የወሰደው አቋምና ኢሕአዴግ በዚህ ጦርነት ጊዜ ሉአላዊነትን ለማስከበር ያካሄደው ቅስቀሳ ይመሳሰላሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ማንም በመሪነት ሥልጣን ላይ ይቀመጥ ጠላት መጣብህ ሲሉት ዳር ድንበሩን ለማስከበር መዝመት ልማዱ ነው፡፡ አትንኩኝ ባይነቱ ከጥንት ተያይዞ የመጣ ባህል ነው፡፡ የመሪዎቹ አቋም ግን አጠያያቂና መመርመር የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ለአንድ በሥልጣን ላይ ላለ መንግሥት አገር ወዳድነት መለኪያው ምንድን ነው? ወራሪ ሲመጣ ለመመከት ሕዝብን ዝመት ማለት ነው? ሕዝብ ሲጨፈጭፍ የነበረ መንግሥት፣ በሥልጣን ላይ ለመቆየት በቀይ ሽብር ተቃዋሚዎችን የፈጀ መንግሥት፣ ሌላም ሌላም ብዙ በደሎችን የፈፀመ መንግሥት እንዴት አገር ወዳድ ሊባል ይችላል፡፡ አንድ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት በአገር ውስጥ ያሸውን እየሰራ ወራሪን ስለመከተ ብቻ አገረ ወዳድ ተብሎ የፈፀመው በደል ሊፋቅለት አይችልም፡፡ በዚህ የተነሳ የደርግም ሆነ የኢሕአዴግ መንግሥታት አገር ወዳድ ሊባሉ አይችሉም፣ አይደሉምም፡፡ ምናልባት ሥልጣናቸውን ጠብቀው ለማቆየት ሕዝብን በመቀስቀስ ለአገር ሉአላዊነት ያበረከቱት ሚና በአገር ወዳድነት ሳይሆን በራስ ወዳድነት የሰሩት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተረፈ አገር ወዳድነት ለሕዝቧም ሆነ ለአገሪቷ በሰላሙም ሆነ በጦርነት ጊዜ መቆርቆርን ይጠይቃል፡፡

በዓለም ላይ የአንድ አካባቢ አገሮች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግንኙነት ከጊዜያዊ ጥቅም ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እንጥፍጣፊ በአካባቢው አገሮች ላይ የፈጠረው ሁኔታ ይለያይ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የኤርትራን

ወደቦች መጠቀም ካቆመች ጊዜ ጀምሮ የውጪ ንግድ ግንኙነቷን በጅቡቲ ወደብ በኩል ስላስፋፋች የጅቡቲ መንግሥት በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ሊሆን ችሏል። በዚህ የተነሳ በፊትም በቋፍ የነበረው የኤርትራና የጅቡቲ ግንኙነት የበለጠ ሊሻክር ጅቡቲም በኤርትራ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት ደጋፊ በሚል ልትፈረጅ ቻለች። ኤርትራና ኢትዮጵያ በራሳቸው ችግር ስለተጠመዱ፣ ሱዳን አክራሪ እስልምናን የምታራምድ መንግሥት በሚል በጎሪጥ መታየቷ ቀነሰላት። እንዲያውም የአሜሪካን መንግሥት የሱዳንን የመድኃኒት ፋብሪካ ከዓለም አቀፍ አሸባሪው ከቢንላደን ንብረት ጋር የተያያዘ የነርቭ ጋዝ ማምረቻ ሳይሆን አይቀርም በሚል ጥርጣሬ በሚሳይል ካወደመ ጀምሮ ሱዳን ከሽብርተኞች ጋር ግንኙነት እንደሌላት ለማሳየት የማታደርገው ጥረት አልነበረም። ውጤቱ በጊዜው ባይሰምርላትም ባገሯ የትጥቅ ትግል ከሚያካሂዱት ተቃዋሚዎች ጋር ለመታረቅ ጥረት እያደረገች ነበር። ከዚያም አልፎ ሱዳን የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በአፍሪካ ቀንድ አገሮች መካከል የፈጠረውን አለመግባባት ቀዳዳ በመጠቀም ከኤርትራም ሆነ ከኢትዮጵያ ጋር የተቀራረበ ወዳጅነት ለመመሥረት ችላለች። እንግዲህ ሱዳን በብዙ መልኩ ተጠቃሚ ሆና ነበር ማለት ነው።

አሜሪካ ወዳጆቿ ሲነታረኩ ማንን እንደምታቀርብና ማንን እንደምታርቅ የጨነቃት በመሆኑ ጦርነቱን ማስቆም አልቻለችም ነበር። ሆኖም ወራሪና ተወራሪን እኩል በመመልከቷና ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደችውን ወረራ ባለማውገዟ በኢትዮጵያ በኩል ያጋጠማት ተቃውሞ እየጨመረ መጥቶ ነበር። አሜሪካ፣ ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደችውን ወረራ ሳታወግዝ በዝምታ መመልከቷ ከኢትዮጵያ ይልቅ ኤርትራ ተጠቃሚ ናት ለማለት ሳይሆን ሁለቱንም እኩል በማየት ለማስታረቅና በአካባቢው ሰላም እንዲፈጠር ለማድረግ ነበር የሚል ሃሳብ አንዳንዶች ይሰነዝራሉ። (64) ይህ አባባል እውነትነቱ አጠራጣሪ ቢመስልም በአቋሟ ገፍታበታለች። ነገር ግን በስውርም ሆነ በይፋ ተፅኖዋን በማሳደር ጦርነቱን ለማስቆም ሞክራለች። በጊዜው በሷ ግፊት ሁለቱም ተፋላሚ አገሮች ከሰብአዊ ልግስና ውጪ ከዓለም ገንዘብ አበዳሪዎችና እርዳታ ሰጪዎች ድጋፍ እንዳያገኙና እንዲገለሉ አስደርጋለች። በተጨማሪም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ጦርነቱ እንዲቆም ያስተላለፈው ጥሪ ባለመከበሩ ከሰኔ 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ለአንድ ዓመት ጊዜ ሁለቱም ወገኖች የጦር መሣሪያ ከማንም አገር እንዳይገዙ ማዕቀብ ተጥሎባቸው ነበር። ባጭሩ ሁለቱም አገሮች ጦርነቱን እንዲያቆሙ ለማስገደድ ከአሜሪካም ሆነ ከዓለም ህብረተሰብ ተፅኖ ተደርጎባቸዋል።

ሶማሊያ የራሷ ማዕከላዊ መንግሥት ስለሌላት የተለያዩ የጦር አበጋዞቿን ኤርትራና ኢትዮጵያ በመርዳት በእጅ አዙር ለመቆራቆስ ሞክረዋል። በተለይም ኤርትራ የሶማሌውን የጦር አበጋዝ ሁሴን አይዲድን በማቀፍ ሶማሌን ለኦነግ መሸጋገሪያና ኢትዮጵያን ለማጥቂያ ያደረገችው ሙከራ ከሽፏል። ኢትዮጵያም ብትሆን ኦነግ፣ ተከቴማና (የኦሮሞ አንድነት ድርጅት) የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን ለማሳደድ ድንበር ዘለል ጥቃት ከመፈፀም አልፋ የሁሴን አይዲድን ተቀናቃኝ የጦር አበጋዞች ደግፋለች። ኢትዮጵያና ኬንያ ከዱሮ ጀምሮ መልካም ጉርብትና ቢኖራቸውም የኢሕአዴግ የጎሳ ፖለቲካ ውሽንፍር ኬንያን ሳያርሳት አልቀረም። የኦነግ ታጣቂ ቡድኖች ኬንያን መሸሻና ማፈግፈጊያ በማድረግ የሁለቱን መንግሥታት የድንበር አካባቢ ፀጥታ ለማደፍረስ ሞክረዋል። (65)

በመጨረሻ ደርግን በኃይል አስወግዶ በኢትዮጵያ ሥልጣን የተቀመጠውን የኢሕአዴግን የፖለቲካ አቅጣጫ ለመቋጨት ቀድም ብሎ ሁለቱን ለማወዳደር ወደ ተጀመረው መመለስ ያስፈልጋል። ደርግ አርሶ አደሩን ገባር ያደረገውን የፊውዳል ስርአት ቢገረስስም ዴሞክራሲያው አሰራር ባለመከተሉ፣ በቀይ ሽብር ሕዝብ በመጨፍጨፉና ጦርነት በማስፋፋቱ ሊወድቅ ችሏል። ኢሕአዴግም የአገሪቷ ኢኮኖሚ እንዲበለፅግ በነፃ ኢኮኖሚ ስም እንቬስተሮችን ለመሳብ ቢጣጣርም የተሳሳተ የፖለቲካ አሰራር መንገድ ስለሚከተል ራሱ ያወጣውን ደንብ እንኳን የሚያከብር አለመሆኑን ቀደም ብሎ ተገልጿል። አንዳንድ የሚያሳየው የዴሞክራሲ ነፀብራቅ እንኳን የጊዜው የዓለም አቀፍ ሁኔታ የፈጠረው ግፊት እንጅ ታስቦበት በሥራ ላይ የሚውል አይደለም። እንግዲህ ሁለቱም በተከታታይ በሥልጣን ላይ የወጡት መንግሥታት በታሪክ ሊጠቀስ የሚችል አንዳንድ በጎ ነገር ቢኖራቸውም ሁለቱም የዴሞክራሲያዊ አሰራር የላቸውም። ደርግ አቋሙን ሳይቀይር ሁልጊዜ «ከድጡ ወደ ማጡ» እየተሸጋገረ በመጨረሻ ስለወደቀ ታሪክ እንዳንቋሸሸው ይኖራል። በምዕራፍ ሁለትም የቀረበው ይኸው ነበር። ኢሕአዴግም ቢሆን እስከ አሁን ብዙም የተሻለ አሰራር አላሳየንም። ስለዚህ ወደፊት ወይ በጀመረው ይዘልቃል፣ አለበለዚያም ሳይመሸበት አቋሙን ሊቀይር ይገባል።

2. ያልተቋጨው የዴሞክራሲ ትግል

ደርግ ከወደቀ በኋላ አሁንም እንደበፊቱ ያው መፋጠጥ፣ ማሰርና መግደል እንዳለ ነው። ኢሕአዴግም በተራው ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ክርችሌን በአዲስ ታሳሪዎችና በአዲስ ጋቢና ዋራንት አሰራር ተክቶታል። አንዱ ሲታሰር ሌላው ሲፈታ እየተቀያየሩ መኖር ችግሩን እንደማይፈታው ካለፈው ትምህርት አላገኘም።

የአገራችን የዴሞክራሲ ችግር አሁንም አልተቀረፈም። ከኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ ሕገ መንግሥት ቢኖርም የሕዝብ መብቶች አልተከበሩም፣ ምርጫ ቢካሄድም ሕዝብ ወኪሉን አላገኘም። በኃይለ ሥላሴ፣ በደርግና በኢሕአዴግ መንግሥታት ድርቅ ተከስቷል፣ ሕዝብም ተርቧል። በሦስቱም የሥልጣን ጊዜ ጦርነት ተካሂዷል፣ በሦስቱም ጊዜ ተቃዋሚዎች የትጥቅ ትግል አካሂደዋል። ኃይለ ሥላሴ በደርግ፣ ደርግ በኢሕአዴግ በኃይል ቢተኩም የኢትዮጵያ ችግሮች ሊፈቱ አልቻሉም። የብሔር ብሔረሰብ መብት ተከብሯል በሚባልለት አገር የጎሳ ማበላለጥ ይታያል፣ ለእርሻ ምቹ ለም መሬት ባለበት አገር ሕዝብ ይራባል፣ የተለያዩ ወንዞች ከኢትዮጵያ አልፈው ወደ ጎረቤት አገር በሚፈሱበት አገር ድርቅ በመጣ ቁጥር ሕዝብ በረሃብ ይቆላል፣ ኢኮኖሚያችን አደገ በሚባልበት አገር አብዛኛው ሕዝብ በድህነት ይማቅቃል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጤናና በትምህርት በዓለም ላይ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ በዓለም ላይ የመጨረሻዎቹ ድሃ አገሮች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት።

የኢሕአዴግ መንግሥት ገጠርን ማዕከል ያደረገ በግብርና ልማት ላይ የሚያተኩር የኤኮኖሚ ልማት መርሃ ግብር ነድፏል። ይህንን እቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ ብዙ ጥረት ቢደረግም የአገሪቷ እድገት በጣም አዝጋሚና እንዲያውም ቁልቁል እንደ ካሮት የሚያድግ በመሆኑ ከዓለም

የመጨረሻ ድሃ አገሮች ከሚባሉት ተርታ ነች። መሬት በመንግሥት ባለቤትነት መያዙ፣ ምርታማነት የሌለው ኋላ ቀር የርሻ ዘዴ መከተሉ፣ ዘመናዊ ሰፋፊ የግልና የማህበር እርሻዎችና የእንስሳት እርባታዎች አለመኖራቸውና ለመስኖ ልማት ትኩረት አለመስጠቱ አርሶ አደሩን እንኳን ትርፍ አምራች ሊያደርገው ቀርቶ ራሱንም ለመመገብ አላስቻለውም። የገበሬው ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ የመከር አዝመራ በበልግ ካልታገዘ ለረሃብ እየተጋለጠ ይገኛል። ድርቅ በተከሰተ ቁጥር ከረሃብ ከልመናና የዓለም አቀፍ ህብረተሰብን ከማስቸገር ልንላቀቅ አልቻልንም።

ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1992 ዓ.ም ባጋጠመው ድርቅ ከ10 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ለረሃብ ተጋልጦ ነበር። ሦስት ሚሊዮን የሚሆኑ የቀንድ ከብቶችም አልቀዋል። ከእርሻ የምናገኘው ምርት ሕዝባችንን በበቂ መመገብ አልቻለም። የዝናብ ጥረት በሌለበትም ጊዜ ቢሆን መንግሥታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በቋሚነት ስለሚደጉሙን እንጂ አገራችን ከችግር ተላቃ አታውቅም። (66) ብዛት ያላቸው የመሰረተ ልማቶች የሚካሄዱት በረጅ ድርጅቶች ድጋፍ ነው። እንግዲህ ለችግራችን መፍትሔ ለማግኘት እኛም እንደሌሎች አገሮች የመሬት ስሪታችንን መቀየር ይጠበቅብናል። ይህ እስከ አሁን ያልተፈተሸው አማራጭ መንገድ የእርሻም ሆነ የእንስሳት ሐብታችንን በተገቢው መንገድ ለመጠቀምና ከልመና ለመላቀቅ ያስችለናል ተብሎ ይታመንበታል።

85% የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር የሚኖር አርሶ አደር በመሆኑ ሕይወቱ ከመሬት ጋር የተያያዘ ነው። ይኸ ሁሉ አርሶ አደር ባለበት አገር ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን መቻል አቅቷታል። በሌሎች አገሮች ግን ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነው። ስለዚህ የአገራችንን ግብርና ምርታማነት ለማሳደግ የመሬትን ስሪት ከመንግሥት ባለቤትነት ወደ ግል ይዞታ ማዛወር፣ ከፖለቲካ መጠቀሚያነት ማላቀቅና እንደ ማንኛውም ሸቀጥ መሸጥና መለወጥ የግድ አስፈላጊ ነው። በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ከንብረት ማፍራት ጋር የተዓመረው የመሬት ባለቤትነት እንደ አንቀፅ 39 ሁሉ የኢሕአዴግ ስስ ብልት ሆኖ ቆይቷል። ብዙም አነታርኳል።

የመሬት መሸጥና መለወጥ በገጠሩ ሕዝብ ሕይወት ላይ ሁለት ተፃራሪ የሆኑ ነገሮችን ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ይገመታል። በመጀመሪያ ደረጃ በገጠር ያለውን የተበታተነ ኋላ ቀር የእርሻ ይዞታ በመቀየር ወደ ዘመናዊ ሰፋፊ የግልና የማህበር እርሻዎች እንዲያድጉ እገዛ ያደርጋል፣ ደግሞም የተሻሻሉ የእርሻ ዘዴዎችንና ለግብርና ምርታማነት አስፈላጊ ግባቶችን እንደ ማዳበሪያ፣ የተባያ ማጥፊያ፣ የተሻሻሉ ምርጥ ዘሮችንና አስፈላጊ የአፈር ጥበቃን ለመጠቀም ያስችላል። ከዚህ ውጪ ሁኔታው በዚህ በተበጣጠሰ የገበሬ የርሻ ይዞታ ከቀጠለ በኤክስቴንሽንም ታገዘ ወይም የሚታረሰው መሬት ልክ ጨመረ ትርፍ አምራች ለመሆንና ራስን በምግብ ለመቻል አጠራጣሪ ነው። እንዲያውም የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የገበሬው መሬት የባሰ እየተበጣጠሰና እያነሰ ስለሚሄድ ችግሩ እየከፋ ይመጣል። ለአንድ ገበሬ የሚደርሰው አራት ቀርጥ መሬት ወደ ሁለትና አንድ ዝቅ ይላል።

በሌላ መልኩ የመሬት መሸጥና መለወጥ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል የሚሉት ወገኖች ገበሬው መሬቱን እየሸጠ ወደ ከተማ በመፍለስ ሥራ አጥነትን ያበራክታል የሚል ስጋት አላቸው። ለገጠሩ አርሶ አደር መሬት መገልገያው ብቻ ሳይሆን የማንነቱና የመስረቱ መግለጫው ስለሆነ ስለቸገረው

ብቻ እንደ ሸቀጥ እንዳገኝ ይቸበቸበዋል የሚለው አባባል ተቀባይነት የለውም። የተሻለ አማራጭ ሥራ መመስረት እችላለሁ ብሎ ካሰበም የመሸጥ መብቱ መጠበቅ አለበት። ሌላው ደግሞ መሬት በግልም ተያዘ በመንግሥት የገጠር ሕይወቱ ስኬታማ ያልሆነ ገበሬ የተሻለ ፍለጋ ወደ ከተማ መፍለሱ አይቀርም። ይህንን መቋቋም የሚቻለው ከግብርና ጋር የተያያዙ አደ ጥበብና አነስተኛ የርሻ ኢንዱስትሪዎች በገጠር ከተሞች እንዲስፋፉ በማድረግና በግብርና ለተሰላቸው ገበሬ ወይም የመሬት ጥበት ላለበት አማራጭ የስራ እድል እንዲያገኝ በመፍጠር እንጅ መሬትን በመንግሥት ባለቤትነት በመያዝ አይደለም።

መሬት መሸጥና መለወጥ የለበትም የሚሉት ወገኖች የቻይናን የእድገት ሁኔታ እንደ ምሳሌና መከራከሪያ ነጥብ ያቀርባሉ። ቻይና መሬትን በመንግሥት ይዞታ ስር በማድረግ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚዋን ለማሳደግና በምግብ ራሷን ለመቻል ስለበቃች የሷን መንገድ መከተል ለኢትዮጵያም የማይጠቅምበት ምንም ምክንያት የለም ባይ ናቸው። ይህ አባባል ቻይና አሁን አደረሰችበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረድ ማሳለፏን፣ እንዱ የርሻ ፖለሲ አላዋጣ ሲላት በተለያየ ጊዜ መከለሱን አያመለክትም። በተጨማሪም ቻይና በርሻ ትርፍ አምራች ልትሆን የቻለችው የእርሻ ኢኮኖሚዋን የእንዱስትሪው ፈጣን እድገት እየደጎመው እንደሆነ እያብራራም። ሌላው ደግሞ ቻይና ፈጣን እድገት ያሳየችበት ወቅትና የአሁኑ የዓለም የኢኮኖሚ ሁኔታ የተለያየ መሆኑን ይዘነጋል። አሁን ዓለም «በግሎባላይዜሽን» የተነሳ የተቆላለፈ የኢኮኖሚ ግንኙነት ላይ ስለምትገኝ ቻይና የሄደችበትን መንገድ መከተል የሚቻል አይመስልም። ኢትዮጵያ በየትኛው መንገድ ብትራመድ ለራሷ በጅታ በዓለም ገበያ ውስጥ ገብታ መወዳደር ትችላለች የሚል ተጨባጭ ፖለሲ መንደፍ እንጅ የሌሎችን መቀላወጥ የሚያዋጣ አይመስልም። በአጠቃላይ አገራችን ልትከተለው የሚገባው የመሬት ባለቤትነት ይዞታና የእርሻ ፖለሲ ምርት ለማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብትንና የአካባቢ ጥበቃን ለመንከባከብና በአግባብ ለመጠቀም የሚያስችሉ መሆን ይገባቸዋል።

ምንም እንኳን የሰፋፊ እርሻዎች መኖር ትርፍ አምራች ለመሆንና በምግብ ራስን ለመቻል እንደ መፍትሄ ተደርጎ ቢቆጠርም የምርት ትኩረት አቅጣጫው በውጪ ገበያ ላይ ብቻ የሚያተኩር ከሆነ ትርፉ ልፋት ብቻ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ቡና በኢትዮጵያና ኡጋንዳ፣ ጥጥ በሱዳን ፣ ትምባሆ በዚምባብዌ፣ ካካዋ በጋናና በኮትዲቫር፣ ወዘተ. ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ የሚያስገኙ ተክሎች ቢሆኑም ለምግብነት የሚያገለግሉ አይደሉም። ስለዚህ ሰፋፊ እርሻዎች የሚያመርቱት ምርት ለአገር ውስጥና ለውጪ አገር ተጠቃሚዎች እንዲያገለግሉ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ መንግሥት ለአነስተኛ ገበሬዎችም ሆነ ለሰፋፊ እርሻ ባለቤቶች የምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የተባይ ማጥፊያና ሌሎች አስፈላጊ የማምረቻ መሣሪያዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚውን መደገፍ ይገባዋል። በእነኝህ ድጎማዎች መንግሥት የገበሬዎችን የእርሻ ምርት አቅጣጫ መቆጣጠርም (Influence) ይችላል።

መንግሥት መሬት አይሸጥም አይለወጥም በሚል የመሬት ይዞታውን ከሚገድብ ይልቅ የተሻሻለ የመሬት አጠቃቀምና የልማት ስልት በመቀየስ 1) የሰብል ምርትና የውጪ ምንዛሪ የሚያስገኙ ተክሎች የሚስፋፉበትን አካባቢዎች ለይቶ ትኩረት መስጠት፣ 2) ቅይጥ እርሻና እንስሳት እርባታ በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች መሬትን ለእርሻና ለግጦሽ በማዋል በኩል ችግር

እንዳይፈጠር ለሰውና ለእንስሳት ምግብ የሚያገለግሉ ምርቶች የሚመረቱበትን መንገድ ማመቻቸት፣ 3) ለደንና ለዱር አራዊት ጥበቃ የሚውሉትን አካባቢዎች መከለል፣ 4) የአርብቶ አደሩን የእንስሳት እርባታ ችግሮች መፍታት የሚችሉ ዘዴዎችን መቀየስ፣ 5) የእርሻ ውጤቶች የተሻለ ገበያ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና 6) በአጠቃላይ የገበሬዎችን ምርታማነት የሚያሳድጉ ምርምሮችን ማካሄድ ይጠበቅበታል:: (67) አርብቶ አደር የእንስሳት አርቢዎች ከቦታ ቦታ ውሃና ግጦሽ ፍለጋ እንዳይንከራተቱና በአንድ ስፍራ እንዲወሰኑ ለማደፋፈር የውሃ ኩሬዎችንና ጉድጓዶችን በስፋት ማዘጋጀት፣ የመኖ አገልግሎት የሚሻሻልበትን መንገድ መፈለግ፣ የእንስሳት ብዛት የአካባቢውን ግጦሽ እንዳይጎዳው ማስተማርና መቆጣጠር፣ ለእርሻ ሥራ ትኩረት እንዲሰጡ መገፋፋትና የገበያ ልውውጥን ማስፋፋት ያስፈልጋል::

በየጊዜው የኤኮኖሚ ዕድገት እንዳለ ተደርጎ አሣዛዊ መረጃ ይቀርባል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከችግር አልተላቀቀም:: ደርግ በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ሕዝብ በድህነት እየተቆራመደና ጦርነት እየተሰፋፋ እያለ ኢኮኖሚያችን እድገት አሳይቷል ይል እንደነበረ ይታወሳል:: በወቅቱ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መረጃዎች መሰረት ከመጨረሻዎቹ ድሃ አገሮች የምትቆጠር የአገሪቷ የዓመት የነፍስ ወከፍ ገቢ ከሶማሊያ ያነሰ 130 የአሜሪካ ዶላር እንደነበረ ይታወቃል:: (68) መቸም «አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ነውና ደርግ ምንም ቢዋሽ ውድቀቱን አፋጠነ እንጅ ሕዝብን ሊያሞኝ አልቻለም:: የኢሕአዴግም የዚያኑ አይነት ጨዋታ ነው:: በኢሕአዴግ ጊዜ የኤኮኖሚ ዕድገት እንዳለ ቢነገርም በአብዛኛው ሰዎች ሕይወት ላይ ብዙም ለውጥ አላመጣም:: ድህነት ጨምሯል፣ በሐብታምና ድሆች መካከል ያለው ልዩነት የተየለሌ ነው:: መሰረታዊ የኑሮ ፍላጎቶችን እንደ ምግብ፣ መጠጥ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ ጤና፣ ወዘተ ለማሟላት አዳጋች ሆኗል:: ይህ በሐብታሞችና በድሆች መካከል እየሰፋ የመጣው የኤኮኖሚ መራራቅ በዓለም ላይ በብዙ አገሮችና በኢትዮጵያም ጭምር እየተባባሰ ይገኛል:: ለዚህ የተለያየ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋነኛነት የኢኮኖሚ ፖለሲ ድክመት፣ ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ በፖለቲካ ልዩነት የተነሳ የሚፈጠር አድልዎ፣ ሥራ አጥነት፣ ከዓለማ አቀፍ የንግድ ልውውጥ ተጠቃሚ አለመሆን፣ የልማት አቅጣጫው ለብዙሐን ሳይሆን ለጥቂቶች መጠቀሚያ መሆን፣ ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው::

ለእነኝህ ሁሉ ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ በጋራ ለመፈለግ የዴሞክራሲ መስፈን አማራጭ የማይገኝለት ጉዳይ ነው:: የዴሞክራሲ መሰረት የሌለው መንግሥት ምንም ቢማስን ግቡን ሊመታ እንደማይችል በተደጋጋሚ ታይቷል:: ደርግ የወደቀው የዴሞክራሲ አሰራር ስላልነበረው መሆኑ ቀድም ብሎ ተገልጿል:: ነገም ኢሕአዴግ ካላወቀበት ይደገማል፣ ተነገ ወዲያም ሌላ ቢመጣ የዴሞክራሲ መሰረት ከሌለው መውደቁ አይቀርም:: ሁሉም ሳያምርበት ሥልጣን ላይ ቆይቶ ይወድቃል፣ ከወደቀም በኋላ በታሪክ ሲሰደብ ይኖራል:: ስለዚህ ለአገራችን የቆየ ችግር መፍቻ ሊሆን የሚችል እውነተኛ ለጊዜው ተስማሚ የሆነ ዴሞክራሲ ለማምጣት መታገል አማራጭ የሌለው የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው::

የዴሞክራሲ መስፈን የሚለካው በአንድ አገር ባለው ሕገ መንግሥት ወይም ሕዝብ በመረጣቸው ወኪሎቹ አማካኝነት በመተዳደር ብቻ አይደለም:: ምክንያቱም የዴሞክራሲ አሰራርን የማይከተል በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት የሚፈይደው የለምና:: ይህንን ሃቅ የዴሞክራሲ አመጣጥና እድገት

ያስገነዝባል:: የዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ በተመሰረተበት በጥንቱ የአቴና መንግሥት በጊዜው ከሚገኙት 400000 ዜጎች መካከል 250000 መብት የሌላቸው ባሮችና 150000 ነፃ ሰዎች ነበሩ(69):: የጊዜው ዴሞክራሲ ለነፃ ሰዎች በሙሉ በአስተዳደር ሸንጎ ስብሰባ በቀጥታ የመወከል ሥልጣን ሲሰጣቸው ባሮች ግን ምንም መብት አልነበራቸውም:: ይህ የሚያመለክተው የዴሞክራሲ አሰራር ሲጀመር ብዙኃኑን ያቀፈ አለመሆኑን ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዴሞክራሲ አሰራር በየዘመኑ እየተሻሻለ ከተለያዩ መብቶች ጋር እየተቆራኘ መጣ:: የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የአሜሪካና የሩሲያ አብዮቶችን ተከትሎ ዘመናዊ ሕገ መንግሥትና የውክልና ዴሞክራሲ በሥራ ላይ መዋል ጀመሩ:: እነሱንም ለማስፈፀም የተሻለ አሰራር ተቀየሰ:: በዚህ ሂደት ተፃፃሪ አቋም ያላቸው ለከበርቴው መደብ የቆሙ የምዕራብ ዴሞክራሲና ለላብ አደሮችና ለጭቁኖች መደብ የቆመው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ተፈጠሩ::

እነኝህ ተፃራሪ የሆኑ የዴሞክራሲ ገፅታዎችና አሰራሮች ለብዙ ጊዜ ከተፎካከሩ በኋላ አብዮታዊ ዴሞክራሲን የምታራምደው ሶቬት ህብረት ስትፍረከረክ የምትመካበት ዴሞክራሲም አብሮ ሊያከትም ቻለ:: በዚህ የተነሳ ብዙ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አሰራር ተከታይ የነበሩ አገሮች አቋማቸውን እያሻሻሉ የለዘብተኛ ዴሞክራሲ ተከታይ እየሆኑ መጡ:: የለዘብተኛው ዴሞክራሲ አሰራር መንገድ በዴሞክራሲ ላይ ያለው መደባዊ አመለካከት ቀርቶ ወይም ተለውጦ በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመሰረተ ሆነ:: ይህም የሁሉንም እኩልነት የሚያጎናፅፍና ሁሉም መደቦች በእኩልነት መብታቸው ተጠብቆ በመቻቻልና በመከባበር እንዲኖሩና እንዲሰሩ ማድረግን የሚጠይቅ ስልት ነው:: እንግዲህ ይህን የዴሞክራሲ አሰራር መንገድ ለማስፈን የሁሉንም መደቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ ትግል ይጠይቃል:: መለያ ባህርይውም በተለያዩ ፓርቲዎች መካከል አድልዎ የሌለበት ነፃና ተቀባይነት ያለው አስተማማኝ ምርጫ ማካሄድ ነው:: እነኝህን የምርጫ መመዘኛዎች አብዮታዊ ዴሞክራሲም ሆነ ሊብራል ዴሞክራሲ ይቀበላሉ፤ በተግባር ግን ለራስ በማድላት ይጣላሉ::

የተለያየ የፖለቲካ ዓላማና ግብ ያላቸው ድርጅቶች የራሳቸውን ፕሮግራም ነድፈው ያንን በሥራ ለመተርጎም የተለያየ የትግል ስልት ይጠቀማሉ:: ከሌሎች ጋር በመተባበር የጋራ ህብረት በመመስረት የፖለቲካ ግባቸውን ለማሟላት ይጣጣራሉ:: በዚህ የተነሳ በተለያዩ ተቃዋሚዎች መካከል እየተፈጠረ ያለው ህብረት የሚያስደስት ቢሆንም መጥፎ ጎኖችም ይታይበታል:: አንዳንዶች ከኢሕአዴግ ጋር ስምም ሆነው ቆይተው በአንድ ምክንያት ሲያኮርፉ ተንደርድረው ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር ይለጠፋሉ:: ኩርፊያው ሲያበቃ ለተቃዋሚዎች ጀርባቸውን ሰጥተው ከኢሕአዴግ ጋር ሽር ጉድ ማለት ይጀምራሉ:: በዚህ መልክ የሚዋልሉት የፖለቲካ ቡድኖች በሁለቱም በኩል አሽሩሩ የሚላቸውን ይፈልጋሉ:: ኢሕአዴግ የፈጠረውን የፖለቲካ መድረክ የማይፈልገውን ለማግለልና የሚመስለውን ለማቅረብ ስለሚጠቀምበት ይህን መሰል የአቋም መዋገቅ የሚታይባቸውን በመከፋፈል የተቃዋሚዎችን ህብረት ማዳከም ችሏል:: እንግዲህ በህብረቱ ዙሪያ ያሉ ድርጅቶች ይህንን ተንኮል ተገንዝበው በአንድ ወገን ሳይረጉ የሚዋዥቁትን ማግለል አለባቸው::

በሌላ መልኩ ሕጋዊ እውቅና ያላቸውን ተቃዋሚ ድርጅቶች መረማመጃ በማድረግ ከኢሕአዴግ መንግሥት የሚገኝ የፖለቲካ ጥቅም እንደሌለ በተቃዋሚዎች የተዘጋጀው የግዮን ኮፍራንስ ውጤትና ከሱም በኋላ የተካሄደው የፖለቲካ ትግል ያረጋግጣል:: ሕጋዊ እውቅና ያላቸው ድርጅቶች

ሰብሔራዊ እርቅ እንደ ድልድይ ያገለግላሉ የሚለውም አልሰመረም። እርግጥ ኢሕአዴግን መቀየር አልቻሉም እንጅ ሕጋዊ እውቅና ያላቸው ድርጅቶች እርቅ እንደሚያስፈልግ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንደወተወቱ ናቸው። ነገር ግን ሊሳካ አልቻለም። እንግዲህ ይህንን ለማሳካት በተቃዋሚዎች መካከል የማያወላውል ህብረት መመስረትና ሁለገብ ትግል ማካሄድ ያስፈልጋል።

የግዮን ኮንፍራንስን ተከትሎ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት መቋቋም የአገር ቤቱን ፖለቲካ አንድ ሰሞን ሞቅ ደመቅ አድርጎት ነበር። ይህም ሊሆን የቻለው ለዚህ ምክር ቤት አስተዋፅኦ ያደረጉትን ሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመመልከትና ከኂላቸው የሚያራምዱትን ፖለቲካ በመመርመር እንጅ ሌላ ምክንያት አልነበረውም። ለሰልፍና ለፖለቲካ ድጋፍ ሲጠራ ሕዝቡ አያጀበ ከዚህ ምክር ቤት በስተጀርባ ያለውን ሁኔታ በአንክሮ ተከታትሏል። በሂደት ግን የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ሕጋዊ እውቅና ያላቸውን መስራቾቹን ብቻ ይዞ ቀረ። ያ ሁሉ የአንድ ሰሞን ደጋፊም ፊቱን አዞረ። ኢሕአዴግም በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ዙሪያ የተሰባሰቡትን ድርጅቶች ሕጋዊና ሕገወጥ እያለ በመከፋፈል ሊያዳክመው ቻለ።

ሌላው ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ አሸን መብዛት የተከታዮቻቸውን ቁጥር እያሳነሰና ሕዝብንም እምነት እያሳጣው መጥቷል። በምርጫም ጊዜ የምልክቶች መበርከትና መመሳሰል ችግር ፈጥሯል። በዚህ ላይ የግል ተወዳዳሪዎች መብዛትም አይጣል ነው። ለዚህ ያለው መፍትሔ ሊመሳሰሉና ሊቀራረቡ የሚችሉ የተለያዩ ድርጅቶች ህብረት ብቻ ሳይሆን ውህደትም መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ማድረግ ለድርጅታቸው ጥንካሬን ይሰጣል፣ ደጋፊዎቻቸውም ይሰባሰቡና ይጨምራሉ። የድርጅቶች ህብረትና ውህደት ሌላም ጥቅም አለው። የወደፊቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በሁለት ግዙፍ ፓርቲዎች (Biparty) መካከል እንዲሆን ያደርገዋል። መራጩ ሕዝብም ትኩረቱ በእነኝሁ ታላላቅ ድርጅቶች ራዕያ ላይ ይሆናል።

በመጨረሻ አሁን ባለንበት ክፍለ ዘመን ዓለም በኢኮኖሚ እድገትና በዴሞክራሲያዊ አሰራር እየተሻሻለ መጥቷል። ለዘብተኛ የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ ዓለም አቀፍ የንግድና የመዋዕለ ንዋይ ትስስር (Globalization) እና የዴሞክራሲያዊ ባህሪያት የተላበሰ አሰራር እየጎለበቱ በመጡበት በአሁን ወቅት ኢትዮጵያ በእነኝህ ዙሪያ ያላትን ድክመት ተሸክማ ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን መሸጋገር የለባትም። ስለዚህ ከጊዜው ጋር ለመራመድ በአገሪቷ የሥልጣን ኮርቻ ተቀምጦ ልጓሙን ይዞ የሚጋልበውን ፈረሰኛ ወይ ግልቢያውን እንዲያስተካክል ማድረግ አለበለዚይም ሌላ የተሻለ ጋላቢ ፈረሰኛ መምረጥ የግድ ያስፈልጋል። ዓለም አቀፍ የንግድና የመዋዕለ ንዋይ ትስስር የተከሰተው አሁን በአገሮች መካከል በመገናኛና በኮምፒተር የመረጃ መለዋወጥ ከፍተኛ እድገት ባሳየበት ወቅት ቢሆንም ኂላ ቀር የሆኑትና የዴሞክራሲ አሰራር የሌላቸው የአፍሪካ አገሮች ከዚህ ብዙም ተጠቃሚ ሊሆኑ አልቻሉም።

ድሕረ ጽሑፍ

ይህ መጽሐፍ በ1992 ዓ.ም. ተጽፎ ካለቀ በኋላ በኢትዮጵያ ሁለት ታላላቅ ድርጊቶች ተፈፅመዋል። የመጀመሪያው በ1992 ዓ.ም. በግንቦት ወር የተከናወነው አገር አቀፍ ምርጫ ሲሆን ሌላው ደግሞ በተመሳሳይ ጊዜ የተካሄደው የሦስተኛው ዙር የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት መጠናቀቅ ነባ። ሁለቱም ለኢሕአዴግ አመራር በጣም ፈታኝና የወደፊቱን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የሚወስኑ ነበሩ። ኤርትራ በጦርነቱ ስለተሸነፈች ቀደም ብሎ ስትጋፋቸው የነበሩትን የድርድር ሃሳቦችንና የአሸናፊውን ወገን ተፅኖ ለመቀበል ተገዳ የተኩስ አቁም ስምምነት ፈርማል። የተኩስ አቁም ስምምነቱን መከበር የሚታዘብ የተባበሩት መንግሥታት ጦር በመካከላቸው ገብቶ በተለይ በኤርትራ በኩል እንዲስፍርና ድርድሩ እንዲቀጥል ሁለቱም ተስማምተዋል። ሆኖም የዚህ ጦርነት ቀጣይ የሆነው የዲፕሎማሲ ድርድር ከወታደራዊ ሽኩቻው የማይተናነስ ፍጥጫ እንደሚታይበት ይገመታል። የሁለቱ አገሮች ግንኙነትም ምን መልክ እንደሚይዝ ወደፊት ይታወቃል።

ከዚህ በፊት በ1987 ዓ.ም. ለተካሄደው ምርጫ እንደተደረገው ለ1992 ዓ.ም. ምርጫ ሰፋ ያለ መረጃዎች ለማሰባሰብ አልተሞከረም። በአጠቃላይ ለምርጫው የተካሄደው የምረጡኝ ዘመቻና ቦ ጉድድሩም የተሳተፉት የተቃዋሚ ድርጅቶች ቁጥር ብዛት ይህን ምርጫ ከ1987 ዓ.ም. የተሻለ ቢያስመስለውም ከበፊቱ የተለየ ነገር አላጋጠመም። በዚህ ምርጫ የምረጡኝ ዘመቻ የመድረክ ላይ ክርክር አብዛኞቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ለአገሪቷ ወቅታዊ ችግሮች ማለትም ለኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት፣ በጊዜው ለተከሰተው ድርቅ፣ ብዙ ሕዝብ በመፍጀት ላይ ላለው የኤድስ በሽታ፣ ለሥራ አጥነትና ለኑሮ ውድነት ብዙም ትኩረት ሳይሰጡ የራሳቸውን የፖለቲካ ፕሮግራም በማስተዋወቅና ከገዢው ድርጅት የሚለዩበትን በማጉላት ተገድበዋል። አድማጭ ደግሞ ይህንን በመጠኑም ስለሚያውቅ የተወዳዳሪዎቹን ብቃት የሚለካበት በአገሪቷ ችግሮች ዙሪያ ያላቸውን ራዕይ በማነፃፀር ነበር። በዚህ ላይ ተቃዋሚዎች ያሳዩት ድክመት የገዢውን ድርጅት በጦርነቱ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ሌላው ቀርቶ ምርጫ ከመካሄዱ <u>ሁለት ቀን</u> በፊት ጦርነቱን እንዲጀምርና በአሸናፊነት እንዲኮፈስ አድርገውታል። በዚህ የተነሳ የኢሕአዴግ ድርጅቶች እንደተለመደው ከነደጋፊዎቻቸው 95% የአሸናፊ ድምፅ በማግኘት የተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫወችን ተቆጣጥረዋል። በርከት ያሉ ደጋፊዎች እንዳላቸው ከሚነገርላቸው በምርጫው ከተሳተፉት ተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል መኢሕድ፣ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስና የደቡብ ህብረት ያገኙት ድምፅ ከ2% አይበልጥም ነበር። ቀረውን 3% የግል ተመራጮችና አዲስ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ተካፍለዋል። ይልቅ አንዳንድ ተቃዋሚ ድርጅቶች በክልል ምክር ቤት ምርጫ የተሻለ ድምፅ አግኝተዋል።

የዚህ ጦርነትና አገር አቀፍ ምርጫ በተመሳሳይ ጊዜ መካሄድ የኢሕአዴግን በራስ መተማመንና በቀላሉም ሁለቱንም በአሸናፊነት እንደሚወጣ በቅድሚያ ማረጋገጥ ቢያመለክትም ሦስት ጥያቄዎች ማስነሳቱ አይቀርም።

1. ለመሆኑ ዴሞክራሲና ጦርነት አብረው <u>መሄድ</u> ይችላሉ?

2. በዚህ ጦርነት ገዢው ድርጅት ባይቀናው ኖሮ የምርጫው ውጤት ይቀየር ነበር?
3. ጦርነቱና ምርጫው በአንድ ጊዜ የተካሄዱት አንዱ ለሌላው ደጋፊ እንዲሆን ታስበው ይሆን?

ለነኝህ ጥያቄዎች ቁርጥ ያሉ መልሶች መስጠት ቢያስቸግርም በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ምርጫውና ጦርነቱ በአንድ ላይ እንዲካሄዱ ታስበው የተሰሩ ድርጊቶች አንጅ አጋጣሚዎች አልነበሩም። ምርጫው በተወሰነለት ጊዜ መካሄድ ቢገባውም ቢያስፈልግ ከጦርነቱ ጋር እንዳይገጣጠም ማድረግ ይቻል ነበር። ይልቅ ኢሕአዴግ ጦርነትና ዴሞክራሲን ጎን ለጎን አብሮ ማካሄድ እንደሚችል ለማሳየት መረጠ። ጦርነቱን ንቆት ነበር እንዳይባል መቆራቆሱ ከሁለት ዓመት በላይ ፈጅቷል። በምርጫ የተገኘው ከፍተኛ ድምፅ ኢሕአዴግን ያለምንም ተቀናቃኝ በበላይነት እንዳሸነፈ አስመስክሯል። ከዚህ በመነሳት የምርጫው ውጤት የጦርነቱን ድል እንዲያጎላ ታስቦ የታቀደ አንጅ ጦርነቱ ምርጫውን እንዲያደምቅ አልታሰበም። የጦርነቱ ውጤትም የምርጫውን ውጤት ሊቀይረው አይችልም ነበር። በአጋጣሚ ይሁን በሁኔታው አስገዳጅነት ኢሕአዴግ ለሁለቱም የቤት ሥራውን በቅድሚያ ተጠንቅቆ ሰርቶ ጨርሷል። ስለሰመረለት በጦርነቱ ያገኘውን ድል በአድናቆት ብንቀበልም የምርጫውን ውጤት ግን እንጠራጠራለን፣ ጦርነትና ዴሞክራሲም አብረው አይሄዱም።

እንግዲህ ከዚህ መንደርደሪያ በመነሳት የ1992 ዓ.ም. ምርጫ ነፃና ፍትሐዊ ነበር ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም አሁንም እንደበፊቱ ምክር ቤቱን በከፍተኛ የበላይነት የሚቆጣጠረው ያው አንድ ድርጅትና አንድ አስተሳሰብ ነበር። በምርጫው ጊዜ በደቡብ ክልልና በሌሎችም ቦታዎች ብዙ ወንጀሎች እንደተፈፀሙ፣ አንዳንዶች እንደታሰሩና እንደተገደሉ የምርጫው ተወዳዳሪዎችም ሆነ ታዛቢዎች አሰታውቀዋል። ምርጫውም በአንዳንድ ቦታዎችም እንዲደገም ተደርጓል። በምርጫ ጊዜ ይህን አይነት ድርጊቶች በሌሎች መሰል የአፍሪካ አገሮችም ስለሚያጋጥም ሁኔታው ሳያስደንቅ ይችላል። ነገር ግን ከምርጫው ውጤት መራራቅ ጋር ስናገናዝበው የኛን አገር ሁኔታ የተለየ ያደርገዋል፣ ምርጫውም ምንም ተአማኒነትና ተቀባይነት እንደሌለው ውጤቱ ይመሰክራል።

ኢሕአዴግ አድልዎ የሌለበት ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሂድ ስለማይችል በምርጫው መሳተፍ አያስፈልግም/ያስፈልጋል በሚል ከምርጫው በፊት ተፋጠው ለነበሩት ወገኖች፣ በተለይም ለተማረው ትውልድ፣ ውጤቱ አጥጋቢ መልስ ሰጥቷል። ምላስ አንድ ነገር መምረሩን ወይም መጣፈጡን የሚያውቀው ከቀመሰው በኋላ በመሆኑ አብዛኛው የምረጥ/ተመረጥ አቀንቃኝ የነበሩት ወገኖች ኢሕአዴግ የሚያካሂደው ምርጫ ነፃና ፍትሐዊ ሊሆን እንደማይችል ትምህርት ሳያገኙበት አልቀረም።

ይህ መጽሐፍ ከተፃፈ በኋላ ሳይታተም በርከት ላሉ ዓመታት ቆይቷል። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ የተለያዩ ድርጊቶች የተከናወኑ ቢሆንም ከደርግ የቀይ ሽብር ታሪክ ጋር ተዛማጅነት ያለው የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት የሥራ ክንውን ፍፃሜ ማግኘት እዚህ ላይ መጠቀስ ይገባዋል። የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት በ1984 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 22/1984 በኢሕአዴግ ተቋቋመ።(1) የአዋጁ ዓላማ በደርግ ዘመን የዘር ማጥፋት፣ የጦር ወንጀልና የጅምላ ጭፍጨፋ የፈፀሙ ሰዎችን ከሶ በፍርድ ቤት ለማስወሰን ነበር። የፍርድ ሂደቱ

ምንም እንኳን ጊዜ ቢፈጅም በ2002 ዓ.ም. ከተጠናቀቀ በኋላ የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት አንድ አጠቃላይ ሪፖርት አቅርቧል። ይህ ሪፖርት የደርግን የአፈናና የግድያ መዋቅሮች፣ የደርግን የአፈናና የግድያ ስልቶች፣ የደርግን የወንጀል ሰለባዎችና በደርግ ወንጀለኞች ላይ የተላለፈውን ውሳኔ አካቷል።(2)

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት ጠቅላላ ተገጂ የተባሉትን ሰዎች ብዛት 16,496 መሆናቸውን ቢያመለክትም በፍርድ ቤት መጎዳታቸው የተረጋገጠው ጠቅላላ ብዛት 12,733 ነበሩ። ከእነኝህ መጎዳታቸው ከተረጋገጠው መካከል 9,546 የተገደሉ፣ 1,500 የአካል ጉዳት የደረሰባቸውና 1,687 «ቶርች» (የተገረፉ፣ የተደበደቡና በሰውነታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው) የተደረጉ ነበሩ። ከተገደሉት መካከል 7,112 ሰዎች የቀይ ሽብር ሰማዕታት ሲሆኑ 2,434 ሰዎች የሐውዜን የጦር ወንጀል ሰለባ ነበሩ። በኢትዮጵያ ከ100,000 ሰዎች በላይ በቀይ ሽብር እንደተገደሉ በሚገመትበት አገር 7,112 በጣም ዝቅተኛ ቁጥር ነው። ስለዚህ የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት ሪፖርት ያደረገው የቀይ ሽብር ሰለባዎች ብዛት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ወደፊት የሚቀራረብ አሃዛዊ መረጃ ለማግኘት አገር አቀፍ ጥናትና ምዝገባ ያስፈልጋል።

የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት ሪፖርት 3,583 የደርግ ወንጀለኞች ጥፋተኛ ተብለው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ፍርድ እንደተቀጡ ያመለክታል። ከእነኝህ መካከል 2,275 ባሉበት የተፈረደባቸው ሲሆን 1,308 ደግሞ በሌሉበት የተፈረደባቸው ነበሩ። ይህ የሚያመለክተው ከግማሽ በላይ የሆኑት የደርግ ወንጀለኞች እንደተሰወሩና እንዳልተያዙ ነበር። ምንም እንኳን ሪፖርቱ በፍርድ ውሳኔ የተቀጡትን በሙሉ ይፋ ባያደርግም ከ15 ዓመት እስከ ሞት ድረስ ከባድ ፍርድ የተጣለባቸውንና አንዳንድ ዝቅተኛ ፍርድ የተፈረደባቸውን የደርግ ወንጀለኞች ስም ዝርዝርና ወንጀሉን በፈፀሙበት ጊዜ የነበራቸውን ኃላፊነት አካቷል።

የግርጌ ማስታወሻ

ምዕራፍ አንድ

1. R. Pankhurst. *An Introduction to Economic History of Ethiopia From Early Times to 1800* (Lalibela House, London, 1961) p. 339.
2. ታደሰ ታምራት:: ተረትና ታሪክ በኢትዮጵያ፣ *ውይይት* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ አዲስ አበባ፣ 1984) ቅጽ 1፣ ቁ. 2፣ ገጽ 84::
3. J.S. Trimingham. *Islam in Ethiopia* (Oxford University Press, London, 1952) p. 44.
4. ይልማ ደሬሳ:: *የኢትዮጵያ ታሪክ፣* በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1959) ገጽ 63-69::
5. ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ:: *የግራኝ አህመድ ወረራ* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1966) ገጽ 228-236::
6. አባ ባሕርይ:: ዜናሁ ለጋላ (የጋላ ታሪክ)፣ ያልታተመ መጽሐፍ፣ በ1959 ዓ.ም. ከግዕዝ ወደ አማርኛ በብላታ መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ የተተረጎመ፣ ገጽ 25:: (ይህ መረጃ በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ድርጅት ውስጥ ይገኛል:: የመለያ ቁጥር 499)::
7. አለቃ አጥሜ:: የጋላ ታሪክ ያልታተመ መጽሐፍ፣ በ1936 ዓ.ም. በአባ ተስፋ እጅ ከተገኘ ጽሑፍ ላይ የተቀዳ፣ ገጽ 10:: (ይህ መረጃ በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ድርጅት ውስጥ ይገኛል:: የደብተሩ ዋና ተራ ቁጥር 47)::
8. ይልማ ደሬሳ:: ገጽ 242-247::
9. I.M. Lewis. *People of the Horn of Africa: Somalia, Afar and Saho* (International African Institute, London, 1953) p. 45-46.
10. G.W.B. Huntingford. *The Galla of Ethiopia* (International African Institute, London, 1955) p. 19.
11. Mohammed Hassen. *The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860* (The Red Sea Press, 15 Industry Court, Trenton, NJ08638, 1994) p. XII-XVI.
12. አለቃ ታዬ ገብረማርያም:: *የኢትዮጵያ ታሪክ* (አዲስ አባባ፣ 1958) ገጽ 39::
13. አባ ባሕርይ:: ገጽ 27-40::
14. አለቃ አጥሚ:: ገጽ 11-18::
15. G.W.B. Huntingford. *Op.Cit.*, p. 19.
16. አባ ባሕርይ:: ገጽ 29-30::
17. ይልማ ደሬሳ:: ገጽ 227-248::
18. E. Cerulli. *Peoples of South-West Ethiopia and its Borderland* (International African Institute, London, 1956) p. 85-86.
19. D.N. Levine. *Wax and Gold: Tradition and Inovation in Ethiopian Culture* (The University of Chicago Press, Chicago, 1965) p. 20.
20. J.S. Trimingham. *Op.Cit.*, p. 98.
21. Shiferaw Bekele. The State in the Zemana Masafent (1786-1853): An Essay in Reinterpretation, In Tadesse Beyene, Richard Pankhurst and Shiferaw Bekele, ed., *Kasa and Kasa: Papers on the Lives, Times and Images of Tewodros II and Yohannes IV (1855-1889)* (Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa, 1990) p. 25-68.
22. ባሕሩ ዘውዴ:: *የኢትዮጵያ ታሪክ፣* ከ1848 እስከ 1966 (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ አዲስ አበባ፣ 1989) ገጽ 31-63::
23. J. Markakis. *Ethiopia: Anatomy of a Traditional Polity* (Oxford University Press, Addis Ababa, 1975) p. 104-118.
24. R. Pankhurst.. *State and Land in Ethiopian History* (HSIU, Adds Ababa, 1966).
25. ባሕሩ ዘውዴ:: ገጽ 15-23::
26. Zewede Gebresellassie. *Yohannes IV of Ethiopia: Political Biography* (Oxford University Press, London, 1975) p. 223-224.
27. ባሕሩ ዘውዴ:: ገጽ 61::
28. ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ:: *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ* (ብርሃንና ሰላም ማተሚ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1959) ገጽ 153፣ 175-179::

29. ሹመት ሲሻኝ:: የኤርትራ ሕዝብ የአንድነት ትግል፣ *ውይይት* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ አዲስ አበባ፣ 1984) ቅጽ 1፣ ቁ. 2፣ ገጽ 1-38::
30. Restoration. (ትንሣኤ ኤርትራ ኢትዮጵያዊት በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት) (Ministry of Information, Addis Ababa, 1952?) p.11.
31. ዘውዴ ረታ:: *በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኤርትራ ጉዳይ፣ 1941-1963 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር* (ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ገጽ 341-342::
32. *ዝኒ ከማሁ*:: ገጽ 2-6::
33. Fentahun Tiruneh. *The Ethiopian Students: Their Struggle to Articulate the Ethiopian Revolution* (Chicago, Illinois 60613, USA, 1990) p. 59-79.
34. Mesfin Woldemariam. *Rural Vulnerability to Famine in Ethiopia: 1958-1977* (Intermediate Technology Publications, 1986) p. 121-177.
35. Desalegn Rhameto. Revisiting the Land Issue Options for Change, *Economic Focus* (Ethiopian Economic Association, Addis Ababa, 1999) Vol. 2, No. 4, p. 9.
36. ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ:: *መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር* (ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1953) ገጽ 79::

ምዕራፍ ሁለት

1. J.H. Spencer. *Ethiopia at Bay: A Personal Account of the Haile Sellasie Years* (Reference Publications, Algonac, Michigan 48001, 1994) p. 256- 260.
2. Gebru Tareke. *Ethiopia: Power and Protest* (The Red Sea Press, Lawrenceville, NJ08648, 1996) p. 89-194.
3. R. Greenfield. *Ethiopia: A New Political History* (Pall Mall Press, London, 1965) p. 375-416.
4. Tesfatsion Medhane. *Eritrea: Dynamics of a National Question* (Amesterdam, 1986) p. 115-117.
5. Shumet Sishagn. Power Struggle in the Eritrean Secessionist Movement, MA Thesis (Addis Ababa Universty, Addis Ababa, 1984).
6. Dawit Woldegiorgis. *Red Tears: War, Famine and Revolution in Ethiopia* (The Red Sea Press, Trenton, New Jersey 08618, 1989) p. 93.
7. ኢሳያስ አፈወርቂ በ1971 ዓ.ም. ከቢቢሲ ጋዜጠኛ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ::
8. ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ:: *የህወሓት ሕዝባዊ ትግል*፣ 1967-1992 (ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ገጽ 28::
9. *አዲስ ዘመን*:: ህዳር 1፣ 1991፣ ገጽ 1::
10. አውነቱ አበራ:: አንድ አፍታ ለታሪክ፣ *መስታወት* (ሚዛን ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ቅጽ 1፣ ቁ. 3፣ ገጽ 24::
11. አውነቱ አበራ:: አንድ አፍታ ለታሪክ፣ *መስታወት* (ሚዛን ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ቅጽ 1፣ ቁ. 2፣ ገጽ 23::
12 ወርቁ ፈረደ:: *ዕድገት ብሎ ውድቀት፣ የወታደር ሶሻሊዝም* (አዲስ አበባ፣ 1990) ገጽ 27-32::
13. Babile Tola. *To Kill a Generation: The Red Terror in Ethiopia* (Free Ethiopia Press, Washington D.C., 1989) p. 160-164.
14. ወርቁ ፈረደ:: ገጽ 124::
15. *አፎይታ (መጽሔት)*:: (ፋና ዴሞክራሲ፣ አዲስ አበባ፣ 1984) ቅጽ 1፣ ቁ. 5፣ ገጽ 9-10::
16. ክፍሉ ታደሰ:: *ያ ትውልድ ቅጽ 2 ፣ የለውጥ ማዕበል በኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ)* (ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፣ 1991) ገጽ 262::
17. እንዳርጋቸው አሰግድ:: *በአጭር የተቀጨው ረጅም ጉዞ፣ መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ* (ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ገጽ 408::
18. ክፍሉ ታደሰ:: ቅጽ 2፣ ገጽ 219-230::
19. *ዝኒ ከማሁ*:: ገጽ 298::
20. *ዝኒ ከማሁ*:: ገጽ 283-288::
21. ክፍሉ ታደሰ:: *ያ ትውልድ ክፍል 1፣ ከአጀማመሩ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ)* (ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፣ ?) ገጽ 158-161::
22. አውነቱ አበራ:: እንዳፍታ ለታሪክ፣ *መስታወት* (ሚዛን ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፣ አዲስ አበባ፣ 1986) ቅጽ 1፣ ቁ. 3፣ ገጽ 25::
23. ክፍሉ ታደሰ:: ቅጽ 2፣ ገጽ 165-168::

24 ኦውነቱ አበራ:: *አንዳፍታ ስታሪክ፣ መስታወት* (ሚዛን ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፣ አዲስ አበባ፣ 1986) ቅጽ 1፣ ቁ. 3፣ ገጽ 2-30::

25.. Kiflu Tadesse. *The Generation Part II: Ethiopia, Transformation and Conflict (The History of the Ethiopian People's Revolutionary Party)* (University Press of America, Boston, USA, 1998) p. 400.

26. *Ibid. . p. 400-405.*

27. *Ibid.* p. 401-405.

28. *Ibid.* p. 401.

29. *Ibid.* p. 441-462.

30. *ጦቢያ* (መጽሔት):: (አክፓክ ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ቅጽ 7፣ ቁ. 3፣ ገጽ 7-10::

31. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 375-383.

32. ኃይሌ ፊዳ በ1970 ዓ.ም. በደርግ በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የሰጠው ማረጋገጫ::

33. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 449-452.

34. *Ibid.* p.460.

ምዕራፍ ሦስት

1. A. Camus. *The Rebel* (Penguin Books, Cox and Wyman, Ltd., London, 1962) p. 26.
2. Babile Tola. *Op. Cit.*, p. 67-205.
3. D.C. Blood and J.A. Henderson. *Veterinary Medicine* (Bailliere, Tindall and Cassell, London, 1968) p. 520-524.
4. Dawit Woldegiorgis. *Op. Cit.*, p. 118.
5. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ «ነፍጠኛ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው የምኒልክ ጦር ባስገበረበት ቦታዎች ተሰማርቶ ስነበረው ነፍጥ ያነገበ ሠራዊትና ስተከታዮቹ የተሰጠ መጠሪያ መሆኑን ነው::
6. Babile Tola. *Op. Cit.*, p 118.
7. ወርቁ ፈረደ:: ገጽ 137::

ምዕራፍ አራት

1. *አዲስ ዘመን*: መጋቢት 27፣ 1970፣ ገጽ 1::
2. *አዲስ ዘመን*: ሚያዝያ 5፣ 1970፣ ገጽ 1::
3. ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» የተገኘ መረጃ::
4. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 420-425.
5. *ዴሞክራሲያ*: ቅጽ 4፣ ቁ. 9፣ 1969 ዓ.ም.፣ ገጽ 3 (በሕቡዕ የሚሰራጭ ጋዜጣ)::
6. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 446.
7. ክፍሉ ታደሰ:: ቅጽ 2፣ ገጽ 303-304::
8. ዝኒ ከማሁ:: ገጽ 338 (በዴሞክራሲያ ቅጽ 4፣ ቁ. 9፣ ገጽ 3 የሰፈረውን በኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የተላላፈውን ውሳኔ ይመለከታል)::
9. ወያኔ በሻዕቢያ ድጋፍ በኢሕአፓ ላይ ያካሄደውን ጦርነት ይመለከታል::
10. አንዳንድ የቆዩ የፖሊስ መኮንኖችን በማነጋገር የተገኘ መረጃ::
11. በአመራር ላይ የነበሩ የአንዳንድ ድርጅቶች አባላት እንዴት ከሌሎች ቀደም ብለው በጋቢና ዋራንት እንደተፈቱ በምዕራፍ አምስት ይቀርባል::
12. ከከተማ ልማት ሠራተኞች የተገኘ መረጃ::
13. ቀደም ብሎ ወይዘሮ ትንሣኤ በሚል ስም የተጠቀሰችውን የትራንስፖርትና መገናኛ ካድሬ ያስታውሷል::
14. *አዲሰ ዘመን*: ጥቅምት 18፣ 1970፣ ገጽ 9::
15. Babile Tola. *Op. Cit.*, p. 147.
16. *ጦማር* (ጋዜጣ):: ጥር 3፣ 1992፣ ገጽ 3::
17. Babile Tola. *Op. Cit.*, p. 151.
18. ከልዩ ልዩ ክፍተኞች የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::
19. ከማዕከላዊና ከደርግ ጽ/ቤት የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::
20. ከከፍተኛ 2 የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::
21. ከከፍተኛ 7 እና ከከፍተኛ 18 የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::

22. ከከፍተኛ 5 እና ከከፍተኛ 8 የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::
23. Babile Tola. *Op. Cit.*, p. 165-200.
24. ከኢሕአፓ እስረኞችና ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» የተገኘ
 መረጃ::
25. Dawit Woldegiorgis. *Op. Cit.*, p. 100.
26. ከአስመራ ታስረው ከርቸሌ ከመጡ ወታደሮችና ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት
 ወንጀል የክስ «ቻርጅ» የተገኘ መረጃ::
27. ከከፍተኛ 8 እና ከከፍተኛ 25 የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::

ምዕራፍ አምስት

1. ጌታቸው ጉበሬ:: *ፓፒሮ* (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ገጽ 1-500:: (ከሔንሪ_
 ሻሪይ ሥራዎች ወደ አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ)::
2. *The Ethiopian Herald*. September 11, 1974, p. 11.
3. የኢትዮጵያ መንግሥት አዋጅ:: *ነጋሪት ጋዜጣ* (አዲስ አባባ፣ 1967) አዋጅ ቁጥር 31::
4. *አዲስ ዘመን*:: እብዛኛው 1973 እና 1974 እትሞች::
5. ዳኛቸው ወርቁ:: *ሐደፍርስ* (ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1962) ገጽ 5-330::
6. ጎሕ (መጽሔት):: (ጨረቃ ማስታወቂያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1968) ቅጽ 2፣ ቁ. 3፣ ገጽ 24::
7. *ጎሕ (መጽሔት)*:: (ጨረቃ ማስታወቂያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1968) ቅጽ 2፣ ቁ. 7፣ ገጽ 12::
8. ከአቶ ሠራዊቱ ይመር የተገኘ መረጃ::
9. *ዝኒ ከማሁ*::
10. *አዲስ ዘመን*: አብዛኛው 1971 እና 1972 እትሞች::
11. ዝኒ ከማሁ::
12. በዕለቱ ከእስር ከተፈቱት ግለሰቦች የተገኘ መረጃ::
13. በጊዜው ይገባናል ብለው ካመለከቱት የከርቸሌ እስረኞች የተገኘ መረጃ::

ምዕራፍ ስድስት

1. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 312-316.
2. ወርቁ ፈረደ:: ገጽ 121::
3. ዝኒ *ከማሁ*:: ገጽ 131::
4. ዝኒ *ከማሁ*:: ገጽ 134::
5. ዝኒ *ከማሁ*:: ገጽ 135::
6. ኃይሌ ፊዳ በ1970 ዓ.ም. በደርግ በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የሰጠው ማረጋገጫ::
7. Dawit Woldegiorgis. *Op. Cit.*, p. 62.
8. ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሦስት ከቀረበው የግርጌ ማስታወሻ ትርጉም ጋር ተመሳሳይነት አለው::
9. ተስፋዬ መኮንን:: *ይድረስ ለባለታሪክ* (ብሬና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ገጽ
 289::
10. Dawit Woldegiorgis. *Op. Cit.*, p. 47-50.
11. ተስፋዬ መኮንን:: ገጽ 295::
12. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 239.
13. ከአንድ የቀይ ሽብርን ወንጀል ከሚያጣራ ስሙ እንዳይጠቀስ ከፈለገ የሕግ ባለሙያ የተገኘ
 መረጃ::
14. *ዝኒ ከማሁ* ::
15. Babile Tola. *Op. Cit.*, p. 118.
16. ብርሃነ መስቀል ረዳ የአርማት ንቅናቄ ለማካሄድ በሚል በ1971 ዓ.ም. ከመርሐቤቴ በቴፕ ልኮ
 የተባፈው «የብዙሐን መስመር» መጣጥፍና ከደርግ ጋር ተባብሮ ለመስራት ቃል
 የስጠበት ሰነድ::
17. ከከፍተኛ 5፣ 7፣ 8 እና 18 የኢሕአፓ እስረኞች የተገኘ መረጃ::
18. ክፍሉ ታደሰ:: ቅጽ 2፣ ገጽ 293-301::
19. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 316-317.
20. ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» የተገኘ መረጃ::
21. በቦታው ከነበሩ የአይን ምስክሮች፣ የሟች ቤተ ዘመዶችና ከአንዱ የሟች ወንድም ከአቶ ታደሰ
 ቦጋለ የተገኘ መረጃ::
22. Kiflu Tadesse. *Op. Cit.*, p. 184, 275, 313, 316 and 325.

23. Palme Dutt. Fascisim and Social Revolution (1936).
24. ክፍሉ ታደሰ:: ክፍል 1፣ ገጽ 259::
25. *ዴሞክራሲያ*:: ቅጽ 4፣ ቁ. 9፣ 1969 ዓ.ም.፣ ገጽ 13 (በሕቡዕ የሚሰራጭ ጋዜጣ)::
26. ከከፍተኛ 8 የኢሕአፓ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
27. ከከፍተኛ 5 የኢሕአፓ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
28. ከከፍተኛ 7 የኢሕአፓ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
29. ከከፍተኛ 12 የኢሕአፓ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
30. ቺቺ በደርግ ዘመን የኢትዮጵያ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት አባላት የሚታጠቁት በሶቬት የተሠራ የጠመንጃ አይነት ነው::
31. በደርግ ዘመን ሰዎች ሲገደሉ «አርምጃ» ተወሰደባቸው ይባል ነበር::
32. ከኢሕአፓ አስረኞች፣ ከግለሰቦችና ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንገጀል የክስ «ቻርጅ» የተጠናከረ መረጃ::
33. ከኢሕአፓ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
34. ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» የተገኘ መረጃ::
35. ከከፍተኛ የኢሕአፓ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
36. Babile Tola. *Op. Cit.*, p. 138-139.
37. Ibid. p. 140-141.
38. *ሜጋ አሳታሚ ድርጅት:: ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ* (ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1989) ገጽ 8-104::
39. በጊዜው ከነበሩት የማዕከላዊ አስረኞች የተገኘ መረጃ::
40. *አዲስ ዘመን*:: መስከረም 2፣ 1992፣ ገጽ 1::
41. ከደርግ ዘመን አስረኞች፣ ከግለሰቦችና ከደርግ ባለሥልጣኖች የዘር ማጥፋት ወንጀል የክስ «ቻርጅ» የተገኘ መረጃ::
42. *አዲስ ዘመን*:: ታህሳስ 5፣ 1992፣ ገጽ 6::
43. Dawit Woldegiorgis. *Op. Cit.*, p. 109.
44. *አዲስ ዘመን*:: ግንቦት 10፣ 1981፣ ገጽ 1::

ማሳረጊያ

1. Margaret A. Novicki. Good Governance: Key to Progress, *The Eye on Ethiopia and the Horn of Afrca* (Emma Eyob, Stohagsvagen 31A, S-72465 Vasteras, Sweden, 1997) Vol. VIII, No. 48, p. 31-33.
2. *የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት:: ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ ነሐሴ 15፣ 1987፣ ገጽ 13-14::
3. *አዲስ ዘመን*:: ነሐሴ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 1991፣ ገጽ1::
4. *ጦቢያ* (መጽሔት):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1989) ቅጽ 5፣ ቁ. 8፣ ገጽ 9-14::
5. *አዲስ ዘመን*:: ህዳር 10፣ 1992፣ ገጽ 6::
6. *ዝኒ ከማሁ*:: ገጽ 6::
7. *አዲስ ዘመን*:: ጥር 14፣ 1992፣ ገጽ 2::
8. V.I. Lenin. The Socialist Revolution and the Right of Nations to Self Determination (Theses). *Selected Works* (Progress Publishers, Moscow, 1964) p. 157-168.
9. ሚሃየል ጎርባቾቭ:: *ፔሮስትሮይካ፣ አዲስ አስተሳሰብ ለሃገራቸውና ለመላው ዓለም* (ፕሮግረስ አሳታሚ ድርጅት፣ ሞስኮ፣ 1989) ገጽ 54-57::
10. *የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት:: ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ ነሐሴ 15፣ 1987፣ ገጽ 5-28::
11. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: *የተጠቃለለ የኢሰመጉ መግለጫዎች፣ ከህዳር 1984 እስከ ህዳር 1990* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ገጽ 15::
12. *ጦቢያ* (መጽሔት):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1991) ቅጽ 6፣ ቁ. 12፣ ገጽ 20::
13. *አዲስ ዘመን*:: የካቲት 30፣ 1992፣ ገጽ 1::
14. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: ገጽ 1-300::
15. *ዝኒ ከማሁ*:: በተለያዩ ገጾች የተጠቀሱትን በማዳመር የተገኘ::
16. *ዝኒ ከማሁ*:: ገጽ 259::
17. *ጦቢያ* (መጽሔት):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1991) ቅጽ 6፣ ቁ. 12፣ ገጽ 21::
18. *ጦቢያ* (ጋዜጣ):: ነሐሴ 14፣ 1990፣ ገጽ1::
19. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: ገጽ 27፣ 37፣ 55፣ 126፣ 145፣ 169::

20. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ቅጽ 2፣ ቁ. 1፣ ገጽ 4::
21. *ዝኒ ከማሁ*:: ገጽ 4::
22. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1991) ቅጽ 6፣ ቁ. 11፣ ገጽ 23-29::
23. *አዲስ ዘመን*:: ጥር 4፣ 5፣ 6፣ 1992፣ ገጽ 6::
24. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1991) ቅጽ 6፣ ቁ. 12፣ ገጽ 21::
25. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1991) ቅጽ 6፣ ቁ. 12፣ ገጽ 20::
26. *አዲስ ዘመን*:: ነሐሴ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 1991፣ ገጽ 1::
27. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1991) ቅጽ 7፣ ቁ. 3፣ ገጽ 7::
28. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: ገጽ 104::
29. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ቅጽ 7፣ ቁ. 3፣ ገጽ 7::
30. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: ገጽ 22::
31. *ማለዳ* (*መጽሔት*):: (ዓረና አሳታሚና የማስታወቂያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ቅጽ 1፣ ቁ. 1፣ ገጽ 33::
32. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት:: *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ ነሐሴ 15፣ 1987፣ ገጽ 16::
33. *ጦማር*:: ጥር 10፣ 1992፣ ገጽ 1::
34. ይህንን አሳዛኝ ድርጊት በህይወት ካመለጠው የምርጫ ቦርድ ሠራተኛ ከሙኸዲን አልደንፊቂ የተገኘ መረጃ::
35. *ጦቢያ* (*ጋዜጣ*):: መስከረም 12፣ 1992፣ ገጽ 4::
36. *ጦቢያ* (*ጋዜጣ*):: ነሐሴ 28፣ 1990፣ ገጽ 5::
37. *ጦቢያ* (*ጋዜጣ*):: ነሐሴ 14፣ 1991፣ ገጽ 1::
38. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: ገጽ 19-28::
39. *ጦቢያ* (*ጋዜጣ*):: ነሐሴ 24፣ 1990፣ ገጽ 1::
40. *ጦቢያ* (*ጋዜጣ*):: ህዳር 1፣ 1992፣ ገጽ 1::
41. *አዲስ ዘመን*:: ህዳር 10፣ 1992፣ ገጽ 6::
42. *አዲስ ዘመን*:: ህዳር 10፣ 1992፣ ገጽ 6::
43. Berhanu Nega. Prevention of Monopolistic Tendencies in the Business Area: Is it Desireable in Countries Such as Ethiopia, *Economic Focus* (Ethiopian Economic Association. Addis Ababa, 1999) Vol. 1, No. 6, p. 24.
44. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1990) ቅጽ 5፣ ቁ. 8፣ ገጽ 17-19::
45. በፈቃዱ ደግፌ:: ኢትዮጵያ ከምስራቅና ከደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮች ምን ልትማር ትችላለች? *Economic Focus* (Ethiopian Economic Association, Addis Ababa, 1999) Vol. 2, No. 1, p. 16.
46. የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ጋር ለማጣጣም የወጣ አዋጅ ቁጥር 111/1987 ዓ.ም.:: *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ የካቲት 16፣ 1987::
47. *አዲስ ዘመን*:: ግንቦት 1፣ 2፣ 3፣ 1987፣ ገጽ 1::
48. *አዲስ ዘመን*:: ህዳር 10፣ 1992፣ ገጽ 6::
49. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ቅጽ 7፣ ቁ. 5፣ ገጽ 22-23::
50. *አዲስ ዘመን*:: ህዳር 9፣ 1992፣ ገጽ 6::
51. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ቅጽ 7፣ ቁ. 5፣ ገጽ 23 ና 33::
52. ደሳለኝ አለሙ:: *የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የምርጫ ጉድለቶች ማረሚያ ቦርድ ውሳኔዎች* (የምርጫ ማረሚያ ቦርድ ሊቀመንበር፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ገጽ 1-270::
53. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ቅጽ 7፣ ቁ. 3፣ ገጽ 8::
54. *አዲስ ዘመን*:: መስከረም 24፣ 1991፣ ገጽ 2::
55. Brook Debebe. The Economics of the Ethio-Eritrean War, *Economic Focus* (Ethiopian Economic Association, Addis Ababa, 1999) Vol. 1, No. 7, p. 5-6.
56. Medhane Tadesse. *The Eritrean War: Retospect and Prospects* (Mega, Addis Ababa, 1999) p. 135.
57. *አዲስ ዘመን*:: ጥር 18፣ 1992፣ ገጽ 6::
58. *ሪፖርተር* (*መጽሔት*):: (ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ሴንተር፣ አዲስ አበባ፣ 1990) ቅጽ 1፣ ቁ. 9፣ ገጽ 12::
59. Brook Debebe. *Op. Cit.*, p. 5-6.
60. *Ibid. p. 5-6.*
61. *ጦቢያ* (*መጽሔት*):: (አክፓክ ፣ አዲስ አበባ፣ 1992) ቅጽ 6፣ ቁ. 12፣ ገጽ 21::

62. Samuel Assefa. On Deportations, *Addis Tribune*, May 7, 1999, p. 2.
63. *ጦቢያ* (ጋዜጣ)። *መጋቢት* 23፣ 1991፣ ገጽ 1።
64. P.B. Henze. Eritrea's War Against Ethiopia: Causes and Effects, Reflections, Prescriptions, *The Ethiopian Herald*, January 30, 2000, p. 5.
65. *አዲስ ዘመን*፡ ሰኔ 1፣ 1991፣ ገጽ 3።
66. *መስፍን ወልደማርያም*። *መሬትና ልማት በኢትዮጵያ*፣ *Economic Focus* (Ethiopian Economic Association, Addis Ababa, 1999) Vol. 2, No. 4, p. 13.
67. Winrock International. *Assessment of Animal Agriculture in Sub-Saharan Africa* (Winrock International Institute for Agricultural Development, Morrilton, Arkansas, USA, 1992) p. 61-84.
68. International Livestock Centre for Africa (ILCA). *A Handbook of African Livestock Statistics* (Livestock Economic Division Working Document, No. 15, ILCA, Addis Ababa, 1991) p. 9 (Table54).
69. Will Durant. The Story of Philosophy (Washington Square Press, INC., NewYork, 1926) p. 4.

ድህረ ጽሑፍ

1. *የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት አዋጅ ቁጥር 22/1984 ዓ.ም.። ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ነሐሴ 2፣ 1984።*
2. የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት። ደም ያዘለ ዶሴ፤ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር ደርግ ወይም *መንግሥት* አባላት በንፁሃን ዜጎች ላይ የተፈፀመ ወንጀል ዘገባ (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም.) 441 ገፅ።

ዋቢ መረጃዎች

በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት

- ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ:: *የሕወሓት ትግል፣ 1967-1992* (ሜጋ ኢንተርፕራይዝ፣ አዲስ አበባ፣ 1992)::
- ሜጋ አሳታሚ ድርጅት:: *ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ* (ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣1989)::
- ባሕሩ ዘውዴ:: *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከ1848 እስከ 1966* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፣ 1989)::
- ተስፋዬ መኮንን:: *ይድረስ ለባለታሪኩ* (ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ 1985)::
- ተክለጻዲቅ መኩሪያ:: *የግራኝ አህመድ ወረራ* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1966)::
- አለቃ ታዬ ገብረማርያም:: *የኢትዮጵያ ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1958)::
- አለቃ አጥሜ:: *የጋላ ታሪክ፣* ያልታተመ መጽሐፍ፣ በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ድርጅት ውስጥ ይገኛል::
- አባ ባሕርይ:: *ዜናሁ ለጋላ፣* ያልታተመ መጽሐፍ፣ በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ድርጅት ውስጥ ይገኛል::
- አንዳርጋቸው አሰግድ:: *በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ፣ መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ* (ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1992)::
- ክፍሉ ታደሰ:: *ያ ትውልድ ክፍል 1፣ ከአጀማመሩ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ)* ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፣ ?)::
- ክፍሉ ታደሰ:: *ያ ትውልድ ቅጽ 2፣ የለውጥ ማዕበል (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ)* (ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች፣ 1991)::
- ወርቁ ፈረደ:: *ዕድገት ብሎ ውድቀት፣ የወታደር ሶሻሊዝም* (አዲስ አበባ፣ 1990)::
- ዘውዴ ረታ:: *በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኤርትራ ጉዳይ፣ 1941-1963 እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር* (ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1992)::
- የልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት:: ደም ያዘለ ዶሴ፣ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር ደርግ ወይም መንግሥት አባላት በንፁሃን ዜጎች ላይ የተፈፀመ ወንጀል ዘገባ (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም.)::
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ:: *የተጠቃለሉ የኢሰመጉ መግለጫዎች፣ ከህዳር 1984 እስከ ህዳር 1990* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1992)::
- ይልማ ደሬሳ:: *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1959)::
- ዳኛቸው ወርቁ:: *አደፍርስ* (ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1962)::
- ገብረሕይወት ባይከዳኝ:: *መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር* (ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አ.ደስ አበባ፣ 1959)::
- ገብረሥላሴ (ፀሐፊ ትዕዛዝ):: *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1959)::
- ጌታቸው ገብሬ:: *ፓፒዮ* (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ፣ ከሔንሪ ሽሪይ ሥራዎች ወደ አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ::
- ጎርባቾቭ፣ ሚሃየል:: *ፔሮስትሮይካ፣ አዲስ አስተሳሰብ ለሀገራችውና ለመላው ዓለም* (ፕሮግረስ አሳታሚ ድርጅት፣ ሞስኮ፣ 1989)::

በውጪ አገር ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት

- Babile Tola. *To Kille a Generation: The Red Terror In Ethiopia* (Free Ethiopia Press, Washington D. C., 1989).
- Blood, D.C. and Henderson, J.A. *Veterinary Medicine* (Bailliere, Tindall and Cassell, London, 1968).
- Camus, A. *The Rebel* (Penguin Books, Cox and Wyman Ltd., London, 1962).
- Cerulli, E. *Peoples of Southwest Ethiopia and its Borderland* (International African Institute, London, 1956).

- Dawit Woldegiorgis. *Red Tears: War, Famine and Revolution in Ethiopia* (The Red Sea Press, Trenton, New Jersey 08618, 1989).
- Durant, Will. The Story of Philosophy (Washington Square Press, INC., NewYork, 1926).
- Dutt, Palme. Fascisim and Social Revolution (1936).
- Fentahun Tiruneh. *The Ethiopian Students: Their Struggle to Articulate the Ethiopian Revolution* (Chicago, Illinois 60613, USA, 1990).
- Gebru Tareke. *Ethiopia: Power and Protest* (The Red Sea Press, Lawrenceville, NJ08648, 1996).
- Greenfield, R. *Ethiopia: A New Political History* (Pall Mall Press, London, 1965).
- Huntingford, G.W.B. *The Galla of Ethiopia* (International African Institute, London, 1955).
- Kiflu Tadesse. *The Generation: Part II: Ethiopia, Transformation and Conflict (The History of the Ethiopian People's Revoltutionary Party)* (University Press of America, Boston, USA, 1998).
- Lenin, V.I. *Selected Works* (Progress Publishers, Moscow, 1964).
- Levine, D.N. *Wax and Gold: Tradition and Inovatition in Ethiopian Culture* (The University of Chicago Press, Chicago, 1965).
- Lewis, I.M. *Peoples of the Horn Africa: Somalia, Afar and Saho* (International African Institute, London, 1955).
- Markakis, J. *Ethiopia: Anatomy of a Traditional Polity* (Oxford University Press, Addis Ababa, 1975).
- Medhane Tadesse. *The Eritrean War: Retrospect and Prospects* (Mega, Addis Ababa, 1989).
- Mesfin Woldemariam. *Rural Vulnerabilty to Famine in Ethiopia: 1958-1977* (Intermediate Technology Publications, 1986).
- Mohammed Hassan. *The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860* (The Red Sea Press, 15 Industry Court, Trenton, NJ08638, 1994).
- Pankhurst, R. *An Introduction to Economic History of Ethiopia From Early Times to 1800* (Lalibela House, London, 1961).
- Pankhurst, R. *State and Land in Ethiopian History* (HSIU, Adds Ababa., 1966).
- Shiferaw Bekeele. The State in the Zemana Masafent (1786-1853). An Essay in Reinterpretation, In Tadesse Beyene, Richard Pankhurst and Shiferaw Bekele, ed., *Kasa and Kasa: Papers on the Lives, Times and Images of Tewodros II and Yohannes IV (1855-1889)* (Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa, 1990).
- Spencer, J.H. *Ethiopia at Bay: A Personal Account of the Haile Selassie Years* (Reference Publications, Algonac, Michigan 48001, 1994).
- Tesfatsion Medhane. *Eritrea: Dynamics of a National Question* (Amesterdam, 1986).
- Trimingham, J.S. *Islam in Ethiopia* (Oxford University Press, 1952).
- Zewede Gebresellasie. *Yohannes IV of Ethiopia: Political Biography* (Oxford University Press, London, 1975).

በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ሌሎች መረጃዎች

- *መስታወት*:: (ሚዛን ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፣ አዲስ አበባ፣ 1985 እና 1986) ቅጽ 1፣ ቁ. 2 እና 3::
- *ማለዳ (መጽሔት)*:: (ዓረና አሳታሚና የማስታወቂያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1985) ቅጽ 1፣ ቁ. 1::
- ምርጫ ማረሚያ ቦርድ:: *የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የምርጫ ጉድለቶች ማረሚያ ቦርድ ውሳኔዎች* (የምርጫ ማረሚያ ቦርድ ሊቀመንበር፣ አዲስ አበባ፣ 1985)::
- *ሪፖርተር (መጽሔት)*:: (ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ሴንተር፣ አዲስ አበባ፣ 1990) ቅጽ 1፣ ቁ. 9::
- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ:: *የምርጫ አፈጻጸምና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርአትን ለመወሰን የወጣ ደንብ* (የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ፣ አዲስ አበባ፣ 1986)::
- *ነጋሪት ጋዜጣ*:: አዋጅ ቁጥር 31፣ 1967::
- *አዲስ ዘመን*: ልዩ ልዩ የ1970፣ 1971፣1973፣ 1974፣ 1975፣ 1981፣ 1987፣ 1989፣ 1990፣ 1991 እና 1992 እትሞች::

- *አፎይታ* (መጽሔት)። (ፋና ዴሞክራሲ፣ አዲስ አበባ፣ 1984) ቅጽ 1፣ ቁ. 5።
- *ውይይት*። (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፣1984) ቅጽ 1 ቁ. 2።
- *ዴሞክራሲያ*። ቅጽ 4፣ ቁ. 9፣ ህቡዕ ጋዜጣ።
- *ጎሕ* (መጽሔት)። (ጨረቃ ማስታወቂያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1968) ቅጽ 2፣ ቁ. 3 እና 7።
- *ጦማር*። ጥር 3 እና 10፣ 1992።
- *ጦቢያ* (መጽሔት)። (አክፓክ፣ አዲስ አበባ፣ 1985፣ 1989፣ 1990፣ 1991፣ 1992) ልዩ ልዩ ቅጾችና እትሞች።
- *ጦቢያ* (ጋዜጣ)። ልዩ ልዩ የ1990፣ 1991 እና 1992 እትሞች።
- *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*። ነሐሴ 1984፣ የካቲት 1987 እና ነሐሴ 15፣ 1987።

በውጭ አገር ቋንቋ የተጻፉ ሌሎች መረጃዎች

- *Addis Tribune*. May 7, 1999.
- *Economic Focus*. (Ethiopian Economic Association, Addis Ababa, 1999) Vol. 1 and 2, No. 6, 1 and 4.
- International Livestock Centre for Africa (ILCA). *A Handbook of African Livestock Statistics* (Livestock Economic Division Working Document, No. 15, ILCA, Addis Ababa, 1991).
- *Restoration* (ትንሣኤ ኤርትራ እትዮጵያዊት በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት). (Ministry of Information, Addis Ababa, 1952?).
- *The Ethiopian Herald*. Sept. 11, 1974 and Jan. 30, 2000.
- *The Eye on Ethiopia and the Horn of Africa*. (Emma Eyob, Stohagsvagen 31A, S-72465 Vasteras, Sweden, 1997).
- Winrock International. *Assessmenet of Animal Agriculture in Sub-Saharan Africa* (Winrock International Institute for Agricultureal Development, Morrilton, Arkansas, USA, 1992).

- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]

[illegible]

- [illegible] May 7, 1995.
- [illegible] (Ethiopian Economic Association, Addis Ababa, 1999 Vol. I and [illegible]
- International Livestock Centre for Africa (ILCA), A Handbook of African Livestock Statistics (Livestock Economic Division Working Document, No. 15, ILCA, Addis Ababa, 1991).
- Restoration [illegible] (Ministry of Information, Addis Ababa, 1952 E.C.).
- The Ethiopian Herald, Sept. 11, 1974 and Jan. 19, 2000.
- The Eye of Ethiopia and the Horn of Africa (Emma Eyob [illegible], Sweden, 1997).
- Winrock International, Assessment of Animal Agriculture in Sub-Saharan Africa (Winrock International Institute for Agricultural Development, Morrilton, Arkansas, USA, 1992).

3488[illegible]

3488038

በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት የተከማቹትንና ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ እየተንከባለሉ የመጡትን ችግሮች ለመፍታትና ከአምባገነን የፖለቲካ ስርዓት ለመገላገል ሰፊ ትግል ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየው ይህንኑ በገዢ መደቦች ላይ የተካሄደውን ትግልና ጦርነት ቢሆንም ለአገሪቷ ጭቁን ሕዝቦች መፍትሔ አላጎናጸፈም። እንግዲህ ኢትዮጵያ እነኝህን ሁሉ ችግሮች ተሸክማ ወደፊት መራመድ እንደማትችል በመገመት ከዚህ አዙሪት ለመውጣት በተደረገ የአንድ ወቅት ትግል የደረሰው ጉዳት በከፊል ምን ይመስል እንደነበረ ለማስታወስ ይህ መጽሐፍ ተጻፈ። ...

ፋሽዝም ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአንዳንድ የካፒታሊስት አገሮች ሶሻል ዴሞክራሲ በኮምኒዝም ላይ በነበረው ጥላቻ የተነሳ ለመደብ ትግል እንቅፋት በመሆን የላብ አደሩን መደብ ሶሻሊስት አብዮት እንዳያካሂድ ስለገደበው በጊዜው የተፈጠረውን የኤኮኖሚና ሌሎች ቀውሶች ተከትሎ የተከሰተ «የቶታሊቴሪያን» (የአንድ ድርጅት ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት) መንግሥት ነበር (23)። ይህንን መንግሥት የመሰረቱት በ1930 ዓ.ም. አካባቢ የጀርመኑ ሒትለር፣ የጣሊያኑ ሞሶሎኒና የስፔኑ ፍራንኮ ነበሩ። ካፒታሊዝም ባላደገበት ታዳጊ አገሮችም ሌሎች አምባገነኖች በኢንዶኔዥያ ሱሐርቶ፣ በቺሊ ፒኖሽ፣ በካምቦዲያ ፖልፖትና በኢትዮጵያ መንግሥቱ ኃይለማርያም የአብዮታውያንን ትግል በማኮላሸት «የቶታሊቴሪያን» ባህርይ ያላቸው የፋሽስት መንግሥታት መስርተው ነበር። ሁለቱን የሚያመሳስላቸው የሚያለያያቸውም ባህርያት አሉ። ...

እንዲህ እያለ ቀስ በቀስ የከርቸሌ እስረኞች በጋቢና ዋራንት ጥሪ እየተፈቱ ቢሄዱም መስከረም 25 ቀን 1978 ዓ.ም. አንድ አስደንጋጭ የጋቢና ዋራንት ጥሪ ተካሄደ። ከዘጠኝ ዓመት በላይ በእስር የማቀቁ የኢሕአፓ እስረኞች፣ የጆሆቫ እምነት ተከታዮች፣ አንዳንድ የወያኔ አባላትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ቃል ኪዳን (ኢፒዴኤ) አባላት በጋቢና ዋራንት ተጠርተው ተረሸኑ። በዚህ የተነሳ ከርቸሌ እንደ ልማዱ ተረበሸ፣ የጥንቱ ትዝታ አገረሸ፣ ለመፈታት የነበረው ተስፋ ሚሸሸ። ...

ዜድኤ ማተሚያ ቤት

ዋጋ ብር 37.5